# አደፍርስ




ልቦለድ

ከዳኛቸው ወርቁ




. . . ለምሳሌ ፡ ኅሊናን ፡ የሚያነቁ ፡ ሁኔታዎችን ፡ ባህላዊ ፡ ሙዚቃን — ቀረርቶና ፡ ፉከራ . .
የመሳሰሉትን ፡ ሲሰማ ፡ ልቡስ ፡ ጥላ ፡ ጀግናው . .

# ልቦለድ

ከዳኛቸው ፡ ወርቁ

ሠዐሊ—አቶ ፡ ታዬ ፡ ወልደ ፡ መድኅን ፡

የእጅ ፡ ጽሑፌን ፡ ስርዝና ፡ ድልዝ ፡ አስተካክላ ፡ በመኪና ፡ በመጻፍ ፡ ለእትም ፡ እንዲቀርብ ፡ ያበቃችው ፡ — ወይዘሮ ፡ ትዕግሥት ፡ ወርቄ ።

# መታሰቢያ

ለልዑል ፡ ራስ ፡ መኰንን ፡ ወልደ ፡ ሚካኤል ፡

ለራስ ፡ እርእያ (የእጼ ፡ ዮሐንስ ፡ አጐት)

ለፊታውራሪ ፡ ሀብተ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ዲነግዴ ፡

ለደጃዝማች ፡ ባልቻ ፡ ሣፎ ፡

እና ፡

ለራስ ፡ ቢትወደድ ፡ መኰንን ፡ እንዳልካቸው ፡

---

በግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዘኢትዮጵያ ፡
በ፴፱ኛው ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ በ፲፱፻፷፪ ፡ ዓ ፡ ም ፡

በንግድ ፡ ማተሚያ ፡ ቤት ፡ ታተመ ።

በሬዲዮ ፡ ለማሰማት ፡ ሕዝብ ፡ በተሰበሰበበት ፡ ለማንበብ ፡ በከፊልም ፡ ሆነ ፡ በሙሉ ፡ ለማራባት ፡ መልሶ ፡ ለማሳተም ፡ ወይም ፡ ለመተርጐም ፡ መብቱ ፡ የደራሲው ፡ ብቻ ፡ ነው ።

# ፩

# አደፍርስ

ቁንዲ ፣ እንገቷን ፣ አስግጋ ፣ ቃፊርነት ፣ የቆመች ፣ መስላለች ። የዓዋዲና ፣ የጀውሃ ፣ ጅረቶች ፣ ደረታቸውን ፣ ለፀሐይ ፣ ሰጥተው ፣ ይምቦገቦጋሉ ። ሰማይና ፣ ምድር ፣ የተገናኘበት ፣ ሕይወት ፣ ያሸለበችበት ፣ የሚመስለውን ፣ በስተግርጌ ፣ የሚታይ ፣ ሜዳ ፣ አቧራ ፣ ረግቶበታል ። በየስርንጉጡ ፣ በየሸለቆው ፣ በየተረተሩ ፣ በየሸንተረሩ—ጉርጅ ፣ ወፍ ፣ ዋሻ ፣ ዋንዛበረት ፣ ጃናቦሬ ፣ የልቶኪ ፣ መጢ ፣ ዲያውዲያምባ ፣ ዓዋዲ ፣ ጨዋ ፣ እጋምበር ፣ ዋይሎ ፣ ደብረ ፣ ሲና ፣ አርማኒያ ፣ ሸረሸር ፣ ወይን ፣ ውሃ ፣ ማንያምባ ፣ እብዲላቅ ፣ ማፋድ ፣ ግልዲማ ፣ ካሴ ፣ አገር ፣ ራሳ ፣ መዘዞ ፣ አያበር ፣ ቀወት ፣ ወጃ ፣ ጠማሚት ፣ ሾተል ፣ አምባ - - - በየከፍተኛዎቹ ፣ ጉባዎች — ግፍት ፣ ሚካኤል ፣ ጉርጅ ፣ ሚካኤል ፣ ዋንዛበረት ፣ ሚካኤል ፣ ዶቃቂት ፣ ሚካኤል ፣ ባራምባ ፣ ሚካኤል ፣ ራምቤ ፣ ሚካኤል ፣ ማኒያምባ፣ ሚካኤል ፣ የልቶኪ ፣ ሚካኤል ፣ ዋይሎ ፣ ሚካኤል ፣ ሐራምባ ፣ ሚካኤል ፣ ማፋድ ፣ ሚካኤል ፣ ወጃ ፣ ሚካኤል - - - የደፋትና ፣ ጥሙጋ ፣ አውራጃን ፣ ጣርማበር ፣ ተራራ ፣ላይ ፣ ሆኖ ፣ ሲመለከቱት ፣ እግዚአብሔር ፣ ዓለምን ፣ ሠርቶ ፣ ሲያበቃ ፣ የተረፈውን ፣ ትርክምክም ፣ ያጕረበት ፣ እቃ ፣ ቤቱ ፣ ይመስላል ።-ሸለቆው ፣ ጉባው ፣ ተራራው ፣ ገመገሙ ፣ ጭጋጉ ፣ አቧራው ፣ ሕይወትን ፣ አፍኗት ፣ ተኝታለች ።-ያቺ ፣ በሌላው ፣ አገር ፣ የምትጣደፈው ፣ የምትፍለቀለቀው ፣ የምትምቦለቦለው ፣ ሕይወት ፣እዚህ ፣እፎይ ፣ ብላለች— በርጋታ ፣ በዝግታ ፣ ታምማለች ፣ በተገማሸረ ፣ መስክ ፣ ውስጥ ፣ እንደሚብሰከሰክ ፣ውሃ- - -ሰኞ ፣ ማክሰኞ ፣ ረቡዕ - - - ልደታ—(ራጉኤል)—አባ ፣ ጉባ — በዓታ — ዮሐንስ ፣ ወልደ ፣ ነጕድጓድ — አቡየ ፣ ጻድቁ — የሱስ ፣ ክርስቶስ — ሥላሴ — አርባዕቱ ፣ እንስሳ — ቶማስ ፣ ሰማዕት — መስቀለ ፣ የሱስ — ቅድስት ፣ ሐና — ቅዱስ ፣ ሚካኤል — እግዚአብሔር ፣ አብ — ( ሩፋኤል ) — አቡነ ፣ አረጋዊ — (ገብረ ፣ ክርስቶስ ) —ሕፃን ፣ ቂርቆስ— ኪዳነ ፣ ምሕረት — እስጢፋኖስ ፣ ቀዳሚ ፣ ሰማዕት — ኤዎስጣቴዎስ ፣ ጻድቅ — ገብርኤል —ህንፀታ — ማርያም — ሐዋርያት — ጊዮርጊስ — ተክለ ፣ ሃይማኖት— መርቆሬዎስ — ዮሴፍ — መድኀኔ ፣ ዓለም — እማኑኤል — በዓለ ፣ እግዚእ — ቅዱስ ፣ ማርቆስ — ደመራ — መስቀል —

ቅዱስ ፡ ዮሐንስ — ገና — ጥምቀት — ፋሲካ — ትፈስሳለች — ታምማለች ፤
ሕይወት ፤ በተገማሸረ ፡ መስክ ፡ ውስጥ ፡ እንደሚብሰከሰክ ፡ ውሃ ---
ወገብ ፡ በመዛወር — በመናፈስ — በማሽራሽት — በመዋጥ — በማድ
ቀቅ — በማኘክ — በመጉረስ — በመጋገር — በማቡካት — በመከርተፍ —
በመሰለቅ — በመጐተር — በመጐድጐድ — በመጫን — በመውቃት —
በመከመር — በማጨድ — በማረም — በመቆፈር — በመጐልጐል — በመ
ትለም — በማረስ — በመጨፈቅ — በመጥረግ — ከብት ፡ በማሠማራት —
የከብት ፡ ራት ፡ በማስገባት — ማምሻ ፡ እንጨት ፡ በመልቀም ፤ ታልፋ
ለች ፣ ትፈስሳለች ፡ ታምማለች ፡ ሕይወት ፤ በተገማሸረ ፡ መስክ ፡ ውስጥ ፡
እንደሚብሰከሰክ ፡ ውሃ ።- በፋሲካ — በፍልሰታ — በገሐድ — በነነዌ —
በሑዳዴ — በጾመ ፡ ሐዋርያት — ባርብ ፡ ሮብ ፡ ትደለላለች ፣ ትዳከማለች --
በታናሽ — (ሹልዳ) — በታላቅ — በጭቅና — (ሰብራዳ) — በሽንጥ —
በፍርምባ — በማህል ፡ አገዳ — (ጡንቻ) — በወርች — (ነብሮ) — በጐ
ድን ፡ ተዳቢት (ቤተ ፡ ሳልገኝ) — በምላስና ፡ ሰምበር — በልብ — በጉ
በት — በኩላሊት — በጨጓራ — በሽምፍላ — በቅንጣቢ — በነጭ ፡ ጤፍ —
ጥቁር ፡ ጤፍ — ጥቁር ፡ ጤፍ — ነጭ ፡ ጤፍ — በማሽላ — ዘንጋዳ — ጨረ
ቂት — በባቄላ — በሽምብራ — በቀይ ፡ ወጥ — በአልጫ — በአልጫ —
በቀይ ፡ ወጥ — በጠጅ — በብርዝ — በጠላ — ቅራሪ ፡ እንደገና ፡ ደግሞ ፡
ቂፍ ፡ ብላ ፡ ትሞላለች — ትፈስሳለች — ትፈስሳለች — ትፈስሳለች — ታም
ማለች ፡ ሕይወት ፡ በተገማሸረ ፡ መስክ ፡ ውስጥ ፡ እንደሚብሰከሰክ ፡ ውሃ ።-
ኤዛና — ዐምደ ፡ ጽዮን — ዘርአ ፡ ያዕቆብ — ሱስንዮስ — እምነየስ — አብዬ —
መሳፍንት — ዮሐንስ — ቴዎድሮስ — ምኒልክ — ደለሏን ፡ ትተዋለች —
አዝብጤ — ጫልቱ — ለጼሳ — ጐንጤ — ሐዳስ — ቀመሩ — አዛለች —
ወርዶፋ — አርያም — ጨቡዴ — አያንቱ — ገብሬ — ተዋበች — ነስሩ —
መገርቱ — ቢራቱ — ለተሚካኤል — እርገጤ — አያንቱ — ሐጐስ —
ኩሬ — ጉድባ — ጉድባ — ኩሬ — ክትር — ክትር — ጉድባ — ጉድጓድ —
ኩሬ — ክትር — ጐለንታ — መስኖ — በርጋታ — በዝግታ — ትፈስ
ሳለች — በሌላ ፡ አገር ፡ የምትባደፈው — የምትፍለቀለቀው — የምትምቦ
ለቦለው ፡ ይችው ፡ ሕይወት . . . .

« እግዚአብሔር ፡ ሩቁን ፡ የማያይ ፡ ይመስልሃል ? ተሳስተሃል ፡ ወን
ድሜ ፤ እግዚአብሔርን ፡ ርቀትና ፡ ቅርበት ፡ አይወስነውም ። እግዚአ
ብሔር ፡ እዚህ ፡ እዚያ ፡ እሁሉ ፡ ቦታ ፡ ነው — አሁን ፡ ከኛ ፡ ጋር ፡ ነው ፡
ስንነጋገር — ሁሉን ፡ ይሰማል — ሁሉን ፡ ያያል — ሁሉን ፡ ያውቃል ። እዎ ፡

እንዳንዱ ፡ የማያይ ፡ የማይሰማ ፡ የማያውቅ ፡ መስሎ ፡ መታየትን ፡ ይመርጣል ። የበደሉትን ፡ ሰዎች ፡ እግሮች ፡ ተምበርክኮ ፡ ያጥባል — እንደፈለጋችሁ — እንደምላዳችሁ — እንደስሜታችሁ ፡ ኑሩ ፡ የሚል ፡ ይመስላል ፡ ለብልኀቱ ። አንድ ፡ ቀን ፡ የሱን ፡ ትልቅነት ፡ የሱን ፡ ወሰን ፡ የለሽነት ፡ የሱን ፡ አይመረመሬነት ፡ ዘንጋ ፡ ያልን ፡ ጊዜ ፡ ድራሻችንን ፡ ሊያጠፋ ። ሊያመጣው ፡ ውርጅብኙን ።- ሥልጣናችሁን ፡ በሚገባ ፡ አልተጠቀማችሁበትም—ለክብሬ ፡ የሚገባኝን ፡ አላቀረባችሁልኝም — ከየምታገኙት ፡ ገንዘብ ፡ ጥቂት ፡ ጥቂት ፡ እያነሣችሁ—ጧፍና ፡ ዕጣን ፡ ጋድና ፡ ሻማ ፡ መገበሪያና ፡ ጃንጥላ ፡ በማቅረብ ፡ ፈንታ ፡ በሙሉ ፡ ተጫወታችሁበት—ጠጅ ፡ መሰርገቢያና ፡ መገሰቢያ ፡ አደረጋችሁት — ስለዚህ ፡ እኔም ፡ የምሠራውን ፡ ዐውቃለሁ ፡ ሊለን — መጠጡ ፡ ራሳችሁን ፡ እያብረጀረጀ ፡ ከሳንቃ ፡ ጉብን ፡ እንዲደስማችሁ ፡ አንበጣ ፡ አመዳይና ፡ ቸነፈር ፡ የምትበሉትን ፡ አሳጥተው ፡ ችጋር ፡ እንዲነዘባችሁ — ተጓባቢውን ፡ ጐረምሳ ፡ ጥጋብ ፡ የነፋውን ፡ በዱላ ፡ የሚመላጐደውን ፡ ዱለኛ ፡ ለባለርስቱ ፡ ለባላባቱ ፡ የማይታዘዘውን ፡ ገበሬ ፡ አንገቱን ፡ ሰብረው ፡ ጭራውን ፡ እንደውሻ ፡ እንዲሸጉብ ፡ እስኪያደርጉት ፡ ድረስ — ሊለን ! ሊያመጣው ፡ የጭቃ ፡ ጅራፉን - - - » ይላሉ ፡ ወይዘሮ ፡ እሲጋሽ ፡ ለአንዱ ፡ ጭሰኞቸው —

« ገባኝኮ ፡ አሁን ፡ ገባኝ » ይመልሳል ፡ ጭሰኛው

« አዎ ፡ ይኸውልህ ፡ አሁን ፡ ገባህ - - ለምን ፡ እንደገባህ ፡ ታውቃለህ - - ? » ይቀጥላሉ ፡ ወይዘሮ ፡ እሲጋሽ « እግዚአብሔር ፡ ከእመቤትህ ፡ ስለተመሳጠረብህ ፡ ግርማ ፡ ሞገሱን ፡ ከትከሻህ ፡ ላይ ፡ ስለገፈፈብህ ፡ ሀብትህ ፡ ስለሕሰሰ ፡ ነው ። እርሻህ ፡ ተጐናገዘሎ ፡ ብዙ ፡ አምርተህ ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ ፡ ኩራት ፡ እንደነፋህ ፡ ትኖር ፡ ነበር - - -

« ይገባኛል - -

« ቆይ ፡ ቆይ ፡ ልጨርስ ! እግዚአብሔር ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ ማስታወሻ ፡ ነገር ፡ ይልካል ፡ ለሚረሱት ፡ ሁሉ ። ማጉረምረም ፡ የለብንም — ለኛ ፡ ሲል ፡ ነው ፡ የሚያደርገው — እንዲገባን ፡ ያሻል ። አስቀድመን ፡ እስታውሰነው ፡ በነበር ፡ እሱም ፡ በበትረ ፡ መንግሥቱ ፡ ባልረሳን ፤ የፈለግነውን ፡ በሰጠን ፡ ነበር — ጤፍ — ስንዴ — ገብስ — ማሽላ — ባቄላ — ጨረቂት — ያውልህ ፡ የፈለገህን ፡ ያህል ፡ ባለን ፡ ነበር ።- አሁን ፡ ግን ፡ ይኸውልህ—የእጅህን ፡ ፈለግ ፡ የእግርህን ፡ ንቃቃት ፡ የለበስከውን ፡ ቡትቶ - - -

« ምንኮ ፡ አላጣሁትም - -

« እግዚአብሔርን ፡ መፍራት ፡ የመጀመሪያው ፡ ጥበብ፡ ነው ፡- ከዚያም ፡ የበላዮችህን ፡ ማክበር—ባላባቶችን ፡ ባለርስቶችን ፡ የንጉሣቸው ፡ ልግሥና ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቸርነት ፡ ያልተለያቸውን - - - - አዎ ፡ ‘ዝምብ ፡ ቢጠራቀም ፡ ቋሚ ፡ አይከፍትም - - -

« ሀውቃለሁ ፡ እመዮቴ ! »

« ምናልባት ፡ ታውቀው ፡ ይሆናል ፤ ግን ፡ አዞረህ ፡ ብትመለከት ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ እንዳልዋለ ፡ ልትረዳ ፡ ትችላለህ ። አሁን ፡ ለምሳሌ ፡ ትንሽ ፡ ማሽላ ፡ ልትበደር ፡ መጣህ ። እርግጥ ፡ ነው ፣ የዛሬን ፡ አያድርገውና ፡ አክባሪዬና ፡ መልካም ፡ ሰው ፡ ነበርህ ። ነገር ፡ ግን ፡ አምና ፡ ትዝ ፡ ይልህ ፡ እንደሁ ፡ ትዝ ፡ ይልሃል ፡ ርግጠኛ ፡ ነኝ ፡ ላጨዳና ፡ ለውቂያ ፡ እንድታግዘኝ ፡ ብጠይቅህ ፡ ምን ፡ ብለህ ፣ ነበር ፡ የመለስህልኝ ? ‘ዶጎና ፡ ዋልስልቻ ፡ ፍሬውን ፡ ከትቻለሁ’ - - የራሴንም ፡ አላጨድሁ—የራሴንም ፡ አልወቃሁ ፤ እኔም ፡ የሚረዳኝ ፡ እፈልጋለሁ ! አላልከም ? ለመንግሥትኮ ፡ ግብር ፡ ከፋይ ፡ ነኝ ፤ ግዳጅ ፡ የለብኝም ፡ እስከዚህ ፡ አላልከም ? አምቧትረህብን ፡ ነበርኮ ፡ በል—ታኸርረህብን ፡ ነበር ! ‘ዝናብ ፡ ባይመጣ ፡ ሁሉ ፡ ቤት ፡ እንግዳ ፡ ባይመጣ ፡ ሁሉ ፡ ሴት !’ አዎ ፡ ርግጥ ፡ ነው ፡ ግዳጅ ፡ የለብህም - - ግን ፡ እየው . . . እየው . . . ጊዜው ፡ ባይሆንልህ ፡ እንዲህ ፡ ሱልል ፡ ብለህ ፡ ጭራህን ፡ እንደ ፡ ቡችላ ፡ ስታወናውን— ! ‘የወደዱትን ፡ ቢያጡ ፡ የጠሉትን ፡ ይቀላውጡ !’ በኔ ፡ በኔ ፡ ላይ ፡ ተጥርረህብኝ ፡ ነበር - - -

« ‘ጠጉራም ፡ ውሻ ፡ አለ ፡ ሲሉት ፡ በራብ ፡ ይሞት’ የለም - - ?

« በጣም ፡ ኩሩ ፡ ነህ ፤ ስለዚህ ፡ ነው ፡ ችግር ፡ የጐለሰሰህ - - - ግን ፡ ምን ፡ ታደርግ ‘ አውራ ፡ ዶሮ ፡ በየፍጉ ፡ ክምር ፡ ላይ ፡ ቆሞ ፡ ይጮሃል’ - - እኔን ፡ ተመልከተኝ ፡ ለምሳሌ — አዎ ፡ እግዜር ፡ ሞገስን ፡ ንጉሡ ፡ ነገሥቴ ፡ ክብርን ፡ አልነሡኝም ። ሆኖም ፡ አልኩራም ፤ እንዴት ፡ ልኩራ ፡ እችላለሁ ? ማነኝና ! ትል ፡ ለራሴ ! ትንሽ ፡ ፍጥረት—ምናምን ! ግን ፡ እንደምታየው ፡ ራሴን ፡ ዝቅ ፡ ዝቅ ፡ በማድረጌ ፡ እግዜርና ፡ ንጉሤ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ አደረጉኝ ፡ በፊታቸው - - - በሰማያዊ ፡ ኃይል ፡ የጐለበተ ፡ እንዲህ ፡ ነው ፡ ይኸውልህ - - - እግዜር ፡ ሞገሱን ፡ ሰጥቶ ፡ በንጉሤ ፡ ፊትም ፡ ሞገስ ፡ እንዳገኝ ፡ አደረገኝ - - -

« የዱሮው ፡ ጊዜ ፡ ይሻል ፡ ነበር ፡ እመዋቴ ፤ እንዲህ ፡ እንደ ፡ ዛሬው ፡ ሳይሆን ፡ ባላባትና ፡ ገበሬ ፡ የሚተሳሰቡበት - - -

« እንዴታ ፡ ምን ፡ ጥርጥር ፡ አለው ፤ እንዲህ ፡ እንደዛሬ ፡ የጌታና ፡ አሽከር ፡ መንገራበብ ፡ ያልነበረበት — በየጊዜው ፡ የሚያፈጠፍጥ ፡ ክፉ ፡ ዐመል - - ጥሩው ፡ ጊዜ ፡ አለፈ ፤ ዓለማችሁን ፡ ያያችሁበት — አደንጓ ሬው ፡ በቆሎው ፡ ደንጎሎው ፡ ጨረቂቱ ፡ ዘንጋዳው . . . ምን ፡ ያረ ጋል ፡ ብቻ ፡ ያለፈውን ፡ ቢያስታውሱት ? አሁን ፡ ማስታወሱ ፡ አይ በጅም ። ዱሮ ፡ ዱሮ ፡ ነው — ስለዱሮው ፡ የረሳሁትን - - ! ‘ ፍላጻ ፡ ባየር ፡ ውስጥ ፡ አልፎ ፡ ፍለጋ ፡ አይተውም ! ’ እና ፡ አሁን ፡ ታዲያ ፡ የመጣኸው ፡ ትንሽ ፡ ዘንጋዳ ፡ ለመበደር ፡ ነው ፡ አልክ - - ?

« ነበራ ፡ እመዋቴ ፡ ማስቸገሬ ፡ ባይሆን - - -

« ለመግዛት ፡ ነው ፡ የምትፈልገው - - ?

« ከየቴ ፡ እመዋቴ ፤ ብሩ ፡ ከየት ፡ ተገኝቶ ? በዚያው ፡ ባይነቱ ፡ ለመ ክፈል ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በትሣሥ - -

«ነገር ፡ ማሞድሞድ ፡ ገንዘብ ፡ አይሆንም ፡ ይኸውልህ ! ‘ ለቀን ዳም ፡ በሬ ፡ ቤት ፡ አትክልክለው ፡ ቀንዱ ፡ ይከለክለዋል ! ’ ነው »

« መቼምኮ ፡ የሚሉት ፡ ሳይገባኝ ፡ ቀርቶ ፡ አይደለም - -
ብቻ ፡ እንዲያው ፡ ሰኔና ፡ ሰኞ - - -

«አዎ ፡ ካጡ ፡ ወዲያ ፡ ማንኛውም ፡ ነገር ፡ እያምር ‘ በሰም ፡ የተጣ በቀ ፡ ጥርስ ፡ ቢስቁበት ፡ አይደምቅ ፡ ቢበሉበት ፡ እያደቅ - - ! ’

« ታዲያ ፡ ምን ፡ ተሻለኝ ፡ ይመስልዎታል ፡ አሁን - - ?

« መከልከሌ ፡ አይደለምኮ ‘ ሰው ፡ ሆኖ ፡ የማይብስ ፡ እንጨት ፡ ሆኖ ፡ የማይጨስ ! ’ - - ‘ ሰው ፡ ከስሕተት ፡ ብረት ፡ ከዝገት - - ’

« ታዲያ ፡ ያሉትን ፡ ብለውኝ ፡ ብሄድ - - -

« ‘ ብረት ፡ ካልፈላ ፡ አይላላ ’ — እንዲህ ፡ ልክ ፡ ገባህ ፡ ይኸው ልህ - - -

« ዱሮምኮ ፡ ቢሆን - - እንዲያው ፡ ባንጣጣም ፡ ይሆናሊ - - -

« ያለፈው ፡ አለፈ ፤ አሁን ፡ አንድ ፡ ልልህ ፡ የምፈልገው - - ምን ፡ ነበር ፡ እቴ ! አዎ ፡ ለሁሉ ፡ እግዚአብሔርን . . ማለቴ ፡ ከሆነ ፡

ወዳያ ‘ ደም ፡ ማልቀስ ፡ ድንጋይ ፡ መንከስ ’ እያስፈልግም - - ‘ ወረ ቱን ፡ እንደተቀማ ፡ ነጋዴ ፡ ዋግ ፡ እንደመታው ፡ ስንዴ ’ መሟሰስ ፡ የወ ንድ ፡ ልጅ ፡ ተግባር ፡ አይደለም - - ያሁኑ ፡ ወራት ፡ ስሕተትህን ፡ ማረሚያ ፡ ነው ። ‘ ከዝንጀሮ ፡ ጋሚ ፡ ያንበሳ ፡ መላጣ ’ መሻሉን ፡ መገን ዘቢያህ - - እንዲያ ፡ ተንዝባረህብኝ ፡ የነበረው ፡ ስውዬ ፡ ቢኖረኝ ፡ ነው ፡ የመጣኸው ‘ - - ተስካር ፡ ያየ ፡ ተማሪ ፡ ሽቀጥ ፡ ያየ ፡ አጣሪ - - ’

« የመሄጃ ፡ እጦት ፡ ነው ፡ እመዩቴ - -

« ግርምቢጠኛነትህን ፡ ትንሽ ፡ አብርዶልሃል ፤ መቼስ ፡ ጨርሶም ፡ ባይጠፋ ። አዎ ፡ ለወደፊቱ ፡ መንገድ ፡ ስንገናኝም ፡ ቢሆን ፡ ከፈለፈቷ ፡ ሽረር ፡ ብለህ ፡ መንገዱን ፡ ብትለቅልኝ ፡ ነውር ፡ የለውም - - - እን ዳንዴ ፡ እንደሚማልግ ፡ ነብር ፡ አንዳንዴ ፡ እየተፍረገረገ ፡ እንደሚለማ መጥ ፡ ድመት ፡ መሆን ፡ ያስተዛዝባል - - እዎ ፡ ፊት ፡ ማጭገግ ፡ ወይም ፡ መሰንገጭም ፡ በኔ ፡ አይደለም - - ከግምባርህ ፡ ትሕትናን ፡ አታጥፋ - - -

« እመዩቴ ፡ መቼም ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ አላስቸገርኩዎትም - - -

« እንደት ፡ አዝን ፡ ይመስልሃል ፡ እንዲህ ፡ ተቆራምደህ ፡ ሳይ - -

« ታዲያ ፡ ታዘኑ - - -

« እንዴታ ! በርግጥ ፡ ታሳዝነኛለህ ፡ ነገር ፡ ወዲያ ፡ ወዲህ ፡ ሆኖ ብኝ ፡ ነው ፡ እንጂ ‘ እህል ፡ ያለው ፡ ፈርዛዛ ፡ ገንዘብ ፡ ያለው ፡ ቀበዝ ባዛ ’ - - የተቻለኝን ፡ ባደረግሁልህ - - - እንደምታውቀው ፡ ግን ፡ ዘንጋዳው ፡ ተወደ.ል ፤ የሚሆንልህ ፡ ቢሆን ፡ ጥሬው ፡ ገንዘብ ፡ ይሻለኝ ፡ ነበር ። ሳት ፡ ሆኗል ፡ ዘንጋዳ - - እንደ ፡ ዘንድሮ ፡ ሆኖም ፡ አያውቅ - - ምን ፡ ይመስልሃል ፡ ታዲያ - - ? ደግሞስ ፡ ደግሞስ ፡ ሰማሆይ ፡ መረዳዳ ትን ፡ የመሰለ ፡ ምን ፡ ዓለም ፡ አለ ? መረዳዳቱ ፡ አይከፋም - - ዛሬ ፡ ባበ ድርህ ፡ ነገ ፡ ደግሞ ፡ እኔ ፡ አበድረኝ ፡ ልልህ ፡ እመጣ ፡ ይሆናል - - -

« ይሆን ፡ ይሆን ፡ እመዩቴ - - መቼስ - - -

« አይ ፡ ይሆናል ፡ እንኳ ፡ ብዬ ፡ አይደለም - - - ያልጠረጠረ ፡ ለማ ለት ፡ ያህል ፡ ነው - - እና ፡ ታዲያ ፡ አሁን ፡ የምትፈልገው ፡ አሥራምስት ፡ ቁና ፡ መሆኑ ፡ ነው - - ?

« አዎ ፡ እመዩቴ ፡ ፈቃድዎ ፡ ከሆነ - - -

« ጥሩ ፡ ነው - - አሥራምስት ፡ ቁና - - - ዘጠኝ ፡ ቁና ፡ እሰጥሃለሁ ፡ ማለት ፡ ነው ፤ በትሣሥ ፡ አሥራምስት ፡ አድርገህ ፡ ትመልሳለህ - -

« አይ ፡ እኔ ፡ እንኳን - - -

« እንደምታየው ፡ ወለድ ፡ አልፈልግም ፤ ያው ፡ ዓይነት ፡ ባይነቱ ፡ ነው ፤ በብዛት ፡ አምርተህ ፡ ከምታገባው ። እዎ ፡ ብዙ ፡ አይደለም ። ደግሞ ፡ በደንብ ፡ እየተንቸረፈፈ ፡ ይሰፈርልሃል ‘ ወዶ ፡ የዋጡት ፡ ቅል ጥም ፡ ከፍርምባ ፡ ይጥም ’

« ትንሽ ፡ አልበዛም ፡ እመዮቱ - - ?

«ብዛ ? አይ ፡ እንግዲያው ፡ ከበዛ ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ ብትጠይቅ ፡ ይሻላል ።- እኔ ፡ እስከዚህ ፡ የምንጓለት ፡ ነገር ፡ አይደለም ፤ ስላዘኔታዬ ፡ ነው ፡ የማበ ድርህ ፡— አንተ ፡ መጣህብኝ ፡ እኔ ፡ አልመጣሁብህም - - -

« መቼም ፡ እመዮቴ ፡ አዘኔታዎን ፡ አልከሉ ፡ እንጂ - - -

« አዘኔታዬ ፡ አልተለየህም - - - ደግሞም ፡ ነገር ፡ ቢዘበዝቡት ፡ ምን ፡ ያደርጋል - - -

« እርግጥ ፡ ነው ፡ ብቻ ፡ የምመልሰው ፡ ትንሽ ፡ የበዛ ፡ መሰለኝ - -

« አይ ፡ አይ ፡ አይ ፡ እንግዲህ ፡ በነገር ፡ አትጉሸምጠኝ ። መንግ ሥት ፡ ከፈቀደልኝ ፡ በላይ ፡ የምወስድብህ ፡ አራጣ ፡ በሊታ ፡ ማድረግህ ፡ ነው ? አጉል ፡ ተናገርክ ። እኔ ፡ ደሞ ፡ ጥንክር ፡ ሰው ፡ ስትመስለኝ ፡ ወስዋሳና ፡ ተልካሻ ፡ ወጣህ ፡ ልበል - - ?

« ዋ ፡ እመዮቴ ፡ መቼም ፡ ያላትሟ - -

« ምነው ፡ ቢገባህ ! እኔስ ፡ በምን ፡ ልኑር ፡ ትላለህ ? ስንት ፡ መሰ ለህ ፡ የሚተኮሰው ፡ ጉዳዬ - - - የየቁረንጮው ፡ ግብር ፡ ራሴን ፡ ሲያ ዞረው ፡ ነው ። በዚያ ፡ ላይ ፡ የሮማን ፡ ሠርግ ፡ ደርሷል - - የየመንኮሳቱ ፡ ድርጐ ፡ አለብኝ - - ስንቱን ፡ ልበልህ - - - እዎ ፡ ባይሆን ፡ ለወደ ፊቱ ፡ በየቦታው ፡ ከማዘዋዘዋ ፡ ጠንከር ፡ ብሎ ፡ መሥራት ፡ ይኖርብሃል ።- ‘ ወስፈ ፡ ቢለግም ፡ ቅቤ ፡ አይወጋም ’ - - -

« መቼስ ፡ ምን ፡ ይደረጋል ፡ ይሁና ፡ ከጩከኑ - - -

« ጭካኔ ! የምን ፡ ጭካኔ ፡ ጭካኔን ፡ ምን ፡ አመጣው - - ? አይ ፡ አድራጐቴ ፡ ጭካኔ ፡ ከመሰለህ ፡ ብትተወው ፡ ይሻላል - - -

« ማለቴኮ ፡ እመዮቴ - - -

« ሰማሁኮ ፡ ያልከውን - - -

« ይሁና ፡ እንግዲያው ፡ መቼስ ፡ ምን ፡ አደርጋለሁ - - -

« እዎ ፡ እንዲያ ፡ ይሻላል - - ዘንድሮ ፡ እምናን ፡ አይደለም ፤ የምታደርገው ፡ ነገር ፡ የለም - - - በነገራችን ፡ ላይ ፡ እኔ ፡ ላንተ ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ ስውልልህ ፡ አንተም ፡ ለኔ ፡ መዋል ፡ ሳይኖርብህ ፡ አይቀርም - - የክርስቲያን ፡ ምልክቱ ፡ ነው - - -

« ምን ፡ ከፍቶኝ ፡ የሚሆን ፡ ከሆነ - - -

« የክርስቲያን ፡ ምልክቱ ፡ ሲውሉልህ ፡ መዋል ፡ ነው ፡ ትልቁ ፡ ትምርት ፤ እና ፡ ታዲያ ፡ እዚያ ፡ አንተ ፡ አዋሳኝ ፡ ያለውን ፡ ድርቆሼን ፡ ብታስተጫጭቀኝ - - - እንደምታየው ፡ ወለድ ፡ አልጠየቅሁህም - - ማለቱ ፡ እንደውለታ ! ውለታ ፡ እንዳይከብድህ - - - እኛ ፡ ስንረዳዳ ፡ እግዜር ፡ ይረዳናል ፡ ደስ ፡ ይለዋል ፡ ቁልቁል ፡ ሲመለከተን - - - ደግሞም ፡ ላንተ ፡ ያን ፡ ድርቆሽ ፡ ማጨድ ፡ ምንም ፡ አይጐዳህም ፤ እኔ ፡ ግን ፡ ለወደፊቱ ፡ ውለታህን ፡ አልረሳም - - ገር ፡ ሰው ፡ ነኝ ፡ እንደምታውቀው - - - እርምጃህ ፡ ታዲያ ፡ ቅድም ፡ እንዳነጣሁልህ ፡ ትንሽ ፡ ተፋጥኗል ‘ ሲሮጡ ፡ ያውሩት ፡ ሲሮጡ ፡ ይፈታል ’ - - ትንሽ ፡ ልጓም ፡ አብጅለት - - እዎ ፡ እፍንጫ ፡ መሰቀሉን ፡ ትደርስበታለህ ። እኔም ፡ ብሆን ፡ ባንደዜ ፡ ብቻዬን ፡ አይምሰልህ ፡ እዚህ ፡ ደረጃ ፡ ለመድረስ ፡ የቻልኩት ፤ አያት ፡ ቅድም ፡ አያቶቼ ፡ ጠጅ ፡ የሚያጠጣ ፡ ርስት ፡ በማቆየታቸው ፡ ነው ፤ ሸንተውብት ፡ ስላላለፉ ። እዎ ፡ ሰው ፡ እንደቤቱ ፡ እንጂ ፡ እንደ ፡ ጐረቤቱ ፡ አይኖርም ፡ - - ድርቆሹን ፡ እንግዲህ ፡ ካጨድኸው ፡ በኋላ - - አንድ ፡ ስማኒያ ፡ ሽከም ፡ ቢሆን ፡ ነው - - እያመጣህ ፡ እደጁ ፡ እንድትከምረው - - መንገዱ ፡ ትንሽ ፡ ይርቅሃል - - ስለዚህ ፡ አላቻኩልህም — ባሥራምስት ፡ ቀንም ፡ ቢሆን ፡ በወር ፡ ልትጨርሰው ፡ ትችላለህ - -

« እንግዲህ ፡ እመንገዱ ፡ ልግባ ፡ እመዩቴ ፡ ላይን ፡ ሳይዝብኝ - - ጀምበሯ ፡ መጥለቋ ፡ ነው - - -

« እዎ ፡ ስለ ፡ ዘንጋዳው ፡ አታስብ ፤ ቲፍፍ ፡ እየተደረገ ፡ ይሰፈርልሃል - - -

« ላይን ፡ ሳይዝ ፡ ቢሰፈርልኝ - - -

ጊዜው ፡ የከብቶች ፡ ከሥምሪት ፡ መመለሻ ፡ ሰዓት ፡ ስለነበረ ፡ የቀንድ ፡ ከብቶች ፡ ባንድ ፡ ፈት ፡ በጐችና ፡ ፍየሎች ፡ ባንድ ፡ ፈት ፡ የጋማ ፡ ከብቶች ፡ ባንድ ፡ ፈት ፡ የቤታቸውን ፡ አቅበት ፡ ተያይዘውታል ። የፈን

ጣው ፡ ሲርሲርታ ፡ የዝንቡ ፡ ዝዝታ ፡ የንቦቹ ፡ እምምታ ፡ በዙሪያ ፡ ጉብ ታው ፡ ያስተጋባል ። አውራ ፡ ዶሮ ፡ እልፎ ፡ እልፎ ፡ ይኮኩላል ። እውሃ ፡ መቅጃው ፡ ኩሬ ፡ የእንቁራሪቶች ፡ ሥርግና ፡ ምላሽ ፡ ሆኗል ። ላሞች ፡ ያም ቡዋሉ ፡ ጥጆች ፡ ያስተጋባሉ ፡ ያምቧርቃሉ ፤ ያ ፡ ጭር ፡ ብሎ ፡ የሚው ለው ፡ ቀዬ ፡ ላንድ ፡ አፍታ ፡ በሕይወት ፡ መምቦልቦል ፡ ይጀምራል ። እያ ደር ፡ በሚጣደፈው ፡ ጭለማ ፤ ታፍኖ ፡ ሊጠፋ - - -

« ሮማን - -

« ማነህ ፡ አንተ ? » ድንግጥ ፡ ብላ ፡ የሸምጡን ፡ አጥር ፡ ተገን ፡ በመያዝ ።

« ሮማን ፤ አይዞሽ ፡ እኔ ፡ ነኝ - -

« ማ - -

« እኔ - -

« ማ ፡ አብዬ - - » ድንጋጤዋ ፡ በረድ ፡ ባለ ፡ መንፈስ ።

« የለም ፤ ጉርፋ ፡ ነኝ - - ዋንዛ ፡ ይዠልሻለሁ - - -

« እኔ ፡ ዋንዛ ፡ አልፈልግም - - -

« ቅሞም ፡ ብትፈልጊ ፡ አለኝ - -

« የለም ፡ አልፈልግም - -

« ኮሽምስ ?

« አልፈልግም ! ደግሞ ፡ ያልገባኝ ፡ አይምሰልህ ፡ የመጣህበት - -

« ኮክስ ?

« አትቀልድ ፡ እባክህ - -

« ቀጋስ ፤ ሎሚስ ?

« አልፈልግም ፡ አልኩህ ፡ እንግዲህ - -

« እውነትሽን ፡ ነው ፡ አሁን ?

« እንዴታ ! እውነቴን ፡ ነው - -

ጉርፋ ፡ የሰዓቱን ፡ አስባታሊነትና ፡ አጣድፊኝነት ፡ የከብቶቹን ፡ መውጣት ፡ መግባት ፡ የፍየሎቹንና ፡ የበጉቹን ፡ መሯሯጥና ፡ ትርምስ ፡ የጆ ምበሯንም ፡ ጥላ ፡ እየዘፈቃት ፡ መሄድ ፡ በመተማመን ፡ ነበር ፡ እንደል ማዱ ፡ የመጣው ፤ ገበሮችና ፡ እረኞች ፡ እንዳያዩት ፡ ቆም ፡ እያለ ፡ ዙሪያ ውን ፡ እየማተረ ፡ ስላች ፡ ስላች ፡ መንገድ ፡ እየመረጠ ።-ቁመናው ፡ ጥም

ጥም ፡ ያለ ፡ እግሮቹ ፡ የሚያጉጧቸውን ፡ አፈናጥረው ፡ አረጋገጣቸው ፡ የተዝናና ፡ የተደላደለ ፡ ልቡ ፡ በዝቅተኝነት ፡ መንፈስ ፡ ያልተበረዘ - - ፍልጥ ፡ ፍልጥ ፡ ጥርሶቹን ፡ በክትክታ ፡ መፋቂያው ፡ ሚዝቅ ፡ ሚዝቅ ፡ አድርጐ ፡ በረጅሙ ፡ ጢቅ ፡ ያለ ፡ እንደሆን ፡ ኩራቱን ፡ ለመገመት ፡ የሚቻል ፡— ገንጋኝ ፡ ጠርጣሪ ፡ ከፈለገበት ፡ ግብ ፡ ለመድረስ ፡ ታጥቆ ፡ የተነሣ ፡ የባላገር ፡ ቃንቄ ፡ ነው ።— ያዳል ፡ ጫማ ፡ አድርጓል — ቀጭን ፡ ሱሪ ፡ ታጥቋል — እጀ ፡ ጠባብ ፡ አጥልቋል — የሳርያን ፡ ኮት ፡ ደርቧል — ቀጭን ፡ ኩታ ፡ ሸው ፡ አድርጓል — በግራ ፡ ትከሻው ፡ የተወለወለ ፡ አጭር ፡ አል ቤን ፡ አንግቷል ።— አጭር ፡ ነው — ቀጭን ፡ ነው — ጠይም ፡ ነው — ግምባረ ፡ ሰፊ ፡ ጭንቅላተ ፡ ገምናና ፡ ፊት ፡ ኮስታራ ፡ ነው ። - ጺ.ወኔን ፡ እናቲቱ ፡ ፈቃዳቸው ፡ ቢሆን ፡ ባገር ፡ ደንብ ፡ መሠረት ፡ እንዲድሩለት ፡ ደጅ ፡ የሚጠና ፡ ፈቃዳቸው ፡ የማይሆን ፡ ቢሆን ፡ ደግሞ ፡ ጠልፎ ፡ ለመውሰድ ፡ ቁርጥ ፡ ሐሳብ ፡ ያደረገ ፡ ነው ።

« እንጆሪም ፡ አትፈልጊ ? » ቀጥሏል ፡ ማባባሉን ።—

« እንጆሪ ?!

« አዎ ፡ እንጆሪ - - -

« እንጆሪ - - -

« አዎ ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ ብቻ ፡ ካደረግሽልኝ - -

« ምን - -

« ጺ.ወኔን ፡ ወዲህ ፡ ብቅ ፡ ብታሰኝልኝ - - -

« ጺ.ወኔን - - - ጺ.ወኔን ¡ - - - አይ ፡ ጺ.ወኔ ፡ ደክሟታል ፡ ኮሶ ፡ ጠጥታ - -

« ታዲያ ፡ የኮሶ ፡ ራት ፡ አትሻም ? ማለቴ ፡ ተሰናብቸሃለሁ ፡ ብላኝ ፡ ነበር - - !

«ባላገሯን ፡ ፈልግና ፡ አታል ፡ እባክህ ፤ ቀድሞ ፡ የት ፡ አገኘችህና ፡ ነው ፡ የምትሰናበትህ ? ደግሞስ ፡ ጺ.ወኔ ፡ ነች ፡ አንተን ፡ የምታነጋግር - - ረሳ ሽው ፡ በቀደም ፡ እዚያ ፡ ውሃ ፡ መቅጃ ፡ እንዴት ፡ እንዳስደነገጥሽን - -

« ለመሆኑ ፡ አንችስ ፡ ኮሶ ፡ ጠጥተሻ ፡ የለም ፡ እንዴ - - ?

« እኔማ ፡ እንዲያውም ፡ በትልቅ ፡ ዋንጫ ፡ ነው ፤ ግን ፡ እንደምታየው ፡ ንክችም ፡ አላረገኝ - - እንጆሪውን ፡ ያመጣህላት ፡ ለኮሶ ፡ ራቷ ፡ ነው - - ?

« አይ ፣ እንጀራውንስ ፣ ላንቺ ፣ ነው - -

« መቼ ፣ ተሰናበትሁህና ፣ ቀልደኛ ፣ ነህ ፣ ለካ ! ሮማንን ፣ አታልላለሁ ፣ ማለት ፣ ዘበት ፣ ነው ፣ ዕወቀው - - -

« እምልሽ ፣ አንድ ፣ ነገር ፣ እንደሚጠይቅ ፣ ጠርተሻት ፣ ብቅ ፣ ብታሰኝልኝ - - የያዝኩትን ፣ እንጀራ ፣ በሙሉ ፣ እሰጥሻለሁ - -

« ባንተ ፣ ቤት ፣ የሚታለልልህ ፣ አግኝተሃል- -ይልቅ ፣ አብዬን ፣ ጠርቼ ፣ ማጣፊያው ፣ እንዳያጥርህ ፣ ብትሄድ ፣ ይሻልሃል - -

« እሱን ፣ እንኳን ፣ እርሽው ፤ ያንቺን ፣ አባት ፣ የሚፈራ ፣ የለም - - ይልቅ ፣ የጠየቅሁሽን ፣ አድርጊልኝ - -

« የኔን ፣ አባት ፣ አትፈራም ? የኔን ፣ አባት ፣ አትፈራም - - -

« ቆይ ፣ ቆይ ፣ ነይ ፣ እባክሽ ! ቀልዱን ፣ እንደምር ፣ አታድርጊው - - -

« አልፈራውምኮ ፣ ብለሃል - - -

« በቀደም ፣ እጉድባ ፣ ውሃ ፣ ስትቀዱ ፣ ደነገጣችሁ ፣ ለካ - - - !

« መደንገጥ ፣ ይነስን - - -

« እባክሽ ፣ ጂወኔን ፣ ብቅ ፣ አሰኝልኝ ፣ ሮማን - - -

ሮማን ፣ ከኋላዋ ፣ ኮሽታ ፣ ትሰማና ፣ ዘወር ፣ ትላለች « መጣችልህ ፣ እንዲያውም ! እስኪ ፣ እስከዚህ ፣ የቀሠፍኸኝ ፣ ለምን ፣ እንደሆነ ፣ እናያለን » ጉርፉ ፣ ወደ ፣ አጥሩ ፣ ጠጋ ፣ ብሎ ፣ በመሸሸግ ፣ የጂወኔን ፣ መምጣት ፣ ይጠባበቃል ።-እንገቷን ፣ ውዝ ፣ ውዝ ፣ እያደረገች ፣ ወደ ፣ ዋናው ፣ አጥር ፣ በር ፣ ታመራለች ፤ አህያ ፣ ኖራለች ፣ ለካ ፤ በጀርባዋ ፣ ላይ ፣ አንድ ፣ ስልቻ ፣ ተጭኖባታል ።- ባለቤቷ ፣ ጭሰኛው ፣ ዱላውን ፣ እትከሻው ፣ ላይ ፣ ጣል ፣ አድርጎ ፣ ራቅ ፣ ብሎ ፣ ተከትሏታል ።

« ተጫወትሽብኝኮ ፣ ሮማን ! ተጫወትሽብኝ ! » ይላታል ፣ ሮማንን ፣ አህያና ፣ ጭሰኛ ፣ ካለፉ ፣ በኋላ ።-

« እኔ ፣ አላወቅሁም ፤ መሰለችኝ - -

« አህያዋ ፣ የእመቤትሽን ፣ ልጅ ፣ መሰለችሽ - - ?

« ካልክስ ፣ ጭሰኛውም ፣ አብዬ ፣ ወርቃፋን ፣ መስሎኝ ፣ ነበር ።- ለመሆኑ ፣ ቢሆን ፣ ኖሮ ፣ ምን ፣ ታደርግ ፣ ነበር ? እንዲያ ፣ ዱላውን ፣ እንግበ ፣ ሲመጣብህ - - - ?

« እሸሽ ፡ ነበራ - - -

«መማሪያ ፡ ይዘህ ፡ ትሸሻለህ - - - ?

« እቮፍሽብኝኮ ፡ ሮማን ፤ እቮፍሽብኝ - - ለመሆኑ ፡ ብቅ ፡ እታሰ ኝልኝም ፡ ማለት ፡ ነው ፡ እንግዲህ - - - ?

« እንዴት ፡ ያለኸው ፡ ነህ ፡ ለመሆኑ ? እመዮቴስ ፡ ያዩ ፡ እንደሆን ፡ ምን ፡ መልስ ፡ ይኖረኛል ፤ ታልፍልኛለህ ፡ አንተ - - ? አትቀልድ ፡ እባክህ - - ! » በእስኪ - እሞክራለሁ - ተሆነልኝ ፡ እስተያየት ፡ እየት ፡ ታደርገውና ፡ ዞር ፡ ብላ ፡ ወደ ፡ ቤት ፡ ታመራለች ፡፡—

# ፪

# አደፍርስ

ለዓይን ፡ እየያዘ ፡ እየያዘ ፡ እየጠየመ ፡ እየጠየመ ፡ ሲሄድ ፡ ጕራው - - - በየጉባው ፡ በየተራራውና ፡ በየሸንተረሩ ፡ ላይ ፡ በመትጉልጉልና ፡ በመብነን ፡ ላይ ፡ ያሉት ፡ ደመናዎች ፡ ቦታቸውን ፡ ለጥቁሩ ፡ ሰማይ ፡ ይለቃሉ ፡ በመጣደፍ ።—የሳት ፡ ኩብ ፡ የመሰለች ፡ ጨረቃ ፡ ትወጣለች ።—ጀምበሯ ፡ ጨርሶ ፡ ትጠልቃለች ፡ አድማሱን ፡ በሁለት ፡ የብርሃን ፡ ስለቶች ፡ በስተቀኝ ፡ ዝቅ ፡ ብሎ ፡ በሚታየው ፡ ሰማያዊ ፡ በስተግራ ፡ ከፍ ፡ ብሎ ፡ በሚታየው ፡ አብረቅራቂ ፡ ሐምራዊ ፡ ወትራ ፡ ደብዘዝ ፡ ያሉ ፡ ወርቅማ ፡ መሥመሮችንና ፡ ገርጣ ፡ ያሉ ፡ ብጫ ፡ ቀለሞችን ፡ እያፈለቀች ። ቀዬውም ፡ ቀስ ፡ በቀስ ፡ ጸጥታውን ፡ መመለስ ፡ ይጀምራል ። ላሞቹ ፡ ከጥጆቻቸው ፡ ሲገናኙ ፡ ዝም ፡ ይላሉ ፤ በጐችና ፡ ፍየሎች ፡ ሞቃት ፡ ጥጋታቸው ፡ ሲታሠሩ ፡ ዝም ፡ ይላሉ ፤ ንቦች ፡ እየቀፎቻቸው ፡ ሲሠርጉ ፡ ዝም ፡ ይላሉ ፤ ዝንቦች ፡ እየጣራው ፡ እየሥርቻው ፡ ሲስገሰጉ ፡ ዝም ፡ ይላሉ ። የከብቶች ፡ ራት ፡ ተሰጠ ፤ ማምሻ ፡ እንጨት ፡ በየቤቱ ፡ ውስጥ ፡ መንቀልቀል ፡ ጀመረ ።—ገበሮች ፡ እሹታቸውን ፡ ቃቅመው ፡ ራት ፡ መብላታቸውን ፡ ከብቶች ፡ ሣር ፡ ወይም ፡ ጭዳቸውን ፡ ገርደፍ ፡ ገርደፍ ፡ እያደረጉ ፡ ማጠራቀማቸውን ፡ ጨርሰው ፡ ማመንዠካቸውን ፡ ቀጥለዋል ፡—ሸከም—ሸከም—እንካ !— ሸከም— ሸከም —እንካ ! እያለ ፡ የሚያምምና ፡ እንደስርቅታ ፡ እንደህቅታ ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ የሚቋቁር ፡ የፌንጣና ፡ የእንቁራሪቶች ፡ ቁርቁርታ ፡ ብቻ ፡ ቀርቷል ።

« ምነው ፡ ዝም ፡ ዝም ፡ ሆነ ፡ እትነጋገርም ? » ትለዋለች ፡ ጺወኔ ፡ ጐርፉን ።

« እነጋገራለሁኮ - - - ! ኮሶ ፡ ተጣብቶሽ ፡ ነበር ፡ መሰለኝ - - ?

« ኢዲያ ፡ እንዲያው ፡ ያጉ ፡ ነህ ፡ ምንም ፡ አልተለወጥህም » ለራሷ ፡ የምትናገር ፡ ይመስል « - - ስማ ፡ የጠለፍኳቸውን ፡ ጥቅሶች ፡ ላሳይህ - - - ? ደብረሲና ፡ ከወጣሁኮ ፡ ብዙ ፡ ነገር ፡ ተምሪያለሁ - - -

አብዛኞቹ ፡ ገበሬዎችና ፡ እረኞች ፡ ጋደም ፡ ጋደም ፡ ለማለት ፡ ይዘጋጃጃሉ ። ልማዱን ፡ ሳያደርስ ፡ የማይተኛው ፡ ወርዶፋ ፡ ደግሞ ፡ የም

ሽቱን ፡ ጸጥታ ፡ ጥሶ ፡ ዋሽንቱን ፡ ማሰማት ፡ ይጀምራል ።— አልፎ ፡ አልፎ ፡ የሚያፏጭ ፡ ነፋስ ፡ ይነፍሳል ። እርስ ፡ በርሳቸው ፡ የሚመስጣጠሩት ፡ ቅርንጫፎች ፡ ራሳቸውን ፡ እዚህና ፡ እዚያ ፡ ያንገናሉ ። — ሰማዩን ፡ የተጠጉ ፡ የሚመስሉት ፡ በሩቅ ፡ የሚታዩት ፡ ደመናዎች ፡ በሩጫ ፡ ይበራረራሉ ፤ ጨረቃንም ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ በመሸፈን ፡ ሠፈሩን ፡ በየድንገቱ ፡ በተመሳሰለ ፡ ጥላ ፡ ሥር ፡ ያሳርፉታል ።

« ምነው ፡ ምን ፡ ሆንሃል ? የከፋህ ፡ ትመስላለህ - - - ዘና ፡ ብለህ ፡ ተጫወት ፡ እንጂ - - -

«እንዳይከፋኝና ፡ እንድዝናና ፡ ትፈልጊያለሽ - - - ?

«እንዴታ ፡ ምነው ? » የማወቅ ፡ ፍላጐትና ፡ ርኅራኄ ፡ ባለበት ፡ ድምፅ ።

የጨረቃ ፡ የብርሃን ፡ ውሽምፍር ፡ በየቅጠሉ ፡ ውስጥ ፡ ይንገዋገዋታል ። በእልፎሽ ፡ እግድሞሽ ፡ የተሰበጣጠረ ፡ የብርሃን ፡ ጥላ ፡ ሙካሽ ፡ በመጥለፍ፡ — ወርዶፉ ፡ ዋሽንቱን ፡ ይጫወታል ፡— የዛፎቹ ፡ የእንቅስቃሴ ፡ ድምፅ ፡ የልዩ ፡ ዓይነት ፡ ፈንጠዝያ ፡ ደስታ ፡ እየመሰለ ፡ ይሄዳል— የሚያጣድፍ ፡ ደስታ ፡— የልዩ ፡ ዓይነት ፡ የልብ ፡ ወጀብ ፡—ባዘንና ፡ በጭንቅ ፡ ጊዜ ፡ የሚነሣ ፡ ድንገታዊ ፡ ነውጽ ፡—

« እንግዲያው ፡ መጀመሪያ ፡ እንዲህ ፡ እንደምታይኝ ፡ አትይኝ ። ከደብረ ፡ ሲና ፡ ከተመለስሽ ፡ ጀምሮ ፡ ሌላ ፡ ነው ፡ የሆንሽብኝ ።— ይገርምሻል ፡ አስተያየትሽማ ፡ የባሰውን ፡ ዝም ፡ ነው ፡ የሚያሰኘኝ » የባሰ ፡ አጉርጣ ፡ ታየዋለች « እንደሱ ፡ አትይኝ ፡ ስልሽ ! ፍሬ ፡ ነገርም ፡ ሳንጫወት ፡ ተመልሺ ፡ እንድጊድልሽ ፡ ነው ፡ መሰለኝ ፡ የምትፈልጊው - - -

« ምነው ፡ ይዘህልኝ ፡ የመጣኸውን ፡ የኮሶ ፡ ራቱን ፡ ሳትሰጠኝ ? ሮማንኮ ፡ ነግራኛለች - - -

ጨረቃዋ፡ እያደር ፡ ትንቀለቀላለች ፤ በያቅራቢያውና ፡ በየሩቁ ፡ እጅብ ፡ ብለው ፡ ከሚታዩት ፡ የባሕር ፡ ዛፍ ፡ ጉራንጉሮች ፡ ቦግ ፡ ቦግ ፡ ያሉ ፡ ኪሳኪሶችን ፡ ፈጥራ ፡ አጉርጠው ፡ የሚያዴቡ ፡ እስደንጋጭ ፡ የጐልያዶች ፡ ዓይኖችን ፡ በማስመሰል ። ቅርንጫፎቹና ፡ ቅጠሎቹ፡ ቢሆን ፡ ሲንቀሳቀሱ ፡ መታየታቸው ፡ ይቀራል ። ራሳቸውን ፡ ወደ ፡ ሞቃቱ ፡ ጎዋ ፡ እስግገው ፡ የወርዶፉን ፡ ዋሽንት ፡ በጸጥታ ፡ እንደሚያዳምጡ ፡ ዓይነት ።—ከየደብዛዛውና ፡ ርቆ ፡ ከሚታየው ፡ ጥልቀት ፡ ውስጥ ፡ ከዋክብት ፡ ይንተገተጋሉ ። ከየጉባው ፡ ደረት ፡ ከየሸለቆው ፡ ከየቤቱ ፡ ፉካዎች ፡ ጭሱና ፡ ጭጋጉ ፡

ይርመስመሳል ።—ምሽቱ ፡ ቀለል ፡ ያለ ፡ አየሩ ፡ በሙቀትና ፡ በቅዝቃዜ ፡ የተበረዘ ፡ ጣዕመ ፡ መለኪያው ፡ ውድቱና ፡ ደስሳው ፡ የሆን ፡ በለዘብታ ፡ አፍንጫን ፡ ሰንጠር ፡ ዓይንንና ፡ ጉንጭን ፡ ዳበስ ፡ ጕንተል ፡ የሚያደርግ --- ዙሪያ ፡ አካባቢው ፡ ጸጥታ ፡ የነገሠበት ፡ ታምቆ ፡ የተያዘ ፡ የሕይወት ፡ እፎይታ ፡ የሚብሰከሰክበት ፡ ነው—በዋሸንት ፡ አሸንዳ ፡ የሚፈስ ---

« ሦስት ፡ አራት ፡ ጊዜ ፡ መገናኘታችን ፡ ነው ፡ ይኸው ፡ ከተመለስሁ --- ግን ፡ እንደ ፡ ዱሮው ፡ አይደለም ፡ ሁኔታህ --- እምልህ ፡ ገሸሽ ፡ አድርጉሃል --- ሳቅህ ፡ ቀልድህ — ስድብህ ፡ እንኳ ፡ ቀርቷል » የማወቅ ፡ ፍላጐት ፡ አስተያየቷን ፡ አስቀርታ ፡ በርኅራኄና ፡ በወዳጅነት ፡ ዓይን ፡ እየተመለከተች ።

« ምን ፡ አለ ፡ አልሽው ፡ እንግዲህ — ማርጀታችን ፡ አይደለም ? --- ወዲት ፡ መሄዳችን ፡ ይመስልሻል --- የልጅነት ፡ ጠባያችን ፡ እንዲሁ ፡ ሳይታወቀን ፡ ይጠፋል ---

« ደሞ ፡ ይኸ ፡ አትይኝ ፡ ብሎ ፡ ነገርህ ፡ ከመቼ ፡ ወዲህ ፡ ያመጣኸው ፡ ነው ---

« አይ ፡ እሱ ፡ እንኳ ፡ እንዲያው -- የውስጤን ፡ የሚያይብኝ ፡ እየመሰለኝ ፡ ነው ---

«ምንቸገረህ ፡ ታዲያ ፡ አንተ ፡ ቢያየው ? ምን ፡ እስከዚህ ፡ የምታፍርበት ፡ ነገር ፡ አለብህ ? » ሳቅ ፡ እንደ ፡ ማለት ፡ ብላ « --- እዳል ፡ ለመግደል ፡ ራሳ ፡ መውረድህን ፡ እንደሁ ፡ ሰምቻለሁ ---

« አትቀልጂ ፡ እባክሽ ---

« እምልህ ፡ እዚህ ፡ ራሳ ፡ ሚሉት ፡ አገር ፡ ሰዎቹም ፡ ሆኑ ፡ እንስሶቹ ፡ የከተማ ፡ ሰውን ፡ ከሩቅ ፡ ነው ፡ አሉ ፡ የሚለዩት ፤ ይሸታቸዋል ፡ ይሉኛል ፤ አፍንጫቸው ፡ ከሩቁ ፡ ነው ፡ የሚያነሣ -- እውነት ፡ ነው ---

« እውነት ፡ ነዎይ ?! እንስሶቹማ ፡ አገርግረው ፡ ነው ፡ ገደል ፡ የሚገቡት — ገና ፡ ከሩቅ ፡ ነው ፡ ነፋሱ ፡ የሚወስድላቸው ---

« ሰዎቹስ ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ ሁኔታቸው -- እምልህ ፡ የከተማ ፡ ሰው ፡ ሲቀርባቸው --- ?

« እንገጫቸውን ፡ ወደላይ ፡ ያነሡና ፡ አፍንጫቸውን ፡ በጣቶቻቸው ፡ ጥርቅም ፡ አርገው ፡ ይይዙታል ፤ ሽታው ፡ እንዳይገባ --- እንዳንዴማ ፡

በግልጽ ፡ ትከረፈያለሽ ፡ ነው ፡ የሚሉሽ ፤ በተለይ ፡ ከነሱ ፡ ጋር ፡ ያለሽ ፡ ወዳጅነት ፡ የቆየ ፡ የሆነ ፡ እንደሁ - - - »

« እናንተስ ፡ ምን ፡ ትሏቸዋላችሁ - - - ?

« እይ ፡ እኛ ፡ ምንም ፡ አንላቸው ፤ ለምደናቸዋል »

« እሺ ፡ እኔንስ ፡ አንተ ፡ ምን ፡ ትለኛለህ ? »

« ምን ፡ እልሻለሁ ? » ድንገት ፡ ግራ ፡ ይገባዋል ።

« እኔ ፡ እከተማ ፡ ብዙ ፡ ተቀምጬ ፡ ነው ፡ የመጣሁት - - - አንተ ፡ ደግሞ ፡ ከባላገር ፡ ብዙ ፡ አልተንቀሳቀስከም - - - እንዲያውም ፡ እንደስ ማሁት ፡ ከሆነ ፡ እነዚያኑ ፡ አዳሎቼን ፡ አዳሎቹን ፡ ለመሸተት ፡ ቅቤ ፡ እየ ተቀባህ ፡ ቅቤ ፡ የተነከረ ፡ ሸርጥ ፡ እያሸረጥህ ፡ ዓዋዲ ፡ ለዓዋዲ ፡ ትዞር ፡ ነበር ፡ ብለውኛል - - - በለባ ፡ ፍሊጋ - - -

« ምነው ? እነሱን ፡ እነሱን ፡ አልኩሽ ፡ ልበል ? ማለቴ - - - » ፊቱ ፡ ድንገት ፡ ቅጭም ፡ ይላል ።

« የታባቱ ፡ አግኝቼ ፡ የነሱን ፡ ጠረን ፡ ዐውቄው ? » በፊቱ ፡ ላይ ፡ ያለ ፈውን ፡ ለውጥ ፡ አላጤነችውም ።

«ሰው ፡ መቼምኮ ፡ የራሱን ፡ ሽታ ፡ አያውቀውም - - - » ጠበን ጃውን ፡ ከትከሻው ፡ ላይ ፡ አውርዶ ፡ ሰደፉን ፡ እቀኝ ፡ ጫማው ፡ እናት ፡ ላይ ፡ ያደርግና ፡ በቀኝ ፡ እጁ ፡ በማዟዟር ፡ መሬት ፡ መሬት ፡ እያየ ፡ ትንሽ ፡ ይቆያል ።— ጂወኔ ፡ ሁኔታውን ፡ ስታይ ፤

« ጠበንጃህ ፡ በጣም ፡ ታምራለች - - - ማን ፡ ይሏታል ፡ ስሟን ? ተኩሰህባት ፡ ታውቃለህ ? » በማለት ፡ ቶሎ ፡ ርእሱን ፡ ትለውጣለች ።— እሱ ፡ ግን ፡ አይመልስላትም « - - ከሩቁ ፡ እንኳን ፡ የዚያን ፡ ያህል ፡ ሲሮጥህ ፡ ጆሮችሁን ፡ አለማደንቆሩ ፡ ይገርመኛል - - » ቀና ፡ ብሎ ፡ እን ኳን ፡ ሊያያት ፡ የፈለገ ፡ አይመስልም ።

« ያለፈው ፡ ሐሙስ ፡ ነበር ፡ ልብሴን ፡ ያሰፋሁት ፡ ደብረ ፡ ሲና ፡ ወጥቼ - - » ዓይኑን ፡ ከመሬት ፡ ሳይነቅል ፡ በኃይል ፡ ይተነፍስና ፡ መና ገር ፡ ይጀምራል ።

የወርደፉ ፡ ዋሽንት ፡ ይሽልላል - - - ይድረቀረቃል - - - የጉርም ስናን ፡ የግደለሽነትን ፡ የድፍረትን ፡ ሥራሥር ፡ እየነካካ — የሕይወትን ፡ የጥንካሬን ፡ ጅማት ፡ እየደባበሰ - - - በማስገምገም - - - በመዝለል - - -

በመጋፋት --- በመንቆርቆር --- ርስ ፡ በርስ ፡ በመንተራረስ ፡ ከሚሸፖ ጐለጐለው ፡ የድምፅ ፡ ጭፍራ ፡ ጋር ---

« አንድ ፡ ጥይት ፡ ብታስተኩሰኝ ፡ እንዴት ፡ በወደድሁህ ! » ትላለች ፡ ጺወኔ ፡ ሳታስበው ፡ አፏ ፡ ይገባና ።

« ላስተኩስሽ ? » ይላታል ፡ ጕርፉም ፤ በቅጽበት ፡ ፊቱ ፡ ፈክቶ ፡ ቀና ፡ በማለት -- በመቀጠልም « እመየቴ ፡ ታዲያ ፡ ሰው ፡ እያደርጉኝ ፡ ምን ፡ አባቴ ፡ ይበጀኛል ፡ ኋላ ፤ እንዴት ፡ ብዬ ፡ ዓይናቸውን ---

«አትወደኝም ፡ ማለት ፡ ነው ፤ ላንድ ፡ ጥይት ፡ ምክንያት ፡ ከፈለግህ» ታቋርጠዋለች ፡ ጺወኔ ፡ የፊቱ ፡ ወደ ፡ ደግ ፡ ማብራት ፡ ይገፋፋትና ።

« አልወድሽም ? አልወድሽም -- እኔ --- ! ገድሌ ፡ ይሙት ፡ እልሻለሁ ! እንኳን ፡ ላንድ ፡ ጥይት --- » ጠበንጃውን ፡ ያቀባብልና ፡ አፈ ፡ ሙዙን ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ አድርጎ ፡ ባጥሩ ፡ ላይ ፡ ተንጠራርቶ ፡ ይይዝላታል « በይ ፡ ምላጪን ፡ ወደታች ፡ ጫን ፡ በያት ! » እያለ ።

« የትኛዋ ፡ ነች ፡ ምላጪ ? » ሌባ ፡ ጣቷን ፡ እምላጪ ላይ ፡ ያደርግላታል ፤ ለመጫን ፡ ትፈራለች ።

« ጫን ፡ በያት ፡ ወደታች --- እንደሱ ፤ አይዞሽ ፡ አትፍሪ » ትንሽ ፡ ሰውነቱ ፡ ይዝናናል « ግዴለሽም ፡ ተጫኛት -- » ሞት ፡ ሽረቷን ፡ ትጫናታለች --- ቋ ፡ ብሎ ፡ ይከሽፋል ።

ደሟ ፡ ፊቷ ፡ ላይ ፡ ድንገት ፡ ጥቁር ፡ ይላል «ባዶውን ፡ ነው ፡ ለካ --!»

ቶሎ ፡ ብሎ ፡ አስፈንጥሮ ፡ በመክሸፉ ፡ ምክንያት ፡ መሆኑን ፡ ያሳያታል ። እንደገና ፡ ያቀባብልና ፡ እንድትተኩስ ፡ ያቀርብላታል ።—

« የለም ፤ በቃኝ ፤ እንዲያውም ፡ ስፈራ ፡ ስቸር ፡ ነበር --- እማየም ፡ አውሬ ፡ ነው ፡ የምትሆነው ---

« ግዴለሽም ፡ ይችን ፡ ሞክሪ --- ምነው ፡ የያዝሁት ፡ ጥይት ፡ ሁሉ ፡ ፋፍሪካ ፡ መሰለሽ ፡ እንዴ --- ?

« ለሱ ፡ ሳይሆን ፣ እኔ ፡ ብቻ ፡ በቃኝ ---

ቁልቁል ፡ ወደሚያስመሰሙው ፡ ጭለማ ፡ መለስ ፡ ብሎ ፡ ራሱ ፡ ይተኩሰዋል ። ጥይቲቱ ፡ ብልጭ ፡ ብላ ፡ እስገምግማ ፡ ትጠፋለች ። የተከተሏት ፡ የጺወኔ ፡ ዓይኖችም ፡ አብረው ፡ እንደበረሩ ፡ አይመለሱም ፤ ርቀቱ ፡ ትክታቸውን ፡ አልቀነሰውም ።—

የወርዶፋ ፡ ዋሽንት ፡ ይንሴረሴራል ፡ በረጅሙ ፡ እያፏጨ ፡ ትንፍስ ፡
ትንፍስ ፡ እያለ — እየራቀ — እየጠለቀ — እየወደቀ — እየተንሣ — እየ
ለሰለሰ - - - ሹክሹክታና ፡ ጭውውት ፡ እየመሰለ - - እንደ ፡ መንፈስ ፡
እርንት ፡ እንደፍቅር ፡ ጥልቀት ፡ የቅርብ ፡ ሩቅ ፡ እየሆነ - - እንደተዋ
ሐዶ ፡ የኑሮ ፡ ሹክሹክታ ፡ ጆሮን ፡ እየደሳሰሰ—እየራቀ - - እየራቀ - -
እየራቀ . . .

ጐርፉ ፡ ባይኑ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ በሐሳቡ ፡ በልቦናው ፡ በመላ ፡ ሰው
ነቱ ፡ ይከተላታል ጺወኔን « - - - እንዴት ፡ ቆንጆ ፡ ሆናለች ፤ እውብኝ ፡
እስቲ ፡ የፊቷን ፡ ጸዳል ፤ እነዚህን ፡ ዓይኖች ፡ እንደ ፡ ከዋክብት ፡ የሚንተ
ገተጉ ፡ እንደ ፡ ጥልቅ ፡ ጉድጓድ ፡ ውሃ ፡ የሚጐትቱ ፡ የነፍሷ ፡ ብርሃን ፡
የሚታይባቸው - - እውብኝ ፡ እስቲ - - - » ይላል ፡ በመንፈሱ ፡ ባድና
ቆት ፡ ተውጦ ።— ጺወኔ ፡ ድንገት ፡ መለስ ፡ ትልና ፡ ታይበታለች ።

« ይኸው ፡ አንተም ፡ አስተያየትህ ፡ ተለውጧል - - -

« - - - ከፊገግታዋ ፡ መልክቷን ፡ ማንበብ ፡ የሚቻል - - እንዲህ ፡
ያሉ ፡ ጥርሶች - - እንዲህ ፡ ያለ ፡ ጭንቅላት ፡ ምንኛ ፡ አቀማመጥ ፡ በተ
ደላደለ ፡ ትከሻዋ ፡ ላይ - - - ዘምበል ፡ ዘምበል ፡ ታረገዋለች ፡ ደግሞ —
እንደ ፡ አበባ ፡ ራስ — ሽታውን ፡ በየመዓዘኑ ፡ እንደሚናኝ — ሽቶ ፡ እን
ደሚተነፍስ - - -

« ናና ፡ አቶ - - ምነው ፡ ምን ፡ ሆንሃል ? ተመልከት ፡ እንዴት ፡
እንደምታየኝ » ትለዋለች ፡ ጺወኔ ፤ ጥይቲቱ ፡ የሰነጠቀችውን ፡ መሥ
መር ፡ እንዲለቁ ፡ ያልፈለገች ፡ ይመስል ፡ ዓይኖቿን ፡ ቶሎ ፡ መለስ ፡ በማ
ድረግ ።—

« - - - መውደድ ፡ የሚሉት ፡ ነገር - - - የእግዚአብሔር ፡ ትንግ
ርት - - - ወንድና ፡ ሴትን ፡ ሲሠራ - - - ምን ፡ ይሏል ፡ እስቲ - - - ልቤ ፡
ድውድውድው - - - መርገብገብ ፡ ትርትር ፡ ማለት - - - ምን ፡ ይሏል - - -
ምን ፡ ይሏል - - » ጺወኔ ፡ እንደገና ፡ አየት ፡ ታደርገውና ፡ መለስ ፡ ትላ
ለች ።—

« እይ ፡ እንደዚህ ፡ አትየኝ ፤ እፈራለሁ ።—ምነው ፡ እኔም ፡ እንዳን
ተኮ ፡ ዝም ፡ ያሰኘኛል - - - ያንጀቴን ፡ ለማወቅ ፡ ነው ፡ መሰለኝ ፡ የም
ታየኝ - - -

« ያንጀትሽን ? » ያስተጋባል ፡ የተናገረችውን ፡ ድንገት ፡ የነቃ ፡
ዓይነት ። —

« ምነው ? እኔም ፡ እንዳንተኮ ፡ ብዙ ፡ ውጥን ፡ አለኝ — የተጀመረ — ያልተጨረሰ — ብዙ ፡ ብዙ ፡ ምኞት ፡ አለኝ - - - ብዙ ፡ ለማድረግ ፡ የምፈልገው ፡ ነገር - - አዲስ ፡ አበባ ፡ ለመሄድ - - ፈረንጅ ፡ አገር ፡ ለመሄድ - - - ሙዚቃ ፡ ለመማር - - ምን ፡ ብቻ ፡ ልንገርህ - - -

«ጂ.ወኔ ! ጂ.ወኔ ! እናትሽ ፡ ይጠሩሻል » ትላለች ፡ ሮማን ፡ ተሹለክልካ ፡ መጥታ - - ጥይት ፡ ሲሮጣህ ፡ አልሰማችሁም - - - እመየቴ ፡ ተቆጥተዋል ፤ ጭሰኞቼ ፡ ብለው ፡ ብለው ፡ ደግሞ ፡ በጥይት ፡ ይጫወቱ ፡ ጀመር - - - ቆይ ፡ ግዴለም ፡ ይላሉ ። ጂ.ወኔ ፡ ጒርፋን ፡ አየት ፡ ታደርገውና ፡ ደኅናደርም ፡ ሳትል ፡ ወደናቷ ፡ እልፍኝ ፡ ትመለሳለች « - - - እንጀረውን ፡ ሰጠሃት ? » ትጠይቀዋለች ፡ ሮማን ፡ ጒርፋን ፤ እሱም ፡ ለመሄድ ፡ ዘወር ፡ ሲል - - - ምንም ፡ ሳይናገር ፡ በብሳና ፡ ቅጠል ፡ የተጠቀለለ ፡ ነገር ፡ ከኪሱ ፡ አውጥቶ ፡ ይሰጣትና ፡ መንገዱን ፡ ይቀጥላል - - - ሮማን ፡ ቅጠሉን ፡ በመገላለጥ « - - እይ ! ዱሮ ፡ ፈራርጧል - - ተበላሽቷል - - - ተበላሽቷል - - - ተበላሽቷል - - - ፈራርጧል - - - » እያለች ፡ ከዚህና ፡ ከዚያ ፡ አንዳንድ ፡ እያነሣች ፡ ወደ ፡ አፏ ፡ በመውሰድ ፡ ትመለሳለች ።

« ምነው ? እኔም ፡ እንዳንተኮ ፡ ብዙ ፡ ውጥን ፡ አለኝ — የተጀመረ — ያልተጨረሰ — ብዙ ፡ ብዙ ፡ ምኞት ፡ አለኝ - - - ብዙ ፡ ለማድረግ ፡ የምፈልገው ፡ ነገር - - አዲስ ፡ አበባ ፡ ለመሄድ - - ፈረንጅ ፡ አገር ፡ ለመሄድ - - - ሙዚቃ ፡ ለመማር - - ምን ፡ ብቻ ፡ ልንገርህ - - -

«ጂ.ወኔ ! ጂ.ወኔ ! እናትሽ ፡ ይጠሩሻል » ትላለች ፡ ሮማን ፡ ተሹለክልካ ፡ መጥታ - - ጥይት ፡ ሲጮህ ፡ አልሰማችሁም - - - እመየቴ ፡ ተቆጥተዋል ፤ ጭሰኞቹ ፡ ብለው ፡ ብለው ፡ ደግሞ ፡ በጥይት ፡ ይጫወቱ ፡ ጀመር - - - ቆይ ፡ ግዴለም ፡ ይላሉ ። ጂ.ወኔ ፡ ጐርፋን ፡ አየት ፡ ታደርገውና ፡ ደኅናደርም ፡ ሳትል ፡ ወደናቷ ፡ እልፍኝ ፡ ትመለሳለች « - - - እንጀራውን ፡ ሰጠሃት ? » ትጠይቀዋለች ፡ ሮማን ፡ ጐርፋን ፤ እሱም ፡ ለመሄድ ፡ ዘወር ፡ ሲል - - - ምንም ፡ ሳይናገር ፡ በብሳና ፡ ቅጠል ፡ የተጠቀለለ ፡ ነገር ፡ ከኪሱ ፡ አውጥቶ ፡ ይሰጣትና ፡ መንገዱን ፡ ይቀጥላል - - - ሮማን ፡ ቅጠሉን ፡ በመገላለጥ « - - እይ ! ዱሮ ፡ ፈራርጧል - - ተበላሽቷል - - - ተበላሽቷል - - - ተበላሽቷል - - - ፈራርጧል - - - » እያለች ፡ ከዚህና ፡ ከዚያ ፡ አንዳንድ ፡ እያነሣች ፡ ወደ ፡ አፏ ፡ በመውሰድ ፡ ትመለሳለች ።

« ምን ፡ ይላል ? » ይጠይቃል ፡ አንዱ ፡ ነገረተኛ ፡ ጐላ ፡ ባለ ፡ አን ደበት —

« ደሞ ፡ ራሱን ፡ የማያቅ ፡ አለ ፡ ሊል ፡ ነው » ይለጥቃል ፡ ሌላው—

« አቅሙን ፡ ዐውቆ ፡ በመኖር » ይመልሳል ፡ ሌላው —

- - - እንግዲህ ፡ እስኪ ፡ አንድ ፡ ባንድ ፡ ለመተንተን ፡ እንሞክር - - ለመ ተንተን ፡ እንድንችል ፡ ከልቡሰ ፡ ጥላ ፡ እንጀምራለን - - -

« ከጉድፍ ፡ ሴጣን ! ምን ፡ ማለቱ ፡ ነው ? » በመገረም ፡ ይጮሃል ፡ አንዱ —

- - - ልቡሰ ፡ ጥላ ፡ የምለው ፡ ከአእምሮ ፡ ክፍሎች ፡ በአነስተኛው ፡ ውስጥ ፡ የሚገኝ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ነገሮች ፡ ማየትና - - ማውጠንጠን ፡ ከጀ መርንበት ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ የሚጠራቀም - - መያዣ ፡ መጨበጫ ፡ የሌለው ፡ የሚመስል ፡ ምስቅልቅል ፡ ሁኔታ ፡ ነው - - - ምስቅልቅል ፡ ሁኔታ ፡ ነው ።— ከቤተ ፡ ሰቦቻችን ፡ ይወረሳል ። ከልዩ ፡ ልዩ ፡ መጻሕፍት ፡ ይዘራል - - -

« መጣፍማ ፡ ብንማር ፡ መቼ ፡ እንዲህ ፡ የማንም ፡ መጫወቻ ፡ እንሆን ፡ ነበር ? » በሊኖሳስ ፡ ይጀምራል ፡ አንዱ ፡ ነገረተኛ —

- - - ከልዩ ፡ ልዩ ፡ ተረቶች ፡ ሃይማኖት ፡ ነክ ፡ ከሆኑ ፡ ድርጊቶ ችና ፡ አዋልድ ፡ መጻሕፍት ፡ ይቃረማል - - -

«ዱሮም ፡ ሃይማኖትና ፡ መጣፍ ፡ አጥፊና ፡ ጠፊ ፡ ናቸው » ይለጥ ቃል ፡ ሌላው —

« - - - ከየዕለታዊ ፡ ተግባራችን ፡ ከሚጠቅመንም ፡ ሆነ ፡ ከማይ ጠቅመን ፡ ከመልካሙም ፡ ሆነ ፡ ከመጥፎው ፡ ለዓይናችን ፡ ከሚያስደስተ ንም ፡ ሆነ ፡ ከሚያስጠላን ፡ ሁሉ ፡ ወደ ፡ አእምሯችን ፡ እየገባ ፡ ይጠራ ቀማል - - -

« አንድ ፡ ዓይንህ ፡ ብታስትህ ፡ አውጥተህ ፡ ጣላት ፡ አዶለም ፡ መጣፉስ ፡ የሚለው » ያውጠነጥናል ፡ አንዱ ፡ ነገረተኛ —

« ባምሮው ፡ ያሰበም ፡ እንደሠራ ፡ ያህል ፡ ነው - - » ይለጥቃል ፡ ሌላው ።—

- - - ብዙ ፡ ጊዜ ፡ እንዴት ፡ እንደተጠራቀመ ፡ ለማወቅ ፡ ያዳግተናል - - -

« ምንሳ ! ሰው ፡ ብሎ ፡ ፍጡር - - -

- - - መጠራቀሙን ፡ ግን ፡ ሌሊት ፡ በሕልማችን ፡ ቀን ፡ በሥራ ፡ ፈትነታችን ፡ መከታነት ፡ እየመጣ ፡ ሲያስቸግረን ፡ ለመረዳት ፡ እንችላለን - - -

« ርግጥ ፡ ሥራ ፡ መፍታትስ ፡ ሚጣን ፡ ያስከትላል - -

« ቀድሞ ፡ ማደሮው ፡ መቼ ፡ አሳርፎ ፡ ቢሳካም ፡ ባይሳካም ፡ ቆላ ፡ ደጋ ፡ መሮጥ ፡ ነዪ - - -

- - - አእምሯችን ፡ ጮርቃ ፡ በነበረበት ፡ ጊዜ ፡ ቤተ ፡ ሰቦቻችን ፡ ያደነቁትን ፡ በማድነቅ ፡ ያከበሩትን ፡ በማክበር ፡ ያመሰገኑትን ፡ በማመስገን ፡ ይዘራል - - -

« መቼም ፡ ዘር ፡ መዝራት ፡ ለፍሬ ፡ ነውና ፡ እንዲያፈራ ፡ ማረምና ፡ መጠበቅ ፡ ያስፈልጋል - -

- - -የጠሉትን ፡ በመጥላት ፡ የነቀፉትን ፡ በመንቀፍ ፡ ያንጓለሉትን ፡ በማንጓለል ፡ ያለመልማል ። በነሱ ፡ እምነት ፡ የኛ ፡ እምነት ፡ በነሱ ፡ ትዕግሥት ፡ የኛ ፡ ትዕግሥት ፡ በነሱ ፡ ቸርነት ፡ የኛ ፡ ቸርነት ፡ ያብባል ። አንዳንድ ፡ የማያስፈልጉ ፡ ነገሮች ፡ አብረው ፡ ቢያድጉም ፡ እንኳ ፡ እንደ ቤተ ፡ ሰቦቻችን ፡ መታረም ፡ የኛም ፡ እየታረሙ ፡ ይሄዳሉ - - -

« እዚህ ፡ ላይ ፡ በጊዜ ፡ መዝራትንና ፡ በጊዜ ፡ ማረምንም ፡ ቢጨምሩ ፡ አይከፋ - - ምክንያቱም ፡ አለጊዜው - - - አሁን ፡ ለምሳሌ ፡ የኔ ፡ ባለቤት ፡ የከሰሰችኝ - - -

- - -ቆይ ፡ ቆይ ፡ አላስጨረስከኝምኮ ? እና ፡ የኛም ፡ ይታረማል ፡ ፍሬነት ፡ ይደርሳል ። በቤተ ፡ ሰብ ፡ ዓይን ፡ ጀግና ፡ ሠራተኛ ፡ ቆንጆ ፡ ባለሞያ ፡ የተማረች ፡ የምትባል ፡ ሚስት ፡ በልጅም ፡ ዓይን ፡ እንደዚሁ ፡ የተመሳሰለ ፡ ሚዛን ፡ ይዛ ፡ ታድጋለች ። የልጅ ፡ አእምሮ ፡ በቤተ ፡ ሰቡ ፡ አእምሮ ፡ ትይዩና ፡ መሰልነት ፡ ይበለጽጋል - - -

«የዛሬ ፡ ልጅ ፡ መቼ ፡ በጄ ፡ ብሎ ፡ በናት ፡ አባቱ ፡ እግር ፡ ይተካና --» ይላሉ ፡ ከዕድሚያቸው ፡ ገፋ ፡ ያሉ ፡ አዛውንት ።

- - - በተጨማሪ ፡ ሽማግሌዎችና ፡ መጻሕፍት ፡ ዐዋቆች ፡ ከሚናገሯቸው ፡ ተረቶችና ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ታሪኮች ፡ የሶምሶንና ፡ የደሊላ ፡ ታሪክ ፡ የቅዱስ ፡ ጊዮርጊስ ፡ የብሩታዊትና ፡ የዘንዶው ፡ አዋልድ - - -

« ብሩታዊትን ፡ ከዘንዶ ፡ አፍ ፡ ያወጣው ፡ አምላክ ፡ ያውቃል » ይላል ፡ በግረ ፡ ሙቅ ፡ የታሠረው ፡ እሥረኛ ።

--- ሌሎችም ፡ እነዚህን ፡ የመሳሰሉ ፡ ሁሉ ፡ በአእምሮው ፡ ውስጥ ፡ ይቀረጹበታል - - -

« ርግጥ ፡ ነው ፡ ልብ ፡ ላረገው - - - » ይላሉ ፡ አንድ ፡ ጠና ፡ ያሉ ፡ ሴትዮ

- - - ቀስ ፡ በቀስም ፡ በአእምሮው ፡ ውስጥ ፡ እንደሚመላለሰው ፡ ጀግና ፡ ለመሆን ፡ በአእምሮው ፡ ውስጥ ፡ ዝናዋን ፡ እንደሚያስተጋባው ፡ ሴት ፡ ዓይነት ፡ ለማግኘት ፡ ይፈልጋል ። ይህ ፡ እንግዲህ ፡ የሚሆነው ፡ ጊዜውና ፡ ሁኔታው ፡ ያልተለዋወጠ ፡ እንደሆን ፡ ነው - - - በታሪክ ፡ ከተ ያያዘ ፡ ዘመን ፡ ከእናት ፡ ካባት ፡ ቀዬ ፡ ሳይወጡ ፡ የቆዩ ፡ እንደሆነ ፡ ነው---

« የናት ፡ ያባትን ፡ ቀዬ ፡ የሚያህል ፡ የለም ! የስንቱ ፡ ዘመዶቻችን ፡ አጥንታቸው ፡ የተከሰከሰበት ፡ ደማቸው ፡ የፈሰሰበት - - ለዚሁ ፡ ብዬ ፡ ነው ፡ እኔም ፡ ሽንጤን ፡ ገትሬ ፡ በየፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የምዞረው ፤ የዘር ፡ መቁ ጠሪያዬን ፡ ያባቴን ፡ እርስት ፡ አላስወስድም ፡ በማለት - - እግዚአብ ሔር ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ያድርጋቸውና ፡ ያንተ ፡ አጐት ፡ ካዩት ፡ ዘንዳ ፡ ብርረ ታም ፡ ብረታ ፡ ተደስቼ ፡ ነው ፡ አገሬ ፡ የምገባው ፡— እየፎከርሁ ! እየሸ ለልሁ ! ዳኛ ፡ አይቻለሁ ፡ እሳቸው ፡ ዘንድ ፡ የሚደርስ ፡ የለም ! ያ ፡ የሚ ያስገመግም ፡ ድምፃቸው ፡ ፍርድ ፡ ለመስጠት ፡ ሲምቦለቦል ፡ እግዚአብ ሔር ፡ እንጂ ፡ ሰው ፡ የተናገረ ፡ አይመስልም ። ረጂም ፡ ዕድሜ ፡ ይስጣቸው !

« ስማ ፡ ስማ ፡ አደፍርስ — አላየሽኝም ፡ መሰለኝ ፡ ሳዳምጥህ ፡ ነበርኮ - -

- - - በላይ ! አላየሁህም ፤ ምን ፡ እባክህ ፡ በሙሉ ፡ በምናገረው ፡ ተውጩ ፡ ዓይኔ ፡ ከሰው ፡ ሰው ፡ ይለፍ ፡ እንጂ ፡ አረጋግጦ ፡ አይመለከ ትም ።— እህሳ ፡ ምን ፡ ይመስልሃል ፤ ይኽ ፡ የምተነትንላቸው ፡ ያኗኗር ፡ ዘዴ ? ችግሩን ፡ ከሥሩ ፡ የመታሁት ፡ አይመስልህም ? ብዙዎቹ ፡ የተከታ ተሉት ፡ ይመስለኛል ፤ በተለይ ፡ ባስተያየታቸውና ፡ ባለመንቀሳቀሳቸው ፡ ስመለከተው ።— አንዳንዶቹ ፡ ግን ፡ ይገርምሃል — ጭራሽ ፡ የምለውን ፡ ፈጽሞ ፡ አይሰሙኝም ፤ ደንቆሮ ፡ ናቸው ፡ ወይም ፡ አይገባቸውም ፡— እኔ ፡ ስለ ፡ ግብርና ፡ ሳወራ ፡ እነሱ ፡ የሚያወሩት ፡ ስለብሩታይት ፡ ነው - - -

«ምን ፡ አለፋህ ፡ ብቻ ፡ ላቦትህን ፡ ነው ፡ የጨረስከው ።—እነሱ ፡ አፍ ፡ አፍክን ፡ የሚያዩት ፡ ለምትናገረው ፡ ነገር ፡ ጓጉተው ፡ ሳይሆን ፡ ከመቼ ፡ የሚናገረውን ፡ ጨርሶ ፡ ከመቼ ፡ ብሶታችንን ፡ እጫውተነው ፡ እማልዶን ፡ ብለው ፡ ሲጠባበቁ ፡ ነው ። ከተናገርከው ፡ እንኳን ፡ ለነሱ ፡ ለኔም ፡ ብዙ ፡

ያልገባኝ ፡ ነገር ፡ አለ - - እምልህ ፡ ባንተ ፡ አስተያየት ፡ ይኸ ፡ ልቡስ ፡ ጥላ ፡ የምትለው ፡ ነገር ፡ ከኖሩበት ፡ ቀዬ ፡ ካልለቀቁ ፡ በስተቀር ፡ መጻሕፍት ፡ በማንበብ ፡ ሌሎች ፡ አገሮችን ፡ ከሚያውቁ ፡ ሰዎች ፡ ጋር ፡ ሐሳብ ፡ ለሐ ሳብ ፡ በመለዋወጥ ፡ እያደገና ፡ አስተያየትን ፡ እየለወጠው ፡ አይሄድም ፡ ነው ፡ የምትለው - - ? አይመስለኝም ፤ በኔ ፡ አስተያየት ፡ በእንደዚህ ፡ ዓይነት ፡ መንገድ ፡ የሚያድገው ፡ ልቡስ ፡ ጥላ ፡ አለቅጥ ፡ ይመጥቅና ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ተመሳሳይ ፡ ስለማይኖረው ፡ ሰውዬውን ፡ ወይም ፡ ሴትዮይቱን ፡ አቻ ፡ አሳጥቶ ፡ በብስጭት ፡ ያኖራቸዋል ፡ ነው ፡ የምለው - - - በነገራችን ፡ ላይ ፡ ጋሼ ፡ ክብረት ፡ ይፈልግሃል ፤ አንተንና ፡ እኔን ፡ ሊሥለን ፡ ይፈልጋል ፤ ከፍሬዋ ፡ ጋር - - -

« ጥሩ ፡ ነው ፡ እንሂድ » ዙሪያውን ፡ ወደ ፡ ነገረተኞቹ ፡ አየት ፡ በማ ድረግ « - - በሉ ፡ እንግዲህ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይቅናችሁ ፤ ሐሳቤን ፡ ባልጨር ስላችሁም ፡ ዋና ፡ ዋናውን ፡ ጐረፍ ፡ ጐረፍ ፡ አድርጌላችኋለሁ - - - ደህና ፡ ሁኑ - - -

« ትንሽ ፡ ጉዳይ ፡ ነበረኝ ፡ ጌታዬ ፡ የሚያቻኩል ፤ እዚህ ፡ ከኛ ፡ ጋር ፡ ያጠፉትን ፡ ጊዜ ፡ ሩቡን ፡ እንኳ ፡ አልወሰድብዎትም - - ቁም ፡ ነገር ፡ ነው ፡ ብዬ ፡ ነው ፡ ጌታዬ ፡ የማስቸግርዎት - - » ይለዋል ፡ አንዱ ፡ ነገረ ተኛ ፡ ከተል ፡ ይልና ።

« አዬ ፡ አሁን ፡ ጊዜ ፡ የለኝም ፤ ባይሆን ፡ ነገም ፡ እዚሁ ፡ ትገኝ ፡ እንደሁ ፡ ነገ ፡ ይሻላል - - -

« ነገማ ፡ ቀጠሮዬ ፡ ነው ፡ ጌታዬ ! ቀጠሮው ፡ ካለፈ ፡ ምን ፡ ይበጀ ኛል ። እባክዎ ፡ ስለእግዚአብሔር ፡ ብለው ፡ ያነጋግሩኝ - - ባላጋራዬ ፡ ሀብታም ፡ ሰው ፡ ነው ፡ ደግሞ ፡ ምክንያቱን ፡ አላውቅም ፡ ይኸው ፡ ካገር ፡ ቤት ፡ ከመጣ ፡ አምስት ፡ ቀን ፡ አልፎታል ፤ ርስዎ ፡ አጐት ፡ ዙሪያ ፡ ያኮ በኩባል - - -

« እኔ ፡ ትምህርቴ ፡ ችግርን ፡ ከሥሩ ፡ ስለ ፡ መቋቋምና ፡ መፍትሔ ፡ ስለ ፡ ማግኘት ፡ ነው ፡ የኔ ፡ ወንድም - - ደግሞስ ፡ ስታስበው ፡ ሞትና ፡ ሕይወት ፡ ድንቁርናና ፡ ዕውቀት ! ለየትኛው ፡ ነገር ፡ ብለህ ፡ ትቸገራለህ ? - - - አዎ - - መቸገር ፡ አያሻም - - - እና - - ስለዚህ ፡ ስለ ፡ ግል ፡ ጉዳይህ ፡ ብዙ ፡ አታስብ ፡ አትደንግጥለት - - - እውነት ፡ ካለህ ፡ እው ነቱ ፡ ያወጣሃል - - -

« እውነቱ ! እውነቱ ! እውነቱ ፡ የቱ ፡ ነው ፡ ጌታዬ ? እውነቱን ፡ የሚ ያገኘው ፡ የቀደመ ፡ ነው - - እውነቱን ፡ የሚያገኘው ፡ ጊዜ ፡ የሰጠው ፡ ሀብት ያለው ፤ አባባሉን ፡ የሚያውቅበት ፡ ነው ፡ ጌታዬ - -

« ታዲያ ፡ ጠበቃ ፡ ግዛ ! እኔ ፡ እንደሆንሁ ፡ ምናልባት ፡ እንደምታ ውቀው ፡ ተማሪ ፡ ነኝ - - ጠበቃ ፡ አልሆንህ ፤ ወይ ፡ በገንዘብ ፡ አልረዳህ - - -

« መቼስ ፡ ምን ፡ አደርጋለሁ ፡ መስሎ ፡ ካልታየዎት ፡ ካልመሰለዎት ፡ አፌን ፡ ባላጠፋ ፡ ይሻላል - - » ድንገት ፡ ዘወር ፡ ይልና ፡ በኀይል ፡ እየተ ራመደ ፡ ወደ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ይመለሳል ። — አደፍርስና ፡ በላይ ፡ ለጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ሳይነጋገሩ ፡ መንገዳቸውን ፡ ይቀጥላሉ ።-

« ቅድም ፡ የጠየቅሁህንኮ ፡ አልመለስክልኝም ፤ እንዴት ፡ ነው ፡ መጻሕፍት ፡ ስታነብና ፡ ብዙ ፡ የኑሮ ፡ ልምምድ ፡ ያላቸውን ፡ (ግብር ፡ የገቡ) ሰዎች ፡ ስትሰማ ፡ ስለብዙ ፡ ነገሮች ፡ ስታውቅ ፡ ልቡስ ፡ ጥላህ ፡ አይለዋ ወጥሞይ ? ለመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ በባላገር ፡ ሳለህ ፡ በባላገር ፡ የነበረችህን ፡ ልብስተ ፡ ጥላ ፡ የምትመስል ፡ ልጅ ፡ ብታገባ ፡ እከተማ ፡ መጥተህ ፡ ልቡስ ፡ ጥላህ ፡ ሲያድግ ፡ ባርጌዋ ፡ ልብስተ ፡ ጥላ ፡ አምሳል ፡ ያገባሃት ፡ አታስጠላ ህሞይ ? አትፈታትሞይ ? ወይም ፡ እሷ ፡ በበኩሏ ፡ አትፈታህም ፡ አትጠላ ህሞይ - - - ?

« በመሠረቱ ፡ መቼም ፡ እነዚህን ፡ ሁሉ ፡ ጥያቄዎች ፡ አስቤባቸዋለሁ ። ልቡስ ፡ ጥላ ፡ ሊያድግ ፡ ይችላል ። መጀመሪያ ፡ እንደተነጋገርነው ፡ ከቤተ ፡ ሰብ ፡ ጋር ፡ አብሮ ፡ በመኖር ፡ ያድጋል ። ከዚያም ፡ ሌላ ፡ ተረትና ፡ ታሪ ኮችን ፡ አዘውትሮ ፡ በመስማት ፡ መጻሕፍትን ፡ አዘውትሮ ፡ በማንበብ ፡ አዘውትሮ ፡ በማሰላሰል ፡ ሊያድግ ፡ ይችላል ። ነገር ፡ ግን ፡ እነዚህ ፡ ሁሉ ፡ ተዋሕደው ፡ በሰውነቱ ፡ ካልሰረጹበት ፡ የሚያመጡበት ፡ ለውጥ ፡ አይታ ወቀውም - - - -

« በሰውነቱ ፡ መዋሐድ ፡ አለመዋሐዳቸውን ፡ እንዴት ፡ ሊያውቅ ፡ ይችላል - - - ?

- - - የልቡስ ፡ ጥላውን ፡ ውጋጋን ፡ የሚያሳዩ ፡ ሁኔታዎች ፡ ሲገጥሙት ፡ ስሜት ፡ ሳይሰጡት ፡ በመቅረታቸው ፡ ነዋ ! - - ለምሳሌ ፡ ኀሊናን ፡ የሚያነቁ ፡ ሁኔታዎችን ፡ ባህላዊ ፡ ሙዚቃን ፡ ቀረርቶና ፡ ፉከራ ፡ የመሳሰ ሉትን ፡ ሲሰማ ፡ ልቡስ ፡ ጥላ ፡ ጀግናው ፡ ትዝ ፡ ካላለው ፡ የፍቅር ፡ እን ጉርጉሮ ፡ ሲሰማ ፡ ልብስተ ፡ ጥላ ፡ ፍቅሩ ፡ ትዝ ፡ ካላለችው ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ሥዕሎች ፡ ላይ ፡ የነሱን ፡ ሕይወት ፡ ሲንቀሳቀስ ፡ ካልያዘው - - - በውኑ ፡

እያንጉ ፡ በህልሙ ፡ ካልመጡበት ፡ በርግጥ ፡ ተዋሕዶውኛል ፡ ሊል ፡ አይ ችልም ። በርግጥ ፡ ተዋሕደውት ፡ እንደሆን ፡ ግን ፡ በየዕለቱ ፡ ለሚገጥመው ፡ ለዙሪያ ፡ አካባቢው ፡ የሚኖረው ፡ ፍቅር ፡ እየተቀነሰ ፡ ለልቡሰ ፡ ጥላው ፡ ያለው ፡ ግን ፡ እያደገ ፡ እየበለጸገ ፡ ይሄዳል ። እንዲያውም ፡ አንዳንዴ ፡ ከሰዎች ፡ ተገልሎ ፡ መኖርን ፡ ይመርጣል ፤ ልቡሰ ፡ ጥላው ፡ በሚያስመለ ክተው ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ሁኔታና ፡ ቅርጺ ፡ ቅርጽ ፡ እየተደሰተ ።- ከአእምሮው ፡ የሚመነጩት ፡ እነዚህ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ነገሮች ፡ ለልቡ ፡ ደስታ ፡ ይሰጡታል ።- ዓይኑ ፡ ይበራል ። የደሙ ፡ ገንዳ ፡ የስሜቱ ፡ መስኖ ፡ ወደ ፡ ልቡሰ ፡ ጥላው ፡ ይከተራል ። ለሰብአዊ ፡ ፍጡር ፡ ያለው ፡ ስሜቱ ፡ በውስጡ ፡ ተውጦ ፡ ይቀራል ። ልቡሰ ፡ ጥላውም ፡ በዓይን ፡ ታይቶ ፡ ልኩ ፡ ዓይነቱ ፡ ቦታ ፡ አያ ያዙ ፡ ወሰኑ ፡ የማይታወቅ—ሽንጥ ፡ ዳሌ ፡ ክብር ፡ ግርማ ፡ ሞገስ ፡ ኀይል ፡ ገናናነት ፡ በሚል ፡ ጌጣጌጥ ፡ ይክበሰበሳል ። ጥቅሙና ፡ ወሰኑ ፡ የማይገ መት ፡ ይሆናል ። በሰዎች ፡ ላይ ፡ ሲፈልገው ፡ ያጣዋል ። ራሱ ፡ ላይ ፡ ምስቅልቅል ፡ ትርኢት ፡ ይሆንበታል ። በሕልም ፡ ሩጫ ፡ እያኳተነ ፡ በማ ስጐምዠት ፡ ወላንሳ ፡ አስቀምጦ ፡ ከማትገኝ ፡ ሚስት ፡ አጋብቶ ፡ ከሌለ ፡ ፍቅር ፡ አፋቅሮ ፡ የማይደረስበት ፡ ክብርና ፡ ኀይል ፡ ሰጥቶ ፡ ከሚኖርበት ፡ ዓለም ፡ ውጭ ፡ የሚኖር ፡ ሰንኳላ ፡ ፍጡር ፡ ያደርገዋል ። እንደዚህ ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ ዕድሜ ፡ ልኩን ፡ ሳያገባ ፡ ይኖራል ። — ከሌላው ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፡ ሌላው ፡ ዓይነት ፡ ሰው ፡ በልቡሰ ፡ ጥላው ፡ የተጠራቀመውን ፡ ምስቅል ቅል ፡ ትርኢት ፡ በግዙፋዊ ፡ ሁኔታ ፡ ለመያዝ ፡ ይፈልጋል ። በሩቅም ፡ መንገድ ፡ ቢሆን ፡ ልቡሰ ፡ ጥላውን ፡ የሚመስል ፡ ሰብአዊ ፡ ፍጡር ፡ ሰብ አዊ ፡ ሁኔታ ፡ ለማግኘት ፡ ይሞክራል ። ለኑሮ ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ የታመነበትን ፡ የጋብቻ ፡ ድንጋጌ ፡ በግዳጅ ፡ ሳይሆን ፡ በሙሉ ፡ ፈቃድና ፡ እምነት ፡ ይቀበላል ። ከጊዜ ፡ ብዛትም ፡ እምኖበት ፡ የተቀበለው ፡ አፍአ ዊው ፡ እውነታ ፡ ውስጣዊውን ፡ ምስል ፡ ያስለቅቀዋል ፤ ማለት ፡ ልቡሰ ፡ ጥላው ፡ የነበረው ፡ በግዙፋዊ ፡ ነገር ፡ ለምሳሌ ፡ በሚስት ፡ ይለወጣል ፡— በግዙፋዊነት ፡ የነበረው ፡ ደግሞ ፡ የማይደረስበት ፡ መስሎ ፡ በነበረው ፡ በል ቡሰ ፡ ጥላው ፡ ይተካል ፤ አንዱን ፡ ከሌላው ፡ መለየት ፡ ያዳግታል ። ውጫ ዊው ፡ ውስጣዊ ፡ ውስጣዊው ፡ ውጫዊ ፡ ሆኑ ፡ ማለት ፡ ነው ። ለዚህ ፡ ነው ፡ በነገራችን ፡ ላይ ፡ ቤተክርስቲያን ፡ ሰዎች ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ባልና ፡ ሚስት ፡ ሲሆኑ ፡ አንድ ፡ አካል ፡ አንድ ፡ አምሳል ፡ ሆኑ ፡ ብላ ፡ የምትለፈው ። እውስጡ (ልብስተ ፡ ጥላው ፡) የነበረችው ፡ እውጭ (ሚስቱ ፡ ሆና ) ብትወጣም - - - እውጭ ፡ የነበረችው ፡ እውስጡ ፡ ገብታለች ፡ ማለት ፡ ነው ፤ አንድ ፡ አካል ፡ አንድ ፡ አምሳል - - -

« እውነቱን ፡ ለመናገር ፡ የተናገርከው ፡ ሁሉ ፡ ደስ ፡ ይላል ፤ ግን ፡ መቼም፡ ትንሽ ፡ ለኔ፡ ረቀቅ ፡ ብሎብኛል --አዎ ፡ ርግጥ ፡ ነው ፡ ተምሪያለሁ— በመማር ፡ ላይ ፡ ነኝ ፤ እምልህ ፡ አሥራሁለተኛ ፡ ክፍል ፡ ደርሻለሁ - - ሆኖም ፡ ያልከው ፡ ሁሉ ፡ አልገባኝም - -እና ፡ አሁን ፡ ይልቅ ፡ ጋሼ ፡ ክብ ረት ፡ እኛ ፡ ግቢ ፡ ውስጥ ፡ ሳይጠብቀን ፡ ስለማይቀር ፡ እንግባና ፡ ሥዕሉን ፡ እንነሣ - - -

## ፲

# አደፍርስ

እነበላይ ፡ ቤት ፡ ግቢ ፡ ደርሰው ፡ በሩን ፡ ከፍተው ፡ ሲገቡ ፡ አንድ ፡ ትልቅ ፡ ወሠራ ፡ አውራ ፡ ዶሮ ፡ ካጥር ፡ ላይ ፡ ወደ ፡ መሬት ፡ ዘሎ ፡ ይኮኩላል ። ወዲያውም ፡ በረት ፡ ውስጥ ፡ ትለቅም ፡ እነበረች ፡ ሴት ፡ ዶሮ ፡ ዙሪያ ፡ ማንኮራፋት ፡ ይጀምራል - - ከቀኝም ፡ ከግራም ፡ አንኮራፍቶ ፡ ለሽ ፡ ለሽ ፡ ማለቷን ፡ ሲያይ ፡ አንገቷን ፡ ዘሎ ፡ ይነክስና ፡ ለልም ፡ ታህል ፡ ጊዜ ፡ ላዋ ፡ ላይ ፡ ኮርፈፍ ፡ ብሎ ፡ ይወርድላታል ።- ቡናኝ ፡ የበተነባት ፡ ይመስል ፡ እንደወረደላት ፡ እሷም ፡ በተራዋ ፡ ላባዎቿን ፡ አንኮራፍታ ፡ ታራግፍና ፡ ለቀማዋን ፡ ትጀምራለች ።- አውራው ፡ በመገረም ፡ ዓይነት ፡ እየኮኮለ ፡ የሚለቃቀም ፡ ነገር ፡ ለማግኘት ፡ እየጠቋቆመ ፡ ይሄዳል ።- አንድ ፍሬ ፡ እንደያዘ ፡ ወደ ፡ ግራ ፡ ወደ ፡ ቀኝ ፡ መልከት ፡ መልከት ፡ ይላል ፡— ሌላ ፡ ሴት ፡ ዶሮ ፡ ባቅራቢያው ፡ ያያል - - ይጋብዛታል ፡ በመስቆሩ ፡ እያነሣ ፡ እየጣለ - - ስትፈራ ፡ ስትቸር ፡ ስትጠጋው ፡ ፍሬውን ፡ ይለቅላትና ፡ ትንሽ ፡ ራቅ ፡ ብሎ ፡ ደግሞ ፡ ሌላ ፡ ፍሬ ፡ ይፈልጋል - - - ያገኛል - - - እንደገና ፡ ይጠራታል - - - አንዴ ፡ ሁለቴ ፡ ያንኮራፋል - - - ይኮኩላል - - ይንደረደራል - - ዶሮይቱም ፡ ቡናኟን ፡ ታራግፋለች ።

አቶ ፡ ክብረት ፡ እበረንዳ ፡ በወምበር ፡ ላይ ፡ ተቀምጦ ፡ ፀሐውን ፡ ይመለከካል ። ዓይኑ ፡ የዶሮቹን ፡ ሁኔታ ፡ የሚመለከት ፡ ይመስላል ፡ «እንዴት ፡ ያለ ‘ኩርብ’ ይመስልሃል ፡ ያ ፡ አውራ ፡ ዶሮ ፡ የሠራው - - » ይጀምራል ፡ ክብረት ፡ ግምባሩን ፡ ኮስተር ፡ ራሱን ፡ ነቅነቅ ፡ አድርጐ ፡ እነበላይን ፡ እንዳያቸው ፡ ቶሎ ፡ ብድግ ፡ በማለት « - - እንዴት ፡ ያለ ‘ ኩርብ ’ ይመስላችኋል ፡ ያ ፡ አውራ ፡ ዶሮ ፡ የሠራው - - ካረፈ ፡ ወዲያ ፡ ደግሞ ፡ ያሳየው ፡ ንቅናቄ ‘ሙቭማው’ የተከተለው ፡ መሥመር ፡ ደሞ ‘ሊኙ’ እንዴት ፡ ያለ ፡ የማያደናግር ፡ ቀጥታ ፡ ነው ፡—ወደ ፡ ዋናው ፡ ትርኢት ፡ ወደ ፡ መልዕክቱ ፡ የሚመራ ! በክንፎቹ ፡ ውዝዋዜ ፡ ጊዜ ፡ ደግሞ ፡ ያሳየው ፡ የቀለም ፡ ትርግርግታ ‘ አርሞኒው ’ እንዴት ፡ ይመስላችኋል - - ከተገኑ ፡ ጋር ፡ አዋሐዱ ‘ ኮንትራስቱ ’ ፡ አስተራረፉ ፡ ‘ፔርስፔክቲቩ’ እንዴት ፡ ይመስላችኋል - - ካለመኖር ፡ ወደ ፡ መኖር ፡

ከጨለማ ፡ ወደ ፡ ብርሃን ፡ እንደሚመጣ ፡ ዓይነት ፤ ከኋላው ፡ አጥር ፡ ወደ ፡ ፊቱ ፡ ሜዳ --- ሕይወት ፡ ነፃነት ፡ ዘለዓለማዊነት ፡ ወሰን ፡ የለሽነት ---

« ወንድን ፡ ሲፈጥረው ፡ እጁን ፡ ታጥቦ ፡ ነው ፡ እግዚአብሔር -- » ይጀምራል ፡ በላይ

« ሴትን ፡ በፈጠረ ፡ ጊዜ ፡ እጁን ፡ ያቆሸሸው ፡ ነገር ፡ ባይኖር ፡ ይሆናል ፡ እሱስ --- እምልሀ -- » ያቋርጠዋል ፡ አደፍርስ ፡ ንግግሩን

« ቅድምኮ ፡ ስለ ፡ ባልና ፡ ሚስት ፡ የተፈላሰፍከው ፡ ብዙ ፡ ሳይቆይ ፡ እዚሁ ፡ ፋርሽ ፡ ሆነ ፡— ተመልከተሃል ፡ ያ ፡ አውራ ፡ ምን ፡ እንዳደረገ ፤ መጀመሪያ ፡ ዛጐልማዋን ፡ ዶሮ ፡ ነበር ፡ የወደደው -- ወዲያው ፡ ግን ፡ ፍቅሩ ፡ አልቆለት ፡ ወደ ፡ ገብስማዋ ፡ ሄደ — ባጭሩ ፡ ብቻ ፡ እንደንብ ፡ ማለት ፡ ነው ፤ ካንዱ ፡ አበባ ፡ ወደ ፡ ሌላው ---

--- አልስማማም ፡ በላይ ! አልስማማም ! ሰውና ፡ ዶሮ ፡ አንድ ፡ አይደሉም -- ሰው ፡ ውጫዊ ፡ ብቻ ፡ አይደለም ፤ ውስጣዊም ፡ ጭምር ፡ ነው -- ስብእዊ ፡ ሰውነቱን ፡ ከልቡሰ ፡ ጥላው ፡ ማስማማት ፡ ይኖርበታል ።— ለመሆኑ ፡ ማነው ፡ ልቡሰ ፡ ጥላውን ፡ የማያፈቅር ? ልቡሰ ፡ ጥላውስ ፡ ያስመለከተውን ፡ ለመፈጸም ፡ የማይጥር ? ሰው ፡ በተፈጥሮው ፡ ራሱን ፡ ወዳድ ፡ ስለሆነ ፡ በዓይነ ፡ ኅሊናው ፡ እውነት ፡ መስሎ ፡ የሚታየውን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ከተፈጥሮ ፡ ጓደኛው ፡ ጋር ፡ ሲገናኝ ፡ ሐሰት ፡ መሆኑን ፡ እንኳን ፡ ቢገነዘበውም ፡ ልቡሰ ፡ ጥላው ፡ ለዘራበት ፡ አስተያየቱ ፡ ያለው ፡ እምነት ፡ የማያቋርጥና ፡ የማይዛባ ፡ ነው ። በዚህም ፡ ምክንያት ፡ ልቡሰ ፡ ጥላው ፡ ያመለከተው ፡ ሁሉ ፤ በዓይኑ ፡ ከሚያየው ፡ ተመሳሳይ ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ በልጦ ፡ ያገኘዋል ---

አቶ ፡ ክብረት ፡ መጣያ ፡ ሸራውንና ፡ ቡርሽ ፡ ቀለሞቹን ፡ አውጥቶ ፡ የመጀመሪያውን ፡ ንድፍ ፡ ይነታትባል ።—

«እንዴት ፡ ነው ፡ ጋሼ ፡ ክብረት ሳንዘገጃጅ ፡ ማንጣት ፡ ጀመርህ ---

« ሳንዘገጃጅ ? ! ትቀልዳለህ ፡ በላይ -- ከዚህ ፡ በላይ ፡ ዝግጅት ፡ የለም ።— ቀጥሉ ፡ ክርክራችሁን -- ይታወቅ ፡ የዘመኑ ፡ ወጣት ፡ በናንተ ፡ ውስጣዊ ፡ ግመት -- በስሜት ፡ ተምቦልቦሉ ! የምነት ፡ አገቸሬነታችሁ ፡ በፊታችሁ ፡ ይነበብ ---

--- እዚህ ፡ ላይ ፡ አንድ ፡ ልናስታውሰው ፡ የሚገባን ፡ መሰላል ፡ የሚሆን ፡ አስተያየት ፡ አለ ፤ ማለት ፡ ምንም ፡ ዓይነት ፡ ጥረት ፡ መፍጨርጨርና ፡ ድካም ፡ ልቡሰ ፡ ጥላችን ፡ ያመለከተንን ፡ በሙሉ ፡ ልንደርስበት ፡

አለመቻላችንን ፡ ነው ። ልቡስ ፡ ጥላችንን ፡ መሰል ፡ ማንኛውም ፡ ድር ጊት ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ በከፊል ፡ እንጂ ፡ ተሟልቶ ፡ ልናገኘው ፡ አንችልም ። ነገር ፡ ግን ፡ ተመሳሳይ ፡ መስሎ ፡ የምናገኘውን ፡ አትኩረን ፡ ብንመረም ረው ፡ ምድራዊ ፡ ኑሮ ፡ እንደሚፈቅድልን ፡ መጠን ፡ በቂያችን ፡ ሳይሆን ፡ አይቀርም ። ለማስረጃ ፡ ያህል ፡ ባሁኑ ፡ ጊዜ ፡ ውጤቱ ፡ አጥጋቢ ፡ መስሎ ፡ ያልተገኘውን ፡ የጋብቻን ፡ ሁኔታ ፡ እንመልከት ። ብዙ ፡ ጊዜ ፡ እንደሚነ ፍሰው ፡ ተጽፎም ፡ እንዳነበብኩት ፡ ሚስት ፡ ከየት ፡ እናምጣ ? በተለይማ ፡ የተማረች ፡ ሴት ፡ ሚስት ፡ አትሆንም ፤ እሠራለሁ ፡ ትሠራለህ ፡ ተምሬያ ለሁ ፡ ተምረሃል ፡ ሀብት ፡ አለህ ፡ ሀብት ፡ አለኝ ፡ እያለች ፡ ጋብቻን ፡ መልክ ፡ ታሳጣዋለች - - ወንዱም ፡ እንዲሁ ፡ ካሥሯ ፡ ጋር ፡ ዳንኪራ ፡ ሲረግጥ ፡ ትዳርን ፡ አያስበውም ፡ በሚል ፡ አኳኋን ፡ የተውተፈተፈ—እውነትን ፡ በሙሉ ፡ ያልጨበጠ ፡ ውሸትም ፡ በሙሉ ፡ ያልነገሠበት ፡ ያምባ ፡ ገነን ፡ ንግግር ፡ እሰማለሁ ። እንደኔ ፡ አስተያየት ፡ ግን ፡ የተማረችም ፡ ሆነች ፡ ያል ተማረች ፡ እንደደረጃቸው ፡ የሞቀ ፡ የደመቀ ፡ ትዳር ፡ ለመቀለስ ፡ ይችላሉ ። ወንድም ፡ የምትሆነውን ፡ ካገኝ ፡ ቅድም ፡ አንተ ፡ እንዳልከው ፡ ሳይሆን ፡ ማለቴ ፡ አበባ ፡ እንደምትቀስም ፡ ንብ ፡ አሥሯን ፡ መቅመሱ ፡ ይቀርና ፡ በአንድ ፡ ሴት ፡ ይወሰናል ። ደምወዙን ፡ በውጪ ፡ ጨርሶ ፡ ሚስቱና ፡ ልጆቹ ፡ በችጋር ፡ ሲያልቁ ፡ ዝም ፡ ብሎ ፡ ይመለከታል ፡ እንደሚለው ፡ እንደሌሎችም ፡ አነጋገር ፡ ሳይሆን ፡ ለትዳሩ ፡ ለሚስቱና ፡ ለልጆቹም ፡ አሳቢ ፡ ይሆናል ። አንድ ፡ ጊዜም ፡ በተክሊልም ፡ ሆነ ፡ በማዘጋጃ ፡ ቤት ፡ ድንጋጌ ፡ መሠረት ፡ ካገባ ፡ ጸንቶ ፡ ሊኖር ፡ ይችላል ፡ ነው ፡ የምልህ - - ያንተን ፡ የንብና ፡ ከአበባ ፡ አበባ ፡ አስተያየት ፡ አልቀበልም - -

« እንዴት ፡ ነው ፡ ጋሼ ፡ ክብረት ፡ ይኽ ፡ የምታነሣው ፡ ሥዕል ፡ ጨርሶ ፡ የኛን ፡ አይመስልም - - » ይለዋል ፡ በላይ ፡ ቀረብ ፡ ራቅ ፡ ቀጥ ፡ ሽንደል ፡ በማለት ፡ በመሣያ ፡ ሸራው ፡ ላይ ፡ የተምቦራጨቀውን ፡ የልዩ ፡ ልዩ ፡ የቀለም ፡ አንድነት ፡ ትግል ፡ በመመልከት ።

« እኔ ፡ ለመሣል ፡ የምፈልገው ፡ እውነታን ፡ አይደለም ፤ እንደ ፡ ካሜራ ፡ መገልበጥ ፡ አይደለም ፡ ዓላማዬ ። በየፎቶግራፍ ፡ አንሽው ፡ ሱቅ ፡ መስተ ዋት ፡ ውስጥ ፡ እንደምታይዋቸው ፡ ሕይወት ፡ ሲንቀሳቀስ ፡ እንደማይታ ይባቸው ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ አቋቋም ፡ የተነሡ ፡ የበድን ፡ ሥዕሎች ፡ የሚ መሳስሉ - - በውነት ፡ እላችኋለሁ ፡ እነዚያ ፡ ፎቶግራፎች ፡ የሙት ፡ (የሬሳ) ወይም ፡ በሕይወቱ ፡ ያለ ፡ ሰው ፡ የተነሣቸው ፡ ፎቶግራፎች ፡ ለመ ሆናቸው ፡ የሚያረጋግጥ ፡ ምልክት ፡ አይታይባቸውም - - -

«እውነትህን ፡ ነው ፡ ጋሼ ፡ ክብረት ፡ አንተ ፡ የምታነሣው ፡ ሥዕል ፡ በላይን ፡ ወይም ፡ አደፍርስን ፡ መሆን ፡ የለበትም ። በአፍአዊው ፡ ሰውነታቸው ፡ እንዲታይ ፡ ልዩ ፡ ጥበብ ፡ ያለው ፡ ተመልካች ፡ ያስፈለገውን ፡ ውስጣዊነታቸውን ፡ ወይም ፡ በሌላ ፡ አነጋገር ፡ እነሱነታቸውን ፡ ነው ።- ‘እኔ ፡ ማነኝ ? ’ ብሏል ፡ አንድ ፡ ዐዋቂ ? አንተ ፡ ማንሣት ፡ ያለብህ ፡ ወጣትን ፡ ሳይሆን ፡ ወጣትነትን — በላይን ፡ ሳይሆን ፡ በላይን ፡ ስታይ ፡ የሚሰማህን ፡ መሆን ፡ አለበት - - ውስጣዊው ፡ ነገራችን ፡ የሕይወታችን ፡ የኑሯችን ፡ ቁልፍ ፡ ነው ። ለምሳሌ ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ ውስጣዊ ፡ የሆነችውን ፡ ልብስተ ፡ ጥላዊ ፡ ሚስቱን ፡ ቢያገኝ ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ከሚያያቸው ፡ ቆንጃጅት ፡ አብልጦ ፡ እንደሚወዳት ፡ የታወቀ ፡ ነው ። ካለማግኘቱ ፡ የተነሣ ፡ ግን ፡ የሚገጥሙትን ፡ ሴቶች ፡ ሁሉ ፡ በመጥላት ፡ ያገባትን ፡ ሚስቱን ፡ በመፍታት ፡ ስለ ፡ ቁንጅና ፡ ያለው ፡ አስተያየቱ ፡ ከጊዜ ፡ ወደ ፡ ጊዜ ፡ እየተለዋወጠ—ጥቁር ፡ ሲያይ ፡ ጥቁር ፡ ቀይ ፡ ሲያይ ፡ ቀይ ፡ ነጭ ፡ ሲያይ ፡ ነጭ ፡ ብጫ ፡ ሲያይ ፡ ብጫ ፡ መሆኑን ፡ ሁላችንም ፡ በየዕለቱ ፡ እናያለን ። እያንዳንዱ ፡ ሰው ፡ የቆንጆ ፡ አመራረጡ ፡ የተለያየ ፡ ነው ፤ ያንዱ ፡ ኩስኩስት ፡ ላንዱ ፡ ድምቢጥ - - ያንዱ ፡ ረቂቅ ፡ ላንዱ ፡ ኮፍጣና - - ያንዱ ፡ ኮምበር ፡ አፍ ፡ ላንዱ ፡ አበባ ፡ ፍንድ ፡ ከንፈር - - ያንዱ ፡ ዱፍንዱፍ ፡ ላንዱ ፡ መከዳ - - ያንዱ ፡ ድሁር ፡ ላንዱ ፡ ምጥን - - ያንዱ ፡ ቀጨሞ ፡ እግር ፡ ለሌላው ፡ ቀላቅሌ - - ያንዱ ፡ ወርሃ ፡ ለሌላው ፡ ቁም ፡ ነገረኛ ፡ ናቸው ፤ ማለቴ ፡ እንግዲህ ፡ የያንዳንዱ ፡ ሰው ፡ ልቡስ ፡ ጥላው ፡ የተለያየ ፡ ነው ።- በዚህም ፡ ምክንያት ሁሉም ፡ የየራሱ ፡ ምርጫ ፡ አለው ፡ እንጂ ፡ ያንዱ ፡ ቆንጆ ፡ ለሌላው ፡ ቆንጆ ፡ አትሆንም - - -

«- - እሱን ፡ እንኳን ፡ ርሳው ፡ እባክህ - - »ይለዋል ፡ በላይ ።-

- - - እንዴት ፡ አድርጌ ፡ እውነት ፡ አይረሳምኮ ፡ በላይ - - ! ርግጥ ፡ ነው ፡ አንተ ፡ የታሰበህ ፡ ገብቶኛል ። አንዳንድ ፡ ሰዎች ፡ የሌላን ፡ ቆንጆ ፡ በመመልከት ፡ የራሳቸውን ፡ ልብስተ ፡ ጥላ ፡ ትመስላቸውና ፡ በጣም ፡ ይታለላሉ ፤ ለፍተው ፡ ጥረው ፡ ግረው ፡ ሊያገኟት ፡ ይጣጣራሉ ። ያገኟት ፡ እንደሆነ ፡ ግን ፡ ያ ፡ እንደዚያ ፡ ያስፈቸላቸው ፡ ውበት ፡ በወር ፡ ውስጥ ፡ ግፋ ፡ ቢል ፡ በዓመት ፡ ያስጠላቸውና ፡ ፍቅራቸው ፡ ይቋረጣል ። ዓይናቸው ፡ አይቶ ፡ ያሯሯጣቸው ፡ ጆሯቸው ፡ ሰምቶ ፡ ያናወዛቸው ፡ ዘላቂነት ፡ ያለው ፡ ሳይሆን ፡ ከልቡስ ፡ ጥላቸው ፡ ጋር ፡ የማይስማማ ፡ ጊዚያዊ ፡ ሥዕል ፡ አጥበርብሮትና ፡ አንቀሳቅሶት ፡ መሆኑን ፡ ይገነዘባሉ ። በእንደዚህ ፡ ዓይነት ፡ ይሁን ፡ ይሁን ፡ የምትገባው ፡ ሚስት ፡ ከባሏ ፡ ልቡስ ፡ ጥላ ፡ ጋር ፡ ካለመ

ስማሚቷ ፡ የተነሣ ፡ የባሏ ፡ ጠባይ ፡ ሲለዋወጥባትና ፡ በመጨረሻም ፡ ሰል ችቷት ፡ ጥላው ፡ ስትሄድ ፡ ይታያል ።

«- - ለምሳሌ ፡ እኔ ፡ አሁን ፡ የምሥለው ፡ እናንተ ፡ በየምታምኑበት ፡ ነገር ፡ ስትከራከሩ ፡ ሳያችሁ ፡ ስለ ፡ እናንተ ፡ የተሰማኝን ፡ ያን ፡ ልብ ፡ እንደሚይዝ ፡ ፍቅር ፡ ድንገት ፡ ያዝ ፡ አድርጐ ፡ እንደሚለቅ ፡ ዓይነት ፡ የሆነውን ፡ የማይደጋገመውን ፡ ደራሽ ፡ ስሜት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ እናንተ ፡ ሁልጊዜ ፡ እያያችሁ ፡ የተለማመዳችሁትን ፡ የዘወትር ፡ እውነታችሁን ፡ አይደለም - - - ውስጣዊውን ፡ ሰብእናችሁን ፡ ነው ፡ ልደርስበት ፡ እም ሻው - - -

---ሞትና ፡ ሕይወት ፡ ድንቁርናና ፡ ዕውቀት ! እርግጥ ፡ ነው ፡ የእው ነተኛ ፡ ሠዐሊ ፡ ተግባሩ ፡ ውስጣዊውን ፡ ንቅናቄ ፡ አፍልቆ ፡ ማሳየት ፡ ነው ፡ መሆን ፡ ያለበት — ለምሳሌ ፡ የባሏ ፡ ውስጣዊ ፡ ስሜት ፡ ልቡሰ ፡ ጥላው ፡ ሲተኛና ፡ ሲደክም ፡ ጊዜያዊ ፡ የባሏ ፡ ፍቅር ፡ አይለያት ፡ ይሆ ናል ። ያጫውታታል ፡ ያስቃታል ፡ ያስደስታታል ። ነገር ፡ ግን ፡ ባልታ ሰበ ፡ ጊዜ ፡ የባሏ ፡ ልቡሰ ፡ ጥላ ፡ ሲነሣና ፡ አቅም ፡ ሲያገኝ ፡ እንደጭ ጐጐት ፡ ሳይወድ ፡ ተሰግስጋበት ፡ የምትኮሰኩሰው ፡ ነው ፡ የሚመስ ለው - - ባይኑም ፡ ለማየት ፡ እንኳ ፡ ቢጸየፋት ፡ አይገርምም ። እንደ ዚህ ፡ ያለ ፡ ሁኔታ ፡ የደረሰባት ፡ ሴት ፡ ጥላው ፡ ካልሄደች ፡ በስተቀር ፡ የባሏ ፡ ልቡሰ ፡ ጥላ ፡ በተለዋወጠ ፡ ቁጥር ፡ እየተሸማቀቀች ፡ ምን ፡ ጊዜም፡ ሙሉ ፡ እምነት ፡ ሳይኖራት ፡ ዓይኗ ፡ ርቆ ፡ እየተመለከተ ፡ ልቧን ፡ ግን፡ እንጀራ ፡ እያሸነፈው ፡ ስትበደል ፡ ትኖራለች ።-ካልፈታችውና፡ መስሏን ፡ ካላገኘች ፡ በስተቀር ፡ ከባል ፡ የሚገኘውን ፡ ደስታ ፡ ልታገኝ ፡ አትች ልም ። ባሏንም ፡ ቢሆን ፡ ጭራሹንም ፡ ሌሎችን ፡ ሴቶችና ፡ ራሱንም ፡ ጭምር ፡ አስከመጥላት ፡ ሊያደርሰው ፡ ይችላል ። በርግጥ ፡ በርግጥ ፡ ሠዐሊ ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ የልቧን ፡ ፍመትና ፡ ያይኗን ፡ አይደረሴነት ፡ መሆን ፡ ይገባዋል ፡ መሣል ፡ ያለበት - - ለእንጀራ ፡ የተገዛው ፡ ሰውነቷ ፡ ጭራሽ ፡ ዋጋ ፡ የለውም - - -

«- - አንድ ፡ ሕፃን ፡ ልጅ ፡ የእግሩን ፡ አውራ ፡ ጣት ፡ ጐርሶ ፡ አል ጋው ፡ ላይ ፡ ተኝቷል ፡ ፊቱ ፡ ፈገግ ፡ ፈገግ ፡ እያለ--ሣስት ፡ ቡችሎች ፡ አፋቸውን ፡ አጠጋግተው ፡ እመኪና ፡ መንገድ ፡ ማህል ፡ ተጥለዋል - - - አንዷን ፡ ባለ ፡ መኪና ፡ ይለያታል ፤ ወደ ፡ ፊት — ወደ ፡ ኋላ — ወደ ፡ ፊት ፡ ወደ ፡ ኋላ — ውጭ ፡ ነፍስ ፡ ግቢ ፡ ነፍስ ፡ ትተናንቃለች - - -

ጨርሶ ፡ አልጨፈለቃትም ፡ ባለመኪናው ። እሺ ! እንግዲህ ፡ እኔ ፡ እነዚህን ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ነገሮች ፡ ባየሁ ፡ ጊዜ ፡ ምን ፡ ነበር ፡ ስሜቴ ! እነዚያን ፡ ስሜቶች ፡ ነው ፡ በሠዐሊነት ፡ ጥበቤ ፡ አፍኜ ፡ ይዤ ፡ መለየት ፡ የሚኖርብኝ - - - እነዚያን ፡ ግላዊ ፡ የሆኑ ፡ የሕይወት ፡ ፈገግታና — የሕይወት ፡ ውጊቶች - - እነዚያን ፡ አይደገሜዎች - -

- - - አንድ ፡ ሰው ፡ ድንገት ፡ የተሰማውን ፡ ስሜት ፡ ፍላጐት ፡ ተስፋ— ወይም ፡ እነዚህን ፡ የመሳሰሉ ፡ ሌሎችን ፡ ንቅናቄዎች ፡ በመንፈሱ ፡ የመያዝ ፡ ችሎታ ፡ አለው ። ነገር ፡ ግን ፡ በገቢር ፡ ለማዋል ፡ በሥነ ፡ ጽሑፍም ፡ ሆነ ፡ በሙዚቃ ፡ ወይም ፡ በሥዕል — ወይም ፡ በጠቅላላው ፡ በአናኗር ፡ መንገድ ፡ ይዞ ፡ ለመገኘት ፡ አስቸጋሪ ፡ ነገሮች ፡ ናቸው ። — ልዩ፡ ተሰጥኦ ፡ ያስፈልጋቸዋል ።-ከተሰጥኦ ፡ ውጪ ፡ ማለት ፡ ተሰጥኦ ፡ የሌለ ፡ እንደሆነ ፡ ግን ፡ የማያቋርጥ ፡ የመንፈስ ፡ ቆራጥነትና ፡ ከግቡ ፡ የሚያደርስ ፡ የየዕለት ፡ ትግል ፡ ይጠይቃሉ - - ለምሳሌ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ሚስት ፡ ለማግባት ፡ሲፈልግ፡መጀመሪያ ፡ ልብስተ ፡ ጥላ ፡ ሚስቱ ፡ ምን ፡ ዓይነት ፡ እንደሆነች ፡ በዓይኑ ፡ ኅሊናው ፡ መገንዘብ ፡ አለበት ። መቼም ፡ ልብስተ ፡ ጥላ ፡ ሚስቱ ፡ በተፈጥሮው ፡ ያደገች ፡ የሰውነቱ ፡ ክፍል ፡ ስለሆነች ፡ በጣም ፡ ሳያፈቅራት ፡ አይቀርም ። ስለዚህ ፡ ዓይነተኛ ፡ እርምጃው ፡ ሊሆን ፡ የሚገባው ፡ ልብስተ ፡ ጥላ ፡ ሚስቱ ፡ ከኅሊናው ፡ ወጥታ ፡ የኑሮ ፡ ጓደኛው ፡ እንድትሆን ፡ ማድረግ ፡ ነው ። ይህንንም ፡ ሲያደርግ ፡ ልብስተ ፡ ጥላዊ ፡ ሚስቱ ፡ ያላትን ፡ አቀራረጽ ፡ ያላትን ፡ ጠባይ ፡ ሌሎችንም ፡ ስለ ፡ ድምፅዋ ፡ ስላነጋገሯ ፡ ሊያገኝ ፡ የሚፈልገውን ፡ ማንኛውንም ፡ ነገር ፡ እሱ ፡ እሷን ፡ ሲያገኝም ፡ ሊያደርግላት ፡ የሚፈልገውንና ፡ የሚችለውን ፡ ሁሉ ፡ በነጭና ፡ ጥቁር ፡ ማሥፈር ፡ አለበት - - -

« - - እውነትህን ፡ ነው - - » በቡርሹ ፡ የሚሥለውን ፡ ሥዕል ፡ ነካ ፡ ነካ ፡ እያደረገ « - - እውነትህን ፡ ነው ፤ በተለይ ፡ በሥዕል ፡ ሥራ ፡ ስለ ፡ ብርሃን ፡ አጣጣል—ስለ ፡ ጥላ—ስለ ፡ ፀሐይ—ስለ ፡ ዳመና—ስለ ፡ ጭፍና—ስለ ፡ ምሽት—ስለ ፡ ጭለማ—በጠቅላላው ፡ ነጭና ፡ ጥቁርን—የፀሐይን ፡ ብርሃን ፡ እንዴት ፡ እንደምትጠቀምበት ፡ ማወቅ ፡ ትልቅ ፡ ጥበብ ፡ ነው - - -

- - - በዚህ ፡ በነጭና ፡ ጥቁር ፡ ስለሚያሠፍረው ፡ ነገር ፡ ደግሞ ፡ ዝግጅት ፡ ያስፈልገዋል ። ጧት ፡ ጧት ፡ ወደ ፡ ሥራው ፡ ሲሄድ ፡ በወረቀት ፡ ላይ ፡ ያሠፈረውን ፡ የልብስተ ፡ ጥላዊ ፡ ሚስቱን ፡ ፎቶግራፍ፡እያ

ነበበ ፡ ቢያጋጥመው ፡ ለመፈለግ ፡ ይሞክር --» በላይ ፡ ወገቡን ፡ በእጁ ፡ ይዞ ፡ ግምባሩን ፡ ኮስተር ፡ አፉን ፡ ኩርትም ፡ አድርጐ ፡ የእውነተኛ ፡ ኮፍጣና ፡ ፊት ፡ እንዳለው ፡ ዓይነት ፡ ሆኖ ፡ እንዲነሣ ፡ ይጥራል ። ጭውውቱን ፡ የተከተለው ፡ አይመስልም --- ካለፍ ፡ አገደም ፡ ክብረት ፡ በላይን ፡ አየት ፡ ያደርጋዋል ።

---እንግዲህ ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ውቃቢው ፡ የደነገጠላት ፡ አንዲት ፡ ልጅ ፡ ያግኝ ፡ እንበል--ምናልባት ፡ በጽሑፍ ፡ ካሠፈራቸው ፡ አስፈላጊዎች ፡ ውስጥ ፡ ከሀያ ፡ እስከ ፡ ሠላሳ ፡ በመቶውን ፡ የሚኖራት --- ከዚያ፡ በኋላ ፡ ሳይተዋወቃት ፡ በፊት ፡ በሩቁ ፡ ሆኖ ፡ ይከታተላት — በርግጥ ፡ ያያቸው ፡ ነገሮች ፡ መኖራቸውን ፡ ሲገነዘብ ፡ በቀጥታ ፡ መንገድ ፡ ተዋውቆ ፡ (የስሜቱን ፡ ፈጽሞ ፡ የእንጀራ ፡ ገመዱን ፡ በጥሶ ፡ የሰው ፡ በታች ፡ ለማድረግ ፡ ሳይሆን) ልብስተ ፡ ጥላ ፡ ሚስቱን ፡ ቢያገኝ ፡ ሊያደርግላት ፡ ያሰበው ፡ የነበረውን ፡ የሚያስደስትበትን ፡ መንገድ ፡ በዚች ፡ ልጅ ፡ ላይ ፡ ምን ፡ ዓይነት ፡ ስሜት ፡ እንደሚፈጥር ፡ ለማወቅ ፡ እየቆጠበ ፡ ይሞክረው ። ይህን ፡ በሚያደርግበት ፡ ጊዜ ፡ በጻፈው ፡ መግለጫ ፡ መሠረት ፡ ከልጅቷ ፡ ከሚፈልጋቸው ፡ ነገሮች ፡ ውስጥ ፡ ሊያውቅ ፡ የሚፈልጋቸውን ፡ በቅርብ ፡ እንጂ ፡ በሩቅ ፡ ሊታወቁ ፡ የማይችሉትን ፡ ያጥና ---

« እሷስ ፡ አልጠና ፡ ያለች ፡ እንደሁ ፤ ስታይህ ፡ የምትሸሽ ፡ የምትቆጣ ፡ የሆነችስ ፡ እንደሁ ። — ጨርሶ ፡ ያልወደደችህስ ፡ እንደሁ ። — ወይም ፡ ደግሞ ፡ የተዋወቅህበትን ፡ ምክንያት ፡ እስክታውቅ ፡ ድረስ ፡ ብታነጋገርህ ፡ እንኳ ፡ ልታነጋግራት ፡ በተጠጋህ ፡ ቁጥር ፡ ልብህ ፡ በኃይል ፡ እየመታ ፡ ግምባርህን ፡ እያላበህ ፡ ንፍጥህ ፡ ያለወትሮው ፡ እየመጣ፡ ልትናገረው ፡ ያሰብከው ፡ ነገር ፡ እየጠፋብህ ፡ እየዘባረቅህ ፡ ጭራሽ ፡ ያይደለኸው ፡ ሰውነትህ ፡ እየታዬ ፡ ያስቸገረህስ ፡ እንደሁ—ምን ፡ ትሆናለህ ፡ ወንድሜ — ምን ፡ መፍቻ ፡ ምን ፡ ማገጃ — ምን ፡ ዘዴ ፡ ታገኝለታለህ ? ለእንዲህ ፡ ያለው ፡ ሊቆጣጠሩት ፡ የማይቻል ፡ ነገር---» ይለዋል ፡ በላይ ፡ ድንገት ፡ አደፍርስን ።

--ሞትና ፡ ሕይወት ፡ ድንቁርናና ፡ ዕውቀት ! እዚህ ፡ ላይ ፡ ወንድነትህን ፡ መርሳት ፡ የለብህም ፤ ቆስካማነትህን ፡ ማሳየት ፡ የለብህም — ብታጉማማ ፡ ብትበሳጭ ፡ ዋጋ ፡ የለውም ። —እና ፡ ብቻ ፡ እንዳጋጣሚ ፡ ሆኖ ፡ የምትፈልገው ፡ ነገር ፡ ከጎምሳ ፡ ሲያልፍና ፡ በተፋጠነ ፡ ሁኔታ ፡ እያደር ፡ ሲያድግ --ያንን ፡ ጽሮት ፡ የነበረውን ፡ ማንበቡን ፡ ያቋርጥና ፡

እሷ ፡ ዘንድ ፡ ቶሎ ፡ ቶሎ ፡ እየሄደ ፡ ሊያነጋግራትና ፡ ሊያጫውታት ፡ ይሞክር - - -

« እምቢ ፡ አልጫወትም ፡ ያለችውስ ፡ እንደሁ ፡ ነውኮ ፡ የሚ ልህ — አልተዋወቅም ፡ አላነጋግርም ፡ ያለችውስ ፡ እንደሁ ፡ ነው ፡ የሚ ልህ ፡ በላይ ! » ሠዓሊው ፡ ድንገት ፡ ቀና ፡ ብሎ ፡ ይናገራል ።

- - - እዚህ ፡ ደረጃ ፡ ሲደርስ - - » ጨርሶ ፡ ያልሰማ ፡ መስሎ ፡ አርቆ ፡ እየተመለከተ « - - በወረቀት ፡ ላይ ፡ የሠፈረው ፡ የልብስተ ፡ ጥላው ፡ መግለጫ ፡ ተደጋግሞ ፡ ከመነበቡ ፡ የተነሣ — ምንም ፡ እንኳ ፡ ልብስተ ፡ ጥላው ፡ ከሆነችው ፡ ሚስቱ ፡ ውስጥ ፡ በዛ ፡ ያለ ፡ ሊገለጥ ፡ የማይችልም ፡ ነገር ፡ ቢኖር ፡ እወረቀቱ ፡ ላይ ፡ ባለው ፡ ብቻ ፡ ተወስናለችና ፡ እንዲ ሁም ፡ እወረቀቱ ፡ ላይ ፡ የሠፈረው ፡ በተገኘችው ፡ ልጅ ፡ ቀስ ፡ በቀስ ፡ እየተለወጠ ፡ ሄዷልና ፡ ቢጋቡ ፡ በባልና ፡ ሚስትነት ፡ ጸንተው ፡ መኖራ ቸው ፡ አያጠራጥርም — ውጫዊው ፡ በውስጣዊው ፡ ውስጣዊው ፡ በውጫ ዊው ፡ ተለወጡ ፡ ማለት ፡ ከአዳም ፡ ከግራ ፡ ጐኑ ፡ ተፈነቀለች — ማለት ፡ ባልና ፡ ሚስት ፡ አንድ ፡ አካል ፡ አንድ ፡ አምሳል ፡ ናቸው — ማለት ፡ ባጭሩ ፡ ትርጉማቸው ፡ ይኸው ፡ ነው - - -

« እኔ ፡ የቸገረኝ ፡ ሌላ ፡ እሱ ፡ የሚያወራው ፡ ሌላ ! እባክህ ፡ ጋሼ ፡ ከብረት ፡ ጨርሰህ ፡ እንደሆን ፡ እንሂድ - - - !

« ምንም ፡ ያህል ፡ አልቀረኝ - - የብርሃኑን ፡ አበታተን ፡ ላስተካ ክለው ፡ ብዬ ፡ ነው - - -

- - - እንግዲህ ፡ እውነተኛ ፡ ሚስቱ ፡ ልትሆን ፡ የምትችለውን ፡ ደጋግሞ ፡ ከማነጋገሩ ፡ የተነሣ ፡ ስለ ፡ እሷ ፡ ብዙ ፡ ነገሮች ፡ ሲያውቅ ፡ የሚፈልጋቸውም ፡ ነገሮች ፡ ከመቶው — ከሃምሳ ፡ በላይ ፡ ሲሆኑና ፡ እድ ገታቸውም ፡ የሚያኮራ ፡ ሲሆን ፡ እሱ ፡ መጀመሪያ ፡ ላይ ፡ በሠራበት ፡ ፎርም ፡ መሠረት ፡ እሷም ፡ በተራዋ ፡ የምትፈልገውን ፡ ሰው ፡ መግለጫ ፡ እንድትሰጠው ፡ ያድርግ - - -

« እሱን ፡ የሚመስል ፡ ሳይሆን ፡ የቀረስ ፡ እንደሁ ?— በተራዛሚ ፡ መንገድ ፡ እንኳን ፡ ቢሆን ፡ ሳይቀራረብ ፡ የቀረስ ፡ እንደሁ — ከዚያ ፡ ሁሉ ፡ ጥረት ፡ በኋላ - - -

- - - እዚህ ፡ ላይ ፡ የሚገርመው ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ስላነጋገረችውና ፡ ውቃቢዋም ፡ በከፊል ፡ ሳይፈቅደው ፡ ስለማይቀር ፡ የምትጽፈው ፡ መግ ለጫ ፡ እሱን ፡ የሚመለከት ፡ መሆኑ ፡ ነው - - -

« ይቺ ፡ በጭራሽ ፡ መሠረት ፡ የሌላት ፡ ያንተ ፡ የብቻ ፡ መላ ፡ ምትህ ፡ ናት ፡— በበኩሌ ፡ አልቀበልህም » ይለዋል ፡ ሠዓሊው ።

- - - ባይሆንም ፡ እንኳኮ ፥ እሷ ፡ ከሱ ፡ ላይ ፡ ከምትፈልገው ፡ ሀያ ፡ ከመቶ ፡ ከተገኘበት ፡ ለጋብቻ ፡ መጠየቁ ፡ አይከፋም፡—ምናልባት ፡ ለልብስተ ፡ ጥላ ፡ ሚስቱ ፡ ሊያደርገው ፡ ይመኘው ፡ ከነበረው ፡ ውስጥ ፡ አንድ ፡ አሥረኛውን ፡ እንኳ ፡ አላደረገላት ፡ ይሆናል ። ስለዚህ ፡ ወደፊት ፡ የሚበልጠውን ፡ የሚያስደስታትን ፡ ነገር ፡ ባደረገላትማ ፡ ጊዜ ፣ ልጅቱ ፡ ለሱ ፡ የሚኖራት ፡ አስተያየት ፡ እያደገ ፡ እንደሚሄድ ፡ አያጠራጥርም- - -

« አጉል ፡ ነው ፡ የምታጠቃልለው—አደፍርስ ! » ያስታውሰዋል ፡ ሠዓሊው ፡ እንደገና ።

- - - እነዚህ ፡ ባልና ፡ ሚስቶች ፡ አይፋቱም ፤ ለመጀመሪያው ፡ ጊዜ ፡ ሚስቱ ፡ ለባሏ ፡ የልብስተ ፡ ጥላው ፡ መስታዋት ፡ ናት ፤ እንዲሁም ፡ ባሏ ፡ ለሚስቱ ፡ የልቡሰ ፡ ጥላዋ ፡ መስታዋት ፡ ነው ። ከጥቂት ፡ ጊዜ ፡ በኋላ ፡ ግን ፣ ያገባት ፡ ሚስቱ ፡ በአእምሮው ፡ ውስጥ ፡ ልብስተ ፡ ጥላውን ፡ የነበረች ፣ በተጨማሪም ፡ እውነተኛና ፡ በዓይኑ ፡ የሚያያት ፣ በእጁ ፡ የሚዳስሳት ፡ ስትሆን ፣ እሱም ፡ በሚስቱ ፡ አእምሮ ፡ ውስጥ ፡ ልቡሰ ፡ ጥላዋን ፡ ሆኖ ፡ የኖረ ፣ በተጨማሪም ፡ እውነተኛና ፡ በዓይኗ ፡ የምታየው ፡ በእጅዋ ፡ የምትዳስሰው ፡ የምትመካበት ፡ ባሏ ፡ ይሆናል - - -

« እኔኮ ፡ የምለው ፣ እንዲህ ፡ ያለው ፡ የተውዘገዘገ ፡ የኑሮ ፡ አተረጓጐም ፡ ከወዴት ፡ ተፈጠረብህ - - ? » ይጠይቀዋል ፡ ሠዓሊው

- - ከየት ፡ የተፈጠረብኝ ፡ ይመስልሃል — ከዩንቨርስቲ ፡ ነዋ ! ምትና ፡ ሕይወት ፡ ድንቁርናና ፡ ዕውቀት ! — ለምን ፡ ይመስልሃል ፡ ዩኒቨርስቲ ፡ የገባሁት ፣ የተጻፈን ፡ ለማስተጋባት ፡ አይምሰልህ - - የፕሮብሌሞችን ፡ መነሻ ፡ ከሥራቸው ፡ እያጠናሁ ፡ መልስ ፡ ለማግኘት ፡ ነው ።— እውነትን ፡ ካለችበት ፡ ፈልፍዬ ፡ ለማውጣት - - ብቻ ፡ እንግዲህ ፡ እኔ ፡ ባገኘሁት ፡ እውነት ፡ መሠረት ፣ ወንድም ፡ ሆነ ፡ ሴት ፡ ልቡሰ ፡ ጥላቸውን ፡ መሰል ፡ ካላገኙ ፣ ወንድ—ነጠላ ፡ ትከሻ ፣ ቀትረ ፡ ቀላል ፣ አጉራዘላይ ፡ ይሆናል ፤ ሴትም—ቀኸርቃሣ ፣ ቀበጥ ፣ ተለዋዋጭና ፡ የእንግዳ ፡ ቁርበት ፡ ትሆናለች ።—ማለት ፡ የወንዱ ፡ ልብስተ ፡ ጥላ ፡ በሰብአዊ ፡ ሴት ፡ የሴቷ ፡ ልቡሰ ፡ ጥላ ፡ በሰብአዊ ፡ ወንድ ፡ ካልተለወጠ ፡ ሴትና ፡ ወንድ ፡ አንድ ፡ አካል ፡ አንድ ፡ አምሳል ፡ ይሆናሉ ፣ ብዬ ፡ አላምንም ፡ ነው ፡ የምልህ ። — ሌላውን ፡ ተወው ፤ የዱሮ ፡ አባቶቻችን ፡ እንኳ ፡ ቢሆኑ ፣ እን

ደኛ ፡ እንደዛሬዎቹ ፡ ወጣቶች ፡ አይተንትኑት ፡ እንጂ ፡ የጋብቻቸው ፡ ሥርዓት ፡ ይኸንኑ ፡ እኔ ፡ የተናገርኩትን ፡ መንገድ ፡ የተከተለ ፡ ነበር — ሽማግሌዎችም ፡ ሆኑ ፡ ልጆቻቸው ፡ ከበረታቸው ፡ ውጪ ፡ የማያውቁ ፡ ከነሱ ፡ የተሻሉ ፡ አርአያነታቸውን ፡ የሚከተሉት ፡ ሰዎች ፡ ያላጋጠሟ ቸው ፡ ሐሳባቸው ፡ ከአያት ፡ ከቅድም ፡ አያት ፡ በወረሱት ፡ ልቡስ ፡ ጥላ ቸውና ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ተረቶችና ፡ ምሳሌዎች ፡ ብቻ ፡ የተወሰነ ፡ ነበር ። ከዚህም ፡ የተነሣ ፡ በሚወልዷቸው ፡ ልጆች ፡ የሚቀረጸው ፡ ልቡሰ ፡ ጥላ ፡ ያንኑ ፡ የባቶቻቸውን ፡ መሰል ፡ ስለነበረ ፡ ባባቶች ፡ ልብስተ ፡ ጥላ ፡ መሠ ረት ፡ ትመረጥ ፡ የነበረችው ፡ ሚስት ፡ የልጅዮውም ፡ ልብስተ ፡ ጥላ ፡ መሰል ፡ ስለነበረች ፡ ልጆቹ ፡ ቤተሰቦቻቸው ፡ የመረጡላቸውን ፡ ያገቡ ፡ ነበር ። ሲያስተሣሥራቸውም ፡ ይኖር ፡ የነበረው ፡ ከአባቶች ፡ የወረሱት ፡ የሚወዱት ፡ የሚያፈቅሩት ፡ ልቡስ ፡ ጥላ ፡ ባባቶቻቸው ፡ እንደገና ፡ የተ መረጠ ፡ ስለነበረና ፡ ልጆቹም ፡ በሙሉ ፡ እምነት ፡ በአእምሯቸው ፡ ውስጥ ፡ ምስቅልቅል ፡ ሁኔታ ፡ የነበረውን ፡ ልቡሰ ፡ ጥላቸውን ፡ በተጨበጠ ፡ መን ገድ ፡ ያገኙት ፡ ስለሚመስላቸውና ፡ አእምሯቸው ፡ የፈለገውን ፡ በአእም ሯቸው ፡ ያደገውን ፡ ከአእምሯቸው ፡ ወጥቶ ፡ የኑሮ ፡ ጓደኛቸው ፡ ሆኖ ፡ ስለሚያገኙት ፡ ነበር ። ብዙ ፡ ሳይመራመሩ ፡ በቀላሉ ፡ ሂዋን ፡ ከአ ዳም ፡ ከግራ ፡ ጐኑ ፡ እንደወጣችና ፡ እስከ ፡ ዕለተ ፡ ሞቱ ፡ እንዳልተለየ ችው ፡ በመገንዘብ ፡ ባልና ፡ ሚስት ፡ አንድ ፡ አካል ፡ አንድ ፡ አምሳል ፡ ናቸው ፡ ምን ፡ ጊዜም ፡ መለያየት ፡ የለባቸውም ፡ በማለት ፡ አምነውበት ፡ ኖረዋል ። — በአእምሮ ፡ የተፀነሰች ፡ ልብስተ ፡ ጥላ ፡ ናትና ፡ ከሰውነት ፡ ጋር ፡ አብራ ፡ ያደገች ፡ ስለሆነች ፡ ሥጋ ፡ ለበስ ፡ ሆና ፡ በጐን ፡ በምትገ ኝበት ፡ ጊዜ ፡ የሰውነት ፡ ክፍል ፡ የማትሆንበት ፡ ምክንያት ፡ የለም - - -

« ይኸ ፡ ሥዕል ፡ አይገባኝም ፡ ጋሼ ፡ ክብረት ፤ እዚህ ፡ ላይ ፡ የሣ ልከው ፡ እኛን ፡ ባየህ ፡ ጊዜ ፡ የተሰማህን ፡ ስሜት ፡ አይደለም — እዚህ ፡ ላይ ፡ በቀጭኑ ፡ የተሰነጠበ ፡ የፊት ፡ ግማሽ ፡ እዚህ ፡ ላይ ፡ ደሞ ፡ በቀ ጭኑ ፡ የተሰነጠበ ፡ የፊት ፡ ግማሽ — አፍ — ጆሮ — ለየብቻቸው ፡ እዚ ህጋ ፡ ደግሞ ፡ ዓይን — ደግሞ ፡ እዚህጋ ፡ አለቦታው ፡ እግር - - በተ ረፈ ፡ ሜዳ ፡ ሙሉ ፡ በያይነቱ ፡ ቀለም - - ይኸ ፡ እንኳ ፡ የቀለም ፡ ቦግታ ፡ እንስራ ፡ የተሸከመች ፡ ሴት ፡ ይመስላል — ፍሬዋ ፡ እንደሁ ፡ አል መጣችም ፤ ማን ፡ አየህና ፡ ተሰምቶህ ፡ ነው ፡ የሣልከው - - - ? » ይለ ዋል ፡ በላይ — ዓይኑን ፡ ባለማመን ፡ እንዴ ፡ ሁለቴ ፡ አሸት ፡ አሸት ፡ ብልጭ ፡ ድርግም ፡ አድርጐ ፡ ከተመለከተ ፡ በኋላ ። —

« ይኸኮ ፡ የእናንተ ፡ ሥዕል ፡ እናንተን ፡ አይቼ ፡ በተሰማኝ ፡ ስሜት ፡ ላይ ፡ አይደለም ፡ የተመሠረተው — እዚህ ፡ ላይ ፡ ለማሳየት ፡ የሞከርኩት ፡ አደፍርስን ፡ ወይም ፡ በላይን ፡ አይደለም — እናንተ ፡ በም ትኖሩበት ፡ በአሁኑ ፡ ጊዜ ፡ ያለውን ፡ ቄደረኛ ፡ ጉበዝነትን ፡ ነው ። የዘ መናሁችን ፡ ቃንቄነት — የዘመናችሁን ፡ ወጣትነት — እንደምታየው ፡ ይኸን ፡ ሳደርግ ፡ የተለየ ፡ የወጣትነት ፡ መልክ ፡ ወይም ፡ የተለየ ፡ በስም ፡ የታወቀ ፡ ወጣት ፡ ፊት ፡ ወይም ፡ ካላስፈለገኝ ፡ በስተቀር ፡ ሙሉ ፡ ሰው ፡ የሚታይበት ፡ ሰውነት ፡ መሣል ፡ የለብኝም ። የዘመኑን ፡ ቄደረኛ ፡ ወጣ ትነትን ፡ የሚገልጹ ፡ ማለት ፡ ሊገልጹ ፡ ይችላሉ ፡ የምላቸው ፡ ጥቂት ፡ ምልክቶችን ፡ ከጠቆምሁ ፡ በቂ ፡ ነው ፡ ማለት ፡ ነው ። የቀለሙ ፡ መወ ራቸት ፡ ደግሞ ፡ ዓላማው ፡ የዘመኑን ፡ ድምፀታና ፡ ቀልብ ፡ ፍላጐት ፡ አዝማሚያና ፡ ጠቅላላ ፡ አየር ፡ ለማሳየት ፡ ያህል ፡ ነው - - -

« እንደዚህ ፡ መሆኑን ፡ ባውቅ ፡ ኖሮ ፡ ጋሼ ፡ ክብረት ፡ ጭራሽ ፡ ጊዜ ዬን ፡ አላጠፋም ፡ ነበር ።—እኔ ፡ የፈለግሁት ፡ አፍንጫዬም ፡ እንዳለ ፡ ዓይ ኔም ፡ እንዳለ ፡ ጆሮዬም ፡ እንዳለ ፡ እጄም ፡ እንዳለ ፡ ሆዴም ፡ እግሬም ፡ እንዳለ ፡ እንደተፈጠርሁ ፡ እንድትሥለኝ ፡ ነበር ፡ እንጂ ፡ ለዚህ ፡ ኖሯል ? ዱሮ ፡ ፈረንሣይ ፡ አገር ፡ ከመሄዴ ፡ በፊት ፡ የሣልኩት ፡ ነው ፡ ብለህ ፡ ያሳየኸኝ ፡ እንዴት ፡ ይሻል ፡ ነበር ።—መልክ ፡ ለሌላቸው ፡ እንኳ ፡ መልክ ፡ ነበር ፡ የምትሰጣቸው — የመላእክት ፡ ዘር ፡ እንጂ ፡ የሰው ፡ ዘር ፡ አይ መስሉም ፡ ነበር ፤ እንዲያም ፡ ሆኖ ፡ ታዲያ ፡ ለመለየት ፡ አላዳገቱም --አሄሄ! ትምህርት ፡ ሲበዛ ፡ ጥሩ ፡ አይደለም - - -

« ወንድሜ ፡ አፍንጫ ፡ እንዳለ ፡ ዓይን ፡ እንዳለ ፡ ወይም ፡ ደግሞ ፡ ሌላው ፡ ዘዴ ፡ ሰው ፡ የመልአክ ፡ ዘር ፡ መስሎ ፡ የሚሣልበት ፡ ዘመን ፡ አልፏል ። ዛሬ ፡ ሕዝቡ ፡ ተራቋል ፤ ጸጉር ፡ ሰንጥቋል ።—ልቡን ፡ የሚያረ ካው ፡ አእምሮውን ፡ የሚመግበው ፡ የሚያሳስበው ፡ ነገር ፡ ይፈልጋል ።— አንተ ፡ ጠቅልለህ ፡ ከምታጐርሰው ፡ ይልቅ ፡ በገዛ ፡ እጁ ፡ መርጦ ፡ አስ ተካክሎ ፡ አመቻችቶ ፡ ቢመገብ ፡ ይመርጣል ፤ የሚደክምበት ፡ ነገር ፡ የበለጠ ፡ ይጣፍጠዋል - - -

«-- ሕዝብ ፡ ተራቋል ፡ ትለኛለህ ፡ ደግሞ ፡ እኔ ፡ ከሕዝቡ ፡ ውስጥ ፡ መሆኔን ፡ እየረሳህ - - - ! ርቅቀት ፡ እንደዚህ ፡ ከሆነ ፡ እኔ ፡ አልተራ ቀቅሁም— መራቀቅም ፡ አልፈልግም — ይኸን ፡ ዓይነቱ ፡ ርቅቀት ፡ ግል በት ፡ ነው ፡ ለኔ ፡ የሚመስለኝ - - -

«ለመሆኑ ፡ ግን ፡ ከፍሬዋ ፡ ጋር ፡ እንዲያ ፡ ስለሲያንሱ ፡ ጀግራፌው ፡ ሥነ ፡ ጥበቡ ፡ ኪነ ፡ ጥበቡ ፡ ስለ ፡ ስንቱ ፡ ነገር ፡ ስትከራከሩ ፡ ምንም ፡ ያህል ፡ አልለወጠችህም - - - » ይለዋል ፡ ክብረት ፡ በላይን ።— በዚህን ፡ ጊዜ ፡ በላይ ፡ ዘወር ፡ ቢል ፡ አደፍርስን ፡ ያጣዋል ።

«- - ምን ፡ ዓይነት ፡ ጥላ ፡ ቢስ ፡ ፍጥረት ! ምን ፡ ጊዜ ፡ ከፊቴ ፡ ተሰወረ ! » መለስ ፡ ብሎ ፡ ፊጥኖ ፡ ሊያስደርሰው ፡ በሚያስችል ፡ ሩጫና ፡ ርምጃ ፡ ይፈተለካል ።

- - - ሰበብህ ፡ አመለጠህ ፡ ፍሬዋን ፡ ማያ ፡ ዘዴህ ! » ይላል ፡ ክብረት ፡ ለራሱ ፡ እንደሚናገር ፡ ዓይነት ፡ የሚሥለውን ፡ ሥዕል ፡ ፊቱን ፡ ሠየፍ ፡ ሠየፍ ፡ እያደረገ ፡ በቀኝና ፡ በግራ ፡ እየተመለከተ ።

# ፱

## አደፍርስ

ሰበቡ ፡ ያመልጠዋል ፡ ክብረት ፡ እንደተናገረው ። አደፍርስ ፡ የሄ ደበትን ፡ አቅጣጫ ፡ ተከትሎ ፡ አልነበረም ፡ ጥድፊያው ። — ፍሬዋን ፡ ቢሆን ፡ እቤቷ ፡ ስለነበረች ፡ ያገኛታል ። — ከነገር ፡ ነገር ፡ የተነማም ፡ እሷ ፡ የምትወደውና ፡ እሱም ፡ በደንብ ፡ የሚያውቀው ፡ ዓይነት ፡ የመሰ ለው ፡ ርእስ ፡ ይገጥመውና ፡ በረጅሙ ፡ ይይዘዋል ፤ ጨዋታውን - - - « ያን ፡ ጊዜ ፡ ገና ፡ ከባላገር ፡ ደብረሲና ፡ አልመጣንም - - - ግፋ ፡ ቢል ፡ አሥር ፡ ዓመት ፡ ቢሆነኝ ፡ ነው ። ድግስ ፡ ተጠርተን ፡ ካባቴ ፡ ጋር ፡ ሄድ ሁና ፡ አባቴ ፡ ወደ ፡ ቤታቸው ፡ ሲመለሱ ፡ እኔ ፡ ካላደርሁ ፡ ሞቼ ፡ እገኛ ለሁ ፡ ብዬ ፡ ስላስቸገርሁ ፡ እዚያው ፡ እድግሱ ፡ ቤት ፡ ቀረሁ ።— ማታ ፡ ራት ፡ ቀርቦ ፡ ስንበላ ፡ እኔ ፡ ስለ ፡ ቤቴ ፡ ስለ ፡ አባቴ ፡ ስለ ፡ ማሳድጋት ፡ ውሻ ፡ እያሰላሰልሁ ፡ አንድ ፡ ከወጥ ፡ ውስጥ ፡ የወጣ ፡ የዝልዝል ፡ ሥጋ ፡ ጉራጅ ፡ አፌ ፡ አድርጌ ፡ አልታኘክ ፡ ብሎኝ ፡ በመተናነቅ ፡ ላይ ፡ ሳለሁ ፡ ተናደድ ሁና ፡ ብውጠው ፡ በሥራሥር ፡ ነገር ፡ ከጥርሴ ፡ ጋር ፡ ተያይዞ ፡ ኖሮ ፡ እንቅ ፡ አደረገኝ ። ወዲያ ፡ ብል ፡ ወዲህ ፡ የተያያዘበትን ፡ ልፋጭ ፡ ላገኘው ፡ አል ቻልኩም ። ነፍስ ፡ ውጭ ፡ ነፍስ ፡ ግቢ ፡ ሆነ ። በጣቴ ፡ ብኮረኩር ፡ ጉሮሮ ዬን ፡ ያዝ ፡ ለቀቅ ፡ እያደረግሁ ፡ ብተናነቅ ፡ ፋይዳ ፡ አልሠራም ። እንባዬ ፡ ርግፍ ፡ ርግፍ ፡ ይል ፡ ጀመር ። አብሮኝ ፡ ይበላ ፡ የነበረው ፡ የባለቤቱ ፡ ልጅ ፡ አየኝ ። የምሞት ፡ የመሰለው ፡ ዓይነት ፡ ደንግጦ ፡ አባቱን ፡ ጠራ ። ወዲያውኑ ፡ መጡ ። ጣታቸውን ፡ ወደ ፡ አፌ ፡ አልጨመሩም ፤ ማጅራ ቴን ፡ በጃቸው ፡ ሰደፍ ፡ መቱት —ከጥርሴ ፡ የተያያዘው ፡ ተመንጭቆ ፡ በጉሮሮዬ ፡ ወደታች ፡ ተሽቀነጠረ ። ዓይኔ ፡ ተገለጠ ። ባለቤቱ ፡ ሳቅ ፡ አሉ ። - - ለወትሮው ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ ቱር ፡ ይል ፡ ነበር ፡ ዛሬ ፡ እንዴት ፡ ወደ ፡ ታች ፡ ወረደ ፡ ብለው ፡ ገረማቸው — ‘መዘዘኛ ፡ ላም ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ አስ ከትላ ፡ ነበር’ አሉ ፡ በመቀጠልም ።—ላሚቱ ፡ ገደል ፡ ስለገባች ፡ ነበር ፡ የታ ረደችው - - » እያለ ።—

ፍሬዋም « እስካሁንኮ ፡ ስለ ፡ አየሃቸው ፡ ሠይጣኖች ፡ ምንም ፡ አልነ ገርከኝም ፤ እኔ ፡ የምፈልገው ፡ ስለ ፡ እነሱ ፡ ለመስማት ፡ ነው ፤ ሌላውን ፡

በሌላ ፡ ጊዜ ፡ እንጫወተዋለን - - » በማለት ፡ የተነሣበትን ፡ እንዳይስት ፡ እያስታወሰችው ።—

---እሺ ፡ እሺ — ወደ ፡ ሠይጣኖቹ ፡ መምጣቴ ፡ ነው ።— ለካ ፡ ታዲያ ፡ ይኸውልሽ ፡ ዋናው ፡ ነገር ፡ ይኸ ፡ በሥጋ ፡ መታነቅ ፡ የተለመደ ፡ ነገር ፡ ኖሯል ። ሰውን ፡ ሥጋ ፡ ካነቀው ፡ ጊዜ ፡ ሞቱ ፡ ደርሶ ፡ ነው ፡ ይላሉ ፡ አባቶቻችን ፡ አሉ ፡ ባለቤቱ ። ተመልከችው ፡ እንግዲህ ፡ በዚህ ፡ ዓይነት ፡ ሁኔታ ፡ ምናልባት ፡ ታንቀው ፡ የሞቱ ፡ ምናልባትም ፡ እንደ ፡ እኔ ፡ የዳኑ ፡ ከዚያ ፡ በፊት ፡ አይጠፉም ፡ ማለት ፡ ነው ። ገረመኝ ። መብላቴንም ፡ አቆምሁ ። ለማባበል ፡ ያህል ፡ እንደገና ፡ ከሳቸው ፡ ወጥ ፡ አስወጥተው ፡ በርቦ ፡ መሳይ ፡ ለብቻዬ ፡ ሰጡኝ ። እኔ ፡ ግን ፡ ከድንጋጤዬ ፡ የተነሣ ፡ ብዙ ፡ ሊበላልኝ ፡ አልቻለም ' እረ ፡ አንተስ ፡ ዘበናይ ፡ ነህ ' አሉኝ ። ብርቅ ፡ ሆኖብኝ ፡ እንደ ፡ ልጅ ፡ ጐረስ ፡ ጐረስ ፡ የማደርግ ፡ መስሏቸዋል ። እኔ ፡ ለራሴ ፡ ካባቴ ፡ ጐን ፡ ቂጥጥ ፡ እያልኩ ፡ አብሬ ፡ መመገቤን ፡ አላወቁም ።—ቅይጥ ፡ እንኳን ፡ በልቼ ፡ አላውቅም—ይገርምሻል ።— ታዲያ ፡ ብርቅ ፡ የሆነብኝ ፡ መስሏቸዋል ፡ ከሳቸው ፡ ወጥ ፡ ማጥቀስ ። መልስ ፡ አልሰጠሁም ። የኔ ፡ ትራፊ ፡ ለሳቸው ፡ ልጅ ፡ ተሰጠው ። ደኅና ፡ አድርጐ ፡ አቀላጠፋት ። እንደዚያ ፡ ያለ ፡ ዕድል ፡ አጋጥሞት ፡ የሚያውቅ ፡ አልመሰለም ፡ እንዳበላሉ ። ወደ ፡ መኝታዬ ፡ ልሄድ ፡ ስል ፡ የባለቤቱ ፡ ሚስት ፡ የደረሰብኝ ፡ አደጋ ፡ በጣም ፡ ስግጥጧቸው ፡ ኖሮ ፡ እጄን ፡ ያዝ ፡ አድርገው ፡ ፊት ፡ ፊቴን ፡ በማየት ፡— ወዳጄ ፡ እንኳን ፡ እግዜር ፡ የናትህ ፡ ውቃቢ ፡ ያዳነህ ፡ ብለው ፡ እንትፍትፍትፍ ፡ አሉብኝ - - -

« በላይ ፡ እኔ ፡ ስለ ፡ እሳቸው ፡ እንትፍትፍ ፡ ደንታ ፡ የለኝም ፤ ስለ ፡ ሠይጣኖቹ ፡ ትነግረኝ ፡ እንደሁ ፡ ንገረኝ ፤ አለዚያ ፡ ተወው - - » አጣሁ ፡ ወሮታ ፡ የናደፍርስ ፡ የኖረች ፡ የቤት ፡ አሽከር ፡ ተከታትላቸው ፡ ኖሮ ፡ የምትሠራበትን ፡ የጭስ ፡ ቤት ፡ ግድግዳ ፡ ተገን ፡ አድርጋ ፡ የሚሉትን ፡ ታዳምጣለች ።

---ልነግርሽኮ ፡ ነው - - ! በመቀጠልም ፡ ታዲያ ፡ የሳቸው ፡ ዛር ፡ ፈረስ ፡ ከተነሣ ፡ መቼ ፡ ከብቱንም ፡ ሰዉንም ፡ ካልጨረሰ ፡ ይቆማል ? አሉ ። ለካ ፡ ባለቤትየው ፡ ዛር ፡ ኖሮባቸዋል ። ላሟንም ፡ ገደል ፡ የጨመራት ፡ ዛራቸው ፡ ኖሯል ። ጊዜ ፡ ጊዜ ፡ አለው ፡ እንጂ ፡ ዛራቸው ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ ቢቆጣ ፡ ሁላችንንም ፡ ይጨርሰን ፡ ነበር ።— ዛሬ ፡ ደሞ ፡ ምን ፡ ጐደለኝ ፡ ምን ፡ አምጡ ፡ ይሆን ፡ የሚለው ? እንደ ፡ ልማዳቸው ፡ ከሚያስጨርሱን ፡

በፊት ፡ ያንኑ ፡ ስም ፡ አይጠሬን ፡ ጐትተው ፡ ምክንያቱን ፡ አይጠይቁም ? አሉ ።—

« ስም ፡ አይጠሬ ፡ ደሞ ፡ ምንድነው ? » ትለዋለች ፡ ፍሬዋ ፡ በተቆጣ ፡ አንደበት ።

- - - ስም ፡ አይጠሬ ፡ የምሥጢር ፡ ስም ፡ ነው ፡ ሠይጣን ፡ ለማለት ፤ እና ፡ ይኸውልሽ ፡ ነገሩ ፡ ሁሉ ፡ ገረመኝ ። ስም ፡ አይጠሬም ፡ ማን ፡ እንደሆነ ፡ ለማወቅ ፡ ፈለግሁ ። ግን ፡ ወዲያ ፡ ወዲህም ፡ ብል ፡ ማንም ፡ አልነገረኝም - - -

« ለምን ፡ ሴትዮዋን ፡ አልጠየቅሃቸውም - - ?

« አይነግሩኝም ፡ ነበር - -

« በምን ፡ ዐወቅህ ፡ ሳትጠይቃቸው ፡ በፊት » አጣሁ ፡ ወሮታ ፡ የሚነጋገሩበት ፡ ነገር ፡ ስለምን ፡ እንደሆነ ፡ ሊገባት ፡ አልቻለም ፤ ስለ ፡ ፍቅር ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ ጋብቻ ፡ ሳይሆን ፡ አይቀርም ፡ በማለት ፡ ግን ፡ ልቧ ፡ ገንግኗል ።

- - - አይነግሩኝም ፡ ነበር ፡ ብቻ ፡ ምን ፡ አለፋሽ--እና ፡ ይኸውልሽ ፡ ዝም ፡ ብዬ ፡ ወደ ፡ መኝታዬ ፡ ሄድሁ ።— ሌሊት ፡ አንድ ፡ ሁለት ፡ እመም ፡ እንቅልፍ ፡ እንዳሳለፍሁ ፡ አሽከሮች ፡ ሲያጉተመትሙ ፡ ሰማሁ ። ስም ፡ አይጠሬ ! ስም ፡ አይጠሬ ! ጌቶች ፡ ስም ፡ አይጠሬን ፡ ይጠራሉ ፡ ሲሉ ። ለማየት ፡ ንጉቻለሁና ፡ ተነሣሁ ። ነገር ፡ ግን ፡ ከኋላዬ ፡ አንድ ፡ ጠንካራ ፡ እጅ ፡ ወደ ፡ ነበርኩበት ፡ ጐትቶ ፡ በደረቴ ፡ ደፋኝ ። ደነገጥሁ ። ስም ፡ አይጠሬ ፡ መሰለኝ ። መለስ ፡ ብዬ ፡ እንዳላየውም ፡ ፈራሁት - - -

« መለስ ፡ ብለህ ፡ ማየት ፡ ነበረብህ - - -

- - - የለም ፡ ፈራሁ ፤ ያረፈብኝ ፡ እጅ ፡ ከላዬ ፡ አልተነሣም ፤ እያደር ፡ ከበደኝ ፤ ጩህጩህ ፡ አለኝ — ጮኩኝ !

« ጮህህ - - - ? ! ! !

- - - አዎ ፡ ጮኩኝ ፤ ያረፈብኝ ፡ እጅም ፡ ከላዬ ፡ ተነሣ - -

« አዬ ፡ ወንድ ፡ አትባልም - - ! » አጣሁ ፡ ወሮታ ፡ ድንግጥ ፡ ብላ ፡ ዓይኗ ፡ ያጕረጥና ፡ አፏን ፡ ትይዛለች ።

- - - መለስ ፡ ብል ፡ ከኋላዬ ፡ ምንም ፡ ነገር ፡ የለም ።—አንድ ፡ ሁለት ፡ እረኞች ፡ ራቅ ፡ ብለው ፡ ቆመዋል ። እኔ ፡ ግን ፡ የሆንኩትን ፡ ለመናገር ፡ አልቻልኩም - - -

« ዋጋ ፡ አልነበረውም ‘ ጅብ ፡ ከሄደ ፡ ውሻ ፡ ጮኸ ’ ሳይሄድ ፡ በፊት ፡ መለስ ፡ ብለህ ፡ ማየት ፡ ነበረብህ - - -

- - - ከዚያ ፡ ብቻ ፡ ይኸውልሽ ፡ ከእረኞቹ ፡ አንዱ ፡ ጠጋ ፡ አለኝ - - -

« ሞትና ፡ ሕይወት ፡ ድንቁርናና ፡ ዕውቀት ፡ ይላል ፡ አደፍርስ - - - በ ቃኝ ፡ እንግዲህ ፡ እባክህ - - ! ስለ ፡ ሠይጣኑ ፡ ጨርሰህ ፡ የለም ? ጨርሰ ሃልኮ ፡ ሳታየው ፡ ቀርተሃል - - -

- - - ምነው ፡ ብታስጨርሽኝ ! ገና ፡ መጀመሪ ፡ ነው ፡ የምን ፡ መጨ ረስ - - ! እና ፡ ታዲያ ፡ ይኸ ፡ እረኛ ፡ የጮኩብትን ፡ ምክንያት ፡ ጠየ ቀኝ ። መልስ ፡ ግን ፡ አላገኘም ። ቅዝቃት ፡ ቃኘኮትህ ፡ ይሆናል ፡ አለኝ ። በመቀጠልም ፡ ጌቶች ፡ ሥራ ፡ ይዘዋልና ፡ ማንም ፡ ወደ ፡ በረት ፡ እንዳ ይወጣ ፡ ብሎ ፡ ተናገረ ። እኔ ፡ ግን ፡ ስም ፡ አይጠሬን ፡ ለማየት ፡ የነበ ረኝ ፡ ጉጉት ፡ እንዲያውም ፡ እጁን ፡ ካሳረፈብኝ ፡ ወዲህ ፡ እየገነነ ፡ ሄዶ ፡ ስለነበረ ፡ ሽንቴንም ፡ ለመሽናት ፡ ልወጣ ፡ አልችልምይ ፡ ብዬ ፡ ጠየቅ ሁት - - -

« መጠየቅ ፡ አልነበረብህም ፤ እሱን ፡ ተደብቀህ ፡ ልታይ ፡ የምትች ልበትን ፡ መንገድ ፡ ነበር ፡ መፈለግ ፡ የነበረብህ - - -

- - - ምን ፡ መሆንሽ ፡ ነው - ልጅ ፡ ነኝ - ይኸን ፡ መርሳት ፡ የለብሽም - - የሆነው ፡ ሆኖ ፡ እሱም ፡ መልስ ፡ አልሰጠኝም ። ዝም ፡ ብሎ ፡ ወደ ፡ ጓዳ ፡ ገባ ። ከዚያም ፡ ቆሬ ፡ መሳይ ፡ መክፈያ ፡ ይዞ ፡ መጥቶ ፡ እዚህ ፡ ላይ ፡ ክፈ ለው ፡ አለኝ - - -

« ከፈልከው ! »

- - - ለመውጣት ፡ አልቻልኩም ፡ ማለት ፡ ነው - - - እረኛው ፡ ኮቴ ውን ፡ ሳያሰማ ፡ እንደ ፡ ሰላቢ ፡ ተመልሶ ፡ ወጣ ። ሁለቱ ፡ እረኞችና ፡ እኔ ፡ ቀረን ። ስለ ፡ ስም ፡ አይጠሬ ፡ እነሱን ፡ መጠየቅ ፡ ግድ ፡ ሆነብኝ ፤ ጠየቅ ኋቸው ።— እነሱም ፡ በሹክሹክታ ፡ አባ ፡ ድብልብሌ ፡ የሚባል ፡ ቁጣው ፡ ከባድ ፡ ልግስናው ፡ ትልቅ ፡ የሆነ ፡ የቀያችን ፡ ንጉሥ ፡ ነው ፡ አሉኝ ። ገረመኝ - - - -

« እኔ ፡ ገና ፡ አልገረመኝም - - -

- - - እውነትሽን ፡ ነው ፤ የሰጡኝ ፡ መግለጫ ፡ አላጠገበኝም ።—ርግጥ ፡ ስለ ፡ አባ ፡ ድብልብሌ ፡ ከዚያ ፡ በፊት ፡ ሰምቻለሁ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ አላየሁ ትም - - እንደሰማሁት ፡ ከሆነ ፡ አባ ፡ ድብልብሌ—አጥር ፡ የማያግደው ፡

መዝጊያ ፡ የማይመልሰው ፡ ሲያስኘው ፡ ከጣራ ፡ የሚወርድ ፡ ሲያስኘው ፡ ከመሬት ፡ የሚወጣ ፡ ቢበላ ፡ የማይጠግብ ፡ ዙሪያ ፡ ሆድ ፡ በተለይ ፡ የል ጆችና ፡ የከብቶች ፡ ጠላት ፡ ነው ።— እናቴ ፡ እንዳወራችልኝ ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ ያየው ፡ እንደሌለና ፡ ማንም ፡ ደግሞ ፡ ወዳጅ ፡ እንደማያደርገው ፡ ነበር ። ግን ፡ አሁን ፡ እረኞቹ ፡ እንደሚያወሩት ፡ ከሆነ ፡ ጌቶች ፡ እየጠሩ ፡ ያነጋግሩታል ።— ለማየት ፡ እችላለሆይ ፡ ብዬ ፡ ጠየቅኋቸው - - -

« ለምን ፡ ራስህ ፡ መንገድ ፡ ፈልገህ ፡ አታየውም ? ለምን ፡ ትጠይቃ ቸዋለህ - - - ?

- - - ካየኸውማ ፡ ዓይንህን ፡ ያሳውርሃል—ሰውነትህን ፡ ያሳብጥሃል ፡ አሉኝ ። ወዲያውም ፡ ይህን ፡ ስንነጋገር ፡ ከሁሉም ፡ በዕድሜ ፡ ከፍ ፡ ያለው ፡ እረኛ ፡ ከመኻታው ፡ ተነሥቶ ፡ እያዛጋ ፡ መጣ ። ሁለቱን ፡ እረ ኞች ፡ እየቦታቸው ፡ ተመልሰው ፡ ሄደው ፡ እንዲተኙ ፡ አዘዛቸው ። እሱ ፡ ግን ፡ ከኔ ፡ ጋር ፡ ቀረ ።— የሚሉህን ፡ አትስማቸው ፤ እንዲያው ፡ ነው ፡ የሚ ያስፈራሩህ ፡ አለኝ ። ለኔ ፡ የነበረውንም ፡ መልካም ፡ አስተያየት ፡ በመመ ልከት ፡ እሱንም ፡ ስለ ፡ ስም ፡ አይጠሬ ፡ ጠየቅሁት — በሹክሹክታም ፡ እንዲህ ፡ እያለ ፡ ሊነግረኝ ፡ ጀመረ - - -

« ስማ ፡ ስማ ፡ በላይ ፡ እኔ ፡ የምፈልገው ፡ ያየኸውን ፡ እንድትነግረኝ ፡ ነው ፤ የመስማት ፡ የመስማት ፡ ከሆነ ፡ ካንተ ፡ የበለጠ ፡ ስምቻለሁ—በመ ድረክ ፡ ላይ ፡ ምታት ፡ ሲፈስ ፡ አይቻለሁ ፡— ስለ ፡ እስማትም ፡ ብዙ ፡ አንብቢያለሁ ። ያየኸውን ፡ ንገረኝ ፤ አለዚያ ፡ በከንቱ ፡ ጊዜዬን ፡ አታስ መሽብኝ - - -

- - - ስም ፡ አይጠሬ ፡ ብዙ ፡ ዓይነት ፡ ነው - - - ሲል ፡ ጀመረ ፤ የባሕር ፡ ውስጥ ፡ ስም ፡ አይጠሬ ፡ አለ ። የአየር ፡ ስም ፡ አይጠሬ ፡ አለ ። የጉድፍ ፡ ስም ፡ አይጠሬ ፡ አለ ። ሁሉም ፡ ለየብቻ ፡ ሥራ ፡ ሥራ ፡ አላቸው ። በጎይለኝነት ፡ የሚበልጠው ፡ ግን ፡ የአየሩ ፡ ስም ፡ አይጠሬ ፡ ነው ፡ አለኝ ። — ቀጠለም ፡ — የጌቶች ፡ አባት ፡ መምሬ(ማነው - - ስማቸውን ፡ እረሳሁት ) የሰማውንም ፡ የባሕሩንም ፡ ስም ፡ አይጠሬ ፡ ይጐትቱ ፡ ነበር ። በዚህ ፡ ላይ ፡ ድምበር ፡ ገፊ ፡ ሰላቢ ፡ ነበሩ ፡ ይባላል ። ነፍሳቸውን ፡ ይማ ረውና ፡ ሲቀበሩ ፡ መቃብራቸው ፡ መቅን ፡ ገባ ፡ ይሉናል ። እስከዛሬ ፡ ድረስ ፡ መቃብራቸው ፡ ይጮሃል - - -

« ለምንድነው ፡ የሚጮኸው ? » ትጠይቀዋለች ፡ ፍሬዋ ፤ የመጮሁ ፡ ነገር ፡ በጣም ፡ የገረማት ፡ በሚያስመስል ፡ አመለካከት ፡ እየተመለከተች ።

- - - እኔም ፡ ጠይቄው ፡ ነበር ፡ የዚህኑ ፡ ዓይነት ፡ ጥያቄ ፡ እረኛውን ፡ እና ፡ ባለማወቄ ፡ እየተገረመ ፡ እንደሚከተለው ፡ ነገረኝ- - ብቻ ፡ ለሰው ፡ እንዳትነግሪ ፡ መሬት ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ ሬሳቸውን ፡ አልተቀበለችውም ። በየጊዜው ፡ ልትተፋው ፡ ትሞክራለች ። እንደተቀበሩማ ፡ ሰዓት ፡ ሦስት ፡ ጊዜ ፡ እየተፋቻቸው ፡ ታቦት ፡ ወጥቶ ፡ መሬት ፡ ተገዝታ ፡ ነው ፡ የተቀበለቻቸው ። ከዚያም ፡ ጀምሮ ፡ ቁልቁል ፡ መቀመቅ ፡ ይኸው ፡ እስከዛሬ ፡ ይወርዳሉ ፤ እና ፡ መቃብራቸው ፡ የሚጮኸው ፡ ቁልቁል ፡ ወደ ፡ አንጦረጦስ ፡ ስለሚወርድ ፡ ነው ፡ አለኝ - - -

« ብቻ ፡ ምን ፡ አለፋህ ፡ ከረኛው ፡ ጋር ፡ ስትጨቃጨቅ ፡ ሰውዬው ፡ እውጪ ፡ የሚሠሩትን ፡ ነገር ፡ አላየኸውም ፡ ማለት ፡ ነው - - ዋናውን ፡ ነገር- - - ብታየው ፡ ኖሮ ፡ ይኸ ፡ ሁሉ ፡ ዝባዝንኬ - - -

- - - ላመጣልሽኮ ፡ ነው - - እና ፡ ታዲያ ፡ በመከያው - - - ምን ፡ ነካቸውና ፡ ሞቱ ? ታመው ፡ ነወይ ፡ ብዬ ፡ ጠየቅሁት ። እሱም - - -

« እኔ ፡ ልንገርህ ፡ ስለ ፡ ሰውዬው ፡ አባት ፡ ስትጨርስ ፡ ደግሞ ፡ ስለ ፡ ሰውዬው ፡ እንደምትጀምር ፡ ይገባኛል - - - እና ፡ ይኸን ፡ እንደጨረስህ ፡ ወደ ፡ ፍሬ ፡ ነገሩ ፡ ካልሄድህ - - - ምናለፋህ ፡ ብቻ ፡ መቆራረጣችን ፡ ነው - - - ምንድነው ፡ ተምረሃል - - - መንግሥት ፡ ተማሪ ፡ ቤት ፡ ገብተህ — እንደምን ፡ ከረሙ ፡ ቤት ፡ ሰቡስ ፡ ልጆቹስ ፡ ከብቶቹስ ፡ የወለደችውስ ፡ ላም ፡ እርሻውስ ፡ ጥጃውስ - - የሚል ፡ ዓይነት ፡ አነጋገር ፡ መናገር - - - » ትለዋለች ፡ ንዴቷ ፡ በድምፅዋ ፡ ጉልህነትና ፡ ንዝረት ፡ እየታየ ።—

- - - አሄሄ - - ገና ፡ ልጅ ፡ ነህ ፡ አለኝ ፡ እሱም ፡ በመቀጠል ። እሳቸው ፡ ሞቱ ፡ አይባልም ፤ ስም ፡ አይጠሬ ፡ ጠራቸው ፡ ነው ።— አንድ ፡ ወራት ፡ ሰብላቸውን ፡ ተምችና ፡ አንበጣ ፡ ተጫውቶበት ፡ ነበር ። ከዚያም ፡ የተነሣ ፡ ከመዐቱ ፡ እንዲያወጣቸው ፡ ስም ፡ አይጠሬን ፡ ለመጠየቅ ፡ ፈለጉ ። ነፍሳቸውን ፡ ይማረውና ፡ ባለቤታቸውን ፡ ለስም ፡ አይጠሬ ፡ የሚያስፈልገውን ፡ ምስ ፡ ሁሉ ፡ እንዲቋጥሩላቸው ፡ ካደረጉ ፡ በኋላ ፡ የወንዙ ፡ ስም ፡ አይጠሬ ፡ ለመቆጣቱ ፡ በሕልም ፡ ተገልጾለቸው ፡ ነበርና ፡ እወንዝ ፡ ወረዱ ። በነገርህ ፡ ላይ ፡ ያባትዮው ፡ ሁዳድ ፡ የነበረው ፡ መኖሪያቸው ፡ እዚያ ፡ ማዶ ፡ ነበር ። አባትዮው ፡ ከሞቱ ፡ በኋላ ፡ ነው ፡ እኝህ ፡ ልጃቸው ፡ ሸሽተው ፡ እዚህ ፡ የሠሩት ፡— ከዚያ ፡ ይኸውልህ ፡ እወንዝ ፡ ወርደው ፡ ስም ፡ አይጠሬን ፡ ከጠሩት ፡ በኋላ ፡ የሚፈልጉትን ፡ ሁሉ ፡ አግኝተው ፡

ወደ ፡ ቦታው ፡ እንዲመለስ ፡ ምሱን ፡ ሊሰጡት ፡ ስልቻቸውን ፡ ቢፈቱ ፡ በጣም ፡ ተፈላጊ ፡ የነበረው ፡ ሪሚጦ ፡ ተረስቶ ፡ አገኙት --- መኖስ ፡ አይ ጣል ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ምን ፡ ይኳል -- ይናደድልህና ፡ አረባይቶ ፡ አረባይቶ -- ለጳቸው ፡ ኖሮ ---

« ሞትና ፡ ሕወይት ፡ ድንቁርናና ፡ ዕውቀት ፡ የሚሉ ፡ እንጋገር --- አደ ባይቶ ፡ አደባይቶ ፡ ለጳቸው ፡ ኖሮ --- እጂ --- ! » ፍሬዋ ፡ መቀ መጡ ፡ ይደክማትና ፡ ተነሥታ ፡ ያጣው ፡ ወሮታን ፡ ጭስ ፡ ቤት ፡ ተደግፋ ፡ ትቆማለች ።— አጣው ፡ ወሮታ ፡ እንዳትታይ ፡ ሸሸት ፡ ትላለች ።—በላይ ፡ ፍሬዋ ፡ የምትሄድ ፡ መስሉት ፡ ቀና ፡ ብሎ ፡ ያያትና ፡ አለመሄዷን ፡ ሲያ ረጋግጥ ፡ ታሪኩን ፡ ይቀጥላል --- እርቆ ፡ እየተመለከተ ።

--- በቃሬዛ ፡ እቤት ፡ ያመጧቸዋል ፡፡ ምን ፡ ይሆናል --የቀበሯ ፡ ለት ፡ ሞት ፡ አይተኙም -- ጠላትህ ፡ ይታሠርና ፡ በጠፍር ፡ እንደ ፡ ታሥሩ ፡ ካሌጋ ፡ ሳይወርዱ ፡ በውኑታቸው ፡ ሁሉ ፡ አባ ፡ ሰንጋ ፡ እንደ ፡ ያዘው ፡ አባብጦ ፡ በመጨረሻ ፡ ተገላገሉ ፡ እልሃለሁ --- እሳቸው ፡ ከሞቱ ፡ በኋላ ፡ የቀንድ ፡ ከብቱንም ፡ በጉንም ፡ ፍየሉንም ፡ እየተከታተለ ፡ ስም ፡ አይጠሬ ፡ ፈጀው ። ባለቤታቸውንም ፡ እግራቸውን ፡ እስከ ፡ ሙሃሊታቸው ፡ አሳብጦ ፡ እየበላ ፡ እየቆረጠማቸው ፡ እትንን ፡ ደግፉኝ ፡ እግሬን ፡ ጨብጡልኝ ፡ እያሉ ፡ ለሰ ፈር ፡ አስቸግረውና ፡ አሰልችተው ፡ መሞት ፡ አይቀርምና ---

« ተገላገሉ ! አለህ --

--- ሞቱ ፡ አለኝ ። በዚያን ፡ ጊዜ ፡ እኝህ ፡ የኛ ፡ ጌቶች ፡ እዚህ ፡ አልነ በሩም ። አባትየው ፡ በንጉሥ ፡ ዘንድ ፡ የታወቁ ፡ አቅኚ ፡ ስለነበሩ ፡ ቤተ መንግሥት ፡ ወስዶ ፡ ያሳድጋቸው ፡ ነበር ። ገና ፡ ዕድሜያቸው ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ሲሆነው ፡ ጀምሮ ። አባትና ፡ እናታቸው ፡ ካለቁ ፡ በኋላ ፡ ነው ፡ እዚያው ፡ አድገው ፡ ተሾመው ፡ ተሸልመው ፡ በመንግሥቱ ፡ ሁዳድ ፡ ላይ ፡ አዛዥ ፡ ሆነው ፡ የመጡት ። ከደህና ፡ ተወለድ ፡ ወይም ፡ ከድኀና ፡ ተጠጋ ፡ እንዲሉ ፡ ዱሮም ፡ ባባታቸው ፡ የተደላደሉ ፡ ጌታ ፡ ነበሩ ፡ ንጉ ሡም ፡ ጨመሩላቸው --- አሰለቸሁህ ፡ መሰለኝ ፡ በንግግሬ ፡ አለኝ ---

« -- የለም ፡ የለም — ትንሽ ፡ ደግሞ ፡ ስለሚስትዮዋ ፡ አስተዳደግ ፡ ንገረኝ ፡ አልኩት ---

--- እኔምኮ ፡ ልለው ፡ ነው ፤ ምን ፡ ማለትሽ ፡ ነው ፤ ብዙ ፡ ነው ፡ ያወጋነው -- ትኩር ፡ ብዬ ፡ ተመለከትሁት ---



« ዓይኑን ፡ ቀሎ ፡ ስብር ፡ አረገ
--- ትኩር ፡ ብሎ ፡ ተመለከተ
ድንገት ፡ አሁን ፡ ጌቶች ፡ የሚጠሩትን
አሰበት ፡ ያልኩት ፡ — እንገተን ፡ በበር
ቀኝ ፡ ብሎኝ ፡ ወጣ ። ከትንሽ ፡ ጊዜ ፡ በኋ
ሁለት ፡ ቀምበጦች ፡ ይዟል ። አዲስ ፡ የ
ሰጠኝ ፡ አንዱን ፡ ራሱ ፡ ያዘ ። ተከተለኝ
ችን ፡ እየዳሠን ፡ አንድ ፡ እህሉ ፡ ተጣ
ሪቅ ፡ ቦታ ፡ ደረስን ። ባለቤቱ ፡ እፍግ ፡ መ
ሐፍ ፡ ያንባሉ ። እሳቸውም ፡ ባንዱ ፡ እ
ቸውን ፡ ናቸው ፡ — እረኛው ፡ ልጅ ፡ እ
ጥርቅም ፡ አድርገህ ፡ ያዝ ፡ ይነጥቁሃል
ባት ፡ የሚያስት ፡ ወይም ፡ አስጸያፊና
ስታይ ፡ እንዳትስት ፤ የሳቅህ ፡ እንደሆ
ቀምበጡን ፡ ጥርቅም ፡ አድርጊ ፡ ይገዘ
ባጠገባቸው ፡ ሁለት ፡ ጠያይሞችና
ቤቱ ፡ እጃቸውን ፡ እየዘረጉ ፡ ስም ፡ በመ
ጀመር ። ሦስቱ ፡ ሰዎች ፡ እያንዳንዳቸው
ላይ ፡ አስቀመጡት ። ወዲያውም ፡ እግረ
አትል ፡ የወገብ ፡ ንቅናቄ ፡ እያሰዩ ፡ በፍ
ይጨፍሩ ፡ ይጀሯጡ ፡ ጀመር ። ሦስቱም
ከመያዛቸውና ፡ ሐፍረታቸው ፡ ላይ ፡ ት
ቸው ፡ በስተቀር ፡ ራቁታቸውን ፡ ናቸው
ትመስላለች ። በጥርስና ፡ በጥርሷ ፡ መካ
ሙዳ ፡ ሥጋ ፡ ነክሳ ፡ ይዛለች ። ጥቁሩ ፡
ርሱና ፡ በጥርሱ ፡ መካከል ፡ ነክሶ ፡ ይዟል
ልዩ ፡ ልዩ ፡ አንጉል ፡ የሰውነት ፡ ንቅ
ልዩ ፡ ዓይነት ፡ የማከመታተር ፡ ሁኔታ
ያው ፡ ይኸው ፡ ሦስተኛው ፡ ሰውዬ ፡
አፈር ፡ እየዘገነ ፡ ከነድንጋዩና ፡ ጠጠሩ ፡
ላይ ፡ ይበትን ፡ ጀመር ። እንደጨረሰም
ጡበት ፡ ተመለሱ ፡— ባለቤቱ ፡ ቢሆ
የጥድፊያ ፡ ነበር ፡ እንዲያውም ፡ አነባበ
ታላቅ ፡ ድምፅ ፡ እንሰማ ፡ ጀመር ፡ ትር

ወደ ፡ ቦታው ፡ እንዲመለስ ፡ ምሱን ፡ ሊሰጡት ፡ ስልቻቸውን ፡ ቢፈቱ ፡ በጣም ፡ ተፈላጊ ፡ የነበረው ፡ ሪሚጦ ፡ ተረስቶ ፡ አገኙት - - - መቼስ ፡ አይ ጣል ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ምን ፡ ይሏል -- ይናደድልሀና ፡ አረባይቶ ፡ አረባይቶ -- ለቋቸው ፡ ኖሮ - - -

« ሞትና ፡ ሕወይት ፡ ድንቁርናና ፡ ዕውቀት ፡ የሚሉ ፡ አነጋገር - - - አደ ባይቶ ፡ አደባይቶ ፡ ለቋቸው ፡ ኖሮ - - - እሺ - - - ! » ፍሬዋ ፡ መቀ መጡ ፡ ይደክማትና ፡ ተነሥታ ፡ ያጣሁ ፡ ወሮታን ፡ ጭስ ፡ ቤት ፡ ተደግፋ ፡ ትቆማለች ።— አጣሁ ፡ ወሮታ ፡ እንዳትታይ ፡ ሸሸት ፡ ትላለች ።—በላይ ፡ ፍሬዋ ፡ የምትሄድ ፡ መስሎት ፡ ቀና ፡ ብሎ ፡ ያያትና ፡ አለመሄዷን ፡ ሲያ ረጋግጥ ፡ ታሪኩን ፡ ይቀጥላል - - - አርቆ ፡ እየተመለከተ ።

- - - በቃሬዛ ፡ እቤት ፡ ያመጧቸዋል ። ምን ፡ ይሆናል --የቀበጡ ፡ ለት ፡ ሞት ፡ አይገኝም -- ጠላትህ ፡ ይታሠርና ፡ በጠፍር ፡ እንደ ፡ ታሠሩ ፡ ካልጋ ፡ ሳይወርዱ ፡ ሰውነታቸው ፡ ሁሉ ፡ አባ ፡ ሰንጋ ፡ እንደ ፡ ያዘው ፡ አባብጦ ፡ በመጨረሻ ፡ ተገላገሉ ፡ እልሃለሁ - - - እሳቸው ፡ ከሞቱ ፡ በኋላ ፡ የቀንድ ፡ ከብቱንም ፡ በጉንም ፡ ፍየሉንም ፡ እየተከታተለ ፡ ስም ፡ አይጠሬ ፡ ፈጀው ። ባለቤታቸውንም ፡ እግራቸውን ፡ እስከ ፡ ሙሃሊታቸው ፡ አሳብጦ ፡ እየበላ ፡ እየቆረጠማቸው ፡ አቅኑኝ ፡ ደግፉኝ ፡ እግሬን ፡ ጨብጡልኝ ፡ እያሉ ፡ ለሰ ፈር ፡ አስቸግረውና ፡ አሰልችተው ፡ መሞት ፡ አይቀርምና - - -

« ተገላገሉ ! አለህ - -

- - - ሞቱ ፡ አለኝ ። በዚያን ፡ ጊዜ ፡ እኝህ ፡ የኛ ፡ ጌቶች ፡ እዚህ ፡ አልነ በሩም ። አባትየው ፡ በንጉሥ ፡ ዘንድ ፡ የታወቁ ፡ አቅኚ ፡ ስለነበሩ ፡ ቤተ መንግሥት ፡ ወስዶ ፡ ያሳድጋቸው ፡ ነበር ። ገና ፡ ዕድሚያቸው ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ሲሆነው ፡ ጀምሮ ። አባትና ፡ እናታቸው ፡ ካለቁ ፡ በኋላ ፡ ነው ፡ እዚያው ፡ አድገው ፡ ተሾመው ፡ ተሸልመው ፡ በመንግሥቱ ፡ ሁዳድ ፡ ላይ ፡ አዛዥ ፡ ሆነው ፡ የመጡት ። ከደህና ፡ ተወለድ ፡ ወይም ፡ ከደጎና ፡ ተጠጋ ፡ እንዲሉ ፡ ዱሮም ፡ ባባታቸው ፡ የተደላደሉ ፡ ጌታ ፡ ነበሩ ፡ ንጉ ሡም ፡ ጨመሩላቸው - - - አሰለቸሁህ ፡ መሰለኝ ፡ በንግግሬ ፡ አለኝ ---

« - - የለም ፡ የለም — ትንሽ ፡ ደግሞ ፡ ስለሚስትዮዋ ፡ እስተዳደግ ፡ ንገረኝ ፡ አልኩ.ው - - -

- - - እኔምኮ ፡ ልለው ፡ ነው ፤ ምን ፡ ማለትሽ ፡ ነው ? ብዙ ፡ ነው ፡ ያወጋነው - - ትኩር ፡ ብዬ ፡ ተመለከትሁት - - -

« ዓይኑን ፡ ቶሎ ፡ ስብር ፡ አረገ - -

- - - ትኩር ፡ ብሎ ፡ ተመለከተኝ ፡ እሱም — ከዚያ ፡ ነው ፡ ድንገት ፡ አሁን ፡ ጌቶች ፡ የሚጠሩትን ፡ ስም ፡ አይጠሬ ፡ ብናይ ፡ ምን ፡ አለበት ፡ ያልኩት ፡ — እንገቱን ፡ ሰበር ፡ አድርጐ ፡ ትንሽ ፡ አሰበ ። ጠብቀኝ ፡ ብሎኝ ፡ ወጣ ። ከትንሽ ፡ ጊዜ ፡ በኋላ ፡ ተመለሰ ። በቡልኮው ፡ ውስጥ ፡ ሁለት ፡ ቀምበጦች ፡ ይዟል ። አዲስ ፡ የተቀጠፉ ፡ ነበሩ ። አንዱን ፡ ለኔ ፡ ሰጠኝ ፤ አንዱን ፡ ራሱ ፡ ያዘ ። ተከተለኝ ፡ አለኝ ። ተከተልኩት ። በደረታችን ፡ እየዳህን ፡ አንድ ፡ እህሉ ፡ ተሚጠ ፡ ደረባው ፡ እመሬት ፡ እተቀመጠ ፡ ሪቅ ፡ ቦታ ፡ ደረስን ። ባለቤቱ ፡ እፍግ ፡ መቆለያው ፡ ዲብ ፡ ላይ ፡ ቆመው ፡ መጽሐፍ ፡ ያነባሉ ። እሳቸውም ፡ ባንዱ ፡ እጃቸው ፡ ቀምበጥ ፡ ይዘዋል ። ብቻቸውን ፡ ናቸው ፡— እረኛው ፡ ልጅ ፡ እጄን ፡ ነካ ፡ አደረገኝና ፡ ቀምበጡን ፡ ጥርቅም ፡ አድርገህ ፡ ያዝ ፡ ይነጥቁሃል ፡ አለኝ ። በመቀጠልም ፡ ምናልባት ፡ የሚያስቅ ፡ ወይም ፡ አስጸያፊና ፡ መጥፎ ፡ መጥፎ ፡ ሥራ ፡ ሲሠሩ ፡ ስታይ ፡ እንዳትስቅ ፤ የሳቅህ ፡ እንደሁ ፡ በጥፊ ፡ ያጠናብሩሃል ፡ አለኝ ። ቀምበጡን ፡ ጥርቅም ፡ አድርጌ ፡ ይዤ ፡ እሳቸውን ፡ እመለከት ፡ ጀመር ። ባጠገባቸው ፡ ሁለት ፡ ጠያይሞችና ፡ አንድ ፡ ጥቁር ፡ ሰው ፡ አለፉ ። ባለቤቱ ፡ እጃቸውን ፡ እየዘረጉ ፡ ስም ፡ በመጥራት ፡ አኳኋን ፡ በኃይል ፡ ያነቡ ፡ ጀመር ። ሦስቱ ፡ ሰዎች ፡ እያንዳንዳቸው ፡ የያዙትን ፡ እቃ ፡ እፍጉ ፡ ቁልል ፡ ላይ ፡ አስቀመጡት ። ወዲያውም ፡ እግራቸውን ፡ እያነሡ ፡ አንዳንዴም ፡ አጉል ፡ የወገብ ፡ ንቅናቄ ፡ እያሳዩ ፡ ባፋቸው ፡ ይመስለኛል ፡ እያንዛረጡ ፡ ይጨፍሩ ፡ ይሯሯጡ ፡ ጀመር ። ሦስቱም ፡ ሰዎች ፡ ቀምበጥ ፡ በጃቸው ፡ ከመያዛቸውና ፡ ሐፍረታቸው ፡ ላይ ፡ ቅጠል ፡ ዓይነት ፡ ነገር ፡ ከማሠራቸው ፡ በስተቀር ፡ ራቁታቸውን ፡ ናቸው ። ከመካከላቸው ፡ አንዲቷ ፡ ሴት ፡ ትመስላለች ። በጥርስና ፡ በጥርሷ ፡ መካከል ፡ ፊቷን ፡ የሚሸፍን ፡ ትልቅ ፡ ሙዳ ፡ ሥጋ ፡ ነክሳ ፡ ይዛለች ። ጥቁሩ ፡ ሰውዬ ፡ ደግሞ ፡ ወምበርቲ ፡ በጥርሱና ፡ በጥርሱ ፡ መካከል ፡ ነክሶ ፡ ይዟል ። ሦስተኛው ፡ ግን ፡ ዋና ፡ ሥራው ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ አጓጉል ፡ የሰውነት ፡ ንቅናቄ ፡ ማሳየትና ፡ ፊቱን ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ዓይነት ፡ የማኮመታተር ፡ ሁኔታ ፡ መለዋወጥ ፡ ብቻ ፡ ነበር ። ወዲያው ፡ ይኸው ፡ ሦስተኛው ፡ ሰውዬ ፡ በኃይል ፡ ጮኸ ። ከዙሪያውም ፡ አፈር ፡ እየዘገነ ፡ ከነድንጋዩና ፡ ጠጠሩ ፡ ከነፍጉ ፡ ወደ ፡ እኛ ፡ በኩል ፡ ቤቱ ፡ ላይ ፡ ይበትን ፡ ጀመር ። እንደጨረሰም ፡ ሦስቱም ፡ አብረው ፡ ወደመጡበት ፡ ተመለሱ ።— ባለቤቱ ፡ ቢሆን ፡ ንባባቸውን ፡ አላቋረጡም ፤ የጥድፊያ ፡ ነበር ፡ እንዲያውም ፤ አነባበባቸው ። — ብዙ ፡ ቆይተውም ፡ ታላቅ ፡ ድምፅ ፡ እንሰማ ፡ ጀመር ፤ ትርጉሙ ፡ የማይገባ ፡ የሚያጓራ ፡ የተ

ናገረም ፡ የሚመስል — ከወዴት ፡ እንደሚመጣ ፡ ለማወቅ ፡ የማይቻል — የሰውዬው ፡ ንባብ ፡ እንኳ ፡ አይሰማም ፡ ነበር — ሳይታሰብ ፡ ባለቤት ዮው ፡ መጽሐፉን ፡ እንደያዙ ፡ ወደቁ ። አሽከራቸው ፡ ራቅ ፡ ብሎ ፡ ይጠብቃቸው ፡ ኖሮ ፡ አነሣና ፡ ደግፎ ፡ ወደ ፡ ቤት ፡ አገባቸው ።— አብሮኝ ፡ የወጣውም ፡ እረኛ ፡ ዛሬ ፡ አልተሳካላቸውም ፡ መሰለኝ ፡ ሳያውን ፡ እየመኙታችን ፡ እንመለስ ፡ ብሎኝ ፡ እንዳመጣጣችን ፡ እየዳህን ፡ እየመኙታችን ፡ ደረስን ።- ስለ ፡ ሦስቱ ፡ ሰዎች ፡ ጠየቅሁት ፤ ምናልባት ፡ የሠይጣኑ ፡ አሽከሮች ፡ ይሆናሉ ፡ አለኝ - - በመቀጠልም ፡ እኔም ፡ የመጀመሪያ ፡ ጊዜዬ ፡ ነው ፤ አንተን ፡ አይቼ ፡ ነው ፡ ተደፋፍሬ ፡ ላይ ፡ የመጣሁት ፤ እስከ ፡ ዛሬ ፡ አይቼ ፡ አላውቅም ፡ አለኝ - - - ከዚያ ፡ በኋላ ፡ ትንሽ ፡ ቢያሸልበን ፡ ብለን ፡ ወደየመኙታችን ፡ ሄድን - - -

ፍሬዋ ፡ የማድ ፡ ቤቱን ፡ ግድግዳ ፡ ከለላ ፡ በማድረግ ፡ ሹልክ ፡ ብላ ፡ ኮቴዋ ፡ ሳይሰማ ፡ ወደ ፡ ቤቷ ፡ በር ፡ ታመራለች ።

- - - መንጋት ፡ አይቀርምና ፡ ነጋ ።- ወደባለቤቱ ፡ እልፍኝ ፡ ሄድሁ ።— ባለቤቱ ፡ እንደተኙ ፡ ናቸው ። ያቃስታሉ ። ከጭሰኞቻቸው ፡ አንድ ፡ በዕድሜ ፡ ጠና ፡ ያሉ ፡ አዛውንት ፡ አጠገባቸው ፡ ተቀምጠዋል ። ለሳቸው ፡ ረጅም ፡ ወሬ ፡ ጀምረዋል - -

አጣሁ ፡ ወሮታ ፡ ተደብቃ ፡ ታዳምጥበት ፡ ከነበረው ፡ ከማድ ፡ ቤቱ ፡ ውስጥ ፡ ቀስ ፡ ብላ ፡ ትወጣለች ። ፍሬዋ ፡ ቆማበት ፡ እነበረው ፡ ቦታ ፡ ቆማ ፡ ሳትንቀሳቀስ ፡ ትሰማለች ፤ ፊቷን ፡ ጨምደድ ፡ ለቀቅ ፡ ፈገግ ፡ ኮስተር ፡ ቆጣ ፡ በማድረግ - - የሚናገረው ፡ ነገር ፡ የገባት ፡ አይመስልም ፤ አልተያያዘላትም ።

« - - ቀያችን ፡ አባቴን ፡ አላግባብ ፡ ካጐሳቆላቸው ፡ ወዲህ ፡ እኔ ፡ ሁለተኛ ፡ ከርኩሳን ፡ መናፍስት ፡ ጋር ፡ ምንም ፡ ዓይነት ፡ ግንኙነት ፡ እንዳላደርግ ፡ ምዬ ፡ ይኸው ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ተቀምጬ ፡ ነበር ፡ ይላሉ ፡ ባለቤቱ - - ትላንትና ፡ ማታ ፡ ግን ፡ ጤና ፡ አልነበረኝም ። ሌሊቱንም ፡ ቅዠት ፡ አጠቃኝ ። ስለዚህ ፡ ያረገውን ፡ ያርገኝ ፡ ብዬ ፡ ማላዬን ፡ ጥሼ ፡ ካንድ ፡ ከኃይለኛ ፡ ቅዠት ፡ በኋላ ፡ ሰውነቴ ፡ ሁሉ ፡ በላብ ፡ እንደተጠመቀ ፡ መጽሐፉን ፡ ከተሰቀለበት ፡ አውርጄ ፡ በቂውን ፡ ምስ ፡ ሳላዘጋጅ ፡ ወጣሁኝ ። የባሕሩና ፡ የአየሩ ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ ፡ እስከዚህ ፡ አልዳፈርም ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ የጉድፍ ፡ ልቡሰ ፡ ሥጋ ፡ እንደዚያ ፡ የሚጸረረኝ ፡ አልመሰለኝም ፡ ስለዚህ ፡ ዶሮ ፡ መልሶ ፡ መልሶ ፡ ሲጮህ ፡ ሰውነቴን ፡ ሳላደርቅና ፡ ታጥቤ ፡ ሰውነቴን ፡ ሳላነጻ ፡ ወጣሁኝ ። እንደሚ

ወደው ፡ እንደሚወደውም ፡ ጨዋታውም ፡ ሳይቀርበት ፡ አቀረብኩለት ። እሱ ፡ ግን ፡ እንደ ፡ ነፋስ ፡ ባጠገቤ ፡ እያለፈ ፡ መልስ ፡ ከለከለኝ ። እንዲያውም ፡ በመጨረሻ ፡ ግራ ፡ ጐኔን ፡ ጠቅ ፡ አደረገኝ ፤ ሰውነቴንም ፡ ላብ ፡ አጠመቀኝ ። እንደ ፡ ልቤም ፡ ተገዝናንቼ ፡ ለመቆም ፡ አልቻልኩም - - - በስንት ፡ ፈተና ፡ እንዳልተለመነኝ ፡ ስገነዘብ ፡ መመለሻውን ፡ አንብቤ ፡ ስጨርስ ፡ አዞረኝና ፡ ወደቅሁ ። ከዚያ ፡ በኋላ ፡ ልጆች ፡ አንሥተው ፡ አገቡኝ ፡ መሰለኝ ፡ እኔ ፡ ግን ፡ ነፍሴን ፡ አላውቀውም ፡ ነበር ፡ ሲሉ ፡ ያበቃሉ - - - እና ፡ ይኸውልሽ ፡ ሳይሳካልኝ - - - » እያለ ፡ ፊቱን ፡ ዘወር ፡ ሲያደርግ ፡ አጠገቡ ፡ ቆማ ፡ የነበረችው ፡ ሴት ፡ ቶሎ ፡ ራመድ ፡ ሸተት ፡ ብላ ፡ ወደ ፡ ማድ ፡ ቤት ፡ ስትገባ ፡ ያያታል ። — ሰውነቷ ፡ ይወፍርበታል ። — ልብሷ ፡ አልባሌ ፡ አረማመዷ ፡ የፍራት ፡ ትከሻዋ ፡ ሰፊ ፡ ጀርባዋ ፡ ጐባጣ ፡ ይሆንበታል ። ተለዋወጠችበት ፡ ፍሬዋ ። — ሁኔታው ፡ አልገባህ ፡ አለው ። ያ ፡ በልጅነቱ ፡ በደረቱ ፡ የደፋው ፡ ያልታወቀ ፡ ነገር ፡ ታወሰው ። ባይኑ ፡ ላይ ፡ አጥበርባሪ ፡ ነገር ፡ የመረገበት ፡ መሰለው ። — መላው ፡ ጠፍቶበት ፡ ቀና ፡ ቢል ፡ የጣርማበር ፡ ተራራ ፡ ጭጋጉን ፡ ተሸክሞ ፡ ለምቦጩና ፡ ለንጨጩ ፡ የተሞለጨ ፡ አርባ ፡ ስምንት ፡ ጥርሱን ፡ ገልጦ ፡ ያለማቋረጥ ፡ የሚስቅበት ፡ ልቡሰ ፡ ሥጋ ፡ መሰለው « - - ሞትና ፡ ሕይ—ወ—ት—ድንቍ - - » — ከንፈሮቹ ፡ ለመላወስ ፡ ሲሞክሩ ፡ ዓይኖቹ ፡ መናወዝ ፡ ይጀምራሉ — ከቦታ ፡ ቦታ ፤ ጢሻዎች ፡ አዲስ ፡ የታረሱ ፡ ጉባዎች ፡ ሸለቆዎችና ፡ ጉድባዎች ፡ እርጭ ፡ ያሉ ፡ የባሕር ፡ ዛፍ ፡ ጫካዎች — ኮርች — አመራሮ — ምሥርች — ችፍርግ — ኩርንችት — የምድር ፡ እምቧይ — ገበር ፡ እምቧይ — የቆላ ፡ እምቧይ — እምቧይ — እምቧይ — የምድር ፡ እምቧይ — አፈርማ ፡ መንደሮች — ቁራዎች — ዋኔዎች — ርግቦች — ጭልፊቶች - - - የነፍሬዋን ፡ አጥር ፡ ግቢ ፡ ወጥቶ ፡ ወደ ፡ ራሱ ፡ አጥር ፡ ግቢ ፡ ያመራል ።

# ፩

# አደፍርስ

ማታ ፡ ቤተ ፡ ሰቡ ፡ ሁሉ ፡ ወደ ፡ የመኝታው ፡ ሄዶ ፡ አጣሁ ፡ ወሮታ ፡ የእመቤቷን ፡ የወይዘሮ ፡ አከላትን ፡ እግር ፡ አጥባ ፡ የሚቆረጣጥማቸውን ፡ ስታሻሽላቸው —

- - - የለም ፡ የለም ፡ ማንም ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ነገር ፡ አላወራም ፤ ስለ ጋብቻ ? ስለ ፡ ጋብቻ ፡ ማንም ፡ አላነሣም ። በላይ ፡ ለራሱ ፡ ህጣን - - ገና ፡ ህጣኖች ፡ ለራሳቸው - - ሆሆይ ፡ ምን ፡ ቢቆርጣቸው - - ምን ፡ ቢቆርጠኝ ፡ እዋሻለሁ - - የመድኃኒ ፡ ዓለምን ፡ ቤተስኪያን ፡ በር ፡ ዘጋለሁ ፡ ቢፈልጉ - - በሥዕለ ፡ ስእለቱ ፡ እምላለሁ - - - ለማን ፡ ይድላው ፡ ብዬ - - - የመጀ መሪያ ፡ ጊዜዬ ፡ ነው ፡ ስሰማ - - አዎ ፡ ግን ፡ ስምቻለሁ - - በጣም ፡ የተለየ ነገር ፡ ነው ፡ ግን ፡ የሰማሁት - - - ይኸ ፡ ክብረት ፡ የሚባል ፡ ሰው ፡ ደሞ - - - ጌቶች ፡ ለምን ፡ እንዳስከተሉት ፡ አይገባኝም - - የሚኻየልን ፡ የገብ ሬልን ፡ እሺ ! የሴትና ፡ የወንድ ፡ ሥዕል ፡ መሣል — የዛሬ ፡ ትምርት ፡ ተበላሽቷል ፡ ግዴለዎትም - - - ደግሞ ፡ እንድታገባው ፡ መጠየቁ - - -

« ምን ? ምን ? ክብረት - - - » እግራቸውን ፡ ምንጭቅ ፡ አድርገው ፡ ይሰበስቡታል « - - ምን ፡ ጠይቋታል ፡ ነው ፡ ያልሽው - - - ?

« የለም ፡ ይኸም ፡ እልም ፡ ያለ ፡ ውሸት ፡ ነው ፤ የሚኻየልንና ፡ የገ ብሬልን ፡ ሥዕል ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ የሚያስተምራት - - - ምን ፡ ቢያገደው - - ምን ፡ የመሰለ ፡ አልጋ ፡ ላይ ፡ ሞቀ ፡ ቤት ፡ የሚያንፈላስስ ፡ ጌታ - - ሆሆይ ፡ መቤታችንን ፡ ነው ፡ የምትመስለው - - ሥዕሉን ፡ ሲያሳያት ፡ እን ኳ ፡ ፊቱን ፡ አዙሮ ፡ ነው ። ምን ፡ ቢያገደው ፡ ያሥር ፡ ድሃ ፡ ልጅ - - - እን ዚህ ፡ ደሞ ፡ የሰፈሩ ፡ አሽከሮችና ፡ ገረዶች ፡ እንዴት ፡ ያሉ ፡ ወሬኞች - - ደሞ ፡ እንዴት ፡ ያምርባቸዋል ፡ እያሉ ፡ ማውራታቸው - - - የማይ ቋጥሩ - - - ያቺ ፡ ታየች — ለተፈሪ — ተፈሪ — ለወለቱ — ወለቱ ፡ ለታደሰ — ታደሰ ፡ ደሞ ፡ እዚህ ፡ ድረስ ፡ መጥቶ ፡ ለኔ — የዋዛ ፡ ሰው መስየዋለሁ ፡ በሱ ፡ ቤት — ከማንም ፡ ሰው — ከማንም ፡ ባላገር ፡ ጋር ፡ የም ዋዛ — ቢያሳው ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ሸናንበት ፡ አያውቅም - - የወሬ ፡ ነገር ፡

ክብረት ፡ ቢያገባት ፡ ምንኛ ፡ በተስማሙ ፡ ማለት ፡ ደሞ — የሚኻየልን ሥዕል ፡ እንኳ ፡ የማያስተምር - - -

« ምን ፡ ዓይነት ፡ ወሬኛ ፡ ሰፈር ፡ ገባን ፡ እባካችሁ - - ደግሞ ፡ አንቺስ ፡ ከምኔው ፡ ዐወቅሻቸው - -

« በጣም ፡ እንጂ - - - እመቤቶቻቸው ፡ ወጣ ፡ ሲሉ ፡ ቡና ፡ እያ ፈሉ ፡ የሚጠጡ — ቅቤ ፡ የሚጠጡ—ጠላ ፡ የሚጠጡ - - ይኸ ፡ ታደሰ ደሞ ፡ ጌታውን ፡ እንኳ ፡ ተከትሎ ፡ ሲሄድ ፡ የሚያንቀላፋ ፡ ነው ፡ የሚመስ ለው - - ፍሬዋ ፡ ቀድሞ ፡ ሁሉ ፡ ወንድ ፡ ወንድ ፡ አይመስላትም - - ወንድ ፡ አትባልም ፡ ነው ፡ የምትለው - - ሽንትህን ፡ በመክፈያ ፡ የምትከፍል - - ደሞ ፡ የማግባት ፡ ደሞ ፡ የሠርግ ፡ ጣጣ - - ሆሆይ ! ምን ፡ ቢያገድ ! ከሠርግ ፡ ይልቅ ፡ አርባ ፡ ወይም ፡ ሰማኒያ ፡ መደገስ ፡ ይሻላል - - የኔ ፡ ብጤ ፡ የሚበሉበት—የእግዜር ፡ አገልጋይ ፡ የሚበሉበት - - -

« ብቻ ፡ ለወደፊቱ ፡ ስለዚህ ፡ ለማንም ፡ እንዳትለፈልፊ - - -

« ልፍለፋ ! ምን ፡ ቢቆርጠኝ - - ትዝም ፡ አይለኝ - - ደሞ ፡ መለፍለፍ ! ምን ፡ አልለና ፡ የሚለፈልፉት - - ገና ፡ ይኸው ፡ ስለ ፡ በላይም መጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ ማየቴ ፡ ነው ። እግዚአብሔር ፡ ይቅሠፈኝ - - ስሙን እርስዎ ፡ ሲያነሡት ፡ እንዴት ፡ ገርሞኛል - - አስደነገጠኝ ፡ እንዳንዳች ! አንቀጠቀጠኝ ፡ እንዴት ፡ ይሆናል ፡ ብዬ ! ደሞ ፡ የምን ፡ ሠርግ—ርሶ ፡ የመ ጡት ፡ አየር ፡ ሊናፈሱ - - ማንም ፡ አላለመውም — እኔ ፡ ራሴ ፡ ሁለዜ ወጥ ፡ ቤት ፡ ከማን ፡ ተነጋግሬ - - እነዚያንም ፡ አሽከሮች ፡ ካየኋቸው ፡ ከወር ፡ አልፎኛል - - ስማቸው ፡ እንኳ ፡ ተረስቶኛል - - ደግሞስ ፡ ማን ፡ አለ ፡ እዚህ ፡ የሚያነጋግሩት - - ታደሰ ፡ ብሎ ፡ ሰው - - የሚያንቀ ላፋ - - በውነት ፡ ነው ፤ ጆሮዬን ፡ ይድፈነው ፤ አልሰማሁም ።-ግድግዳው ፡ መቼ ፡ አሰምቶ - - -

« ጥሩ ፡ ነው ፡ ጥሩ ፡ ነው ፡ በቃ ፡ አሁን - - -

«- - -እንዴት ፡ ያልሆነ ፡ ነገር ፡ ሆነ ፡ ይባላል - - ? እኔ ፡ ለራሴ ፡ ጊዜም ፡ የለኝ ፡ እቴ ! ለእንዲህ ፡ ያለው ፡ ነገር - - ለራሴ ፡ ከጧት ፡ እስከ ፡ ማታ ፡ በሥራ ፡ ተወጥሬ ! ቢሆንስ ፡ ደሞ - - ሲያቅፋት ፡ ባይስ - - ሆሆይ ፡ ምን ቢያገደኝ — ሚኻየል ፡ ምስክሬ ፡ ነው — የሚኻየልን ፡ ሥዕል ፡ እንኳ ፡ የማያስተምር - - -

## ፲፩

# አደፍርስ

አቶ ፡ ጥሶ ፡ ደብረ ፡ሲና ፡ ከወረዱ ፡ ጀምሮ ፡ እንደ ፡ ልማድ ፡ አድ ርገውት ፡ ራት ፡ ከበሉ ፡ በኋላ ፡ ጠለላ ፡ ወጥተው ፡ ቁጭ ፡ ይላሉ ። በዚ ህን ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ ካደፍርስና ፡ ከጺወኔ ፡ ከሌሎችም ፡ ሰዎች ፡ ጋር ፡ ስለ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ነገሮች ፡ የሚያወጉት - - -

« ስለ ፡ ባህል ፡ ትንሽ ፡ ትንሽ ፡ ባስረዳኸኝ ፡ መሠረት ፡ የገባኝ ፡ መስሎኝ ፡ ለበላይ ፡ ላስረዳው ፡ ብሞክር ፡ ዛሬ ፡ ድንግርግር ፡ አለኝ ። ልማድ ፡ ወግ ፡ ቅርስ ፡ በጠቅላላው ፡ ባህል ፡ ይባላሉ ፡ ብለኸኛል - - -

« አዎ ፡ ብየሻለሁ ! » ይላሉ ፡ አቶ ፡ ጥሶ ፡ ለልጃቸው ፡ ለፍሬዋ ።

« ልማድ ፡ ስንል ፡ ጥሩ ፡ ልማድና ፡ መጥፎ ፡ ልማድ ፡ እንዳለ ፡ ነግ ረኸኛል ። የስምንትና ፡ የዘጠኝ ፡ ዓመት ፡ ልጃገረዶች ፡ ለባል ፡ መስ ጠት — ራስ ፡ ምታት ፡ ውጋት ፡ ሲይዘን ፡ በጋለ ፡ ብረት ፡ መተኮስ— በታመምን ፡ በተጨነቅን ፡ ጊዜ ፡ እዛር ፡ፈረስ ፡ መጽሐፍ ፡ ገላጭ ፡ ሞራ ና ፡ ስኒ ፡ ተመልካች ፡ ጠጠር ፡ ጣይ ፡ ጨሌ ፡ መች ፡ ዘንድ ፡ መሄድና፡ ዕወ ቅልን ፡ ማለት — በየበዓላቱ ፡ በመስቀል ፡ ወሰራ ፡ ዶሮና ፡ ዳለቻ ፡ በግ ፡ በጥር ፡ ዛጐልማ ፡ በዚያ ፡ ላይ ፡ ለጠቋር ፡ እያሉ ፡ ከለድማ ፡ ፍየል ፡ አራ ት ፡ አሻል ፡ በግ ፡ ዋላ ፡ በግ ፡ ጣዝማ ፡ ካላረዱ ፡ በሽታና ፡ መዐት ፡ ይመጣል ፡ ብሎ ፡ ማመን - - -

- - - እኔ፡ የነገርኩሽን ፡ ነው ፡ መልሰሽ ፡ ለኔው ፡ የምትደግሚው? ያልገባሽ ፡ እንዳለ ፡ ይልቅ ፡ ብንነጋገርበት ፡ አይሻልም - - - ?

« - - እኮ ፡ እኔ ፡ ያልገባኝ - - ጥሩ ፡ ልማድ ፡ ጥሩ ፡ ወግ ፡ ጥሩ ፡ ቅርስ ፡ የምንላቸው ፡ የቶቹ ፡ ናቸው - - - ?

- - - ከልማድም ፡ ከወግም ፡ ከቀርስም ፡ ብዙ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ዓይ ነቶች ፡ አሉ - - » ብለው ፡ ይጀምራሉ ፡ አቶ ፡ ጥሶ « - - ለምሳሌ ፡ ብዙ ዘመን ፡ ሲሠራበት ፡ የኖረ ፡ የሰው ፡ ንብረትን ፡ የማክበር ፡ ልማድ ፡ አለን ። የራሳችንንም ፡ እናስነካ ፡ የሰውም ፡ አንፈልግም ። — ይኸን ፡ አክብሮታ

ችንን ፡ የሚያስከብር ፡ መብታችንን ፡ የሚጠብቅ ፡ የሥልጣንና ፡ የበላይ ነት ፡ ልማድ ፡ አለን ። — ምን ፡ ማለት ፡ ነው ፡ እንግዲህ ፡ ሥልጣንን ፡ የማክበርና ፡ በላይነትን ፡ የመታዘዝ ፡ ልማድ ፡ አለን ፡ ማለት ፡ ነው ።— በቤተ ፡ ሰብ ፡ ውስጥ ፡ አንድነት ጸንቶ ፡ የሚኖረው ፡ በአባት ፡ ሥልጣ ንና ፡ በላይነት ፡ ነው ፡ ለምሳሌ ። ያባት ፡ ሥልጣን ፡ ከተሻረ ፡ ያባት ፡ በላይነት ፡ ተወዳዳሪና ፡ ተቀናቃኝ ፡ ከገጠመው ፡ አንድ ፡ የነበረው ፡ ቤተ ሰብ ፡ ይበታተናል ፡ ማለት ፡ ነው - - ከዚህም ፡ ሌላ ፡ ቤተ ፡ ክህነት ፡ የሃይማኖት ፡ ሥልጣን ፡ መንግሥት ፡ ለሰላማዊ ፡ ኑሮ ፡ ዋስትና ፡ የሚበጅ ፡ የሹማምንት ፡ ሥልጣንና ፡ የበላይነት ፡ አላቸው ።

« - - እዚህ ፡ ላይ ፡ የመንግሥትንና ፡ የቤተ ፡ ክህነትን ፡ ሥልጣን ፡ መለየትህ ፡ አልገባኝም - - -

- - - ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ደጋግሜ ፡ እንደነገርኩሽ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የም ታምነው ፡ በሰማያዊና ፡ በምድራዊ ፡ በመንፈሳዊና ፡ በሥጋዊ ፡ ኃይል ፡ በጐለበተ ፡ እንደ ፡ ሰሎሞን ፡ ባለ ፡ መሪ ፡ ነው ። ለዚህ ፡ ነው ፡ አርማች ንም ‘ ሞአ ፡ አንበሳ ፡ ዘእምነገደ ፡ ይሁዳ ’ የሚለው ።— ስለዚህ ፡ እስከ ፡ ቅርብ ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፡ የቤተ ፡ ክህነታችን ፡ ሥልጣን ፡ በግብጻውያን ፡ ተይዞ ፡ ስለነበረ ፡ በውነትም ፡ የመንግሥቱና ፡ የቤተ ፡ ክህነቱ ፡ ሥል ጣን ፡ እሁለት ፡ የተከፈሉ ፡ መስለው ፡ ነበር ። ዛሬ ፡ ግን ፡ ሁለቱ ፡ ሥል ጣናት ፡ አንድ ፡ ሆነዋል ። የኢትዮጵያ ፡ መሪ ፡ ለመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ ቤተ ክህነትን ፡ በውጭ ፡ ሥልጣን ፡ ሥር ፡ ከመዋል ፡ አድኖ ፡ በራሷ ፡ ሥልጣን ፡ ሥር ፡ እንድትኖር ፡ አድርጓታል ።—ኢትዮጵያዊ ፡ ሥልጣን ፡ ይመራታል ፡ ማለት ፡ ነው ፡ እንግዲህ ። እንዲያ ፡ ከሆነ ፡ ዘንድ ፡ ደሞ ፡ ማንኛውም ፡ ነዋሪ ፡ ነው ፡ የምንለው ፡ የሀገር ፡ መታወቂያ ፡ ሳይንሱም ፡ ሆነ ፡ ሀይማ ኖቱ ፡ ፍልስፍናውም ፡ ሆነ ፡ ኪነቱ ፡ ከልማዱ ፡ ከወጉና ፡ ከቅሪቶቹ ፡ ጋር በመዋሐድ ፡ በመሪው ፡ ሰብእና ፡ አድሮ - - ከዚያም ፡ እያንጸባረቀ ፡ መታ የት ፡ ይኖርበታል ፡ ማለት ፡ ነው ። —ይገባሻል - - - ?

« አዎ ፡ አዎ ፡ ይገባኛል - - -

- - - ንጉሥ ፡ ከፕሬዚደንት ፡ ከጠቅላይ ፡ ሚኒስትር ፡ ይለያል ፡ ብዬ ፡ ያስረዳሁሽ ፡ ትዝ ፡ ይልሻል - - - ?

« ትዝ ፡ ይለኛል - - -

- - - አዎ ፡ እንግዲህ ፡ ንጉሥ ፡ የነዚህ ፡ ሁሉ ፡ ጥሩ ፡ ነገሮች ፡ ማን ጸባረቂያ ፡ ከሆነ ፡ የቤተ ፡ ክህነቱም ፡ ጥሩ ፡ ነገሮች ፡ ማንጸባረቂያ ፡

ነው ፡ ማለት ፡ ነው ። እና ፡ በዚህ ፡ መሠረት ፡ የቤተ ፡ ክህነት ፡ ነዋሪ ፡ ሥልጣን ፡ በንጉሡም ፡ ስለሚገለጽ ፡ ከምድራዊ ፡ ሥልጣኑ ፡ ጋር ፡ ተዋ ሕዶ ፡ አንድ ፡ ሆኗል ፡ ማለት ፡ ነው - - -

« ሥልጣኑስ ፡ በግብጻውያኑ ፡ እጅ ፡ ቢሆን ፡ ሁለት ፡ ሥልጣኖች ፡ ይኖሩ ፡ ነበር ፡ ማለት ፡ ነው - - ?

- - - እንዴታ ! አታውቂም ፡ እንዴ ፡ ከታሪክ ፡ ጥናትሽ - - - በነአጼ ዮሐንስ ፡ አጼ ፡ ቴዎድሮስ ፡ አጼ ፡ ምኒልክ ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፡ ሳይቀር— ስንት ፍጅት ፡ ነበረበት ፡ ወዳጄ - - -

« - - እሺ ፡ ስለ ፡ ጥሩዎቹ ፡ ልማዶቻችን ፡ ነበር ፡ የምትገልጽልኝ— ሌሎች ፡ ደሞ ፡ ጥሩ ፡ የምትላቸው ፡ እንዴት ፡ ያሉት ፡ ናቸው ?

- - - ተሰብስቦ ፡ የመወያየት ፡ የመመካከር ፡ ልማድ ፡ አለን ። — በሸንጎ ፡ በእድር ፡ እንደምታይው ። በኅብረት ፡ የመሥራት ፡ ልማድ ፡ አለን ።— በወንፈል ፡ በጊሶ ፡ በደቦ ፡ እንደምታይው - - አብሮ ፡ የመ ብላት ፡ የመጠጣት ፡ የመዝፈን ፡ የመጫወት ፡ ልማድ ፡ አለን — በማ ኅበር — በሠርግ ፡ በየበዓላቱ ፡ ሲደረግ ፡ እንደምታይው ።—የሰው ፡ ሰብእ ናው ፡ ትልቅነት ፡ የሚገለጽባቸው ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ልማዶች ፡ አሉን ፡ — ገና ፡ በልጅነታችን ፡ ክርስትና ፡ ስንነሣ ፡ የሐዋርያቱን ፡ ስም ፡ እንሰጣለን ። — ስንሠረግ ፡ በተክሊል ፡ በሥጋወ ፡ ደሙ ፡ እናገባለን ።—ስንሞት ፡ እንደ ፡ ውሻ ፡ ሬሳ ፡ መወርወር ፡ ሳይሆን—ሲሆን ፡ ኀዞ ፡ ፍታት ፡ ሳይሆንም ፡ እንደዩ ፡ ተፈተን ፡ የመጨረሻ ፡ ክብርን ፡ እናገኛለን - - -

« ጥሩ - - ለጊዜው ፡ ስለ ፡ ልማድ ፡ ይበቃኛል - - ወግ ፡ ከፍንላ ቸው ፡ ደግሞ ፡ ጥቂት ፡ ብትጠቅስልኝ - - -

- - - አ ! ብዙ ፡ ብዙ ፡ ወግ ፡ አለን — ስለ - - ስለ ፡ ሰላምታ ፡ አሰጣጥ - - ስ ለ ፡ አበላል — ስለ ፡ አቀማመጥ ፡ የሴትና ፡ የወንዱ ፡ ተለይቶ — ለምሳሌ ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ እግሮቿን ፡ ከፍታ ፡ መቀመጥ ፡ የለባትም — ስለ ፡ አለባበስ ፡ ከነጠላ ፡ እንኳን ፡ አቅም — ወንድ ፡ በቀኙ — ሴት ፡ በግራዋ ፡ ነው ፡ የም ታጣፋው — ስላረማመድ - - -

« - - እሺ ፡ ስለ ፡ ቅርስስ - - - ?

- - - በልብስ ፡ በኩል — ባለ ፡ ወርቅ ፡ ጥብጣብ ፡ ካባ — ላንቃ — ጐፈር — ለምድ — እጀጠባብ ። ልዩ ፡ ልዩ ፡ የበቅሎ ፡ እቃዎች ፡ በያይ ነቱ ።—የግብርና ፡ እቃ ፡ በያይነቱ ።- የሙዚቃ ፡ እቃ ፡ በያይነቱ ፡ ዋሽንት ፡

እምቢልታ ፣ ክራር ፣ በገና ።—የቤት ፣ አሠራር —ቤተ ፣ ንጉሥ ፣ ሠቀላ ።-የምስሉ ፣ ዓይነት—የሐውልቱ ፣ ዓይነት - - ምናለፋሽ ፣ ብቻ ፣ ከያይነቱ ፣ ቅርስ ፣ አለን - - -

« እኔ ፣ እምልህ ፣ አባዬ - - እነዚህ ፣ የዘረዘርካቸው ፣ ሁሉ — በርግጥ ፣ ከሌሎች ፣ ሠልጥነናል ፣ ከሚሉት ፣ አገሮች ፣ እኩል ፣ ነን ፣ ሊያስብሉን ፣ ይችላሉ ?

- - - ካልሽስ ፣ የምንበልጥባቸውም ፣ አይጠፉ - - ብቻ ፣ ቢሆንም — አዎ — መሠረታችን ፣ የጸና ፣ ስለሆነ ፣ እኩል ፣ ነንም ፣ ብንል ፣ የሚያሳፍረን ፣ አይደለም ። ሕንጻው ፣ ታንጾ ፣ እስኪያልቅ ፣ ብዙ ፣ ጊዜ ፣ ይፈጅ ፣ ይሆናል ። ከታነጸ ፣ በኋላ ፣ ግን—እንደ ፣ ግሪኮች ፣ እንደሮማውያን ፣ ሕንጻዎች ፣ መፈራረስ ፣ እንደማያስፈራው ፣ እተማመናለሁ - - -

« በተለይ ፣ ስሜት ፣ በሚገለጽባቸው ፣ ነገሮች ፣ ወደ ፣ ኋላ ፣ የቀረን ፣ አይመስልህም - - - ?

- - - በመሳቅ ፣ በማልቀስ ፣ በማዛጋት—በማስነጠስ—በቡጢ ፣ በዱላ— በዘፈን ፣ በጭፈራ ፣ ነው ፣ መቼም ፣ ስሜት ፣ የሚገለጸው— እኛ ፣ ኢትዮጵያውያን ፣ በነዚህ ፣ ነገሮች ፣ ወደ ፣ ኋላ ፣ ቀርተናል ፣ ብትይኝ ፣ አይገባኝም - - -

« አባዬ ፣ ግን ፣ በውነት ፣ በውነት — ካንጀትህ ፣ ነው ፣ የምታምነው - - - በኢትዮጵያ ፣ ትልቅነት - - -

- - - እንዴታ ! አንቺም ፣ እንድታምኚ ፣ ያሻል ፣ እንጂ—ያልገባሽን እየጠየቅሽ ፣ መረዳት - - - ስድብን ፣ በጣሊያንኛ — ፍቅርን ፣ ማላን ፣ በፈረንሳይኛ — ቴክኖሎጅን ፣ በእንግሊዝኛ ፣ ካልተናገርን — ትልቅ ፣ ላንባል ፣ ይሆን ፣ እንዴ ፣ እባክሽ - - - ? ፍሬዋ—አይሆንም ፣ ኋላ ፣ ቀስ እያልሽ ፣ ተረመጂ - - -

« እኔኮ ፣ የሚገርመኝ — ሀገርህንና ፣ መንግሥትህን ፣ እስከዚህ ፣ የምትወደው ፣ ምን ፣ ኖሮህ ፣ ነው - - ? ሀገሬን ፣ ለምትልበት ፣ መሬት— መንግሥቴን ፣ ለምትልበት ፣ እስከዚህ—ትልቅ ፣ ሹመት ፣ የለህ—በጣም ፣ ነው ፣ የሚገርመኝ - - -

- - ፍሬዋ ! እየበሰልሽ ፣ ስትሄጂ ፣ ታውቂዋለሽ - - - አየሽ ፣ እኔ ፣ አባትሽ — አንቺ ፣ አሁን ፣ የጠየቅሽውን ፣ ሁሉ ፣ አላጣሁትም—

እዎ ፡ እንድታውቂው ፡ ያሻል — እኔ ፡ አባትሽ — ሀገሬን ፡ እወዳለሁ ፡ የምልበት ፡ ብዙ ፡ ርስት ፡ አለኝ - - -

« አባዬ - - - !

- - - ካንዱ ፡ ቦታ ፡ ወደ ፡ ሌላው ፡ አፍንጫዬን ፡ አየር ፡ ላይ ፡ ሰቅዬ ፡ እግሬ ፡ ሳይፈራ ፡ ሙሉ ፡ ለሙሉ ፡ የተራመድሁበት ፡ ሁሉ ፡ ርስቴ ፡ ነው ። ሹመትም ፡ ስላልሽው ፡ የያዝሁትን ፡ ለጤና ፡ ያድርግልኝ ፡ የሚል ፡ አን ጀት ፡ ባይኖረኝ ፡ ኖሮ ፡ አቅሜ ፡ የሚፈቅደውን ፡ ሹመት ፡ መንግሥቴ ፡ አያሳጣኝም - - -

« - - ብቻ ፡ አባዬ ፡ አለህ ፡ ነገር ፡ አንተ - - - !

- - - አዳምጭ ፡ ፍሬዋ ! ሀገርና ፡ መንግሥት ፡ ርስትና ፡ ሹመት ፡ ብቻ ፡ አይደለም — ርስትና ፡ ሹመትስ ፡ የትም ፡ ቢሔዱ ፡ ማንም ፡ ቢገዛ አይታጣም ። ሀገርና ፡ መንግሥት ፡ አለኝ ፡ የሚያሰኙ ፡ ልማድ ፡ ወግ ፡ ቅርስ — ሌሎችም ፡ የጠቀስናቸው ፡ ባህሎች ፡ በሰው ፡ ላይ ፡ አድረው ፡ ውዶሕታቸው ፡ ደም ፡ ግባትና ፡ ትከሻ ፡ ክብደት ፡ ሲያመጣ ፡ ነው — አለዚያ ፡ ሀገረ ፡ ቢስ ፡ ወይም ፡ ውቃበ ፡ ቢስ ፡ ነሽ ፡ እንጂ ፡ ባለ ፡ ሀገር ፡ ባለ ፡ መንግሥት ፡ አይደለሽም - - -

## ፲፪

# አደፍርስ

ከስድሳ ፥ ከሰባ ፥ ከሰማንያ ፡ ዓመት ፡ በላይ ፡ ነው ፡ ስናውቀው ፡ የማይል ፡ ባላገር ፡ የለም ፥ ወርካውን - - - ዙሪያውን ፡ በአምስት ፡ ሰው ፡ እቅፍ ፡ አይደረስም ። ሥር ፡ ሥሩን ፡ ሥጋጃ ፡ የሚመስል ፡ ሣር ፡ ስለማያጣ ፥ አጠገቡ ፡ በነበረው ፡ ጐዳና ፡ የተጓዘ ፡ ሁሉ ፡ ሳያርፍበት ፡ አያልፍም ። በየቅርንጫፎቹ ፡ ላይ ፥ ብዙ ፡ የስለት ፡ ፈትሎች ፥ ጨሌዎች ፥ የሻሽ ፡ ቁር ጥራጮች ፡ ተንጠልጥለውበታል ። በዋናው ፡ ግንድ ፡ ዙሪያ ፥ ሰው ፡ እን ዳይደርስበት ፡ ሆኖ ፥ ሰፊ ፡ ጃኖ ፡ ታሥሮበታል ። ቅቤም ፡ የተቀባ ፡ ቦታ ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ አለበት ። በየጊዜው ፡ የተሾሙት ፡ ያውራጃው ፡ ገዥዎች ሦስት ፡ ጊዜ ፡ ያህል ፡ ሊያስቆርጡት ፡ እየመጡ ፥ ቆራጮቹን ፡ ስለተተናኮ ለባቸው ፡ አልሆንላቸውም ፡ እየተባለ ፡ ይወራል ፤ አንዱን ፡ ገድሎ ታል—አንዱን ፡ አዙሮ ፡ ደፍቶታል—አንዱን ፡ እንዳውሬ ፡ አስጨሆ ፡ ከሥፍራው ፡ አባሮታል ፡ ይባላል ። ያም ፡ ሆነ ፡ ይህ ፡ ወርካው ፡ የሚታ የው ፡ በታላቅ ፡ አክብሮትና ፡ ፍራት ፡ ነው ።—በሥሩ ፡ ክረምት ፡ ሲሆን ብቻ ፡ ግንፍል ፡ ግንፍል ፡ የምትል ፡ ወንዝ ፡ ትወርዳለች —

ከወርካው ፡ በላይ ፥ ወደ ፡ ደሴ ፡ እሚወስደው ፡ መኪና ፡ መንገድ ፡ አቅራቢያ ፡ ሲል ፥ የማርያም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፥ ከበታቹ ፡ ደግሞ ፥ ወደ ፡ አረጋዊ ፡ ደብር ፡ መገንጠያው ፡ ላይ ፡ የድንጋይ ፡ ቁልል ፡ ይታ ያል — የድንጋዩን ፡ ቁልል ፡ አድባር ፡ ይሉታል ። ክርስቲያኑም ፥ እስላ ሙም ፥ ዛር ፡ ፈረሱም ፥ ጠንቋዩም ፥ ሃይማኖት ፡ የለሹም ፥ በዚያ ፡ ጐዳና ፡ የሚያልፉ ፡ ከሆነ ፥ ከሩቅ ፡ ሥፍራ ፥ እጃቸው ፡ የገባውን ፡ ነገር ፥ እንጨትም ፡ ሆነ ፡ ድንጋይ ፡ ይዘው ፡ መጥተው ፡ እላዩ ፡ ላይ ፡ መጨመር ፡ ይኖርባቸዋል ። ያልታሰበ ፡ አደጋ ፡ እንዳይመጣ ፡ ይከላከላል ፡ የሚል ፡ እምነት ፡ አላቸው ።

ከወርካውና ፡ ከድንጋዩ ፡ ቁልል ፡ ባሻገር ፡ ኮረብታ ፡ ላይ ፡ የአቡነ ፡ አረጋዊ ፡ ደብር ፡ ነው ። በጥድ ፥ በወይራ ፥ በሾላ ፥ በጋሜና ፡ በብሳና ፡ ዛፎች ፡ ተከቦ ፡ ችፍግ ፡ ብሎ ፡ ይታያል ። መግቢያው ፡ አጠገብ ፡ እሚታየ ው ፡ ዛፍ ፡ ላይ ፡ ረጅም ፥ የተጠረበና ፡ ጠፍጣፋ ፡ ድንጋይ ፡ ተንጠል

# ፲፪

## አደፍርስ

ከስድሳ ፥ ከሰባ ፥ ከሰማንያ ፡ ዓመት ፡ በላይ ፡ ነው ፡ ስናውቀው ፤ የማይል ፡ ባላገር ፡ የለም ፥ ወርካውን - - - ዙሪያውን ፡ በአምስት ፡ ሰው ፡ እቅፍ ፡ አይደረስም ። ሥር ፡ ሥሩን ፡ ሥጋጃ ፡ የሚመስል ፡ ሣር ፡ ስለማያጣ ፥ አጠገቡ ፡ በነበረው ፡ ጐዳና ፡ የተጓዘ ፡ ሁሉ ፡ ሳያርፍበት ፡ አያልፍም ። በየቅርንጫፎቹ ፡ ላይ ፥ ብዙ ፡ የስለት ፡ ፈትሎች ፥ ጨሌዎች ፥ የሻሽ ፡ ቁር ጥራጮች ፡ ተንጠልጥለውበታል ። በዋናው ፡ ግንድ ፡ ዙሪያ ፥ ሰው ፡ እንዳይደርስበት ፡ ሆኖ ፥ ሰፊ ፡ ጃኖ ፥ ታሥሮበታል ። ቅቤም ፡ የተቀባ ፡ ቦታ ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ አለበት ። በየጊዜው ፡ የተሾሙት ፡ ያውራጃው ፡ ገዥዎች ሦስት ፡ ጊዜ ፡ ያህል ፡ ሊያስቆርጡት ፡ እየመጡ ፥ ቆራጮቹን ፡ ስለተተናኮለባቸው ፡ አልሆነላቸውም ፡ እየተባለ ፡ ይወራል ፤ አንዱን ፡ ገድሎታል—አንዱን ፡ አዙሮ ፡ ደፍቶታል—አንዱን ፡ እንዳውሬ ፡ አስጮሆ ፡ ከሥፍራው ፡ አባሮታል ፡ ይባላል ። ያም ፡ ሆነ ፡ ይህ ፡ ወርካው ፡ የሚታየው ፡ በታላቅ ፡ አክብሮትና ፡ ፍራት ፡ ነው ።—በሥሩ ፡ ክረምት ፡ ሲሆን ብቻ ፡ ግንፍል ፡ ግንፍል ፡ የምትል ፡ ወንዝ ፡ ትወርዳለች —

ከወርካው ፡ በላይ ፥ ወደ ፡ ደሴ ፡ እሚወስደው ፡ መኪና ፡ መንገድ ፡ አቅራቢያ ፡ ሲል ፥ የማርያም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፥ ከበታቹ ፡ ደግሞ ፥ ወደ ፡ አረጋዊ ፡ ደብር ፡ መገንጠያው ፡ ላይ ፡ የድንጋይ ፡ ቁልል ፡ ይታያል — የድንጋዩን ፡ ቁልል ፡ አድባር ፡ ይሉታል ። ክርስቲያኑም ፥ እስላሙም ፥ ዛር ፡ ፈረሱም ፥ ጠንቋዩም ፥ ሃይማኖት ፡ የለሹም ፥ በዚያ ፡ ጐዳና ፡ የሚያልፉ ፡ ከሆነ ፥ ከሩቅ ፡ ሥፍራ ፥ እጃቸው ፡ የገባውን ፡ ነገር ፥ እንጨትም ፡ ሆነ ፡ ድንጋይ ፡ ይዘው ፡ መጥተው ፡ እላዩ ፡ ላይ ፡ መጨመር ፡ ይኖርባቸዋል ። ያልታሰበ ፡ አደጋ ፡ እንዳይመጣ ፡ ይከላከላል ፡ የሚል ፡ እምነት ፡ አላቸው ።

ከወርካውና ፡ ከድንጋዩ ፡ ቁልል ፡ ባሻገር ፡ ኮረብታ ፡ ላይ ፡ የአቡነ ፡ አረጋዊ ፡ ደብር ፡ ነው ። በጥድ ፥ በወይራ ፥ በሾላ ፥ በጋሜና ፡ በብሳና ፡ ዛፎች ፡ ተከቦ ፡ ችፍግ ፡ ብሎ ፡ ይታያል ። መግቢያው ፡ አጠገብ ፡ እሚታየው ፡ ዛፍ ፡ ላይ ፡ ረጅም ፥ የተጠረበና ፡ ጠፍጣፋ ፡ ድንጋይ ፡ ተንጠል

ጥኋል — የቤተክርስቲያኑ ፡ ደወል ፡ ነው ። በሩቁ ፡ ሲያውት ፡ የተሰ
ቀለ ፡ ሰው ፡ ይመስላል ።

ቀኑ ፡ እሁድ ፡ በአራት ፡ ሰዓት ፡ ገደማ፡ ከቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መልስ፡ ተናጋሪው ፡ የደብረ ፡ ቢዘኑ ፡ አባ ፡ ዮሐንስ ፡ ከአዲስ ፡ አበባ ፡ የተላኩ ፡ የአረጋዊ ፡ ደብር ፡ አለቃ ፡ ቦታው ፡ የወርካው ፡ ሥር ፡ የሚናገሩት ፡ ንግግር ፡ ዓላማ ፡ የከተማው ፡ ሕዝብ ፡ ገንዘብ ፡ አዋጥቶ ፡ ተጨማሪ ፡ የትምህርት ፡ ቤት ፡ ክንፍ ፡ እንዲሠራ ፡ ለማበረታታት ፡ ነበር ።

- - - በሰላም ፡ ጊዜ ፡ ተባባሪ ፡ በዘመቻ ፡ ጊዜ ፡ ጀብዶኛ ፡ በጦርነት ፡ ጊዜ ፡ መንፈስ ፡ ቆራጥ ፡ የሚያደርግ ፡ የወንድነት ፡ ሐሞትን ፡ የሚያፈላ ፡ ያርበኝነት ፡ ወኒን ፡ የሚያገነፍል ፡ የድፍረት ፡ ግመት ፡ የማያሞኘው ፡ አንድነት ፡ ነው ---» ይላሉ ፡ አባ ፡ ዮሐንስ ፡ ካዘጋጁት ፡ ንግግር ፡ ጮክ ፡ ብለው ፡ ለሕዝቡ ፡ ሲያነቡ « - - - ጐበዝን ፡ የሚያስሞካሽ ፡ የሚያጋንን ፡ የሚያስፋፋ ፡ እከሌ — እንደ ፡ ጥይት ፡ ተወርዋሪ ፡ እንደ ፡ አንበሳ ፡ ግርማዊ ፡ እንደ ፡ ነብር ፡ ግልፍተኛ ፡ የሆነ ፡ ጐበዝ ፡ ቁጡ ፡ ኃይለኛ ፡ የማይደፈር ፡ ወንድ ፡ ነው ፡ የሚያሰኘው--ለሴት ፡ አሞት፡ ለወንድ ፡ ድፍረት ፡ የሚሰጠው ፡ አንድነት ፡ ነው - - - » ያነባሉ ፡ አባ ፡ ዮሐንስ ።

ፍሬዋ ፡ ከቤተ ፡ ስቦቿ ፡ ጋር ፡ መጥታ ፡ ስለነበር ፡ ግራ ፡ እግሯን ፡ እድንጋይ ፡ ላይ ፡ አሳርፋ ፡ ቀኝ ፡ እግሯን ፡ እሚወርደው ፡ ውሃ ፡ ውስጥ ፡ ነክራ ፡ እወንዙ ፡ ዳር ፡ በመቀመጥ ፡ በላይ ፡ የላከላትን ፡ ግላዊ ፡ የፍቅር ፡ ደብዳቤ ፡ በለኆሳስ ፡ ታነባለች

«እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ በተስፋ ፡ የቆየሁ ፡
ሁነው ፡ ልቤ ፡ ባሕር ፡ መስከረም ፡ ይጥባልህ ።
እንዳንች ፡ ያለ ፡ ቆንጆ ፡ ትንፋሽ ፡ የሚያሳጣ ፡
አበድሁ ፡ ከነፍሁ ፡ ነው ፡ ነፍሴ ፡ ልትወጣ - - -

« - - - የሥልጣኔ ፡ ኩርንችት ፡ የኑሮ ፡ አሽክላ ፡ የመወያየት ፡ እንቅፋት፡ የፍቅር ፡ ሻህላ ፡ እየሆኑ ፡ በጥራዝ ፡ ነጠቅነት ፡ በተመረዘው ፡ ወጣት ፡ መካከል ፡ እንቁራሪት ፡ በሆዱ ፡ እንደቋጠረ ፡ እባብ ፡ ተቋጥረው ፡ የሚታዩትን ፡ አንዳንድ ፡ አጉራ ፡ ዘላይ ፡ አጥንተ ፡ ብልዝ ፡ ሰዎች ፡ የሚሻለውን ፡ መንገድ ፡ አሲዞ ፡ ከግብ ፡ የሚያደርሳቸው ፡ አንድነት ፡ ነው - - -

ጥኋል — የቤተክርስቲያኑ ፡ ደወል ፡ ነው ። በሩቁ ፡ ሲያውት ፡ የተሰቀለ ፡ ሰው ፡ ይመስላል ።

ቀኑ ፡ እሁድ ፡ በአራት ፡ ሰዓት ፡ ገደማ፡ ከቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መልስ ፡ ተናጋሪው ፡ የደብረ ፡ ቢዘኑ ፡ አባ ፡ ዮሐንስ ፡ ከአዲስ ፡ አበባ ፡ የተላኩ ፡ የአረጋዊ ፡ ደብር ፡ አለቃ ፡ ቦታው ፡ የወርካው ፡ ሥር ፡ የሚናገሩት ፡ ንግግር ፡ ዓላማ ፡ የከተማው ፡ ሕዝብ ፡ ገንዘብ ፡ አዋጥቶ ፡ ተጨማሪ ፡ የትምህርት ፡ ቤት ፡ ክንፍ ፡ እንዲሠራ ፡ ለማበረታታት ፡ ነበር ።

- - - በሰላም ፡ ጊዜ ፡ ተባባሪ ፡ በዘመቻ ፡ ጊዜ ፡ ጀብዶኛ ፡ በጦርነት ፡ ጊዜ ፡ መንፈስ ፡ ቆራጥ ፡ የሚያደርግ ፡ የወንድነት ፡ ሐሞትን ፡ የሚያፈላ ፡ ያርበኝነት ፡ ወኒን ፡ የሚያገነፍል ፡ የድፍረት ፡ ግመት ፡ የማያሞኘው ፡ አንድነት ፡ ነው ---» ይላሉ ፡ አባ ፡ ዮሐንስ ፡ ካዘጋጁት ፡ ንግግር ፡ ጮክ ፡ ብለው ፡ ለሕዝቡ ፡ ሲያነቡ « - - - ጉበዝን ፡ የሚያስሞካሽ ፡ የሚያጋንን ፡ የሚያስፋፋ ፡ እከሌ — እንደ ፡ ጥይት ፡ ተወርዋሪ ፡ እንደ ፡ አንበሳ ፡ ግርማዊ ፡ እንደ ፡ ነብር ፡ ግልፍተኛ ፡ የሆነ ፡ ጉበዝ ፡ ቁጡ ፡ ኃይለኛ ፡ የማይደፈር ፡ ወንድ ፡ ነው ፡ የሚያሰኘው--ለሴት ፡ አሞት ፡ ለወንድ ፡ ድፍረት ፡ የሚሰጠው ፡ አንድነት ፡ ነው - - - » ያነባሉ ፡ አባ ፡ ዮሐንስ ።

ፍሬዋ ፡ ከቤተ ፡ ስቦቿ ፡ ጋር ፡ መጥታ ፡ ስለነበር ፡ ግራ ፡ እግሯን ፡ እድንጋይ ፡ ላይ ፡ አሳርፋ ፡ ቀኝ ፡ እግሯን ፡ እሚወርደው ፡ ውሃ ፡ ውስጥ ፡ ነክራ ፡ እወንዙ ፡ ዳር ፡ በመቀመጥ ፡ በላይ ፡ የላከላትን ፡ ግላዊ ፡ የፍቅር ፡ ደብዳቤ ፡ በለጥሳስ ፡ ታነባለች

«እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ በተስፋ ፡ የቆየሁ ፡
ሁነው ፡ ልቤ ፡ ባሕር ፡ መስከረም ፡ ይጥባልህ ።
እንዳንች ፡ ያለ ፡ ቆንጆ ፡ ትንፋሽ ፡ የሚያሳጣ ፡
አበድሁ ፡ ከነፍሁ ፡ ነው ፡ ነፍሴ ፡ ልትወጣ - - -

« - - - የሥልጣኔ ፡ ኩርንችት ፡ የኑሮ ፡ አሽክላ ፡ የመወያየት ፡ እንቅፋት ፡ የፍቅር ፡ ሻህላ ፡ እየሆኑ ፡ በጥራዝ ፡ ነጠቅነት ፡ በተመረዘው ፡ ወጣት ፡ መካከል ፡ እንቁራሪት ፡ በሆዱ ፡ እንደቋጠረ ፡ እባብ ፡ ተቋጥረው ፡ የሚታዩትን ፡ አንዳንድ ፡ አጉራ ፡ ዘላይ ፡ አጥንተ ፡ ብልዝ ፡ ሰዎች ፡ የሚሻለውን ፡ መንገድ ፡ አሲዞ ፡ ከግብ ፡ የሚያደርሳቸው ፡ አንድነት ፡ ነው - - -

« ዓይንሽ ፡ የሚመስለው ፡ የብር ፡ ጉልላት ፡
ጸጉርሽ ፡ የሚመስለው ፡ የሃር ፡ ጉንጉናት ፡
ጥርስሽ ፡ የሚመስለው ፡ የበረዶ ፡ እምብርት ፡
ሽንጥሽ ፡ የሚመስለው ፡ የነብር ፡ ጅራት - - -

«- - - ሳቅን ፡ በደስታ ፡ ጭብጨባን ፡ በማጉልመሻ ፡ ለቅሶን ፡ በሐዘን ፡ መጉሳቆልን ፡ በድህነት ፡ ያለጊዜ ፡ ማርጀትን ፡ በብስጭት ፡ ተርጉሞ ፡ ከሰው ፡ እኩል ፡ የሚያራምድ ፡ አንድነት ፡ ነው - - -

« ትናንትና ፡ ማታ ፡ ብዬ ፡ ካልጋ ፡ ደገፍ ፡
የፍቅርሽ ፡ ወለምታ ፡ ሰበረኝ ፡ ወደ ፡ እንቅልፍ ።
እረ ፡ እንዴት ፡ ያለው ፡ ነው ፡ ፍቅር ፡ የሚሉት ፡
ሲያወራኝ ፡ ቆይቶ ፡ ጠፋ ፡ በድንገት ።
አንገት ፡ የምትሆኚ ፡ ወዝሽ ፡ እጅ ፡ ያልነካው ፡
ፍቅርሽ ፡ በሽታ ፡ ነው ፡ ልቤን ፡ ደነዘዘው ።
ስጭኝ ፡ መሀረብሽን ፡ ለፍቅሬ ፡ ትዝታ ፡
ባስታወስኩሽ ፡ ቁጥር ፡ እንድድን ፡ አንዳፍታ - - -

« - - - አንድነት ፡ ከሌለ ፡ ግን ፡ ሳቁ—በጥጋብ ፡ በማናለብኝነት ፡ በማሽሟጠጥ ፡ በማፌዝ ፡ በማናካት ፡ ይተረጐማል ።- ጭብጨባው — ቀረ ! ቀረ ! ተበላሽ ! ተበላሽ ! አስቀየመ ! አጀብ ፡ አጀብ ፡ ጉድጉድ ! በሚል ፡ ስሜት ፡ ተገዝቶ ፡ የመደሰቻው ፡ ምልክት ፡ መቀለጃ ፡ ይሆንና ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ እንዲያስጨበጭብለት ፡ ያሰበው ፡ የወጠነው ፡ አስጨብጭቦበት ፡ ይፈጸማል ። ለቅሶው— በስካር ፡ በማጭበርበር ፡ በማደናገር ፡ በጥጋብ ፡ ተተርጉሞ ፡ እንዲያውም ፡ ገፍቶ ፡ ይብስና ‘እዞ ፡ ልትተናኮል ፡ ስትፈልግ ፡ እያለቀሰች ፡ ትጠጋለች ’ እንደሚባለው ፡ በተንኮል ፡ መሠረትነት ፡ ይለወጣል ። መጉሳቆል ፡ በአያት ፡ በቅድም ፡ አያት ፡ ዘመን ፡ በተሠራ፡ የዘር ፡ ግፍ ፡ ባገኙ ፡ በበለጸጉ ፡ ጊዜ ፡ በተፈጸሙ ፡ እኮያት ፡ በልብ ፡ ክፉ ፡ በተፈጥሮ ፡ ጠማማነት ፡ የኀጢአት ፡ ዋጋ ፡ በመሆን ፡ ተለውጦ ፡ ሲያራርቅ ፡ ሲያመናጭቅ ፡ ይኖራል ። ያለ ፡ ጊዜ ፡ ማርጀትም—ያለ ፡ አቅም ፡ መንጠራራት ፡ የራስን ፡ ልክ ፡ አለማወቅ ፡ ጋት ፡ ሲያሳዩ ፡ ስንዝር ፡ ስንዝር ፡ ሲያሳዩ ፡ ክንድ ፡ መመኘት ፡ የተነሡበትን ፡ ረስቶ ፡ ለማይደርሱበት ፡ መንጠራራት ፡ ይሆንና ፡ የሰውን ፡ ልጅ ፡ ዕድሜው ፡ ለማይፈቅድለት ፡ ሥራ ፡ ስለባከነ — በስሜት ፡ አርጅቶ ፡ በሐሳብ ፡ ረግረግ ፡ ተውጦ ፡

ሕልማዊ ፡ መንግሥትን ፡ በመግዛት ፡ ከሰውነት ፡ መዝገብ ፡ ስለተፋቀ— የመጨረሻ ፡ ጐደሎ ፡ ፍጥረት ፡ የሚያሰኝ ፡ የሰው ፡ በታችነት ፡ ስም ፡ ይሰጠዋል - - -

« ብትታዩ ፡ ባይሽ ፡ የማላፍርብሺ ፡
መላእክት ፡ በሰይፋቸው ፡ አጥረው ፡ የያዙሺ ፡
ወተት ፡ ከሰማይ ፡ ላይ ፡ የሚመግቡሺ ፡
ለፍቅርሽ ፡ ወለምታ ፡ ጠበል ፡ ያፈለቅሺ ፡
ነይልኝ ፡ በሞቴ ፡ ልፈወስልሺ - - - » ታነባለች ፡ ፍሬዋ ፡ በሉኖሳስ ፤ ምንም ፡ ዓይነት ፡ ለውጥ ፡ ፊቷ ፡ ላይ ፡ ሳታሳይ ።

« - - - አንድነት ፡ ነፃነት ፡ ነው ፤ ነፃነት ፡ አንድነት ፡ ነው ። አንድነት ፡ አገር ፡ አገር ፡ አንድነት ፡ ነው ። አንድነት ፡ መንግሥት ፡ ነው ፤ መንግሥት ፡ አንድነት ፡ ነው ። ሥልጣኔ ፡ አንድነት ፡ አንድነት ፡ ሥልጣኔ ፡ ነው ። ሕይወት ፡ አንድነት ፡ ነው ፡ አንድነት ፡ ሕይወት ፡ ነው ። ኀይል ፡ አንድነት ፡ አንድነት ፡ ኃይል ፡ ነው ። እንኪያስ ፡ የሀገር ፡ ማተቧ ፡ ከተበጠሰ ፡ የሕዝብ ፡ እምነቱ ፡ ከጐደለ ፡ ሀገሪቱም ፡ ሕዝቡም ፡ አወዳደቃቸው ፡ አያምርም ፡ ማለት ፡ ነው - - -

« ሳልበላ ፡ እንድጠግብ ፡ አንቺን ፡ አንቺን ፡ ሳዪ ፡
ነይልኝ ፡ የኔ ፡ አካል ፡ ባይን ፡ እንተያዩ ።
ብርሃን ፡ አንቺ ፡ ነሽ ፡ የውስጥ ፡ አከላት ፡
ላዩ ፡ የጀምበር ፡ ነው ፡ ጥንት ፡ የመራሁት ።
አንድ ፡ ቤት ፡ ለሁለት ፡ እንገንባ ፡ ፍጠኚ ፡
ቀን ፡ ሠርተን ፡ ለማታ ፡ ብርሃኔ ፡ ሁኚ - - -

«- - - አንድነት፡ነፃነት ፡ ነፃነት፡አንድነት ፡ ነው።—አለዚያማ ፡ ነፃነት ፡ ነፃነት ፡ ቢሉት ፡ ለአፍ ፡ ሞልቶ ፡ አንጀት ፡ አይደግፍ—ለዓይን ፡ ደምቆ ፡ ለሰውነት ፡ ፍሥሐን ፡ አይሰጥ—ለጀሮ ፡ የራቀ ፡ የጠለቀ ፡ የጣመ ፡ የጣፈጠ ፡ ቢመስል ፡ ልባችንን ፡ አኩርቶ ፡ እንዳሻን ፡ አያክበሰብስ—ምን ፡ ተስፋ ፡ ምን ፡ አለኝታነት ፡ ሊኖረው ፡ ይችላል ? የለም ! ነፃነት ፡ አንድነት ፡ ነው ፤ የግል ፡ የጋራ ፡ እንደ ፡ ፀሐይ ፡ እንደ ፡ ውሃ ፡ እንደ ፡ ዓየር— ጌታና ፡ ድሃን ፡ የማይመርጥ ፡ የማያፍነሸንሽ ፡ የሚያንቦላካ—ሌት ፡ ተቀን ፡ ቀን ፡ ከማታ ፡ እንዳሰኘ ፡ የሚያረካ ፡ የሚመግብ—ባጉል ፡ ነገር ፡ ያልተ

በረዘ ፡ በእስከ — ያልተወሰነ ፡ ነው ። ነፃነት ፡ ሕያው ፡ ዘለዓለማዊ ፡ ነው ፤ ሆኖም ፡ በሰማይ ፡ ላም ፡ አለኝ ፡ ብቻ ፡ የሰውን ፡ ልጅ ፡ ደስታ ፡ ለመደለል ፡ አይሻም - - - - ታዲያ ፡ እንግዲህ ፡ እንዴት ፡ ይሆናል ? እንዴት ፡ ምድራዊውን ፡ ከሰማያዊው ፡ ለማስተባበር ፡ ይቻላል - - - ? ሊሆን ፡ የሚችለው - - -



አንድነት ፡ ነፃነት ፡ ነፃነት ፡ አንድነት ፡ ነው ።—
አለዚያማ ፡ ነፃነት ፡ ነፃነት ፡ ቢሉት - - -

« ሂድ ፡ ሂድ ፡ ትይኛለሽ ፡ ብሄድ ፡ አላፈጥን ፡
ታስፈራሪኛለሽ ፡ አልሰማ ፡ በድን ፡
ፍቅርሽ ፡ ደራሽ ፡ ሆነ ፡ የድንገት ፡ ውጥን ፡
ፍቅር ፡ የድንገት ፡ ነው ፡ እንዳለ ፡ ሰሎሞን ፡
ነይልኝ ፡ የኔ ፡ ሆድ ፡ እንመሥርት ፡ ፍቅርን - - -

ቀጥላለች ፡ ፍሬዋ ፡ ንባቧን —

« - - ለማስተባበር ፡ የሚቻለው ፡ ማግኘትም ፡ ማጣትም ፡ መደሰትም ፡ ማዘን ፡ አንድነት ፡ ሲሆን ፡ ነው ። ነፃነትና ፡ አንድነት ፡ መንትዮች ፡ ናቸው ። የአንደኛው ፡ አንድነትና ፡ አድራጐት ፡ ከሌላው ፡ የተለየም ፡ ቢሆን ፡ እንደነፍስና ፡ ሥጋ ፡ አብረው ፡ የሚሠሩ ፡ መሆናቸውን ፡ ዐውቀን ፡ እንድንሠራባቸው ፡ ያስፈልጋል ። እንዲህ ፡ ካልሆነ ፡ ግን ፡ ነፃነት ፡ ምናልባት ፡ ያልታወቀ ፡ ትርጉም ፡ ይኖረዋል ፡ ማለት ፡ ነው ። ምናልባት ፡ ይህ ፡ ትርጉም ፡ ማለት ፡ ያልታወቀው ፡ ትርጉሙ ፡ ለጥቂት ፡ ሰዎች ፡ እንጂ ፡ ለብዙዎች ፡ አልተገለጸ ፡ ይሆናል ። ምናልባት ፡ ለብዙዎች ፡ ሲገለጽ ፡ በሽታ ፡ ይሆን ፡ ይሆናል ። ምናልባት ፡ እንደ ፡ ማር ፡ በጥቂቱ ፡ እንጂ ፡ ሲበዛ ፡ ይመር ፡ ይሆናል ። ምናልባት ፡ ይህ ፡ ልዩ ፡ ትርጉሙ ፡ እየታወቀን ፡ አያናግር ፡ አያሠራ ፡ አያበረታታ ፡ ደዌውን ፡ ተክሎብን ፡ ይሆናል — ምናልባት ፡ ማን ፡ ያውቃል - - - - » ያስተጋባል ፡ ያባ ፡ ድምፅ ፡ ከጋራ ፡ ጋራ ።

« ብሄድስ ፡ ምን ፡ ልድን ፡ እንዲያው ፡ እኔ ፡ ብቻ ፡
የጣትሽን ፡ ጌጥ ፡ ሳልይዝ ፡ ለፍቅሬ ፡ መተቻ ።
እራብሽኝ ፡ እራብሽኝ ፡ ጠማሽኝም ፡ ከቶ ፡
ባይን ፡ እንኳ ፡ እንገናኝ ፡ ሌላው ፡ እንኳ ፡ ቀርቶ - - - » የዲወኔም ፡ ንባብ ፡ ባይኖቿ ፡ ብቻ ።

« - - - አገር ፡ አንድነት ፡ አንድነት ፡ አገር ፡ ነው ። አለዚያማ ፡ አገር ፡ አገር ፡ አይሆንም ፤ ውሃው ፡ ይመራል — እህሉ ፡ ያንገፈግፋል — ዓየሩ ፡ ይጐመዝዛል — መሬቱ ፡ እንደ ፡ ረሞጫ ፡ ያቃጥላል — የሣር ፡ የቅጠሉ ፡ ሽታ ፡ ይመርዛል — ሸጥ ፡ ሸለቆው ፡ ይከብዳል ፡ ያስጠላል — ተራራ ፡ ሸንተረሩ ፡ ያንሸራትታል ፡ ያዳልጣል — ኑዋሪውም ፡ እንደ ፡ አይጥና ፡ ድመት ፡ እንደ ፡ ተኩላና ፡ ፍየል ፡ ተፋጦ ፡ ዕድሜውን ፡ በሙሉ ፡ ድንግጥ ፡ ድንግጥ ፡ ፍርግግ ፡ ፍርግግ ፡ ንቅል ፡ ንቅል ፡ ትክል ፡ ትክል ፡ ሲል ፡ ነጠላ ፡ ትከሻ ፡ ሆኖ ፡ የተጠራበትን ፡ ምድራዊ ፡ ኑሮ ፡ በሕልም ፡ እሩጫና ፡ በገደል ፡ ማሚቶ ፡ ዘዬ ፡ ይጨርሳል - - - ይህ ፡ እንዳይሆን ፡ ታዲያ ፡ እንዴት ፡ ይከላከሏል ? እንደምንስ ፡ ራስን ፡ ይደልሏል - - ? አገራችን ፡ የጋራችን ፡ እንደ ፡ መሆኗ ፡ መጠን — አያት ፡ ቅድም ፡ አያት ፡ ቅም ፡ አያት - - -

« እቴ ፡ በወለዱሽ ፡ በናት ፡ ባባትሺ ፡
ነይልኝ ፡ እኔ ፡ ቤት ፡ አንዳፍታ ፡ ልይሺ ።

« - - ጣርማበር ፡ ላይ ፡ ሆኖ ፡ ይታያል - - - » በማለት ፡ እየዘፋፈነ ፡ በጐዳናው ፡ ይመጣል ። የወርካውን ፡ ሥር ፡ ሰው ፡ ተሰብስቦበት ፡ ሲያይ ፡ ዘፈኑን ፡ ያቋርጥና « ትውውሼ ! » በሚለው ፡ ቋንቋ ፡ ይቀጥላል — ቀርቃባቸውን ፡ እያስተካከለ—መንገድ ፡ የለቀቁትን ፡ አህዮች ፡ ጆሮ ፡ ጆሯቸውን ፡ እያጠኸዬ ፡ በመመለስ ።—

« - - - እንዲህ ፡ ካልሆነ ፡ ግን ፡ ከሰው ፡ የባሰ ፡ አውሬ ፡ የለምና ፡ እራሱን ፡ ስንኳን ፡ ለመግደል ፡ የማይመለሰው ፡ ፍጡር - - ሌላው ፡ ቀርቶ ፡ ጌታ ፡ የሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ እንኳ ፡ እንደገና ፡ ተወልዶ ፡ ቢመጣ — ዓላማውን ፡ የሚያሰናክልበት ፡ ሆኖ ፡ ካገኘው—ይሁዶች ፡ ካሠቃዩት ፡ የበለጠ ፡ አይሠሩ ፡ ሥራ ፡ እንደሚሠራው ፡ አይጠረጠርም - - -

« - - አንቺ ፡ በእንጉርጉሮ ፡ እኔ ፡ በፉጨት ፡
አልማዜ ፡ እንገናኝ ፡ ጀውሃ ፡ ጅረት » ሲል ፡ ይሰማል ፡ ነጋዴው ፡ ከሩቁ ።

« ታዲያንን ! ይህን ፡ የሰውን ፡ አውሬነት ፡ እንደምን ፡ ለማስወገድ ፡ ይቻላል - - - ? አንድነት ፡ ኀይል ፡ ኀይል ፡ አንድነት ፡ መሆኑን ፡ በማስገንዘብ ፡ ነዋ ! እያንዳንዳችን ፡ ራሳችንን ፡ በዚህ ፡ ጐዳና ፡ በመምራት ፡ ነዋ ! ምናልባት ! ምናልባት ! አንድነት ፡ ኀይልን ፡ ተሸከሞ ፡ ከጐዳናው ፡ አፍንጫ ፡ ላይ ፡ ብናገኘው - - - » በማለት ፡ ንባባቸውን ፡ ይጨርሱና ፡ በኃይል ፡ ተንፍሰው ፡ ወደ ፡ መቆሚያቸው ፡ አለፍ ፡ እላለሁ ፡ ሲሉ « - - - እረግኝ ፡ ዋ ፡ የኔ ፡ ነገር - - - ዋናውን ፡ ነገር ፡ ረስቸው - - እንግዲህ ፡ ሁላችሁም ፡ ለዚህ ፡ አንድነታችንን ፡ ለሚያጠነክረው ፡ ያማራው ፡ የጋላው ፡ ያዳሉ ፡ የእስላሙ ፡ ልጅ ፡ ለሚማርበት ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ የያቅማችሁን ፡ እርዳታ ፡ አድርጉ - - - በመሬት ፡ የሰጣችሁት ፡ በሰማይ ፡ ይቆያችኋል - - - እኔ ፡ በበኩሌ ፡ ይኸውና ፡ ሦስት ፡ ብር ፡ ረድቻለሁ - - - » ገንዘብ ፡ ለመቀበል ፡ ወደ ፡ ተዘጋጁት ፡ ወደ ፡ አቶ ፡ ወልዱ ፡ ይቀርቡና ፡ ሦስት ፡ ብሩን ፡ ይሰጣሉ « - - በነገራችን ፡ ላይ ፡ የምሥጢር ፡ ቤታችን ፡ ቆርቆሮ ፡ ስላረጀና ፡ መቅቀየር ፡ ስላለበት ፡ የእግዚአብሔር ፡ ወዳጆች ፡ የሆናችሁ ፡ ሁሉ ፡ የእርዳታ ፡ እጃችሁን ፡ እንድትዘረጉልን ፡ አሳስባችኋለሁ - - - ዞሮ ፡ ዞሮ ፡ በሙሉ ፡ ሲበላሽ ፡ ጉዳቱ ፡ የእናንተ ፡ መሆኑን ፡ በማሰብ ፡ ነው - - -

« ካራማራን ፡ ዞረሽ ፡ ጅጅጋን ፡ ያየሽው ፡
እንደልብሽ ፡ ኩራት ፡ የታል ፡ ያገኘሽው - - -

እያለ ፡ ይመጣል ፡ ሌላው ፡ ነጋዴ ፡ አህዮቹን ፡ አስቀድሞ—

« በቃሪያ ፡ በርበሬ ፡ አትሠሪም ፡ ዶሮ ፡
እንዴት ፡ ነው ፡ ጅጅጋ ፡ ካራማራን ፡ ዞሮ - - -

ይቀጥላል ፡ ነጋዴው — ወርካውን ፡ አልፎ ፡ ከሄደ ፡ በኋላ !

ፍሬዋ ፡ በተጻፈላት ፡ ደብዳቤ ፡ ውሀ ፡ እየቀዳች ፡ ትጫወትበታለች - - ሁለት ፡ ሦስት ፡ ጊዜ ፡ ስትዘግንበት ፡ ጽሑፉ ፡ ይደመሰሳል - - ወረቀቱ ፡ እጅዋ ፡ ላይ ፡ መበሳሰክ ፡ ሲጀምር — ጭራሹኑ ፡ ውሃው ፡ ላይ ፡ ትለቀዋለች ፤ ሳግ — ሳግ — ሳግ — ስጐ ፡ ሲያበቃው ፡ ቁልቁል — ይመነጠቃል ።

« ጣርማበር ፡ ላይ ፡ ሆኖ ፡ ይታያል ፡ አጋምበር ፡
ልቤን ፡ አናወጥሽው ፡ አረግሽው ፡ ፍር ፡ ፍር - - - » ያስተጋባል ፡
ነጋዴውን ፡ ጣርማበር ።

# ፲፫

## አደፍርስ

« ፍደሳ ፡ መቼም ፡ ዓይነት ፡ ዓይነት ፡ አለው — ለአጉልም ፡ ለበጐም ፡ ይሆናል ። ለበጐ ፡ ምግባር ፡ ዓይነተኛ ፡ ምልክት ፡ ሲሆን ፡ ኅብረተ፡ ሰባዊና ፡ ፖለቲካዊ ፡ ይዞታ ፡ ይኖረዋል ። ቤተ ፡ ሰባዊ ፡ አፋዳሽ ፡ የጋብቻን ፡ ትልቅነት ፡ የመውለድን ፡ የማሳደግን ፡ አስተምሮም ፡ ጠቃሚ ፡ ዜጋ ፡ ለሀገር ፡ የማበርከትን ፡ ያህል ፡ ደስታ ፡ ያለመኖሩን ፡ ያወራል ። ጋብቻን ፡ የማይፈልጉን ፡ ያገቡትንም ፡ የሚያኪያኪሱትን ፡ ሸንጡን ፡ ገትሮ ፡ ይከራከራል — የሞቀ ፡ የደመቀ ፡ ንብረት ፡ እንዴት ፡ እንደሚገኝ ፡ ልጆች ፡ በታረመ ፡ ሁኔታ ፡ እንዴት ፡ እንደሚያድጉ ፡ እንደሚበለጽጉ ፡ የተጠየቀ ፡ እንደሆነ — ስሜት ፡ በተሞላበት ፡ አንደበት ፡ ይናገራል - - -

« እራሱስ ፡ የሚናገረውን ፡ የሚሰብከውን ፡ ይኖረዋል - - ? » ይጠይቃቸዋል ፡ አደፍርስ ፡ እጐቱን ፡ አቶ ፡ ጥሶን — እጠለላ ፡ ቍጭ ብለው ፡ የምሽት ፡ አየራቸውን ፡ ሲቀበሉ —

« አላስጨረስከኝምኮ ! አስጨርሰኝ ፡ — የሃይማኖት ፡ አፋዳሽ ደግሞ ፡ አለ - - -

« እንደ ፡ ጧቱ ፡ እንደ ፡ አባ ፡ ዮሐንስ ፡ ዓይነት - - ! » ያቋርጣቸዋል ፡ እንደገና ፡ አደፍርስ ።

- - - አስጨርሰኝ ! የሃይማኖት ፡ አፋዳሽ - - - ስለ ፡ ሃይማኖት ፡ አስፈላጊነት ፡ ስለ ፡ እምነት ፡ ጥናት ፡ ስለማይመረመረው ፡ የእግዚአብሔር ፡ ሥልጣን ፡ ስለ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ስለ ፡ ገሃነመ ፡ እሳት - - ስለ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ትልቅነትና ፡ መሠረትነት—ስለነዚህና ፡ እነዚህን ፡ ስለመሳሰሉ ፡ ሌሎች ፡ ሁኔታዎች ፡ በሰፊው ፡ ያትትልሃል —ባገኘሽው ፡ ቁጥር ፡ ስለሌላ ፡ ነገር ፡ ጭራሹንም ፡ ማውራት ፡ አይሻም - - -

« እኔኮ ፡ የሚገርመኝ - -

- - - ቆይ ፡ ቆይ ፡ አስጨርሰኝ - - - ! እንግዲህ ፡ በዚህ ፡ ዓይነት ፡ መንገድ —የሀገር ፡ ፍቅር ፡ አፋዳሽ ፡ የገንዘብን ፡ ፍቅር ፡ አፋዳሽ ፡ የጎ

ብረተ ፡ ሰብ ፡ አፋዳሽ ፡ የሥልጣኔ ፡ አፋዳሽ ፡ የጥንታዊን ፡ ቅርስ ፡ አፋዳሽ ፡ ትምህርትን ፡ አፋዳሽ — ድንቁርናንም ፡ አፋዳሽ ፡ አይጠፋም ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ከሌላው ፡ ከተራ ፡ ዓይነት ፡ የሚያፋድሰውን ፡ ነገር ፡ ለይቶ ፡ ሳያውቅ ፡ ከመቅረቱ ፡ የተነሣ ፡ ባገኘሽው ፡ ቂጥር ፡ ማፋደሻውን ፡ ከሚለዋውጠው ፡ አጉል ፡ ወይም ፡ አምባልጋ ፡ አፋዳሽ ፡ ተለይተው ፡ የሚታወቁበት ፡ መምሪያ ፡ አላቸው ።— መታወቂያ ፡ አላቸው ።— ዐዋቂ፡ አፋዳሾች ፡ ናቸው - - -

« - - ዐዋቂም ፡ ሆኑ ፡ አላዋቂ ፡ መቼም ፡ ያው ፡ አፋዳሾች ፡ ናቸው ። የሚለፈልፉትን ፡ በሥራ ፡ የማይገልጹ ፡ ቢላሾች — የሀገር ፡ ሽክሞች — አምባ ፡ ገነኖች — አጉሎች - -

- - - አልተግባባንም ፡ አደፍርስ ፤ መጀመሪያ ፡ አስጨርሰኝ ። ዐዋቂ ፡ አፋዳሾች ፡ ናቸው ፡ ብየሃለሁ ። ምን ፡ ማለት ፡ ነው ፡ እንግዲህ ፡ ይኸ — ራሳቸው ፡ ማፋደሳቸውን ፡ ዐውቀው ፡ ነው ፡ ማለት፡ ነው ፡ የሚያፋድሱት ። ራሳቸው ፡ ራሳቸውን ፡ ጭምር ፡ መሸንገላቸው ፡ ይታወቃቸዋል ፤ ሌሎችም ፡ ሰዎች ፡ እንደሚያውቁባቸው ፡ ያውቃሉ ። ስለዚህ ፡ ማፋደሳቸውን ፡ የማያቋርጡት ፡ ዘበናይ ፡ የሚያሰኝ ፡ የኑሮ ፡ ግዳጅ ፡ ሆኖባቸው ፡ ነው - - -

« የኑሮ ፡ ግዳጅ ! የኑሮ ፡ ግዳጅ - - ? አብዮ ፡ ጥሶ - - - -

- - - አስጨርሰኝ ፡ አደፍርስ - - ! ለነሱ ፡ ፍደሳ ፡ የመልካም ፡ አነጋገር ፡ የመልካም ፡ አቋቋም ፡ የመልካም ፡ አኗኗር ፡ በጣም ፡ የሠለጠነ ፡ የዘበናይ ፡ ኅብረተ ፡ ሰብ ፡ ምልክታቸውና ፡ ማስፈራሪያቸው ፡ ነው ። ሰላምታ ፡ አሰጣጣቸው ፡ ምግብ ፡ አመጋገባቸው ፡ አለባበሳቸው ፡ አካሄዳቸው ፡ ሁሉ ፡ ነገራቸው ፡ የታቀደና ፡ የተመተረ ፡ ነው ። የነሱ ፡ ጐሳ ፡ የሆነውንና ፡ ያልሆነውን ፡ የሚለዩትም ፡ በዚሁ ፡ መለኪያቸው ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ደጉ ፡ ነገር ፡ ብቻ ፡ ይህ ፡ ግብዝነታቸው ፡ ዘበናይ ፡ ነን ፡ ብለው ፡ በሚያስቡት ፡ በነሱው ፡ አካባቢ ፡ ብቻ ፡ ተወስኖ ፡ መቅረቱ ፡ ነው ። እንዲያስ ፡ ባይሆን ፡ ኖሮ ፡ ሌላው ፡ ኅብረተ ፡ ሰብ ፡ ባልተለጐመ ፡ ዘመናዊ ፡ ፍላት ፡ ተቀቀለ ፡ ማለት ፡ ነበር ። በሀብትም ፡ ሆነ ፡ በደረጃ ፡ ከፍ ፡ ያሉ ፡ ሰዎች ፡ ብቻ ፡ ስጦታ ፡ በመሆኑ ፡ ግን ፡ ሲያያዝ ፡ የመጣው ፡ ያብዛኛው ፡ ሕዝብ ፡ ባህል ፡ ተጠበቀ ። ላብዛኛው ፡ ሰው ፡ ልቅ ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ ፡ ግን ፡ ለመለወጥ ፡ ወይም ፡ ለመወሰን ፡ የሚጥር ፡ ኅብረተ ፡ ሰብ ፡ ስለሚነሣ ፡ የተለየ ፡ ክብር ፡ አጐናጻፊነቱ ፡ ተደምስሶ—

ሕጋዊ ፡ መሆኑ ፡ ቀርቶ ፡ ባህላዊ ፡ አብሮ ፡ የመኖር ፡ ሥርዓት ፡ መሆኑ ፡ ቀርቶ ፡ ልማዳዊ ፡ ይሆን ፡ ነበር ፡ ማለት ፡ ነው ። ከፍተኛ ፡ ደረጃ ፡ ላይ ፡ ባሉ ፡ ሰዎች ፡ በገዥዎች ፡ ሲወሰን ፡ ግን ፡ ባህላዊ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ሕጋዊ ፡ ልማዳዊ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ አብሮ ፡ የመኖር ፡ ሥርዓት ፡ ወይም ፡ ድንጋጌ ፡ ስለሚሆን ፡ ከሥራቸው ፡ የሚኖሩትን ፡ ያርበደብድ ፡ ያንሸቀ ሸቅላቸዋል ፡ ነው ፡ የምልህ - - -

« - - እኮ ፡ አሁን ፡ የምትለው ፡ ፍደሳ ፡ በጥቂት ፡ ሰዎች ፡ ብቻ ፡ ሲወሰን ፡ ጥቅም ፡ ሊኖረው ፡ ይችላል ። አፋዳሾቹ ፡ ዐውቀው ፡ ስለሚሠ ሩበት ፡ ከሚያመጣው ፡ ጉዳት ፡ ይጠነቀቃሉ ፡ አይደለም ፡ የምትለኝ ?

« - - አዎ ፡ በመጠኑ ፡ እንዲያ ፡ ነው - - -

« ሞትና ፡ ሕይወት ፡ ድንቁርናና ፡ ዕውቀት - - - ! ታዲያ ፡ እሺ ፡ ዐውቀውትም ፡ በራሳቸው ፡ ላይ ፡ የሚያመጣውን ፡ ጉዳት ፡ መከላከል ፡ አቅቷቸው ፡ ያየህስ ፡ እንደሁ ? ከጊዜ ፡ ብዛት ፡ አምነው ፡ ያልጀመሩ ትን ፡ ራሱን ፡ የሐሰቱን ፡ ፕሮፓጋንዳ ፡ ሆነው ፡ ያገኘሃቸውስ ፡ እንደሁ ? የሚናገሩትና ፡ እናምንበታለን ፡ የሚሉት ፡ ከሚሠሩት ፡ ሥራ ፡ ጋር ፡ ሲያ ስተያዩት ፡ እንደ ፡ ሰማይና ፡ ምድር ፡ ርቆ ፡ ያየኸውስ ፡ እንደሁ - - - ?

« እዚህ ፡ ላይ ፡ መልሱ ፡ አጭር ፡ ነው ፤ አንደኛ ፡ አፋዳሽ ፡ ለአፋ ዳሽ ፡ ስለሚግባባ ፡ የሚነገረው ፡ ማንኛውም ፡ ፍደሳ ፡ ጊዜያዊ ፡ እንደ ሆነ ፡ ይተዋወቃል — መሳቂያና ፡ ጊዜ ፡ ማሳለፊያ ፡ እንጂ ፡ ለአእም ሮው ፡ ምግብ ፡ እንዳልሆነ ፡ ያውቃል — እንደ ፡ አንገት ፡ በላይ ፡ ሳቅ ፡ ማለት ፡ ነው ። — ሁለተኛ ፡ ከጊዜ ፡ ብዛት ፡ የሚናገሩት ፡ ሐሳብ ፡ ምስ ልም ፡ ቢሆኑ ፡ የሚናገሩትና ፡ የሚሠሩትም ፡ ቢለያይ ፡ የሚኖሩበት ፡ ኅብ ረተ ፡ ሰብና ፡ አካባቢ ፡ የተለየ ፡ ስለሆነ ፡ የውጭ ፡ ግለ ፡ ሰብእ ፡ መጥቶ ፡ ንግግራቸውን ፡ ከአድራጐታቸው ፡ ጋር ፡ አስተያይቶ ፡ ሊታዘባቸውም ፡ ሆነ ፡ ሊፈርድባቸው ፡ እድል ፡ አይገጥመውም—እርስ ፡ በርሳቸው ፡ ቢሆን ፡ ቅድም ፡ እንዳልኩት ፡ ይተዋወቃሉ — እትዝብት ፡ አይደራረሱም - - -

«እሺ—እኔ ፡ ግለ ፡ ሰቡ ፡ አንተ ፡ እንዳልከው ፡ ሳይሆን ፡ ሰውዬው ፡ የተናገረውን ፡ ካዳመጥሁ ፡ በኋላ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ እንዴት ፡ እንደሚያ ውለው ፡ ለማየት ፡ ተከታትዬ ፡ የምደርስበት ፡ ዘዴ ፡ ያገኘሁስ ፡ እንደሁ ?

« - - አይጠቅምህም — ቀጣፊ ፡ ለፍላፊ ፡ እበላ ፡ ባይ - - - አጭ በርባሪ ፡ የሚል ፡ ሕዝብ ፡ ነው ፡ ዙሪያህን ፡ ያጠረህ ፡ አንተን ። የሱን ፡

ሁኔታ ፡ የምትቀዳበት ፡ አካባቢ ፡ የለህም — ኑሮህን ፡ የምትደብቅበት ፡
ግቢ ፡ የለህም ፡፡- ድንቁርናህን ፡ የምትሸፍንበት ፡ ሀብት ፡ የለህም —
ምን ፡ አለፋህ ፡ ብቻ ፡ ተከታትለህም ፡ ብትደርስበት — አንደኛ ፡ ባገኘ
ኸው ፡ ውጤት ፡ የሚያምን — ሁለተኛ ፡ እንደ ፡ ሰውዬው ፡ ለመሆን ፡
ብትሞክር — ሁኔታህን ፡ የሚቀበል ፡ ኅብረተ ፡ ሰብእ ፡ አይደለም ፡
የከበበህ ፡ ነው ፡ የምልህ — ለፍላፊ — እበላ ፡ ባይ ፡ የሚሉትን ፡ ቅጽ
ሎች ፡ ነው ፡ የምታተርፈው ፡ ነው ፡ የምልህ - - -

« - - - የለም ፡ የለም ፡ ጋሼ ፡ ጥሶ — የሀገሩ ፡ ሰው ፡ እውነተኛ ፡
ሁኔታ ፡ መታወቅ ፡ አለበት - - -

« - - - ባጉል ፡ ዝላይ ፡ እንዲታወቅ ፡ ለማድረግና ፡ ለውጥ ፡ ለማ
ምጣት ፡ አይቻልም ፡ አደፍርስ - - - ስለ ፡ ሀገሩ ፡ ሁኔታ ፡ አጥልቆ ፡
ሳያውቁ ፡ በዩኒቨርስቲ ፡ ውስጥ ፡ ወይም ፡ በቢሮ ፡ ውስጥ ፡ ብቻ ፡ ይሠራ
በመሰለ ፡ መላ ፡ ምት ፡ ተነሣሥቶ ፡ ይኸ ፡ ይኸ ፡ መሆን ፡ አለበት ፡
ማለት ፡ በቂ ፡ አይደለም ፡፡ እርግጥ ፡ እንዳልከው ፡ የሀገሩ ፡ ሰው ፡ እው
ነተኛ ፡ መንፈስ ፡ መታወቅ ፡ አለበት ፤ ግን ፡ የኔ ፡ መታወቅ ፡ አለበት ፡
ከአንተ ፡ መታወቅ ፡ አለበት ፡ የሚለይ ፡ ይመስለኛል — የኔ ፡ መታወቅ ፡
አለበት — የሰዉ ፡ አስተሳሰብ — የኔ ፡ ኅሊና ፡ የማይቀበለው ፡ አጉል፡
ዓይነት ፡ እንኳ ፡ ቢሆን ፡ እሱኑ ፡ ጠንቅቆ ፡ ዐውቆ ፡ ማንኛውም ፡ መሻሻ
ልም ፡ ሆነ ፡ ለውጥ ፡ በሱ ፡ ላይ ፡ መመሥረት ፡ አለበት ፡ ባይ ፡ ነው ፡፡
ያ ፡ ምናልባት ፡ ለኔ ፡ አጉል ፡ መስሎ ፡ የሚታየኝ ፡ የሕዝብ ፡ መንፈስ ፡
ዓላማውን ፡ ዐውቆ ፡ አጥብቆ ፡ የሚከተል ፡ መሆኑን ፡ መርሳት ፡ የለብ
ኝም ፡፡—በሃይማኖትህ— በንብረትህ — በመሬትህ ፡ መጣብህ ፡ በለው—
ጋሻውን ፡ አንግቦ ፡ ጦሩን ፡ ነቅንቆ ፡ ይነሣል — ግብ ፡ አለው ፡፡ የምት
ጠጣውን ፡ ውሃ ፡ የሚመርዝ ፡ የምትዘራውን ፡ እህል ፡ የሚያጠፋ —
ደክመህ ፡ እቤትህ ፡ ስትመጣ ፡ የማያስተኛ ፡ ሥልጣኔ ፡ መጣብህ ፡ በለው ፡
— ዓይኑ ፡ ደም ፡ ጎርሶ ፡ ጠመንጃውን ፡ አንግቦ ፡ ይነሣል — ግብ ፡
አለው ፡፡ ስለዚህ ፡ ማንኛውም ፡ ለውጥ ፡ በነዚህ ፡ የመንፈስ ፡ አለኝታ
ነት ፡ ነው ፡ መገልገል ፡ ያለበት—አለዚያ ፡ የማይበጅን ፡ የማይጠቅምን
— ውሸት ፡ መስሎ ፡ የሚገመት ፡ ማንኛውንም ፡ ነገር ፡ ለመቋቋም ፡ የሚ
ደረገው ፡ ትግል ፡ አጉል ፡ ይሆናል - - -

« - - - እኮ ፡ በዚህ ፡ አስተያየት ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ፊታችንን ፡ ሌላው
ዓለም ፡ ይወቀው ፤ ራሱን ፡ የቻለ ፡ እንጂ ፡ ግልባጭ ፡ አለመሆኑን ፡

ይረዳው ፡ ማለት — ዓላማ ፡ የሌለው ፡ ነው ፡ ማለት ፡ ነው - - - ? በሀ ገር ፡ ፍቅር ፡ በሃይማኖት ፡ ጽኑነት ፡ በንብረት ፡ አክባሪነት ፡ ኩር ትም ፡ ብሎ ፡ በወንድነት ፡ በጀግንነት ፡ በቆራጥነት ፡ በልበ ፡ ሰፊነት ፡ በእንግዳ ፡ ተቀባይነት ፡ የዳጐሰው ፡ ፊታችን — የአንዱን ፡ የእንስሳ ፡ ዘር ፡ ፊት ፡ ከሌላው ፡ ተመሳሳይ ፡ እንስሳ ፡ መለየት ፡ እንደማይቻለው ፡ እንደ ፡ ውሻ ፡ ሙርሙር ፡ አይቆጠር — ኢትዮጵያዊ ፡ መልካችን ፡ ይገለጥ — ይመርመር ፡ ማለት ፡ ዓላማ ፡ አይደለም ፡ ማለት ፡ ነው ?

« - - - እስካሁን ፡ በለፈለፍኩት ፡ የገባህ ፡ ይኸ ፡ ከሆነ ፡ ጥፋተኛ ው ፡ እኔ ፡ ነኝ ። በተራዛሚም ፡ መንገድ ፡ እንኳ ፡ ቢሆን ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ መልካችን ፡ ተለይቶ ፡ አይታወቅ ፡ የሚል ፡ አነጋገር ፡ በአንደበቴ ፡ የገባ፡ አይመስለኝም ። ይልቁንም ፡ መገለጥ ፡ አለበት ፡ ብዬ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን፡ የማምነው ፡ የሚያይ ፡ ታገኘ ፡ ምን ፡ ጊዜም ፡ እንደተገለጠ ፡ ነው ፡ ብዬ ነው ። ንጉሥ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ የሚለው ፡ የኢትዮጵያ ፡ መሪዎች ፡ የማዕረግ ፡ ስም ፡ በሌላው ፡ ዓለም ፡ በብዛት ፡ ከሚሠራበት — ፕሬዚ ደንት ፡ ጠቅላይ ፡ ሚኒስትር ፡ ከሚለው ፡ የማዕረግ ፡ ስም ፡ ይልቅ ፡ የበ ለጠ ፡ ግዳጅን ፡ ይጠይቃል ። መሠረታችንን ፡ አጽንቶ ፡ አንድነታችንን፡ አጠንክሮ ፡ የነበረውንና ፡ የሚኖረውን ፡ ፊታችንን ፡ አስተካክሎና ፡ አዋሕዶ ፡ የሚገልጽ ፡ መልክ ፡ መያዝ ፡ አለበት ። አንድ ፡ ጠቅላይ ፡ ሚኒ ስትር ፡ ወይም ፡ አንድ ፡ ፕሬዚደንት ፡ የመንግሥቱ ፡ የአስተዳደሩ ፡ መሪ ነው ።- አንድ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ግን ፡ ከእንደዚህ ፡ ዓይነቱ ፡ ጊዚያዊ ፡ መረዳዳት ፡ በላይ ፡ ነው — ሀገሩና ፡ የሀገሩ ፡ ሰው ፡ ላለው ፡ ወይም ፡ እያ ንዳንዱ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ሊኖረው ፡ ለሚመኘው ፡ ኑዋሪና ፡ ዘላቂ ፡ ለሆነ፡ ባህል—ቅርስ ፡ ወግና ፡ ልማድ—አስተሳሰብና ፡ ሰብእና ፡ ሁሉ ፡ ማንጸባረ ቂያ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ነው ። የፕሬዚደንቱ ፡ ወይም ፡ የጠቅላይ ፡ ሚኒስ ትሩ ፡ የግል ፡ ልማድ ፡ የግል ፡ አስተሳሰብ ፡ የግል ፡ አኗኗር ፡ ዘዴ ፡ ሊኖር፡ ይችላል - - ካስተዳደር ፡ ሥራቸው ፡ ውጭ ፡ የሚያሳዩት ፡ ማንኛውም ፡ ነገር ፡ በግላዊ ፡ መንገድ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ እኔን ፡ አይመለከተኝም — የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ ግን ፡ የራሴም ፡ ጭምር ፡ ነው ። የማንኛውም ፡ ዘላቂ ፡ ነገር ፡ ማንጸባረቂያዬ ፡ ስለሆኑ — የሚናገሩትም፡ ሆነ ፡ የሚሠሩት ፡ ግላዊውም ፡ ሆነ ፡ ሕዝባዊው ፡ ሥራቸው ፡ ሁሉ ፡ ኢትዮጵያዊነቴ ፡ የሚታይበት ፡ መሆን ፡ አለበት ። ስለዚህ ፡ ስለ ፡ ንጉሠ ነገሥቴ ፡ አጉል ፡ ነገር ፡ ለመስማት ፡ አልፈልግም ። ምናልባት ፡ አንዳ ንድ ፡ ለመቀለድ ፡ ለማሾፍ ፡ ወይም ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱን ፡ ለማረም ፡ ለማ

ኪያኪያስ—ለመንቀፍ ፡ የሚነሣ ፡ ቢኖርም ፡ ወደ ፡ ኋላዬ ፡ የማልል ፡ ጠላቱ ፡ ነኝ - - -

« - - ሞትና ፡ ሕይወት ! እሱን ፡ አላጣሁትም ፤ ብቻ ፡ እኔ ፡ የምለው! ‘ ቅዳሴ ፡ ቢጐድልበት ፡ ቀረርቶ ፡ ሞላበት ’ እንዳንባል ፡ ንጉሡ ፡ ነገሥታችን ፡ እንዲያንጸባርቁ ፡ ከፈለግን ፡ ትንሽ ፡ ትንሽ ፡ እንዳቅማችን ፡ ብርሃን ፡ እንሁናቸው ፡ ነው ፡ — የኛ ፡ ብርሃን ፡ ከያለበት ፡ ሲንተገተግ ፡ ነው ፡ የሳቸው ፡ ጸዳል ፡ የሚያበራው ፡ ነው ፡ የምለው - - -

« ‘ አድላዊ ፡ ዳኛ ፡ እምጣ ፡ ይላል ፡ የዶሮ ፡ ሻኛ ’ እንዳትባሉ ፡ እንጂ ፡ ብርሃን ፡ መስጠታችሁም ፡ ሆነ ፡ ለመስጠት ፡ መፈለጋችሁ ፡ አያጣላንም ። — እንዲያውም ፡ ሀብታችን ፡ እስከፈቀደልን ፡ ያህል — ሰውነታችሁን ፡ ማንቂያ ፡ የሚሆኑ ፡ የትምህርት ፡ ቤቶች ፡ የተከፈቱላችሁ ፡ የብርሃንነታችሁ ፡ አስፈላጊነት ፡ ስለታወቀ ፡ ነው - - -

እቤት ፡ ውስጥ ፡ ወይዘሮ ፡ አከላት ፡ በገናቸውን ፡ መቃኘት ፡ ጀምረዋል - - አንዳንዴ ፡ የሚተከዙ ፡ አንዳንዴ ፡ የሚያለቅሱ ፡ አንዳንዴ ፡ የሚለምኑ ፡ ድምፆች ፡ ይስረገረጋሉ ። ግርማዊ ፡ ሞገሳዊ ፡ መንፈሳዊ ፡ ድምፆች ፡ ይዘንባሉ - - ሰሚዎችን ፡ ከወገባቸው ፡ ቀና ፡ አድርገው ፡ አንገታቸውን ፡ እንዲያነሡ ፡ የሚኮረኩሩ—የልብን ፡ ግመት ፡ እየቀሰቀሱ ፡ የዝናን ፡ የመታወቅን ፡ ሕልም ፡ የሚደባብሱ ፡ ይመስላል ። እንደ ፡ ታፈነ ፡ እንደ ታመቀ—ከሩቁ ፡ እንደሚሰማ ፡ ያጀብ ፡ ድምፅ ፡ እንደ ፡ ታዛዥ ፡ አድናቂ ፡ ዜጋዎች ፡ እልልታና ፡ ውካታ ፡ አውራውን ፡ ተከትሎ ፡ እንደሚያስገመግም ፡ የንብ ፡ ሠራዊት - - ያምማል - - - ያምማል - - የወይዘሮ አከላት ፡ በገና - - የሰውን ፡ ልጅ ፡ ድካምና ፡ የግቡን ፡ አይደረሴነት ፡ የሚያወሳ ፡ በመምሰል - - ያምማል - - ያምማል - - ያምማል - - - ተስፋ ፡ እንደ ፡ ቆረጠ ፡ ልብ ፡ አውታር ፡ የጎሊና ፡ ነውጽ ፡ እንደተሰማው ፡ አፍቃሪ ፡ ረዘም ፡ ባለ—የተሰነጠበ ፡ በሚመስል ፡ እንደ ፡ ሾህ ፡ በሚወጋ ፡ እፎይታ ፡ በመፈጸም - - -

አቶ ፡ ጥሶ ፡ በኃይል ፡ ተንጠራርተው ፡ ከመቀመጫቸው ፡ በመነሣት ፡ ከበረንዳው ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ውስጥ ፡ ይገባሉ ።— አደፍርስም ፡ ወዲያው ፡ ይከተላቸዋል — ትንሽ ፡ ቆይቶ — የሕፃናትን ፡ ጫጫታ ፡ የልጆችን ፡ ጩኸት ፡ የሕይወትን ፡ ያልታፈነ ፡ ድምፅ ፡ የሚመስል — ስርግርግታ ፡ ከቤት ፡ ውስጥ ፡ መፍለቅ ፡ ይጀምራል - - - እየደደረ — እየለዘበ - - እያንቋረረ — እየበራ — እየጠፋ - - - የአደፍርስ ፡ አኮርዲዮን ።

በጣርማበር ፡ ተራራ ፡ ላይ ፡ ጥቁር ፡ ዳመናዎች ፡ ትርምስምስ ፡ መሥመር ፡ እየሠሩ ፡ ይላወሳሉ ። ሥር ፡ ሥሩን — ጫካና ፡ ተረተሮቹን ፡ እታች ፡ ረባዳው ፡ ከተማው ፡ ድረስ ፡ ስስ ፡ ወተትማ ፡ ጭጋግ ፡ አፍኗቸዋል ። ኃይለኛ ፡ ደረቅ ፡ ነፋስ ፡ ሳያቋርጥ ፡ ይነፍሳል — ቃጠሎ ፡ ቃጠሎ በሚል ፡ ሽታ — አፍንጫን ፡ አብሶ ፡ እያለፈ - - -

# ፲፬

# አደፍርስ

ወይዘሮ ፡ አሰጋሽ ፡ የተቻላቸው ፡ እመቤት ፡ ናቸው ። የሚቼ ፡ ባለቤ ታቸው ፡የሻለቃ ፡ ይነሡ ፡ ሀብት ፡ ብቻ ፡ ቀላል ፡ አልነበረም ፤ ባይበልጥ አሥር ፡ ጋሻ ፡ የሚሆን ፡ ባገልግሎት ፡ የተገኘ ፡ የማደሪያ ፡ መሬት —ያባታ ቸው ፡ የነበረ ፡ ለብቻው ፡ ጠጅ ፡ የሚያጠጣ ፡ ርስተ ፡ ጉልት - - - - በተ ለይ ፡ በገባሮቻቸው ፡ ላይ ፡ ግብር ፡ የመጨመርም ፡ ሆነ ፡ የመማር ፡ መብት፡ ስለነበራቸው ፡ በውስጡ ፡ የሚተዳደሩትን ፡ ሁሉ ፡ አንሸቅሽቀው ፡ የሚ ገዙበት—(በአንድ ፡ ጋሻ ፡ ብቻ—አንድ ፡ ጉንዶ ፡ ማር ፡ ማስከፈል ፡ ሚሶ፡ ማሳረስ ፡ ሦስት ፡ ዳውላ ፡ እህል ፡ ማስገበር ፡ አምስት ፡ ቁና ፡ እህል ፡ ወፍጮ ፡ ማስፈጨት ፡ ጐተራ ፡ ማስጠበቅ ፡ እንጨት ፡ ለማገዶ ፡ ማስ ቀረብ ፡ ቀላል ፡ ነገር ፡ አልነበረም) —አንድ ፡ ሻምበልና ፡ የበታች ፡ ሹማ ምንት ፡ የሚያስተዳድር ፡ የመንግሥት ፡ ሁዳድ - - - በጠቅላላው ፡ የባ ሌን ፡ ነፍስ ፡ ይማር ፡ ብለው ፡ ሳይጸልዩ ፡ የማያልፉበት ፡ ሰፊ ፡ ይዞታ ፡ ነበራቸው ።

በራሳቸው ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፡ ከነአለቅነቱ ፡ ከአባታቸው ፡ የወረሱት ፡ ርስት ፡ ነበራቸው ። —ባለቤታቸው ፡ በሕይወት ፡ በነበሩ ፡ ጊዜ ፡ በተለይ ፡ ባለቅነታቸው ፡ ብቻ ፡ ቀጥታ ፡ ከየምንዝሮቻቸው ፡ ከሚያዙት ፡ የማርና ፡ ዶሮ ፡ ግብር ፡ ሌላ ፡ ይጠይቁት ፡ የነበረው ፡ ግዳጅ ፡ ሀብታም ፡ የሚባል ፡ ሰው ፡ እንኳ ፡ የሚቀናበት ፡ ነበር ፡ — አረም ፡ ማሳረም ፡ እርሻ ፡ ማሳረስ ፡ ውቂያ ፡ ማስወቃት - - - ውሃ ፡ እስከማስቀዳት ፡ እንጨት ፡ እስከማስ ለቀም ፡ ከብት ፡ እስከማሳገድ ፡ ድረስ ። — በተለይማ ፡ በእርሻና ፡ በዘር ፡ ወራት ፡ ምንዝሮች ፡ ሲባሉ ፡ የማያዛቸው ፡ ሹም ፡ አልነበረም ፤ አለቃው ፡ ሻለቃው ፡ መልከኛው - - - ሁሉ ፡ የኔ ፡ ሥራ ፡ ይሠራ ፡ ባይ ፡ ነበር ። ስለዚህም ፡ የየምንዝሮቹ ፡ ሥራ ፡ ዞላ ፡ እየቀረ ፡ ችጋር ፡ ቤታቸውን ፡ ይፈታዋል—ልጆቻቸውን ፡ ለረኀነት ፡ ሚስቶቻቸውን ፡ ለፈጫይና ፡ ለፈታ ይ ፡ ራሳቸውን ፡ ለግብርና ፡ ላጃቢነትና ፡ ለተከታይነት ፡ ያሳድራሉ ።— በመጨረሻም ፡ ውቃቢ ፡ ርቋቸው ፡ የራስን ፡ መቻል ፡ ኑሮ ፡ አንገፍግፏ ቸው ፡ ቤታቸውን ፡ ዘግተው ፡ ቤተሰባቸውን ፡ እስከ ፡ መበተን ፡ ይደርሳሉ ወይም ፡ ጠቅልለው ፡ ለሻለቃው ፡ ለአለቃው ፡ ለመልከኛው ፡ ያድራሉ ።—

ባሁኑ ፡ ጊዜ ፡ ማንኛውም ፡ ቁጥጥር ፡ ጴጥሮስ ፡ በሚባል ፡ የቅርብ ፡ ረዳታቸው ፡ አማካይነት ፡ በወይዘሮ ፡ አሰጋሽ ፡ ሥር ፡ የሚካሄድ ፡ ስለ ሆነ ፡ አብዛኛው ፡ ግዳጅ ፡ እየቀረ ፡ ሄዷል ። እርግጥ ፡ አሁንም ፡ እቤት ፡ ካሉት ፡ እረኞች ፡ ውስጥ ፡ ሁለቱ ፡ በግብር ፡ የተያዙ ፡ ናቸው ፡ አባቶቻቸው ፡ ግብሩን ፡ እስኪከፍሉ ፡ ድረስ ፡ ሊያገለግሉ ፡ የመጡ ።— ሆኖም ፡ ልጆቹን ፡ የተቀበሉት ፡ ተለምነው ፡ ለነፍሴ ፡ ብለው ፡ ነበር ፡ እንጂ ፡ አስገድደው ፡ አልነበረም ።— ስለዚህ ፡ የዱሮ ፡ አስተዳደር ፡ ይዞታቸው ፡ አብዛኛው ፡ ቀርቷል ። ምናልባት ፡ ያልቀረ ፡ ነገር ፡ ቢኖር ' እኔን ፡ መንገድ ፡ ላይ ፡ ስታውኝ ፡ አትጋፉኝ ፡ ሽረር ፡ ብላችሁ ፡ መንገድ ፡ ልቀቁልኝ ' የሚለው ፡ አስተሳሰባቸው ፡ ይሆን ፡ ይሆናል ።

ዛሬ ፡ ከአዲስ ፡ አበባ ፡ የወረዱትን ፡ የከፍተኛ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ዳኞች ፡ የሚጋብዙበት ፡ ቀን ፡ ስለ ፡ ሆነ—ዝግጅቱ ፡ ከሌሊት ፡ ጀምሮ ፡ በመጣደፍ ፡ ላይ ፡ ነው ። ጴጥሮስ ፡ የሀብታቸው ፡ ሁሉ ፡ የበላይ ፡ ተቆጣጣሪ ፡ ሠርግና ፡ ምላሹ ፡ ሆኗል ። ከቁመናው ፡ ሰፋ ፡ ብሎ ፡ የወጣ ፡ ሹል ፡ ግምባር ፡ ጥርጣሬ ፡ የተሞሉ ፡ ትንንሽ ፡ ዓይኖች ፡ ልል ፡ ጉንጮች ፡ ያሉት ፡ ኩርፋ ፡ ፊት ፡ መሳይ ፡ ቢሆንም ፡ አጋጊጦ ፡ ከወዲያ ፡ ወዲህ ፡ ተፍ ፡ ተፍ ፡ ሲል ፡ ሲያውት ፡ በቤቱ ፡ ያለው ፡ እሱው ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ የሚመስለው ። ሽር ፡ ጉድን ፡ ከመጠን ፡ በላይ ፡ ይወዳል ፤ በተለይ ፡ እንደ ዚህ ፡ እንደዛሬው ፡ ዳኞች ፡ በሚጋበዙበት ፡ ጊዜ ፡ ዙሪያውን ፡ ሲያንጃብብና ፡ ጠብ ፡ ርግፍ ፡ ሲል ፡ መታየት ፡ ልማዱ ፡ ነው ። ደረጃውን ፡ የማሳየት ፡ ፍላጐቱ ፡ ይጠናበታል ። ራሱን ፡ ቢያከብሩት ፡ ባያከብሩትም ፡ እምብዛም ፡ ደንታ ፡ ያለው ፡ ስለማይመስል ፡ እሱም ፡ ሁኔታው ፡ ካላስገደደው ፡ በቀር ፡ ሌላን ፡ ሰው ፡ የማክበር ፡ ልማድ ፡ አይታይበትም ። ውርደት ፡ የፈለጉትን ፡ ማጣት ፡ እንጂ ፡ ፍላጐትን ፡ ለማግኘት ፡ ሲባል ፡ የሚደርሰው ፡ ርግጫና ፡ ግልምጫ ፡ አይደለም ፡ ባይ ፡ ነው ።— በመክሊታዊነት ፡ ላይ ፡ የተመሠረተው ፡ እምነቱ ፡ ዘለቄታ ፡ ያለው ፡ የመኖር ፡ ፈትሕ ፡ ሆኖ ፡ አግኝቶታል ።—

ወይዘሮ ፡ አሰጋሽ ፡ እንደ ፡ ሌሎቹ ፡ ሠራተኞች ፡ ሁሉ ፡ ማልደው ፡ ተነሥተው ፡ ነበርና ፡ አሁን ፡ እወርዶፋ ፡ ጐጆ ፡ በር ፡ አጠገብ ፡ እግርምቡድ ፡ ላይ ፡ አረፍ ፡ ብለዋል ።—በትክሻቸው ፡ ላይ ፡ አንገት ፡ ልብስ ፡ ጣል ፡ አድርገው ። በጃቸው ፡ መታረሪያ ፡ ዓይነት የቀጨጭ ፡ እንጨት ፡ ይዘዋል ።— ከአሥር ፡ ወይም ፡ ከአሥራ ፡ ሁለት ፡ ዓመት ፡ ዕድሜ ፡ በላይ ፡ የማይሆነው ፡ ወንድ ፡ ልጅ ፡ የጸጉራቸውን ፡ አናት ፡ ቀስ ፡ እያለ ፡ ይነድፍላቸ

ዋል — በደጋን ፡ ብን ፡ ብሎ ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ እንዲጨፈቅ ። አንዲት ፡ ኮረዳ፡ ጫማዎቻቸውን ፡ አጥባ ፡ ጨርሳ ፡ ጥፍራቸውን ፡ ታስተካክላለች ። ሥጋ ቸውን ፡ ቆንጠር ፡ በማድረግ ፡ ታሳምማቸዋለች ፡ መሰለኝ ፡ ራቧን ፡ ቋ ፡ ይሰጧታል ፡ እንደዘበት — በመታረሪያው ።

እንግዶቹን ፡ የሚቀበሉበት ፡ ዋናው ፡ እልፍኛቸው ፡ በሚገባ ፡ ተዘ ጋጅቷል ። በየማዕዘኑ ፡ ሦስት ፡ መሶበ ፡ ወርቆች ፡ ቁጭ ፡ ቁጭ ፡ ብለ ዋል — እስከየግርጌ ፡ እስከየግርጊያቸው ፡ የሚጀቡን ፡ ጃኖ ፡ ለብሰው ። አጠር ፡ ያለ ፡ የሳጠራ ፡ ገበታ ፡ መካከል ፡ ገደማ ፡ ተዘርግቷል ፤ ባንድ ፡ ፊት ፡ ባለመቀመጫና ፡ ንቅሳታም ፡ ሽክናዎች ፡ ባንድ ፡ ፊት ፡ ብርጭቆ ዎች ፡ ተደርድረውበታል ። በአንድ ፡ ሰታቴና ፡ በሁለት ፡ አነስ ፡ አነስ ፡ ያሉ ፡ ድስቶች ፡ የሚቁላላው ፡ ሽንኩርት ፡ ድልህና ፡ ቅቤ—በምሰሶው ፡ ዙሪያ ፡ የተሰቀለው ፡ ጮማ ፡ የሆነ ፡ ትኩስ ፡ የሙክት ፡ ሥጋ—በመካከ ለኛ ፡ ጋን ፡ የተሰየመው ፡ የሚሰነፍጥ ፡ አዲስ ፡ የተቀዳ ፡ የማሽላ ፡ ጠላ— ውሃው ፡ ያልረገፈ ፡ ትኩስ ፡ ታጭዶ ፡ የተጎዘጎዘው ፡ ሣር—ዝናብ ፡ ካጨ ቀየው ፡ በረት ፡ ውስጥ ፡ እየተግፈጠፈጠ ፡ የሚነሣው ፡ ያዛባና ፡ የከ ብት ፡ ሽታ — አንድነት ፡ ሆነው ፡ ልብን ፡ ናድ ፡ ናድ ፡ የሚያደርግ ፡ ዓይነት ፡ ዓየር ፡ ሰጥተውታል ፡ ለእልፍኙ—ነፍስን ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ ጐትቶ ፡ እጐሮሮ ፡ ውስጥ ፡ የሚወትፍ ፡ ውደት - - -

«- - -እንግዲህ ፡ የማስተናገዱን ፡ ነገር ፡ ባንተ ፡ ትቸዋለሁ»ይላሉ ፡ ወይዘሮ ፡ አሰጋሽ ፡ ለጴጥሮስ ፡ ታጥበው ፡ ተበጥረው ፡ ተኩለው ፡ አጊ ጠው ፡ ከጨረሱ ፡ በኋላ—የእልፍኙን ፡ ውስጥ ፡ ዝግጅት ፡ አንድ ፡ ባንድ ፡ እየተመለካከቱ «- - ስለ ፡ ክትፎውና ፡ ስለ ፡ ቁርጥ ፡ ሥጋው ፡ ስላልጫው ፡ ስለቀይ ፡ ወጡና ፡ ስለፍትፍቱ ፡ እኔም ፡ ቄሱ ፡ ነኝ ፡ አላስቸግርህም - - - ስለዚህ ‘ ስላሮቶ ’ ለጋ ፡ ጥብስ ፡ ብስል ፡ ጥብስ ፡ ስለምትለው ፡ የፈረ ንጅ ፡ ቅርንጥህ ፡ ነው ፡ ትንሽ ፡ ግራ ፡ ገባ ፡ ያለኝ - - - ደሞ ፡ ምንድነው ፡ ያ ፡ ሌላ ፡ ነገርህ ‘ ዎሞሌ ’ ነው ፡ ምንድነው ፡ የምትለው ? ስለ ፡ ዕንቁ ላል - - - አዎ ፡ እሱ ፡ እሱን ፡ ባንተ ፡ ላይ ፡ ጥየዋለሁ - - - ጣጣ ፡ ነገር ፡ በፈረንጅ ፡ ስም ፡ ካልተጠራ ፡ በቀር ፡ ሥልጥንና ፡ አይደለም ፡ የሚሉ ፡ ፈሊጥ ።— አንድ ፡ አዲስ ፡ ነገር ፡ አናይበት ፡ ተሠርቶ ፡ ሲቀርብ - - - እስኪ ፡ ላንተም ፡ ይታይህ - - እሁን ፡ ጤፍ ፡ እንጀራን ፡ በፈረንጅ ፡ አፍ ፡ ብትጠራው ፡ ባበሻ ፡ አፍ - - -እርቦኝ ፡ ከፈለግሁት ፡ ዘንዳ ፡ ልተ ወው ፡ ማለት ? ጤፍ ፡ ያው ፡ ጤፍ ፡ ነው ፡ ውላጁ — በማንም ፡ አፍ ፡ ተናገርከው ፡ መልኩንም ፡ ሆነ ፡ ጣሙን ፡ አይለውጥም — ራብ ፡ ብቻ ፡

ሁሉን ፡ አጣፋጭ — ሌላው ፡ ዘበት ፡ ነው - - እና ፡ ታዲያ ፡ ሁሉንም ፡ ነገር ፡ ልቤ ፡ እያወቀው ፡ ነው ፡ እንደ ፡ ብጤህ ፡ ያልኩት - -

« እኔ ፡ መቼም ፡ በምን ፡ በኩል ፡ ነኝ ፡ የምይረዳቸው ፡ ቢዬ ፡ ሳስብ ፡ መጀመሪያ ፡ በጆሮዬ ፡ ወሬ ፡ የምሰማቸው ፡ የነበርኩ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የምግብ ፡ ስም ፡ ትዝ ፡ አለኝ - - - እኛ ፡ ባላገሮች ፡ እንዳይመስል - - - የዛሬ ፡ ሊቃውንት ፡ ጨረቃ ፡ ደርሰው ፡ ሕይወት ፡ መኖሩ ፡ አለመኖሩ ፡ መርምረው ፡ እንደ ፡ የምንኖራት ፡ መሬት ፡ እንዲጠቀሙላት ፡ ብዙ ፡ ጣር ፡ ችግር ፡ ያሳልፋሉ - - - በፈረንጅ ፡ አፍ ፡ መናገር ፡ ክብር ፡ አለው ፤ ግን ፡ ጨረቃ ፡ ላይ ፡ መውጣት ፡ አይሆኑም - - - ዳኞች ፡ ካቀረቡላቸው ፡ ሆዳቸው ፡ ሳይሞሉ ፡ አይተውም ፤ ዐውቃሎህ ። ሆኖም ፡ ለመዮቴ ፡ ስል ፡ በፈረንጅ ፡ አፍ ፡ እንድናገር ፡ ኅሊናዬ ፡ ይገድደኛል - - -

«ጥሩ ፡ ነው ፡ ጥሩ ፡ ነው ፡ በፈረንጅ ፡ አፍ ፡ ታናግራቸዋለህ - - -

« እመዮቴ ፡ ክፉ ፡ ያድርግ ፡ አለ ፡ እንዳይሉኝ - - -

« ምን ፡ ቆርጦኝ - - - - ክፉ ፡ አሳቢን ፡ ክፋቱ ፡ ይጣለው - - ብቻ ፡ ያፍክን ፡ ብዛት ፡ ጠላሁቲ—ክፉ ፡ ያደርጋልስ ፡ አልልም - - ባይሆን ፡ እፊት ፡ እፊቴ ፡ ሲሆን ፡ ባበሻ ፡ አፍ ፡ ብትናገር ፡ ደስ ፡ ይለኛል - - -

« እኔ ፡ ትግሪኛ ፡ ትግረ ፡ እችላሎህ ፤ እርሶ ፡ አይችሉም - - አማርኛ ፡ ለኔ ፡ ያስቸግራል - - - የርሶ ፡ እናት ፡ ትግሬ ፡ ናቸው - - እርሶ ፡ ለምን ፡ ትግሪኛ ፡ አይችሉም ?

« የጠራች ፡ መንዜ ፡ ናት ፡ የኔ ፡ እናት - -

« ወንድሞ ፡ እናቴ ፡ ትግሬ ፡ ናት ፡ ብሎኛል !

« የሱ ፡ እናት ፡ ርግጥ ፡ ትግሬ ፡ ነበሩ - - በናቱ ፡ ወጥቶ ፡ ነው ፡ ባሕር ፡ ማዶ ፡ ለባሕር ፡ ማዶ ፡ ሲንከራተት ፡ የኖረው - - ባባታችን ፡ ነው ፡ ከወልዱ ፡ ጋር ፡ የምንገናኘው - - -

« - - - እኔ ፡ አላወኩም ፡ ነበርኩ - - !

« እና ፡ ታዲያ ፡ እንዳልኩህ ፡ ማስተናገዱን ፡ ባንተ ፡ ትቸዋለሁ - - የከተማ ፡ ሰው ፡ ዐመሉ ፡ አይታወቅምና ፡ በዘዴ ፡ በዘዴ ፡ አድርገህ ፡ እንድታስተናግድልኝ - - - አዎ ፡ ይኸው ፡ ነው - - - ጺወኔንና ፡ ሮማንን ፡ ጥራልኝ - - - እንግዲህ ፡ መምጫቸው ፡ ደርሷል ፤ አፋፍ ፡ ወጥተህ ፡ ብትጠብቃቸው - - -

« ለመውጣት ፡ ቢዬ ፡ አስቤ ፡ ነው ፡ ለመሄድ ፡ ያሎህ - - -

« አዎን ፡ ጥሩ ፡ አስበሃል - - - » ወደ ፡ ምድጃው ፡ ጠጋ ፡ ብለው ፡ ማማሳያቸውን ፡ ደኅና ፡ አድርገው ፡ ካጠቡ ፡ በኋላ ፡ አልሚውንና ፡ ቀይ ፡ ወጡን ፡ እያጠቀሱ ፡ ወዳፋቸው ፡ በመውሰድ ፡ ሲቀማምሱ ፡ እነ ፡ ጺወኔ ፡ ይገባሉ ። እንደገቡም « - - ሮማኔ ፡ እንግዲህ ፡ እንደነገርኩሽ ፡ የክት ልብስሽን ፡ ለብሰሽ ፡ በሚገባ ፡ ታደገድጊና ፡ እበርጩማዬ ፡ ኋላ ፡ ትቆሚያለሽ - - - ያንን ፡ ያይንሽን ፡ መቃኀትና ፡ አሥረዬ ፡ ምራቅሽን ፡ መዋጥሽን ፡ ኋላ ፡ አደራ - - ጺወኔ ፡ መቼም ፡ ነግሬሻለሁ - - ባይነት ፡ ባይነቱ— እንጀራ ፡ ሲያልቅ ፡ እንጀራ - - ፍትፍት ፡ ሲያልቅ ፡ ፍትፍት - - እሬት ፡ እሬታችን - - እሬት ፡ እሬታችን - - ማቅረብ ፡ ያንቺ ፡ ፈንታ ፡ ነው ።— እቃ ፡ ማጋጨትና ፡ እግር ፡ ማማታት — እሰው ፡ ላይ ፡ ማንጠባጠብ — በሰው ፡ ትከሻ ፡ ላይ ፡ ማምጣት — ቢያናግሩሽም ፡ አፍሽን ፡ ሳትሸፍኚ ፡ መናገር - - አደራሽን ፡ እንዳላይ — ጥንቅቅና ፡ ኩስትር ፡ እንድትይልኝ - - ምናልባት ፡ ያጕረሱሽ ፡ እንደሆነ ፡ አፍሽን ፡ በትንሹ ፡ ከፍተሽ — የሚበልጠውን ፡ በጅሽ ፡ ደገፍ ፡ አድርገሽ ፡ መቀበል ፡ አለብሽ — አዎ ! እንደ ፡ ሥራ ፡ ቤቶች ፡ ባፍሽ ፡ ሙሉ ፡ እንዳትቀበይ - - » እያሉ ፡ የመጨረሻ ፡ ምክራቸውን ፡ ያቀርባሉ ።—

ከቤት ፡ በታች ፡ ወደ ፡ ወይዘሮ ፡ አሰጋሽ ፡ ቤት ፡ ወደሚያወጣውና ፡ ወደ ፡ ማፉድ ፡ እሚያወርደው ፡ መንታ ፡ ጐዳና ፡ መገናኛ ፡ ጥቂት ፡ ሰዎች ፡ ያመራሉ ። በቃሬዛ ፡ በሽተኛ ፡ ተሸክመው ፤ አንድ ፡ ጥቁር ፡ በግ ፡ እየጐተቱ ። ጊዜው ፡ አንድስቅጤና ፡ ተልከስካሽ ፡ መንገዱን ፡ ይዞታል ፡ ተብሎ ፡ የሚታመንበት ፡ ከባድ ፡ ተሲያት ፡ ላይ ፡ ነው ። እነ ፡ አቶ ፡ ጥሶ ፡ ባሻገሩ ፡ እሚገኘው ፡ ጉባ፡ ላይ ፡ ብቅ ፡ ይሉና ፡ ወደ ፡ መንታው ፡ መንገድ ፡ ያሽቆለቁላሉ ። ባለ ፡ ቃሬዛዎቹ ፡ ጥቁሩን ፡ በግ ፡ በታመመው ፡ ሰውዬ ፡ ዙሪያ ፡ ሦስት ፡ ጊዜ ፡ ያዞሩና ፡ በአብ ፡ በወልድ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ስም ፡ ያርዱታል — መንታው ፡ መንገድ ፡ መገናኛ ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ደረሱ ። በደሙም ፡ የመስቀል ፡ ምልክት ፡ እበሽተኛው ፡ ግምባር ፡ ላይ ፡ ያደርጉና ፡ በጥድፊያ ፡ ቦታውን ፡ ለቀው ፡ ወደ ፡ መጡበት ፡ ይመለሳሉ ።

በጉ ፡ ይንፈራፈራል ፤ አቶ ፡ ጥሶ ፡ እቦታው ፡ ይደርሳሉ ።-‘ዕድላችን ፡ ነው !’ ይሉና ፡ ከኪሳቸው ፡ ሴንጢ ፡ አውጥተው ፡ የበጉን ፡ ጆሮ ፡ ይቀነጥቡታል — በአብ ፡ በወልድ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ስም — አሽከራቸውንም ፡ ዕድላቸውን ፡ እሚሄዱበት ፡ ቤት ፡ ድረስ ፡ እንዲያመጣ ፡ አዝዘው ፡ መንገዳቸውን ፡ ያቃናሉ ። ባላቦረንትቾች ፡ ወደ፡ጭዳው ፡ መለስ ፡

አላሉም ፤ ቦታውን ፡ እንደለቀቁ ፡ ሚጣኑ ፡ መጋበዙን ፡ ይጀምራል ።—በሚጋ በዝበት ፡ ጊዜ ፡ ደግሞ ፡ ጋባዦቹ ፡ መለስ ፡ ብለው ፡ ካዩት ፡ ሕመምተኛ ውን ፡ የለቀቀው ፡ በሽታ ፡ መልሶ ፡ እንደሚይዘው ፡ ያውቃሉ ።

አቶ ፡ ጥሶ ፡ ወደ ፡ ወይዘሮ ፡ አስጋሽ ፡ ቤት ፡ የሚያወጣውን ፡ አቀ በት ፡ ሲያያዙት ፡ ጴጥሮስ ፡ ይደርስና ፡ እንዳገሩ ፡ ደንብ ፡ አደግድጎና ፡ እጅ ፡ ነሥቶ ፡ ይቀበላቸዋል ።

# ፲፫

## አደፍርስ

የአቶ ፡ ጥሶ ፡ አሽከር ፡ እንደታዘዘው ፡ በኋን ፡ ይገፍና ፡ በቅጥ ፡ በቅጡ ፡ ካደረገ ፡ በኋላ ፡ ሥጋውን ፡ በቆዳው ፡ ጠቅልሎ ፡ መንገድ ፡ ይገባል ። የወይዘሮ ፡ አሰጋሽ ፡ አሽከር ፡ የሆነ ፡ መንታው ፡ መንገድ ፡ አቅራቢያ ፡ ጥጃች ፡ ያግጥ ፡ ስለነበረ ፡ በቀዩው ፡ አይቶት ፡ የማያውቀው ፡ ሰው ፡ ያደርገው ፡ የነበረውን ፡ ሁሉ ፡ ተደብቆ ፡ ተመልክቶ ፡ ነበርና ፡ መጨረሻውን ፡ ለማየት ፡ ብሎ ፡ ቀስ ፡ እያለ ፡ ኋላ ፡ ኋላው ፡ ይከተለዋል ። ወደ ፡ እመቤቱም ፡ ግቢ ፡ ማምራቱን ፡ ሲያይ ፡ ያቆራርጥና ፡ ቀድሞ ፡ ደርሶ ፡ አቶ ፡ ጴጥሮስን ፡ ከተፋፋመ ፡ ግብግብ ፡ ከደራ ፡ ጨዋታ ፡ ላይ ፡ አስጠርቶ ፡ የጥቁር ፡ እንግዳውን ፡ መምጣት ፡ ይነግረዋል ።—

«- -ኢትዮጵያ ፡ ምን ፡ ጊዜም ፡ ቢሆን ፡ ጠባቂ ፡ አላጣችም - - ጥንት ፡ በሕገ ፡ ልቡና ፡ ቀጥሎ ፡ በሕገ ፡ ኦሪት ፡ ኋላም ፡ በሕገ ፡ ወንጌል ፡ ባዲሱ ፡ ዘመንም ፡ በሕገ ፡ መንግሥት ፡ የተጠበቀች ፡ ነች - - - » ይላሉ ፡ አባ ፡ አዲሴ ፡ የወይዘሮ ፡ አሰጋሽ ፡ ነፍስ ፡ አባት - - ከአደፍርስ ፡ ጋር ፡ ክርክር ፡ ገጥመው ፡ አይተውት ፡ አይቀጥሉት ፡ ነገር ፡ ሆኖባቸዋል ። እንደመንቀፍም ፡ እንደማጕዘልም ፡ እንደማኪያኪያስም ፡ ይሻቸዋል ፡ ያደፍርስን ፡ ንግግር ።—አደፍርስ ፡ በበኩሉ ፡ በሞቀና ፡ ስሜት ፡ በተሞላበት ፡ አንደበት ፡ ይናገራል - - ሐሳቡ ፡ ሁሉ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ያሰበበትና ፡ አውጥቶ ፡ ያወረደው ፡ ያሰላሰለው ፡ ይመስላል - - የስሜቱ ፡ ክፍል ፡ እየተቦጨቀ ፡ እንደሚወጣ ፡ ዓይነት - - -

« ሞትና ፡ ሕይወት ፡ ድንቁርናና ፡ ዕውቀት ! እኔ ፡ የምለውኮ ፡ ጠባቂ ፡ አጥታ ፡ ነበር ፡ አይደለም ።—በዚህ ፡ በሀያኛው ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ ላደረግነው ፡ ግሥጋሤ ፡ ቅድምና ፡ የለውም ፤ የድህውም ፡ የሀብታሙም ፡ ልጆች ፡ በኩልነት ፡ ደረጃ ፡ ዕውቀትን ፡ ሹመትን ፡ መታወቅን ፡ ያገኙበት ፡ ዘመን ፡ በኢትዮጵያ ፡ ታሪክ ፡ ውስጥ ፡ አልነበረም — የመጀመሪያ ፡ ጊዜው ፡ ነው ፡ ነው ፡ የምልዎት - - ኢትዮጵያ ፡ እጆቿን ፡ ሰብስባም ፡ ሆነ ፡ ዘርግታ ፡ ያልተቀመጠችበት — በርግጥ ፡ በሚታይ ፡ በሚጨበጥ ፡ በሚገባ ፡ መንገድ ፡ መሥራት ፡ የጀመረችበት ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡

ነው ፡ የምልዎት - - ኢትዮጵያ ፡ እንደ ፡ ግመል ፡ ሽንት ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ መሄድ ፡ ቀርቷል — ወደፊት ፡ በመገሥገሥ ፡ ላይ ፡ ነች ፡ ነው ፡ የምልዎት - - እን ዴት ፡ ብዬ ፡ ልንገርዎት ፡ ይሆን ? » ይመልሳል ፡ አደፍርስ ።

ጺወኔ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ አሳላፊነቷን ፡ እየዘነጋች ፡ አፍ ፡ አፉን ፡ ትመ ለከተዋለች ። አንዳንዱ ፡ ይገባታል ፤ አብዛኛው ፡ አይገባትም ።- ገባትም ፡ አልገባትም ፡ ግን ፡ ከሰውነቱ ፡ የሚፈልቀው ፡ በቃላት ፡ ሊገለጽ ፡ የሚ ተናነቀው ፡ የአደፍርስ ፡ ስሜቱ ፡ እየገነፈለ ፡ ወጥቶ ፡ እንደ ፡ ዳመና ፡ ግላጭ ፡ ድርቅርቅታ ፡ ደሟን ፡ ሲንደው ፡ ይሰማታል ። በአደፍርስ ፡ በኩል ፡ ቢሆን ፡ ግን ፡ መኖርና ፡ አለመኖሯንም ፡ ያጤነው ፡ አይመስል ፤ ተስቶት ፡ እንኳ ፡ ወደ ፡ እሷ ፡ እየተመለከተ ፡ አላወራም — እንጀራ ፡ እንኳን ፡ እየቆ ረሰች ፡ እፊት ፡ እፊቱ ፡ ስታደርግላት ።— ያለወትሮዋ ፡ ነደድ ፡ ነደድ ፡ ሊያደርጋት ፡ ጀምሯል ፡ ጺወኔንም ‘ ከከመ ፡ ጤፍም ፡ አልቆጠረኝ - - - ገረድ ፡ መስዬው ፡ ይሆናል - - ቢሆንስ ፡ እንዴት ፡ አንዴ ፡ እንኳ ፡ ተሳ ስቶት ፡ አያየኝም - - - ’ የሚሉ ፡ የሐሳብ ፡ ነጸብራቆች ፡ ይፈልቁ ፡ ይጠ ልቁባታል ።

«‘ ኢትዮጵያ ፡ ታበጽሕ ፡ እደዊሃ ፡ ኀበ ፡ እግዚአብሔር’ የሚለውን ፡ ቅዱስ ፡ ቃል ፡ ለማጉዘል ፡ ነው ፡ መሰለኝ ፡ አነጋገርህ - - ያልያዝኩልህ ፡ አይምሰልህ - - እንኳን ፡ ይችንና ፡ የዝንብ ፡ ጠንጋራም ፡ እናውቃለን - - እ . ሄ . ሄ . ሄ — የትና ፡ የት ! ሰማሆይ ‘ ኢኮነ ፡ ሠናየ ፡ ነሢአ ፡ ኅብስተ ፡ ውሉድ ፡ ወወሂብ ፡ ለከለባት - - ’ የልጆቹን ፡ ኅብስት ፡ ለውሾቹ - - - ኢትዮጵያ ፡ ታዲያ ፡ ምን ፡ ተጠቀመች - - የማንንም ፡ እከሌን ፡ የማይ ባል ፡ ልጅ ፡ ሰብስበው ፡ አይደለም ፡ እንዴ ፡ ንጉሡ ፡ መከራቸውን ፡ የሚያውት - - - ?

« ሞትና ፡ ሕይወት - - ! ይስሙኝ ፡ አባ — የእልህ ፡ ሳይሆን ፡ እየ ተደማመጥን ፡ እናውጋ - - እግዚአብሔር ፡ ማንኛውንም ፡ ሰው ፡ በአ ምሳሉ ፡ ነው ፡ የፈጠረው ።— ጥበብን ፡ ለማግኘት ፡ የእከሌ ፡ ልጅ ፡ ተብሎ ፡ መታወቅ ፡ የሚያስፈልገው ፡ ነገር ፡ አይደለም ፤ ጤነኛ ፡ ሰውነትና ፡ የሚያስብ ፡ ጭንቅላት ፡ ነው ፡ የሚያስመርጠው ።— ምነው ! ‘ ከእናንተ ፡ ማህል ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ለማለት ፡ የሚሻ ፡ ቢኖር ፡ ራሱን ፡ ዝቅ ፡ ዝቅ ፡ ያድ ርግ ’ - - ‘ እግዚአብሔር ፡ ከእነዚህ ፡ ድንጋዮች ፡ ማህል ፡ መሪና ፡ አስ ተማሪ ፡ ለመፍጠር ፡ ይችላል ’ ተብሎ ፡ የተጻፈውን ፡ ቅዱሳዊ ፡ አነጋገር ፡ ወዴት ፡ ያንጓልሉታል - - የለም ፡ አባ — የነገርን ፡ አንድ ፡ ፊቱን ፡ ብቻ ፡

አይመልከቱ ። ቢያስጠላዎትም ፡ እንኳን ፡ ሌላውንም ፡ በኩል ፡ መመ ልከቱ ፡ አይከፋም - - -

« - - - ምነው ፡ ታዲያ ፡ ቢሆንስ — ከሰውምኮ ፡ ሰው ፡ አለው ፤ ‘ ከእንጨት ፡ መርጦ ፡ ለታቦት ፡ ከሰው ፡ መርጦ ፡ ለሹመት ’ ሲባል ፡ አል ሰማህም ፡ የኔ ፡ ልጅ - - አሁን ፡ ለምሳሌ — አሽከሮቼን ፡ ገና ፡ ለገና ፡ በዝጌር ፡ አምሳል ፡ ተፈጥረዋል ፡ ብዬ ፡ ከኔ ፡ ጋር ፡ እኩል ፡ ናቸው ፡ ልል ፡ ነው ? የለም ፡ የኔ ፡ ልጅ ፡ ዙሪያንም ፡ አካባቢን ፡ እያዩ ፡ ነው ፡ ጨዋታ - - - » ወይዘሮ ፡ አሰጋሽ ፡ ጣልቃ ፡ ይገባሉ ።

« እረ ፡ ከወዴት ! ሁሉ ፡ ሰውማ ፡ እኩል ፡ ከሆነ ፡ የሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ራሱ ፡ መቼ — ‘ ሀቡ ፡ ዘነጋሚ ፡ ለነጋሚ ’ ይል ፡ ነበር ? » ይቀጥላሉ ፡ አባ ።

« ሞትና ፡ ሕይወት ! የሱስማኮ ፡ የቁማሩ ፡ ምስል ፡ ያለበትን ፡ ለቁማሩ ፡ ብሎ ፡ የተናገረው ፡ ሕዝቡ ፡ ለመንግሥቱ ፡ ይከፍለው ፡ የነበ ረውን ፡ ግብር ፡ እንዳያገባ ፡ ይሰብካል ፡ ብለው ፡ እንዳይወነጅሉት ፡ ነበር ፡ እንጂ— ቁማር ፡ ያልሆነ ፡ ሰው ፡ በገንዘቡ ፡ እንዳይጠቀምበት ፡ ለማለት ፡ አልነበረም » ይመልሳል ፡ አደፍርስ ።

« ትውልድ ፡ ዕሉት ፡ ወዘማ ! የዛሬ ፡ ዘመን ፡ ልጆች ፡ ምናችሁም ፡ አያምረኝ - - ‘ ነስሐ ፡ በእንተ ፡ ዘገብሮ ፡ ለሰብእ ’ ተብሎ ፡ የተነገረው ፡ አምላካዊ ፡ ቃል ፡ በእንደ ፡ እናንተ ፡ ያለው ፡ ላይ ፡ ነው - - -

« ታዲያ ፡ እኛ ፡ የዱሮዎቹ ፡ ከዛሬዎቹ ፡ እንበልጣለን ፡ ማለትዎ ፡ ነው ፡ እንዴ ፡ አባ ? » ይጠይቃሉ ፡ አቶ ፡ ወልዱ ። — አቶ ፡ ጥሶና ፡ አቶ ፡ ክብ ረት ፡ ዝም ፡ ብለው ፡ ያዳምጣሉ ።—ለሁለቱም ፡ ተከራካሪዎች ፡ የሚጠ ቅም ፡ ማቃኛ ፡ አስተያየት ፡ ሊኖራቸው ፡ ሲችል ፡ ለጊዜው ፡ ምንም ፡ ዓይነት ፡ ሐሳብ ፡ ሊያቀርቡ ፡ የፈለጉ ፡ አይመስሉም ።— ሁለቱም ፡ ተከ ራካሪዎች ፡ ሊሰሙና ፡ ሊያሰሙ ፡ እንጂ ፡ ሊማሩና ፡ ሊያስተምሩ ፡ የፈ ለጉ ፡ ዓይነት ፡ በቅን ፡ መንፈስ ፡ የተነሣው ፡ ለመሆናቸው ፡ የሚገልጽ ፡ የሐሳብ ፡ መለዋወጥ ፡ ይዘው ፡ የቀረቡ ፡ መስሎ ፡ አልታየም ።

« ባንበልጥም ፡ አናንስም - - - » ይመልሳሉ ፡ አባ ።

« እርግጠኛ ፡ ነኝ ፡ ከዱሮዎችም ፡ ሰዎች ፡ ዐዋቂና ፡ ደንቆሮዎች ፡ ከዛ ሬዎቹም ፡ እንዲሁ ፡ አይጠፉባቸውም - - » ይቀጥላሉ ፡ አቶ ፡ ወልዱ ።

« እሱማ ‘ እምፍሬሆሙ ፡ ታአምርዎሙ ’ — በፍሪያቸው ፡ ታውቋቸዋላችሁ ፡ ተብሎ ፡ የለም—እርግጥ ፡ ነው ፡ ከሁሉም ፡ ብስልና ፡ ጥሬ ፡ አይጠፋም - - -

« ታዲያ — ‘ እብን ፡ ዘመነንዋ ፡ ነደቅት ፡ ወይእቲ ፡ ኮነት ፡ ውስተ ፡ ርእሰ ፡ ማእዘንት ’ ንም ፡ ይጥቀሱ ፡ እንጂ ፡ ለምን ፡ የዘመኑን ፡ ልጆች ፡ ዘማዊነት ፡ ብቻ ፡ ያጐሉታል - - ?

« ጊዜው ፡ ነውኮ ! ጊዜው ፡ ስምንተኛው ፡ ሺህ ፡ ባይሆን ፡ ኖሮ ‘ ይከውኑክሙ ፡ ለዕቅፍት ’ ተብሎ ፡ ይነገርባቸው ፡ ነበር ? የለም ፡ ግዴለዎም ፡ ጊዜው ፡ ነው - - -

« አሄ - - - በጊዜውም ፡ ማመካኘት ፡ አይበጅም - - የተነገረውንም ፡ ቅዱስ ፡ ቃል — ቃል ፡ በቃል ፡ መውሰድ ፡ ቤተክሲያንን ፡ ከልጆቿ ፡ ይነጥላታል ፡ እንጂ ፡ አያቀራርባትም - - ሰሙኖይ - - ? ! ለመሆኑ ፡ ‘ ይቀልል ፡ ይኀልፍ ፡ ገመል ፡ እንተ ፡ ስቍረተ ፡ መርፍእ ፡ እምባዕል ፡ በዊአ ፡ መንግሥተ ፡ እግዚአብሔር ’ ን ፡ ቀጥታ ፡ ከተረጐምነው ፡ የትኛው ፡ የነጋዊ ፡ የትኛው ፡ የመስፍንና ፡ የትልቅ ፡ ሰው ፡ ልጅ ፡ ነው ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ የሚገባው ? ሀብታም ፡ የሆነን ፡ ሁሉ ፡ ለሲዖል ፡ ዳረግነው ፡ ማለት ፡ አይደለም ? » ይቀጥላሉ ፡ አቶ ፡ ወልዱ ።

« አዎ ፡ በዚህ ፡ ጥቅስ ፡ መሠረት ፡ እከሌን ፡ የማይባሉ ፡ ልጆች ፡ ብለው ፡ የጠቀሷቸው ፡ ናቸው ፡ ማለት ፡ ነው ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያትን ፡ የሚወርሷት - - - » ጣልቃ ፡ ይገባል ፡ አደፍርስ ፡ አባ ፡ አባን ፡ እየተመለከተ ።-

ካጥር ፡ ውጪ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ጭቅጭቅ ፡ ተፈጥሯል ። ያቶ ፡ ጥሶን ፡ አሽከር ፡ እስኪተሸከመው ፡ የበግ ፡ ሥጋ ፡ ይዘውታል ። በእመቤታቸው ፡ ላይ ፡ ጭዳ ፡ ሊጥልባቸው ፡ የመጣ ፡ መስሏቸው ፡ በጡጫና ፡ በጥፊም ፡ አቅምሰውታል ። በኋላ ፡ ነው ፡ እነ ፡ ሮማን ፡ ፍሬዋን ፡ ከሚያስተናግዱበት ፡ ከወርዶፋ ፡ ጐጆ ፡ ወጥተው ፡ መጥተው ፡ ጉዳዩ ፡ የተገለጸው ።— ፍሬዋ ፡ ሁኔታውን ፡ በሙሉ ፡ ታስረዳቸዋለች ።

«- - - ቢሆንም ፡ የቦረንትቻ ፡ ሥጋ ፡ እመቤቴ ፡ ግቢ ፡ አይገባም ፤ እኑሱን ፡ የለቀቃቸወ ፡ በሽታ ፡ እኛንም ፡ ከብቶቹንም ፡ ነው ፡ የሚጨርሰን » ይላል ፡ ወርዶፋ ፡ አለቅጥ ፡ በተጨነቀ ፡ አነጋገር ።

« እንዲያ ፡ ከሆነ ፡ እንግዲያው ፡ እኔ ፡ እዚህ ፡ የምቆይበት ፡ ምክንያት ፡ የለም ፤ ደብረ ፡ ሲናዬ ፡ እመለሳለሁ - - - እንዲያውስ ፡ ምን ፡ የምቆይበት ፡

ምክንያት ፡ አለ - - » ቁርጥ ፡ ባለ ፡ ቃል ፡ ተናግራ ፡ መለስ ፡ ልትል ፡ ስትል — ወይዘሮ ፡ አሰጋሽን ፡ ሮማን ፡ ትጠራቸውና

« ምንድነው ፡ ነገሩ ? የምን ፡ የቦረንትቻ ፡ ሥጋ ፡ ነው ፡ ደሞ ፡ እኔ ፡ ግቢ ፡ የሚገባው ? በክርስቲያን ፡ ደንብ ፡ የተባረከው ፡ መቼ ፡ ጠፋና - - ቢያስፈልግ ፡ ሌላ ፡ ሙክት ፡ እናርዳለን - - - » እያሉ ፡ ፈገግ ፡ ኮስተር ፡ በማለት ፡ እየተናገሩ ፡ ይመጣሉ ።

« እኔ ፡ የእርስዎን ፡ ሙክት ፡ አልፈልግም - - - ፈቃድዎ ፡ ቢሆን ፡ ለብቻዬ ፡ ቤት ፡ ይፍቀዱልኝና ፡ የቦረንትቻውን ፡ ሥጋ ፡ በመብላት ፡ በሽታ ፡ ሲይዘኝ ፡ እስኪ ፡ ሊያዉ ፡ ይችላሉ ! » በማለት ፡ ትቋቋማቸዋለች ፡ ፍሬዋም ።

« ብኖር ፡ አይደለም ፡ ለማየት ፡ የምችለው ? — የለም ፡ የኔ ፡ ልጅ - - ሁሉ ፡ ነገር ፡ ሞልቶ ፡ ተርፎ ፡ የሰው ፡ ጂኒ ፡ እግቢዬ ፡ አስገብቼ ፡ መከራዬን ፡ አላይም - -

«እንግዲያው ፡ ይፍቀዱልኝና ፡ ወደ ፡ ደብረ ፡ሲናዬ ፡ ልመለስ - - ምን ፡ ያደርጋል ፡ አጉል ፡ ሐሳብ ፡ ከምሆንብዎ ፡ ይሻላል - - -

« እኔ ፡ ምን ፡ አግብቶኝ ፡ ወዳጄ ? ደሞ ፡ የመፍቀዱ ፡ ጋጋታ ! ምን ፡ ቢያገደኝ ! አባትሽን ፡ ጠይቂና ፡ እንዳፈተተሽ ፡ ልትሆኚ ፡ ትችያለሽ - - -

አባ ፡ አዲሴ ፡ አቶ ፡ ጥሶ ፡ አቶ ፡ ወልዱና ፡ በላይ ፡ የጭቅጭቁን ፡ መካረር ፡ ይሰሙና ፡ ይወጣሉ ።—

«- - - ልጅዎን ፡ አንድ ፡ ይበሉን - - - የቦረንትቻ ፡ ሥጋ ፡ እዚህ ፡ ግቢ ፡ ካላስገባሁ ፡ ብላ ፡ ደብረ ፡ ሲና ፡ እወጣለሁ ፡ እያለች ፡ ታስፈራራናለች » ይላሉ ፡ ወይዘሮ ፡ አሰጋሽ ፡ ውዴታና ፡ ልመና ፡ በተመላበት ፡ ዓይናቸው ፡ የፍሬዋን ፡ ዓይን ፡ ዓይኗን ፡ እየተመለከቱ ።

« ምናለ ፡ ታዲያ ፡ ትውጣ ! ለመቆየት ፡ ብትፈልግ ፡ ያገሬውን ፡ የቀየውን ፡ ደንብ ፡ ተከትላ ፡ ትቆይ ! አለበለዚያ ፡ ደግሞ ፡ እምቢ ፡ ካለች ፡ መሄዱ ፡ የራሷ ፡ ፈንታ ፡ ነው - - » ይመልሳሉ ፡ አቶ ፡ ጥሶ ፡ ዝግ ፡ ባለ ፡ አንደበት ።

« እንዴት ፡ ብለው ፡ አንድ ፡ ልጅዎን ፡ መረን ፡ ይለቃሉ ? በዚህ ፡ ባጉል ፡ ነገር ፡ የተለከፈች ፡ እንደሁ ፡ ጠጡቱ ፡ የማነው ? » ይጠይቃሉ ፡ ወይዘሮ ፡ አሰጋሽ - እናታዊ ፡ በሆነ ፡ የፊት ፡ አየርና ፡ አነጋገር ።-

« ‘ እምፍሬሆሙ ፡ ታእምርዎሙ ’ የዛሬ ፡ ዘመን ፡ ልጆች ፡ የናት ፡ ያባታቸውን ፡ ትእዛዝ ፡ አይፈጥሙ—ራሳቸው ፡ የሚያደርጉትን ፡ አያውቁ— ነገራቸው ፡ ደረቅ ፡ ዕድሜያቸው ፡ አጭር - - - » አባን ፡ ሁኔታው ፡ ያናደዳቸው ፡ ይመስላል ።

« ፍሬዋ ፡ የምትሄድ ፡ ከሆነች ፡ እንግዲያው ፡ እኔም ፡ አብሬያት ፡ እሄዳለሁ ። እኔም ፡ እንደ ፡ እሷ ፡ የቦረንትቻው ፡ በግ ፡ ሥጋ ፡ እዚህ ፡ ቤት ፡ የማይገባበት ፡ ምክንያት ፡ አይታየኝም - - - » ሳይታሰብ ፡ ድንገት ፡ ቀደም ፡ ይልና ፡ በላይ ፡ የፍሬዋን ፡ ሐሳብ ፡ ይደግፋል ።

« አንተ ፡ ደሞ ፡ ምን ፡ ትባል ፡ ይሆን ፡ አሳራችን - - ያየሁት ፡ አይ ቅረኝ ፡ ነው ? አንተንስ ፡ ማሸነፍ ፡ አያቅተኝም - - አባትህን ፡ ወል ዱን ፡ እንኳን ፡ እሥሬ ፡ አግብቼዋለሁ - - እንኳን ፡ አንተን - - -

« እንግዲያው ፡ ፍሬዋ ፡ ከሄደች ፡ እኔም ፡ በመሄዴ ፡ ቆርጫለሁ ፡ ይወቁት - -

« ወልዱ ፡ ምን ፡ ዝም ፡ ብለህ ፡ ታየኛለህ ፡ እኔን ! ይኸን ፡ ሁሉ ፡ ገብ ፡ ልጅህን ፡ አንድ ፡ አትለኝም - - ?

« አይ ፡ መቼስ ፡ እንግዲህ ፡ ካንቺ ፡ ሙክት ፡ የቦረንትቻ ፡ በግ ፡ ከበ ለጠበት ፡ ምን ፡ ማድረግ ፡ ይቻላል ? እንደምታውቂወ ፡ የዛሬ ፡ ልጆች ፡ የራሳቸው ፡ አስተሳሰብ ፡ አላቸው ፤ እኛ ፡ ባልናቸው ፡ አይሄዱም - - እና ፡ ምን ፡ ላርግ ፡ ትይኛለሽ - - ?

በላይ ፡ በላይን ፡ እያዩ « - - ሁለተኛ ፡ ብቻ ፡ አክስቴ ፡ ብለህ ፡ ቁልቁል ፡ ሰበር ፡ ሰካ ፡ እንዳትሊ ፡ ዛሬስ ፡ መቼም ፡ ሠለጠንሁ ፡ ብለህ ፡ አምልጠሃል — ባንተ ፡ ቤት - - ! አንቺ ፡ የኔ ፡ ልጅ - - ፍሬዋ ፡ ብት ሆኝ - - ልቤ ፡ ወዶሻል ፤ ዓይንሽን ፡ እንኳ ፡ ሙሉ ፡ ለሙሉ ፡ አይቼ ፡ ሳል ጠግበው ፡ አንድ ፡ ሁለት ፡ ሳንነጋገር ፡ ልሂድ ፡ በማለትሽ ፡ ባዝንብሽ ፡ አይክፋሽ ፡— እውነቱን ፡ ነው ፡ እምልሽ ፤ እንዲህ ፡ ባንደዜ ፡ ሰውን ፡ አይቼ ፡ እንኳን ፡ ወድጄ ፡ አላውቅም - - ጥሎሽ ፡ ሆነሽብኛል ።— ብቻ ፡ ምን ፡ ያደርጋል ፡ ቦረንትቻውን ፡ እንድታስገቢ ፡ ልፈቅድልሽ ፡ አልችልም - - እኔ ፡ እንኳን ፡ ልቤ ፡ ቢፈቅድ ፡ ይኸ ፡ የምታይው ፡ አሽከሬ ፡ ሁሉ ፡ ነው ፡ ጥሎኝ ፡ እብስ ፡ የሚለው - - በስንት ፡ ዓይነት ፡ ቋንቋ ፡ የሚናገረው ፡ ጴጥሮስ ፡ እንኳ ፡ ቢሆን - - ለነፍሱ ፡ የማይፈራ ፡ ሰው ፡ የለም ፡ እንደምታውቂው - - » ፍሬዋ ፡ ወይዘሮ ፡ አሰጋሽ ፡ ሳያስ ቡት ፡ ድንገት ፡ ወዳጠገባቸው ፡ ሮጥ ፡ ሮጥ ፡ በማለት ፡ በሁለት ፡ እጆቿ ፡

አንገታቸውን ፡ አቅፋ ፡ አፋቸው ፡ ገደማ ፡ ሳም ፡ ታደርጋቸውና ፡ በቀረበ ችበት ፡ ዓይነት ፡ መለስ ፡ ብላ ፡ ወደ ፡ ነበረችበት ፡ ታመራለች ።

«እንዲህ ፡ ያለች ፡ ልጅ ? ! ቍንጥርጥር ፡ ያለች - - - ከኔ ፡ ጋር ፡ ውላ ፡ ብታድር ፡ ልቤን ፡ በሙሉ ፡ በወሰደችው - - ጣጣ ፡ ነው ፡ እባካ ችሁ - - ውዴታ ፡ የሚሉት ፡ ነገር ፡ የማይቆጣጠሩት - - -

«'ቅንዑ ፡ ለእንተ ፡ ተዐቢ ፡ ጸጋ' ብሎ ፡ የለም ፡ ሐዋርያው ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ።—ሃይማኖትን ፡ ታሪክን ፡ ልማድን ፡ ወግን ፡ በጠቅላላው ፡ ባህ ልን ፡ የመሰለ ፡ ክብረ ፡ ስብእና ፡ ሲነካ ፡ የሚወደውን ፡ ነገር ፡ የማይሠዋ ፡ የለም 'ኢመሀኮ ፡ ለወልድከ ፡ እምኔየ' አንድ ፡ ልጅህን ፡ እንኳን ፡ ከኔ ፡ አልደበቅኸውም —ለመሥዋዕት ፡ አቅርበኸዋል ፡ ተብሎ ፡ ለአብርሃም ፡ የተነገረው ፡ ዛሬም ፡ ለእናንተ ፡ ቢነገር ፡ አይገርምም - - እግዚአብ ሔር ፡ በመለኮትነቱ ፡ ንጉሥ ፡ በመንግሥቱ ፡ ጕልማሳ ፡ በሚስቱ ፡ ቢደ ርሱበት ፡ እንዳይወድ—በለምለም ፡ መሬቱ ፡ በነፃነት ፡ ሀብቱ ፡ በጸናው ፡ መንግሥቱ ፡ በተደላደለው ፡ ንብረቱ ፡ በሚያምንበት ፡ ወግና ፡ ልማዱ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ቢደርሱበት ፡ አይወድም - - እና ፡ እግዚአብ ሔር ፡ አስመልክቶሽ ፡ ያደረግሽው ፡ ሁሉ ፡ በሚገባ ፡ ነው - - እነሱንም ፡ እመንገድ ፡ የሚገቡትን ፡ እሱ ፡ የልብን ፡ ዐዋቂው ፡ አምላክ ፡ አቅፎ ፡ ደግፎ ፡ በደኅና ፡ እቤታቸው ፡ ያግባልን - - አቡነ ፡ ዘበሰማያት - - አንችንም ' እግዚአብሔር ፡ ልዑል ፡ ይባርከኪ ፡ ወያርኢ ፡ ገጾ ፡ ላዕሌኪ' ቡርክት ፡ ሁኚ - - የጳጳሳቱ ፡ የቀሳውስቱ ፡ የመነኮሳቱ ፡ የነገሥታቱ ፡ የመኳንንቱ ፡ በጠቅላላው ፡ የቅድስት ፡ ሀገራችን ፡ ሕዝብ ፡ ጸሎት ፡ ከስምንተኛው ፡ ሺ ፡ መቅሠፍት ፡ ይጠብቀን - - ቡሩክ ፡ ሁኑ - -

ሁሉም ፡ ተያይዘው ፡ ወደ ፡ ግብግሩው ፡ ይገባሉ ። ወይዘሮ ፡ አሰጋሽ ፡ ትንሽ ፡ ቆይተው ፡ ብቅ ፡ ቢሉ ፡ የፍሬዋንና ፡ የበላይን ፡ መሄድ ፡ አሽከር ፡ ይነግራቸዋል — ቀና ፡ ሲሉ ፡ የባሻገራቸውን ፡ አቀበት ፡ ተያይዘውት ፡ ይመለከታሉ ። — እነ ፡ ፍሬዋ ፡ ቢሆን ፡ መለስ ፡ ያላችሁ ፡ እንደሁ ፡ የጨው ፡ ዐምድ ፡ ትሆናላችሁ ፡ ያሏቸው ፡ ይመስል — አፋፉ ፡ ላይ ፡ እንኳ ፡ ሲደርሱ ፡ መለስ ፡ አላሉም - - እደፍርስ ፡ ከወይዘሮ ፡ አሰጋሽ ፡ ለጥቆ ፡ ብቅ ፡ ይላል - - እቤት ፡ በታች ፡ ሸለቆ ፡ ውስጥ ፡ አንድ ፡ ገበሬ ፡ ያቅ ራራል—

« ግራ ፡ ነፍሶ ፡ ቀኝ ፡ እስቲመልሰው ፡

የተናገሩህን ፡ እሺ ፡ በል ፡ አንተ ፡ ሰው - - -

« ድንቁርናና ፡ ዕውቀት ! እምቢ ፡ በል ፡ አንተ ፡ ሰው ! አይልም ፡ ላፉ ፡ እንኳ ፡ ቢሆን ! ? » ያስተጋባል ፡ አደፍርስ ፡ ሽለላውን ።

ጺወኔ ፡ ብቅ ፡ ትላለች ።—

« እንዲህ ፡ ያለች ፡ ልጅ ! » ይሉና ፡ ተመልሰው ፡ ይገባሉ ፡ ወይ ዘሮ ፡ አሰጋሽ—ፍሬዋን ፡ በዚያ ፡ ጠምዛዛ ፡ አቀበት ፡ ለዓይናቸው ፡ እስ ክትጠፋ ፡ ድረስ ፡ ሲከተሏት ፡ ይቆዩና - - -

« ታውቂያለሽ ? » ይላል ፤ ጺወኔ ፡ ከቤት ፡ ስትወጣ ፡ እንጂ ፡ ወደ ፡ አጠገቡ ፡ መጥታ ፡ መቆም ፡ አለመቆሟን ፡ ሳያይ ፡ የሚናገረው ፡ አደፍ ርስ « - - ከቃላት ፡ ሁሉ ፡ ደስ ፡ የሚሉኝን - - እምቢ ! አሻፈረኝ ! እምቢ ፡ አሻፈረኝ ! እነዚህ ፡ ናቸው ፡ ከቃላት ፡ ሁሉ ፡ ነፍስ ፡ ያላቸው ፡ የሚመስለኝ - - ሙዚቃ ፡ እንደሰማሁ ፡ ዓይነት ፡ ደሜን ፡ የሚያፍለ ቀልቁት - - በሙዚቃ ፡ መደርደር - - በድምፅ ፡ መታወጅ ፡ ያለባቸው ፡ የሚመስለኝ - - -

እቤት ፡ በታች ፡ ደሞ ፡ እሥምሪቱ ፡ ሆኖ ፡ ሲዘፋፍን ፡ ይሰማል ፡ ወርዶፋ - -

« አዲስ ፡ አበባ ፡ ሜ ፡ በይ ፡
እሥመራ ፡ ቡኢ ፡ መሌ ፡
አባ ፡ ፌቴ ፡ ጃለ — ዱ ፡
ነጀላ ፡ እንዱኢን ፡ መሌ - -

## ፲፪

# አደፍርስ

« በዛሬው ፡ ዘመን ፡ ሳይጋቡ ፡ መፋታት ፡ በተማሩት ፡ ሰዎች ፡ ውስጥ ፡ ተጋብቶ ፡ መፋታት ፡ ባልተማሩት ፡ ውስጥ ፡ ይበዛል ። በኔ ፡ አስ ተያየት ፡ ሳይጋቡ ፡ መፋታት ፡ በተማሩት ፡ ሰዎች ፡ ውስጥ ፡ የሚበዛበት ፡ ምክንያት ፡ ልቡሰ ፡ ጥላቸው ፡ ተመሳሳይ ፡ ስለማይገኝለትና ፡ አስቀድሜ ፡ እንዳጫወትሁሽ - - በመጀመሪያ ፡ በወረቀት ፡ ማስፈር ፡ የሚገባቸውን ፡ የልቡሰ ፡ ጥላቸውን ፡ መግለጫ ፡ ስለሚዘነጉ ፡ ነው - - በትሆናለች ፡ በም ስቅልቅል ፡ ልቡሰ ፡ ጥላ ፡ እየተመሩ ፡ እውነተኛ ፡ ልቡሰ ፡ ጥላቸው ፡ የሠ ነዘረውን ፡ እየተዉ ፡ በዓይን ፡ ዐዋጅ ፡ ስለሚመሩ - - እንዳጫወት ሁሽ ፡ እንግዲህ ፡ ይኸንን ፡ ሁኔታ ፡ ለማስወገድ ፡ መጻፉ ፡ ይጠቅማቸ ዋል ፡ ማለት ፡ ነው - - - » እያለ ፡ ያመጣዋል ፡ አደፍርስ ፡ ጥላ ፡ እንደ በረዶ ፡ ካጥር ፡ ውጭ ፡ ሲዝናና ፡ ጺወኔን ፡ ባርማሽላ ፡ እሸት ፡ ስትቆርጥ ፡ ያያትና ፡ ጠጋ ፡ ብሎ ፡ ቆረጣውን ፡ እየረዳት ፡ ሲያወራ - - - ጺወኔ ፡ የሚናገረው ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ጨርሶ ፡ ባይገባትም ፡ በስሜት ፡ እየገነፈለ ፡ ስለነበረ ፡ አነጋገሩ ፡ ባድናቆትና ፡ ባክብሮት ፡ ዓይን ፡ እየተመለከተች ፡ ነበር ፡ የምታዳምጠው - - -

« - - ከተጋቡ ፡ በኋላ ፡ የሚፋቱት ፡ ከየቦታው ፡ እየመጡ ፡ ከተማውን ፡ የሚያጣብቡት ፡ ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ ምክንያት ፡ ግን ፡ ምን ፡ ይመስልሻል? - - ባባትና ፡ እናቶቻቸው ፡ ልቡሰ ፡ ጥላ ፡ ትይዩ ፡ ተመሥርቶ ፡ የነበ ረው ፡ ልቡሰ ፡ ጥላቸው ፡ ድንገት ፡ እከተማ ፡ በመምጣት ፡ ስለሚያድግ ባቸው ፡ ነው ። ተመልከችው ፡ ለምሳሌ—ስንት ፡ ዘመዶቻቸው ፡ አሉ ፡ እከተማ ፡ ደርሰው ፡ እየተመለሱ ፡ ብዙ ፡ ነገር ፡ የሚያጫውቷቸው - - ስንት ፡ ጓደኞቻቸው ፡ አሉ ፡ እከተማ ፡ ደርሰው ፡ እየተመለሱ ፡ ብዙ ፡ ነገር ፡ የሚያጫውቷቸው - - እነሱም ፡ በበኩላቸው ፡ እየከተማው ፡ እየሄዱ ፡ ማየትና ፡ መስማታቸው ፡ አይቀርም ፡ እንግዲህ - - ሌላው ፡ ቢቀር ፡ የሰሙትን ፡ ለማረጋገጥ - - እንግዲህ ፡ ምን ፡ ይሆን ፡ ይመስል ሻል ፡ ልቡሰ ፡ ጥላቸው ፡ በዚህን ፡ ጊዜ - - ? ያለመጠን ፡ ያለመጠን ፡ ያድጋል - - ድንገተኛው ፡ ልቡሰ ፡ ጥላቸው ፡ የዱሮውን ፡ ልቡሰ ፡

ጥላቸውን ፡ ይደመስሰዋል ፡፡ እያደገ ፡ የሄደው ፡ ልቡሰ ፡ ጥላ ፡ በጥንታዊው ፡ ልቡሰ ፡ ጥላ ፡ ከተመሠረተው ፡ የኑሮ ፡ ጓድ ፡ ጋር ፡ ሊኖር ፡ አይችልም ፡፡ በርግጥ ፡ ሁኔታውን ፡ ለማሻሻል ፡ ከተፈለገ ፡ የልቡሰ ፡ ጥላው ፡ እድገት ፡ እንዲቋረጥ ፡ ማድረግ ፡ ያሻል ፡ ማለት ፡ ነው ፡፡ በዘመናዊ ፡ ትምህርት ፡ ሳይበለጽጉ ፡ ልቡሰ ፡ ጥላን ፡ ብቻ ፡ ማዳበር ፡ በሽታ ፡ ማትረፍ ፡ ነው ፡፡ ስለከተማው ፡ ያዩትንም ፡ ሆነ ፡ የሰሙትን ፡ ሁኔታ ፡ ጠንቁን ፡ ሳይተክል ፡ በፊት ፡ ብሽር ፡ ብሽር ፡ እንዳለ ፡ ማስቀረት ፡ ያስፈልጋል ፡፡ ጥንታዊ ፡ ልቡሰ ፡ ጥላቸውን ፡ ባለበት ፡ እንዲላወስ ፡ እንጂ ፡ እንዲድህና ፡ ቆሞ ፡ እንዲሄድ ፡ በማይረዳው ፡ በዚህ ፡ በያዝነው ፡ መሸጋገሪያ ፡ ዘመን ፡ እስከዚህ ፡ የከተማው ፡ ሁኔታ ፡ እንዲያጓጓ ፡ አያሻም ፡፡ ከቅሬነትና ፡ ካጉራ ፡ ዘላይነት ፡ ኑሮ ፡ በስተቀር ፡ ምን ፡ ሊገኝ ፡ ነው ፡ እከተማ ፡ በመምጣት ? የያዝሁት ፡ ያገዝሁትና ፡ የይድረስ ፡ ይድረስ ፡ ኑሮስ ፡ የቱን ፡ ያህል ፡ ደስታ ሊሰጣቸው ፡ ነው - - ? አይመስለኝም ፤ ደስታ ፡ ሊሰጣቸው ፡ አይችልም ፡፡ የከተማዎቹም ፡ ሆኑ ፡ የባላገሮቹ ፡ እንደ ፡ ልቡሰ ፡ ጥላቸው ፡ መኖር ፡ አለባቸው ፡፡ እንዳጫወትሁሽ ፡ የከተማዎቹ ፡ ሰዎች ፡ እንደየልቡሰ ፡ ጥላቸው ፡ ሲያገቡ ፡ ከየባላገሩ ፡ የሄዱት ፡ ቅሬዎች ፡ ጐብኚ ፡ ያጡና ፡ ወደ ፡ የመጡበት ፡ ጐሬ ፡ ይመለሳሉ ፡፡ ለመውጣት ፡ እየጐሬው ፡ አፍንጫማ ፡ ላይ ፡ የደረሱት ፡ ጓደኞቻቸው ፡ የነሱን ፡ መመለስ ፡ ሲያዩ ፡ እየጐረያቸው ፡ ይቀራሉ ፡፡ የያዙትን ፡ እንዳይነጠቁ ፡ እንጂ ፡ ያልያዙትን ፡ ለመያዝ ፡ አይፈልጉም - - -እንዴ ! ምን ፡ ማለትሽ ፡ ነው ? አሁንማኮ ፡ የባላገሩ ፡ ዳንዴ ፡ ሁሉ ፡ ያለሚስት ፡ ቀረ ? መልከ ፡ ቀናና ፡ ልጅነት ፡ ያላት ፡ ሁሉ ፡ ወደ ፡ ከተማ ፡ መጉረፍ - - በልዩ ፡ ልዩ ፡ ዓይነት ፡ ያባለ ፡ ዘር ፡ በሽታ ፡ መለከፍ - - መክኖ ፡ መቅረት - - የሕዝባችን ፡ ቁጥር ፡ መቀነስ - - እንዴ ፡ ምን ፡ ማለትሽ ፡ ነው - -

እቤት ፡ ውስጥ ፡ አቶ ፡ ጥሶ ፡ ወይዘሮ ፡ አሰጋሽና ፡ አቶ ፡ ወልዱ ፡ ወሬ ፡ ይዘዋል ፡፡ የቦረንትቻው ፡ ሥጋ ፡ ነገር ፡ ከጨዋታ ፡ ጨዋታ ፡ በመውለድ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ መልክ ፡ እያወጣ ፡ ሄዷል—

« - - የፈጥመኝ ፡ ንጉሥ ፡ ያፈራርደን ፡ ካለ ፡ አለቀ - - የጨው ፡ ዐምድ ፡ ነው ፡ የሚሆነው ፡ ያገሬው ፡ ሰው ፡ ሁሉ - - - » በረጅሙ ፡ ይዘዋል ፡ ወጉን ፡ ወይዘሮ ፡ አሰጋሽ« - - አሁን ፡ በቀደም ፡ ታምር ፡ ነውኮ ፡ የሆነው - - ጆሮ ፡ የማይሰማው ፡ ነገር ፡ የለ - - -! እርስዎማ ፡ መቼም - - ወምበር ፡ የሆኑ ፡ ሰው - - ስንቱን ፡ ነገር ፡ ሰምተውታል -- በኛ ፡ አገር ፡ ግን ፡ ጉድ ፡ ተባለ - - ጉድ ፡ ማለቂያ ፡ የለው ፡፡ እዚህኮ ፡

ተጉለት ፡ ውስጥ ፡ ነው ። — ሴትዮዋ ፡ ልጅዋን ፡ ትልከዋለች ፡ ድውር ፡ አሲዛ፡እሸማኔ ፡ ቤት ። ሕፃን ፡ ልጅ ፡ የስድስት ፡ ይሁን ፡ የሰባት ፡ ዓመት ። ምን ፡ ይመጣ ፡ ብላ ፡ አስባ ! ወደ ፡ ሌላ ፡ ጉዳይዋ ፡ ሄዳ ፡ ኖሯል ። እግዜር ፡ ያሳያችሁ ፡ እንግዲህ—እቤቷ ፡ ስትመለስ ፡ ብትጠብቅ ፡ አይመጣ ብትጠብቅ ፡ አይመጣ - - ምነው ፡ ዘገዬ ፡ ይኸ ፡ ልጅ ፡ ትልና ፡ ወጣ ፡ ማለት - - እንዲህ ፡ አለ ፡ አይደለም - - መንገዱንም ፡ ሰፈሩንም ፡ ቃኘት ፡ ቃኘት ፡ ከየት ፡ ቢመጣ - - በቀዬውም ፡ ታጣዋለች ። ትሮጣ ለች ፡ ወደ ፡ ሸማኔው ‘ - - ልጄን ፡ ድውር ፡ አሲዤ ፡ ልኬው ፡ ነበር ’ ትለዋለች ።— ‘ አዎ ፡ ልከሽው ፡ ነበር ፤ ድውሩን ፡ ሰጥቶኝ ፡ ወዲያው ፡ ተመልሷል—እዚህ ፡ እንዲጠብቅሽ ፡ ከፈለግሽ ፡ ለምን ፡ አልነገርሽኝም? ’ ይላታል ። ከዚያ ፡ መቼስ ፡ ምኑን ፡ ትያዘው—የናት ፡ ሆድ ፡ የናት ፡ ሆድ ፡ ነው ፡ ወደ ፡ ዱርም ፡ ወደ ፡ ወንዝም ፡ ወደየዘመዱም ፡ ብትል ፡ ከዬት ! ምን ፡ ይዋጣት ! ምን ፡ ትሁነው ? ብትጠብቀው ፡ አይመጣ - - ብትጠ ብቀው ፡ አይመጣ—ዋለ — አደረ — ሰነበተ — ቂቂ ፡ ሆነ - - ‘ የተቸ ገረ ፡ መቼም ፡ እርጉዝ ፡ ያገባል ’ አይደለም - - ትሄዳለች - - ወደፈጥመኝ ። ‘ ልጄን ፡ ተነጠቅሁ ! ልጄን ፡ ተነጠቅሁ ! ቀማኛ ፡ ወሰደብኝ - - መል ስልኝ ፡ ልጄን ፡ መልስልኝ ፡ ልጄን ! ’ በማለት ፡ እጫማው ፡ ላይ ፡ ወድቃ ፡ እየተንፈራፈረች ፡ ትነግረዋለች ። ባለውቃቢውም ‘ ተነሽ ! ተነሽ ! ይልና ፡ ይጠይቃታል ፡ ሁኔታውን - - አትነሣም ፡ እሷ ፡ ግን ።—እን ዳለች ፡ ሆና ፡ እሸማኔ ፡ ቤት ፡ ልኬው ፡ ነው ፡ ሳይመለስ ፡ የቀረው ፡ ትለዋለች ‘ - - ተነሽ ፡ ተነሽ ! ! ’ ይላታል ፡ እንደገና ። አትነሣም ፡ እሁ ንም ።-‘ ተነሽ ፡ ነው ፡ የምለው ! ’ ሲላት ፡ ነው ፡ በሦስተኛው ፡ ጊዜ ፡ ብድግ ፡ የምትለው ። ከዚያ ፡ ነው ፡ እንግዲህ ፡ ቀጥታ ፡ ሂጂ ፡ የሚላት ፡ ወደ ፡ ሸማኔው ፡ ቤት - - ጉድ ፡ ስሙልኝ ፡ እንግዲህ ‘ - - ወደ ፡ ሸማኔው ፡ ቤት ፡ ሂጂና ፡ እግሩን ፡ እሚያወዛውዝበት ፡ ጉድጓድ ፡ ውስጥ ፡ ት. . .ክ ፡ ብለሽ ፡ ትክ ፡ ብለሽ ፡ ተመልክተሽ ፡ ነይ ’ ይላታል ። እንደታዘዘችው ፡ ትሄድና ፡ የሸማኔውን ፡ ጉድጓድ ፡ ትክ ፡ ብላ ፡ አይታ ፡ ትመለሳለች ። — ‘ ምን ፡ አየሽ ? ’ ይላታል ፡ ይሰየምና ።—እንደ ፡ ዱሮው ፡ አይደለም ፤ ዱሮ ፡ የተደመደመ ፡ ነበር ፤ አሁን ፡ ግን ፡ አፈሩ ፡ ተቆፍሮ ፡ ገና ፡ አልረጋም ’ ትለ ዋለች ። ከመቀመጫው ፡ ብድግ ፡ ይላል ፡ ባለውቃቢው - - ጐርደድ ፡ ጐር ደድ ‘ - - ሂድና ፡ ሸማኔውን ፡ ጥራው ’ ብሎ ፡ መጮህ ፡ ነዋ ! አንዱን ፡ አሽ ከሩን ፡ ትክ ፡ ብሎ ፡ እየተመለከተ ። ተላላኪው ፡ እንደ ፡ ታዘዘው ፡ ይሄዳል ። ሸማኔው ፡ ግን - - ‘ እኔ ፡ ባለውቃቢ ፡ ምኔ ፡ ነው ፡ እሽከሩ ፡ መስየዋለሁ ፡ እንዴ ? አልመጣም ’ ብሎ ፡ ይመልሳል ።—ሁለተኛ ፡ ጊዜ ፡ ይልክበታል ።

ሽማኔው ፡ ለበን ፡ ጠበንጃውን ፡ ያወጣና ፡ ጥይቱን ፡ አጉርሶ ፡ በመልክ ተኛው ፡ ላይ ፡ ሊተኩስበት ፡ ሲያነጣጥር ፡ መልክተኛው ፡ አይቶ ፡ ያመ ልጥና ፡ ይመለሳል ። ሦስተኛ ፡ ጊዜ ‘ ሄደህ ፡ አሁንም ፡ የፈጥመኝ ፡ ንጉሥ ፡ ና ፡ ይልሃል ’ በለው ፡ ብሎ ፡ ያዘዋል ፡ አሽከሩን ።—‘ ይገድለኛል ፤ እንዴት ፡ ብዬ ፡ ተመልሼ ፡ እሄዳለሁ ? ምን ፡ ብዬ ፡ እሄዳለሁ ? ’ ብሎ ፡ ይጨነቃል ፡ አሽከሩ ። ‘ እሱ ፡ ከገደለህማ ፡ እኔ ፡ ገደልሁህ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ሂድ ! ’ ብሎ ፡ ያዘዋል -- ይሄዳል ።— ሽማኔው ፡ ለበኑን ፡ ያወጣና ፡ አነጣጥሮ ፡ መተኮስ ፡ ነዋ ፤ ቃታውን ፡ ሳብ ፡ ሲያደርግ ፡ ‘ ቋ ! ’ ይልና ፡ ዝም -- ሁለተኛ ፡ ጊዜ ፡ አጉርሶ ፡ ቃታውን ፡ ሳብ ፡ ሲያረግ ‘ቋ ! ’ ይልና ፡ ዝም -- ሦተኛ ፡ ጊዜ ፡ አጉርሶ ፡ ሳብ ፡ ሲያረግ ፡ ‘ ቋ ! ’ ይልና ፡ ዝም -- መለስ ፡ ነዋ ፡ አሽከር ፡ በዚህን ፡ ጊዜ ።—የፈጥመኝ ፡ ንጉሥ ፡ የሽማኔውን ፡ ሆድ ፡ ወዲያውኑ ፡ ሌሊቱን ፡ ንፍትፍት ፡ አድርጎት ፡ ማደር -- ወዲያ ፡ ቢል ፡ ወዲህ ፡ ውጪ ፡ ነፍስ ፡ ግቢ ፡ ነፍስ ፡ መጨነቅ ፡ መጠበብ ፡ ሆነ --እምን ፡ ይግባ ? ጐረቤቶች ፡ ይሰበሰቡና ፡ ጉዱን ፡ መቼም ፡ አላወቁም -- ምነው ፡ ብትማልደው ፡ ምናለበት ፡ ምን ፡ ክብርህን ፡ ይቀንሰዋል ፡ ይሉና ፡ በግድ ፡ ይገፋፉታል ። ጉድ ፡ አልሰሜ ፡ የጐረቤት ፡ ነገር -- ሽማኔም ፡ የተያዘ ፡ የተጨነቀ ፡ ምን ፡ ይሁነው—ሌላ ፡ ዘዴ ፡ ስላጣ ፡ በቃሬዛ ፡ ውሰዱኝ ፡ ይልና ፡ እፈጥመኝ ፡ ዘንድ ፡ መምጣት ፡ ነዋ ! እደጅ ፡ ያሳርፉታል ፤ እቤት ፡ እንኳን ፡ ሳያስገቡ --ያን ፡ በግሩ ፡ ለመምጣት ፡ የኮራ ፡ ሰውዬ ። የፈጥመኝ ፡ ንጉሥ ፡ ይሰየማል -- ይፈርድበታላ ! ገድለህ ፡ እመሥሪያ ፡ ጉድጓድህ ፡ ውስጥ ፡ የቀበርከውን ፡ ልጅ ፡ ስታስወጣ ፡ ትድናለህ ፡ ብሎ -- ! ሁለት ፡ ተመልካች ፡ ይጨምርና ፡ በቃሬዛው ፡ እንዳለ ፡ ይመልሰዋል --- ! ጉድጓዱ ፡ ሲቆፈር ፡ በዝተት ፡ ተሸፍኖ ፡ ብቅ ፡ ይላል ፡ ሬሳው ።— ሽማኔ ውም ፡ ወዲያው ፡ በሽታው ፡ ይተወውና ፡ ይነሣል ።-ምን ፡ አለ ፡ ከዚያማ-- ሬሳንና ፡ ገዳይን ፡ አያይዞ ፡ ለደብረ ፡ ብርሃን ፡ ችሎት ፡ ላካቸዋ -- መን ግሥት ፡ እንደ ፡ ፍጥርጥሩ ፡ እንዲያደርጋቸው ---

« ለመሆኑ ፡ ለምን ፡ ገደልሁት ፡ አለ ? » አቶ ፡ ወልዱ ፡ ይጠይቃሉ።

« እረግ ፡ እረግ ፡ ዋናውን ፡ ነገር ፡ ረስቸዋለሁ ፡ ለካ--ደሙም ፡ በጠ ርሙስ ፡ ሆኖ ፡ ተከቶ ፡ ተገኘ ፡ እቤቱ ---

« የምኑ ፡ ደም ?

« የልጁ ፡ ደም ---

« ምን ፡ ሊያደርግለት ፡ ቀዳው ፡ ደሞ ፡ የልጁን ፡ ደም -- ?

« - - የእናንተ ፡ ነገር — እንዱ ፡ ዐባይ ፡ ጠንቋይ ፡ ባልባለቀ ፡ ልጅ ፡ ደም ፡ ዕፅ ፡ እስጥሀ ፡ ትጨምርና—እጅህን ፡ ደረትህን ፡ ጀርባህን ፡ ሙላህን ፡ ከተነቀስህ ፡ ሀብታም ፡ ትሆናለህ ፡ ብሎት ፡ ነዋ ! ሊከበር ፡ ሀብታም ፡ ሊኮን - - ! ዛሬ ፡ ሰዉ ፡ ሁሉ ፡ የያዘው ፡ ይኸንኑ ፡ አይደለም ፡ እንዴ - - ? እነዚህ ፡ በየቦታው ፡ አዳዲስ ፡ የእህል ፡ ወፍጮ ፡ የሚተክሉ ፡ ሁሉ ፡ ትንንሽ ፡ ልጆች ፡ እየፈለጉ ፡ ሲሆን ፡ እዚያው ፡ እተተከለበት ፡ ቦታ ፡ ድረስ ፡ ወስዶ ፡ በማረድ ፡ ካልሆነም ፡ ደግሞ ፡ እሌላ ፡ ቦታ ፡ ታርዶ ፡ በጠርሙስ ፡ በመጣው ፡ ደም ፡ ባቡሩን ፡ ካልረጩ ፡ መቼ ፡ ገበያ ፡ ያገኛሉ ? - - የስንቱ ፡ ልጅ ፡ ነው ፡ ይመስላችኋል ? እንደዋለ ፡ የሚቀረው - - - የዚህ ፡ በጠርሙስ ፡ የሚመጣውማ ፡ ደም ፡ ሺሺ ! ብር ፡ ነው ፡ አሉ ፡ ዋጋው - - -

« በምን ፡ ያውቀዋል ፡ የሰው ፡ ደም ፡ መሆኑን ? የበግ ፡ የፍየል ፡ ደም ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ፡ ለምሳሌ ! » ይናገራሉ ፡ አቶ ፡ ጥሶ ፡ ሲያዳምጡ ፡ ይቆዩና —

« የለም ፡ ሁለት ፡ ጆሮቹን ፡ ቀንጥቦ ፡ ይዞ ፡ መሄድ ፡ አለበት ፡ ይላሉ፡ ለምልክት ! »

« የሚገርም ፡ ነገር—የከፋታቸው፡ ከፋት ፡ ደሞ ፡ ሁለቱንም ።-እውነታቸውን ፡ ነው ፤ በባላገር ፡ ገንዘብ ፡ አለመገኘት ፡ የጠቦት ፡ በግ ፡ ደሙን ፡ በጠርሙስ ፡ እያደረገ ፡ ካንድ ፡ ጆሮ ፡ ጋር ፡ የሚያቀርበው ፡ ሰው፡ ይበዛ ፡ ነበር ።-ምን ፡ ከፋው ፡ ባንድ ፡ ጆሮ ፡ ሽ ! ብር ፡ ካገኘ - - ? ለመሆኑ ፡ ከነነፍሱስ ፡ የሚመጣው ፡ ስንት ፡ ያወጣ ፡ ይሆን ? » ይጠይቃሉ ፡ አቶ ፡ ወልዱ ።

« እሱ ፡ ሁለት ፡ ይደፍን ፡ እንደሁ—ነገሬም ፡ ብዬ ፡ አላጤንኩት ፤ ብቻ ፡ መቼስ ፡ በየቦታው ፡ ንግድ ፡ አድርገው ፡ ይዘውታል ፡ ይሉኛል - -

አቶ ፡ ጥሶ ፡ ኩስትርትር ፡ ያለና ፡ የተጨነቀ ፡ የመሰለ ፡ ግንባራቸውን ፡ በጃቸው ፡ እያሻሹ ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ ይወጣሉ ።

« አሁን ፡ ታዲያ ፡ ይኸን ፡ ያንተን ፡ ድርቆሽ ፡ በስንት ፡ ብር ፡ ልሽጥልህ ? ስድሳ ፡ ብር ፡ በጣም ፡ ውድ ፡ ዋጋ ፡ የሆን ፡ መሰለኝ - - እምልህ » ይጠይቃሉ ፡ ወይዘሮ ፡ አሰጋሽ ፡ ወንድማቸውን ፡ አቶ ፡ ወልዱን ።

« - - ሞትና ፡ ሕይወት ፡ ድንቁርናና ፡ ዕውቀት - - - ! ባላገሩ ፡ ነው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ተስፋ - - ከባላገሩ ፡ ከሚወለዱት ፡ ልጆች ፡ ነው ፡ ላገራችን ፡ ዶክተሮች ፡ መሐንዲሶች ፡ እናገኛለን ፡ ብለን ፡ ተስፋ ፡ ያለን - -

ታዲያ - - እባላገር ፡ የሚቀሩት ፡ አሮጊቶች ፡ ብቻ ፡ ከሆኑ ፡ የመውለድ ፡ ጊዜያቸው ፡ ከተላለፈ ፡ አሮጊቶች ፡ ጋር ፡ ብቻ ፡ ከቀሩ - - ይኸ ፡ ተስፋችን ፡ እንዴት ፡ ይሳካ ፡ ይመስልሻል - - ? የለም ! የለም—ኮረዳ ፡ ኮረዳዎቹ ፡ ከየመንደራቸው ፡ የማይወጡበት ፡ የወጡትም ፡ ወደየመንደራቸው ፡ የሚመለሱበት ፡ መንገድ ፡ መገኘት ፡ አለበት ።- እስቲ ፡ ለምሳሌ ፡ ተመልከችው — ይኸን ፡ ባገር ፡ ቤት ፡ ያለውን ፡ ሃይማኖታዊነት ፡ ርኅራሄ ፡ ገርነት ፡ ሰው ፡ አፍቃሪነት ፡ እንግዳ ፡ ተቀባይነት ፡ ዘመናዊ ፡ ትምህርት ፡ የቀላቀልሽበት ፡ እንደሆን ፡ እንዴት ፡ ይመስልሻል ፡ ውጤቱ ? አይናፍቅሽሞይ ? አያስቀናሽሞይ ? ምንኛ ፡ የሚያኳኳ ፡ ይመስልሻል ! እስኪ ማ ፡ በረጅሙ ፡ አስቢው - - » ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ከንፈሮቿን ፡ ሳትከድን ቆይታ ፡ ኖሮ ፡ ጥያቄ ፡ ሲያቀርብላት ፡ ነቅነቅ ፡ ስታደርጋቸው ፡ እንደባይተዋር ፡ ገላ ፡ ሲገናኙ ፡ በመሰማታቸው ፡ ፈዝዛ ፡ መቆየቷ ፡ ይታወቃትና ፡ መልስ ፡ በመመለስ ፡ ፈንታ ፡ አፏን ፡ ኩርትም ፡ አድርጋ ፡ ይዛ ፡ እሱን ፡ እሱኑ ፡ ታየዋለች ።

«--የዋሁ ፡ ሰላማዊው ፡ አገሩን ፡ ወዳዱ ፡ ንጉሠ፡ነገሥቱን፡ አፍቃሪው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ምንኛ ፡ በተበራከተ ! ምንኛ ፡ በተራመደ ! ምን ፡ ይመስልሻል ፡ ታዲያ ፡ አንቺስ ፡ ስታስቢው ? እንዴት ፡ ይመስልሻል -- የወደፊቱን ፡ ባሳብ ፡ መነጥር - - -

« ጥልያኒኛም ፡ እችላለሁ ! » ጴጥሮስና ፡ ሮማን ፡ እየተነጋገሩ ፡ በዚያው ፡ በሽቱ ፡ ውስጥ ፡ ሲያልፉ ፡ ይሰማል ።

« አስተምረኝ ፡ እስቲ ፡ ጥልያኒኛ - - ካማራ ፡ አፍ ፡ ያስቸግራል ? » ትጠይቀዋለች ፡ ሮማን ።

« አ ፡ ቤ ፡ ቼ ፡ ዴ - - አዎ ፡ አዎ ፡ አስቸጋር ፡ ነው— ዶሞ - - እኔ ፡ ላንች ፡ አስተማር ፡ ሆኜ ፡ ልያገለግል ፡ እመየቴ ፡ አይወዱም - - እመኩር ፡ ነበር ፡ ግን - - -

« ታዲያ ፡ ለምን ፡ አታስተምረኝም - - ?

« ከፎሎክ ፡ ዶሞ ፡ በቀላል ፡ ምይንገድ ፡ ከሳቸው ፡ ልያመልጥ ፡ እችላለሁ - - -

« የትውልድ ፡ አገርህ ፡ አይናፍቅህም ፡ ብዙ ፡ ዓመትህ ፡ ነው ፡ መቼም ፡ እዚህ ፡ ከመጣህ - - -

« አዎ ! ካሥመራ ፡ ከመጣሁት ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ቆይቷል ፤ ክንፍ ፡ ብይኖረኝ ፡ እንደ ፡ ሚካኤል ፡ አድርጌ ፡ ሰውነቴ ፡ ያወጣት ፡ ነበር - - -

## ፲፯

# አደፍርስ

በማግስቱ ፡ ከብት ፡ ማጐሪያ ፡ ሰዓት ፡ ገደማ ፡ ጺወኔ ፡ አጥሩን ፡ መርኮዝ ፡ ብላ ፡ ቆማ ፡ ማዶ ፡ ማዶውን ፡ ትመለከታለች—ሽለቆውን ፡ ጉባውን ፡ ድንጋዩንና ፡ ጫካውን - - አልፎ ፡ አልፎ ፡ ቆቅና ፡ ጅግራዎች ፡ ድንገት ፡ ግርብብ ፡ ሽ-ተት ፡ ብለው ፡ እየመጡ ፡ እየጐጅዋቸው ፡ አጠገብ ፡ ዶፍ ፡ ዶፍ ፡ በማለት ፡ ሲያርፉበት ፡ ይታያል ። ደርሶ ፡ ተወርውረው ፡ የተተከሉ ፡ ይመስል ፡ የጺወኔ ፡ ዓይኖች ፡ ግን ፡ የሕይወትን ፡ እንቅስቃሴ ፡ ሲከታተሉ ፡ አይታዩም ፤ ባንድ ፡ ነገር ፡ ላይ ፡ ረግተዋል—ሌላውን ፡ ትርኢት ፡ ሁሉ ፡ አንድ ፡ ላይ ፡ አምጥቶ ፡ የከሠተ ፡ በሚመስል ።-

ከኋላዋ ፡ ሁለት ፡ እጆች ፡ ቀስ ፡ እያሉ ፡ እያሰሉ ፡ ይጠጉና ፡ ዓይኖቿን ፡ በጣቶቻቸው ፡ ሽፍን ፡ ያደርጉታል ። ጭንቅላቷን ፡ ሹልክ ፡ አድርጋ ፡ በማስለቀቅ ፡ ፈንታ ፡ እሷም ፡ በበኩሏ ፡ በጉንጭና ፡ በጉንጮቿ ፡ አቅጣጫ ፡ ጣቶቹን ፡ በጣቶቿ ፡ ያዝ ፡ እንደማድረግ ፡ ትልና ፡—

« ዐውቄሻለሁ ፡ እባክሽ ፤ ሮማን ፡ ነሽ - - » ትላለች ፤ የሸፈኗት ፡ ጣቶች ፡ ቢሆን ፡ አይነሡም « ፍቅርተ ፡ ነሽ » ትላለች ፡ ትቀጥልና ። አሁንም ፡ አይነሡም ። ለሦስተኛ ፡ ጊዜ ፡ እንደምታስብ ፡ ዓይነት ፡ ትንሽ ፡ ቆየት ፡ ትልና ፡ ያለጥርጥር ፡ ያወቀች ፡ በሚያስመስላት ፡ አንደበት - - « ማሚቴ ፡ ነሽ ! » ትላለች ። ጣቶቹ ፡ ቢሆን ፡ ንቅንቅም ፡ አይሉም ።- እንደምንም ፡ ታግላ « እንዴ ፡ ምነው ፡ ልቀቂኝ ፡ የምን ፡ ጣብቂያ ፡ ነው » ብላ ፡ ዓይኖቿን ፡ ትገልጣለች ።

« ሴቶች ፡ ብቻ ፡ ናቸው ፡ እንዴ ፡ ካንቺ ፡ ጋር ፡ የሚቃለዱት ? » ይጠይቃታል ፡ አደፍርስ ፡ ጣቶቹን ፡ እንዳስለቀቀችው ፡ ቀስ ፡ ባለ ፡ አንደበት ።

« አዎ ፡ ሴቶች ፡ ብቻ ፡ ናቸው - - ከጐርፉ ፡ ወዲህ ፡ ከወንድ ፡ ጋር ፡ ተዋዝቼም ፡ አላቅ - - -

« ጐርፉ—ጐርፉ ! » ያስተጋባል ፡ አደፍርስ ፡ ስሙን ።

« የትምህርት ፡ ቤት ፡ ጓደኛዬ ፡ ነበር ፤ ዛሬ ፡ እንዲህ ፡ ነገር ፡ ዓለ ሙን ፡ ሊተወው - - -

« - - ድንቁርናና ፡ ዕውቀት ! እና ፡ ታዲያ ፡ እኔ ፡ አዲስ ፡ ነገር ፡ ሆኜ ብሻለኋ ? !

« ምን ፡ ጠርጥሬ ፡ ደሞ ፡ እጅህ ፡ እንኳ ፡ የወንድ ፡ አልመሰለኝም - -

« ሻከር ፡ ጕልደፍደፍ ፡ ብሎ ፡ ጨቦድ ፡ የሚያደርግ ፡ ዓይነት ፡ አይ ደለም ፤ እውነትሽን ፡ ነው - - -

« እሱ ፡ ሳይሆን ፡ እጅህንስ ፡ ለነገሩ ፡ ያህል ፡ ያዝ ፡ አርጌው ፡ አል ነበር - - - ?

« አዎ ፡ ጣቶቼን ፡ ያዝ ፡ አድርገሻቸው ፡ ነበር - - -

« ምን ፡ ጠርጥሬ ፡ ደሞ ፡ አንተን - - ወደርሻ ፡ ወርደሃል ፡ አል ተባለም ፡ ነበር ፡ እንዴ ? ምን ፡ ዓይነት ፡ ሰላቢ ፡ ነህ ፡ ለመሆኑ - - - » ሳቅ ፡ ሳቅ ፡ በሚል ፡ ፊት ፡ እየተመለከተችው « ጭራሽ ፡ ኮቴህን ፡ አልሰማሁትም - - -

« ተመለስኋ ፡ ታዲያ ! እዚያው ፡ ያመሻል ፡ ብለሽ ፡ ነበር - - ?

« እምልህ ፡ ያን ፡ አኮርዲዎ ፡ ተሸክመህ ፡ የመጣኸው ፡ ላትጫወት በት ፡ ነው ፡ እንዴ ? ምን ፡ አሸካከመህ ፡ ለዚህ ፡ ለዚህ - - -

« ሙዚቃ ፡ የሌለበት ፡ ገጠር ፡ መስሎኝ ፡ ነበር ፡ ያመጣሁት - - -

« ታዲያ ፡ አሁንስ ፡ የት ፡ ሰማህ ፡ ሙዚቃ - - - ?

« - - ሞትና ፡ ሕይወት ! የት ፡ ሰማህ ፡ ሙዚቃ ? ሙዚቃ ፡ የት ፡ ሰማህ ? ትቀልጃለሽ ፡ ልበል - - ከዚህ ፡ አካባቢያችን ፡ ከሚያምመው ፡ የድምፅ ፡ ዑደት ፡ የበለጠ ፡ ምን ፡ ሙዚቃ ፡ አለ ? ልንገርሽ ፡ እንግዲያው፡ እውነቱን ፡ የተሰማኝን ።— ከዱር ፡ እንደገባሁ ፡ አጥሩ ፡ አጠገብ ፡ ቆመሽ ፡ ባየሁሽ ፡ ጊዜ ፡ አንቺ ፡ መስለሽኝ ፡ ነበር ፡ በልዩ ፡ ጥበብሽ ፡ ዙሪያውን ፡ የምትቃኚው ፤ ጉር ፡ ጉራንጉሩን ፡ ሸጥ ፡ ሸለቆውን ፡ የምታ ዘፍኚው ፡ ከወጣት ፡ ጉሮሮ ፡ እንደሚፈስ ፡ ዜማ ፡ እንደ ፡ ጉልማሳ ፡ ጩኸትና ፡ ድንፋታ ፡ እንደ ፡ ቤተክስያን ፡ ማሕሌት ፡ እንደሚኾጉደ ጉድ ፡ የማዕበል ፡ አመጣጥና ፡ እንደሚያስገረግር ፡ እንደሚያስረገርግ ፡ የድል ፡ ድምፅ ፡ እንደ ፡ መከራ — ጭንቅ — ብስጭት — ምን ፡ ልሁነው፡ ዋይታ ፡ ነፋስ ፡ እንዳጠሽየው ፡ የዝናብ ፡ ዳመና ፡ ስግምግምታ — ዙሪ

ያውን ፡ ሲምሽከሽክ ፡ ሲደረደር ፡ ሲድረቀረቅ — አንቺ ፡ መስለሽኝ ፡ ነበር ፡ የምትቃኝው ።— ዓይኖችሽን ፡ በጣቶቼ ፡ ስሽፍናቸውስ ፡ የነ በረው ፡ ጸጥታ - - - የልብ ፡ ምታችን ፡ እንኳ ፡ የቆመ ፡ መምሰሉ ፡ ላን ዳፍታ - - ምናለፋሽ ፡ ብቻ ፡ የመላው ፡ ቀዬ ፡ ንዝረቱ ፡ ውህደቱ ፡ ዝማ ሬው ፡ እሮይታው - - - ከዚህ ፡ የበለጠ ፡ ሙዚቃ ፡ ይኖር ፡ ይመስል -- ከዚህ ፡ የበለጠ ፡ ሙዚቃ ፡ ይሰማ ፡ ይመስል - - ? ! ሙዚቃ ፡ የት ፡ ሰማህ ፡ ትይኛለሽ ? !

« ቢሆንም ፡ እኔ ፡ መስማት ፡ የምፈልገው ፡ አኮርዲዮን ፡ ነው - - ይኸ ፡ ያገሬ ፡ ጭልቅልቅታ ፡ በየለቱ ፡ የሚያደነቁረኝ ፡ ስለሆነ ፡ ሙዚቃ ነቱ ፡ አይሰማኝም - - -

« እውነትሽን ፡ ነው ፤ በየለቱ ፡ የሚደጋገም ፡ ነገር ፡ ዋጋ ፡ ያለው ፡ መሆኑ ፡ አይታወቅም ።— ከድግግሞሽ ፡ የተነሣ ፡ ዓይን ፡ ጆሮና ፡ ሌሎ ችም ፡ የስሜት ፡ አውታሮች ፡ እንኳን ፡ በጠቅላላው ፡ ይበድናሉ - - ተግ ባራቸውን ፡ ይረሱታል - - -

« እኮ ፡ ታዲያ ፡ አኮርዲዮውን ፡ ተጫወታ - - - ?

ከወፍራሙ ፡ ወደ ፡ ቀጭኑ ፡ ከቀጭኑ ፡ ወደ ፡ ወፍራሙ ፡ ጣቶቹን ፡ ሽርተት ፡ ሽርተት ፡ ያደርግና ፡ ትዝታን ፡ መጫወት ፡ ይጀምራል—አኮር ዲዮውን ፡ ከተሰቀለበት ፡ ከወይዘሮ ፡ አሰጋሽ ፡ እልፍኝ ፡ ያመጣና - - ቀስ ፡ ቀስ ፡ እያለ ፡ የሚስብ ፡ በሚመስል ፡ የድምፅ ፡ ፍልቅልቅታ — ትን ፋሽ ፡ እንደሚቆርጥ ፡ የድንጋጤ ፡ ሀቅታ—ቀስፎ ፡ ይዞ ፡ መላ ፡ ሰውነትን ፡ እንደሚሰገጥጥ ፡ ድንገተኛ ፡ ርግፍገፋ—እንደ ፡ ሻህላ ፡ እንደ ፡ ምስጥ ፡ ውስጥ ፡ ውስጡን ፡ ነከስ ፡ ነከስ ፡ ቆንጠር ፡ ቆንጠር ፡ እያደረገ ፡ አመም ፡ ደስ ፡ የሚል ፡ ስሜትን ፡ በመስጠት ፡ አታሎ ፡ አታሎ ፡ እንደሚጐለስስ ፡ ብር ክርክታ ።—እየተሰነጠበ ፡ እየተሰነጠረ ፡ ይማታ—ይላጋ—ይርመሰመስ ፡ ይጀምራል—ካኮርዲዮው ፡ እየተመጠነ ፡ የሚፈሰው ፡ የድምፅ ፡ ርቺት ።—

ሮማን ፡ ትመጣለች — የየገበሬዎቹ ፡ ልጆች ፡ ይመጣሉ —ገረዶቹ ፡ ሁሉ ፡ እነ ፡ ማሚቴ ፡ ፍቅርተ ፡ ሳይቀሩ ፡ ሁሉም ፡ ይሰበሰባሉ ፤ ይከቡ ታል — ያውታል — ያውታል—የሚነካውም ፡ የሚጐርሰውም ፡ ይመስ ላል ፡ ዓይናቸው - - በማየት ፡ ወይም ፡ በማጥናት ፡ ዓይነት ፡ አመለካ ከት ፡ ሳይሆን — የቧምቧ ፡ ውሃ ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ አሁን ፡ ለቀቅ ፡ አድ ርጐ ፡ ድንገት ፡ ሲዘጉት ፡ የውሃው ፡ ጉራጅ ፡ ከቧምቧው ፡ እንዳልመጣ ፡

ዓይነት ፡ ድምፅ ፡ ሰጥቶ ፡ ነጥሮ ፡ የሚበተነው—ልክ ፡ እንደዚያ - - - ያውታል — ያውታል — ያውታል - - -

« ሮማን ! ሮማን ! » ወይዘሮ ፡ አሰጋሽ ፡ ይጣራሉ ፤ መልስ ፡ አያገኙም ፡፡—

«ጺወኔ ! ጺወኔ ! » ይጣራሉ ፡ ደግመው ፡ ወይዘሮ ፡ አሰጋሽ ፡፡—አሁንም ፡ መልስ ፡ አያገኙም ፡፡

« ፍቅርተ — ሮማን — ማሚቴ ! - - እንዴ ! ምን ፡ ዘጋችሁ ፡ ይባላል ? ! » እያሉ ፡ ከእልፍኛቸው ፡ በቁጣ ፡ መንፈስ ፡ ወጥተው ፡ ወደ ፡ በረቱ ፡ ይመጣሉ ፡፡- ወደ ፡ ተሰበሰቡበትም ፡ ቦታ ፡ ጠጋ ፡ ይላሉ ፡፡- እንደ ፡ ተጠጉ ፡ ለጊዜው ፡ ሙዚቃው ፡ የሳቸውንም ፡ ልብ ፡ ነካ ፡ ያረገው ፡ ዓይነት ፡ ቁጣቸው ፡ በረድ ፡ ይልና ፡ ሌላ ፡ ብርሃን ፡ ፊታቸው ፡ ላይ ፡ ሲረብብ ፡ ከጺወኔ ፡ ጋር ፡ ድንገት ፡ ዓይን ፡ ለዓይን ፡ ግጥም ፡ ይላሉ ፡፡ ራሳቸውን ፡ የረሱና ፡ የዘነጉ ፡ ይመስል ፡ ቶሎ ፡ ሰብሰብ ፡ ኮስተር ፡ ብለውም « - - የምን ፡ መደናቆር ፡ ነው ፡ እባካችሁ ? ድምጼ ፡ ጣራ ፡ በጥርቆ ፡ እስኪወጣ ፡ ድረስ ፡ ስጣራ ፡ ደሞ ፡ አለመስማቴ ? ማነው ፡ እንደዚህ ፡ መረን ፡ እንድትወጡ ፡ የፈቀደላችሁ - - ሮማን ፡ ብል ፡ ማሚቴ፡ ማን ፡ ሰምቶኝ - - ያሙስ ፡ ገበያ ፡ ይመስል ፡ ስትጮሁበት ፡ ግቢዬን - - -

አኮርዲዮው ፡ ጨዋታውን ፡ ይቀጥላል ፡፡—ገረዶቹ ፡ ቅር ፡ እያላቸው ፡ ተነሥተው ፡ ወደ ፡ ሥራቸው ፡ ይመለሳሉ ፡፡ ጺወኔ ፡ ብቻ ፡ አትንቀሳቀስም ፡፡ —ወይዘሮ ፡ አሰጋሽ ፡ በንዴት ፡ መንፈስ ፡ እየተናገሩ ፡ መለስ ፡ ሲሉ ፡ የነፍስ ፡ አባታቸውን ፡ አባ ፡ አዲሴን ፡ ደስ ፡ ባለው ፡ መንገድ ፡ የሙዚቃውን ፡ ንዝረት ፡ ተከትለው ፡ አንገትና ፡ ትከሻቸውን ፡ ከእንቅስቃሴው ፡ አስማምተው ፡ ይመለከታሉ ፡፡ እዚያው ፡ አቅራቢያ ፡ አቶ ፡ ወልዱ ፡ ፊታቸውን ፡ ፈካ ፡ አድርገው ፡ ደስ ፡ ባለውና ፡ በተዝናና ፡ ፍልቅልቅታ ፡ ቆመዋል ፡፡

« ንሺ ፡ እቴ ! ሁሉንም ፡ ትተነው ነው - - ! ! አንቺን ፡ ነውኮ ፡ የምለው ፡ ነይ ፡ ተነሽ ! » ጉንተል ፡ ያደርጓታል ፡ ጺወኔን ፡ በግራቸው ፤ ሊሄዱ ፡ ከዞሩ ፡ ወዲያ ፡ ተመልሰው ፡፡ ጺወኔ ፡ ድንግጥ ፡ ትልና ፡ ብድግ ፡ ትላለች - - ያኮርዲዮው ፡ ድምፆች ፡ ይሰባበራሉ « ክራርሽን ፡ አውጭና ፡ ነይ ፡ አሰሚያቸው ፡ ለአቶ ፡ ጥሶ ፡፡— ሰው ፡ ማስረሳቱን ፡ ዐውቀን ፡ ነበር ፡ ዱሮም ፡ ዘፈን ፡ የከለከልነው - - የኔ ፡

ልጅ ፡ እንኳን ፡ ሰዉንና ፡ ነብርና ፡ እንበሳውን ፡ ነው ፡ የምታብረከር ኪው ፡ ከተጫወትሽ - - ደሞ ፡ እንደ ፡ ደንቆሮ ፡ አፍሽን ፡ ከፍተሽ ፡ እዚህ ፡ መቀመጥሽ - - ድንቄም ፡ ሙዚቃ ፡ ተጫውታለች ፡ የከተማ ፡ ጩኸት ! - - ወርዶፉ ፡ ወርዶፉ ! » ይጣራሉ ፡ ወደ ፡ ሰቀላው ፡ ቤት ፡ መለስ ፡ ይሉና ።—የወርዶፉ ፡ ከሥራ ፡ መግቢያ ፡ ጊዜ ፡ አለ ፡ መድረሱን ፡ ዘንግተው ታል ። ጴጥሮስ ፡ ብቅ ፡ ይላል « - - የጺ.ወኔን ፡ ክራር ፡ እባክህ ፡ አውርድ ላት » - - ቀና ፡ ብለው ፡ አላዩትም ። የልጃቸውን ፡ እጅ ፡ ያዝ ፡ አድር ገው ፡ ወደ ፡ እልፍኛቸው ፡ ይመለሳሉ ።

ጴጥሮስ ፡ አንድ ፡ አገር ፡ አቧራና ፡ ትቢያ ፡ የተሸከመ ፡ ስልቻ ፡ ያወጣና ፡ ለማራገፍ ፡ ይሞክራል ፡ እውጪ ። አቧራው ፡ ልብሱ ፡ ላይ ፡ እየ ተራገፈ ፡ ሲያበሳጨው ፡ ይታያል ። የስልቻውም ፡ ማሠሪያ ፡ ያስቸግረ ውና ፡ ታግሎ ፡ ታግሎ ፡ ሲፈታለት ፡ አንድ ፡ እንጨቱ ፡ የተጣመመ ፡ የሚ መስል ፡ ክራር ፡ ብቅ ፡ ይላል—ሮማን ፡ ትመጣና ፡ ትቀበለዋለች ። በራፌ ፡ ጨርቅ ፡ መሳይም ፡ እየጠራረገች ፡ ይዛ ፡ ወደ ፡ እልፍኙ ፡ ትገባለች ።

« ‘ የዮሴፍን ፡ ሞት ፡ ለዮሴፍ ፡ አረዱት ’ ይላሉ ፡ አባ ፤ ነገርን ፡ ወዲያ ፡ ወዲህ ፡ ሆኖ ፡ ሲያገኙት - - ጥሩ ፡ አባባል - - ! ጥሩ ፡ አባ ባል - - ! ያሰጋሽ ፡ ልጅ ፡ ለከተማ ፡ ሙዚቃ ፡ አፏን ፡ ከፈተች ! ! ጆሮ ፡ የማይሰማው ፡ ነገር ፡ የለ ።—ዐውቆ ፡ መናቅ ፡ ያስደፍራል ፡ ቢሉኝ ፡ አፌን ፡ ዳባ ፡ ዳባ ፡ ባለው - - » እውጪ ፡ የጀመራቸው ፡ ሁኔታ ፡ አልለ ቀቃቸውም ፡ ወይዘሮ ፡ አሰጋሽን ።

« ቅዱስ ፡ ያሬድኮ ፡ ጨርሶታል ፡ የሙዚቃን ፡ ነገር ፤ ከግዕዝ ፡ ከዕዝል ፡ ከአራራይ ፡ በላይ ፡ የሙዚቃ ፡ ውህደት ፡ ይኖራል ፡ ማለት ፡ ዘበት ፡ ነው ።—በግዕዝ ፡ ጀምሮና ፡ አነሣሥቶ ፡ በዕዝል ፡ ደርቦና ፡ ጨ ምሮ ፡ በአራራይ ፡ አሳዝኖ ፡ ልብን ፡ መስጦና ፡ አስደስቶ ፡ አርራቆ ፡ አሳ ምሮ ፡ ያቀረበ ፡ ከሱ ፡ ሌላ ፡ የለም - - ! » ይላሉ ፡ አባ ፡ አዲሴ ፡ ቀስ ፡ ብለው ፤ የውጪ ፡ ሁኔታቸውን ፡ ወይዘሮ ፡ አሰጋሽ ፡ እንዳጤኑባቸው ፡ በመገንዘብ ፍራት ፡ የተጫነው ፡ በሚመስል ፡ አንደበት ።—

« የርሶ ፡ ደሞ ፡ የያሬድና ፡ ሌጊዎን ፡ ታሪክ ፡ ተነግሮ ፡ አያልቅም - - አንድ ፡ ሰሞን ፡ ሙዚቃን ፡ የሚያስወድድ ፡ ሌጊዎን ፡ የሚባል ፡ የዝሙት ፡ ጋኔል ፡ ነው ፡ ይሉ ፡ ነበር ። አንድ ፡ ሰሞን ፡ ደሞ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ሰው ፡ የነበረው ፡ የበቃው ፡ የነቃው ፡ ቅዱስ ፡ ያሬድ ፡ ነው ፡ ሙዚቃን ፡ ያፈለ ቀው ፡ ሲሉኝ ፡ ነበር - - - ቅድም ፡ በከተማ ፡ ሙዚቃ ፡ እስከስ ፡ ሊሉ ፡

# ፲፰

## አደፍርስ

« - - - አኮሪዶዎ ፡ በጣም ፡ ደስ ፡ ይላል » ትለዋለች ፡ ሮማን ፡ ቀስ ፡ እያለች ፡ መጥታ ፡ ትጠጋና ። አደፍርስ ፡ እንደ ፡ መሳቅ ፡ ዓይነት ፡ የፊቱን ፡ ሥሮች ፡ ነቅነቅ ፡ ያደርግና ፡ ዝም ፡ ይላል « - - - እንደዚህ ፡ እንደርሶ ፡ የሚዘፍን ፡ ባገራችን ፡ የለም - - ድምፅዎ ፡ ደሞ ፡ በጣም ፡ ደስ ፡ ይላል ።—አኮሪዶ ፡ የሚሉት ፡ ነገር ፤ በጣም ፡ ነው ፡ ደስ ፡ የሚለው - -

« የወለደሽ ፡ አባትሽ ፡ ነው ፡ አቶ ፡ ወርዶፋ - - » ይጠይቃታል ፡ አደፍርስ ፡ ንግግሯን ፡ ያዳምጣትና ።

« አዎ ፡ የወለደኝ ፡ አባቴ ፡ ነው ፤ ግን ፡ እኔን ፡ አይመስልም - - ይመስላል - - - ?

« ገጥ ፡ ስትይ ፡ ከወደዚህ ፡ ከወደ ፡ ጉንጪሽ ፡ አጥንት ፡ በኩል ፡ ትመስያለሽ » ይመልስላታል ፡ አደፍርስ ።—የሮማን ፡ ፊት ፡ ይፍታታና ፡ ደስታ ፡ ይሞላበታል ። አባትሽን ፡ ትመስያለሽ ፡ ላላት ፡ ሁሉ ፡ የልቧን ፡ ያንጀቷን ፡ ማውራት ፡ ልማዷ ፡ ነው ።

« ጋሼ ፡ ወርዶፋ ፡ ጥሩ ፡ ሰው ፡ ነው ። ዋሽንት ፡ ደሞ ፡ ሲጫወት ፡ እባቡ ፡ ሁሉ ፡ ከየድንጋዩ ፡ ውስጥ ፡ እየወጣ ፡ ያዳምጠዋል ፡ ይላሉ ። እርሶን ፡ ወዶዎታል ፡ ጋሼ ፡ ወርዶፋ - - አኮሪዶውንም ፡ ወዶታል - - - » እያለች ፡ ትጀምራለች ።—

« እናትሽ ፡ የታገር ፡ ናቸው - - ? » ይጠይቃታል ፡ አደፍርስ ፡ ነገሯን ፡ ያቋርጥና ።

« ሞታለች ፡ እናቴ - - ! አንዳንዴ ፡ ደስ ፡ ያለው ፡ ቀን ፡ እናትሽን ፡ ትመስያለሽ ፡ ይልና ፡ እቅፍ ፡ ያደርገኛል ፡ ጋሼ ፡ ወርዶፋ - - ሶዶ ፡ ነው ፡ የተወለደችው ፤ አባቷ ፡ አማራ ፡ እናቷ ፡ የስልጢ ፡ ጉራጌ ፡ ናቸው ፡ ይባላል ። ቆንጆ ፡ ነበረች ፡ ይላሉ ፡ ደሞ - - እንደናቴ ፡ ቆንጆ ፡ ነኝ ፡ አዶለሁ - - - ?

« አዎ ፡ ቆንጆ ፡ ነሽ — የጠይም ፡ ቆንጆ - - - » ይመልስላታል ፡ አደፍርስ ።

« - - ባልጠቁር ፡ ኖሮ ፡ ይሻል ፡ ነበር - - -

« ጠይም ፡ ዓሣ ፡ መሳይ ፡ ሲባል ፡ አልሰማሽም - - ?

« ገና ፡ ዛሬ ፡ ነው ፡ ሰው ፡ ቆንጆ ፡ ነሽ ፡ ሲለኝ ፡ የሰማሁት - - ጐርፉ ፡ እንኳ ፡ ልቡ ፡ እየወደደኝ ፡ ቅልጥልጥ ፡ ነው ፡ የሚለኝ - - ቆንጆ ፡ አይለኝም - - ሹርባ ፡ ልሠራ ? ሹርባ ፡ ስትሠሪ ፡ ደስ ፡ ትያለሽ ፡ ይለ ኛል ፡ ጋሼ ፡ ወርዶፋ - -

« ባትሠሪም ፡ እንደዚሁ ፡ እንዳለሽ ፡ ደስ ፡ ትያለሽ - - -

« ከጺወኔ ፡ ጋር ፡ ሲላፉ ፡ ሲጫወት ፡ ከኔ ፡ ጋር ፡ አይላፋም - - የጐርፉ ፡ ነገር ፡ እንዳንዴስ ፡ ይነደኛል ! አንችን ፡ አይሰድብሽም ፡ ትለ ኛለች ፡ ጺወኔ ፡ እንኳን - - እሷን ፡ ይሰድባታል ፡ ሲናደድ ! እኔን ፡ ግን ፡ አይሰድበኝም - -

« ምነው ፡ ቅልጥልጥስ - - ?

« አይ ፡ ቅልጥልጥ ፡ የቤቱ ፡ ሰው ፡ ያወጣልኝ ፡ ነው - - የሱ ፡ አይ ለም — ቅልጥልጥ ፡ ደሞ ፡ ያንጀት ፡ ስድብ ፡ አይለም ። የቀልድ ፡ ስድብ ፡ ነው - - ሰው ፡ ሲናደድ ፡ የሚሳደበው ፡ አይለም ።— አሁን ፡ እርሶ ፡ ቅልጥልጥ ! ቢሉኝ ፡ ያስቀኛል ፤ አያናድደኝም ።

« እግርሽ ፡ ተረከዝሽ ፡ ደሞ ፡ ቆንጆዎች ፡ ናቸው - - -

« መልክሽ ፡ ዓይንና ፡ ጥርስሽ ፡ ነው ፡ ነው ፡ የሚሉኝ - - እግሬ ፡ ደስ ፡ ይላል ? የቤቱን ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ሲያስቸግሩት ፡ እኔን ፡ ምንም ፡ አያረ ጉኝ ፡ ሙያሌዎች — ጺወኔን ፡ እንኳን ፡ ይይዟታል ። እኔን ፡ ግን ፡ ጨርሶ ፡ አይዙኝም ፤ አመድ ፡ ውስጥ ፡ እንኳን ፡ ብወትፈው ፡ እግሬን - - እጅ ፡ ጣታቸው ፡ ላይ ፡ ሁሉ ፡ ነው ፡ የሚወጡት ፡ እሌሎቹ ፡ ሰዎች ፡ ላይ - - -

« - - እንግዲህ ፡ የምታገቢበት ፡ ቀን ፡ ደረሰ ፡ አይደለም ፡ እን ዴ - - ? እርግጠኛ ፡ ነኝ ፡ ቀሚስሽን ፡ አሠርተሻል - - አገልግልና ፡ ሌማት ፡ ሰፍተሻል - - -

« በትሬንታ ፡ ተሳፍሬ ፡ ነው ፡ የምጠፋው - - -

« ለማግባት ፡ አትፈልጊም — ለምን ፡ ትጠፊያለሽ - - ? እንዴት ፡ ነው — የሚያገባሽን ፡ ሰው ፡ አትወጂውም - - - ?

« እንኳን ፡ ልወደው ፡ ዓይኑንም ፡ አይቼው ፡ አላውቅ - - -

« ሞትና ፡ ሕይወት - - ! ታዲያ ፡ በትሬንታ ፡ ወዴት ፡ ትሄጃለሽ - - ?

« የትም — የትም — እዚህ ፡ እባላገር ፡ ማደሮ ፡ ከመያዝ — የትም ፡ ብሞት ፡ ይሻለኛል - - -

« እስከዚህ ፡ የባላገር ፡ ማደሮ ፡ አንገፍግፎሻል ፡ ማለት ፡ ነው - - ?

« አሥመራ ፡ ነው ፡ የምሄደው ፡ በትሬንታ - - -

« አሥመራ - - ?

« አዎ ፡ አሥመራ - - -

« ቀረብ ፡ የሚለው ፡ ይልቅ ፡ አይሻልሽም - - ? አዲስ ፡ አበባ - - -

« ድራሽ ፡ አባቴ ፡ እንዲገኝ ፡ አልፈልግም - - እርቄ - - እ . . . ር . . . ቄ ፡ ለመጥፋት ፡ ነው ፡ የምፈልገው ?

« አባትሽ ፡ አያዝንብሽም ፡ ድንገት ፡ ስትጠፊ - - -

« አያዝንብኝም - - እሱም ፡ መሄጃ ፡ እጦት ፡ ነው ፡ እዚህ ፡ የተቀመጠው - - የባላገር ፡ ማደሮ ፡ አንገፍግፎታል - - -

« አዲስ ፡ አበባ ፡ ቢሆን ፡ እኔም ፡ ባቅሜ ፡ ልረዳሽ ፡ እሞክር ፡ ነበር ፤ እምልሽ — እፈረንጅ ፡ ቤት ፡ እንድትሠሪ — ልጅ ፡ አሳዳጊነት ፡ ወይም ፡ ግህን ፡ አጣቢነት ፡ እንድትቀጠሪ - - -

« የፈረንጅ ፡ አፍ ፡ አልችልሚ - - አዲሳባ ፡ መሄዱ ፡ ምን ፡ ከፍቶኝ ።— ብቻ ፡ ጥሊያንኛ ፡ አልችልም - - አይ ፡ እርሶማ ፡ ቢረዱኝ ! ሥራ ፡ ቢዶሉኝ ፡ ያሉኝን - - ያሉኝን - - ያዘዙኝን ፡ ነው ፡ የምሠራው - - ያሉኝ ! ለምን ፡ እሳት ፡ ውስጥ ፡ አልገባም - -

ጺወኔ ፡ ብቅ ፡ ትላለች ፡ በወርዶፉ ፡ ጐጆ ፡ አጠገብ ፡ ሽምጥ ፡ ላይ « ያሉኝን ፡ ያሉኝን ፡ ያዘዙኝን ፡ ሁሉ ፡ እሠራለሁ - - » ስትል ፡ ትሰማለች ፡ ፍሬዋን ።

« - - እሱ ፡ ነው ፡ ትልቁ ፡ ነገር - - » ይመልስላታል ፡ አደፍርስ ፡ ማዶ ፡ ማዶውን ፡ እየተመለከተ ።— ጺወኔ ፡ ነቅታ ፡ ታዳምጣለች ።

« ይኸን ፡ ሥራ ፡ እሺ - - ! ይኸን ፡ ሥራ ፡ እሺ - - ! ካልኩኝ ፡ ምነው ፡ ዘበናይ ፡ ሥራስ ፡ ቢሆን ፡ ለምን ፡ ያቅተኛል - - ?

« ትልቁ ፡ ነገር ፡ እሺታ ፡ ነው - - ትልቁ ፡ ነገር - - -

« እንዲያው ፡ ያሉኝን ፡ አልኩዎት - - ያሉኝን - - -

« ግዴለም ፡ እንግዲያው - - እንረዳዳለን - - » አደፍርስ ፡ ከነበረበት ፡ ካጥር ፡ ውጭው ፡ አፋፍ ፡ ላይ ፡ ብድግ ፡ ይልና ፡ ወደ ፡ ውሃው ፡ መቅጃ ፡ ኩሬ ፡ ያመራል ። ጺወኔ ፡ ወደ ፡ ወርዶፉ ፡ ጐጆ ፡ ትመለሳለች ። — ሮማን ፡ ቢሆን ፡ ብዙ ፡ ትቆያለች ፡ እንደ ፡ ተቀመጠች ፡—

- - - ነጭ ፡ ቀሚስ ፡ እለብሳለሁ - - በዚያ ፡ ላይ ፡ ካባ ፡ እደርባለሁ - - ሚዜዎቹ ፡ እኔ ፡ ልዘል ፡ እኔ ፡ ልዘል ፡ እያሉ ፡ ይጣላሉ - - ከዚያ - - ምን ድነው ፡ ነገሩ - - የለም ፡ የለም - - ቆይ - - መጀመሪያ ፡ እኔን ፡ ለማ የት ፡ ይፈልጋል - - እንዲያው ፡ ላይኑ ፡ ያህል - - እደበቅበታለሁ ፡ እኔ ፡ ደሞ - - ውሃ ፡ መቅጃ ፡ እንኳን ፡ አልሄድም - - ከዚያ ፡ ምንድነው ፡ ነገሩ - - ለጓደኛዬ ፡ ጉቦ ፡ ይሰጥና - - ጫማዋን ፡ ይስምና - - አንድ ፡ ምክኛት ፡ ፈጥራ ፡ እንድትጠራኝ ፡ ያደርጋል - - ሞኝት ፡ ተላሊት ፡ ምንድነው ፡ ነገሩ - - አገር ፡ ጤና ፡ ነው ፡ ብያለሁ ፡ በኔ ፡ ቤት - - ፈሰስ ፡ ፈሰስ ፡ ስል - - አንድ ፡ ሪቅ ፡ ሥር ፡ ተደብቆ ፡ አየዋለሁ - - ሪቅ ! ሪቅ ! - - አዲሳባ ፡ ሪቅ ፡ የለም ! የብረት ፡ በርሚል ፡ ነው ፡ ብለዋል ፡ የእህል ፡ ማስቀመጫቸው - - ያላየሁት ፡ መስሎት ፡ ታዲያ ፡ እንገቱን ፡ ብ - - ቅ ፡ ሲያ ረግ ፡ ከበርሚሉ ፡ ሥር - - ምንድነው ፡ ነገሩ - - እንደ ፡ መሮሀ ፡ ብዬ ፡ እደ ነግጥና ፡ ወደ ፡ ቤት ፡ እበራለሁ - - ምኑ ፡ ቅጡ - - አኮርፋታለሁ ፡ ከዚያ ፡ በኋላ ፡ ጺወኔንም ፡ አላነጋግራትም - - አኮርፋታለሁ - - ! አባ ፡ አዲሴ ፡ አማላጅ ፡ ሆነው ፡ ይመጣሉ ፤ ይለምኑኛል - - በቅዱስ ፡ ሚካኤል ፡ ይገ ሻለሁ - - ሊቀ ፡ መልአኩን ፡ ይገ ፡ ነው ፡ ላስቸግርሽ ፡ የመጣሁት - - በሊቀ ፡ መልአኩ - - ይሉኛል - - ዳሩ ፡ ጺወኔስ ፡ አባ ፡ አዲሴስ ፡ የት ፡ ይመጣሉ ፡ አዲሳባ - - ? የለም ፡ የለም ፡ ሌላ ፡ በጣም ፡ ትልቅ ፡ ቄስ ፡ ነው ፡ የሚሆኑት - - ጥምጥማቸው ፡ ብቻ ፡ እንደ ፡ ሐምሌ ፡ ዳመና ፡ ሰማይ ፡ የደረሰ ፡ መስቀላቸው ፡ የወርቅ ፡ ካባቸው ፡ እንደ ፡ ወርቅ ፡ የሚያበራ - - - ይቅርታ ፡ አድርጌላታለሁ ፡ እላቸዋለሁ - - የኔ ፡ ልጅ ! ብለው ፡ በካባ ቸው ፡ እቅፍ ፡ ያደርጉኛል - - የወርቅ ፡ መስቀሉን ፡ ያሳልሙኛል - - ምንድነው ፡ ነገሩ - - -

« - - እንረዳዳለን - - ? እንረዳዳለን - - ? » ትደጋግማለች ፡ የሰማችውን ፡ ቃል ፡ ጺወኔ « - - ያሉኝን ! ያሉኝን - - ! ያሉኝን - - » አጠገቧ ፡ የሚነገሩ ፡ ዓይነት ፡ ይሰሚታል ።—ሮማንን ፡ ትወዳታለች ።— አደፍርስን ፡ ግን ፡ ትወደው ፡ አትወደው ፡ ገና ፡ አላወቀችውም ። ቢሆ ንም ፡ የሰማቻቸው ፡ ቃሎች ፡ አገንግነዋታል ። በሮማንም ፡ ጌታዋ ፡

ከሚሆን ፡ አንቱ ፡ ከምትለው ፡ ሰው ፡ ጋር ፡ እንደዚያ ፡ ተዝናንታ ፡ በመጫወቷ ፡ ትንሽ ፡ ተናዳለች ። ሊከፋባትም ፡ ጀማምሯል ፡ ልቧ ።—የሥራ ፡ ከመፍታት ፡ ሥራ ፡ የሙዳይ ፡ ልጅ ፡ ይዛ ፡ ትጠቋቁማለች ።— አልፎ ፡ አልፎ ፡ ወስፌው ፡ እጅዋን ፡ እየጠቆማት ፡ በስጨትጨት ፡ ስትል ፡ ይታያል ።—

« - - ዳሱ ፡ በሰፊው ፡ ይጣላል - - ገበታው ፡ ይዘረጋል - - ጠላው ፡ በጋን ፡ በጋን ፡ እየሆነ—መቀነት ፡ እየታሠረ ፡ ይደረደራል ።— እንጀራው — ነጩ ፡ ጤፍ ፡ ባንድ ፡ ፊት ፡ ጥቁሩ ፡ ጤፍ ፡ ባንድ ፡ ፊት ፡ ቅይጡ፡ ባንድ ፡ ፊት ፡ ይቆለላል - - ጮማው ፡ ሥጋ ፡ በየባላባልቾው ፡ ላይ ፡ ተሰቅሏል ።— ቢላዋው ፡ ተስሎ ፡ ተስሎ ፡ ተደርድሯል - - » ትቀጥላለች ፡ ሮማን « - - ምንድነው ፡ ነገሩ - - የኔ ፡ ዘመድ ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ ያዝለኛል ፡ - - ካሥር ፡ በላይ ፡ ሰው ፡ የበራ ፡ ጢፍ ፡ ይይዛል ።—መዐት ፡ ሴቶች ፡ እየዘፈኑ ፡ እያጨበጨቡ ፡ ይከተሉኛል - - ምንድነው ፡ ነገሩ - - ከዚያ ፡ በኋላ - - ከዚያ ፡ በኋላ - - እቤተ ፡ ዘመዶቼ ፡ አጠገብ ፡ እበርጩማ ፡ ላይ ፡ አውርዶ ፡ ቁች ፡ ያደርገኛል - - ከዚያ ፡ በኋላ ፡ ሽማግሌ ፡ ሽማግሌዎቼ ፡ እጃቸውን ፡ ራሴ ፡ ላይ ፡ እያደረጉ ፡ ይመርቁኛል - - ይመርቁኛል - - በየተራ ።—ምንድነው ፡ ነገሩ—ከዚያ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ዳሱ ፡ ይወስዱኛል ።— እዚያ - - እዚያ ፡ ደሞ - - የሚያገባኝ ፡ ሰውዬ ፡ እመየቴ ፡ ይቀመጡበት ፡ እመሰለ ፡ አበባ ፡ ምንጣፍ ፡ ላይ ፡ ተቀምጧል - - መከዳም ፡ የመየቴን ፡ ዓይነት ፡ እጎኑ ፡ ተደርጎለታል - - አፍንጫውንና ፡ አፉን ፡ በቀጭን ፡ ኩታው ፡ ሸፍኖ ፡ በኮራና ፡ ባማረ ፡ ሁኔታ ፡ ቁች ፡ ብሎ ፡ ይጠብቃል ። ከዚያም ፡ እበርጩማ ፡ ላይ ፡ እነገር ፡ አባት ፡ ሽማግሌዎች ፡ አጠገብ ፡ ከባሌም ፡ ሳልርቅ ፡ ቁች ፡ እላለሁ ።— ምንድነው ፡ ነገሩ - - ታገባታለሆይ ፡ ብለው ፡ ይጠይቁታል - - አዎን ፡ አገባታለሁ ፡ ብሎ ፡ ይመልሳል ።— ከዚያ ፡ በኋላ ፡ እንደ ፡ ተሸፈንሁ ፡ እጄን ፡ ያሾልክና ፡ ትንሽ ፡ ጣቱን ፡ ከትንሽ ፡ ጣቴ ፡ ሊያያይዝ ፡ ይሞክራል - - እሺ ፡ አልልም ፡ እኔ ፡ ግን - - በኋላ ፡ በመከራ ፡ ጣቶቻችንን ፡ እናቋልፋለን - - ከዚያ ፡ ምንድነው ፡ የጥሎሹ ፡ ነገር — ይወርዳል — ይወርዳል — አልቦው — ወለባው — ድሪው - - አምባሩ - - ጉትቻው - - -

« - - - እርግጠኛ ፡ ነኝ ፡ አብሬ ፡ ልሂድ ፡ አይደለም ፡ የምትለው ምን ፡ ቢቆርጣት - - ? ከጠፉን ፡ ከጠፉን ፡ ደሞ ፡ አብረን ፡ እንጠፋለን ፡ ብያታለሁ - - » ትላለች ፡ ብቻዋን ፡ ጺወኔ ፡ ሙዳይዋን ፡ እየጠቋቆመች ።

- - አሥር ፡ ፈረሰኛ ፡ ይከተለናል - - ከኔ ፡ ጋር ፡ አንዱ ፡ ፈረስ ፡ ላይ ፡ እኋላው ፡ አንድ ፡ ሚዜ ፡ ይቀመጣል - - ምኑ ፡ ቅጡ ፡ ከዚያማ ፡ በኋላ - - እባሌ ፡ ቤት ፡ ደሞ ፡ ድግሱ ፡ ይቀልጣል - - እዬ ፡ ጣጣዬ - - መምሸት ፡ አይቀርም ፡ መቼም - - ጉዴ ፡ ይፈላል - - ጉዴ ፡ ይፈላል — እነባዋለሁ - - እለቅሰዋለሁ - - መምሸት ፡ አይቀር - - መምሸት ፡ አይቀር - - -

አደፍርስ ፡ ከኩሬው ፡ ገደማ ፡ ቀስ ፡ እያለ ፡ ይመጣል - - የሮማንን ፡ በሐሳብ ፡ መውዋጥ ፡ ያይና - - እያሰላ ፡ ከኋላዋ ፡ ቀርቦ ፡ በጣቱ ፡ ወጋ ፡ ያደርጋታል - - 'ዋይ!' ብላ ፡ እገሩን ፡ አናግታው ፡ ብድግ ፡ ትላለች ። ጺወኔ ከወርዶፋ ፡ ጐጆ ፡ ትወጣለች ፡ ድንግጥ ፡ ብላ ። ክብረት ፡ ማሚቴና ፡ ወይዘሮ ፡ አሰጋሽ ፡ እየተንጋጉ ፡ ይወጣሉ ።

« - - የተመሰጠ ፡ እንጉርጉሮ - - ! የፍቅር ፡ መለከት - - ! ጐሕ ፡ ቅደትና ፡ ጥልቀት - - ቅኔያዊ ፡ ንጋት - - ይህ ፡ ነው ፡ ደንበኛ ፡ የፍጥረት ፡ ድምፅ - - የሕይወት - - የኑሮ - - አለሁ ፡ የማለት ፡ ቋንቋ - - ይህ ፡ ነው ፡ ራስ ፡ ከራስ ፡ ግንኙነት - - ይህ ፡ ነው ፡ ይህ ፡ ነው እውነተኛው ፡ ድምፅ - - » እያለ ፡ ይወራጫል ፡ አደፍርስ ። —ሮማን ፡ የድንጋጤ ፡ ዓይኖቿ ፡ እንዳጐረጡ - - የኋሊት ፡ የኋሊት ፡ እያለች ፡ እሽ ምጡ ፡ ጥጋት ፡ ስትደርስ ፡ መለስ ፡ ብላ ፡ ወደ ፡ ግቢ ፡ ትሮጣለች ። የነ ወይዘሮ ፡ አሰጋሽንም ፡ ሆነ ፡ የነክብረትን ፡ ከውስጥ ፡ በኩል ፡ አጥሩ ፡ አጠገብ ፡ መቆም ፡ አልተመለከተችም ።—

« ራሱን ፡ አመም ፡ ያደርገዋል ? » ብለው ፡ ይጠይቃሉ ፡ ወይዘሮ ፡ አሰጋሽ ፡ ክብረትን « - - እንደ ፡ ድንገተኛኮ ፡ ብናደርግለት - - ?

« አደፍርስ - - አደፍርስ ! » እያለ ፡ የሚሆነውን ፡ ሁኔታ ፡ ሰው ፡ እንደሚመለከተው ፡ በሚነግር ፡ አንደበት ፡ ይጠራዋል ።—

« - - - ሰምተህልኛል ፡ ያን ፡ ድምፅ ! ሰምተህልኛል - - ! ሰምተህልኛል - - ! ሰውነትህን ፡ ሰንጥሮ ፡ የሚገባ ፡ ነገር ፡ ነበርኮ - - እውነተኛ ፡ የሕይወት ፡ ድምፅ - - አማርኛ ፡ እንግሊዝኛ ! ቋንቋ ፡ ይባልልኛል ፡ ደርሶ - - ይገርምሃልኮ ፡ ጋሼ ፡ ክብረት - - ድንገትኮ ፡ ነው - - ፈዘዝ ፡ ማለቷን ፡ እየሁና - - ድንገትኮ ፡ ነው ፡ ከኋላዋ - - ኋጐጥ ፡ ያደረግኋት - - ? ምን ፡ ዓይነት ፡ ሙዚቃ ፡ እንዲያ ፡ ሊሆን ፡ ይችላል - - ? እንዴት ፡ ያለ ፡ ኀይልስ ፡ እንዲያ ፡ ዓይነት ፡ ኃይል ፡ ይሆ

ናል - - ? ምን ፣ ዓይነትስ ፣ ፍጥነት - - ! እንደ ፣ ጥይት - - እንደ ፣ ጥይት ፣ ነውኮ ፣ የተተኮሰችው ፣ ከመሬት - - - »

« - - ግዴለህም ፣ ትንሽ ፣ ድንገተኛ ፣ ምንም ፣ አይለው - - » እያሉ ፣ ካጥር ፣ ውጪ ፣ ይወጣሉ ፣ ወይዘሮ ፣ አሰጋሽ ።—

« - - ይገርምሃልኮ - - ! ይገርምሃል - - ይገርምሃል - - ይገርሃምል - - -

« - - - ከምኑም ፣ ከምኑም ፣ ይከላከላል - - » ቀጥለዋል ፣ ወይዘሮ ፣ አሰጋሽ ፣ ብቻቸውን « - - ከተልከስካሹም - - ካይኑ ፣ ጥላውም - - ከድንገተኛውም - - » ቅጠሉን ፣ እየቀጣጠፉ « - - ማድረጉ ፣ አይከፋም - - ባይበዛም ፣ በትንሹ ፣ ቁር ፣ እናደርግለታለን ፣ ባፍንጫው - - ከሚታኘከውም ፣ ከሥራ ፣ ሥሩ ፣ እኘክ ፣ እኘክ ፣ እንዲያደርግበት - -

## ፲፱

# አደፍርስ

ሞቅ ፡ ሲል ፡ ነው ፡ ጧቱ ፣ ጺወኔ ፡ እወርዶፋ ፡ ጐጆ ፡ አጠገብ ፡ ተቀምጣ ፡ ያንኑ ፡ ሙዳይዋን ፡ ስትሰፋ ፣ አደፍርስን ፡ ውልብ ፡ ብሎ ፡ ሲያልፍ ፡ ታየዋለች—

« የት ፡ ነው ፡ እንደዚህ ፡ ማልደህ፡የምትሄደው ? » ትጠይቀዋለች ።

« አ ፣ አልነገርኩሽም ፣ ትንሽ ' ኤክሰርሳይስ ' አስፈልጐኝ ፡ ነው ፤ እምልሽ ፡ ሰውነቴን ፡ ማዝናናት » ይመልስላታል ፡ አደፍርስ ።

« ታዲያ ፡ ፍሎቤሩ ፡ ምን ፡ ያደርግልሃል - - - ?

« ትምህርት ፡ ያላሻሻለው ፡ ያውሬነት ፡ ተፈጥሮዬ ፡ የቱን ፡ ያህል ፡ እውስጤ ፡ እንደቀረ ፡ ልለካበት - - -

« ትምህርት ፡ ያላሻሻለው ፡ ያውሬነት ፡ ተፈጥሮ ፡ አላውቅም - -

« በተፈጥሮ ፡ አንችም ፡ እኔም ፡ አውሬዎች ፡ ነን ፤ አንችም ፡ እኔም ደም ፡ ለማፍሰስ ፣ ወይም ፡ ደም ፣ ሲፈስ ፡ ለማየት ፡ እንፈልጋለን - - -

« እኔ ፡ አንደኛ ፡ አውሬ ፡ አይደለሁም—ሁለተኛም ፡ ደም ፡ ለማፍ ሰስም ፡ ሆነ ፡ ሲፈስ ፡ ለማየት ፡ አልሻም — የዶሮ ፡ እንኳ ፡ ቢሆን - -

« በእርእያ ፣ ሥላሴ ፡ የተፈጠርሽ ፡ ነሽ ፡ አንቺ !

« አንተም ፡ ነህ - - -

« ሞትና ፡ ሕይወት ፡ ብሎ ፡ ነገር - - - ! ስሚ — የዱሮ ፡ አባቶቻ ችን ፡ አደን ፡ የሚያድኑት ፣ ወንድነታቸውን ፡ ለማሳየት ፣ ወይም ፡ ምግብ፡ ለማግኘት ፡ ነበር ። — አንድ ፡ አጐት ፡ ነበሩኝ ፡ እስከ ፡ ገሙ ፡ ጐፋ ፡ ድረስ፡ዝሆን ፡ ለማደን ፡ ብቻ ፡ ሄጄ ፡ ነበር ፡ እያሉ ፡ የሚያጫውቱኝ - - -

« አንተስ ፡ ለምንድነው ፡ የምታድነው ? ምግብ ፡ ፍለጋ ፡ አይመስ ለኝም - - ደግሞም ፡ እንኳን ፡ የአቶ ፡ ጥሶ ፡ የእኅት ፡ ልጅና ፡ የሌላም ፡ ልጅ ፡ ቢሆን ፡ ወንድነቱን ፡ ለማሳየት ፡ አደን ፡ መሄድ ፡ ያለበት ፡ አይ መስለኝም - - በዚያ ፡ ላይ ፡ የተማርህ - - -

« ለደስታ ፡ ነው ፡ ጂወኔ ፡ ለደስታ ! እኔ ፡ አደን ፡ የምሄደው ።— ራሴን ፡ ለማወቅ ፡ ውስጣዊ ፡ ሰውነቴን ፡ ለመመርመር ፡ ልቡስ ፡ ጥላዬን ፡ ለማግኘት ፡ ያውሬነት ፡ ቅሪቴ ፡ ወደ ፡ አናት ፡ እንዲወጣ - - እንዲሠፍ - - -

« አይገባኝም - - -

« ሊገባሽ ፡ አይችልም ፡ ሰው ፡ ስለነገረሽ ፡ ብቻ - - -

« አንተ ፡ ሰው ፡ ነህ ? ! » ትለዋለች ፡ ጂወኔ ፡ ለሱ ፡ ያላትን ፡ አክብሮትና ፡ ውዴታ ፡ በሚገልጽ ፡ አንደበት ።

« - - ራስሽ ፡ መርምረሽ ፡ ልትደርሽበት ፡ ያሻል ፡ ይሆናል ፡ አይሆንም ፡ ያዋጣል ፡ አያዋጣም ፡ ብለሽ - - ራስሽ ፡ ተኩሰሽ ፡ ራስሽ ፡ አድነሽ - -

« በል ፡ ብቻ ፡ ጊዜህን ፡ አልውሰድብህ - - - !

« - - አንድ ፡ ሊገለጽ ፡ የማይችል ፡ ልዩ ፡ ዓይነት ፡ ደስታ ፡ ነው ፡ የሚሰጠው — ጅግራ ፡ ቆቅ ፡ ሶረኔ ፡ ወይም ፡ ሰስ ፡ ሚዳቋ ፡ ድኩላ ፡ ተኩሰሽ ፡ ስትመቺ - - ይኸ ፡ ነው ፡ የማይባል ፡ ደስታ ፡ ነው ፡ የሚሰጥሽ - - ጭብጥ ፡ ኩርምት ፡ ሲሉ ፡ ማየት — ብድግ ፡ ታደርጊያቸውና ፡ ደሙን ፡ በጣትሽ ፡ ነካ ፡ አድርገሽ ፡ ያነጣጠርሽበትን ፡ ብልት ፡ ያልሳትሽ ፡ መሆኑን ፡ ስታውቂው—ይኸ ፡ ነው ፡ የማይባል ፡ ደስታ ፡ ነው ፡ የሚሰማሽ — ደምሽን ፡ ናድ ፡ ናድ ፡ የሚያደርግ ፡ ዓይንሽን ፡ የሚያበራ - - -

« አይገባኝም ፡ በእንስሳት ፡ ሥቃይ ፡ እኔ ፡ አልደሰትም - - አንተም ፡ ብትሆን ፡ ላፍህ ፡ አልከው ፡ እንጂ ፡ እነሱ ፡ ሲሠቃዩ ፡ አንተ ፡ የምትደሰት ፡ አይመስለኝም - - ይኸው ፡ እንግዲህ ፡ ከሳምንት ፡ በላይ ፡ እንዳወቅሁህ ፡ ከሆነ ፡ የዚህን ፡ ዓይነት ፡ አንጀት ፡ ያለህ ፡ አይመስለኝም - -

« ምን ፡ ይመስልሻል ፡ ምክንያቱ ፡ እንደዚህ ፡ ይኸን ፡ ሁሉ ፡ የሚያስለፈልፈኝ ? ግዴለሽነቴ ፡ ይመስለኛል ።— ከተማም ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ሳልገባቸው ፡ እየቀረሁ ፡ ራሱን ፡ ወዳድ ፡ የሚል ፡ ስም ፡ ሰጥተውኛል ።— እግዚአብሔር ፡ ያሳይሽ ፡ እንግዲህ — ለምሳሌ ‘ ፓርቲ ’ ወይም ፡ ሌላ ፡ ዓይነት ፡ ግብዣ ፡ ትጠሪያለሽ ፡ ስንት ፡ ጕበዛዝት ፡ ተሰብስበዋል ፡ ማለት ፡ ነው - - እሺ ፡ ሁሉም ፡ ካንቺ ፡ ጋር ፡ ለመደነስ ፡ ይፈልጋሉ ።—አንዱ ፡ ደግሞ ፡ በተለይ ፡ ከሁሉም ፡ የበለጠ ፡ ካንቺ ፡ ጋር ፡ ለመደነስ ፡ ይፈልጋል - - ለምሳሌ ፡ ያህል ፡ ነው ፡ ልንገርሽ — እንዳንቺ ፡ ዓይነት ፡ ደስ ፡ የሚል ፡ ነገር ፡ ከተማ ፡ ብዙ ፡ አይገኝም —ለምሳሌ ! እሺ ! አንድ ፡

እንደ ፡ እኔ ፡ ዓይነት ፡ ራሱን ፡ ወዳድ ፡ በተለይ ፡ ለብቻው ፡ ሊይዝሽ ፡ ይፈልጋል — ምን ፡ ታደርጊያለሽ ? ቢያንስ ፡ ቢያንስ ፡ ከሁሉም ፡ ጋር ፡ አንዳንዴ ፡ መደነስ ፡ ይኖርብሻል ፤ እንዲቀየሙሽ ፡ አያስፈልግም ።—ካንዱ ፡ ጋር ፡ ብቻ ፡ ተጣብቀሽ ፡ የቀረሽ ፡ እንደሁ ፡ ይጠምዱሻል ፡ ሌሎቹ - - -

« ምን ፡ ቸገረኝ ፡ ታዲያ ፡ ልቡሰ ፡ ጥላችን ፡ ተገጠመ - - -

« እሱ ፡ እውነትሽን ፡ ነው ፤ ግን ፡ ራሱን ፡ ወዳድ ፡ እንደሚያስብ ለኝ ፡ አይጠረጠርም - - በቀደምለት ፡ ለምሳሌ ፡ የትምህርት ፡ ቤት ፡ መሥሪያ ፡ ገንዘብ ፡ ለመሰብሰብ ፡ አባ ፡ ዮሐንስ ፡ ንግግር ፡ አድርገው ፡ ነበር ። — የተናገሩት ፡ ንግግር ፡ አብዛኛው ፡ ፍሬ ፡ ቢስ ፡ ስለመሰለኝ ፡ ተከራከርኳቸው - - መጀመሪያ ፡ ለብቻቸው ፡ በኋላ ፡ ምስክር ፡ ፊት ።— እርግጠኛ ፡ ነኝ ፡ አሸንፌያቸዋለሁ ፡ በክርክሩ - - ‘ የዛሬ ፡ ልጆች ፡ እውኝ ፡ እውኝ ፡ ደብቁኝ ፡ ደብቁኝ ፡ ለማለት ፡ ነው ፡ ኋላ ! ’ ከማለት ፡ በስተቀር ፡ አንድም ፡ የመለሱት ፡ አጥጋቢ ፡ መልስ ፡ አልነበረም ።— እና ፡ ታዲያ ፡ ላባም ፡ ለሌሎችም ፡ ምናልባት ፡ ራሴን ፡ ወዳድ ፡ መስያ ቸው ፡ ይሆናል - - ግን ፡ እውነት ፡ እውነት ፡ ነው ፡ የምልሽ ፡ ራሴን ፡ ወዳድ ፡ አይደለሁም ። ያሳዝነኛል ፡ በጣም ፡ ላንችም ፡ እንዲያ ፡ መስዬ ፡ ታይቼሽ ፡ እንደሆን ! ስለ ፡ እኔ ፡ ምን ፡ እንደምታስቢ ፡ እግዜር ፡ ይወቅ ፤ አላውቅም — ምናልባት ፡ ማን ፡ ያውቃል ? ሳላውቅ ፡ አስቀይሜሽ ፡ ይሆናል - - እና ፡ ቢሆንም ፡ አንቺ ፡ አስቀይሜሽም ፡ እንደሁ ፡ እውነቱን ፡ እንደምትነግሪኝ ፡ እተማመናለሁ - - ራሴን ፡ ወዳድ ፡ እመስልሻለሁ - - - ?

« እኔ ፡ ስለ ፡ እሱ ፡ ብዙ ፡ ነገር ፡ አላውቅም ፤ ግን ፡ ስላስተማርከኝ ፡ ትምህርትና ፡ ስለ ፡ ሰጠኸኝ ፡ ነገሮች ፡ አመሰግንሃለሁ - - -

« አ ! ስለ ፡ ብዕሩና ፡ ስለ ፡ መጽሐፉ ፡ ማለትሽ ፡ ነው ? ይገባኛል ። ተስፋ ፡ አለኝ ፡ እንዳላስለቀቸሁሽ - - እርግጠኛ ፡ ነኝ ፡ ክፉ ፡ ሰው ፡ እን ደማልመስልሽ ። ቀልድ ፡ ጨዋታ ፡ የማላዘወትር ፡ የተሰማኝን ፡ ሐሳብ ፡ ያስቀይማል ፡ አያስቀይምም ፡ ብዬ ፡ ሳላስብ ፡ ቀጥታ ፡ መግለጽ ፡ የምወድ - -

« - - ብዙ ፡ ሐሳብ ፡ ያለህ ፡ ልብህ ፡ አንድ ፡ ቦታ ፡ ያላረፈ ፡ ተዟ ዟሪ ፡ ዓይነት ፡ ሰው ፡ ነው ፡ የምትመስለኝ ፡ እኔ ፡ እንደማስብህ - - -

« እንዳስመለከተሽ ፡ አስቢኝ - - ራሱን ፡ ወዳድም ፡ እንኳ ፡ በይኝ ፤ ብቻ - - » ትንሽ ፡ ኮስተር ፡ ብሎ « ብቻ ፡ አደራሽን - - የጊዜው ፡ ሰው ፡ አትበይኝ - - ያለም ፡ ሰው ፡ አትበይኝ - - የለም ! የጊዜው ፡ ሰው ፡ አትበይኝ - - ያለም ፡ ሰው ፡ አትበይኝ - - የለም ! የጊዜው ፡ ሰው ፡

ያለም ፡ ሰው ፡ አትበይኝ - - - ያ ፡ ጐርፉ ፡ የምትይው ፡ ልጅ ፡ ራሱን ፡ አይወድም - - - ?

« እኔ ፡ እንጃ ፡ እንግዲህ ፡ እኔ ፡ ብሆን ፡ እወደዋለሁ ። ጨዋታው ፡ ደስ ፡ ይለኛል ፤ ያስቀኛል - - - አንዳንዴ ፡ ባነጋገሩ ፡ ለልቤ ፡ ልብ ፡ ይሆነኛል ። ደሞ ፡ ስለሚያስደስተኝና ፡ ስለሚያስቀኝ ፡ ብቻ ፡ አይምሰልህ ፡ የምወደው ። አውሬ ፡ የሚሆንበት ፡ ጊዜ ፡ አለ ፡ ደግሞ - - ሲያሳዝነኝና ፡ ሲያበሳጨኝ ፡ ደስ ፡ የሚለው ፡ ጊዜ — ሆኖም ፡ ታዲያ ፡ ከሌሎች ፡ አብልጦ ፡ እንደሚወደኝ ፡ ያለጥርጥር ፡ ስለማምን ፡ እኔም ፡ እወደዋለሁ — አልከፋብትም - - -

«ሞትና ፡ ሕይወት ! ታፈቅሪዋለሽ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ እንዳነጋገርሽ ። ልቡስ ፡ ጥላችሁ ፡ ተስማምቷል ፡ ማለት ፡ ነው - - የልቡስ ፡ ጥላ ፡ መገናኘት - - - » ይላታል ፡ ትክ ፡ ብሎ ፡ እየተመለከተ ።

« አዎ ፡ ምነው—ከሌሎች ፡ የበለጠ ፡ ስለሚወደኝ ፡ እኔም ፡ እወደዋለሁ - - ይችን ፡ ሮማንን ፡ ይወዳታል ፡ ለምሳሌ - - አበበች ፡ የምትባል ፡ የትምህርት ፡ ቤት ፡ ጓደኛዬም ፡ አለች ፤ እሷንም ፡ ይወዳታል ፡ ግን ፡ እኔን ፡ ከነሱ ፡ ሁሉ ፡ የበለጠ ፡ ይወደኛል - - - እኔን ፡ የሚወደኝን ፡ ያህል ፡ አይወዳቸውም - - -

« - - ትቀልጃለሽ ፡ ጺወኔ ! በምን ፡ ታውቂያለሽ ? ይኸኮ ፡ እንዲህ ፡ የሚያናግርሽ ፡ ልቡስ ፡ ጥላው ፡ ስለተሟላልሽ ፡ ነው - - -

« ገብቶኛል - - ለምሳሌ ፡ ልንገርህ ! በቀደም ፡ እዚያ ፡ አልሞተ ፡ አጥር ፡ ሥር ፡ ከአንድ ፡ ሰዓት ፡ የበለጠ ፡ ነው ፡ ቆመን ፡ የተጫወትነው - - እያሳቀኝ ፤ የልቡን ፡ ያንጀቱን ፡ እያጫወተኝ—ስለ ፡ አዳል ፡ መግደል - - ስለ ፡ ጥይት ፡ መተኮስ - - ስለ ፡ አዳል ፡ በሮች ፡ ስለጠረናቸው - - ከነሱ ፡ ጋር ፡ ቢሆን ፡ እንዲያ ፡ አስችሎት ፡ አይቆይም - - በጣም ፡ ነው ፡ የሚወደኝ ፤ እንደ ፡ እኅቱ ፡ ነው ፡ እያያዙ ፡ ሁሉ ፡ እኔን - - - አንዳንዴ ፡ ይከፋዋል - - አንዳንዴ ፡ በሐሳብ ፡ አንስማማም - - አንዳንዴ ፡ የሚነግረኝ ፡ ነገር ፡ አይገባኝም ፤ እሱም ፡ የኔ ፡ አይገባው - - አንዳንዴ ፡ የሚጠይቀኝን ፡ ነገር ፡ አላደርግም - - አንዳንዴ ፡ እንዲያውም ፡ ዓይኑን ፡ ላየው ፡ አልፈልግም - - ግን ፡ እንዲያም ፡ ሆኖ ፡ እወደዋለሁ ፤ እሱም ፡ እንደሚወደኝ ፡ ዐውቃለሁ ። አዎ ፡ እውነቴን ፡ ነው ፡ የምልህ ፡

አሁን ፡ ለምሳሌ ፡ እነሮማንን ፡ ቢሆን ፡ ጨርሶ ፡ አይከፋባቸውም ፤ አይ ጨነቅላቸውም - - ብዙ ፡ ሰዓት ፡ ቆሞ ፡ የልቡን ፡ አያወራቸውም - - -

« ብቻ ፡ ባጭሩ ፡ ትወጅዋለሽ ፡ ማለት ፡ ነው - - - » በዝምታ ፡ ዓይን ፡ ትመልስለታለች ።—ፍሎቤሩን ፡ ያነግትና ፡ ወደ ፡ አደኑ ፡ ያመ ራል - - -

## ፳

# አደፍርስ

ከማሳ ፡ ማሳ ፡ ሲዟዟር ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ይቆያል ። ቆቆችም ፡ አግኝቶ ፡ እየተኮሰባቸው ፡ ይስታል ። ወደ ፡ ስምንት ፡ ሰዓት ፡ ገደማ ፡ እወይዘሮ ፡ አሰጋሽ ፡ ቤት ፡ በታች ፡ ይመለስና ፡ ሲተኳኩስ ፡ ይሰማል ። ጺወኔ ፡ የተቀቀለ ፡ ባርማሽላ ፡ ትይዝለትና ፡ ወደ ፡ ቦታው ፡ ትሄዳለች ። እንደደረሰች፡ ደጋግሞ ፡ ሲተኩስ ፡ ታየዋለች ። ሌሎች ፡ የገበሬ ፡ ሚስቶች ፡ ራቅ ፡ ራቅ፡ ካሉ ፡ ጐጆዎች ፡ ወጥተው ፡ ወደ ፡ አደፍርስ ፡ እየተመለከቱ ፡ ይናገራሉ—

« እንዴት ፡ ያለች ፡ ሲካካ ፡ ዶሮ ፡ አለችኝ ፤ ሰሙኔ ፡ ከሁለት ፡ ፍራንክ ፡ እሸጥልዎታለሁ -- ጥይትዎን ፡ ከሚያባክኑ--» ትላለች ፡ አንዷ ።-

«እዚህ ፡ እኛ ፡ ማሳ ፡ ውስጥኮ ፡ ብቻ ፡ ሦስት ፡ ጥይት ፡ መተኮሳቸው ፡ ነው » ትቀጥላለች ፡ ሌላዋ ፡ ኮረዳ ፡ መሳይ ።-

«ሰሙኔም ፡ ቢሆን ፡ እሸጥልዎታለሁ ፤ ለመጠማጥ ፡ ከምገብር--» ታግባባለች ፡ የመጀመሪያዋ ።-

« እኔም ፡ ያን ፡ ኩብኩባ ፡ ዶሮዬን ፡ እሸጥላቸዋለሁ ፡ ከፈለጉ ፡ ስሙኒ ፡ ካራት ፡ ፍራንክ ፡ ይግዙኝ - - ምነው ፡ ካንቺ ፡ በልታ ፡ በልታ ፡ እንዳውራ ፡ ከምትኮኩል ፡ መሲና ፡ የኔ ፡ ኩብኩባ ፡ ይሻላቸዋል - - - » ኮረዳዋ ፡ ትደግማለች ።

«እኔ ፡ ቆቅ ፡ ነው ፡ የምፈልገው ፤ የእናንተን ፡ ዶሮ ፡ አልፈልግም!» ይላቸዋል ፡ ጮክ ፡ ብሎ ፡ ንዴት ፡ በያዘው ፡ ድምፅ ፡ ዓይነት ።

« ቆቆቹ ፡ ሁሉኮ ፡ እየተነሡ ፡ ሲበሩ ፡ ስላየናቸው — ከሚደክሙ ፡ ብለን ፡ ነው - - -

« ለመጠማጥ ፡ ገብሯቸው ፡ እነሱን - - -

« ምናልባት ፡ ለምሳ ፡ ይሹ ፡ እንደሁ ፡ ግዴለም ፡ ይሁን ፡ አምስት ፡ ዕንቁላል ፡ እጨምርልዎታለሁ - - -

« ሞትና ፡ ሕይወት ! ቆቅ ፡ ነው ፡ የምፈልገው ፡ አልኩኝኮ - - !

« ነገም ፡ እዚህ ፡ ከዋሉ ፡ በወጥመድ ፡ ይገባ ፡ እሸጥልዎታለሁ - - - » ይለዋል ፡ አንድ ፡ እረኛ ፡ ድንገት ፡ ከየት ፡ እንደ ፡ መጣ ፡ ሳይታይ ፡ አጠገቡ ፡ ደርሶ ፡ ቆሞ ።

« የኔ ፡ ኩብኩባ ፡ የቆቆቹን ፡ ያህል ፡ ባይገራ ፡ ገንዘብዎን ፡ እመል ሳለሁ ፤ በኔ ፡ ይሁንብዎ — ምነው ! በንዴት ፡ ለምን ፡ ጥይትዎን ፡ ይጨ ርሳሉ ፡ በዛሬ ፡ ጥይት ፡ ውድነት - - - ?

« ለምሳ ፡ ሳትገባ ፡ ቀረህ - - ባርማሽላ ፡ ይዠልህ ፡ መጥቻለሁ ! » ትለዋለች ፡ ጺወኔ ፤ ራቅ ፡ ብላ ፡ አጠገቡ ፡ እንደደረሰች

« ኩብኩባ — ባርማሽላ — ዶሮ ! ! ! » በባሻገሩ ፡ ተረተር ፡ ሥር ፡ እሚያየው ፡ ቋጥኝ ፡ ላይ ፡ እያነጣጠረ ፡ የተረፉትን ፡ ሁለት ፡ ጥይቶች ፡ ይተኩስና — በኀይል ፡ እየተራመደ ፡ ወደ ፡ ቋጥኙ ፡ ያመራል ።—ጺወኔ ፡ ልትደርስበት ፡ አልቻለችም ፤ ብዙ ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ ትቀራለች ።

« አሁንስ ፡ ቀናቸው ፡ መሰለኝ » ስትል ፡ ትሰማለች ፡ ከገበሬ ፡ ሚስ ቶቹ ፡ አንዷ—ምንጥቅ ፡ ብሎ ፡ የተነሣ ፡ አረማመዱን ፡ ተመልክታ ።—

« ዕድለኛ ፡ ልጅ ፡ የሻለቃው ፡ ልጅ ፡ ገድ ፡ ይሆናላ ! » ትላለች ፡ ሌላዋ ።

« - - - ከደጎና ፡ ተወለድ ፡ ወይም ፡ ከደጎና ፡ ተጠጋ ፡ አዶለም - - ?

« ጠሎተኛ ፡ ማንም ፡ ከዘራቸው ፡ እንደሷ ፡ የለም - - -

አደፍርስ ፡ ሰውነቱን ፡ ስለወበቀው ፡ ጃኬቱን ፡ አውልቆ ፡ እትከሻው ላይ ፡ ወርወር ፡ በማድረግ ፡ ዝግ ፡ ብሎ ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ሲያመራ ፡ ያዩታል ፡ ባሻገራቸው ።—አለመጠን ፡ አልቦት — ፊቱም ፡ አንገቱም ፡ እየተንቸፈ ቸፈ —

« አልተሳሳትሽም — ያውና ፡ በብረቱ ፡ ነው ፡ መሰለኝ ፡ ትከሻው ፡ ላይ ፡ ምናምን ፡ አንጠልጥሎ ፡ ይታያል - - -

« አልኩሽኮ - - - !

« አዎ ፡ አልተሳሳትሽም - - - !

ጺወኔ ፡ ያቅሟን ፡ ያህል ፡ እየተራመደች ፡ እነሱ ፡ ደጅ ፡ እሚታ የው ፡ ተረተር ፡ ላይ ፡ ስትደርስ ፡ ትንፋሿን ፡ ለመዋጥ ፡ ያህል ፡ አረፍ ፡ ትላለች — ከቀኟ ፡ ከግራዋ ፡ ከፊለፊቷ ፡ ሙሉ ፡ ይፋት ፡ ይታያል — የጥ

ሙጋ ፡ ጋሎች ፡ የዘላን ፡ አዳሎች ፡ የወላስማዎች ፡ መዘዋወሪያ ፡ የነበረው ፡ ይፋት - - - እነ ፡ ሳብር ፡ አዲን ፡ እነ ፡ ማሕፉድ ፡ እያሸመቁ ፡ እነ ፡ ዐምደ ፡ ጽዮንን ፡ እነ ፡ ዘርአ ፡ ያዕቆብን ፡ ያሰለቹበት ፡ ይፋት--በአንድ ፡ ዘመን ፡ መንዝና ፡ ይፋት ፡ ይባል ፡ የነበረው ፡ ዛሬ ፡ ደግሞ ፡ ተለውጦ ፡ ይፋትና ፡ ጥሙጋ ፡ ተብሎ ፡ የተሰየመው — አንድ ፡ ሺህ ፡ አምስት ፡ መቶ ፡ ሰባ ፡ ገባሮች ፡ አንድ ፡ ሺህ ፡ ዘጠኝ ፡ መቶ ፡ ኀምሳ ፡ ግንደ ፡ በሎች ፡ ስምንት ፡ መቶ ፡ ሃያ ፡ ዘጠኝ ፡ ሰሞነተኞች ፡ አምስት ፡ መቶ ፡ አሥር ፡ ሲሶ ፡ አራሾች ፡ የሚኖሩበት ፡ ይፋት ።—አቅራቢያዋ ፡ ሸለቆ ፡ ውስጥ ፡ ደግሞ ፡ እንደ ፡ ምልክት ፡ የትልቅ ፡ መዛሪያ ፡ ድምፅ ፡ ያስገመግምና ፡ ተራራውን ፡ ሸጥ ፡ ሸለቆውን ፡ ጥሶ ፡ ለመውጣት ፡ የሚታገል ፡ የሚመስል ፡ የሽለላ ፡ ድርቅርቅታ ፡ ይሰማል ፡ ሲያስተጋባ—ከጋራ ፡ ጋራ !

« ወንድሙን ፡ ሲገድሉት ፡ ወንድሙን ፡ ካልከፋው ፡
አቅርቡለት ፡ ልብሱን ፡ ደሙ ፡ እንዲከረፋው ።
የናቴ ፡ አገር ፡ ያባቴ ፡ አገር ፡ ዱሬ ፡
እገባብሻለሁ ፡ የትም ፡ ዞሬ ፡ ዞሬ !

እያለ ፡ ሲያናግረው - - -

# ፳፩

## አደፍርስ

ዝናቡ ፡ አቋርጦ ፡ የመብረቁ ፡ ዳመና ፡ አልፎ ፡ ከንፈሩን ፡ የገጠመ፡ የሚመስል ፡ ነፋስ ፡ ውደቱን ፡ መነስነስ ፡ ጀምሯል ።-እንደስጋጃ ፡ የተነጠፈው ፡ ሣር ፡ በደማቅ ፡ አረንጓዴና ፡ በወርቅማ ፡ ቀለም ፡ አደግድጓል ።-በተሸከመው ፡ ውሃ ፡ ምክንያት ፡ እርስ ፡ በርሱ ፡ የተያያዘው ፡ የዛፍ ፡ ቅጠል ፡ በሕይወት ፡ ይርመሰመሳል — እንዳይታይ ፡ ዓይንን ፡ እያጥበረበረ ። ኃይለኛ ፡ የሆነ ፡ የአዝርእትና ፡ ዕፀዋት ፡ ሽታ ፡ ከየቦታው ፡ ይምቦለቦላል ።— በማይመረመር ፡ ጥበቡ ፡ ተብትቦ - - እንቅ - ጭንቅ -እምቅ-ጥብብ - ስብርብር - ክርሽምሽም ፡ አድርጎ ፡ እከሌን ፡ በማይባል ፡ የልብ ፡ ፍላጐት ፡ የሚያናውጥ ፡ ጸጥታ ፡ ባካባቢው፡ነግሥዋል ።-ጺ ወኔ፡ እንደ፡ ልማዷ ፡እግቢያቸው፡ ሽምጥ ፡ ሥር፡ከውስጥ ፡ በኩል ፡ ቆማለች ።-ዓይኖቿ ፡ ለብዙ ፡ ጊዜ ፡ አርቀው ፡ ሲመለከቱ ፡ ይቆዩና ፡ ቀስ ፡ በቀስ ፡ እየቀረቡ ፡ እየቀረቡ ፡ ይመጣሉ ፡ በደጅዋ ፡ ተረተር፡ ላይ፡ እየዳሩ ፡ በየቆሙት ፡ ዛፎች — በየግንዳቸው — በያይነታቸው ፡ ላይ (አዝጋሮ ፡ አደር ፡ አባሎ ፡ መዛዝኝ - -እመዛዝኙ ፡ ባላባልቾዎች ፡ መካከል — እበታቹ ፡ እሚታየው ፡ ሸለቆ ፡ ውስጥ ፡ እየተመለከተ ) ጀርባውን ፡ ሰጥቶ ፡ እተቀመጠው ፡ አደፍርስ ፡ ላይ ፡ አርፈው — ወደ ፡ ራሷ ፡ እስኪመለሱ ፡ ድረስ ።— ምንጥቅ ፡ ብላ ፡ ወጥታ ፡ አጠገቡ ፡ ትቆማለች ።

« ተቀይመኸኛል ፡ መቼም ፤ ልቤ ፡ ነግሮኛል » ትለዋለች ፡ ቀስ ፡ ብላ - - -

« ድንቁርናና ፡ ዕውቀት ! ለምንድነው ፡ የምቀየምሽ - - አልተቀየምሁሽም» ይመልስላታል ፡ አደፍርስ ፤ ባጠያየቋ ፡ የተደነቀ ፡ በሚመስል ፡ ድምፅ ።

« የለም ፡ ተቀይመኸኛል — አደኑ ፡ ቦታ ፡ ስለመጣሁብህ - - -!

« አልተቀየምሁሽም ፡ አልኩሽ ፡ እንግዲህ - - -

« እሺ ፡ እውነት ፡ ካልተቀየምከኝ ፡ እንደ ፡ ዱሮው ፡ ፊታ ፡ በልና ፡ እንጫወት — እምልህ ፡ ወይም ፡ አኮርዲዮውን ፡ አሰማኝ - -

« አላሰኘኝም - - -

« እኔን ፡ አሰኝቶኛል - - -

« አንገቱን ፡ ወዝወዝ ፡ ወዝወዝ ፡ እያደረገ «አላሰኘኝም ፡ ማለት ፡ አማርኛ - - -

« እሺ ፡ እሺ ፡ ይቅርብኝ - - እንግዲያው ፡ እኔ ፡ እንድጫወትልህ ፡ ትፈልጋለህ - - - ?

« ምንድነው ፡ የምትጫወችልኝ - - - ?

« ክራር - - -

« እናትሽ ፡ የተቆጡሽስ ፡ እንደሆን - - - ?

« እሱ ፡ የኔ ፡ ጉዳይ ፡ ነው ፡ አንተ ፡ ምንቸገረህ—ብቻ ፡ ትፈልጋለህ ፡ አትፈልግም - - - ?

« የለም ፡ እናትሽ ፡ ይቆጡሻል - - -

« ግዴለህምኮ ፡ አልኩህ - - -

« ደግሞ ፡ በቀደም ፡ ተጫውተሽ ፡ እንዳበቃሽ ፡ ልምምድ ፡ ሳታደ ርጊ ፡ መቆየትሽን ፡ ነግረሽኛል - - -

« ምነው ፡ ከትናንት ፡ ወዲያ ፡ ጧት ፡ የተጫወትሁ ፡ ጊዜ ፡ ያሻሻ ልኩ ፡ አልመሰለህም - - - ?

« ከትናንት ፡ ወዲያ ፡ ጧት ? አሻሽለሽ ፡ ይሆናል — ብቻ ፡ እኔ ፡ እስከዚህ ፡ ትዝ ፡ አይለኝም - - -

« ደስ ፡ ብሎኝ ፡ ከተጫወትሁ ፡ እንግዲያውስ ፡ ብዙ ፡ ልዩነት ፡ አያ መጣም - -

« ብዙ ፡ ልዩነት ፡ ያመጣ ፡ እንደሁ ፡ ብቻ ፡ አፍሬም ፡ አላበቃ - - -

« ትናንትና ፡ ተኩሰህ ፡ ስትስት ፡ ሳይህ ፡ እንዳፈርከው - - ? » ሳታስ በው ፡ ያመልጣትና ፡ ትደነግጣለች « - - ወደኸው ፡ ነበርኮ ፡ ታዲያ ጨዋታዬን - - - » ትቀጥላለች ፡ ወዲያውም ፡ ርእሱን ፡ የለወጠች ፡ ይመ ስላትና ።

« ድንቁርናና ፡ ዕውቀት - - ! ትዝ ፡ የማይለኝን ፡ እንዴት ፡ እወ ዳለሁ - - » ይመልሳል ፡ አደፍርስ ፡ ቅሬታው ፡ በድምፁ ፡ እየታወቀ ።

« እምልህ ፡ የትናንት ፡ ወዲያ ፡ ጢቱን - - -

« ትዝም - - ትዝም - - -

« ከፈለግህ ፡ እንደገና ፡ ዛሬ ፡ ልጫወትልህ ፡ እችላለሁ — እምልህ - ከፈለግህ - - -

« ትዝታው ፡ ውሎ ፡ ያላደረ ፡ ነገር - - አላደክምሽም - - - !

« አይመስለኝም ፡ ለኔ ፡ ድካም ፡ የሰጋህ - - አላምንህም - - -

« ሞትና ፡ ሕይወት ! በጣም ፡ ትገርሚያለሽ - - ! ነገርሽን ፡ ሁሉ ፡ ሳየው ፡ ድካምሽ ፡ ሁሉ ፡ እልም ፡ ስልም ፡ ድክም ፡ ጭርስ ፡ የሚያደርግ ፡ ወፎች ፡ የሚያረግፍ ፡ የሚያነሆልል ፡ ጣዕመ ፡ ዜማሽን ፡ እንደገና ፡ አስሰ ሚኝ ፡ እንድልሽ ፡ ዓይነት ፡ የፈለግሽ ፡ ነው ፡ የሚመስለው - - በጣም ፡ በጣም ፡ ግሩም ፡ ትጫወቻለሽ ፡ እንድልሽ ፡ ዓይነት - - ወይም - ወይም - - ወይም - - ብቻ - - -

« ቢሆንም ፡ ምናልባት ፡ ብጫወትልህ ፡ ግዴለህ ፡ ይሆናል - - እምልህ ፡ ጊዜ ፡ ለማሳለፍ ፡ ያህል - - -

« ግድአለኝ ፡ እንጂ ፡ እንዴት ፡ ግድ ፡ የለኝም ።—አንች ፡ የመንደር ፡ አሪሆ ፡ ወይም ፡ አዝማሪ ፡ አይደለሽም - - እመየቴ ፡ እናትሽም ፡ ይኸ ንኑ ፡ ዐውቀው ፡ ነው ፡ እንዳትጫወች ፡ የሚከለክሉሽ - - -

« በርግጥ ፡ አንተ ፡ እንድጫወት ፡ የማትፈልግበትን ፡ ምክንያት ፡ ልንገርህ ?

« ምን ፡ ትነግሪኛለሽ ፡ እኔ ፡ እየነገርኩሽ - - -

« አንተ ፡ እውነቱን ፡ አልነገርከኝም - - -

« አታደርጊውም ! ደግሞ - - -

« ደግሞም ፡ እኔ ፡ እስከዚህ ፡ ችሎታዬን ፡ አልጠራጠረውም - - የሰማኝም ፡ ሁሉ ፡ ሳይደሰት ፡ ቀርቶ ፡ አያውቅም - - -

« የራሱ ፡ ጉዳይ - - -

« ከሰሚዎቹ ፡ ውስጥ ፡ አንተም ፡ ስለነበርህ ፡ ልትደሰት ፡ ይገባ ፡ ነበር - - » ፈገግ ፡ ይልና — ወዲያው ፡ ገታ ፡ ያረጋል ፡ እራሱን ።

«ነግሬሻለሁኮ ፡ እንደ ፡ ሌሎቹ ፡ ሰዎች ፡ መቀላመዱን ፡ አጥቼው ፡ አይደለም - - በጣም ፡ በጣም ፡ ስለሚያስጠላኝ ፡ ብቻ ፡ ነው - - -

« - - እና ፡ ታዲያ ፡ ከትናንት ፡ ወዲያ ፡ ምንም ፡ ሳትል ፡ ሄደህ ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ - - - በፊትህ ፡ ላይ ፡ ምንም ፡ ነገር ፡ ምንም ፡ ልውውጥ ፡ ባላይ ፡ ኖሮ ፡ እርግጠኛ ፡ ነኝ ፡ እታመም ፡ ነበር - - -

« ፊቴ ፡ ላይ ! ፊቴ ፡ ላይ ! አብደሻል - - - !

« አዎ ፡ ፊትህ ፡ ላይ ፡ አይቻለሁ - - - !

« በእግዚአብሔር ፡ እንስማው ፤ ምን ፡ ይሆን ፡ ያየሽው ! » በማያ ምንና ፡ በሚያንጓልል ፡ ዓይነት ፡ ድምፅ ።

« አይቻለሁ ፡ አይቻለሁ - - !

« ያየሽውኮ ፡ ምንድነው ፡ ነው ፡ የምልሽ - - - ?

« እንባ ! እንባ ፡ ነው ፡ ያየሁት - - ምንም ፡ እንኳ ፡ ለመደበቅ ፡ ብትታገል - - እናንተ ፡ ወንዶች ፡ ግን ፡ ትገርማላችሁ - - የልባችሁን ፡ ቋንቋ ፡ ለመደበቅ ፡ መድከማችሁ - - - ምን ፡ እንደሚያሳፍራችሁ ፡ እንጃ ! —ይልቅ ፡ አንዳንዴ ፡ ያለቅጥ ፡ ዐወቅን ፡ ብላችሁ ፡ ስለ ፡ ሃይማኖት፡ ስለ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ስለ ፡ ንጉሥ ፡ ስለምትለፈልፉት ፡ እፈሩ - - ወን ዶች ፡ ስትባሉ ፡ የሚያስቅ ፡ ኩራት ፡ አለባችሁ - - -

« ሀ — ሀ — ሀ — ሀ — ድንቁርናና ፡ ዕውቀት ፡ ይልሻል ፡ ይኽ ፡ ነው - - - ! እውነት ፡ ለመናገር ፡ እፍሬዋ ፡ ዓይን ፡ ላይ ፡ በሆን ፡ ባልገረ መኝ ! እኔ ፡ ዓይን ፡ ላይ ፡ እንባ - - ? ተሳስተሻል ፡ ጺወኔ - - በጣም ፡ ተሳስተሻል - - - !

« አጉል—አጉል— አጉል ፡ ኩሩ ፡ ነህ - - ቢታወቅህ - - - ያላየሁ ትን ፡ አየሁ ፡ አልልም ፡ እኔ - - -

« ያየሁትን ፡ ነገር ፡ ባላይ ፡ እታመም ፡ ነበር ፡ ብለሻልኮ ፡ አንችማ? ጨርሰሽዋል - - - !

« አዎ ፡ ብያለሁ - - -

« ያየሽ ፡ መስለሽ ፡ ስለዚህ - - ራስሽን ፡ በራስሽ ፡ ደለልሽው - - ለምን ፡ ይመስልሻል - - - ?

« ያየሁትን ፡ አላየሽም ፡ ብለህ ፡ ከካድህ - - ምን ፡ አደካከመኝ ፡ መልስ ፡ ለመስጠት ! መድከም ፡ አያሻም - - -

« ድንቁርናና ፡ ዕውቀት ፡ ብሎ ፡ ነገር - - ኩሩ ፡ ስለሆንሽ ፡ ነው - - ራስሽን ፡ የደለልሽው ! እኔ ፡ እመልስልሻለሁ - - ኩሩ ፡ ስለሆንሽ - - !

« ይሆን ፡ ይሆናል - - ሁሉም ፡ በየበኩሉ ፡ ኩሩ ፡ ነው - - ኩራት ፡ ራት ፡ ተብሎ ፡ የለም - - - ኩራት ፡ ራት - - - ምናልባት ፡ አንተ ፡ ኩራት የለህ ፡ ይሆናል - - ማለቴ - - ምናልባት ፡ አንተን ፡ እኔን ፡ የተሰማኝ ፡ አልተሰማህ - - - » ሳትጨርሰው ፡ ትቆማለች —

« ምን ፡ አልሽ - - ? » ይጠይቃታል ፡ አደፍርስ ፡ ደከም ፡ ኮስተር ፡ ባለ ፡ ድምፅ ፡፡-

« ምንም ፡ አላልኩ—እምልህ ፡ ሁለተኛ ፡ አይለምደኝም ፡ ቀልድ - ካንተ ፡ ጋር - - ምላሴ ፡ ነው ፡ ጠላቴ - - መቀለዴኮ ፡ ደሞ ፡ ያልሁት ፡ በሆነ - - ምን ፡ ቆርጦኝ - - » ትለዋለች ፤ ድምፅዋ ፡ እየተርገበገበ —

እስከዚህ ፡ ድረስ ፡ እሷን ፡ የሚያስጨንቅበት ፡ ምክንያት ፡ ስላልነበረው ፡ ሁኔታዋ ፡ አንጀቱን ፡ ይነካዋል ፡፡ ልቧን ፡ መልሶ ፡ አንጀቷን ፡ ለማረጋጋት ፡ ይፈልጋል ፡፡— ምንም ፡ ነገር ፡ ለማለት ፡ ግን ፡ ያቅተዋል፡፡

« - - ምላሴ ፡ ነው ፡ ጠላቴ - - ጉርፉም ፡ ደጋግሞ ፡ ነግሮኛል - - እሱ ፡ እዚህ ፡ ቢኖር ፡ ኖሮ ፡ ምንኛ ፡ በተስማማ - -» ትቀጥላለች ፡ ጺወኔ—ዘወር ፡ ብላ ፡ ዓይኖቹን ፡ ባይኖቿ ፡ ይዛ ፡ በማቆም ፤ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ የሚመጣጠጡ ፡ ይመስል - - የሷ ፡ ፊት ፡ ደም ፡ እየሠረገ ፡ የሱ ፡ ፊት ፡ ደም ፡ ዓይኑን ፡ ሊያፈርጠው ፡ ዓይነት ፡ እያስመሰመ - - -

« አንችን ፡ እያየ ፡ በምትናገሪው ፡ የማይስማማ ፡ የለም - - - » እስኪያሰኘው - - ያመቀውን ፡ ስሜት ፡ እያተነነ — እያጉመ —እያወረዛ ፡ እስኪያሶጣው ፡፡— ጺወኔን ፡ ድንገት ፡ ግራ ፡ ይገባታል ፡፡—

« እኔን ፡ እያየ ፡ የማይስማማ ፡ የለም ? » ደሟ ፡ እንደገና ፡ ፊቷ ፡ ላይ ፡ ይመለሳል «- - ደስ ፡ ይልሃል ፡ ላንተ ፡ የምለው ፡ ነገር - - - ደስ ፡ ይልሃል - - ? ደስ ፡ እልሃለሁ ፡ እኔ - - - ? » አደፍርስ ፡ እንደገና ፡ የሚመልሰው፡ ያጣና ፡ ግራ ፡ ይገባዋል « - - ሁልጊዜም ፡ እንዳሁንህ ፡ ብትናገር - - » ዓይኑን ፡ መሸሽ ፡ ታመጣለች ፡ ስትናገር - - የምትናገረውም ፡ እየተበጣጠሰባት ፡ ይሄድና ፡ ትቆማለች ፡፡

« አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ አንጀታዊ ፡ ንግግር ፡ መናገር ፡ አስቸጋሪ ፡ ነው - - » ይጀምራል ፡ አደፍርስ ፡ ይቆይ ፡ ይቆይና ፤ መቀጠል ፡ ግን ፡ ያቅተዋል ፡፡ እንደገና ፡ ምንም ፡ ሳይነጋገሩ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ይቆያሉ ፤ አንዳቸው ፡ ያንዳቸውን ፡ መኖር ፡ የዘነጉት ፡ ይመስል ፡—ድንገት ፡ ነው - - ያን ፡ እንዲያ ፡ የተቸነነ ፡ ጸጥታ ፡ ጥሳ - - -

« እሺ ፣ አሁን ፣ ታዲያ ፣ ምን ፣ ላድርግልህ ? » ብላ ፣ የምትጠይቀው-ግምባሯን ፣ ሰብሰብ ፣ ዘቅዘቅ - ዓይኖቿን ፣ ቦግ - ፊቷን ፣ ፈገግ ፣ እያደረ ገች « - - እምልህ ፣ እንዳይሰለችህ - - -

« መሰልቸት ? ሞትና ፣ ሕይወት ! ማን ፣ አለሽ ፣ ሰለቸኝ ? » ከሌላ ፣ ዓለም ፣ ውስጥ ፣ የሚፈልቅ ፣ በሚመስል ፣ ድምፅ ፣ የሚመልስላት ፣ አደ ፍርስም « - - ካንቺ ፣ ጋር ፣ ሆኖ ፣ ስልችታ - - ታሾፊብኛለሽ ፣ መሰ ለኝ - - - ?

« ቢሆንም ፣ ቢሆንም - - » በቀልደኛ ፣ ዓይነት ፣ ዓይኖች ፣ ታጠም ደዋለች ፣ እንደገና

« እሺ — እንግዲያው ፣ እንዳልሽ - - - መች ፣ ያጣላናል ፤ አያጣላ ንም ፣ ይኸ - - እኔ ፣ ደሞ - - በተራዬ - - -

« አኮርዲዎ ፣ ትጫወትልኛለህ - - ! » ሕይወት ፣ ትፍለቀለቅ ፣ ትምቦለቦላለች ፣ ካይኖቿ - - የሠራ ፣ አካላቷ ፣ ይፍማል - - በደስታ ፣ ይበረቀቃል ።—ከወገቧ ፣ ቅንጥስ ፣ ያለች ፣ በመምሰል ፣ ተነሥታ ፣ ትመዝ ረጋለች ፤ ክራሩን ፣ ለማምጣት ።—በዓይኖቹ ፣ እየተከተላት ፣ አደፍርስ - - ሮጥ — ሮጥ — ሮጥ — ሮጥ - - እዋናው ፣ አጥር ፣ በር — አፍ ፣ ትደርሳ ለች ።— ጨርሳ ፣ ልትገባ ፣ ሁለት ፣ እግሮቿ - - መጨረሻ — ውዝ — ውዝ — ውዝ — ውዝ — ይላሉ ።— በዚያን ፣ ቅጽበት ፣ አደፍርስን ፣ አይስሰሙ ፣ ስሜት ፣ ይስሰማዋል - - ስግጥጥ ፣ የሚያደርግ - - ጭን ቅላቷን ፣ ደረቷን ፣ ወገቧን ፣ ውጦ ፣ እግሮቿ ፣ ብቻ ፣ አልዋጥ ፣ ብለው ፣ አስችግረው ፣ ከአፉ ፣ ውጪ ፣ ሲወዛወዙ - - -

« ነገርኩህ ፣ እንግዲህ ፣ እከንፈሬ ፣ ላይ ፣ ሳቅ ፣ አልፈልግም - - - የምን ፣ መገለጢጥነት ፣ ነው ፣ እቴ ! » ይላሉ ፣ ወይዘሮ ፣ አሰጋሽ — የእ ጅና ፣ የእጅ ፣ ማስደገፊያ ፣ ያለው — ባላቸው ፣ በጣሊያን ፣ ጊዜ ፣ እዘረ ፋት ፣ ወንበር ፣ ላይ ፣ እግቢው ፣ ውስጥ ፣ ወርዶፋ ፣ ጉጀ ፣ አጠገብ ፣ ቁጭ ፣ ብለው « - - አዎ ፣ አያስፈልግም - - ሳቅና - - ምንድነው ፣ ስሙ ፣ - - ቤት ፣ ያጠፋል - - -

« - - - ባይስቁም - - ትንሽ ፣ ከንፈርዎን ፣ ለቀቅ ፣ ባደርገው — እምልዎት ፣ ኩርትም ፣ ብሎ ፣ ባይጋጠም ፣ ምናለበት ? » ያባብላቸዋል ፣ ክብረት ፣ መሣያ ፣ ሸራውን ፣ በቡርሽ ፣ እየደባበሰ « ምነው ፣ እስከዚህ ፣ ሥራዬን ፣ የማላውቅ ፣ አይምሰልዎት—የሚካኤልን ፣ ቤተክሲያን ፣ ነው ፣ የማስመስልዎት - - -

«ምን ፡ ቢያገድ ! እኔ ፡ ከጌታዬ ፡ ከፈጣሪዬ ፡ አልወዳደርም ።—ቢሆ ንም ፡ አሰጋሽ ፡ አሰጋሽ ፡ ነኝ ፤ የማንም ፡ ደንገጡር ፡ እኛ ፡ አይደለችም ፤ የራሷ ፡ የሆነ ፡ ክብር ፡ አላት — አዎ ፡ እሱን ፡ አትርሳ ፡ ማለቴ ፡ ነው - - -

« የቀሚስዎ ፡ ቀለም ፡ ምን ፡ ዓይነት ፡ እንዲሆን ፡ ይፈልጋሉ - - - ?

« ምን ፡ ዓይነት ፡ ነው ፡ የለበስኩት ? » ይሉታል ፡ ኮስተር ፡ ይሉና— ወዲያውም ፡ ከመቀመጫቸው ፡ ፍንጥር ፡ ብለው ፡ ወደ ፡ ክብረት ፡ በመሄ ድና ፡ የሚነዳድፈውን ፡ በመመለካከት « ይኸ ፡ ደግሞ ፡ የምን ፡ ጉጅ ፡ ነው ፡ ከኋላዬ ፡ የሚታየው ? እናንተ ፡ የከተማ ፡ ሰዎችኮ ፡ የነገር ፡ አካ ሄዳችሁ ፡ አይታወቅም - - እየፈጩ ፡ ጥሬ ፡ ነገር — የምን ፡ ጉጅ ፡ ነው ? ይኸን ፡ ነውኮ ፡ የምልህ - - » በጣታቸው ፡ እያመለከቱ —

« የወርዶፋ - - - !

«እጡ . . . ብ-እጡብ ! ባንተ ፡ ቤት ፡ አሰጋሽን ፡ ከጉጅ ፡ ጋር ፡ ስታነ ሣት ፡ የማይገባት ፡ ይመስልሃል ? ተሳስተሃል—በጣም ፡ ተሳስተሃል - - -» ራመድ ፡ ራመድ ፡ ብለው ፡ ወደ ፡ እልፍኛቸው ፡ ይሄዱና ፡ ሮማንን ፡ የክት ልብሷን—እግር ፡ አሻሻቸውን ፡ ልጅ ፡ አዲስ ፡ የተሰፋለትን ፡ እጀ ፡ ጠባብ ፡ አስለብሰው ፡ ይመለሳሉ « አንቺ ፡ በይ ፡ ጃንጥላውን ፡ አጥሊኝና ፡ ከኋላዬ ፡ ቁሚ - - አንተ ፡ ደሞ ፡ እግር ፡ እግሬን ፡ እያየህ ፡ እዚህጋ ፡ ተቀ መጥ - - » በእግራቸው ፡ የእግራቸውን ፡ አጠገብ ፡ ያመለክቱና ፡ ቀና ፡ ብለው « - - በል ፡ እንግዲህ ፡ አሁን ፡ ልታነሣን ፡ ትችላለህ - - ዐወቅሽ ፡ ዐወቅሽ ፡ ቢሏት ፡ መጣፍ ፡ አጠበች - - ሁሉንም ፡ ዐውቀን ፡ ትተነው ፡ ነው ፤ ንቀነው ፡ ነው - - እና - - አይምሰልህ - - -

# ፳፪

## አደፍርስ

ሮማን ፡ እኩሬው ፡ አጠገብ ፡ ቁጭ ፡ ብላ ፡ እግሮቿን ፡ ትታጠባለች ፤ ተረከዞቿን ፡ እድንጋይ ፡ ላይ ፡ እየፈገፈገች ። ባቶቿን ፡ ሁሉ ፡ ሳይቀር ፡ ትፈ ትጋቸዋለች ።— እስኪሚልጩ ።— በተለይ ፡ ከፊቷ ፡ ቅልጥልጥ ፡ እየ ጠረገች ፡ አበስ ፡ አበስ ፡ ባደረገቻቸውማ ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ቅቤ ፡ ቅል ፡ ማብ ረቅረቅ ፡ ይጀምራሉ ። እንደጨረሰች ፡ እንስራዋን ፡ ሞልታ ፡ ትሸከምና ፡ ወደ ፡ ቤቷ ፡ ትመለሳለች ።

ሁለተኛ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ መቅጃ ፡ ስትወርድ ፡ በአባቷ ፡ ጐጆ ፡ አጠ ገብ ፡ ታልፋለች ፤ የበረቱን ፡ መካከል ፡ እግር ፡ የለመደ ፡ መሄጃ ፡ በመተ ው ።— አደፍርስና ፡ ጺወኔ ፡ በግርምቡድ ፡ ተቀምጠዋል ፡ እጐጆዋ ፡ አጠገብ ።— የሰዓት ፡ በኋላውን ፡ በራድ ፡ አየር ፡ እየጠጡ - - -

« - - ግሩም ፡ የሆነች ፡ ነገር ፡ ይቺ ፡ ሮማን ፡ የምትሏት ፡ ልጅ - -» ይናገራል ፡ አደፍርስ ፡ እንደዘበት ፡ በአጠገባቸው ፡ ማለፏ ፡ ምክንያት ፡ ይሆነውና ። ጺወኔ ፡ አትመልስለትም « - - ብትማር ፡ ኖሮ ፡ እንዴት ፡ ያለች ፡ የቤት ፡ እመቤት ፡ በወጣት » ይቀጥላል ፡ አደፍርስ ።—አሁንም ፡ አትመልስለትም « - - የሚገርመውኮ ፡ ምኗ ፡ መሰለሽ - - ? የልቧ ፡ ትልቅነት - - እና ፡ ደሞ ፡ ወሰን ፡ የማይከልለው ፡ የሚመስለው ፡ አስተያየቷ - - ሩቅ — ሩቅ — ሩቅኮ ፡ ነው ፡ አመለካከቷ - - - » ዘወር ፡ ብላ ፡ አየት ፡ ታደርገውና ፡ ወዲያው ፡ መለስ ፡ ትላለች « - - እን ዲህ ፡ እንዲህ ፡ ዓይነቷ ፡ አሁን ፡ እዚህ ፡ እባላገር ፡ በሞያሌ ፡ በትኋን ፡ በበረሮ ፡ በቁንጫና ፡ ቅማል ፡ ተጨብጣ ፡ ስትቀር ፡ አያሳዝንም ? » ይቀ ጥላል ፡ አደፍርስ « - - በውነት ፡ ነው ፡ የምልሽ ፡ በጣም ፡ ያሳዝናል - - -

« አቶ ፡ ክብረት ፡ የሚካኤልን ፡ ታቦት ፡ አስመስያቼዋለሁ ፡ እናት ሽን ፡ ይሉኛል - - በፎተግራፏ ፡ ላይ ።— እማማ ፡ ግን ፡ እጅግም ፡ አልወደደችላቸው - - - » ትናገራለች ፡ ጺወኔ ፡ ታዳምጥ ፡ ታዳምጥና ።

« - - - ሮማን ፡ ነች ፡ ታቦት ፡ ማለት - - ድምፅዋን ፡ አልሰማሽ ውም ? እንደ ፡ ቤተክስያን ፡ መረዋ ፡ እጠምቧ ፡ ብሎ ፡ የሕይወትን ፡ እውነታ ፡ በለፈፈ ፡ ጊዜ - - በዚያ ፡ ላይ ፡ ደሞ ፡ ልበ ፡ ገርነቷ - - -

« - - - ያይኖቼን ፡ ስንጥቦች ፡ የቁልቁሊት ፡ አድርጓቸዋል - - ፊ ቴን ፡ ያለመልኩ ፡ መልክ ፡ ሰጥቶታል - - አጥቁሮታል - - - ጣቶቼን ፡ አጉል ፡ እርዝማኔ ፡ ሰጥቷቸዋል - - ጥፍሮቼንም ፡ እንደ ፡ ባለጌ ፡ ጥፍር ፡ አስረዝሞ ፡ የጻረ ፡ ሞት ፡ ጥፍር ፡ አስመስሎብኛል - - ውቃቢዬን ፡ ደስ ፡ የማይለው ፡ ብዙ ፡ ነገር ፡ ጨምሮበታል ፡ ነው ፡ የምትለው - - -

« - - - የጅና ፡ እግሯ ፡ ነገርኮ ፡ ልዩ ፡ ነው - - እምልሽ ፡ የሚገ ርም ፡ ነገር - - ድሃን ፡ እግዜር ፡ ይጠብቀዋል ፡ ማለት - - እጇንና ፡ እግ ሯን ፡ ሙያሌ ፡ አያውቀኝም ፡ አለች ፡ ስታጫውተኝ - - -

« ወዲያ ፡ ወደ ፡ ድብኝት ፡ ውስጥ ፡ አስቀምጭው ፡ ብያታለሁ - - ምን ፡ ዕዳ ፡ አለባት ፡ እስከዚህ ፡ ውቃቢዋ ፡ ካልወደደው - - - ?

« - - - ውቃቢ ፡ የወደደው ፡ ነገር ፡ እውነትሽን ፡ ነው—ያስደን ግጥ ፡ አለው - - ስለ ፡ ልቡሰ ፡ ጥላ ፡ እንዳጫወትኩሽ ፡ ማለት ፡ ነው — አጥልቆ ፡ ከተመለከቱት - - የልቡሰ ፡ ጥላ ፡ ግንኙነት - - ልቡሰ ፡ ጥላ ፡ ሲገጥም - - - » እየተናገረ ፡ ብድግ ፡ ይልና ፡ ወደ ፡ ኩሬው ፡ አቅጣጫ ፡ ይሄዳል ።—

# ፳፫

## አደፍርስ

እኩሬው ፡ አጠገብ ፡ ሲደርስ ፡ ሮማንን ፡ እጉድባው ፡ ውስጥ ፡ ገብታ፡ ስትቀዳ ፡ ያያታል ።— ለስለስ ፡ ባለ ፡ ድምፅ ፡ ስሟን ፡ ይጠራዋል ። ድንግጥ ፡ ትልና ፡ የምትቀዳበት ፡ ሽክና ፡ ከጅዋ ፡ ያመልጣታል ።—አንድ፡ አህያ ፡ ወደ ፡ ኩሬው ፡ አፋፍ ፡ ላይ ፡ ስታመራ ፡ ያይና ፡ ደበቅ ፡ ይላል ፡ አደፍርስ ።— ሮማን ፡ ኮቴ ፡ ትሰማለች ።— ምንም ፡ ዓይነት ፡ ፍጥረት ፡ ግን ፡ አታይም ።— የምትቀዳበት ፡ ሽክና ፡ እንዳመለጣት ፡ ብቅ ፡ ጥልቅ፡ እያለ ፡ ተንሳፍፎ ፡ ርቆ ፡ ሄዶ ፡ ነበርና ፡ በቁራጭ ፡ እንጨት ፡ ቀስ ፡ እያለች ፡ እየገፋች ፡ ወዳጠገቧ ፡ ልትመልሰው ፡ ትሞክራለች ።— ይደግምና ፡ ቀስ ፡ ብሎ ፡ ስሟን ፡ ይጠራዋል ፡ አደፍርስ ፡— ድንግጥ ፡ ትልና ፡ አሁንም ፡ ቀና ፡ ትላለች ። ምንም ፡ ዓይነት ፡ ፍጥረት ፡ ግን ፡ አታይም ። ሽክናው ፡ ወደ ፡ ነበረበት ፡ ይመለሳል ።— በእንጨቱ ፡ እየገፋች ፡ እንደገና ፡ ወዳጠገቧ ፡ ልታመጣው ፡ ትሞክራለች ። ሦስተኛ ፡ ጊዜ ፡ ይጠራዋል ፡ ስሟን ፡ አደፍርስ ።— ድንግጥ ፡ ብላ ፡ ቀና ፡ ትላለች ።— አህያይቱ ፡ እጉድባው ፡ ጠርዝ ፡ እሚታየው ፡ ድንጋይ ፡ ላይ ፡ ብቅ ፡ ብላ ፡ ቆማለች ። የቀኝ፡ እግሯን ፡ ሰኮና ፡ አስቀድማ - - ሮማን ፡ የባሰውን ፡ ተደናግጣ ፡ እንስራዋን ፡ ተሸክማ ፡ ልትወጣ ፡ ስትል

« በጣም ፡ በጣም ፡ ድንጉጥ ፡ ነሽ ! » እያለ ፡ ብቅ ፡ ይላል ፡ አደፍርስ ፡ ከወደተደበቀበት ።—

« እርስዎ ፡ ነዎት ፡ ለካ ? እኔ ፡ ደሞ ፡ አህያዋ ፡ አፍ ፡ አወጣች ፡ ብዬ፡ ፈርቼ ፡ መሸሼ ፡ ነበር - - - እንዴት ፡ አስደነገጡኝ - - - » ትናገራለች ፡ ሮማን ፡ ትንፋሿ ፡ ቁርጥ ፡ ቁርጥ ፡ እያለ « - - ምን ፡ አስቤዎት ፡ እዚህ - - - ከጺወኔ ፡ ጋርኮ ፡ ያየሁዎት ፡ መስሎኝ - - - !

« በቀደም ፡ ከኋላሽ ፡ አስልቼ ፡ ስለንጐጥሁሽ ፡ አኩርፈሻል ፡ መቼም - - ?

« ኩርፊያ - - - ! የምን ፡ ኩርፊያ - - ! ኩርፊያ ፡ አላውቅም ፡ እኔ ።— ይልቅ ፡ ያኮረፈች ፡ ጺወኔ ፡ ነች - - እኩል ፡ ቤት ፡ ረገጥሽ ፡ የሚሉ ፡ ፈሊጥ ፡ አምጥታለች - - -



- - - እርስዎ ፡ ነዎት ፡ ለካ ? እኔ ፡ ደሞ ፡ አህያዋ ፡ አፍ ፡ አወጣች ፡ ብዬ ፡ ፈርቼ ፡ መሽሼ ፡ ነበር - - -

« አንቺ ፡ አታኮርፊም - - - ?

« አላኮርፍም - - -

«_ምንም ፡ ቢያደርጉሽ - - - ?

« ምንም ፡ ቢያደርጉኝ - - ቆይ ፡ ይኸን ፡ እንስራዬን ፡ ገልብጬ ፡ ስመለስ ፡ እንጫወታለን - - » እመንገዷ ፡ ገብታ ፡ ሽቅብ ፡ ታቀናለች ።

« - - አሁን ፡ ለምሳሌ ፡ እጅዋን ፡ ያዝ ፡ ባደርገው - - ጡቷን ፡ ጨበጥ - - ትከሻዋን ፡ አቀፍ ፡ እንደማድረግ - - ሂሂ - - - ውሸቷን ፡ ነው ፤ ትከፋለች ።- ደርሶ ፡ መከፋት ፡ ሊበቃት - - ስትሮጥ ፡ ነው ፡ ሄዳ ፡ የምትናገረው ፡ ለቤተ ፡ ሰቡ ፡ ሁሉ ።-በተለይ ፡ ደሞ ፡ ለጺወኔ - - - ! ምን ፡ ትል ፡ እንዲህ ፡ እንዲህ ፡ አረገኝ ፡ ስትላት ? እሷን ፡ እንኳን ፡ ገና ፡ እስከዚህ ፡ አልተጠጋኋትም - - በዚያ ፡ ላይ ፡ ደሞ ፡ የወርዶፋ ፡ ልጅ - - በሷ ፡ ቤት ፡ እሷ ፡ ያሰጋሽ ፡ ልጅ ፡ ስለሆነች ፡ የምትበልጥብኝ ፡ መስሏታል - -

አሁን ፡ ለምሳሌ ፡ የትኛዋን ፡ ትመርጣለህ ፡ ብባል ፡ ለሚስትነት - - አላ ገባም ፡ እንጂ ፡ እኔ - - - እውነት ፡ ነው ፡ የትኛዋን ፡ እመርጣለሁ - - ? ሮማን ፡ ድንጉጥ ፡ ነች--ድንጉጥ ፡ ነገር ፡ እኔ ፡ እወዳለሁ ።— ሙዚቃስ ? ሙዚቃ ፡ ደሞ ፡ በጣም ፡ እወዳለሁ ።—ጂወኔ ፡ የሙዚቃ ፡ ሰው ፡ ነች ።— ግንኮ ፡ ሮማን ፡ ድምጼን ፡ ሳይቀር ፡ ወዳዋለች ። አዎ ፡ አዎ ፡ ግን ! ድንቁር ናዋ ፡ ነው ፡ ድምጼን ፡ ያስወደዳት - - ጐርናና ፡ አይደል ፡ በርዳዳ ፡ የኔ ፡ ድምፅ - - ወይ ፡ ደሞ ፡ እንደ ፡ ሌሎቹ ፡ ቃጭል ፡ አይደል ፡ መረዋ ?— አይመስለኝም ፤ የመውደዷን ፡ ያህል ፡ ነው ፡ የተናገረችው - - » እህ ያዋ ፡ እጉድባው ፡ ትገባና ፡ ጠጥታ ፡ ትመለሳለች - - ጠጠር ፡ እያነሣ ፡ ወደ ፡ ኩሬው ፡ ውስጥ ፡ መወርወር ፡ ይጀምራል — እያረፈ — እያ ረፈ — እያረፈ - - ዝም ፡ ብሎ ፡ ይወረውራል — ጠብታ ፡ ትንሽ ፡ ክብ — ትልቅ ፡ ክብ — ትልልቅ — ትልልልቅ — ትልልልልቅ — ትልልልል ልቅ ፡ ክቦች ፡ እየፈጠረ ፡ ይጠፉል ።— ሮማን ፡ ትመለሳለች ። ራቅ ፡ ብሎ ፡ ኋላ ፡ ኋላዋ ፡ ተከትሏታል ፡ ጴጥሮስ ።

« - - - እምልሽ - - እምልሽ - - » ይጀምራል ፡ አደፍርስ - - እህያዋ ፡ ብቅ ፡ አለችበት ፡ ድንጋይ ፡ ላይ ፡ ቁጭ ፡ ትልና ፡ ሮማን ፡ እግሮቿን ፡ ወደ ታች ፡ ዘርግታ ፡ ውዝ ፡ ውዝ ፡ እያደረገች ፡ እሱን ፡ እሱን ፡ ስትመለ ከተው « እምልሽ - - እውነት ፡ እውነት - - - አታኮርፊም - - - ?

« - - አላኮርፍም ! » ትመልስለታለች ፤ አንገቷን ፡ ቀና ፡ ፊቷን ፡ ፈገግ ፡ እንደማድረግ ፡ ታፍታታና — በሌላ ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ታይቶ ፡ የማ ይታወቅ ፡ ልዩ ፡ ስጦታ ፡ ያገኘባት ፡ ይመስላታል ።

« አሁን ፡ ለምሳሌ ፡ ጠጋ ፡ ብዬ ፡ እጅሽን ፡ ያዝ ፡ ባደርገው - - -

« ምንቸገረኝ ! ያዙት — ይኸውልዎ - - - ! ያዙት - - - እው ቴን ፡ ነው - - » እያለች ፡ እሱ ፡ ወደ ፡ ተቀመጠበት ፡ ወደ ፡ ባሻገሯ ጠርዝ ፡ ላይ ፡ ትመጣለች ።— አደፍርስ ፡ እግር ፡ እግሯን ፡ ይመለከታል -

« - - እሺ - - ጡትሽንስ ፡ ብነካው ! » ይላታል ፡ በተቻኮለ ፡ አ ጋገር ።—

« ምንቸገረኝ ፡ ታዲያ - - ይንኩት - - ! አላኮርፍም - - ! የሚያ ርፍ ፡ ባሪያ ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ ይላሉ ፡ እመዬቴ - - ! ይኸውልዎ ፡ ይንኩት - - ትለዋለች ፡ አንገት ፡ ልብሷን ፡ ገለጥ ፡ ታደርግና ።— ሲፈራ ፡ ሲቸር ቁስል ፡ የሚነካ ፡ ይመስል ፡ ይነካዋል « አይዞዎ ፡ ይንኩት - - እያመ ምኮ ፡ እስከዚህ - - ይንኩት - - -

ጴጥሮስ፡ሰውነቱ፡ሁሉ፡ይለዋወጣል ።—ከመ፡ቅጽበት፡እየሮጠ፡ ይወጣና፡አቀበቱን፡ለጂወኔ፡ይነግራታል ።-ከተልም፡ይላትና፡ወደ፡ ጉድባው፡እሚወስደው፡መንገድ፡ስትገባ፡ከኋላዋ፡ሹልክ፡ብሎ፡ወደ፡ ወርዶፋ፡ሥምሪት፡ይሮጣል ።— ለሱ፡ደሞ፡ለመንገር ።—

« --እግሮቼ፡ቆንጆ፡አልሆኑም ? » ትጠይቀዋለች፡ሮማን፡በተ ራዋ፤ባንድ፡እጅዋ፡አንድ፡እግሯን፡አሸት፡አሸት፡እያደረገችና፡ ተረከዟን፡ሽቅብ፡እየገለበጠች ።—

« - - - እምልሽ - ለምሳሌ — ይኸ፡እየውሃው፡ዳር፡ያለው፡ ሜጣን፡ያገኘሽስ፡እንደሁ - - -

« አያገኘኝም - - - !

« ጡትሽን፡ንክስ፡ነው፡የሚያደርገው - - -

« ጡት ? ጡት፡አይነካም፡እሱ - - ! ልጃገረድ፡ይተናኮላል፡ ነው፡የሚባለው፡እንጂ፡ጡት፡አይነካም ።— አሁንኮ፡ግመሬ፡ ዝንጀሮም፡ቢሆን፡ይተናኮላል ።— ወንድና፡ሴት፡ወንድና፡ሴት፡እየ ሆንን፡ነው፡ሥምሪት፡የምንውለው - - -

« - - ወንድና፡ሴት፡ስትሆኑ፡አይነካችሁም - - - ?

« ወንዱ፡ከሴቷ፡አጠገብ፡ካልተለየ፡አይነካም - - ግን፡በተ ለይ፡ሲመሽ፡መጠንቀቅ፡ያሻል፡ይባላል ።— ወይ፡ወገቡን፡ለመዛ ወር፡ወይ፡ለሽንቱ፡ወረድ፡ያለ፡ጊዜ፡ወንዱ፡ያነዬ፡ነው፡እማማው፡ ላይ፡ወጥቶ፡የሚደፍራት - - አሁን፡በቅርቡ፡እንዲን፡እንዲህ፡ አበላሽቷታል፡ተብሎ፡ይወራ፡ነበር - - - አዎ፡እንጨት፡ሰበራም፡ ብቻችንን፡አንሄድም - - - !

ጡቶቿን፡ነካ፡ነካ፡ማድረግ፡ይጀምራል፡እንደገና፡አደፍርስ ።— ሮማን፡እግሮቿን፡እጥፍ፡ዘርጋ፡ታደርጋለች ።— ጂወኔ፡ሁኔታቸውን፡ አየት፡ታደርግና፡ምንም፡ያህል፡ሳትቆይ፡ወደ፡ቤቷ፡ትመለሳለች ።-

« ሰውስ፡አልፎ፡አልፎ—እምልሽ፡እረኞች፡ገበሬዎች - - ሊያ ንቋችሁ፡አይሞክሩም - - - ?

« አሄሄ . . . አይደፍሩም - - ማን፡በጅ፡ቢላቸው - - እንሚሟታ ለኒ - - ማን፡በጅ፡ቢላቸው - - » ብድግ፡ብላ፡ወደ፡ጉድባው፡ ውስጥ፡ትገባለች ።—ገምቦዋን፡ትሞላና፡ተሸክማ፡መንገድ፡ትገ ባለች « ስመለስ፡ደሞ፡እንጫወታለን » ትለውና ።—

ጴጥሮስ ፡ ለወርዶፋ ፡ ይነግርና ፡ ቀድሞት ፡ ሲሮጥ ፡ ይመለሳል ፡ ወደ ፡ ጉድባው ።— ሮማንን ፡ ወደ ፡ ቤት ፡ ስትመለስ ፡ ያያታል - - - ቆም ፡ ይላል ፡ ላንዳፍታ ።—ድንጋይ ፡ ያነሣና ፡ ወርውሮ ፡ ሮማን ፡ የተሸከመችውን ፡ እንስራ ፡ ያደቀዋል ።—ውሃው ፡ ሰውነቷን ፡ ያጠልቀዋል ።— እንደተደናገጠች ፡ ወደ ፡ ቤቷም ፡ እንደመሄድ ፡ ከጀል ፡ ታደርግና ፡ ግራ ፡ ቀኟን ፡ አየት ፡ አየት ፡ አድርጋ ፡ ወደ ፡ ጉድባው ፡ ትመለሳለች ።— አደፍርስ ፡ ከመቀመጫው ፡ አልተንቀሳቀሰም ።— ሮማንን ፡ ሲያያት ፡ በርግጥ ፡ ይደነግጥና ፡ እቅፍ ፡ እንደማድረግ ፡ እጆቹን ፡ ዘርጋ ፡ አደርጋለሁ ፡ ሲል - - ያልታሰበ ፡ ውርጅብኝ - - ከጁ ፡ ከግሩ — ባንዳፍታ ፡ ያጣድፋታል « - - ሞትና ፡ ሕይወት - - ሞትና ፡ ሕይወት - - ሞትና ፡ ሕይወት - - - » እያለ ፡ ይዘረራል ።—

« - - ሲያንቃት ! ሲያንቃትኮ ፡ ነው - - ! አመልጣለሁ ፡ ብላ ፡ ስትተናነቅ - - ! እንስራው ፡ የተሰበረው - - » እያለ ፡ ይጐዶራል ፡ ወርዶፋም ።—

« - - ነገሩ ፡ አጉል ፡ ሆይኗል ።—ጥንቃቅ ፡ ያስፈልጋል - - ስድ ፡ መልቀቅ ፡ አይሆኑም - - ብያሎህ ፡ በፊት - - » ይናገራል ፡ ጴጥሮስ ፡ በበኩሉ ።—

ሮማን ፡ ድንገት ፡ አጠገቡ ፡ መጥታ ፡ እንደዚያ ፡ ሆና ፡ ስትቆም ፡ የነበረው ፡ ጸጥታ - - ወዲያው ፡ ከመቅጽበት ፡ የተነሣው ፡ ውካታ — ሾፉ — ቀልድና ፡ ለገቻው - - - ከከበቡት ፡ መካከል ፡ አንደኛው ፡ ቀረብ፡ ይልና ፡ እጅ ፡ የሚነሣው ፡ መስሎ ፡ ጐንበስ ፡ በማለት ፡ ከመሬት ፡ ሲደባልቀው ፡ የነበረው ፡ ሁኔታ - - ወዲያው ፡ ሩምታው - - ቻቻታው ፡ መሬት ፡ እንደዘረጉት ።— አረግ ፡ መሳይ ! አረግ ፡ መሳይ ! አረግ ፡ መሳይ ! — አዎ ! እሠረው ! እሠረው ! — በጅራፉ ፡ ለምን ፡ አታሥረውም ? በጅራፉ ፡ እሠረው - - ! ጥድፊያቸው ፡ ትርምሳቸውና ፡ ጩኸታቸው ፡ በሙሉ - - ራሱን ፡ ያስዘነጋዋል ፡ ላንዳፍታ ፡ አደፍርስን ። —አቧራና ፡ ትቢያ ፡ እየቃመ ፡ ታሥሮ ፡ ሞትና ፡ ሕይወትን ፡ ባፉ ፡ እንዳንጠለጠለ ፡ ይወሰዳል ፡ ወደ ፡ ወይዘሮ ፡ አሰጋሽ ፡ ዘንድ ።—

እየተንቻቹ ፡ ሲመጡ ፡ ሲሰሙ ፡ ብቅ ፡ ይላሉ ፡ ወይዘሮ ፡ አሰጋሽ ፡ እደጅ « - - የትኛውን ፡ ነዶ ፡ ሲሰርቅ ፡ ነው ፡ የያዛችሁት ፡ ይኸን ፡ ደሞ - - ቀልባጣ ፡ ውላጅ - - - አሰጋሽ ፡ ዋዛ ፡ መስላዋለች » እያሉ ።— ወዲያው ፡ እሥረኛው ፡ እፊታቸው ፡ ይገፈተርና ፡ ይቆማል ።— እሥረኛ

ይቱ ፡ እፊታቸው ፡ ትገፈተርና ፡ እሥራቸው ፡ ትደፋለች « - - ምንድ ነው ፡ ነገሩ ! »ይጮሃሉ ፡ ወይዘሮ ፡ አሰጋሽ - - ዙሪያቸውን ፡ ገልመጥ ፡ ያደርጉና « - - ወሂዱልኝ ፡ ካጠገቤ - - ! » ሠራተኛው ፡ ሁሉ ፡ ወደ ፡ የሥርቻው ፡ ይገባል ። ጆሮዋን ፡ እያልመዘመዙ ፡ ያዝ ፡ በማድረግ ፡ አን ገቷን ፡ አስግገው ፡ ያስነሥዋትና ፡ ወደ ፡ እልፍኛቸው ፡ ሲያዳፏት« - -እ ንተ ፡ ወርዶፋ - - ወርዶፋ ! » እያሉ ፡ በመዝናናት ፡ አየር ፡ መለስ ፡ ይሉና ፡ በመጥራት « - - አሁን ፡ ውረድና ፡ ምናሳባለን ፡ ጥራልኝ - - ! እ ንትፍ ፡ ያልኳት ፡ ምራቂ ፡ ሳትደርቅ ፡ እንድትደርሽ ፡ ተብለሻል ፡ በላት ! ይኸው - - »እንትፍ ፡ ይሉና « - - እንትፍ ፡ ያልኳት ፡ ሳትደርቅ ! » ወደ ፡ እልፍኛቸው ፡ ይገባሉ ። ምናሳባለ ፡ ባገሩ ፡ የታወቀች ፡ የልጃገረድ፡ ክብር ፡ ያለ ፡ ወይም ፡ የሌለ ፡ መሆኑን ፡ መርምራ ፡ የምትናገር ፡ ጥሩ ፡ መድኀኒተኛ ፡ ነች ።—

« - - በያ ፡ እንግዲህ ፡ እንስማው ! » ይላሉ ፡ ወይዘሮ ፡ አሰጋሽ ።— እትራሳቸው ፡ የተሰቀለውን ፡ ቁርዝ ፡ አውርደው ፡ ሁለት ፡ ሦስት ፡ ጊዜ፡ ካሳረፉባት ፡ በኋላ ፡—እንስማው ፡ እንጂ - - ! እንስማው - - እንስ ማው - - ! » ይደጋግሟታል ፤ የምትበስል ፡ የምትበስልበትን ፡ ቦታ ፡ እየመራረጡ « - - እንስማው - - ! እንስማው - - - !

# ፳፬

« - - አንተ ፡ መቼም ፡ ብልግና ፡ ትሠራለህ ፡ ብዬ ፡ አይደለም ! » ይናገራሉ ፡ አቶ ፡ ወልዱ ፡ በበኩላቸው ፡ አደፍርስ ፡ ሰውነቱን ፡ ከተጣጠበ ፡ በኋላ ፡ ካፕር ፡ ውጪ ፡ ወጥተው ፡ ሲሄዱ « - - ቢሆንም ፡ ግን - - ቢሆንም - - ያገሬውን ፡ ጠባይ ፡ ማወቅ ፡ ነበረብህ! - - አዎ ፡ ከዚህ ፡ በተሻለ ፡ መንገድ ፡ መያዝ ፡ ነበረብህ ፡ እነሱን - - ሠርጓ ፡ በመደገስ ፡ ላይ ፡ ካለ ፡ ልጃገረድ ፡ ጋር ፡ ጨዋታም ፡ ቢሆን ፡ እንኳ ፡ ቢቀርብህ፡ መልካም ፡ ነበር - -

« አውሬ ! አውሬዎች ፡ ናቸው ፡ እነሱ ፡ አቶ ፡ ወልዱ - - ሰዎች ፡ አይደሉም - - » ይናገራል ፡ አደፍርስ ፡ ያመቀውን ፡ አየር ፡ በማስወጣት « አውሬ ፡ ያውቃሉ - - ? ከነሱ ፡ የባሰ ፡ አውሬ ፡ የለም - - -

« - - ዐውቀሃቸው ፡ ቢሆን ፡ ኖሮኮ ፡ እስከዚህ ፡ ባልተናደድህ - - ተፈጥሯቸው ፡ ነው ፡ አደፍርስ ።— በነሱ ፡ ቤት ፡ አሁን ፡ ትክክለኛ ፡ ተግባራቸውን ፡ ማሳየታቸው ፡ ነው ። መሰላችሁ ፡ እንጂ ፡ ምንም ፡ ያደረግሁት ፡ ነገር ፡ የለም ፡ ብትላቸው - - ሌላው ፡ ቀርቶ ፡ አባ ፡ አዲሴ ፡ እንኳን ፡ እንዲህ ፡ ቢነግሯቸው ፡ አይሰሙም - - አይቀበሉም ።— ምናሳባለ ፡ ብቻ ፡ ነች ፡ አሁን ፡ ዳኛዋ - - -

« - - - እኔ ፡ ደሞ ፡ እንዴት ፡ በሐሳብ ፡ ልረዳው ፡ ሞከርሁ ፡ ይመስልዎታል ፡ ወርዶፋን - - - እንዲሻሻል ! አምልኮ ፡ ባዕዱን ፡ እንዲተው ፡ ልጁንም ፡ እንዲያስተምር - ስንት ፡ ነገር ፡ ይመስልዎታል ፡ ያጫወትሁት - - ሥራ ፡ እንኳን ፡ አስገባሃለሁ ፡ ብዬው ፡ ነበር - - በዚህ ፡ በዋሽንት ፡ ጨዋታው - - -

« - - ይግባህ ፡ አደፍርስ - - እነሱ ፡ ያንተ ፡ ሐሳብ ፡ ምናቸውም፡ አይደል ። —የሚጠጡት ፡ የሚበሉት ፡ የሚያዩት ፡ የሚጨብጡት - - ይኸ ፡ ይኸ ፡ ነው ፡ እውነታቸው ፡ ለነሱ ! አንተ ፡ የሰጠሃቸውን ፡ ተስፋ ፡ እንደ ፡ ሰማይ ፡ ላም ፡ አለኝ ፡ ነው ፡ የሚቆጥሩት - - ቢሆንም ፡ ባይሆን ፡ ግድ ፡ የላቸውም - - -

« ግድ ፡ የላቸውም - - - ?

« አዎ ፡ ግድም ፡ የላቸው - - -

# ፳፫

# አደፍርስ

« ፓሪ ፡ በነበርኩ ፡ ጊዜ ፡ ፍሊጶስ ፡ እንለው ፡ ነበር ፤ እንደ ዚሀ ፡ እንዳንተ ፡ ዓይነት ፡ አስተሳሰብና ፡ የነገር ፡ አካሄድ ፡ የነበረውን - - ታሪክ ፡ መቼም ፡ ተምረሃልና ፡ ሳታውቀው ፡ አትቀርም ፡ ፍሊጶስን - - -

« ፍሊጶስ ! ፍሊጶስ - - ! ትዝም ፡ አይለኝ - - » ለማስታወስ ፡ ይሞክራል ፡ አደፍርስ ።

«እንግዲያው ፡ እኔ ፡ እነግርሃለሁ - - » ብለው ፡ ይጀምራሉ ፡ አቶ ፡ ወልዱ « - - ፍሊጶስ ፡ የማሪትሬዛ ፡ ልጅ ፡ የኦስትሪያ ፡ ንጉሥ ፡ ነበር - - ማሪትሬዛን ፡ ታውቃታለህ ፡ መቼም — ይኸ ፡ ብሯ ፡ እኛ ፡ አገር ፡ ድረስ ፡ ዘምቶ ፡ ሥር ፡ የሰደደው - - ?

« አዎ ፡ ስለ ፡ እሷ ፡ ሰምቻለሁ - - !

« ይኸውልህ ፡ እንግዲያው ፡ የማሪትሬዛ ፡ ልጅ ፡ ነው ።— እንደ ዚሀ ፡ እንደናንተ ፡ እንደ ፡ ዘመኑ ፡ ልጆች ፡ ነፃነት ፡ ዕሪና ፡ (እኩልነት) ፡ ወንድማማችነት ፡ በሚሉት ፡ የሰው ፡ ልጆች ፡ ምናብ ፡ ያምን ፡ ነበር ።— እናቱ ፡ ማሪትሬዛ ፡ በዘጠና ፡ ዘጠኝ ፡ ዓመቷ ፡ ነው ፡ ይባላል ፡ የሞተችው ።— እንግዲህ ፡ አስበው - - ዘጠና ፡ ዘጠኝ ፡ ዓመታት ፡ ስትኖር ፡ ስንት ፡ ዓይ ነት ፡ ያገዛዝ ፡ ያመራር ፡ የሥልጣን ፡ መጨበጫ ፡ ክንዶች ፡ እንደነበሯት ።— የምትሰጠው ፡ ሹመት ፡ ከልጅ ፡ ልጅ ፡ የሚተላለፍ ፡ ነበር ።— አባቱ ፡ መስፍን ፡ የነበረ — ልጁም ፡ መስፍን — አባቱ ፡ ድሃ ፡ የነበረ—ልጁም ፡ ድሃ ፡ ነበር ። ሕዝቡም ፡ ተደስቶ ፡ ነበር ፡ የሚኖረው ፤ የበታች ፡ ለበ ላዩ ፡ ታዞ ፡ የበላይም ፡ የበታቹን ፡ አንቀጥቅጦ ።— ፍሊጶስ ፡ እንግዲህ ፡ በዕሪና ፡ መንፈስ ፡ ተነሣሣልህና ፡ የበታችና ፡ የበላይን ፡ ርብራብ ፡ አጥ ፍቶ ፡ አንድ ፡ ሊያደርግ ፡ አቀደ ።—ልክ ፡ እናቱ ፡ እንደ ፡ ሞተች ፡ መሳፍን ቱንና ፡ መኳንንቱን ፡ እቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ ጋበዘ ።—ከግብዣውም ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ የመጡበት ፡ እንዳይመለሱ ፡ በቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ ውስጥ ፡ ዘጋባቸ ውና ፡ ርስትና ፡ ሀብታቸውን ፡ ለየበታቾቻቸው ፡ ከፋፈለው ።—የናቴ ፡ ቅል ቦች ፡ ነበር ፡ ይባላል ፡ የሚላቸው ፡ ሲጠራቸው ።—ምን ፡ ሆነ ፡ ይመስልሃል፡

ታዲያ ? 'ኤጋሊቴ' — 'ፍራቴርንቴ' — 'ሊቤርቴ' — የሚባል ፡ ምናብ ! — በየክፍያውም ፡ ትክክለኝነት ፡ ስላልነበረ ፡ ትንሽና ፡ ትልቅ ፡ ተፈጠረ ፡፡— ፍሊጶስ ፡ የፈጠራቸው ፡ ትልቆች ፡ ማሪትሬዛ ፡ ከፈጠረቻቸው ፡ ትልቆች ፡ ባሱ ፡፡ ሕዝቡን ፡ ገፈፉት ፡ አሰቃዩት — መሳፍንታችንንና ፡ መኳንንታችንን ፡ ልቀቅልን ፡ ብሎ ፡ አቤት ፡ ሊል ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ መጣ ፡፡ — ፍሊጶስን ፡ ሊገባው ፡ አልቻለም ፡፡ — ከዕሪና ፡ ይልቅ ፡ የተበላልጠ ፡ ኑሮን ፡ የመረጡበትን ፡ ምክንያት ፡ ጠየቃቸው ፡፡ — ዘረ ፡ ድሆች ፡ ስለሆንን ፡ ድህነቱን ፡ ችግሩን ፡ መራቡን ፡ መጠማቱን ፡ መገረፍ ፡ መታሠሩን ፡ ( ምደነዋል — አይሰማንም ፡፡ — የሚሰማቸውን ፡ ጌቶቻችንን ፡ ግን ፡ ባልለመዱት ፡ ሁኔታ ፡ ተይዘው ፡ ሲሠቃዩ ፡ ማየት ፡ ስለማንሻ ፡ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ነው ፡ ብለው ፡ መለሱለት - - - 'ኤጋሊቴ' ብሎ ፡ ነገር ! ምን ፡ አለ ፡ ይመስልሃል ፡ ታዲያ ፡ ፍሊጶስ - - ? ባለመማራችሁ ፡ ነው ፤ ቀስ ፡ እያለ ፡ ይገባችኋል — አስተማሪ ፡ እንልክላችኋላን ፤ ተማሪ ፡ ቤት ፡ እንከፍትላችኋለን - - ! አስተማሪም ፡ ትምህርት ፡ ቤትም ፡ አንፈልግም ፤ የምንፈልገው ፡ ጌቶቻችንን ፡ ነው ፡ ብለው ፡ መለሱለታ - - ጋዳ ፡ ማን ፡ ሰምቶ ፡፡ ፍሊጶ ፡ በዕሪና ፡ ምናብ ፡ ተታኳልና ፡ ሳይቀበላቸው ፡ ቀረ ፡፡— ምን ፡ ሆነ ፡ ይመስልሃል ፡ ታዲያ ? — አንድ ፡ ቀን ፡ ሌሊት ፡ እነዚሁ ፡ ባላገሮች ፡ ይመጡና ፡ ባላባቶቹ ፡ የታሠሩበትን ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ መውረር ፡ ነዋ ! ! ወረሩት ! እርግጥ ፡ ዘበኞቹም ፡ ይነቁባቸዋል ፤ ብዙዎች ፡ ባላገሮች ፡ ያልቃሉ — ግን - - አሁን ፡ ትክክለኛ ፡ ቁጥሩን ፡ ረሳሁት ፡ ብቻ - - - ሦስት ፡ ይሁን ፡ አራት ፡ መሳፍንት ፡ ያመልጣሉ - - - በዚህ ፡ ሁሉ ፡ ትርምስ ፡ መካከል — ቀላል ፡ ነው ፡ እንደምታየው — ወገበ ፡ ቀላል ፡ ሆኖ ፡ ከተገኙ — እና ፡ በእነዚሁ ፡ ባመለጡት ፡ መሳፍንት ፡ እየተመሩ ፡ ፍሊጶን ፡ መጠዝጠዝ ፡ ጀመሩታ ፡ አገሬው ! አልቻላቸውም ፤ የቀሩትን ፡ መሳፍንትና ፡ መኳንንት ፡ ሁሉ ፡ እንዲፈታ ፡ አስገደዱት - - የሚገርም ፡ ታሪክ ፡ ነውኮ ? እንዴት ፡ ሳትማረው ፡ እንደቀረህ ፡ አላውቅም - - -

« ሳልማረው ፡ እንኳ ፡ ቀርቼ ፡ አይደለም - - ብቻ ፡ በጊዜው ፡ አላጤንኩትም - - -

« - - እና ፡ ይኸውልህ ፡ ፍሊጶንም ፡ ካገር ፡ አገር ፡ ሲያሳድዱት ፡ ይመስለኛል ፡ በግዞት ፡ ሞተ ፡ እልሃለሁ - - ለመሐይምን ፡ ሕዝብ ፡ ደግ ፡ የማሰብና ፡ የመሥራት ፡ ዋጋው - -

« በእርስዎ ፡ አስተያየት ፡ ታዲያ ፡ የኢትዮጵያም ፡ ሕዝብ ፡ ከዕሪና ፡ ይልቅ ፡ የተበላልጦ ፡ ኑሮን ፡ ነው ፡ የሚመርጠው ፡ ነው ፡ የሚሉት - - ?

« የተበላልጦን ፡ ኑሮ ፡ ብቻ ፡ አይደለም ።— ከነፃነትም ፡ ደልዳ ልነትን ፡ የበለጠ ፡ ይመርጣል ፡ ባይ ፡ ነኝ - - - ያላሳብ ፡ ያለሥጋት ፡ እንዳሰኘው —እንቅልፍም ፡ ቢሆን ፡ ሥራም ፡ ቢሆን ፡ የፈለገውን ፡ እያደረገ ፡ የሚኖርበትን ፡ የጸና ፡ ደልዳልነት ፡ ነው ፡ የሚመርጠው — 'ሊቤርቴ' ምንድነው - - 'ሴኩሪቲ' ይሻለዋል ፡ እውንም - - - ! ለኢት ዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ነፃነት ፡ የሚለው ፡ ቃል ፡ ደልዳልነትን ፡ የሚነካ ፡ የሚ ያቃውስ ፡ ከሆነ ፡ ትርጉም ፡ የለውም ።—በሚስትህ ፡ በንብረትህ ፡ በሃይ ማኖትህ ፡ የሚሉት ፡ ቃላት — የደልዳልነት ፡ ምልክቶቹ ፡ ናቸው ።— ነፃነት ፡ ዕሪና ፡ ወንድማማችነት ፡ የፈረንሳዎች ፡ የነፃነት ፡ ምልክቶች ፡ እንደነበሩ ፡ ዓይነት ።— ምናልባት ፡ ደልዳልነቱን ፡ ካልነካችሁበት — ወንድማማችነቱም ፡ እንግዳ ፡ በማስተናገድ ፡ ባህሉ ፡ ውስጥ ፡ ያለ ፡ የነ በረ ፡ ስለሆነ ፡ እንደ ፡ አዲስ ፡ ግንጥል ፡ ጌጥ ፡ ስለማይቆጥረው ፡ ይቀበለው፡ ይሆናል ። — ዕሪናውንም — ሰው ፡ በእግዚአብሔር ፡ አምሳል ፡ ስለተ ፈጠረ ፡ በፈጣሪው ፡ ፊት ፡ እኩል ፡ ነውና ፡ የእኩልነቱን ፡ ሁኔታ ፡ ሃይ ማኖቱን ፡ አስታኮ ፡ ካስተማሩት ፡ እንደ ፡ አዲስ ፡ ግንጥል ፡ ጌጥ ፡ ስለማ ይቆጥረው ፡ ይቀበለው ፡ ይሆናል ።— ነፃነቱንም ፡ የራስህ ፡ የምትለው ፡ ነገር ፡ እንዲከበርልህ — ሌላ ፡ ሰው ፡ የራሴ ፡ የሚለውን ፡ ነገር ፡ ማክበር ፡ ይኖርብሃል ፡ ማለት ፡ ነው ፤ የራስክን ፡ ርስት ፡ ይዘህ ፡ የሌላ ፡ ሰው ፡ ርስት ፡ ደግሞ ፡ ከሻህ ፡ የራስክን ፡ ንብረት ፡ አስፋፍተህ ፡ የሌላን ፡ ሰው ፡ ንብረት ፡ ከደፈርክ ፡ የነፃነት ፡ ጠላት ፡ መሆንህ ፡ ነው - - ብለው ፡ ካስ ረዱት ፡ እንደ ፡ ግንጥል ፡ ጌጥ ፡ ስለማይቆጥረው ፡ ይቀበለው ፡ ይሆናል።— ስለዚህ ፡ እናንተ ፡ የዘመኑ ፡ ልጆች ፡ በተለይ ፡ ስለ ፡ ነፃነት ፡ ስታወሩ ፡ ያል ታየ ፡ ያልነበረ ፡ ካስመሰላችሁት ፡ ያላዩት ፡ አገር ፡ አይናፍቅምና ፡ እን ኳን ፡ ሐሳባችሁን ፡ ሊቀበሏችሁ ፡ እናንተንም ፡ እንደ ፡ እብድ ፡ ቆጥረው፡ ከኅብረተ ፡ ሰቡ ፡ ውጭ ፡ ሊያደርጓችሁ ፡ ቢፈልጉ ፡ አይገርምም ።— ወሰን ፡ የሌለው ፡ ነፃነት ፡ ነፃነት ፡ ያለመሆኑን ፡ በሥራ ፡ ሊታይ ፡ የማይ ችል ፡ የምናብ ፡ ነፃነት ፡ የሕልም ፡ ሩጫ ፡ ዓይነት ፡ ነገር ፡ መሆኑን ፡ እናን ተም ፡ ጭምር ፡ እንድታውቁት ፡ ያሻል - - -

« እኮ ፡ እርስዎኮ ፡ አሁን ፡ የሚሉት ፡ ባጭሩ —ሮም ፡ ስትሄዱ ፡ እንደ ፡ ሮማውያን ፡ ሁኑ ።—በእግር ፡ መሄዳቸውን ፡ ትተው ፡ በእጅ ፡ ሲድሁ ፡ ብታገኟቸው ፡ እናንተም ፡ በእጃችሁ ፡ ዳሁ ።—ቁንጣን ፡ እስኪይዛችሁ ፡

በልታችሁ ፡ በመንገድ ፡ ስትንሸረሸሩ - - ያጋጣሚ ፡ ነገር ፡ አንድ ፡ ምስኪን ፡ ድሃ ፡ ረኀብ ፡ ይዞት ፡ ሲፈራገጥ ፡ እንደ ፡ እናንተው ፡ በዚያው ፡ በኩል ፡ የምታልፍ ፡ አንዲት ፡ ሴት ፡ ጉርሻ ፡ እንጀራ ፡ ስትሰጠው ፡ ብታዩና - - ቢጐርሰው ፡ ከመሞት ፡ እንዲድን ፡ ብታውቁም ፡—ከጁ ፡ መንጭቃችሁ ፡ ራሳችሁ ፡ ጉረሱትና ፡ ብትፈልጉ ፡ መልሳችሁ ፡ አስወጡት - - አይደለም ? - - ሌላው ፡ ሐሳብዎ ፡ ደግሞ ፡ በባህላችን ፡ ውስጥ ፡ መሰል ፡ ካልተገኘለት ፡ በስተቀር ፡ አዲስ ፡ የሥልጣኔ ፡ አካሄድ ፡ አስፈላጊ ፡ አይደለም ፡፡— ቢያስፈልግም ፡ ሕዝቡ ፡ ስለማይቀበለው ፡ መግባት ፡ የለበትም - - በግድ ፡ መግባት ፡ አለበት ፡ ብትሉም ፡ እንደ ፡ ፍሊጶ ፡ መውደቂያ ፡ ታጣላችሁ ፡ አይደለም - - - ?

«አነጋገርህ ፡ ሁሉ ፡ የጐድን ፡ የጐድን ፡ ሆነ ፡ እንጂ ፡ በልብህ ፡ ዋና ፡ ዋናውን ፡ ነገር ፡ ሳትይዘው ፡ የቀረህ ፡ አይመስለኝም - - እና ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ ደግሞ ፡ እንድታውቀው ፡ የምፈልገው ፡ እኔም ፡ በዘመኔ ፡ የፈረንሳይ ፡ ተማሪ ፡ እየተባልሁ ፡ እንዳጉል ፡ ፍጥረት ፡ ስታይ ፡ የኖርሁ ፡ መሆኔን ፡ ነው ፡፡ ጨርሶ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ትምህርት ፡ ከሌላቸው ፡ አንዳንድ ፡ ሰዎች ፡ ይልቅ ፡ እኔ ፡ ፍላጐታችሁና ፡ ዐላማችሁ ፡ የሚገጥማችሁም ፡ መሰናክል ፡ በይበልጥ ፡ ሳይሰማኝና ፡ ሳይታየኝ ፡ አይቀርም - - እና ፡ የልቤን ፡ ለልቤ ፡ እንዳጫወትሁ ፡ ያህል ፡ ነው ፡ ያጫወትሁህ - - -

« እሱ ፡ ይገባኛል ፤ መጽሐፍ ፡ ካስተማረውም ፡ ኑሮ ( ግብረ ፡ ግበት ) ያስተማረው ፡ መብለጡን ፡ ዐውቃለሁ ፡፡—የመጽሐፍ ፡ ትምህርት ፡ ከደም ፡ ጋር ፡ ተቀላቅሎ ፡ ነፍስን ፡ ስሎ ፡ በመግባት ፡ ወደ ፡ አንድ ፡ ዓይነት ፡ እምነትነት ፡ እስኪለወጥ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ይፈጃል - - በአእምሮ ፡ ውስጥ ፡ መጠራቀሙ ፡ ብቻ ፡ ዋጋ ፡ ሊሰጥ ፡ አይገባውም ፡፡— የሆነው ፡ ሆኖ ፡ ሊገባኝ ፡ ያልቻለው ፡ ለምን ፡ እንደሆነ ፡ አላውቅም ፡ የእምነትዎ ፡ ጽናት ፡ ነው - - -

«ሰማሆይ ፡ አደፍርስ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ለደልዳልነት ፡ ኑሮ ፡ የሚያስፈልገው ፡ ሁሉ ፡ አለው ፤ ዘመናዊው ፡ ነገር ፡ እንኳ ፡ ሳይቀር ፡፡— ተመልከት—ሌላው ፡ ዓለም ፡ እንደ ፡ ፈረንሳይ ፡ መንግሥት ፡ ዓይነቱ ፡ ለምሳሌ ፡ በብዙ ፡ ደም ፡ መፋሰስ ፡ ያገኘው ፡ ቤተ ፡ መማክርት ፡ እንኳ ፡ ሳይቀር - - -

«እንግዲያው ፡ ልንገርዎት ፡ ካመጡት ፡ አይቀር - - የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ መማክርት - - ደም ፡ ስላልፈሰሰለት ፡ ነው ፡ ሕዝቡ ፡ በየጊዜው ፡ በሚያ

ደርገው ፡ የእንደራሴዎች ፡ ምርጫ ፡ ግዴለሽነቱን ፡ የሚያሳየው ፤ ቢመርጥ ፡ ባይመርጥ ፡ ቤት ፡ መማክርቱ ፡ ቢኖር ፡ ባይኖር - - ግዴለውም ።— ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ብቻ ፡ ይኑሩለት ። — ሌላው ፡ ሁሉ ፡ ትርፉቻ ፡ ነው ።— ነገር ፡ ግን ፡ በውነት ፡ ነው ፡ የምልዎት ፡ ደሙን ፡ አፍሶለት ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ ፡ የመምረጥ ፡ መብቱን ፡ ተጠንቅቆ ፡ ነበር ፡ የሚጠቀምበት ።—ስለሚመርጣቸውም ፡ ሰዎች ፡ ብዙ ፡ ድካምና ፡ የግል ፡ ጥናት ፡ ያደርግ ፡ ነበር ።—መቼ ፡ እንዲህ ፡ እንዲያው ፡ እንደ ፡ ግብር ፡ ይውጣ ፡ ነገር - - -

«ይኸኮ ፡ ነው ፡ አደፍርስ ! የመሐይምን ፡ ሕዝብ ፡ መሪ ፡ መሆን ፡ ችግሩ - - ባንዱ ፡ መልኩ ፡ ሲጠቅም ፡ በሌላው ፡ መልኩ ፡ ይጐዳል ።— መሐይምን ፡ ሕዝብ ፡ ከንጉሡ ፡ የሚፈልገውንም ፡ ሆነ ፡ ለንጉሡ ፡ የሚያደርገውን ፡ አያውቅም ።— ነጭ ፡ ኑግ ፡ ጥቁር ፡ ወተት ፡ መግበኝ ፡ ይላል ። ሌላው ፡ ቀርቶ ፡ ከስንፍናው ፡ የተነሣ ፡ ቢርበውና ፡ ቢጠማው ፡ ኑሮውን ፡ ማሸነፍ ፡ ቢያቅተው ፡ ወይም ፡ ደሞ ፡ የፀሐይ ፡ ግለት ፡ ቢያስቸግረውና ፡ ድካም ፡ ቢጫነው ፡ ወይም ፡ ደሞ ፡ ዝናብ ፡ አልዘንብ ፡ ብሎ ፡ ድርቀት ፡ ቢያጠቃው ፡ በንጉሡ ፡ ነው ፡ የሚያመካኘው ።— በንጉሡ ፡ ነው ፡ የሚያዝነው ።— እውነቴን ፡ ነው ፡ የምልህ ፡ ከጥቅሙ ፡ ይልቅ ፡ ጉዳቱ ፡ ነው ፡ የሚያመዝነው ።— ሰማሆይ ! እግዚአብሔርም ፡ ቢሆንኮ ፡ ርዱኝ ፡ ረዳችኋለሁ ፡ ነው ፡ ያለው ።— ራሳችሁን ፡ ርዱ ፡ ማለቱ ፡ ነው ፡ የኔን ፡ ርዳታ ፡ ከፈለጋችሁ ።— ላለው ፡ ይጨመርለታል—ከሌለው ፡ ያለው ፡ ይወሰድበታል ፡ ያለውም ፡ ይኸንኑ ፡ የሚደግፍ ፡ ነው - - ያለው የበለጠ ፡ እንዲኖረው ፡ ስለሚሠራ - - የሌለው - - ስለሚሰንፍ ፡ ስለማይሠራ ።— እግዚአብሔር ፡ የብርቱካን ፡ ገነት ፡ ከሰጠን ፡ በኋላ ፡ እየቀጠፍህ ፡ ለያንዳንዳችን ፡ ባፋችን ፡ ጭመቅልን ፡ ብንለው ፡ ምንኛ ፡ ይከፋው ! በዚያ ፡ ስፋቱና ፡ ምጥቀቱ ፡ እንኳ ፡ ሊያረገው ፡ አይሻም ።— መቼም ፡ እንግዲህ ፡ የምልህ - - እስከ ፡ ዛሬ ፡ አላረገውም ።— ንጉሥማ ፡ ታዲያ ፡ በሰብአዊ ፡ ሰውነቱ ፡ ሰማሆይ ? እንዴት ፡ ይቻለዋል ? ለያንዳንዳችን ፡ አፍ ፡ ብርቱካን ፡ ለመጭመቅ - - አይቻለውም - - -

« እንዴት ፡ አደራችሁ ፡ አቶ ፡ ወልዱ - - አንተስ ፡ ወዳጄ ፡ እንዴት ፡ አደርህ - -» እያሉ ፡ ይገባሉ ፡ አባ ፡ አዲሴ ፤ የወይዘሮ ፡ አሰጋሽ ፡ የነፍስ ፡ አባት - - ሁለቱንም ፡ መልከት ፡ መልከት ፡ እያሉ ፡ መስቀል ፡ በማሳለም « ታዲያስ ፡ አንተ ፡ የኔ ፡ ልጅ ፡ ስለዚያ ፡ ስለመጫወቻህ ፡ የነገርኩህን ፡ አሰላሰልከዎይ ? አኮሪዶ ፡ የሚሉት ፡ ነገር - - -

«አንድ ፡ ጨዋታ ፡ ይዘን ፡ ነበር ፡ አባቴ ! ከመጡ ፡ እንዲያውም ፡ ይረዱኛል - - ጥሩ ፡ የጻድቃን ፡ ቀጠሮ ፡ ሆኗል - - -

ትንሽ ፡ ያመነታታሉ « - - ልጄን ፡ እንዴት ፡ አደርሽ ፡ ሳልላት ? ምነው ፡ ድምፅዋን ፡ አልሰማውም ? እቤት ፡ የለች ፡ ይሆን - - - ?

« ጐተራ ፡ ነች ፡ መሰለኝ - - ግዴለም ፡ በኋላ ፡ ያገኟታል ፡ እሷን - - - ስለ ፡ ዘመኑ ፡ ወጣቶችና ፡ ስለ ፡ እኛ ፡ ስለ ፡ ዱሮዎቹ ፡ ሰዎች ፡ ነበር ፡ ጨዋታ ፡ የያዝነው - - -

«ምን ፡ የዛሬ ፡ ልጆች ፡ ዕቡዮች - - ዕልውና ፡ ናፋቂ ፡ ሁሉ - - -

«የለም ፡ እንዲያ ፡ አልነበረም ፡ ጨዋታችን - - እኔ ፡ የምለው ፡ የኛ ፡ ሕዝብ - - የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ - - የሚያምነው ፡ ከኀልያ ፡ ይልቅ ፡ በታምር ፡ ነው - - ነው - - የምለው - - -

«እንዴታ ! ምን ፡ ጥርጥር ፡ አለው ፤ የኀልያ ፡ ሥራ ፡ አዳምና ፡ ሄዋንን ፡ ከመንግሥት ፡ ሰማያት ፡ ያወጣቸው ፡ ነው - - በሙሉ ፡ ልባ ችሁ ፡ በሙሉ ፡ ነፍሳችሁ ፡ እመኑኝ ፡ አለ ፡ እንጂ ፡ ተመራመሩኝ ፡ አላለም ፡ ጌታ ፡ ሕጉን ፡ ሲሰጠን ፡፡— በመመራመር ፡ ፈትሕ ፡ እንደ ማይኖር ፡ ዐውቆት ፡ ነው ፡ የኢትዮጵያም ፡ ሕዝብ ፡ በታምር ፡ የሚያም ነው - - አሁን ፡ ታምረ ፡ ማርያምን ፡ ያነበበ ፡ ሰው - - ታምረ ፡ ሚካ ኤልን - - ታምረ - - -

« - - እኔ ፡ እምለው ፡ ታዲያ - - » አባን ፡ ያቋርጧቸዋል ፡ አቶ ፡ ወልዱ « - - ገና ፡ በታምር ፡ የሚያምንን ፡ ሕዝብ ፡ በግድ ፡ በኀሊያ ፡ እመን ፡ ብሎ ፡ ማስገደድ ፡ አያስፈልግም ፡ ነው - - -

«ለምን ፡ 'ገና' ፡ ይላሉ ፡ እርስዎ ፡ ደግሞ ፤ ገና ፡ አይባልም - - መጀ መሪያውም ፡ መጨረሻውም ፡ የእግዚአብሔር ፡ ታምር ፡ ነው - - 'እነ ፡ ውእቱ ፡ አልፋ ፡ ወኦ' ብሏል ፡ ጌታ ፡ ራሱ ፡ በመለኮትነቱ - - -

« - - ሁለተኛ ፡ ደግሞ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ በ'አታውራቴ' እንጂ ፡ በ'ቮሎንቴ' መተዳደር ፡ ገና ፡ አይችልም ፡ ነው ፡ የምለው - - -

«ልጄን ፡ እንዴት ፡ አደርሽ ፡ ብላት ፡ ይሻላል ፡ መሰለኝ - - ባማር ኛችን ፡ አልተግባባንም - - » ይሉና ፡ ብድግ ፡ እንደማለት ፡ ሲሉ - - -

« የለም ፡ የለም - - ያልኩትኮ ! ሕዝቡ ፡ ገና ፡ በሥልጣን ፡ ጉል በት 'በመባሕት' ፡ እንጂ ፡ ራሱን ፡ በራሱ ፡ ገዝቶ ፡ በፈቃዱ ፡ መተዳደር ፡ አይችልም ፡ ነው - - -

«ይኸም ፡ ጥርጥር ፡ የለውም - - አሁን ፡ የዚች ፡ የኔ ፡ ልጅ ፡ ጭሰኞችና ፡ ገባሮች - - ይኸውና ፡ ራሳቸውን ፡ ማስተዳደር ፡ እያቃታቸው ፡ አይደለም ፡ ከየሚስት ፡ ከየልጆቻቸው ፡ እየገቡ ፡ የሚያድሩላት - - ይኸውና ፡ እንዳያችሁት ፡ ወንዶቹን ፡ ለገበሬነት — ሴቶቹን ፡ ለፈጫይ ፡ ለፈታይነት ፡ ላረም ፡ ለጉልጓሎ—ልጆቻቸውን ፡ ለረኝነት ፡ ለተከታይነት ፡ ለተላላኪነት ፡ እያዋለች ፡ ታስተዳድራቸዋለች - - ማንም ፡ ሳይጠይቃቸው ፡ ንብረታቸውን ፡ እያፈረሱ ፡ ርስታቸውን ፡ ለባላባቷ ፡ እየመለሱ ፡ ነው ፡ መጥተው ፡ የገቡላት - - ምንም ፡ ጥርጥር ፡ የለውም - - መባሕቱን ፡ በሚችለው ፡ ሰው ፡ ሥራ ፡ መተዳደርን ፡ የመሰለ ፡ ሐሳብ ፡ የሌለበት ፡ ኑሮ ፡ የለም - - በራስ ፡ ፈቃድ ፡ መኖር ፡ የሚሉት ፡ ነገር ! እህሉ ፡ ሲሉት ፡ ልብሱ ፡ ልብሱ ፡ ሲሉት ፡ ጨዉ ፡ ጨዉ ፡ ሲሉት ፡ ግብሩ - - ምኑ ፡ ቅጡ - - በየቦታው ፡ ነው ፡ የሚያፈተልከው ፡ የኑሮ ፡ ትብትብ - - መባሕቱን ፡ በሚችለው ፡ ሰው ፡ ጥላ ፡ ሥር ፡ መኖር ፡ ምንኛ ፡ ሐሳብ ፡ መጣል ፡ ነው - - -

« - - - ይኸውልህ ፡ እንግዲህ ፡ እንደምታየው - - ሕዝቡ ፡ በግፈራ ፡ እንጂ ፡ በምናብ ፡ የመኖርን ፡ ደስታ ፡ ገና ፡ አልደረሰበትም - - 'ሬቨ' —ህ . . ! 'ሬቨ' ! ገና ፡ በሕዝቡ ፡ መንፈስ ፡ የለም - - 'ራሳዚዮይ' ብቻ ! »

«አይፈረድበትም ፡ ደግሞም ! መጀመሪያ ፡ የመቀመጫዬን ፡ ተብሏል ! ሰው ፡ ማን ፡ ይመስላል ፡ ቢሉት ፡ የሚበላውን - - -

«ድንቁርናና ፡ ዕውቀት - - - ! በእርስዎ ፡ አስተያየት ፡ እንግዲህ ፡ የማይዋጥ ፡ ነገር ፡ ሲሳይ ፡ አይደለም ፡ ማለት ፡ ነው - - - ?» ይላቸዋል ፡ አደፍርስ ፡ አባን ፡ ወደ ፡ እሳቸው ፡ ድንገት ፡ ዘወር ፡ ብሎ ፡ ንግግራቸውን ፡ ያቋርጥና ።

«የለም ፡ የሚዋጥ ፡ ነገር ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ ሲሳይ ፡ አላሉም ፡ አባ ፤ እንዲያውም - - አብዛኛው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ የሚኖረው ፡ ለምናቡም ፡ ጭምር ፡ ነው - - ደግ ፡ ሠርቼ ፡ እግዚአብሔር ፡ የሚያዘውን ፡ ሁሉ ፡ ፈጽሜ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ገብቼ ፡ እኖራለሁ ፡ በማለት - - አይደለም ፡ እንዴ ፡ አባቴ - - - ? » ጣልቃ ፡ ይገባሉ ፡ አቶ ፡ ወልዱ—ነገሩ ፡ እንዳይካረር ፡ በማሰብ ።

«ዲያብሎስኮ ፡ የመላእክት ፡ አለቃ ፡ ነበር - - ! » ይጀምራሉ ፡ አባ ፡ አዲሴ ፡ ትንሽ ፡ ከፉ ፡ ባለው ፡ ሰው ፡ አንደበት « - - ዛሬስ ፡

ቢሆን ፡ ምን ፡ ይሳነዋል - - ሲያስኘው ፡ እንደ ፡ ብርሃን ፡ መልአክ ፡ ያበራል—ክቡር ፡ ቅዱስ ፡ ለመሆን ፡ የበቁትን ፡ እንኳን ፡ ለማሳሳት ፡ እስኪያበቃው ፡ ድረስ ። መጠን ፡ የሌለውንም ፡ ዓለምና ፡ ተስፋ ፡ በማሳየት ፡ እንደ ፡ ፈጣሪው ፡ ለመሆን ፡ ይቃጣዋል - - ይኸ ፡ ሁሉ ፡ የኔ ፡ ነው ፡ ከኔ ፡ ጋር ፡ ከሆናችሁ ፡ የእናንተም ፡ ጭምር ፡ ነው ፡ በማለት - - በሕልም ፡ በራእይ ፡ ይገለጻል - - - በልቡሰ ፡ ሥጋነት ፡ ይገለጻል - - -

«ልቡሰ ፡ ጥላን ፡ ማወቅን ፡ የመሰለ ፡ ነገር - - -» ሊጀምር ፡ ሲል—

«ቆይ ፡ አንደዜ ፡ አስጨርሳቸው - - -» ይሉና ፡ ያቆሙታል ፡ አቶ ፡ ወልዱ ።

« - - በትንቢት - - ታምር ፡ እንኳ ፡ በማሳየት ፡ ጭምር - - » ይቀጥላሉ ፡ አባ « - - በልዩ ፡ ልዩ ፡ ቅባት ፡ እያማረ ፡ ያናግራቸዋል ፡ የሚቀርቡትን - - የበሽታ ፡ መዐት ፡ በማውረድ ፡ ኅሊናቸውን ፡ በማናወጥ ፡ ነፍሳቸውን ፡ በማሠቃየት ፡ ሕይወታቸውን ፡ ዓላማ ፡ በማሳጣት ፡ እንዲያከብሩት ፡ እንዲፈሩት ፡ እያደረገ - - ራሱ ፡ ስለተረገመ ፡ ሌሎችም ፡ ከሱ ፡ ጋር ፡ አብረው ፡ እንዲረገሙ ፡ ይሻል - - እሱ ፡ የሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ከእንዲህ ፡ ያለው ፡ አሽከርነት ፡ ያውጣህ - - አቡነ ፡ ዘበሰማያት - - »ይሉና ፡ ደግመው ፡ ሲጨርሱ ፡ በመነሣት « ልጄን ፡ እንዴት ፡ አደርሽ ፡ ልበላት - - » ብለው ፡ ወደ ፡ ጐተራው ፡ ቦታ ፡ ያመራሉ ።

## ፳፮

# አደፍርስ

ከትንሽ ፡ ጊዜ ፡ በኋላ ፡ ይመለሳሉ ፡ አባ ፡ ከጕተራው ፡ ቦታ - ከወ ይዘሮ ፡ አሰጋሽ ፡ ጋር ። የናደፍርስ ፡ ተዋሥኦት ፡ ባለመቋረጡ ፡ የተገ ረሙ ፡ በመምሰል—አቶ ፡ ወልዱን ፡ አየት ፡ ያደርጓቸውና ፡ ወደ ፡ እል ፍኙ ፡ ያመራሉ ።—

«ይኸውልህ ፡ እንግዲህ ፡ እንዲህ ፡ ያለውን ፡ በመድምም ፡ የሚ ያምን ፡ ሕዝብ ፡ ነው ፡ በአእምሮ ፡ ልትመራው ፡ የምትሻው - - - በ'ሚስ ቴር' ፡ የሚኖርን ፡ ሕዝብ ፡ ባንደዜ ፡ በ'ሬዞን' ፡ ለማግባባት ፡ መሞ ከር - - የሚሆን ፡ አይመስለኝም ፡ አደፍርስ — የሚሆን ፡ አይመስለ ኝም - - » ይቀጥላሉ ፡ ተዋሥኦታቸውን ፡ አቶ ፡ ወልዱ ።—

«- - - እኔ ፡ የምልዎት ፡ ደግሞ ፡ የሚሆን ፡ ስለማይመስል ፡ ጭራ ሹኑ ፡ አይሆንም ፡ ብለን ፡ ወስነን ፡ እጃችንን ፡ አጣምረን ፡ ቁጭ ፡ ማለት ፡ የለብንም ፡ ነው ።— እኔ ፡ የምለው ፡ ሕዝቡ ፡ ቢወድም ፡ ባይወድም ፡ በግድም ፡ ቢሆን ፡ የተሻለውን ፡ ኑሮ ፡ እንዲያውቅ ፡ መማር ፡ አለበት ፡ ነው - - በየቦታው ፡ ተማሪ ፡ ቤት ፡ መክፈት - - የግንብና ፡ የሳንቃ ፡ ቤቶች ፡ ሳይሆን ፡ ብዙ ፡ የጭቃ ፡ ቤቶች ፡ መሥራት - - - ዘመናዊም ፡ ሆነ ፡ ጥንታዊ ፡ ትምህርት ፡ የተማሩን ፡ መምህራን ፡ መቅጠር ፡ ቢያንስ ፡ ቢያንስ ፡ ሕዝቡን ፡ ማንበብና ፡ መጻፍ ፡ እንዲችል ፡ ማድረግ ።— ከዚያ ፡ በኋላ ፡ የተሻለውን ፡ የኑሮ ፡ አስተሳሰብ ፡ የሚያሳዩ ፡ መጻሕፍትን ፡ አሳትሞ ፡ መበተን - - ! ማን ፡ ያውቃል ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ የሕዝቡ ፡ አስ ተሳሰብ ፡ የቱን ፡ ያህል ፡ እንደሚለወጥ - - -

« - - - ልጆቼን ፡ ለረኅነት ፡ እጠቀምባቸዋለሁ ፤ ለትምህርት ፡ አል ሰጥም ፡ ያለስ ፡ እንደሁ ፡ ሕዝቡ - - ! በአንድ ፡ ሽልንግ ፡ አንድ ፡ መጽ ሐፍ ፡ ከመግዛት ፡ አራት ፡ ብርሌ ፡ ጠጅ ፡ እጠጣበታለሁ ፡ ያለስ ፡ እንደሁ፡ ሕዝቡ - - የጡት ፡ ማስጣያ ፡ ቋንቋዬ ፡ ትግሪኛ ፡ ነው - - ጋልኛ ፡ ነው - - ጉራጊኛ ፡ ነው - - ወላሞኛ ፡ ነው - - ሶማሊኛ ፡ ነው - - - ባማርኛ ፡ የተጻፉ ፡ መጻሕፍትን ፡ አልፈልግም ፡ ያለስ ፡ እንደሆነ ፡ ደግሞ ፡ ጥቂቱ ፡ ሕዝብ - -?

«እኔ ፡ ይኸ ፡ ሁሉ ፡ መሰናክል ፡ ሊሆን ፡ አይችልም ፡ ባይ ፡ ነኝ - - - በጡት ፡ ማስጣያ ፡ ቋንቋቸው ፡ የሚያመካኙ ፡ ቢኖሩ ፡ በማስገደድ ፡ ሳይሆን ፡ ጡት ፡ ማስጣያ ፡ ባልሆነው ፡ ቋንቋ ፡ የሚያጓጓ ፡ ሥራ ፡ ሠርቶ ፡ ሱካር ፡ ጉንዳንን ፡ እንደሚስብ ፡ ዓይነት ፡ እንዲስባቸው ፡ ማድረግ ፡ ያሻል ።— አለዚያ ፡ ብሔራዊ ፡ ቋንቋ ፡ ብሎ ፡ ስም ፡ በመስጠት ፡ ብቻ ፡ አንድ ፡ ቋንቋ ፡ ሊወደድም ፡ ሆነ ፡ ሊያድግ ፡ አይችልም ። — የእንግሊዝን ፡ የፈረንሳይን ፡ የጣሊያንን ፡ የመስኮብን ፡ ቋንቋዎች ፡ ያስወደዷቸውና ፡ ያሳደጓቸው ፡ እንደ ፡ ሸክስፒር ፡ ሞልየር ፡ ሚልተን ፡ ቶልስቶይ ! ዓይነት ፡ ደራስያን ፡ ናቸው ።— በአገራችንም— ከዱሮዎቹ ፡ እነ ፡ ብላቴን ፡ ጌታ ፡ ኅሩይ ፡ አለቃ ፡ ኪዳነ ፡ ወልድ ፡ ክፍሌ ፡ ነጋድራስ ፡ አፈወርቅ ፡ አለቃ ፡ ታዬ ፡ ለአማርኛ ፡ ቋንቋ ፡ እድገት ፡ የተቻላቸውን ፡ ደክመዋል— በዘመናችንም ፡ የተቻላቸውን ፡ ያህል ፡ የሚጥሩ ፡ ብዙዎች ፡ ናቸው - - ሆኖም ፡ ታዲያ ፡ ጥረታችን ፡ እስከዚህ ፡ የሚያጓጓ ፡ አይደለም - - እና— እኔ ፡ የምለው ፡ እንዲያጓጓ ፡ መሆን ፡ አለበት ፡ ነው - - -

«ጡት ፡ ማስጣያ ፡ ቋንቋችንን ፡ ትተን ፡ በሌላ ፡ ቋንቋ ፡ መሠልጠኑ ፡ የጎሣ ፡ ባህላችንን ፡ ያጠፋብናል ፡ ያሉህስ ፡ እንደሁ - - ? ምን ፡ ትመልሳለህ - - - ?

«ቀላል ፡ ይመስለኛል ፡ የዚህም ፡ መልሱ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ ብዙ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ቋንቋዎች ፡ ቢኖሩ ፡ እምብዛም ፡ የዘርና ፡ የባህል ፡ ልዩነት ፡ የለም ።— ለምሳሌ ፡ አማርኛና ፡ ትግሪኛ ፡ ተናጋሪዎችን ፡ ብንወስድና ፡ የሚያምኑባቸውን ፡ የሚመሩባቸውን ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ነገሮች ፡ ብንመረምር ፡ አንድ ፡ ሆነው ፡ እናገኛቸዋለን ።— የጋብቻቸውን ፡ አስተሣሠር ፡ የሃይማኖታቸውን ፡ አስተሳሰብ ፡ የቀን ፡ በቀን ፡ ኑሯቸውን ፡ አካሄድ ፡ ብቻ ፡ መመልከቱ ፡ በቂ ፡ ነው ።— እንግዲህ ፡ የነዚህ ፡ የሁለት ፡ ጎሣዎች ፡ ዘርና ፡ ባህል ፡ ከሌሎች ፡ ጎሣዎች ፡ ዘርና ፡ ባህል— ምናልባት ፡ ልዩነት ፡ ሊኖረው ፡ ቢችልም— በጣም ፡ ትንሽ ፡ ነው - - ስለዚህ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ቋንቋዎች ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ባህል ፡ ያላቸውን ፡ ሕዝቦች ፡ አያመለክቱም ።— ስለማያመለክቱም ፡ ባህላቸው ፡ የተነካ ፡ ሊመስላቸው ፡ አይገባም - - -

«ባንተ ፡ አስተያየት ፡ የቋንቋ ፡ መለያየት ፡ ችግርን ፡ አይፈጥርም ፡ ማለትህ ፡ ነው - - - ?

«አይደለም ፡ ችግር ፡ ሊፈጥር ፡ ይችላል ፤ ለምሳሌ ፡ በትምህርት ፡ በሰሎች ፡ ተጠንቶ ፡ እንደ ፡ ተደረሰበት - - -

«በትምህርት ፡ በሰሎች - - ? ምን ፡ ማለትህ ፡ ነው - - ?

«አ ! የትምህርት ፡ በሰሎች— በልዩ ፡ የትምህርት ፡ ክፍል ፡ ሙያ ቸው ፡ የታወቁ - - 'ኤክስፐርት' ማለቴ ፡ ነው - - -

«'ኤክስፔር ! !' - - ገባኝ - - እሺ - - -

«እና - - በሰሎቹ ፡ እንደሚሉት ፡ አንድ ፡ ሕፃን ፡ ልጅ ፡ አምስት ፡ ዓመቱ ፡ ድረስ ፡ በጡት ፡ ማስጣያ ፡ ቋንቋው ፡ መማር ፡ አለበት ፡ ነው - - አለ ዚያ ፡ እንቶዝ ! ሞኛሞኝ—በሽተኛ ፡ ይሆናል ፡ ነው ፡ ምክንያታቸው ።— ሁለተኛ ፡ ደግሞ ፡ በተለይ ፡ በአሁኑ ፡ ጊዜ ፡ ብሔራዊውን ፡ ቋንቋ ፡ የሚ ናገረው ፡ ሕዝብ ፡ ቁጥር ፡ ስድሳ ፡ ከመቶ ፡ በላይ ፡ ስለማይሆን - - -

«ምን ፡ ማለትህ ፡ ነው ፡ ስድሳ ፡ ከመቶ - - ? ጋልኛና ፡ አማርኛ ፡ ከሚ ናገር ፡ የትኛው ፡ ሊበልጥ ፡ ነው - - - ?

«አማርኛ ፡ ተናጋሪው ፡ ይበልጣል ፤ ምክንያቱም ፡ አማርኛን ፡ የሚ ናገሩት ፡ ጡት ፡ ማስጣያ ፡ ቋንቋቸው ፡ አማርኛ ፡ ያልሆነ ፡ ሁሉ ፡ ስለሆኑ ፡ ነው - - - ጋልኛ ፡ ትግሪኛ ፡ ጉራጊኛ ፡ ወላሞኛ ፡ ሶማሊኛ ፡ የጡት ፡ ማስጣያ ፡ ቋንቋቸው ፡ የሆነ ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ይናገሩታል ።-ባይናገሩትም ፡ ይሰሙታል ።— ሌሎቹ ፡ ቋንቋዎች ፡ ግን ፡ የዚህን ፡ ዓይነት ፡ ዕድል ፡ አላጋጠማቸውም ።— ምናልባት ፡ በየጠቅላይ ፡ ግዛቱ ፡ የሚገኙ ፡ ጋልኛ ፡ የሚናገሩ ፡ ያማራ ፡ ነፍጠኞች ፡ ይኖራሉ ፤ ግን ፡ ብዙ ፡ አይመስሉኝም ።— በተጨማሪም ፡ አማርኛ— የአምስት ፡ መቶ ፡ ኀምሳ ፡ ዓመታት ፡ በላይ ፡ የጽሑፍ ፡ ቅርስ ፡ ያለውና ፡ ያስተዳደር ፡ ቋንቋ ፡ በመሆኑ ፡ ምናልባት ፡ ሳይረዳው ፡ አልቀረም ።— ስለዚህ ፡ ነው ፡ ስድሳ ፡ ከመቶ ፡ ሳይሆን ፡ አይቀርም ፡ ያልኩት - - -

« - - - ብቻ ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛቱን ፡ ስመለከተው - - - ወሊጋ ፡ ገሙ ፡ ጎፋ - - ከፋ - - -

«ገባኝ ፡ ገባኝ ፡ የሚሉት— እዚህ ፡ ላይ ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ ላስታው ስዎት ፡ የምፈልገው ፡ አለኝ— ኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ያገር ፡ ስፋትና ፡ የሕዝብ ፡ ቁጥር ፡ አይመጣጠንም— ለምሳሌ ፡ የጠቀሷቸውን ፡ አገሮች ፡ ብንወስድ ፡ ወሊጋ - 1-357-087 ሚሊዮን - - ገሙጎፋ - 914-924 - - - ቆይ ፡ ቆይ ፡ እረ ፡ ማስታወሻ ፡ አለኝ ፡ እንዲያውም - - - ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ዩንቨርስቲ ፡ የጆግራፊ ፡ ክፍል ፡ በ፲፱፻፷፩ ፡ ዓ ፡ ም ፡

ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ቁጥር ፡ ባደረገው ፡ ጥናት ፡ መሠረት - - አዎ - - ይኸው - - ! » የማስታወሻ ፡ ደብተሩን ፡ ያወጣና ፡ ያነባል - - -

1ኛ ፡ ክፍል ፥

| | | | |
|---|---|---|---|
| ወለጋ ፡ | — | 1-357-087 | |
| ሲዳሞ ፡ | — | 1-123-492 | (ከምባታ ፡ ወላሞና ፡ ሲዳሞኛ ፡ የሚናገሩት ፡ ተቀን ሰው) |
| ሸዋ ፡ | — | 1-571-872 | (አማርኛ ፡ ትግሪኛ ፡ ጉራጊኛና ፡ ሌሎችም ፡ ቋንቋዎች ፡ የሚናገሩት ፡ ተቀንሰው ፡ |
| ገሙጎፋ ፡ | — | 918-924 | |
| ኢሉባቦር ፡ | — | 845-682 | |
| አሩሲ ፡ | — | 877-872 | |
| ባሌ ፡ | — | 821-000 | |
| ሐረር ፡ | — | 165-327 | (አማርኛ— አደሪኛ— ሶማሌኛ ፡ የሚናገሩት ፡ ተቀን ሰው) |
| ከፋ ፡ | — | 654-020 | (ከፍቾ ፡ ጊሚራ ፡ ቦሻ ፡ ሞቻ ፡ ሸናሻ ፡ ሞአ ፡ የሚናገሩት ፡ ተቀንሰው) |
| ወሎ ፡ | — | 94-000 | (አማርኛና ፡ ትግሪኛ ፡ የሚናገሩት ፡ ተቀንሰው ) |
| በድምሩ ፡ | — | 8-429-276 | |

2ኛ ፡ ክፍል ፥

| | | | |
|---|---|---|---|
| ጐጃም ፡ | — | 1-806-787 | |
| በጌምድር ፡ | — | 1-345-535 | |
| ሸዋ ፡ | — | 3-313-946 | (ጋልኛ ፡ ጉራጊኛ ፡ ትግሪኛና ፡ ሌሎች ፡ አንዳንድ ፡ ቋንቋዎች ፡ የሚናገሩትን ፡ ቀንሶ) |

| | | | |
|---|---|---|---|
| ወሎ ፡ | — | 3-027-115 | (ጋልኛና ፡ ትግሪኛ ፡ ተናጋሪዎች ፡ ተቀንሰው) |
| ሐረር ፡ | — | 1-365-378 | (ጋልኛ ፡ ሶማሌኛ ፡ አደሪኛ ፡ አዳልኛ ፡ ተናጋሪዎች ፡ ተቀንሰው) |
| ድምር ፡ | — | 10-858-761 | |

3ኛ ፡ ክፍል ፡— ትግሪኛ— ጉራጊኛ— ሶማሌኛና— ልዩ ፡ ልዩ ፡ የከፋና ፡ የሲዳሞ ፡ ቋንቋዎች ፡ የሚናገሩ ፡

| | | |
|---|---|---|
| ትግሬ ፡ | — | 1-821-892 |
| ኤርትራ ፡ | — | 2-131-000 |
| ሐረር ፡ | — | 1-043-576 |
| ሸዋ ፡ | — | 438-808 |
| ከፋ ፡ | — | 704-462 |
| ሲዳሞ ፡ | — | 1-658-444 |
| ድምር ፡ | — | 7-798-182 |

ምን ፡ ማለት ፡ ነው ፡ እንግዲህ ፡ ይኸ - - ? በሁለተኛ ፡ ክፍል ፡ የተዘረዘሩት ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛቶች ፡ ሕዝብ ፡ ቁጥር ፡ ባንደኛው ፡ ክፍል ፡ ከተዘረዘሩት ፡ ይበልጣሉ ፡ ማለት ፡ ነው ።— በመጀመሪያው ፡ ክፍል ፡ የተዘረዘሩት ፡ በሙሉ ፡ ጋልኛ ፡ ተናጋሪዎች ፡ ናቸው ፡ ብንል ፡ እንኳን ፡ ከሁለተኛው ፡ ክፍል ፡ ጋር ፡ ሲወዳደሩ ፡ ያነሱ ፡ ናቸው ፡ ማለት ፡ ነው ።— በሙሉ ፡ ግን ፡ ጋልኛ ፡ ተናጋሪዎች ፡ አይደሉም ፤ የወለጋን ፡ የሸዋን ፡ የሐረርን ፡ ጋልኛ ፡ እንደተግባባቢና ፡ እንደ ፡ አንድ ፡ ቋንቋ ፡ ብንቆጥራቸው፡ እንኳ ።— ከስምንት ፡ ሚሊዮን ፡ አራት ፡ መቶ ፡ ሃያ ፡ ዘጠኝ ፡ ሺ ፡ ሁለት ፡ መቶ ፡ ሰባ ፡ ስድስት ፡ ውስጥ ፡ አማርኛን ፡ እንደ ፡ ሁለተኛ ፡ ቋንቋ ፡ የሚናገሩ ፡ በትንሹ ፡ ከግማሽ ፡ በላይ ፡ ሳይሆኑ ፡ አይቀሩም ።— አልፎ ፡ አልፎ ፡ ከሚገኙት ፡ አማርኛን ፡ እንደ ፡ ጡት ፡ ማስጣያ ፡ ቋንቋቸው ፡ ከሚናገሩት ፡ ውጪ ፡ ማለት ፡ ነው - - - በዚያ ፡ ላይ ፡ ደግሞ ፡ አማርኛን ፡ እንደተወለዱበት ፡ አካባቢ ፡ ቋንቋ ፡ ወይም ፡ እንደ ፡ ሁለተኛ ፡ ቋንቋቸው፡ አድርገው ፡ የሚናገሩት ፡ ሦስተኛዎቹ ፡ ክፍል ፡ አሉ ።— ሰባት ፡ ሚሊዮን ፡ ሰባት ፡ መቶ ፡ ዘጠና ፡ ስምንት ፡ ሺ ፡ አንድ ፡ መቶ ፡ ሰማኒያ ፡ ሁለት ፡

ትንሽ ፡ ቁጥር ፡ አይደለም ።— ጋልኛ ፡ ተናጋሪዎቹን ፡ ሊያህል ፡ ምንም ፡ ያህል ፡ የማይቀረው ፡ ማለት ፡ ነው ።—እና ፡ እንግዲህ ፡ ያማርኛ ፡ ብሔ ራዊ ፡ ቋንቋነት ፡ የሚያጠራጥር ፡ መስሎ ፡ አይታይም ፡ በዚህ ፡ አስተ ያየት - - -

«እሺ ፡ አሁን ፡ ወደ ፡ ጀመርከው ፡ ተመለስና ፡ ቀጥል—የቋንቋ ፡ ልዩነት ፡ ስለሚያስከትለው ፡ ችግር ፡ ነበር ፡ የምትዘረዝረው - - - ይችን ፡ ደሞ ፡ የሕዝብ ፡ ቁጥር ፡ ዝርዝርህን ፡ ብትሰጠኝ ፡ ብገለብጣት - - ጥሩ ፡ ነገር ፡ ነች ፤ የየጠቅላይ ፡ ግዛቱን ፡ ሕዝብ ፡ ቁጥር ፡ ለማወቅ - - ለመ ሆኑ - - » ማስታወሻውን ፡ ተቀብለው ፡ በማስታወሻቸው ፡ ላይ ፡ እየገለበጡ « ለመሆኑ — የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ቁጥር ፡ ስንት ፡ ደር ሷል ፡ ይባላል - - - ?

« አ - - - ! በጣሊያን ፡ ጊዜ— አምስት ፡ ሚሊዮን ፡ ብቻ ፡ ነበር ፡ ተብሎ ፡ የተመዘገበው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ቁጥር - - - ዛሬ - - ሰላም ፡ ዘመናዊ ፡ መድኀኒትና ፡ ሕክምና— ከሀያ ፡ ሰባት ፡ ሚሊዮን ፡ ሰማኒያ ፡ ስድስት ፡ ሺህ ፡ በላይ ፡ አድርሶታል ።—እሱን ፡ ዝርዝሩን ፡ ቢደምሩትኮ፡ ሊያገኙት ፡ ይችላሉ - - -

«ጥሩ ፡ ነው ፡ ጥሩ ፡ ነው— ቀጥል ፡ ቅድም ፡ ስለጀመርነው - - -

«አዎ ፡ እና - - ታዲያ ፡ አማርኛን ፡ የሚሰማውም ፡ ሆነ ፡ የሚናገ ረው ፡ ከሚናገረውና ፡ ከሚሰማው ፡ ጋር ፡ ከስድሳ ፡ ከመቶ ፡ ስለማይበ ልጥ—ሌላው ፡ ቀሪው ፡ አርባ ፡ ከመቶው ፡ ማለት ፡ ነው ፡ የተንጓለለ ፡ ስለሚመስለው ፡ የኢትዮጵያዊነት ፡ ስሜቱ ፡ መነካቱ ፡ አይቀርም ፤ እምለው—በሬዲዮ ፡ የሚነገረውን ፡ በጋዜጣ ፡ የሚጻፈውን ፡ በብሔራዊ ፡ መሠረተ ፡ ትምህርት ፡ የሚሰጠውን ፡ ለማግኘት ፡ ስለማይችል - - -

«ታዲያ ፡ ምን ፡ መፍትሔ ፡ የሚኖረው ፡ ይመስልሃል - - - ?

« በውነቱ ፡ ከሆነ ፡ እንደዚህ ፡ እንደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ከአርባ ፡ በላይ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ቋንቋዎች ፡ እሚነገርበት ፡ አገር ፡ በየቋንቋው ፡ የተጻፉ ፡ መጻ ሕፍትና ፡ በየቋንቋው ፡ የሠለጠኑ ፡ መምህራን ፡ ስለሌሉና ፡ እንዲኖሩም ፡ ለማድረግ ፡ ለጊዜው ፡ ኢኮኖሚያችን ፡ ስለማይፈቅድ ፡ ምናልባት ፡ በተ ለይ ፡ ለብሔራዊ ፡ መሠረተ ፡ ትምህርትና ፡ በዝቅተኛ ፡ ደረጃ ፡ ለሚማሩ፡ ሕፃናት ፡ እንደተናጋሪዎቹ ፡ ብዛት ፡ ታይቶ— ማለት ፡ አማርኛንም ፡ እንደ ፡ አንድ ፡ ትምህርት ፡ እያስተማሩ — ሁለት ፡ ወይም ፡ ሦስት ፡ ቋን ቋዎችን ፡ ለመምረጥ ፡ ይቻል ፡ ይሆናል - - -

«ልጆቼን ፡ ለረኝነት ፣ ብሬን ፡ ለብርሌ ፡ አውላቸዋለሁ ፡ ለሚለውስ ፡ ምን ፡ ዘዴ ፡ ታገኝለታለህ - - - ?

«ስለ ፡ እረኝነቱ ፣ በየቦታው ፡ አንዳንድ ፡ የከብት ፡ ማቆሚያ ፡ መስኖጌ ፡ እየቀየሱ ፣ ከብቶቹ ፡ ያለ ፡ እረኛ ፡ የሚሠማሩበትን ፣ ዘዴ ፡ መሻትና—ከዚያም ፡ በላይ ፡ ማንኛውም ፡ ሰው ፡ ልጁን ፡ ቢያንስ ፡ ቢያ ንስ ፡ እስከ ፡ ስድስተኛ ፡ ክፍል ፡ ድረስ ፡ እንዲያስተምር ፡ የሚያስገድድ ፡ ደንብ ፡ ማውጣት - - - ስለ ፡ ብርሌው ፡ ቢሆን ፣ አሁን ፡ ባለንበት ፡ ዘመን ፡ ማስተው ፡ የሚቻል ፡ አይመስለኝም — ምናልባት ፣ ከብርሌው ፡ ይበልጥ ፡ መጽሐፉ ፡ መጣፈጡን ፡ የምናሳይበት ፡ ዘዴ ፡ ካላገኘን - -

«እሱንማ ፡ ቅድም ፡ ተነጋግረንበታል— የሚያንን ፣ የሚጣፍጥ ፡ መጽሐፍ ፡ በመጻፍ ፡ ሕዝቡን ፡ ለመማረክ ፡ ይቻላል ፡ ብለሃል - - - ሐሳ ብህ ፡ ይሠራ ፡ አይሠራ ፡ እንደሆን ፡ የሚያሳየን ፡ እንግዲህ ፡ መቆየት ፡ ነው - - -

«ፃእ ፡ መንፈስ ፡ ርኩስ ! ፃእ ፡ መንፈስ ፡ ርኩስ !» እያሉ ፡ ጠበል፡ እየረጩ ፡ ይመጣሉ ፡ አባ ፡ አዲሴ - - - ሊቸችሩት ፡ ሲዘጋጁ ፡ ሲያይ ፡ ምንጥቅ ፡ ብሎ ፡ ያመልጣቸዋል ፡ አደፍርስ «ጸላኤ ፡ ሠናያት ፡ እኔ ፡ ፊት ፡ አይቆምም » ይሉና ፡ ላደፍርስ ፡ ባመቻቹት ፡ አቶ ፡ ወልዱን ፡ ይቸችሯቸ ዋል—

- - ከት ፡ ያለ ፣ ደስ ፡ የሚል ፡ የጺወኔ ፡ ቃጭል ፡ ድምፅ ፡ ሲሰበረ በር ፡ ይሰማል፣ ካባ ፡ አዲሴ ፡ ኋላ ፡ ኋላ « - - ሌጊዎንን ፡ አባረሩት —ሌጊ ዎንን ፡ አባረሩት ! » እያለ ፡ ሲንሰቀሰቅ—

አደፍርስ ፡ አልሰማትም—

# ፳፪

## አደፍርስ

ጐርፉን ፡ እቤታቸው ፡ ድረስ ፡ አስጠርተውታል ፡ ወይዘሮ ፡ አሰ ጋሽ ።— ጴጥሮስ ፡ እንደ ፡ ነገራቸው ፤ በየሳምንቱ ፡ ወይም ፡ በያሥራምስት ፡ ቀኑ ፡ ውሃ ፡ መቅጃ ፡ ድረስ ፡ መጥቶ ፡ እየጠበቀ ፡ ሮማንን ፡ እንደሚያነ ጋግራት ፡ ሰምተዋል ።— ከቤተ ፡ ሰባቸው ፡ አንዷ ፡ በሚወዱት ፡ የአብሮ፡ አደጋቸው ፡ ልጅ ፡ አልባሌ ፡ ቦታ ፡ መጠበቋ ፡ አንገብግቧቸዋል ።— የወይዘሮ ፡ አሰጋሽ ፡ ቤተሰብ ! በዚያ ፡ ላይ ፡ ደግሞ ፡ ቃል ፡ ያሠረች ፤ ጐድፉ ፡ የተገኘች ፡ እንደሁ ፡ ደግሞ ፡ ምን ፡ ይውጣቸዋል ?— አሰጋሽን ፡ የሚያህል ፡ ስም - - ! ሲመጣ ፡ ምን ፡ ምን ፡ እንደሚሉት ፡ ያወጡ ፡ ያወርዳሉ - - የነፍስ ፡ አባታቸውን ፡ እንኳ ፡ ጠበል ፡ እንደ ፡ ረጩ ፡ ቆይ ተው ፡ እንዲያጫውቷቸው ፡ ሳይፈልጉ ።—

« - - - ነገር ፡ ከሰነበተ ፡ ቅራሪ ፡ ከሆመጠጠ ፡ አጉል ፡ ነው — ነገር ፡ ከሰነበተ ፡ ይከራል ፤ ቅራሪ ፡ ከሆመጠጠ ፡ ያቀራል - - አዎ ፡ ይኸ ፡ ጥሩ ፡ አጀማመር ፡ ነው - - - እሺ ፤ ከዚያ ፡ ቀጥዬ ፡ ደግሞ ፡ ያሳደግሁት ፡ ልጄ ፡ ስለመሆኑ — የዋንጫ ፡ ቡሽ ፡ የውሃ ፡ ጉሽ ፡ የለውም ፤ ዘርህ ፡ የጠራ ፡ ጠባይህ ፡ የታወቀ - - አጓጉል ፡ ነገር ፡ አልታየበት — አሁን ፡ ዋንጫን ፡ ማን ፡ በቡሽ ፡ ይከድናል ? አንተንስ - - ቆይ ፡ ቆይ - - ! ትልቅ ፡ ቡሽ ፡ ያሠራ ፡ ነዋ ፡ ያለኝስ ፡ እንደሁ - - ውሃስ ፡ ይደፈርስ ፡ የለም ፡ እንዴ ፡ እሱማ ፡ ጉሽስ ፡ ባይኖረው - - - የእባብ ፡ ለማዳ ፡ ያህያ ፡ ፍሪዳ — ሴትና ፡ ወንድ ፡ ጭር ፡ አለበት ፡ ቦታ ፡ አጉል ፡ ነገር ፡ ያስ ከትላል - - አሂሂ ፡ ይኸም ፡ አጉል ፡ ነው - - እሱ ፡ እንዲያውም ፡ ነገር ፡ ጠምዛዥ ፡ ነው ፤ እባብ ፡ ብለሽ ፡ ሰደብሽኝ ፡ ነው ፡ የሚለኝ - - ሮማን ንስ ፡ አህያ ፡ አሉሽ ፡ ቢላት - - አይ ፡ እሷ ፡ እንኳን ፡ ልማዷ ፡ ነው ፤ ቢሆንም ፡ እሱ ፡ ስለሰማው ፡ ይከፋት ፡ ይሆናል - - ቃል ፡ ያሠረች ፡ ልጃገረድ ፡ ትንሽ ፡ ትንሽ ፡ ክብር ፡ አይጠላባትም - - የለም ፡ አይበጅም - - - አንተ ፡ ለራስህ ፡ የምታጓጓ — በዕውር ፡ ጐዳና ፡ ብርቅ ፡ ነው ፡ አንድ ፡ ዓይና ! - - ልቧ ፡ ይታለልና - - በዕውር ፡ ጐዳና ? ! - - ይኸማ ፡ አሰጋ ሽም ፡ እውር ፡ ነች ፡ ማለት ፡ ነው - - አሰጋሽ ፡ እንኳን ፡ ባልሳት ፡ ሀብት ፡ የሱን ፡ ዓይነት ፡ አላስገኘችም ፡ ማለት ፡ ይመስለው ፡ ይሆናል - - አሂሂ !

የማይደረገውን - - ራሴን ፡ በራሴ ፡ ልሰድብ ? ተደርጐም ፡ አያውቅ - - - ሲ
ያይ ፡ የሞተውን ፡ ሲሰማ ፡ ቅበረው ፡ እንዳይሆን ፡ ብዬ ፡ ነው ፡ ያስጠ
ራሁህ — አዎ ፣ ይኸ ፡ እንኳን ፡ ጥሩ ፡ መጀመሪያ ፡ ይሆናል - - ግን ፡
የት ፡ ቦታ ፡ አዩኝ ፡ ያለኝስ ፡ እንደሁ— ጴጥሮስ ፡ ዋሽቶስ ፡ እንደሁ ?
አይ ፡ ጴጥሮስ ፡ አይዋሽም - - ባይሆን ፡ ከዚያም ፡ ከዚያም ፡ ትንሽ ፡ ትንሽ፡
እህል ፡ ያጠፋፋ ፡ እንጂ ፡ ውሸት ፡ አያውቅም - - ጉቦ ፡ ምናልባት ፡
ከየጭሰኞቹ ፡ ይቀበል ፡ ይሆናል - - - ቆይ ፡ ቆይ ! ቃልህ ፡ ሳይዘጋ ፡ እግ
ርህ ፡ ሳይዘረጋ ፡ ለምን ፡ የምትሆንህን ፡ ፈልገህ ፡ አታገባም ፡ ብለውስ ?
አዎ ፣ እናቱ ፡ ነኝ ፤ ምክሬን ፡ ባካፍለው ፡ መከፋት ፡ የለበትም - - እንደማ
ትከፋ - - ለኑሮ ፈውስ ፡ የምትሆን - - - የማይፈወስ ፡ ድውይ ፡ የማይ
መለስ ፡ ጊጉይ ፡ እንደማትሆን ፡ ስለማውቅ - - እእእ . . . ! አጉል ፡
አባባል —እንዴታ ! አብሮ ፡ አደጉ ፡ ነች - -አብረው ፡ ሲዘሉ - - - ቢዘል ፡
እማጀት ፡ ቢወጋ ፡ ምንቸት — እእእ . . . ! ያስከፋዋል ፡ ይኸም - - አዳል ፡
ዘመቻ ፡ የወረደ - - ስንቴ ፡ ነው ፡ በሬና ፡ ላም ፡ እየዘረፈ - - - ላም ፡ እሳት ፡
ወለደች ፣ ልጅዋ ፡ ነበርና ፡ ላሰች — ልጇ ፡ ነህ ፡ አንተም ፤ ያጠፋኸውም ፡
ነገር ፡ ቢኖር ፡ መቻል ፡ አለብኝ - - መቻል ፡ አለብኝ - - መቻል ፡ አለ
ብኝ - - ? ! የለም ፡ መቻል ፡ የለብኝም - - ውሃ ፡ መቅጃ ፡ እየጠበቁ ፡
ማነጋገር ፡ ትልቅ ፡ ድፍረት ፡ ነው - - ትልቅ ፡ ድፍረት - - ደሞ ፡ የምን ፡
ጐን ፡ ጐን ፡ መሄድ - - ቀጥታ ፡ ነው ፡ የምንግረው - - ያላዋቂ ፡ ነገር - - ያላ
ዋቂ ፡ ሳሚ ፡ ንፍጥ ፡ ይለቀልቃል - - አዎ ፣ ቢከፋውም ፡ ይክፋው - - የሚ
ያውቅም ፡ ይለቀልቃል ፡ ያለኝስ ፡ እንደሁ - - የለም ፡ እንዲህ ፡ አይ
ደፍረኝም - - - ሰው ፡ እንደ ፡ ቤቱ ፡ እንጂ ፡ እንደ ፡ ጐረቤቱ ፡ አይበ
ላም - - - የፈሰሰ ፡ ውሃ ፡ አይታፈስም - - እና ፡ ታዲያ - - ታዲያ - - አ
ንተ ፡ እርምጃህ ፡ ትንሽ ፡ ተፋጥኗል - - - ሲሮጡ ፡ የታጠቁት ፡
ሲሮጡ ፡ ይፈታል - - -

# ፳፫

## አደፍርስ

ጐርፉ ፣ ከዚህ ፣ በፊት ፣ ጺወኔን ፣ አጥር ፣ ሥር ፣ ባነጋገራት ፣ ጊዜ ፣ ለብሶት ፣ የነበረውን ፣ ልብስ ፣ ለብሶ ፣ ግቢውን ፣ ይገባል ።— እወይዘሮ ፣ አሰጋሽ ፣ እልፍኝ ፣ በር ፣ ሲደርስ ፣ ጠበንጃውን ፣ እውጪ ፣ ቆሞ ፣ ለሚ ጠብቅ ፣ ልጅ ፣ ይሰጥና ፣ ያደገድጋል ።— ልጁ ፣ ጠበንጃውን ፣ ይዞ ፣ ገብቶ ፣ መምጣቱን ፣ ይነግርለታል ።— ወይዘሮ ፣ አሰጋሽ ፣ እጀታሙ ፣ ወንበራቸው ፣ ላይ ፣ ተቀምጠዋል ።— ጐርፉ ፣ ፈቃድ ፣ እንደ ፣ ተሰጠው ፣ ይዘልቅና ፣ እወይዘሮ ፣ አሰጋሽ ፣ ጫማ ፣ ላይ ፣ ዘፍ ፣ ብሎ ፣ ይስማል ---

«እንደምነህ ፣ ወዳጄ --እንደምነህ - - እንደምነህ --እንደምነህ ! » እያሉ ፣ አገጩን ፣ ቶሎ ፣ በጃቸው ፣ ቀበል ፣ ብለው ፣ በመሳም ፣ ፈንታ ፣ በሚያግደረድር ፣ መንገድ ፣ ወደታች ፣ እንደ ፣ ዘረጉት ፣ ብዙ ፣ ጊዜ ፣ ይቆያሉ « --እንደምነህ ፣ ታዲያ ! » ይቀጥላሉ ፣ አሁንም ፣ ቀና ፣ አድ ርገው ፣ ከሳሙት ፣ በኋላ « ---አባትህ ፣ ቀኛዝማችስ ፣ እንደምነው - --?

«ደኅና ! ደኅና ! » እያለ ፣ እጅ ፣ ይነሣል ፣ ጐርፉም ---

«እናትህስ ---!

«እግዚአብሔር ፣ ይመስገን ፣ ደኅና ፣ ነች --

«ልጆቹስ -- ክብቶቹስ --

«ይክበር ፣ ይመስገን ፣ ለፈጣሪ --

«አንተስ ፣ እንደምን ፣ ይዞሃል --?

«ክብሩ ፣ ይስፋ ፣ ክብሩ ፣ ይስፋ ! እስካሁን ፣ ይጠብቀኛል ፣ መቼም --

«እርሻው ፣ ጉልጓሎው ፣ የክረምት ፣ ነገር ---

«ይዘነዋል ፣ መቼም - -እንደ ፣ ነገሩ ---

«እንዲያው ፣ አንድ ፣ ታቦት ፣ እየተሳለምን ፣ መጠፋፋት ---

«ማደሮው ፣ መቼ ፣ ይለቃል ፣ ብለው ---

«ቢሆንስ ! ቢሆንስ ! ከብቶቻችን ፣ አንድ ፣ ሥሪት ፣ እየዋሉ -- አን ተስ ፣ በጇ ! ካብትህስ ፣ ቢሆን ---

«እሱም ፣ አልተመቻቸው ---

«ያለፈው ፣ የሰኔ ፣ ሚካኤልኮ ፣ ሦስት ፣ ወሬ ፣ መሆኑ ፣ ነው ፣ አን ተንም ፣ አባትህንም ፣ ካየኋችሁ ---

«ይሆን ፣ ይሆናል ---

«ግርም ፣ ድንቅ ፣ ነው ፣ የሚለኝ ፣ የዘመኑ ፣ መጠያየቅ ---

«ልጆቹንኮ ፣ ባገኘኋቸው ፣ ቁጥር ፣ እጅ ፣ ንሡልኝ ፣ ማለቴ ፣ አልቀረም ---

«ሆይ ፣ ታሪክ ! ሆይ ፣ ታሪክ— የዛሬ ፣ ልጆች ፣ በመልክት ፣ እጅ ፣ መንሣት -- የማታመጡት ፣ ፈሊጥ ፣ የለ --- እደጇ ፣ ድረስ ፣ መጥተህ ፣ እየተመለስህ ፣ ደግሞ ፣ እጅ ፣ ንሡልኝ -- እንዲያው ፣ ዘመድ ፣ መጠየቄን ፣ ትቼዋለሁ ፣ አትልም ---

«ዋ ፣ እረ ፣ ሳይሞላልኝ ፣ እየቀረ ፣ ነው ---

«ሳይሞላልህ ፣ እየቀረ ! እንዲህ ፣ አርጐም ፣ የለ ! እደጇ ፣ ድረስ ፣ እየመጣህ ፣ እኔን ፣ እናትህን ፣ እጅ ፣ መንሣቱ ፣ ላይ ፣ አልሞላልህም ---» ጐርፉ ፣ ድንግጥ ፣ ይላል ፤ ከጺወኔ ፣ ጋር ፣ ባጥር ፣ ላይ ፣ የተነጋገረ ፣ ለት ፣ መምጣቱን ፣ የሰሙ ፣ ይመስለውና «--- አረፍ ፣ በል ፣ እንጂ ፣ ታዲያ ፤ የኔ ፣ ነገር ፣ ዝም ፣ አልኩህኮ -- እዚያ ፣ እበርጩማው ፣ ላይ ፣ ቁጭ ፣ በል ---

ቁጭ ፣ ብሎ ፣ ምራቁን ፣ እንደዋጠ « እርስዎስ ፣ ይኸን ፣ እግርዎን ፣ የሚቆረጣጥምዎትን -- ምን ፣ ማስታገሻ ፣ አገኙለት ---?

«ምን አገኝለታለሁ ፣ አለ ፣ ሊቀ ፣ መልአኩ -- በሰው ፣ እመት ፣ ሳሻሽው ፣ ነው ፣ እሚታገሥልኝ ---

« ዐዋቂው ፣ እንደ ፣ ብርካቴው ፣ በሽታ ፣ አለ ፣ መጥፋቱ ---

« --- ያዋቂውን ፣ ነገር ፣ አለማንሣቱ ፣ ይሻላል ፣ እባክህ -- በወ ገቤ ፣ ዙሪያውን ፣ ታጥቄው ፣ በትከሻዬ ፣ አልፏል ፣ የጥፈቱ ፣ ዓይነት --- ምኑ ፣ ቅጡ -- ስመ ፣ አምላኩ ፣ ትምርተ ፣ ቦአቱ ፣ አስማተ ፣ ሰለሞኑ ፣ ጩብጩቤው ፣ ግርማ ፣ ሞገሱ ፣ በቁመቴ ፣ ልክ ፣ ብራና ፣ የተጣፈው ፣ ጥፈት ፣ ዓይነት -- ምን ፣ ብቻ ፣ ልንገርህ -- አልለ ፣ የተባለ ፣ መዳኒት ፣ አልቀረኝም ---

«ማስታገሻውን ፡ እሱ ፡ ካላዘዘው ፡ ይሆናል - - -

«አላዘዘውም - - አላዘዘውም - - ባያዘው ፡ ነው - - ሲቀ ፡ መልአኩ ተቀይሞኛል - - እምና ፡ ታስታውስ ፡ እንደሆን ፡ የንግሡ ፡ ለት ፡ ሦስት ፡ ዱለቻ ፡ ጥዬ ፡ አዘከርኩት - - የሦስት ፡ ቤተክሲያን ፡ ቄስና ፡ ደብተራ ፡ ጋብዤ ።— ስንቱን ፡ ለምድርና ፡ ለሰማይ ፡ የከበደ ፡ ሰው ፡ ነው ፡ የኔ ፡ ጠላና ፡ ጠጅ ፡ ያብረጀረጀው - - ታስታውስ ፡ እንደሁ ፡ ዳሱ ፡ እንኳን ፡ የፈረሰው ፡ በሦስተኛው ፡ ቀን ፡ ነው - - እኔ ፡ የት ፡ ላይ ፡ እንደበደልኩት ፡ አይገባኝም ።— አሁን ፡ በበቅሎዬ ፡ ስሄድ ፡ ከየትም ፡ ማዘን ፡ ይሁን ፡ ገጥ ፡ ይለኝ ፡ የለም ? አሽከር ፡ ሳያስፈልገኝ ፡ ዱብ ፡ ብዬ ፡ ነው ፡ የምሳለመው - - አባ ፡ አዲሴም ፡ የኔ ፡ ልጅ ፡ ጥፋት ፡ የለብሽም ፡ ነው ፡ የሚሉት ፤ የወደደውን ፡ መፈታተን ፡ ልማዱ ፡ ነው ፡ ይሉኛል - - ታዲያ ፡ እኔ ፡ የሚገርመኝ ፡ ፈትኖኝ ፡ ፈትኖኝ ፡ የሱ ፡ መሆኔን ፡ ሲያውቅ ፡ አለመተዉ - - እንዲያውም ፡ ቁርጥማቱማ ፡ የሚብስበት ፡ እሁድ ፡ እሁድና ፡ ለሱው ፡ ጠበል ፡ ጠዲቅ ፡ ባደረግሁ ፡ ቁጥር ፡ ነው - - በሌሊት ፡ እየተነሣሁ ፡ ባስቀደስኩና ፡ ከጧት ፡ እስከ ፡ ማታ ፡ አደግድጌ ፡ በየጊዜው ፡ ጠበል ፡ ጠዲቁን ፡ ባዘከርሁ - - ምን ፡ ይውጣት ፡ ብሎ ፡ ነው ፡ እስቲ ! በያመት ፡ ባሉ — ስንዴ ፡ ሲሉኝ ፡ ስንዴ ፡ ጋድ ፡ እንጨት ፡ ሲሉኝ ፡ ጋድ ፡ እንጨት ፡ ጧፍ ፡ ሲሉኝ ፡ ጧፍ ፡ ዕጣን ፡ ሲሉኝ ፡ ዕጣን ፡ ግምጃ ፡ ሲሉኝ ፡ ግምጃ - - አይ ፡ እሱም ፡ አሁንስ ፡ የሚፈልገውን ፡ አጥቶታል - - -

«ሳይቸግረው ፡ ወዳጁን ፡ ይፈታተናል !» ይላል ፡ ጐርፉ ፡ ያዳምጥ ፡ ያዳምጥና ።

«አባ ፡ አዲሴም ፡ ይኸንኑ ፡ ነው ፡ ያሉት - - !» ይመልሳሉ ፡ ወይዘሮ ፡ አሰጋሽ ፤ የልብ ፡ ኩራታቸውን ፡ አውጥቶ ፡ በሚያሳይ ፡ አነጋገር ።

«አብዬ ፡ ወልዱ ፡ መጥተዋል ፡ ልበል ፤ በሩቁ ፡ ያየኋቸው ፡ መሰለኝ» ይጠይቃቸዋል ፡ ጐርፉ ፡ ድንገት ፡ ርእሱን ፡ በመለወጥ ።

«መምጣትህ ፡ ካልቀረ ፡ ታዲያ ፡ እዚህ ፡ ድረስ ፡ ምን ፡ ነበረበት ፡ ገባ ፡ ብለህ ፡ እንዴት ፡ ናችሁ ፡ ብትለን ?» አንዷን ፡ ቃል ፡ ብቻ ፡ ያጤኑለት ፡ ይመስል ፡ ይጠይቁታል ፡ መልሰው ።

«እረ ፡ መጥቼም ፡ አላውቅ - - እንዴት ፡ ሰላምታ ፡ ሳልሰጥዎት ፡ እሄዳለሁ ?» ይላል ፡ ጐርፉ ፡ እንደገና ፡ ድንገት ፡ ድንግጥ ፡ ይልና ።

«ተውተው ! የኔ ፡ ልጅ ፡ እንኳን ፡ ውሸት ፡ አታውቅም ፡ ነበር ---

«የትናንት ፡ ወዲያውን ፡ ካልሆነ ፡ በስተቀር - - እምለው ፡ ሚካ ኤል ፡ ስለት ፡ ነበረብኝ - - እና ፡ ታዲያ ፡ ታቹን ፡ በጉድባ ፡ ሳልፍ ፡ ሮማን ፡ አይታኝ ፡ ነበር ---

«አዎ ፡ እሱን ፡ ማለቴ ፡ ነው ---» ይላሉ ፡ ወይዘሮ ፡ እሰጋሽ ፡ አነ ጋገራቸውን ፡ ጠበቅ ፡ አድርገው « የጉድባውን ! ታዲያ ፡ ምን ፡ ነበረ በት ፡ ከቤተስኪያን ፡ መልስ ፡ እንኳን ፡ ጐራ ፡ ብለህ ፡ ብትጠይቀን ---?

«ማስቸገር ፡ እንዳይሆንብኝ ---

«እንግድነትህ ፡ እንዳያስቸግረን - - ማለትህ ፡ ነው - - ታዲያ ፡ ከሮማን ፡ ጋር - - ቆም ፡ አላልክም ፡ ኖሯል ፡ እንዴ ---?

«አዎ ፡ ብቻ ፡ ቆም ፡ ብዬ ፡ ነበር ---

«ስታልፍ ፡ አይደለም ፡ ያየችህ---?! ታዲያ ፡ እምልህ ፡ ወርዶፋ ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ነገር ፡ አይወድ ፤ አንድም ፡ ብትሆን ፡ ቀጥቶ ፡ ነው ፡ ያሳ ደጋት - - እንዲህ ፡ ያለውን ፡ መገናኘት ፡ ይወደው ፡ ይመስልሃል ---?

«ውይ ፡ ምነው ፡ እመዬት ! ለምን ፡ አይወደውም ? ባነጋግራት ፡ ምን ፡ አለበት - - አብረን ፡ አፈር ፡ ፈጭተን ፡ አድገን - - ሰው ፡ እንትቱን ፡ ሳያነ ጋግር ፡ እንዴት ፡ ያልፋል ? እርግጠኛ ፡ ነኝ ፤ አብዬ ፡ ወርዶፋም ፡ ቢያይ ፡ እሱም ፡ መጥቶ ፡ ነው ፡ የሚያነጋግረኝ ---

«እሱን ፡ ማለቴ ፡ አይደለም - - ብቻ ፡ ቢሆንም ፡ ወንድና ፡ ሴት ፡ ብቻቸውን ፡ መቅጃ ፡ ሲታዩ ፡ አጉል ፡ ትርጉም ፡ ያመጣል - - ዛሬ ፡ እን ኳን ፡ አጋኙ ፡ አግኝቶ ፡ ሌጊዎን ፡ ብቻውንም ፡ አልተቻለ - - የስንቱ ፡ ልጆች ፡ ከሌጊዎን ፡ እያረገዙ ---

«ሌጊዎን ? ሌጊዎን ---?

«አዎ ፡ የዝሙት ፡ ጋኔል ፡ አለ ፤ ሌጊዎን ፡ የሚባል ።-ስንቱን ፡ የጨዋ ፡ ልጅ ፡ አበላሽቷል ፡ ይመስልሃል - - እንዲሁ ፡ እየወንዙ ፡ ዳር ፡ እየውሃ ፡ መቅጃው ፡ እየተፃረራቸው ---

« እኔ ፡ እንዲህ ፡ ያለውን ፡ ነገር ፡ ከየቴ ፡ ዐውቄ - - ሌጊዎን ፡ ብሎ ፡ ጋኔል - -

«አዎ ፡ አታውቅም—አባ ፡ አዲሴ ፡ ያውጉህ ፡ ስለ ፡ እሱ--እንደ ፡ እመቤታችን ፡ የማምናትን ፡ ጺወኔን ፡ እንኳን ፡ እንድጠራጠር ፡ ነው ፡

ያደረጉኝ - - አሁን ፡ ደግሞ ፡ ሰሞኑን ፡ ጨዋታቸው ፡ አኮሪዶ ፡ ብቻ ፡ ሆኗል - - ይኸው ፡ ሌጊዎን ፡ ባኮሪዶ ፡ ተጭኖ ፡ እቤትዎ ፡ ገብቷል ፡ ይሉኛል - - -

«አኮሪዶ ፡ ደግሞ ፡ ምንድነው - - -?

«አንድ ፡ እዚህ ፡ እኔ ፡ ቤት ፡ የሰነበተ ፡ የከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ዳኛ ፡ እኅት ፡ ልጅ ፡ አለ - - እሱ ፡ የሚያጮኸው ፡ ነገር ፡ ነው - - -

«የሚያጮኸው - - - ?

«እዎ ፡ እሱማ ፡ ዘፈን ፡ ዘፈንሁ ፡ ብሎ ፡ ልቡ ፡ ወልቋል - - ውምበርሴት ፡ የሚባለው ፡ ተማሪ ፡ ቤት ፡ የማያመጣው ፡ ነገር ፡ የለ - - - ?

« የውምበርሴት ፡ ተማሪ ፡ ነው - - - ?

«ይሉኛላ - - - !

«እነሱ ፡ ሰዎች ፡ በከተማውም ፡ ወሬያቸው ፡ አላማረ - - አሁን ፡ በቅርቡ ፡ አንዱ ፡ አባት ፡ የውምበርሴት ፡ ተማሪ ፡ ልጁን ፡ ገደለ ፡ ማለትን ፡ ትናንት ፡ ኀሙስ ፡ ገበያ ፡ ሰማሁ - - -

«ምን ፡ አጠፋህ ፡ ብሎ - - -

«ለንጉሥ ፡ አንታዘዝም ፡ የሚሉ ፡ አማርኛ ፡ አምጥተዋል ፡ ነው ፡ የሚባለው - - -

«ለንጉሥ ፡ አንታዘዝም ! ለንጉሥ ፡ አንታዘዝም - - አይጥ ፡ ወልዳ ፡ ወልዳ ፡ ጅራቷ ፡ ሲደርስ ፡ ሲጥ - - ለማን ፡ ሊታዘዙ ፡ ነው ፡ ኋላ ! የማን ንም ፡ የድሃ ፡ ልጅ ፡ ሰብስበውኮ ፡ ነው ፡ እንዲያው ፡ መከራቸውን ፡ የሚያዩት ፡ እኝህ ፡ ንጉሥ - - ዘረ ፡ ድሃ ፡ ያው ፡ ፀመለ ፡ ድሃ ፡ ነው - - ቢሾሙት ፡ ቢሸልሙት - - አሁን ፡ አህያን ፡ ቢያስጌጧት ፡ የትኛውን ፡ ግርማ ፡ ሞገስ ፡ ልታገኝ - - ? ይበጅ ፡ አርጓል - - ሞትም ፡ ሲያንሰው ፡ ነው - - -

«ክራርን ፡ እንኳን ፡ የመሰለ ፡ ጨዋታን ፡ ሲያስከለክሉ ፡ እንዴት ፡ አኮሪዶ ፡ ፈቀዱ - - -

«ምናባቴ ፡ ላርግ ፡ ብለህ - - አጐቴ ፡ ወደ ፡ ደብረ ፡ ሲና ፡ ሲመለሱ ፡ ካንድ ፡ ምስል ፡ ከሚያነሣ ፡ ጓደኛው ፡ ጋር ፡ እዚህ ፡ ከተቀመጡ ፡ ይኸው ፡ አሥራምስት ፡ ቀናቸው ፡ ትናንት ፡ ቅዳሜ ፡ አለፈ - - -

«ምን ፡ እንሁን ፡ ባዮች ፡ ናቸው ?»

«አንዱ ፡ አደን ፡ አድናለሁ ፡ ባይ ፡ ነው ፤ ሌላው ፡ ደግሞ ፡ ያገሩን ፡ ምስል ፡ አነሣለሁ ፡ ይላል - - -

«አይ ፡ እውንም ፡ ነገሩ ፡ አያምርም - - አባ ፡ እንዳሉት - - -

«የሚካኤልን ፡ ምስል ፡ አንሣልኝ ፡ ብለው ፡ ደግሞ ፡ ምን ፡ አደረገ ፡ ይመስልሃል - - - ?

«በየት ፡ አባቴ - - -

«እረ ፡ እሱንስ ፡ አለመስማቱ ፡ ይሻል - - ? ቢያወሩትም ፡ አያ ምር - - -

«ግዴለዎትም ፡ እነዚህ ፡ ያውምበርሴት ፡ ተማሪዎች ፡ ጠግበ ዋል - - -

«እረ ፡ ይኸስ ፡ ጨርሷል ፡ ነው ፡ የሚባለው ፡ ትምርቱን—እኔ ፡ መላውም ፡ አይገባኚ - - ምን ፡ አረገ ፡ ይመስልሃል ፡ ታዲያ - - አንድ ፡ የኔ ፡ ጭሰኛ ፡ አለ ፤ እዚህ ፡ እበታቼ ፡ እትረተሩ ፡ ላይ ፡ የሚኖር - - -

«አዎ ፡ ዐውቀዋለሁ - - -

«ካወቅኸው ፡ ምን ፡ ልንገርህ - - መቶ ፡ ካሥር ፡ ያህል ፡ ዕድሜ ፡ አለኝ ፡ ባይ ፡ ነው - - -

«ሰምቻለሁ - - -

«ዘንጉን ፡ ለድንገቱ ፡ ነቀል ፡ ያደረገ ፡ እንደሆን ፡ ነፋስ ፡ ነው ፡ የሚያግተረትረው - - -

«በነፋስ ፡ ግፊት ፡ ነው ፡ የሚሄደው ፤ ዘንጉን ፡ ቶሎ ፡ መትከሉ ፡ ያቆ መዋሊ ።— አንዳንዴ ፡ ይዞት ፡ እንዳይሄድ ፡ እፈራለሁ - - -

«ይኸውልህ ፡ ታዲያ ፡ እሱጋ ፡ እየወረደ ፡ የሱን ፡ ምስል ፡ ያነሣል ፡ ብለው ፡ ልጆች ፡ ነገሩኝ - - እኔ ፡ ደግሞ ፡ ምን ፡ ጠርጥሬ - - -

«አጥንቱ ፡ የተንቋቋ ፡ ሽማግሌ - - ምን ፡ ይሠራልኝ ፡ ብሎ - - -

«ጉዱ ፡ ሊመጣልህ ፡ አይደለም ? የሚካኤልን ፡ ምስል ፡ ሠራሁ ፡ አለልህና ፡ አመጣ - - - ! በቀኝ ፡ እጁ ፡ የመዘዘው ፡ ጐራዴ ፡ ይንተገተ ጋል ።— በግራ ፡ እጁ ፡ ሚዛኑን ፡ ከፍ ፡ አድርጐ ፡ ይዞ ፡ የፈጣሪን ፡ ፍርድ ፡ በሚገባ ፡ ያሳያል።-በወርቅ ፡ የተንቆጠቆጠ ፡ ክንፉ ፡ ላይን ፡ ያስፈራል —

የብርሃንነቱ ፡ ድልቅልቅታ ፡ መቼስ ፡ ይኸ ፡ ነው ፡ አይባልም - - ዲያብሎስን ፡ እሆዱ ፡ ላይ ፡ ስለቆመበት ፡ ምላሱን ፡ አስጐልጉሎታል — ያይኑ ፡ ደም ፡ መልበስ ፡ የግሩ ፡ ሁናቴ ፡ የጭራው ፡ አቆላለፍ - - ውጭ፡ ነፍስ ፡ ግቢ ፡ ነፍስ ፡ ሆኗል - - መቼም ፡ ደስ ፡ አለኝ ፡ ሲያመጣው - - ወዲያው ፡ ደብረ ፡ ሲና ፡ ላክሁና ፡ ነጭ ፡ ሐር ፡ አስገዝቼ ፡ አስሸፈንኩና ፡ አባቴ ፡ ሲመጡ ፡ አቀረብሁላቸዋ - - - ጐሽ ፡ ልጄ ! ጐሽ ፡ ልጄ ! እንዲህ ፡ ነው ! እንዲህ ፡ ነው ! እሱ ፡ ሚካኤል ፡ ከግራ ፡ ቀኝሽ ፡ ጥላ ፡ ከለላ ፡ ይሁንሽ - - የሠራውንም ፡ እጁን ፡ ይባርከው ፡ በማለት ፡ ወደ ፡ ቀኝ ፡ ወደ ፡ ግራ ፡ እያደረጉ ፡ ራቅ ፡ ቀረብ ፡ እያሉ ፡ ሲያውት ፡ ቆዩና ፡ ድንገት ፡ ፊታቸው ፡ ቅጭም ፡ ሲል ፡ ታየኝ - - - ምነው ፡ ምን ፡ ሆኑ ፡ አልኳቸው ፡ እኔም - - ምን ፡ ጥፋት ፡ ተገኘበት ? - - - የሊቀ ፡ መልአኩን ፡ ፊት ፡ ጠይም ፡ የዲያብሎስን ፡ ፊት ፡ ቀይ ፡ አድርጐት - - አዬ ፡ አዬ ፡ ሠርቶ ፡ መና ፡ እያሉ ፡ ብስጭትጭት ፡ አሉ ። — ማየቱን ፡ መቼም ፡ እኔም ፡ አይቼዋለሁ - - ታዲያ ፡ የዲያብሎስ ፡ ፊት ፡ የሚሠቃይ ፡ ፊት ፡ መሰለኝ ፡ ቅላቱ ፡ አልታየኝም ፡ ለጊዜው - - - ፊቱን ፡ ካላስለወጥሽ ፡ ይኸንን ፡ ይገቡ ፡ አልሄድም ፡ አይሉልህም ፡ ታዲያ ፡ አባ - - !

«እሳቸውም ፡ እንዲያው ፡ ለሁሉ ፡ ነገር ፡ ጥንቁቅነት ፡ ያበዛሉ - - -

«እንደ፡ፈረደብኝ፡ አስጠራሁና፡የሊቀ ፡ መልአኩን ፡ ፊት ፡ ቀላ ፡ የዲያብሎስን ፡ ጠቆር ፡ እንዲያደርገው ፡ ጠየቅሁት ፡ ሣሊውን - - - ሞቼ ፡ እገኛለሁ ፡ አይልልህም ፡ ታዲያ ፡ እሱ !

«ምን ? አልለውጥም ፡ ነው ?

«እንዲያሳ !

«ምነው ፡ አለ !

«ጉድና ፡ ጭራ ፡ ወደ ፡ ኋላ— ሽማግሌው ፡ ፊቱ ፡ ጠይም ፡ ነው ፡ አይለኝም ፡ እንዴ ? የቱ ? ምንም ፡ አላልኩ ፡ ብቻ ፡ የቱ ፡ ሽማግሌ ፡ አልኩት - - - የእርስዎ ፡ ጭሰኛ— እተረተሩ ፡ ላይ - - -

«የመዐት ፡ ያለህ !

«ከመዐት ፡ ያውጣህ ፡ ወንድሜ - - ! ትኩር ፡ ብዬ ፡ እየሁልሃ - - የሣለውን ፡ ምስል - - ቁርጥ ፡ ያያ ፡ አጅቤን ፡ መልክ - - ሚዛኑ ፡ ላይ ፡ ያሉት ፡ ነፍሳት ፡ ደግሞ ፡ ቁርጥ ፡ የሮማንንና ፡ የጂወኔን ፡ ፊት ፡ ዓይነት ፡ ያላቸው - - - ዓይኔም ፡ እንደሆን ፡ አላውቅ ፡ በኋላማ ፡ የዲያብሎስም ፡

ፊት ፡ የኔን ፡ ፊት ፡ መሰል ፡ አለኝ - - - ያንቺ ፡ ምስል ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ከሚለው ፡ መቼም ፡ አይብስም - - -

«ምን ፡ መዐት ፡ ወርዶብዎታል ፡ ወንድሜ !

«በል ፡ እንካ ፡ ወዲያ ፡ እምትወስድበት ፡ ውሰድ ፤ ባይኔ ፡ ሁለተኛ ፡ እንዳላየው ፡ ብዬ ፡ ከእልፍኝ ፡ አስወጣሁት ፡ እልሃለሁ - - - እውነት ፡ ነው ፡ የምልህ ፡ ያን ፡ ለት ፡ ነበር ፡ እሱን ፡ ከነጓደኛው ፡ ከቤቴ ፡ ማባረር ፡ የነበረብኝ - - -

«አባስ ፡ ምን ፡ አሉ - - ? እምቢ ፡ አለ ፡ ሲሏቸው - - -

«ግዴለም ፡ ይመልሰው—ፊቱን ፡ ባገር ፡ ቤት ፡ ሣሊ ፡ እናስለው ጠዋለን ፡ ብለው ፡ ነበር - - እኔ ፡ ግን ፡ እንደ ፡ ሰድቻ ፡ መታኝ - - ያያ ፡ አጅቤን ፡ ፊት ፡ መሳለሙ - - - ለሳቸው ፡ አልነገርኳቸውም - - ብነግራ ቸው ፡ በጃቸው ፡ ስለነኩት ፡ እንኳ ፡ ስንት ፡ ቀን ፡ ሱባዔ ፡ እንደሚገቡ ፡ እግዜር ፡ ይወቅ - - -

«ምን ፡ አረገው ፡ ለመሆኑ ፡ ምስሉን - - -

«እዚህ ፡ ወደ ፡ እዳሉ ፡ ውስጥ ፡ የተተከለ ፡ ሚካኤል ፡ አለ ፤ ለሱ ፡ ሰጠው ፡ ይሉኛል - -

«ወይ ፡ እያ ፡ አጅቤ - - ዕድሜ ፡ ልኩን ፡ የቁም ፡ ስቅሉን ፡ ሲያይ ፡ ሊኖር ፡ ነዋ !

«እሱ ፡ ብቻ ፡ ሊቀ ፡ መልአኩ ፡ ይቅር ፡ ይበላቸው ፡ የሚሳለሙትን ፡ ሰዎች - - -

«አይ ፡ እነሱማ ፡ ሚካኤልን ፡ በነፍስ ፡ አላዩት ፡ በምን ፡ ይወቁት ? የለም ፡ እነሱ ፡ አይፈረድባቸውም - - -

«እያ ፡ አጅቤንስ ፡ መቼ ፡ ያውቁታል ፡ እሱንማ ፡ ካልህ - - እውነ ትህን ፡ ነው — እኛም ፡ አጅቤን ፡ ባናውቀው ፡ ኖሮ ፡ እንሳለመው ፡ ነበር - - እግዚአብሔር ፡ በቸርነቱ ፡ ይቅር ፡ እንደሚለን ፡ አይጠረጠ ርም - - -

«ታዲያ ፡ እርስዎም ፡ ሱባዔ ፡ ለመግባት ፡ አስበዋል - - - ?

«የለም ፡ እኔስ ፡ ዘዴ ፡ አድርጌበታለሁ - - - አንድ ፡ መቃብር ፡ ቤት ፡ የሚኖሩ ፡ የበቁ ፡ ባሕታዊ - - ከስሜን ፡ ነው ፡ አሉ ፡ የመጡት - - እዚህ ፡

አረጋዊ ፡ ደብር ፡ አሉ ፡ ብለውኝ ፡ በጴጥሮስ ፡ በኩል ፡ የሚያስፈልገውን ፡ ገንዘብና ፡ እርዳታ ፡ አድርጌ ፡ እሳቸው ፡ የሚያስፈልገውን ፡ ሁሉ ፡ አደ ርጋለሁ ፡ ብለው ፡ ቃል ፡ ገብተውልኛል - - - ባስተርጓሚ ፡ ነው ፡ አሉ ፡ የሚናገሩት - - - በሽተኛ ፡ ሁሉ ፡ ይፈውሳሉ ፡ ይላሉ - - -

«ስለ ፡ እነዚህስ ፡ የከተማ ፡ ሰዎች ፡ ምን ፡ የበጀ ፡ ነገር ፡ አገኙላ ቸው - - - ?

«አይ ፡ እስከ ፡ ተነገ ፡ ወዲያ ፡ ድረስ ፡ እጠብቃቸውና ፡ ካልሄዱ ፡ ሮብ ፡ ወይ ፡ ኀሙስ ፡ ጧት ፡ ዘመድ ፡ እጠይቃለሁ ፡ ብዬ ፡ ከነ ፡ ልጄ ፡ ጥያቸው ፡ ነው ፡ እብስ ፡ የምለው - - ቀደም ፡ ብለው ፡ ከቤቴ ፡ እንዲ ሄዱልኝ ፡ በጠሎትህ ፡ አትርሳኝ - - ሮማንንም ፡ እንኳ ፡ ወደ ፡ ኋላዬ ፡ አል ተው - - ደግሞ ፡ እስቲ ፡ የወልዱስ ፡ አይብስ - - እሱ ፡ ነው ፡ ያባለጋ ቸው ፡ በየርስቱ ፡ ይዞ ፡ እየዞረ - - እዚህ ፡ ቦታ ፡ ጥሩ ፡ አደን ፡ እዚህ ፡ ቦታ ፡ ደስ ፡ የሚል ፡ ፏፏቴ ፡ አለ ፡ እያለ - - እርግጠኛ ፡ ነኝ ፡ እነሱ ፡ እዚህ ፡ አይቆዩም ፡ ነበር - - -

«ምነው ፡ ንግዱን ፡ ትተውታል ፡ እንዴ ፡ አብዬ ፡ ወልዱ - - -

«ምን ፡ እሱኮ ፡ ዱሮም ፡ ቢሆን ፡ ሥራውን ፡ አይሠራም ፤ አሽከ ሮች ፡ ናቸው ፡ የሚነግዱት - - የሱ ፡ ሥራ ፡ ካለፍ ፡ አገደም ፡ መቆ ጣጠር ፡ ነው - - -

«መጣፈ ፡ ቄደር ፡ ያስነከሯቸው ፡ እርስዎ ፡ መሆንዎን ፡ አባቴ ፡ ይነግሩኛል ። —ዓይንህን ፡ አላይም ፡ አለዚያ ፡ ብለው ። —ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ቆይ ታችኋል ፡ ይመስለኛል ፤ ለእንዴት ፡ ዋላችሁ ፡ አደራችሁ ፡ እንኳን ፡ ሳት ዳረሱ - - የሃይማኖት ፡ ነገር ፡ እሺ ፡ አይልዎትም - - -

« - - - ካንድ ፡ ዘጠኝ ፡ ዓመት ፡ በላይ - - ! የምን ፡ ኮተሊክ ፡ የምን ፡ መጫሚያ ፡ ሰኪ ፡ የምን ፡ ጨርቅ ፡ አሣሪ - - ታስታውስ ፡ እንደሁ - - - የኔ ፡ ነገር ፡ ደግሞ - - - ያኔ ፡ አንተ ፡ አልተፈጠርክም ፡ ቀድሞ - - ከየቴ ፡ ብለህ - - - እንዴትኮ ፡ ይመስልሃል ፡ ከነአርኮ ፡ በፊት ፡ አርኮን ፡ መስሎ ፡ የመጣው — ዥጉርጉር ፡ ጨርቅ ፡ ነገር ፡ አንገቱ ፡ ላይ ፡ አሥ ሯል - - አንዳገር ፡ የሚያብለጨልጭ ፡ ቁልፍ ፡ የተሸከመ ፡ ከቦርታ ፡ ደር ቧል - - ዛሬ ፡ ቦለሴ ፡ የምትሉትን ፡ ሱሪ ፡ ለብሷል - - ብቻ ፡ ምን ፡ አለፋህ - - አይሆኑ ፡ ሁኔታ ፡ ሆኖ ፡ ነበር ፡ የመጣው - - ታዲያ ፡ አሰ ጋሽ ፡ መቼ ፡ ዋዛ ! ዓይንህን ፡ እንዳላየው ። — መጣፈ ፡ ቄደር ፡ ሳትነከር ፡

የናት ፡ ያባትህን ፡ ቀዬ ፡ አትረግጣትም ፡ አልኩታ ! ሊቀ ፡ መልአኩን ፡ እንኳ ፡ እንዳይሰም ፡ ከመሳለሚያው ፡ ውጪ ፡ እንዲቆም ፡ እያስደረ ግሁ - - -

«እንዲህ ፡ ፍቅራችሁ ፡ ለሁሉ ፡ ሊያስቀና ! የማን ፡ እንትና ፡ ወንድም ፡ ነው ፡ በዛሬው ፡ ጊዜ ፡ ባባት ፡ እናቱ ፡ ርስት ፡ ያልተጋጨ - - ማንስ ፡ ነው ፡ መሬቱን ፡ ሳይካፈል ፡ ያፈራውን ፡ ብቻ ፡ እኩል ፡ እየበላ ፡ የሚኖር - - -

«ታዲያኮ ፡ አሁንም ፡ ቢሆን ፡ እንጣላለን ።— ያ ፡ የባሕር ፡ ማዶ ፡ ሚጣኑ ፡ መቼ ፡ ለቀቀው ፡ መሰለህ ! የፈረንጅ ፡ አገር ፡ ስም ፡ ሲጠራ ፡ በፈረንጅ ፡ አማርኛ ፡ ሲናገር ፡ እሰማዋለሁ - - - አሁን ፡ ከነዚህ ፡ ልጆች ፡ ጋር ፡ የሚሆነውን ፡ ነገር - - አፍ ፡ ለአፍ ፡ ገጥሞ ፡ ሲቦተልክ ፡ የሚውለውን ፡ ብትሰማ ፡ ግርም ፡ ነው ፡ የሚልህ - - ዱሮ ፡ ከሚያቃቸው ፡ ፈረንጆች ፡ ጋር ፡ ያለ ፡ ይመስለዋል ፡ መሰለኝ - - የኔ ፡ ያስጋሽ ፡ ግቢ ፡ መሆኑን ፡ ይረሳዋል - - - መጣፊ ፡ ቄደር ? ! አዎ ፡ መጣፊ ፡ ቄደርስ ፡ አስነክሬው ፡ ነበር - - - በነገራችን ፡ ላይ ፡ እዚህ ፡ ጆውሃ ፡ ትልቅ ፡ ጠበል ፡ ፈልቋል ፡ ይላሉ ፤ ለቁርጥማትም ፡ ጠሩ ፡ ነው ፡ ይሉኛል - - ፍል ፡ ውሃ ፡ ነገር ፡ ከመሬት ፡ እየፈለቀ - - -

«እንዲህ ፡ አይደለም - - - ለኔማ ፡ ምን ፡ ልንገርዎ ፡ እንደ ፡ ቤቴ ፡ ያህል ፡ ሆኗል ።— እያቅራቢያው ፡ የሚኖሩትን ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ዐውቃቸዋለሁ - - በየጊዜው ፡ ነው ፡ የምሄደው - - ሥራሥርን ፡ ነውኮ ፡ የሚያፍታታው ፡ እንዲህ ፡ አይምሰልዎት - - ሁለት ፡ ቀን ፡ ቢጠመቁ ፡ የያዘዎ ፡ አባዜ ፡ ነው ፡ ከትከሻዎ ፡ ላይ ፡ ለቆዎት ፡ ብድግ ፡ ሲል ፡ የሚሰማዎት - - -

«አባዜስ ፡ አልያዘኝም ፤ እንዲያው ፡ ይኸን ፡ የእግሬን ፡ ቁርጥማት ፡ አንድ ፡ ቢልልኝ ፡ ብዬ ፡ ነበር - - ! ታዲያ ፡ እንግዲያው ፡ አሁን ፡ አንተ ፡ ልጁ ፡ እያለህ ፡ ምንድነው ፡ ሽጉዱ - - ዓርብ ፡ ባስራዘጠኝ ፡ ገብሬል ፡ ቅዳሜ ፡ እንጊታ ፡ ማርያም - - እርግጠኛ ፡ ነኝ ፡ የዘረ ፡ ክርስቲያን ፡ ልጅ— ሁለቱንም ፡ ታቦቶች ፡ እንደምታከብር - - -

«አይ ፡ እኔ ፡ እንኳን - - -

«እንግዲያው ፡ ለዚህ ፡ ነው ፡ ይኸውልህ ፡ ያስፈለግሁህ - - የወደዱትን ፡ ቢያጡ ፡ የጠሉትን ፡ ይቀላውጡ - - ከነዚህም ፡ የውምበርሴት ፡ ሰዎች ፡ ታድነኛለህ - - ለመቼ ፡ ልትሆነኝ ፡ ነው - - -

«መቼስ ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ ከታጣ--እሱ ፡ እንኳን ፡ የሚያሳስት ፡ አል ነበረም ፡ ቦታው ---

«ምነው ፡ እንዳንተ ፡ ያለ ፡ ሸንቃጣ ፡ ወታደር ፡ እጐኔ ፡ ማስከተ ሌስ— ምን ፡ ያውጣ --?

«እሺ ፡ እንግዲያው ፡ መቼስ ? ማለድ ፡ ብዬ ፡ እመጣለሁ ፡ ዓርብ ፡ ጧት ---

« የለም ፡ ማለዳ ፡ አይደለም ።—ሐሙስ ፡ መጥተህ ፡ እዚሁ ፡ ታድ ርና ፡ አብረን ፡ ሆነን ፡ የሚያስፈልገውን ፡ እናዘገጃጅና ፡ ዓርብ ፡ ጧት ፡ ለማኝ ፡ ሳያራ ፡ ተነሥተን ፡ መንገድ ፡ እንገባለን ---

«መልካም ፡ እንግዲያው -- ሐሙስ ፡ ወደ ፡ ማታ ፡ ገደማ ፡ እመጣ ለሁ ---

«ይኸው ፡ ነው ፡ እንግዲህ ፡ ለእናትህና ፡ ለአባትህ ፡ ሰላምታዬን ፡ አድርስልኝ -- ደኅና ፡ ናችሆይ -- ብርቱ ፡ ናችሆይ -- እንዴት ፡ ከርማ ችኋል -- ብርቱ ፡ ከርማችኋሎይ -- በጐ ፡ ናችሆይ ፡ በጐ ፡ ናችሆይ ----

# ፳፱

# አደፍርስ

አደፍርስ ፡ የአባ ፡ አዲሴን ፡ ጠበል ፡ ሸሽቶ ፡ እንደ ፡ ወጣ ፡ ቀጭን ፡ የእግር ፡ ስላች ፡ ተከትሎ ፡ በመዝናናት ፡ ዓይነት ፡ መንገድ ፡ ያዘግማል ፤ ከዚያ ፡ በፊት ፡ ያለፈበት ፡ ስላች ፡ መሆኑንም ፡ ያለማጤን ።—እጉድባው ፡ ከደረሰ ፡ በኋላ ፡ ነው ፡ የሚያውቀው - - የተደበደበውን ፡ የሚያስታው ሰው - - ይቆማል—ዙሪያ ፡ አካባቢውን ፡ በጥንቃቄ ፡ ይመለከታል—ችፍግ ፡ ብሎ ፡ የሚታየውን ፡ የኩሬውን ፡ ዙሪያ ፡ በማጥናት ፤ ምንም ፡ ሕይወት ፡ አይንቀሳቀስበትም ።— ራሱን ፡ ውሃውን ፡ ያጠናዋል ፡ ይቀጥልና ፡ ቀረብ ፡ ብሎ — ያይጥ ፡ ዓሣዎች ፡ ይምሽከሽካሉ ፤ ውስጥ ፡ ውስጡን —እንቁራሪቶች ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ ብቅ ፡ ጥልቅ ፡ ይላሉ ፤ ያንገታቸውን ፡ ሥር ፡ በውሃ ፡ ቀብተው — ከምን ፡ ወይም ፡ ከወዴት ፡ እንደ ሆነ ፡ ባልታወቀ ፡ እምሽ..ክ -እምሽ..ክ ! እያለ ፡ እያረፈ ፡ በሚሰማ ፡ ያቅራቢያ ፡ ድምፅ ፡ እየታጀቡ ።— በግምት ፡ የአሥራ ፡ አራት ፡ ዓመት ፡ ዕድሜ ፡ የሚኖራት ፡ አንዲት ፡ ልጅ ፡ እንስራዋን ፡ እጀርባዋ ፡ ላይ ፡ እያመናሸች ፡ ብቅ ፡ ትላለች ፡ በዚያው ፡ ባንዱ ፡ ስላች ።— ዝግ ፡ ብላም ፡ ወደ ፡ ጉድባው ፡ ትገባለች ።—የጭቃ ፡ ብጥብጥ ፡ የሚመስለውን ፡ ውሃ ፡ ደምቦቅ ፡ ደምቦቅ ፡ ስታደርገው ፡ ይመለከታል ፡ በአንኮላ — አደፍርስ ። ከቀኟ ፡ በኩል ፡ ትልቅ ፡ ትክል ፡ ጥቁር ፡ ድንጋይ ፡ ይታያል ። ከግራዋ ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፡ ኩሬውና ፡ የባሻገሩ ፡ ጢሻ ፡ አለ ።—ካለፍ ፡ አገደም ፡ ፊቷን ፡ ትኮስትርበታለች ፡ በጢሻው ።— ቀድታ ፡ ልታበቃ ፡ አቅራቢያ ፡ ነው ፡ እምሽክ ፡ እምሽክ ፡ ድንገት ፡ የምትከሰተው— በቋጥኙ ፡ አናት ፡ ላይ ፡ ብቅ ፡ የምትለው— አህያዋ ፡ ኖራለች ።— ቀናም ፡ ብላ ፡ አልተመለከተቻት ፡ ውሃ ፡ ቀጂዋ — ምንዝካዋ ፡ ከአካባቢው ፡ ከሚመነጨው ፡ ድምፅ ፡ ጋር ፡ ተዋሕዶ ፡ የራሱ ፡ የሆነ ፡ መልለያ ፡ የሌለው ፡ ይመስል - - የተለመደ ፡ ጩኸት - - መላልሶ ፡ መላልሶ ፡ የሄዱትን ፡ መንገድ ፡ ይመስል - - ዕለት ፡ በዕለት ፡ የማትለየው ፡ የብዙ ፡ ዘመን ፡ ጓደኛዋ ፡ ይመስል — ምንም ፡ ነገር ፡ የሰማች ፡ አልመሰለችም ።— እንስራዋን ፡ ሞልታ ፡ በሆዷ ፡ ጭምር ፡ ገፍታ ፡ በማንሣት ፡ እቋጥኙ ፡ ላይ ፡ ታስቀምጥና— ቀስ ፡ ቀስ ፡ እያለች— እንስራው ፡ ዙሪያ ፡ እታበተውና ፡

በደረቷ ፡ ዙሪያ ፡ በሚያልፈው ፡ ገመድ ፡ ውስጥ ፡ ትከሻዋን ፡ በማንሸ
ራተት ፡ ጀርባዋ ፡ በእንስራው ፡ ትይዩ ፡ ሲሆን ፡ ተሸክማ ፡ ጉድባውን ፡
ትወጣለች— ጢሻውን ፡ ገርምማ - - - ጸጉሯ ፡ ስለተሸረበ ፡ ፊቷ ፡ ጢም ፡
ብሎ ፡ የሞላ ፡ ይመስላል ። — ከወገቧ ፡ በታች ፡ አጭር ፡ ሽርጥ ፡ ታጥቃ
ለች ። —ከወገቧ ፡ በላይ ፡ ግን ፡ ሳትለብስ ፡ የለበሰች ፡ ትመስላለች ። —
የልብስ ፡ አስፈላጊነት ! ለባሹ ፡ ካልተሰማው ፡ በስተቀር ፡ ተመልካች ፡
የማያየው ፡ ይመስል ! እንስራዋን ፡ እጀርባዋ ፡ ላይ ፡ ሽር ፡ ሽር ፡ እያደ
ረገች ፡ ወደ ፡ ቤቷ ፡ ታቀናለች ። —

አደፍርስ ፡ ቁጭ ፡ ይላል ፡ እኩሬው ፡ አጠገብ— ኩሬ ፡ ኩሬውን ፡
እየተመለከተ - - - ጠጠር ፡ እያነሣ ፡ ወደ ፡ ኩሬው ፡ ውስጥ ፡ መወርወር ፡
ይጀምራል - - ያይጥ ፡ ዓሣዎች ፡ ይሠርጋሉ - - እንቁራሪቶችም ፡ አልፎ ፡
አልፎ ፡ እንኳን ፡ ድምፃቸው ፡ መሰማቱ ፡ ይቀራል - - ሠፈሩ ፡ ሁሉ ፡
እርጭ ፡ ይላል ። — አህያዋ ፡ እንኳን ፡ ዝም ፡ ብላ ፡ እሱን ፡ እሱኑ ፡ ታየዋ
ለች ። — ጠጠር ፡ እያነሣ ፡ ይወረውራል ፡ አደፍርስ - - ጠብታ ፡ ትንሽ ፡
ክብ— ትልቅ ፡ ክብ— ትልልቅ— ትልልልቅ— ትልልልልቅ— ትልልል
ልልቅ— ክቦች ፡ እየፈጠረ ፡ ይጠፋል። —ድንገት ፡ አያምሩ ፡ አምሮት ፡
ያምረዋል ። —አይፈልጉ ፡ ፍላጐት ፡ ይፈልገዋል ። —ወረድ ፡ ብሎ ፡ በርከክ፡
ብሎ ፡ በጆቹ ፡ ዘገን ፡ ዘገን ፡ እያደረገ ፡ ከዚያ ፡ ኩሬ ፡ መጠጣት ! እንደ ፡
ሰዎቹም ፡ ብድግ ፡ ማለቱ ፡ አልቀረም - - ያመነታል - - ያስባል —

- - - አሜባ ፡ የያዘኝ ፡ እንደሁ - - ትል ፡ ያፈራ ፡ እንደሁ ፡ ጨጓራዬ ፡
ጉሮሮዬ ፡ ዐልቅት ፡ የተጣበቀስ ፡ እንደሁ - - እንዴ—ሐኪም ፡ ቤት ፡
ካንዲት ፡ ልጅ ፡ ጉሮሮ ፡ ውስጥ ፡ በመጐጥ ፡ ነገር ፡ መኝርጠው ፡ ሲያ
ወጡት ፡ አይቻለሁ - - እንዴት ፡ ነው ፡ የሰገጠጠኝ - - አፈሩስ ፡
እጉበቴ ፡ ውስጥ ፡ ቀርቶ ፡ ያኮረተ ፡ እንደሁ - - ሌላው ፡ ቢቀር ፡ ተቅማጥ ፡
ሊያስከትል ፡ ይችላል - - -

ውሃ ፡ ቀጅዋ ፡ እንደገና ፡ ትመለሳለች ። — የጢሻውን ፡ አጠገብ ፡
አሁንም ፡ ገላምጣው ፡ ትሄዳለች— ቀድታ ፡ ስታበቃ ። — አደፍርስን ፡
ግን ፡ ከቁም ፡ ነገርም ፡ የቆጠረችው ፡ አልመሰለች ። — አደፍርስ ፡ ተመ
ልሶ ፡ ይቀመጣል - - -

- - እንዲህ ፡ ያለች ፡ ነገር - - ያጐጠጐጢዋ ፡ አቀማመጥ ፡ ደሞ - -
በችንካር ፡ የቆመ ፡ ይመስል - - ነቅነቅ ፡ እንኳ ፡ አይልም - - አይበርዳ
ትም ፡ ልበል - - ምንኛ ፡ ጥብቅ ፡ ያለ ፡ ሰውነት ፡ ቢኖራት ፡ ነው - - አሁን ፡

ጠጋ ፡ ብላት ፡ ትጮሃለች -- ምን ፡ ይባላል ፡ በኋላ ፡ ወይዘሮ ፡ አሰጋሽ ፡ ቢሰሙ -- ወይ ፡ አባቷ ፡ እዚሁ ፡ አቅራቢያ ፡ ያርስ ፡ ይሆናል -- ወይምኮ ፡ እኔ ፡ እዚህ ፡ መኖሬን ፡ ዐውቀው ፡ ይሆናል ፡ እየደጋገሙ ፡ የሚል ኳት -- ለማሳት ፡ ያህል -- ! ሞኝ ፡ ሕዝብ -- እንዝህላል ፡ ይመስላል ፡ ደርሶ ፡ ተንኮሉን ፡ እብሽሽቱ ፡ ይዞ -- » ይወረውራል ፡ አሁንም ፡ ጠጠሩን -- ጠብታ ፡ ትንሽ ፡ ክብ ፡ ትልቅ ፡ ክብ ፡ ትልልቅ ፡ ትልልልቅ — ትልልልልቅ ፡ ክቦች ፡ እየሠራ ፡ ይጠፋል ።— አሁንም ፡ ትመጣለች ፡ ውሃ ፡ ቀጂዋ ! ቀድታ ፡ ታበቃለች ።— ወደ ፡ ጢሻውም ፡ መልኩት ፡ ብላ ፡ መገርመም ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ከደረቷ ፡ ትንጠራራና ፡ በኀይል ፡ ቱፍ ፡ ብላበት ፡ መንገዷን ፡ ትቀጥላለች --- ከጢሻው ፡ ሥር ፡ ክብረት ፡ ብቅ ፡ ይላል -- አንድ ፡ አነስ ፡ ያለች ፡ የሥዕል ፡ መንደፊያ ፡ ደብተርና ፡ እርሳስ ፡ በእጁ ፡ እንደያዘ ---

«ተፍታብን ፡ ሄደችኮ ፡ በል ! ተፋችብንኮ ! ተፋችብን -- ! » አደፍርስ ፡ ምንም ፡ አይመልስም « ተፍታብን ፡ ሄደችኮ -- » ይቀጥላል ፡ አሁንም ።—

«ፋደት ፡ ፋደት ፡ ሸተናት ፡ ይሆናል -- ! » ይመልስለታል ፡ አደፍርስ ፤ በልቡ ፡ ያወጣ ፡ ያወርድ ፡ የነበረውን ፡ ነገር ፡ ፈጽሞ ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ ፡ አይቶ ፡ ይታዘበው ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ ሲረዳው ---

«ይገርምሃል ! ዛሬ ፡ ሳይቀናኝ ፡ የቀረ ፡ አይመስለኝም ! በዚህ ፡ በንድፌ ፡ የተመሠረተ ፡ መልክ ፡ ለማስፈር ፡ ከቻልሁ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ውበትን ፡ ያዝኳት ፡ ለማለት ፡ እችላለሁ ---

«ኢትዮጵያዊ ፡ ውበት ! ትቀልዳለህ ! ኢትዮጵያዊ ፡ ውበት ፡ የሚባል ፡ ነገር ፡ የለም -- ውበት ፡ ውበት ፡ ነው -- ውበትን ፡ ቦታ ፡ አይወስነውም -- ቀለም ፡ አይከልለውም -- ጊዜ ፡ አያስረጀውም ---

«እሱን ፡ እንኳን ፡ ተወው ! ማጠቃለሉን --- ኢትዮጵያዊ ፡ መልክ ፡ ካለ ፡ ኢትዮጵያዊም ፡ ውበት ፡ አለ ።— ምናልባት ፡ አንተን ፡ ያጠራጠረህ ፡ በቅርጽ ፡ ሠሪ ፡ በሠዓሊም ፡ ሆነ ፡ በጸሐፊ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ ተይዞ ፡ ባለማየትህ ፡ ይሆናል— ገና ፡ ስላልተጨበጠ ።— እርግጥ ፡ ነው— እምልህ -- ኢትዮጵያዊ ፡ የሆነ ፡ ግርማ ፡ ሞገስ ፡ ያጐላው ፡ ዘላለማዊ ፡ ውበት ፡ የሰፈነው ፡ እሰውነት ፡ ቅርጽ ፡ ላይ ፡ አይደለም ።— አቋቋምም ፡ ላይ ፡ አይደለም ።— ዝለት ፡ እሚያሳይ ፡ ቀስ ፡ አለ ፡ አረማመድና ፡ ጥንካሬንና ፡ ኀይልን ፡ እሚያሳይ ፡ ንቅናቄም ፡ ላይ ፡ አይደለም—

ውብ ፡ የሰውነት ፡ ትክል ፡ የሚታየው ።— ለምሳሌ ፡ አንዲት ፡ ኢትዮጵ
ያዊትን ፡ ቆንጆ ፡ የምንላት ፡ እንደ ፡ ሐውልት ፡ የተቀረጸች ፡ ሰው ፡
በመሆኗ ፡ አይደለም ። ከሚያበሩ ፡ ዓይኖቿ ፡ የንዳፌነት ፡ ፍላጐት ፡ እንደ ፡
ብርሃን ፡ ወራውርት ፡ ሲንነፍ ፡ ያየን ፡ እንደሆነም ፡ አይደለም ።—ከን
ፈሮቿ ፡ ፈዘዝ ፡ ባለ ፡ የየዋኀን ፡ ሕፃናት ፡ ፈገግታ ፡ በሚመስል ፡ የመ
ሳብ ፡ ዘዬ ፡ ተገልጠው ፡ ያየን ፡ እንደሆነም ፡ አይደለም - - ሌላው ፡
ቀርቶ ፡ ገርጣ ፡ ያለ ፡ ቆዳ ፡ ደከም ፡ ያለ ፡ አስተያየት ፡ የደም ፡ መሽከርከ
ርን ፡ የሚያሳዩ ፡ ጉንጮች ፡ እንኳ ፡ ቢሆኑ ፡ የኛ ፡ አገር ፡ የውብ ፡ መልክ ፡
ምልክቶች ፡ አይደሉም ፤ የኢትዮጵያን ፡ ውበት ፡ አያሳዩም - - -

«እንግዲህ ፡ እንዲያ ፡ ከሆነ ፡ የኢትዮጵያዊት ፡ ውበት ፡ የማይያዝ ፡
የማይጨበጥ ፡ በአእምሮ ፡ ውስጥ ፡ ብቻ ፡ ያለ ፡ የሚመስል ፡ ነው ፡ ማለት ፡
ነው - - እንዲያ ፡ ከሆነ ፡ ደሞ - - ራሳችንን ፡ መደለላችን ፡ ካልሆነ ፡
በቀር ፡ ውበት ፡ የለንም ፡ ማለት ፡ ነው - - -

«አላስጨረስከኝምኮ - - - !

«እኔስ ፡ አስጨርሼሃለሁ - - ብቻ ፡ ካስፈለገህ ፡ ቀጥል - - -

«እሺ ፡ እንግዲያውስ ፡ ስማ - - - የኢትዮጵያዊት ፡ መልክ ፡ እሚን
ቀሳቀስ ፡ ሕይወት ፡ ላይ ፡ ያሰፈፈ ፡ ነው ፤ ነፍስ ፡ ስታልፍ ፡ ስታገድም ፡
የሚታይበት ።— በድንጋይም ፡ ላይ ፡ ሆነ ፡ በመሣያ ፡ ሸራ ፡ ወይንም ፡
በወረቀት ፡ ላይ ፡ ጠቁሞ ፡ ለመያዝም ፡ ያስቸገረው ፡ በዚሁ ፡ ምክንያት ፡
ነው ።— ቆራጥነትና ፡ ልበ ፡ ሙሉነት ፡ ሲፍለቀለቁ ፡ ኀሊና ፡ ያልተቀበ
ላቸው ፡ ረቂቃን ፡ ሲዛዛቱ ፡ መስሎ ፡ ለመኖር ፡ የሚደረጉ ፡ ቸልተኛነት ፡
ቻይነትና ፡ ኀይለ ፡ ስሜት ፡ ሲዋጉ ፡ የተደበቁ ፡ ደስታዎችና ፡ ብሶቶች—
ጠቅላላ ፡ የሐሳብ ፡ ነጸብራቆች — እምቅ ፡ ጭምቅ ፡ ከሚለው ፡ ልብ ፡
እያውገነገኑ ፡ ሲወጡ ፡ የሚታይበት ፡ መነሳንስት ፡ ነው ።— በየፎቶው ፡
ቤት ፡ እንደተሰቀለው ፡ ዓይነት ፡ ሕይወት  የለሽ ፡ ባዶ ፡ ዓይኖች ፡ ያጐ
ጡበት ፡ ሐሳብና ፡ ስሜት ፡ የማይሠርጉበት ፡ መልክ ፡ ውበት ፡ ነኝ ፡
ካለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሰብእና ፡ ጠፋ ፡ ማለት ፡ ነው - - -

«በቃላት ፡ መቼም - - እውነቱን ፡ ልንገርህ ፡ ምንም ፡ አልያዝኩልህ
ም - - ምናልባት ፡ በመሣያ ፡ ሸራህ ፡ ይሳካልህ ፡ እንደሁ ፡ እናያለን - - - ይል
ቅ ፡ ወደ ፡ ቁም ፡ ነገሩ ፡ እንመለስና—ያቺ ፡ ልጅ ፡ ስንት ፡ ጊዜ ፡ እን
ደተመላለሰች ፡ አይተሃል - - - ?

«አዎ ፡ አይቻለሁ !» ይለዋል ፡ ከፋ ፡ ባለው ፡ አንደበት ።—

«ሦስት ፡ ጊዜ ፡ መጣችኮ ፡ እኔ ፡ እንኳን ፡ እያየኋት - - -

«እኔ ፡ ደሞ ፡ ብቻዬን ፡ ከዚያ ፡ በፊት ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ አይቻታለሁ - - ምን ፡ ይሁን ፡ ታዲያ - - - !

«እምልህ ፡ አሁን ፡ ያን ፡ ሁሉ ፡ ውሃ ፡ ምን ፡ ልታደርግበት ፡ ነው ? የሌላ - - -

«ጠላ ፡ ልትሞላበት - - -

«ቀልዱን ፡ ተወውና ፡ የሌላ ፡ ነገር ፡ አይመስልህም?—ምናልባት ፡ አንተን ፡ ወይም ፡ እኔን ፡ ለማጥመድ - - -

«አንተ ፡ ደሞ ፡ አይቸግሩ ፡ ችግር ፡ ይቸግረሃል ፡ ሁል ፡ ጊዜ - - -

«ሙት ፡ እውነቴን ፡ ነውኮ - - - !

«ለመሆኑ - - - ለመሆን - - - ምንህ ፡ ነው ፡ የሚጠመደው - - - እምልህ ፡ ምንድነህ ፡ አንተ ? ራስክን ፡ ከፍ ፡ አድርገህ ፡ ስለምታይ ፡ ብቻ ፡ አይመስልህም - - - -

« ሞትና ፡ ሕይወት ! እኔን ፡ ያበሰለኝ ፡ ጡሜ ፡ አንተንም ፡ አግኝቶህ ፡ ቢሆን ፡ኖሮ ፡ እንዲህ ፡ ባላልህ - - -

# ፴

# አደፍርስ

ሰኞ፡ሌሊትና፡ማክሰኞ፡እስከ፡ሰዓት፡ድረስ፡ያለማቋረጥ፡ይዘንባል።
ከሰዓት ፡ በኋላ ፡ ነው ፡ የመጀመሪያው ፡ ትንሽ ፡ ተግታ ፡ የተገኘው— እያ
ለፈ ፡ መጀጀሩም ፡ ባያቋርጥ ። ዳመናዎቹ ፡ አሁንም ፡ ለርከፍካፊቸው ፡
የሚዘጋጁ፡ይመስላል ፤ዝቅ፡ብለው፡ያሞለሙላሉ—ፀሐይን፡ሳይከልሉ።—
አልፎ ፡ አልፎም ፡ ፈለቅለቅ ፡ ፈለቅለቅ ፡ ይላሉ ፤ አብረቅራቂ ፡ ንስነሳ
ቸውን ፡ ለመቀጠል—በሽውታ ፡ በስልታ ፡ ዓይነት ፡ ድምፅ ፡ ለማነብነብ ፡
እሥራቸው ፡ የተንጣለለውን ፡ ብጫ ፡ አረንጓዴ ፡ አፈርማና ፡ ግራጫ ፡
አገር ፡ በድንገተኛ ፡ ውርጃቸው ፡ ለማጥለቅለቅ ። እስኪያም ፡ ቢሆን ፡
ትንተገተጋለች ፡ ታዲያ ፡ ፀሐይዋ — በዚህ ፡ ሁሉ ፡ የዳመና ፡ ጥርስምስ
ምና ፡ ትርግርግ ፡ መካከል ፡ እያለፈች - - ሞቃት ፡ ብሩኅ ፡ በብርሃን ፡
የሚምቦለቦል ፡ ዓይነት ፡ ሕይወት ፡ ሰጥታው ፡ ለቀኑ ።—

በነፋሱ ፡ ሲመናሸና ፡ ሲመሳቀል ፡ የቆየው ፡ ሣር ፡ አሁን ፡ እርጥበ
ቱን ፡ ይመገምጋል ፤ አይንቀሳቀስም ።— ቅጠላ ፡ ቅጠሎች ፡ እስከ ፡ ሥራ
ሥሮቻቸው ፡ ድረስ ፡ እርሰው ፡ በለዛዛዊ ፡ ግንዶቻቸው ፡ ላይ ፡ ይምሽከ
ሽካሉ ።—ወፎች ፡ ከየቦታው ፡ ይጠራራሉ - - ግሪሳው— ጨረባው—
ወማዩ—ንጉዴው—ዱዱቴው ።—እየተጋፋ ፡ የሚያልፈው ፡ ሽውሽውታ ፡
እየደከመና ፡ እየራቀ ፡ የሚሄደው ፡ የዝናብ ፡ጉርምርምታና ፡ ድርቅርቅታ ፡
ከያካባቢው ፡ ከሚፈልቀው ፡ ከሙሉና ፡ ከስንጥብ ፡ ጉሮሮ ፡ ይወጣ ፡ ከሚ
መስለው ፡ የሕይወት ፡ ሲርሲርታ— ኩርኩርታ —ችርችርታ ፡ ጋር ፡ ተዋ
ሕዶ ፡ ሲሰሙት ፡ የስሜት ፡ ታንቲራ ፡ ይቀሰቅሳል ።—መጫሚያ ፡ ሲጨ
ብጡ ፡ የነበሩት ፡ መንገዶች ፡ አሁን ፡ ይጨሳሉ - - ተግ ፡ እያለ ፡ ከሚ
ቸችረው ፡ ዶፍ ፡ የተነሣ ፡ ጭቃቸው ፡ በየቦታው ፡ አደጥድጦ - - -

ጺወኔ ፡ የባዘነች ፡ እምትመስል ፡ አንዲት ፡ ጥጃ ፡ ኋላ ፡ ኋላ ፡ እያለች ፡
የአደፍርስን ፡ እግር ፡ ተከትላ ፡ በወጣችበት ፡ ጊዜ ፡ አገሩ ፡ በሙሉ ፡
ደስስ . . . እያለ ፡ በየሠራ ፡ አካላት ፡ ውስጥ ፡ በሚሠርግ ፡ ውዶት ፡ ተሞ
ልቶ ፡ ነበር ። ሰማዩም ፡ እንኳን ፡ በከፊል ፡ ጠርቷል ፡ ለማለት ፡ ይቻ
ላል ።— ውጡና ፡ ተንሸርሸሩ ፡ በሚል ፡ ዓይነት ፡ ግልጹታ - - ! ሣሩና ፡

ችፍርጉ ፡ እግሮቿን ፡ እየደባበሷት ፡ በትኩስነት ፡ የሚቡለቀለቁት ፡ ጤዛ ፡ አዘል ፡ ቅጠላቅጠሎች ፡ ዙሪያዋን ፡ እየተንሻሹ ፡ የጥላና ፡ የብርሃን ፡ ውዝግቦች ፡ እላዋ ፡ ላይ ፡ እየወጡ ፡ እየጠለቁ — እየተውረገረጉ ፡ ነበር ፡ ጺወኔም ፡ አረማመዷ -- በነፋሱ ፡ ምሥጢር ፡ እየተገፋፋችና ፡ በወጣትነት ፡ ሕይወቷ ፡ እየተፍለቀለቀች -- ብዙ ፡ ወዲያ ፡ ወዲህ ፡ ካለች ፡ በኋላ ፡ ሳታስበው ፡ ነው ፡ ድንገት ፡ ከወደ ፡ ጢሻ ፡ ውስጥ ፡ ዱብ ፡ ሲል ፡ የምታየው —አደፍርስን ---

«አንተ --!» ትለዋለች ፡ ከወደኋላው—ድንግጥ ፡ ብሎ ፡ ዘወር ፡ ይላል ። «አገኘሁህ ፡ ይኸውልህ ፤ አገኘሁህ — ባንተ ፡ ቤት ፡ ተደብቀህ ፡ መምጣትህ ፡ ነበር ---

«ድን . . ቁ . . ርና ! ለመሆኑ ፡ እዚህ ፡ ምን ፡ አመጣሽ ? እንዴት ፡ አገኘሽኝ --!» ይላታል ፡ ድምፁ ፡ ድንጋጤውን ፡ እንዳያሳይ ፡ ለመደበቅ ፡ በመታገል «እምልሽኮ -- ብቻሽን ፡ እንዴት ፡ ትመጫለሽ ፡ ነው ? !» ይላታል ፡ ይቀጥልና ፡ ግራ ፡ በገባው ፡ ሁኔታ ።

«አሁን ፡ አትጠይቀኝ ! ምን ፡ ያስፈልጋል ፡ አሁን ፡ ጥያቄ --? ምን ፡ ያረጋል— አስልቺ ፡ ነገር --- አንተ ፡ የሄድህበትን ፡ ቦታ ፡ ለማግኘት ፡ ፈለግሁ ፤ መጣሁ -- አለቀ --!» ጠጋ ፡ ትልና ፡ ኮቱን ፡ ያዝ ፡ አድርጋ « ምነው ፡ ተቆጣህ ፡ እንዴ -- ? » ውበቷን ፡ በሚያጋንን ፡ በብሩህና ፡ ደስ ፡ ባለው ፡ ዓይን ፡ ትመለከተዋለች ፤ ሕፃናዊ ፡ እምነትን ፡ በሚተነፍስ ፡ አስተያየት « -- እንደ ፡ ጠረጠርሁት ፡ እዚህ ፡ ሳገኝህ ፡ ምንኛ ፡ ደስ ፡ አለኝ ፡ ይመስልሃል ? ምንኛ -- ! » ሳቅ ፡ በማለት ፡ እሱን ፡ እየተመለከተች « ምናልባት ፡ በጣም ፡ ርቀህ ፡ ሳትሄድ ፡ አትቀርም ፡ ብዬ ፡ ነበር --- ትናንትና ፡ የአባን ፡ ጠበል ፡ እንዳመለጥህ ፡ ነገር ፡ አሳቀኝና -- ወዲያው ፡ ሳቄ ፡ ወደ ፡ ሐዘን ፡ ተለውጦ ፡ ቀኑን ፡ ሙሉ ፡ ደስ ፡ ሳይለኝ ፡ መሸ -- ምን ፡ እንደ ፡ ነካኝ ፡ አላውቅም -- ስለዚህ ፡ አንተንም ፡ እንኳን ፡ ላይህ ፡ አልፈለግሁም ፡ ነበር -- ምን ፡ በወጣህ ፡ ትቸገር ፡ እኔ ፡ መላዬን ፡ ባጣሁ --» መልከት ፡ ትለዋለች ፡ ቀና ፡ ብላ « -- ደስ ፡ አላለህም -- ? ምነው ፡ ፊትህን ፡ ጨፍግገሃል ፡ ዛሬ --! አትናገርም ? ደስ ፡ አላለህም ? እኔስ ፡ እንደዚህ ፡ እንዳውሬ ፡ አሽትቼ ፡ ሳገኝህ ፡ ነገሩ ፡ ገርሞህ ፡ ያስደስትህ ፡ ነበር ፡ የመሰለኝ -- አንተ ፡ ግን ፡ እንቅልፍ ፡ የገረዘዘህ ፡ መስለሃል --- ይንቁ ፡ ይንቁ ፡ ጌታዬ ! ጺዎኔ ፡ ከርስዎ ፡ ጋር ፡ ናት --» ትንሽ ፡ ጉንተል ፡ ታደርገዋለች « ደኅና ፡ አይደለህም ? ምን ፡ ሆነሃል ---?

«ደኅና ፡ ነኝ ፡ እኔስ ፤ ብቻ ፡ ትንሽ ፡ ቅር ፡ ያለኝ ፡ እንደዚህ ፡ እርቀሽ ፡ ብቻሽን ፡ መምጣትሽ ፡ ነው - - -

«ይኸ ፡ የኔ ፡ ጉዳይ ፡ ነው - - ምነው ፡ ከሮማን ፡ ጋር ፡ ብመጣ ፡ ይሻል ፡ ኖሯል - - - ?

«አዎ ፡ ይሻል ፡ ነበር - -

«ባውቅ ፡ ኖሮ ፡ ይዣት ፡ እመጣ ፡ ነበር - - » እሮጥ ፡ ትልና ፡ ወደ ፊት— አንድ ፡ የወይራ ፡ ቀምበጥ ፡ በመቅጠፍ « እኔ ፡ ደሞ ፡ ሮማንን— ለምን ፡ እንደሆነ ፡ አላውቅም - - ላይንህም ፡ እንኳ ፡ ለማየት ፡ የምት ፈልጋት ፡ አልመሰለኝም - - ከኔ ፡ ጋር ፡ ደግሞ ፡ ብቻችንን ፡ ሆነን ፡ ስንጫወት ፡ ደስ ፡ ይለኛል ፡ ብለሽኝ ፡ ነበር ፤ ረሳኸው - - - ?

«አዎ ፡ ብየሻለሁ ፤ ግን ፡ እዚያው ፡ እግቢው ፡ ውስጥ ፡ ማለቴ ፡ ነበር - - -

«ምነው ፡ እዚህ ፡ ቢሆን ፡ ምናለበት ? ትፈራለህ - - ? ማንን ፡ ትፈ ራለህ - - - ?

«አዎን ፡ እፈራለሁ ! ራሴን ፡ እፈራለሁ - - » ስብርብር ፡ ሳቋን ፡ ታመጣለች ፡ ጺወኔ - - ወደ ፡ ሆዷ ፡ ወደ ፡ ሆዷ ፡ የምትውጠው ፡ እያስመሰለች ።— ትንፍስ ፡ ትንፍስ ፡ እያለች—

«ራስክን ፡ ትፈራለህ - - ? ራስክን ፡ ትፈራለህ - - ? ነገርህ ፡ ሁሉ ፡ ያስቀኛል- - - በጣም ፡ ያስቀኛል - - » ትለዋለች ።—

«እንዲያው ፡ ለመሆኑ ፡ ምን ፡ ሰበብ ፡ አግኝተሽ ፡ መጣሽ ፡ ይባላል ? እመየቴ ፡ ቢሰሙ - - ሌላ ፡ ያገሬው ፡ ሰው ፡ ቢያየን - - -

«ይኸ ፡ እባክህ ፡ ሊቸገሩበት ፡ አያሻም - - ይልቅ ፡ ስለ ፡ ሌላ ፡ ነገር ፡ እናውራ—ምን ፡ ኖሯል ፡ ልነግርህ ፡ ያሰብሁት - - ረሳሁት - - -

«ምናልባት ፡ እዚህ ፡ እንዴት ፡ እንደ ፡ መጣሽ ፡ እንደሆን - - ? » በመ ጠባበቅ ፡ ዓይን ፡ እየተመለከታት —

«አይ ፡ ኤዲያ - - ለምን ፡ ችክ ፡ ትላለህ— እስከዚህ ፡ እኔን ፡ ሕፃን ፡ ማድረግህ ፡ ነው ፡ እንዴ ? አንድ ፡ ነገር ፡ መደጋገም ፡ አይሰለችህም - - - ምን ፡ ልል ፡ ነበር ፡ የፈለግሁት - - ግዴለም ፡ አሁን ፡ እስታውሰዋለሁ - - ውዬ . . . ! እንዴት ፡ ደስ ፡ ይላል ፡ እዚህ ! ተመልከት ፡ እዛ ፡ ሥር ፡ የተለሸለሸውን ፡ ክርክም ፡ ያለውን ፡ ሣር - - ተመልከት ፡ ደግሞ ፡ እውጪ

የተጋደመውን ፡ የዚያን ፡ የዋንዛ ፡ ሥር - - ለምን ፡ ወደ ፡ ጫካው ፡ ውስጥ ፡ እንገባም - - ? ደስ ፡ ሲል ፡ እንዲህ ፡ አይምሰልህ - - -

«ጫካ ! አብደሻል ? ጤዛው ፡ ሁሉ ፡ ገና ፡ መቼ ፡ ረገፈ ! እርግጠኛ ፡ ነኝ ፤ በጣም ፡ ነው ፡ የሚያረጥበው ፡ ውስጡ - - ቅጠላ ፡ ቅጠሉን ፡ በነካሽ ፡ ቁጥር ፡ ጤዛው ፡ ሰውነትሽን ፡ እያራሰው - - እኔ ፡ ደሞ ፡ ኮት ፡ ወይም ፡ ቡልኮ ፡ አልለበስኩም ፡ እንደምታይው - - -

«እኔም ፡ አለበስኩም ፤ ምን ፡ ያስፈልጋል ? በጣምኮ ፡ ነው ፡ ደስ ፡ የሚለው - - እንሂድ ፡ እባክህ - - » እንደ ፡ መሮጥ ፡ እያለች ፡ ትጎትተዋለች ።— እያጉረመረመ ፡ ይከተላትና ፡ ወደ ፡ ጫካው ፡ ያመራሉ ።—

«ለመሆኑ ፡ ከግቢው ፡ ሲያጡሽ ፡ ምን ፡ ይሉ ፡ ይመስልሻል ? » እንደገና ፡ ይጠይቃታል ።—

«ልንገርህ - - ? » ስትል ፡ ትጀምራለች ፡ ጫካው ፡ መካከል ፡ ሲደርሱ « አሁን ፡ ልነግርህ ፡ እችላለሁ ፤ ወደ ፡ ኋላ ፡ ሮጠህ ፡ አትመለስም — እርግጠኛ ፡ ነኝ ፡ እሜዳ ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ ፡ እስከዚህም ፡ አትመጣ ፡ ነበር - - -

«ለምን - - - ?

«ዓርብ ፡ ጧት ፡ ጀውሃ ፡ ትሄዳለህ ፡ ከኛ ፡ ጋር - - - ?

«አዎ ፡ ለምን ፡ አልሄድም ፡ ከፈለጋችሁኝ - - - !

«በጧት ፡ ተነሣ ፡ ታዲያ ! ዓርብና ፡ ቅዳሜን ፡ እዚያው ፡ ውለን ፡ እሁድ ፡ ወደ ፡ ደብረ ፡ ሲና ፡ ትወጣለህ - - » ምንም ፡ መልስ ፡ አይመልስላትም ፤ ዝም ፡ ብሎ ፡ በሩቁ ፡ ይመለከታል « አይ ፡ እንግዲያው ፡ እኔም ፡ እዚህ ፡ እንዴት ፡ እንደ ፡ መጣሁ ፡ አልነግርህም - - -

« ዓርብ ፡ ጧት ፡ አብሪያችሁ ፡ ጀውሃ ፡ ድረስ ፡ እሄድና ፡ ከዚያ ፡ ያንለቱኑ ፡ ወደ ፡ ደብረ ፡ ሲና ፡ እወጣለሁ - - -

« ይገርምሃል ! እዚህ ፡ የመጣሁት ፡ ለምን ፡ መሰለህ - - ? አንድ ፡ ነገር ፡ ልነግርህ ፡ ፈልጌ - - -

«ምን - - ? ምንድነው ፡ ልትነግሪኝ ፡ የፈለግሽው - - - ?

«ማለት - - አንተ ፡ ከኛ ፡ ጋር ፡ ጀውሃ ፡ ሄደህ ፡ መክረም ፡ ያለብህ ፡ መሆኑን - - ቸኩዬ ፡ ነበር ፡ ልነግርህ - - -

«ምን ፡ ማለትሽ ፡ ነው ? አሁን ፡ እስከዚህ ፡ ድረስ ፡ ስድ ፡ እለቀቃለሁ ፡ ነው ፡ የምትይኝ - - እምልሽ - - እንዲያው ፡ ወዴት ፡ ሄደችም ፡

አትባይ ?— አረም ፡ አታርሚ ፡ ከብት ፡ አታስወጪ— ወይ ፡ ማምሻ ፡ እንጨት ፡ አትለቅሚ - - -

«ለምን ፡ አላርምም—ለምን ፡ አላስወጣም—ለምን ፡ አልለቅምም - - -

«አያሠሩሽማ ፡ በቃ ! ልሥራም ፡ ብትይ ፡ አያሠሩሽ ! እና ፡ አንድ ፡ ምክንያት ፡ ፈጥረሽ ፡ ይሆናል ፡ ከቤት ፡ የወጣሽው - - -

«ከቤት ፡ የወጣሁት - - ? ህእ . . . ወጣኋ ! በቃ ፡ ወጣሁ - - ! እም ልሀ—ምን ፡ ያረጋል ፡ ብለህ ፡ ነው ፡ አሁን ፡ ስለዚህ ፡ ማውራት - - - ? » በጅዋ ፡ ሙሉ ፡ ቅጠል ፡ አፍሳ ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ትበትናለች - - ውዬ . . . ! እንዴት ፡ ደስ ፡ ይላል ? ሠፈሩ ፡ ሁሉ - - ደስ ፡ አይልም - - ? ደስ ፡ ነው ፡ ያለኝ ፡ እኔስ - - ነገም ፡ እዚህ ፡ እንምጣ ፡ እባክህ - - -

«ሞትና ፡ ሕይወት ! መጀመሪያ ፡ ዛሬ ፡ እዚህ ፡ እንዴት ፡ ልትመጪ ፡ እንደቻልሽ ፡ ንገሪኝ - - ስለ ፡ ነገው - -

« - - አያስቸግርም ፡ እንመጣለን ! » ትሞላለታለች ፡ ጊወኔ ።—

«ቀልድም ፡ ታውቂበታለሽ ፡ ለካ - - - !

«የኔ ፡ ነገር ፡ እየረሳሁትኮ ፡ ነው ፡ ቀልድ ፡ አለመውደድህን - - ? እሺ ፡ አልቀልድም - - አንተ ፡ ብቻ ፡ አትቆጣ - - አሁን ፡ ልሂድና ፡ ለጥጃው ፡ ማር ፡ ልቦጭቅለት ፡ መሰለኝ ፤ ቶሎ ፡ እመለሳለሁ - - -

«ለጥጃው ? የምን ፡ ጥጃ - - !

«ምነው ፡ ቅድም ፡ አልነገርኩህም - - ?

«የት ፡ ነው ፡ የነገርሽኝ - - ?

« ውዬ ፡ አልነገርኩህም ? እንዴት ፡ ብዬ ! ረስቼው ፡ ይሆናል ።— አንዷን ፡ እቤት ፡ የታሠረች ፡ ጥጃ ፡ ለቅቄ ፡ በሷ ፡ ሰበብ ፡ ነው ፡ ልፈል ጋት ፡ ብዬ ፡ የወጣሁት - - -

«ታዲያስ - - - ?

«በቃ ! ምን ፡ ታዲያስ ፡ አለ - - ? ያ— ያ—ያኢ . . . ያ ! » በሩቁ ፡ ታሳየዋለች « ማ ፡ ሚሉት ፡ ቤተክሲያን ፡ ይሆን - - - ! ?

«የቱ ?»

«ያ ! ያ ! በግራችን ፡ በኩል ፡ ያለው - - - ?

«ሚካኤል ፡ ይሆናላ ! ሌላ ፡ ማን ፡ ይሆናል ? አገሩን ፡ ሁሉ ፡ ያለ በሰው ፡ መቼም ፡ እሱው ፡ ነው - - - እሺ ፡ እምልሽ ፡ ጥጃዋን ፡ ለቀቅ ሽና - - -

«- - እንዲህ ፡ መሰለህ ፡ እንዴ ? እምቧ ፡ እምቧ ፡ እያለች ፡ አስቸግ ራኝ - - - ለምለም ፡ ሣር ፡ በጄ ፡ ቦጨቅ ፡ ቦጨቅ ፡ አድርጌ ፡ እፊቷ ፡ ሳደ ርግላት ፡ ነው ፡ ዝም ፡ ያለችው - - -

« ስለ ፡ ሣር ፡ ቡጨታ ፡ አልነበረም ፡ የምናወራው - - እሺ ፡ ከዚያ ፡ ምን ፡ አደረግሽ - - -

«ምን ፡ አደርጋለሁ ፤ ምንም ፡ አላደረግሁ - - -

«ጥጃዋ ፡ ታዲያ ፡ የታለች - - - ?

«ታሥራለቻ ፡ ከመንገድ ፡ ወጣ ፡ ብላ - -» በሩቁ ፡ ፊለፊታቸው ፡ ያለውን ፡ ተራራ ፡ በመመልከት - - -

«እንደታሠረች ፡ አግኝቶስ ፡ አውሬ ፡ የበላት ፡ እንደሁ - - - ?

« ያ ፡ እተራራው ፡ ደረት ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ መንገድ ፡ እንዴት ፡ የተ ጠመዛዘዘ ፡ ነው - - ! እስኪ ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ወደ ፡ አጠገቡ ፡ እንሂድ - - ወደ ፡ አዲሳባ ፡ መሄጃችሁ ፡ በዚያ ፡ በኩል ፡ ነው - - - ?

«አዎን ፡ በዚያ ፡ በኩል ፡ ነው - - -

«በየት ፡ በየት ፡ አርጐ ፡ ነው ፡ የሚያስሄደው ? አታሳየኝም - - - ?

«ጥጃዋንስ ፡ አውሬ ፡ የበላት ፡ እንደሁ - - - ?

« አይበላትም ፤ እኛ ፡ ቀዬ ፡ ደግሞ ፡ አውሬ ፡ የለም - - ይኸኔ ፡ እሷ ፡ ለራሷ ፡ ደኅና ፡ ሣሯን ፡ ትበላለች - - እኔም ፡ ይኸው ፡ ደኅና ፡ ካንተ ፡ ጋር ፡ እጫወታለሁ - - -

«ምን ፡ ማለትሽ ፡ ነው ፡ ጂወኔ ? አትቀልጂ ! እኔ ፡ በምሬ ፡ ስጠይ ቅሽ - - -

«ምን ፡ ቀልድ ፡ አለ ፤ እውነቴን ፡ ነው - - ሆን ፡ ብዬ ፡ ጥጃዋን ፡ ለቀቅኋትና ፡ ከታሠረችበት ፡ ተከትያት ፡ መጣሁ - - -

«አሽከሮች ፡ ተልከው ፡ ያገኟትስ ፡ እንደሁ ፡ ጥጃዋን ? አንቺ ፡ ወዴት ፡ ሄድሽ ፡ ይባላል - - - ?

«አጥታት ፡ እሌላ ፡ ቦታ ፡ ትፈልጋለች ፡ ይባላል - - -

«ማን ፡ አሠራት ፡ ይባላል ፡ ታዲያ ---

«ታሥራ ፡ ተገኘች ፡ አይደለም ፡ የሚባለው ፤ ተጠላልፋ ፡ ተገኘች፣ ነው ---

«የሰው ፡ እሥርና ፡ ዐውቆ ፡ ተጠላልፎ ፡ የታሠረ ፡ መለየት ፡ አው ኳቸው ---

«ከዚህ ፡ በፊት ፡ ጥጃ ፡ ተጠላልፎ ፡ እንጂ ፡ የትም ፡ ታሥሮ ፡ ስላልተገኘ ፣ የታሠረ ፡ አይመስላቸውም ---

«አትቀልጅ ፡ እባክሽ -- ታሥራ ፡ አገኘናት ፡ ያሉ ፡ እንደሆነ ፡ ምን ፡ ይበጅሻል ? እስከ ፡ ዛሬ ፡ ያላሉ ፡ እንደሁ ፡ ዛሬ ፡ ላይሉ ፡ ነው --- ?

«ምንድነው ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ነገር -- ? ሰማይ ፡ ቢከነበልብንስ— ዛፉ ፡ ቢጐርሰንስ -- ተራራው ፡ እግር ፡ አውጥቶ ፡ ቢሄድስ -- ጥጃዋን ፡ አውሬ ፡ ቢበላትስ -- ምንድነው ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ነገር ? » እንደገና ፡ ቅጠል ፡ አፍሳ ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ትበትናለች « ምን ፡ ይሁን ፡ ታዲያ ---?!

« ካንቺ ፡ ቀድመው ፡ ያገኟት ፡ ይሆናል ፡ አሽከሮቹ ፤ እንደ ፡ ታሠ ረች ---! የለም ፡ ይቅርታሽንና ፡ እኔ ፡ ደስ ፡ አላለኝም ፡ ነገሩ -- እን መለስ -- አይሆንም ---

« ምን ፡ መሆንህ ፡ ነው -- ? ምንም ፡ ምንም ፡ ሳትነግረኝ -- ጃን ሆይ ፡ ስለ ፡ ሰጧችሁ ፡ ቤተ ፡ መንግሥት -- ስለዩንቨርስቲው -- ስላስ ተማሪዎቹ -- ስለትምህርቱ -- ምነው ፡ ቀስ ፡ ብለን ፡ እጫውትሻለሁ ፡ ብለኸኝ ---

«ስለ ፡ እሱ ፡ እዚያው ፡ እግቢም ፡ ቢሆን ፡ እናወራለን -- አሁን ፡ ቢሆን ፡ መመለስ ፡ አለብን -- እመየቴስ ፡ ምን ፡ ይሉ ፡ ቢሰሙ -- በሳ ቸው ፡ ግንጋኝነት ---

«እሺ ፡ እንግዲያው ፡ እንዳልህ ፡ መቼስ ---» የተመልሶ ፡ መንገዳ ቸውን ፡ እንደተያያዙት ፡ እሷ ፡ ቀስ ፡ እያለች ፡ ለመሄድ ፡ ስትፈልግ ፡ እሱ ፡ ያጣድፋታል « ለምን ፡ ታጣድፈኛለህ ! ቆይ -- ! ባይሆን ፡ እንኳን ፡ ቀስ ፡ እያልን ፡ እንሂድ -- የምን ፡ ጥድፊያ ፡ ነው -- » ልታስቀስ ሰው ፡ ትሞክራለች ።—

ብን ፡ ያለ ፡ የሚያነበንብ ፡ ካፊያ ፡ ማካፋት ፡ ይጀምራል «--- ይኸ ውልሽ ፡ መመለሳችን ፡ በጅቷል -- እጉል ፡ ቦታ ፡ ሊይዘን ፡ ነበር ፡

ዝናቡ - - -» በሩቁ ፡ እየተመለከተች ፡ ቀስ ፡ እያለች ፡ ትራመዳለች - - ምንም ፡ መልስ ፡ አትመልስለትም « ይኸ ፡ የክረምት ፡ ዝናብ ፡ አባራ ፡ ሲሉት ፡ አካፋ ፡ ነው - - » ምንም ፡ መልስ ፡ አያገኝም ፡ አሁንም - - - ጂወኔ ፡ ከመንገዱ ፡ ወጣ ፡ ወደምትል ፡ ሥርጥ ፡ ታመራለች - - አደፍ ርስ ፡ ይከተላታል - - ጥጃዋ ፡ የተቦጨቀላትን ፡ ጨሌ ፡ በላሏታ ፡ በጉል በቶቿ ፡ ጋደም ፡ ብላለች - - መንገከ— መንገከ— መንገከ ፡ ቆም— መንገከ— መንገከ— መንገከ ፡ ቆም ፡ እያደረገች ፡ አፏን - -ቀናም ፡ ብላ ፡ አላየቻቸው —

«አሁን ፡ ልትነግረኝ ፡ ትችላለህ ፡ እንግዲህ ፡ ስለ ፡ ጃንሆይ ፡ ቤተ ፡ መንግሥት - - -» ትለዋለች ፡ ጂወኔ—ከጥጃዋ ፡ አጠገብ ፡ ተመቻ ችታ ፡ ትቀመጥና —

«አብደሻል ፡ እንዴ ! እንደዚህ ፡ እያካፋ ፡ እንዴት ፡ እዚህ ፡ እን ቆያለን - - ጉንፋን ፡ ብርድ ፡ በሽታ ፡ ትክትክ - - እምልሽ ፡ ስንት ፡ ዓይ ነት ፡ በሽታ — ያስከትላል - - - » አንገቷ ፡ ላይ ፡ የነበረች ፡ ትንሽ ፡ አንገት ፡ ልብሷን ፡ ታወርድና — እጥጃዋ ፡ አጠገብ ፡ አመቻችታ ፡ አን ጥፋ —

«ያውልህ ፡ ሱሪህን ፡ እንዳያረጥብብህ- -እጨርቁ ፡ ላይ ፡ ተቀመጥ !» ትለዋለች ።

«ጂወኔ ! እኔ ፡ እንዲህ ፡ ያለውን ፡ ነገር ፡ አልቀበልም - - -

«እንዳልኩህ ፡ ይኸውና ፡ አሽከሮቹ ፡ አልወሰዷትም ፡ ጥጃዋን ፤ አሁን ፡ እንግዲህ ፡ ምን ፡ የሚያሰጋ ፡ ነገር ፡ አለ - - ?

«ትቀልጃለሽ ፡ ጂወኔ - - !

«ቢወስዷት ፡ ኖሮ ፡ እውነትም ፡ ቶሎ ፡ ወደ ፡ ቤት ፡ እንመለስ ፡ ነበር - - -

«ምነው ፡ ለራሳችንስ ፡ ጤንነት - - በሽታ ፡ ያመጣብናል ፡ ስልሽ ፡ አይገባሽም - - -

«ልጅ ፡ ሆነህ ፡ አሳድገኝ ! አሳድገኝ ! እያልክ ፡ እዝናብ ፡ ውስጥ ፡ ተጫውተህ ፡ አታውቅም - - - ?

«ያ ፡ ሌላ ፡ ይኸ ፡ ሌላ !

«እንግዲያው ፡ ያው ፡ ነው ፤ ዛሬም ፡ ቢሆን ፡ ልጆች ፡ ነን -- በሽታ ፡ አያመጣብንም ---

«አይ ፡ እንግዲህ ፡ አንቺ ፡ እንደ ፡ ብጤትሽ ! እኔ ፡ መሄዴ ፡ ነው -- እዚህ ፡ ኪኒን ፡ እንኳን ፡ እማይገኝበት ፡ አገር -- 'ፍሉ' ይዞኝ ፡ ለመማቀቅ ፡ አልፈልግም ---

«ጨክነህ ፡ ጥለሽኝ ፡ አትሄድም !

«ሞትና ፡ ሕይወት ፡ ብሎ ፡ ነገር -- ! የጭካኔ ፡ ነገር ፡ አይደለም ፡ ይሽ -- » ዘወር ፡ ብሎ ፡ መንገድ ፡ ይገባል ።

«ጨክነህ --- ?

«ነገርኩሽ ፡ እንግዲህ ---

« ጨክነህ -- ጨክነህ --- ? » እምቧ ፡ ማለት ፡ ትጀምራለች ፡ ጥጃዋ ፡ ከባሻገሯ ፡ የከብት ፡ ድምፅ ፡ ስትሰማ ---

# ፴፩

# አደፍርስ

ለሐሙስ ፡ አጥቢያ ፡ ሌሊትም ፡ እንዲሁ ፡ ዘጥሮ ፡ አደረ ፡ ዝናቡ— ዲደን ፡ ቅልቅል ፡ ሆኖ ፡ እየመጣ ፡ ሲያብረገርገው ።- ረፋድ ፡ ገደማ ፡ ነው ፡ ወደ ፡ ንፍንፍ ፡ የተለወጠው ።- ያም ፡ ሆኖ ፡ ታዲያ ፡ እስከ ፡ ሰዓት ፡ በኋላ ፡ ተግ ፡ አላለም ።— ጺወኔ ፡ ብርድ ፡ ብርድ ፡ እያላት ፡ እጅግም ፡ ጤና ፡ የላት ።— ረቡ ፡ ለት ፡ ስለ ፡ አደፍርስ ፡ የተሰማት ፡ ግብት ፡ ግራ ፡ አጋብቷታል ።— አንዳንዴ ፡ ለትስብኤ ፡ ያላት ፡ ሐቅረት ፡ ቀኖቱን ፡ በሠራ ፡ አከላቷ ፡ ነስንሶ ፡ ይሰማታል ።— አንዳንዴ ፡ የርቂት ፡ ዓለም ፡ አንዳንዴ ፡ የበከ ፡ ዓለም ፡ ይታያታል ፤ የሕይወቷ ፡ ሑረት ፡ በማይመ ረመር ፡ ምያኔ ፡ ተውጦ ፡ የሚቀር ፡ ይመስል - - በመታወቅ ፡ ምያኔ — በሀብታምነት ፡ ምያኔ—በሙዚቀኛነት ፡ ምያኔ— በጋብቻ ፡ ምያኔ— በዩ ንቨርስቲ ፡ ትምህርት ፡ በፈረንጅ ፡ አገር ፡ ትምህርት ፡ በዐዋቂነት ፡ ምያኔ።— አንዳንዴ ፡ ደግሞ ፡ ሰው ፡ የማይሰማው ፡ ሕሠም ፡ ያለባት ፡ ይመ ስል ፡ የፍራት ፡ ፍራት ፡ ባርባርታ ፡ ይተራመስባታል ።— ጕርፉ ፡ በቀ ጠሮው ፡ መሠረት ፡ ሲደርስ ፡ ከአደፍርስ ፡ ጋር ፡ አበረት ፡ ይገናኙና ፡ አብ ረው ፡ ወደ ፡ ወይዘሮ ፡ አሰጋሽ ፡ እልፍኝ ፡ ይሄዳሉ ።— ወይዘሮ ፡ አሰጋሽ ፡ እማሳ ፡ የደምበሾ ፡ ጉድጓድ ፡ አስከፍተው ፡ ማሽላ ፡ ያስወጡ ፡ ስለነበረ ፡ አያገኟቸውም ።— ጺወኔ ፡ ግን ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ስለነበረች ፡ ገባ ፡ ሲሉ ፡ ስታያቸው ፡ ቶሎ ፡ ራሷን ፡ ትገዛና ፡ ብድግ ፡ ትላለች ።

«ውዴ ፡ መጣህ ፡ እንዴ ፡ ጕርፉ - - ? እንኳን ፡ የመጣህ ! » ትልና «እማዬ ፡ እጉድጓድ ፡ቦታ ፡ ነች - - ቁጭ ፡ በሏ ፡ ታዲያ - - » አቡዳዎቹን ፡ እመደቡ ፡ ላይ ፡ ታስተካክልላቸዋለች ።

« ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ሳነጋግረው ፡ ፈልጌ ፡ አሁን ፡ ደኅና ፡ አጋጣሚ ፡ አገኘሁ ፡ መሰለኝ - - -» ይላል ፡ አደፍርስ ፡ ፈገግ ፡ ብሎ ።

« እረ ፡ ልታነጋግረው ፡ ፈልገህ ፡ ነበር ? ለምን ፡ አልነገርከኝም ፡ ታዲያ - - » ፊቷ ፡ ላይ ፡ የነበረው ፡ ጭጋግ ፡ ሳንዳፍታ ይነሣል ።

«አንቺ ፡ መቼም ፡ ሰውን ፡ ያለ ፡ አንድ ፡ ምክንያት ፡ ስለማትወጂ - - -

«ትወድሃለች ፡ በልና ፡ በል ፡ አኩራዋ ፡ እንግዲህ ? እንዲያውም ፡ እንዲያ ፡ ነሽ ፡ እንኳንስ ፡ ዘንቦብሽ ---

«መውደዷን ፡ ማወቅህ ፡ ያኮራሃል ?» ይጠይቀዋል ፡ ጐርፋን ፡ ወደ ፡ እሱ ፡ መለስ ፡ ብሎ ።

«ሀእ ! ! » ይልና ፡ ዝም ፡ ይላል ፡ ጐርፋ ።—

«ስቀልድ ፡ ነው ።— ጐርፋ ፡ ባይሆን ፡ የድንገት ፡ ክፊት ፡ አለበት ፡ እንጂ ፡ ኩራት ፡ አያውቅም -- ደሞ ፡ እንደምወደው ፡ ያውቃል -- ታውቅ ፡ የለም ፡ እንዴ ፡ ጐርፋ --- ?

«ሀእ ! ! » ይልና ፡ ዝም ፡ ይላል ፡ አሁንም

«መዋደድን ፡ የመሰለ ፡ ነገር ፡ የለም --» ይላል ፡ አደፍርስ ፤ ከማንም ፡ መልስ ፡ የማይፈልግ ፡ በሚመስል ፡ ድምፅ ።

« ዛቢያና ፡ ምሣርስ ፡ ይዋደድ ፡ የለም ? የመዋደድ ፡ ነገር -- ምን ፡ አሉ ፡ አሉት --?» ድንገት ፡ ያመጣዋል ፡ ጐርፋ ።

« እውነት ፡ ነው ፤ ብዙ ፡ ዓይነት ፡ መዋደድ ፡ አለ -- አሁን ፡ ለምሳሌ ፡ ለጊዜው ፡ የሚሆን ፡ የፍትወት ፡ መዋደድ ፡ አለ — እንግዳ ፡ ቁርበቶች ፡ አጉራ ፡ ዘላዮች ፡ ዘንድ ፡ እንደሚገኘው ፡ ዓይነት ።— በተፈጥሮ ፡ ባካባቢ ፡ ባይነት ፡ በፍላጐት ፡ የተገናኘ፡ በመመሳሰል ፡ ላይ ፡ የተመሠረተ ፡ መዋደድ ፡ አለ— ድመት ፡ ድመትን ፡ ውሻ ፡ ውሻን ፡ እንደሚወድ ፡ ዓይነት ።— ከልማድ ፡ የተነሣ ፡ አብሮ ፡ ከመኖርና ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ እየደጋገሙ ፡ ከመገናኘት ፡ የተነሣ ፡ የሚፈጠር ፡ መዋደድ ፡ አለ ፤ ለምሳሌ— ድመትና ፡ ውሻ ፡ እንደሚኖሩት ፡ ዓይነት ።— ከትንሽነት ፡ ወደ ፡ ትልቅነት ፡ ተከባክቦ ፡ ለሚያሳድጉት ፡ ነገር ፡ የሚኖር ፡ ልዩ ፡ ዓይነት ፡ መዋደድ ፡ አለ — የተከለውን ፡ ዛፍ ፡ ቢቆርጡበት ፡ ያሳደገውን ፡ ውሻ ፡ ቢመቱበት ፡ የሚወድ ፡ ማን ፡ አለ --- ?

«ታዲያ ፡ የኛ ፡ መዋደድ ፡ የትኛው ፡ ዓይነት ፡ ይመስልዎታል ?» ይጠይቃል ፡ ጐርፋ ፡ አደፍርስን ፡ ቀስ ፡ ብሎ ።

«እኔ ፡ ምን ፡ ዐውቃለሁ— የምታውቁት ፡ ራሳችሁ -- ልቡስ ፡ ጥላችሁ ፡ ተገናኝቶ ፡ እንደሁ ---

«እሺ ፡ እኔ ፡ ለምሳሌ ፡ አንተንም ፡ እወድሃለሁ ፤ እና---»ትለዋለች ጺወኔ ፡ አደፍርስን ፡ መሬት ፡ መሬት ፡ እየተመለከተች « -- የቱን ፡ ዓይነት ፡ መዋደድ ፡ ነው ፡ የኛ ---

«እንደ ፡ ድመትና ፡ ውሻው ፡ ዓይነት ፡ እንደሆን ? »ይመልሳል ፡ ጐርፉ ፡ አሁንም ፡ ቀስ ፡ ብሎ ።—

«ሊሆን ፡ ይችላል ፤ እውነትህን ፡ ነው ።— ለትንሽም ፡ ጊዜ ፡ ቢሆን ፡ እየደጋገሙ ፡ ከመገናኘት ፡ የተነሣ ፡ የሚፈጠር - - የማይሆን በት ፡ ምክንያት ፡ አይታየኝም— ሊሆን ፡ ይችላል - - -

«አይመስለኝም ! ! » ትላለች ፡ ጂወኔ ።— ድንገት ፡ አደፍርስና ፡ ጐርፉ ፡ ሲገቡ ፡ ወደነበረችበት ፡ ምያኔ ፡ በመመለስ - - ለትንሽ ፡ ጊዜ ፡ ሁሉም ፡ ዝም ፡ ይላሉ ።—

«ታዲያ ፡ እስኪ ፡ ትንሽ ፡ ስለ ፡ አገር ፡ ቤት ፡ ጨዋታ ፡ አምጣ ! » ይለዋል ፡ አደፍርስ ፡ ጐርፉን ።— ጐርፉ ፡ መልስ ፡ አይመልስም - - - «ስለ ፡ ፈለግሽው ፡ ነገር ፤ ስለ ፡ ባህሉ ፡ ስለ ፡ ኑሮው ፡ ስለ ፡ ጨዋታው - - - ! » አይመልስም ፡ አሁንም ፡ ጐርፉ « እምልህ ፡ ሌላው ፡ ቢቀር ፡ ብዙ ፡ በቃል ፡ ሲተላለፍ ፡ የኖረ ፡ ጨዋታ ፡ አለ - - እንደ ፡ ተረት ፡ ዓይነት— ለምሳሌ - - -

«ካወቁት ፡ እንግዲህ ፡ እርስዎ ፡ ያውጉና - - -

«መኖሩን ፡ ዐውቃለሁ ፤ እንዲህ ፡ ነው ፡ ብዬ ፡ ማውራት ፡ ባል ችልም - - -

«ታዲያ ፡ እንዴት ፡ ዐወቁት - - - ?

«እኔ ፡ ላሜውታችሁ ፡ አንድ ፡ ተረት - - - እንጃ ፡ ብቻ ፡ ምን ፡ ዓይነት ፡ ነው ፡ ልበል - - እያስቅም - - እያሳዝንም - - እንዲህ ፡ እንግ ዲህ ፡ አለ ፡ አይደለም - - -

«ጥሩ ፡ ጥሩ ፡ እንስማው - - - ! እስከዚያ ፡ ድረስ ፡ ደሞ - - - » ይልና ፡ ፈገግ ፡ ብሎ ፡ መለስ ፡ ይላል ፡ ወደ ፡ ጐርፉ ።

«ማነህ ፡ ባለ ፡ ሳምንት ፡ ማለትዎ ፡ ነው ? ይገባኛል - - ! እስኪ ፡ እንግዲህ ፡ የጂወኔን ፡ እንስማና - - -

«ያስጠምድህ ፡ ባሥራስምንት ፡ አይደለም ፡ አጃቢው ? » ይጠይቃል ፡ አደፍርስ ፡ አሁንም ፡ ወደ ፡ ጐርፉ ፡ ዘወር ፡ ብሎ - - -

«አቶ ፡ ጅብ ፡ ሦስት ፡ ልጆች ፡ ነበሩት ፡ ይባላል ።—በተወለዱበት ፡ ቦታ ፡ ስም ፡ ነበር ፡ የሚጠራቸው — አምቡልጋ ፡ አባ ፡ ጆቢጥ ፡ አዲላላ ፡ እያለ ።— እንደ ፡ ልባቸው ፡ ነበር ፡ የሚኖሩት - - » እያለች ፡

ትጀምራለች ፡ ጺወኔ «--አንድ ፡ ቀን ፡ አቶ ፡ ጅብ ፡ ከበኩር ፡ ልጁ ፡ ከአም ቡልጋ ፡ ጋር ፡ አብሮ ፡ ሲዝናና ፡ ያመሽና ፡ ሲመለስ ፡ ሁለቱ ፡ ልጆቹ ፡ አደን ፡ ውለው ፡ ኖሮ ፡ ምንም ፡ ሳይሳካላቸው ፡ ደክመው ፡ መመለሳቸ ውን ፡ ይነግሩታል ።— አባት ፡ ነውና ፡ መቼም— ይነደዋል ፡ በጣም ፡ ይነደዋል—በልጆቹ ፡ ሥራ ፡ አለመሳካት ።— ኑ ፡ እንውጣ ፡ ተመልሰን ፡ ይልና ፡ ይዟቸው ፡ ይሄዳል ።— ሰው ፡ ወደ ፡ ሚኖርበት ፡ ሠፈር ፡ ሄደው ፡ ያገኙትን ፡ እያገኙ ፡ ያስሳሉ ፡ ለብዙ ፡ ጊዜ ! አጣን ፡ ብለው ፡ ተስፋ ፡ ሊቆርጡ ፡ አቅራቢያ ፡ ነው ፡ ዕንግዲህ ፡ ያልታሰበ ፡ ዕድል ፡ የሚገጥማቸው ፤ አንድ ፡ የፈረጠጠች ፡ አህያ ፡ የሚያገኙት ። ይደሰታሉ ፤ ይፈነድቃሉ - - መቼስ ፡ ያልታሰበ ፡ ነገር ፡ የሚሰጠው ፡ ደስታ ፡ ምኑ ፡ ይጠየቃል ፡ ከዚያም ፡ አምቡልጋ ፡ ፈታውራሪ ፡ አባት ፡ ተገን ፡ ሆነው ፡ እየተከታተሉ ፡ ወደ ፡ ምንጭ ፡ አጠገብ ፡ ይነዷታል - -እያረፈ ፡ እያማገ ፡ ቀስ ፡ እያለ ፡ ነው ፡ የሚበላው ፡ ይባላል ፡ ዥብ - - እንዳህያ ፡ ዙሪያ ፡ ሆድ ፡ ነው ፡ ይባላል - - እዚህ ፡ አዲሳባ ፡ እሚሉትማ ፡ አገር ፡ ከሰው ፡ እኩል ፡ ነው ፡ አሉ ፡ የሚጋፋው - - እና ፡ ታዲያ ፡ ምናለ ፡ ከዚያማ ፡ እምንጩ ፡ አጠገብ ፡ እንደ ፡ ደረሱ ፡ አቶ ፡ አባት ፡ ቀስ ፡ ብሎ ፡ ያደባና ፡ ሆድቃዋን ፡ ዘርግፎ ፡ ሊጥላት ፡ ይሞክራል ።— እሷ ፡ ግን ፡ ኀይለኛ ፡ አህያ ፡ ጅማቷን ፡ እየጐተተች— ሆድ ፡ ዕቃዋን ፡ ቦትርፎ ፡ እስኪያወጣው ፡ ድረስ ፡ አትወድቅለትም - - የራበው ፡ ዥብ ፡ ግን ፡ ምን ፡ ርኀራኄ ፡ አለው ? ዓይኗ ፡ እያየ - - ፍርግጥ ፡ ፍርግጥ ፡ ስትል - - ነፍሷ ፡ ሳይወጣ - - ዓይኗ ፡ እያየ ፡ ይበላታል ፡ ቀስ ፡ እያለ ።— ራቡ ፡ ጋብ ፡ ሲልለት ፡ አህያዋም ፡ ስትሞት ፡ የኋላ ፡ ኋላ ፡ ነው ፡ አምቡልጋን ፡ ፊታውራሪውን ፡ እንኳን ፡ የሚጋብዘው ።— መጋበዝ ፡ ግን ፡ ይጋብዘ ዋል - - እና ፡ ሁለቱ ፡ ብቻ ፡ ዝም ፡ ብለው ፡ ይኘደኙዳሉ ።— አባ ፡ ጆቢጥና ፡ አዲላላ ፡ ተጋበዙ ፡ ይሉናል ፡ በማለት ፡ ቢጠባበቁ ፡ ከአቶ ፡ አባት ፡ ትንፍሽ ፡ ይጠፋል ፤ ይናደዳሉ ።— እንዲያው ፡ ለምናልባቱ ፡ ቢሆን ፡ ተገን ፡ ይዘው ፡ ይጠባበቃሉ ። የኋላ ፡ ኋላ ፡ አዲላላ ፡ አላስችል ፡ ይለውና ፡ ከአባ ፡ ጆቢጥ ፡ ተለይቶ ፡ ስጡኝ ፡ ብሎ ፡ አፍ ፡ አውጥቶ ፡ ስለሚጠይቅ ፡ አንድ ፡ ጆሮ ፡ ይወረውሩለታል - - አባ ፡ ጆቢጥን ፡ ግን ፡ ከልክለውት ፡ ዓይኑን ፡ እያቁለጨለጨ ፡ ሲመለከት ፡ ቆይቶ ፡ ሁናቴያ ቸው ፡ አላምር ፡ ይለውና ፡ መሸሻ ፡ ወደሚያመችበት ፡ ሥፍራ ፡ ጥቂት ፡ እንዳነከሰ ፡ አምቡልጋ ፡ አባቱን ፡ እንዲህ ፡ ይለዋል - - -

«የጨረቃ ፡ ንጋት ፡

የቦረቦር ፡ ልማት ! ስለማይታወቅ ፡ እንሂድ ! » አባት ፡ ግን ፡ የተመ ለከተው ፡ ሆዱን ፡ ብቻ ፡ ነበርና - - -

«የጨረቃ ፡ ንጋት ፡

ያህያ ፡ ስባት ፡

ዝም ፡ ብለህ ፡ ብቻ ፡ አንከት ! » ብሎ ፡ ንግግሩን ፡ እንደቀላል ፡ ይወስ ድበታል ። ወዲያው ፡ ይህን ፡ ተባብለው ፡ እርም ፡ ታህል ፡ ጊዜ ፡ ሳይቆዩ ፡ የአህያይቱ ፡ ባለቤት ፡ ዲሞትፈሩን ፡ አንግቶ ፡ ከተፍ ፡ ይልባቸዋል ። ሆዱ ፡ ከሞላ ፡ መቼም ፡ ሆዱ ፡ የጐደለ ፡ በኀይል ፡ ይሮጣልና ፡ አባ ፡ ጆቢጥ ፡ እግሬ ፡ አውጪኝ ፡ ሲል ፡ አባት ፡ መጣራት ፡ ይጀምራል - - -

«ልጄ ፡ አባ ፡ ጆቢጥ ፡

ልጄ ፡ አባ ፡ ጆቢጥ - - - !

«ብቻህን ፡ እንደ ፡ በላህ ፡ ብቻህን ፡ ሩጥ ! » ይደርሰዋል ፡ መልሱ ።—

«ልጄ ፡ አዲላላ ፡

ልጄ ፡ አዲላላ - - - ! » እንደገና ፡ ይጣራል ።

«ምን ፡ አቅምሰሽኛል ፡ ካንድ ፡ ጆሮ ፡ ሌላ - - ! » ይደርሰዋል ፡ መልሱ ።— በመጨረሻም ፡ የተማመነበት ፡ ልጅ ፡ ሲሸሽ ፡ በማየቱ ፡

« ልጄ ፡ አምቡልጋ - - - !

ልጄ ፡ አምቡልጋ - - ! » እየለ ፡ ቢጣራ

« ምነው ፡ እንሂድ ፡ ብየህ ፡ ሳይነጋ - - ! » ብሎት ፡ እብስ ፡ ማለት ፡ ነዋ ።— ምን ፡ ልበላችሁ ፡ እንግዲህ ፡ ከዚያ ፡ ወደዚያማ - - አቶ ፡ አባት - - ማንከሱም ፡ ባይቀር ፡ ለማምለጥ - - ብቻውን ፡ እንደበላ ፡ ብቻውን ፡ ቀራ ! !

«አህ . . . ! » ይልና ፡ እጅዋን ፡ ዘሎ ፡ ይይዘዋል ፡ አደፍርስ ፤ ወዲ ያውም ፡ ቶሎ ፡ ይለቃትና « ይቅርታ ! » ይላታል ፡ ድንግጥ ፡ ብሎ ።

«እንደዚህ ፡ እንዴት ፡ ተሰማህ - - ? » ትለዋለች ፡ ጺወኔ ፡ ቀስ ፡ ብላ— ዓይኖቿ ፡ እንደ ፡ ማጉረጥ ፡ ይሉና

« አ . . አ ! እንዴት ፡ ተሰማኝ - - ? » ይጀምራል ፡ አደፍርስ ፡ ሰብሰብ ፡ ብሎ « ምንም ፡ አልተሰማኝ ! ምን ፡ ተሰማኝ ? ይቅርታ ፡ እጅሽን ፡ ስለ ፡ ያዝኩሽ ፡ እንደሁ - - ይቅርታ - - ! አንዳንዴ ፡ እንዲሁ - - - እንዲህ ፡ ያረገኛል - - -

# ፴፪

# አደፍርስ

« እሺ ፣ የኔን ፡ ተረት ፡ ደግሞ ፡ ለመስማት ፡ ይፈልጋሉ ? » ይጠይቀዋል ፡ ጐርፉ ፣ በአደፍርስ ፡ ሁኔታ ፡ ይገፋፋና ።—

« ያስጠምድህ ፡ ባሥራስምንት ፣ አይደለም - - ? ያስጠምድህ ፡ ባሥራስምንት - - ! ሙሴው ፡ አይደለም ፡ እንዲህ ፣ የሚለው - - ? ሙሴ ፣ የማኅበሩ ፡ አላፊ - - » ያከታትላል ፡ አደፍርስ ፡ ያሳብ ፡ ድግግሙን - - -

« መቼስ ፡ ቅድም ፡ እርስዎም - - ቅድም ፡ ጠቅሰውታል - - ደጋግሞ ፡ ከተያዩ ፡ መለማመድ ፡ አይቀርም- - » ይጀምራል ፡ ጐርፉ « እና ፡ በጥንት ፡ ዘመን - - አንድ ፡ አንበሳና ፡ አሥራሦስት ፡ ናቸው ፡ አሥራራት ፡ ጅቦች ፡ ወደ ፡ አደን ፡ ሄዱ ፣ ይባላል - - እንግዲህ ፡ አብሮነታቸው ፡ ቅድም ፡ ስለ ፡ ድመትና ፡ ውሻ ፡ እንዳስረዱን ፡ ዓይነት ፡ ነው ፡ ማለት ፡ ነው - - እና ፡ ሲያድኑ ፡ ሲያድኑ ፡ ሲያድኑ ፡ ይውሉና ፡ አሥራራታቸውም ፣ አሥራራት ፡ ፍሪዳ ፡ አገኙ ፡ ይባላል - - ያጋጣሚ ፡ ነገር - - ካጋጠመ ፣ ብዙም ፡ ይገኛል ፡ መቼም ፤ ከዚህ ፡ የበለጠ ፡ ማለቴ ፡ ነው - - እኔ ፡ እንኳን ፡ ወደ ፡ አዳሉ ፡ አገር ፡ ወርጄ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ብዙ ፡ ብዙ ፡ ከብቶች - - ምን ፡ ያረጋል ፡ ብቻ ፣ ለነገሩ ፡ ያህል ፡ ማለቴ ፡ ነው - - አሥራራቱም ፡ አሥራራት ፡ ፍሪዳ ፡ አገኙ ።—ጓደኝነት ፡ አብሮ ፡ የለፉበትን ፡ አብሮ ፡ ለመብላት ፡ ነውና ፡ በስምምነት ፡ አድርገው ፣ ያችኑ ፡ አንዳንዳቸውን ፡ ተካፈሉ ።—በዚህን ፡ መካከል - - መቼም ፡ ፈሪ ፡ አይጸድቅምና - -ከነዚያ ፡ ሁሉ ፡ ጅቦች ፡ አንደኛው ፡ ብድግ ፡ ብሎ—እንዴት ፡ እንዲህ ፡ ይሆናል ! አቶ ፡ አንበሳ ፡ እንዴት ፡ አንድ ፡ ፍሪዳ ፡ ይበቃቸዋል ? አይበቃቸውም ፡ ብሎ ፡ ለፈፈ - - ! ማነው ፡ ይበቃቸዋል ፡ ባዩ ፣ ያኔ ? ! ያን ፡ ያቶ ፡ አንበሳን ፡ እንደ ፡ እሳት ፡ የሚንተገተግ ፡ ዓይን - - ያን ፡ ስንቱን ፡ ስንቱን ፡ ሊያደባይ ፡ የሚችል ፡ ያንበሳን ፡ ክርን ፡ እየተመለከተ ።— አሥራሦስቱን ፡ ፍሪዳዎች ፡ ላቶ ፡ አንበሳ ፣ አንዲቱን ፡ ለአሥራሦስታቸው ፣ ተካፈሉና ፡ እየምላዳቸው ፡ ተመለሷ ።—ግን ፡ የወሬን ፡ ነገር ፡ ምን ፡ አለ ፡ አሉት - - የእንጀራ ፡ አባታቸው ፡ የሆነ ፣ ሌላ ፡ ጅብ ፣ ሌላ ፡ ቦታ ፡ ውሎ ፡ ኖሮ ፡ ሲመለስ ፡ ያገኛቸዋል ።— የዋሉበትንም ፡ ይጠይቃቸዋል ።— አሥራሦ

ስታችንና ፡ አንድ ፡ አንበሳ ፡ ሆነን ፡ አደን ፡ ሄደን ፡ ዋልን - - ላሥራራ
ታችን ፡ አሥራራት ፡ ፍሪዳ ፡ አገኘን - - ይኸው ፡ ግን ፡ እንደምታ
የው ፡ አሥራሣስቱን ፡ ላቶ ፡ አንበሳ ፡ ለቀን ፡ አንዷን ፡ ብቻ ፡ ነድተን ፡
መምጣታችን ፡ ነው ፡ ይሉታል - - - አቶ ፡ የእንጀራ ፡ አባት ፡ ይናደ
ዳል - - ይጨሳል - - እንዴት ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ ለጆሮ ፡ የሚቀፍ ፡
ነገር ፡ ብሎ ፡ ይንጐራደዳል - - ላንድ ፡ አሥራሦስት ፡ ላሥራሦስት ፡ አንድ ፡
እንዴት ፡ ያለ ፡ መካፈል ፡ ነው ፡ በማለት ፡ ይጦፋል - - ምኑ ፡ ቅጡ ! !
ደፋርና ፡ ጭስ ፡ መውጫ ፡ አያጣም ፡ አይደለም ፡ የሚባለው - - አን
ዷን ፡ መልሰን ፡ አሥራሦስቱን ፡ እናመጣለን ፡ አላቸው ! አሥራሦስቱ ፡
ጅቦች ፡ የሰጡትን ፡ እሱ ፡ አንዱ ፡ ጅብ ፡ ሊያስመልስ - - ! ልብ ፡ ካለ ፡
ምናለ ፡ መቼም - - ! ወደ ፡ አቶ ፡ አንበሳ ፡ ቤት ፡ እየፎከረ ፡ ሄዳ ! እየፎከረ !
እየተድረቀረቀ - - ! መድረስ ፡ አይቀርም ፡ መቼም ፡ ደረሰ ! አቶ ፡ አንበሳም ፡
ቤት - - እውነትም ፡ ታዲያ ፡ እጅ ፡ ነሥቶ ፡ እንደቀረበ ፡ ያቶ ፡ አንበ
ሳን ፡ ፊት ፡ ቢመለከተው - - እንኳንስ ፡ አንዲቱን ፡ ተቀብሎ ፡ አሥራሦስ
ቱን ፡ ሊመልስ ፡ አንዷም ፡ ስለጐደለችበት ፡ ለካስ ፡ በሆዱ ፡ ተጠጥቶ ፡
ኖሮ - - እሳት ፡ ለብሶ ፡ እሳት ፡ ጐርሶ - - ጉምለል ፡ ጉምለል ፡ እያለ - -
ከወዲያ ፡ ወዲህ ፡ ሲጐደራ ፡ ጠበቀዋ - - ! ጠበቀው ። እህ ! የመጣንበ
ትን ፡ ጉዳይ ፡ ንገረና ! አይለውም — ባሽሙር ፡ ዓይነት ፡ አነጋገር . . .
አቶ ፡ ወንድ ፡ ታዲያ ፡ ምን ፡ አለ ፡ ይመስልሻል - - ? » ወደ ፡ ጂወኔ ፡
ዘወር ፡ ብሎ « - - ዋ ፡ ጌታዬ ፡ ያችን ፡ ያሥራሦስት ፡ ድርሻ ፡ ትሁን ፡
ብለው ፡ የመረቁልንን ፡ ፍሪዳ — አሥራራተኛ ፡ አድርገው ፡ እንዲቀበ
ሉኝ ፡ ነው ፡ በልጆቼ ፡ ስም ፡ ሆኜ ፡ የምማጠንዎት ፡ ሆና - - ! ምን ፡
ከዚያማ ፡ ጉምላላው ፡ አንበሳ ! ከብልህ ፡ ቀንሶ ፡ ከሞኝ ፡ ጨርሶ ፡ የሚኖር ፡
ብልጥ - - እግዚአብሔር ፡ ይስጥልኝ ፡ ብሎ ፡ መቀበል ፡ ነዋ ! ተቀበለው ፡
ሳቅ ፡ ሳቅ ፡ እያለ - - ተቀበለው - - ! ተቀበለው - - -

« - - እኔ ፡ እምልህ ፡ እንዲህ ፡ ጨዋታ ፡ ስታውቅ - - ህእ ! ህእ !
እያልህ ፡ አጉል ፡ አጉል ፡ አስተያየት ፡ ነበር ፡ ያደረብኝ - - » ይለዋል ፡ አደ
ፍርስ ፡ ጐርፉን ፡ በርግጥ ፡ በደስታና ፡ ባድናቆት ፡ በሚያበሩ ፡ ዓይኖቹ ፡
እየተመለከተው « - - እምልህ ፡ እስኪ ፡ ደግሞ - - ስለሌላ ፡ ነገር - -
ባገር ፡ ቤት ፡ ስለሚገኙት ፡ አዝርእት - - እንስሳት - - እምልህ - - የም
ታውቀውን ፡ ያህል - -

« አይ - - ምን ፡ ያህል ፡ ብለው - - ስለ ፡ እንስሳት ፡ ብዙ ፡ አላው
ቅም - - አዎ ፡ አሉ ፡ የማውቃቸው - - እምልዎ - - እየርሻው - -

እየጠረጋው - - እየደኑ ፡ ያጋጠሙኝ - - - ለምሳሌ ፡ ጠቃሚ ፡ የምንላቸው ፡ እንስሳት ፡ አሉ ፤ አጥፊ ፡ የምንላቸው ፡ እንስሳት ፡ አሉ ፤ መርዘኛ ፡ የምንላቸው ፡ እንስሳት ፡ አሉ ፤ ዋጋ ፡ የለሾች ፡ የምንላቸው ፡ እንስሳት አሉ ፤ በጣም ፡ በጣም ፡ አስልችዎች ፡ የምንላቸውም ፡ እንስሳት ፡ አሉ ።— ዶሮ ፡ ቆቅ ፡ ጅግራ ፡ ሶረኔ ፡ በግ ፡ ዓይነቶቹ ፡ ጠቃሚዎች ፡ ናቸው ። ቀበሮ ፡ ተኩላ ፡ ወማይ ፡ ነጐዴ ፡ ጐሴ ፡ ግልገል ፡ አንሣ ፡ አጥፊ ፡ የምንላቸው ፡ ናቸው ።— እባብ ፡ ዘንዶ ፡ ጊንጥ ፡ መርዘኛ ፡ ከምንላቸው ፡ ውስጥ ፡ ናቸው ።—እንደ ፡ እንቁራሪት ፡ ገበሎ ፡ ቢራቢሮ ፡ እንሽላሊት ፡ ዋጋ ፡ የለሾች ፡ ናቸው ።— ቅማል ፡ ቁንጫ ፡ ትኋን ፡ በረሮ ፡ አይጥ ፡ ዝምብ ፡ አይጠ - መጐጥ ፡ የመሳሰሉት ፡ ደሞ ፡ አስልችዎች ፡ ከምንላቸው ፡ ውስጥ ፡ ናቸው ።— ብቻ ፡ ምን ፡ አለፋዎ ፡ ዱሮ ፡ ተማሪ ፡ ቤት ፡ አሉ ፡ የሚሉንና ፡ እኔ ፡ ያገኘኋቸው ፡ የተለያዩ ፡ ናቸው - - -

« አ ! ተማሪ ፡ ቤት ፡ ገብተህ ፡ ኖሯል - - - ?

« አዎ ፡ ገብቼ ፡ ነበር - - ከጺወኔ ፡ ጋር ፡ ነበር ፡ አብረን ፡ የገባ ነው - - -

« እንዴት ፡ ዓይነቶች ፡ ነበሩ ፡ ተማሪ ፡ ቤት ፡ ሆናችሁ ፡ አሉ ፡ የሚሏችሁ - - ?

« ምኑ ፡ ቅጡ ፡ ብዙ ፡ ነበሩ - - መጀመሪያ ፡ በመሬት ፡ ላይ ፡ ያሉትን ፡ ፍጥረቶች ፡ በሦስት ፡ ይከፍሏቸዋል — ሰው ፡ እንስሳት ፡ አዝርእት ፡ ብለው - - ምኑ ፡ ቅጡ ፡ ብቻ - - ባንድ ፡ አፋቸው ፡ ሰውን ፡ አንዴ ፡ እንስሳ ፡ ነው ፡ አንዴ ፡ ነፍስ ፡ ያለው ፡ ፍጡር ፡ ነው ፡ ይሉናል - - እንስሳቱን ፡ ደሞ ፡ አከርካሬ ፡ ያላቸውንና ፡ አከርካሬ ፡ የሌላቸውን ፡ ይለያሉ - - -

« ታዲያ ፡ የተማሪ ፡ ቤቱ ፡ አከፋፈል ፡ የሚሻል ፡ አይመስልህም - - ?

« የሚሻል ? ለምኑ ፡ ነው ፡ የሚሻለው ፡ ጌታዬ ? አንዱ ፡ እንስሳ ፡ አከርካሬ ፡ ያለው ፡ ሌላው ፡ አከርካሬ ፡ የሌለው ፡ መሆኑን ፡ ዐወቅሁትና ፡ የት ፡ ላይ ፡ ነው ፡ ጥቅሙ - - ብዙ ፡ ለማምረት ፡ ነው ፡ የሚጠቅመኝ ? ወይስ ፡ ደግሞ ፡ እስተካክዬ ፡ ለመተኮስ - - - ?

« ለመሆኑ ፡ አሁን ፡ የተማረ ፡ ሰው ፡ ስታይ - - ምነው ፡ ተምሬ ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ ፡ አትልም ፡ ማለት ፡ ነው ? ለምሳሌ ፡ እኔን ፡ ስታይ - - - ?

« መቼም ፡ ያንጀት ፡ አይደለም ፡ ጨዋታ - - - ? አልልም ! ም ነው ፡ ተምሬ ፡ ቢሆን ፡ አልልም - - - ! እኔ ፡ የተማረ ፡ ሰው ፡ አያስቀ ናኝም - - ያሳዝነኛል ፡ እንዲያውም - - -

« ድንቁርናና ፡ ዕውቀት ! ያሳዝነኛል - - ያሳዝነኛል ? ! የሚታዘን ለት ፡ የትኛው ፡ ሆነና - - ?

« አልያዙልኝም ፡ መሰለኝ ፡ አማርኛዬን - - እንዴት ፡ ማለት ፡ መቼም ፡ ደግ ፡ ነው ፡ ለጨዋታ - - -

« እሺ ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ የማሳዝንህ - - ?

« እርስዎን ፡ አላልኩም ፡ ጌታዬ ! የተማረ ፡ ሰው ፡ ቢሉኝ ፡ ነው - - » ይልና ፡ ሊናገር ፡ የጀመረውን ፡ ቁርጥ ፡ አድርጐ ፡ ይቆማል ።—

« እኮ ፡ ታዲያ ፡ የተማረ ፡ ሰው ፡ የሚያሳዝነው ፡ እንዴት ፡ ነው - - ?

« እይ ፡ ምን ፡ ያረጋል - - የባላገር ፡ ነገር - - ወይ ፡ ሳላውቅ ፡ አስቀይ ምዎት ፡ ይሆናል - - የከተማ ፡ ሰውና ፡ የኛ ፡ የነገር ፡ አካሄድ ፡ አይገናኝ - -

«ግዴለም - - ግዴለም - - ምንም ፡ የሚያቀያይም ፡ ነገር ፡ የለ ፡ እዚህ - - -

«እና ፡ ታዲያ ፡ ለምን ፡ እንደሚያሳዝኑኝ ፡ ሊያውቁ ፡ ነው ፡ የሚ ፈልጉት - - - ?

«አዎ ፡ ለምን ፡ ያሳዝኑሃል - - - ?

«አሁን ፡ እርስዎ ፡ ከዚህ ፡ እራሳ ፡ በባዶ ፡ እግርዎ ፡ ይወርዳሉ - - - ? መቼም ፡ አያድርስብዎትና ፡ በዚህ ፡ በልስልስ ፡ እጅዎ ፡ ዶማ ፡ ጨብ ጠው ፡ ሞፈር ፡ ቀንበር ፡ አቀናጅተው ፡ አርሰው ፡ ሊኖሩ ፡ ይችላሉ ? እምልዎ ፡ ንጉሡ ፡ የእናንተ ፡ ሥራ ፡ በቃኝ ፤ አያስፈልገኝም - - እንደገ በሬው ፡ እንደ ፡ ነጋዴው ፡ እንደ ፡ ወታደሩ ፡ እየሠራችሁ ፡ ኑሮ— የቢሮ ፡ ሥራ ፡ አልጠቀመኝም - - ሂዱ ፡ ውጡ ፡ ከተራው ፡ ሰው ፡ ተደባለቁ ፡ ቢሉዎ ፡ ምን ፡ ይውጥዎታል ? ሌላው ፡ ቀርቶ ፡ በረሮውንና ፡ ትኋኑን ፡ ብቻ ፡ የትኛው ፡ ሰውነትዎ ፡ ነው ፡ የሚችለው ? እሾሁን ፡ እንቅፋቱን ፡ ሙያሌውን ፡ የትኛው ፡ እግርዎ ፡ ነው ፡ የሚቋቋመው - - - ? እንዴ - - - ! እኔስ ፡ ካንጀቴ ፡ ነው ፡ ያሳዝኑኛል ፡ ያልኩት - - -

«እይ ፡ እንዲያ ፡ ከሆን ፡ ቀላል ፡ ነው ፤ ለጉዞም ፡ በቅሎ - - መንገድ ፡ ካለም ፡ መኪና - - ካስፈለገም ፡ አይሮፕላን ፡ አለ።—ለእርሻውም፡ የእርሻ ፡

መኪና ፡ እናመጣበታለን - - ተውሳኮቹንም ፡ በ'ዲዲቲ' ድራሻቸውን ፡ እናጠፋዋለን ።— ለሙያሌውና ፡ ለምናምኑም ፡ መጫሚያ ፡ እናደር ጋለን - - ይኸን ፡ ይኸን ፡ ቀላሉን ፡ ነገር - - - ?

«ጌታዬ ፡ መቼም ፡ ይኸ ፡ ይኸ - - ለኛ ፡ የዳመና ፡ ሕልም ፡ ነው ፤ እኛ ፡ አገር ፡ ሌላው ፡ ቀርቶ ፡ በቅሎም ፡ የሚኖረው ፡ የደላው ፡ ነው - - የርሻ ፡ መኪና - - የርሻ ፡ መኪና ፡ ላሉት ፡ በውነቱ ፡ ይኸን ፡ ሜዳ ፡ የማይታይበት ፡ አባጣ ፡ ጐርባጣ ፡ የኛን ፡ አገር ፡ መሬት ፡ የሚያርስ ፡ መኪና ፡ ካለ ፡ ጥሩ ፡ ነው ፤ ግን ፡ ሳስበው ፡ በድንቁርና ፡ ልቦናዬም ፡ ቢሆን ፡ የሚኖር ፡ አይመስለኝም - - ስለ'ዲዲቲ'ው ፡ እኛም ፡ ባቅማችን ፡ እየገዛን ፡ መሞከራችን ፡ አልቀረም ፤ እየጠጡ ፡ ቁጭ ፡ ሆነዪ - - -

«ምን ? ምን ፡ እየጠጡ ፡ ነው ፡ ቁጩ - - - ?

«አዬ ፡ ጌታዬ - - የኛን ፡ አገር ፡ ተውሳኮች ፡ የፈረንጅ ፡ መዳኒት ፡ አይደፍራቸውም - - 'ዲዲቲ'ውን ፡ ይለምዱትና ፡ ውጠው ፡ ውጠው ፡ ሲፈረከሱ ፡ ጠንቃቸው ፡ ለኛው ፡ ነው ፡ የተረፈው ።— ክርፋታቸው ! ከጉድጓድ ፡ አይጥ ፡ የሚያስወጣ ፡ እየሆነ ፤ አይስማማቸውም ።— እኛም ፡ ታዲያ ፡ ምን ፡ እናርግ ፡ መቼስ ፡ አልወደድነውም ።—ከሁል ፡ አሁን ፡ የኛ ፡ የቆላ ፡ አይጦች - - እንዲህ ፡ መርዝ ፡ የሆነ ፡ ነገር ፡ በምግብ ፡ ስናቀርብ ላቸው ፡ ግፋ ፡ ቢል ፡ አንዷ ፡ ቀምሳ ፡ ብትሞት ፡ ነው - - ሌሎቹ ፡ ንክች— ሲያልፍም ፡ አይነካቸው ።— ገና ፡ በሽታው ፡ ነው - - ከሩቁ ፡ የሚሸ ሹት ።— ምን ፡ አለፋዎ ፡ ብቻ ፡ እንኳን ፡ ተውሳኮቹን ፡ እኛንም ፡ አይ ደፍረን ፡ የፈረንጅ ፡ መዳኒት - - -

«አይመስለኝም ! አሰጣጡን ፡ ሳታውቁበት ፡ እየቀራችሁ ፡ ይሆ ናል - - -

«ምነው ፡ የሚያውቁበትስ ፡ መቼ ፡ ሆነላቸው ? በቀደም ፡ አንድ ፡ የኛ ፡ መንደር ፡ ልጅ ፡ ታመመችና ፡ ሮቢ ፡ ወሰድናት ! ላኪሙ ፡ ሦስት ፡ ቀኗ ፡ ነው ፡ እንቅልፍ ፡ ባይኗ ፡ ሳይዞር ፡ አልነው - - የእንቅልፍ ፡ ኪኒን ፡ ብሎ ፡ ሁለትም ፡ እንደሁ ፡ አዘዘላት — ዋጠችና ፡ ዓይኖቿን ፡ ቁልጭ ፡ ቁልጭ ፡ ሆነ - - ! በጣም ፡ ገረመውና ፡ እንደገና ፡ አንድ ፡ እንዲጨ መርላት ፡ አዘዘ - - በጣም ፡ ኃይለኛ ፡ ኪኒን ፡ ነው ፡ እያለ ! ዋጠችና ፡ ምንም - - ! እንደገና ፡ ጨመረላት - - ንክች - - ! አይ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ አደ ገኛ ፡ ነው ፡ አለና ፡ ተዋታ ፡ እንደብጤቷ - - - !

«እርግጥ ፡ ነው ፡ የምትለው ፡ መቼም ፡ እውነት ፡ እያጣም - - - እና ንተ ፡ የባላገር ፡ ሰዎች ፡ ብዙ ፡ የሰውነት ፡ ጥንካሬ ፡ አላችሁ - - - መድ ኅኒት ፡ በቀላሉ ፡ አይደፍራችሁም - - -

«ለራስ ፡ ምታቱ ፡ ኪኒን ፡ ለጭረቱ ፡ ፋሻ ፡ ለሆድ ፡ እመሙ ፡ ስንት ፡ ዓይነት ፡ ቅርንጥ - - መጥኔውን ፡ መጥኔውን ፡ ይስጣችሁ ፡ ብቻ ፡ እና ንተ ፡ የተማራችሁ ፡ ሰዎች - - - እናንተ ፡ ያላሳዘናችሁ ፡ ማን ፡ ያሳዝን ? ተምሬ ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ ፡ አትልሞይ ፡ የተማረ ፡ ስቃይ ፡ አሉኝ ? ይገርማል ! ሌላው ፡ ቀርቶ ፡ በተኩስ ፡ እንኳ ፡ ቢሆን ፡ የተማሩትን ፡ አይተናቸዋል - - ተ ኳሽ ፡ ቆለኛ ! አንድ ፡ ጥይት ፡ በከንቱ ፡ ጠብ ፡ የማትልበት - - የምን ፡ ትምርት ፡ ደሞ - - - አሁን ፡ ሰሞኑን ፡ እዚህ ፡ መንደር ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ መጥቶ ፡ ዝም ፡ ብሎ ፡ ጥይቱን ፡ ያዘራል ፡ ሲሉ ፡ ሰማሁ ፡ በቀደም ፡ ሚካኤል ፡ ወጥቼ ! እስቲ ፡ እግዜር ፡ ያሳይዎ ፡ እንግዲህ - - ቆቅ ፡ ለመ ግደል ፡ ነው ፡ አሉ ፡ ያ ፡ ሁሉ ፡ ጥይት ፡ ማባከን - - -

አደፍርስ ፡ ሰውነቱ ፡ ቅጭም ፡ ይላል ።—ጺወኔ ፡ እነሱን ፡ እያየች ፡ ታዳምጥ ፡ ነበርና ፡ ስለተኩሱ ፡ ማውራት ፡ ሲጀምሩ ፡ ቀስ ፡ ብላ ፡ ብድግ ፡ ትልና ፡ ወደ ፡ ውጪ ፡ ትወጣለች ።

«ታዲያ ፡ አንተና ፡ እኔ ፡ እንተኩስ ፡ እንዴ - - ? ! » ይጠይቀዋል ፡ አደፍርስ ፡ ጐርፉን— የጺወኔን ፡ ሹልክ ፡ ብሎ ፡ መውጣት ፡ ያጤንና —

«ምን ፡ ከፋኝ ፡ ጥይት ፡ ካለዎት - - እኛ ፡ አገር ፡ ጥይት ፡ ውድ ፡ ነው - - -

«ጥሩ ፡ ነው ፡ እንግዲያው ፤ ጠመንጃም ፡ ጥይትም ፡ አለኝ - - - ! ፍሎቤሩን ፡ ከተሰቀለበት ፡ ከወደ ፡ ጓዳ ፡ ያመጣና ፡ ከግቢው ፡ ውጪ ፡ ይወጣሉ ።— አንድ ፡ የቅል ፡ ዒላማ ፡ ባሻገራቸው ፡ ይተክሉና ፡ ሁለት ፡ ሁለት ፡ ጥይት ፡ ይዘው ፡ ይተኩባሉ— መጀመሪያ ፡ የተኮሰው ፡ ጐርፉ ፡ ነበርና ፡ በሁለቱም ፡ ጥይት ፡ ይስታል - - አደፍርስ ፡ ለጥቆ ፡ ሲተኩስ ፡ በሁለተኛዋ ፡ ጥይት ፡ ትንሽ ፡ ጨረፍ ፡ ያደርጋታል— ቅሏን - - -

«ታዲያ ፡ ተኩስ ፡ አንችልም ፡ እንዴ - - - ? !

«ይቺ ፡ የርስዎ ፡ ብረት ፡ ለትክሻ ፡ ትቀላለች - - አሻንጉሊት ፡ ዓይነት ፡ ነገር - - » ግምባሩን ፡ አንገቱን ፡ ያልበዋል « - - እኔ ፡ መቼም ፡ ስለተኩሱ ፡ ጉዳይ - - - አይ ፡ ምን ፡ ዋጋ ፡ አለው ፡ ብቻ - - አገር ፡ ይበል - - -

«ባንተ ፡ ብረት ፡ እንወዳደራ ! በዚህኛው ፡ ካላመንህ - - ? እኔ ፡ ግድ ፡ የለኝም - - -

«በኔ ፡ ብረት ፡ እንወዳደር - - ? ጥሩ ፡ ነው ፡ እስማማለሁ - - አንድ ፡ ጥይት ፡ ለርስዎ ፡ እሰጥዎታለሁ ፤ አንድ ፡ ጥይት ፡ ራሴ ፡ እተኩሳለሁ - - -» ብረትና ፡ ዝናሩን ፡ ያስመጣና ፡ ዝናሩን ፡ ጠጋ ፡ አድርጐ «በሉ ፡ ያውልዎ ፡ አንድ ፡ ጥይት ፡ ይምዘዙ » ይለዋል ።— አደፍርስ ፡ ሲመዝ ፡ ቀለህ ፡ ብቻ ፡ ይሆናል - - ጐርፉ ፡ እፍር ፡ ይላል ፤ ባዶ ፡ ቀለህ ፡ ለዝናር ፡ መሙሊያ ፡ ማስገባቱን ፡ በመርሳቱ « - - - ለዝናር ፡ መሙሊያ ፡ የተደረገ ፡ ነው - - ግዴለም - - ይምዘዙ ፡ ሌላ ፡ ያገኛሉ ! » ይለዋል ።— አደፍርስ ፡ ይመዛል ።—አሁንም ፡ ግን ፡ የመዘዘው ፡ ባዶ ፡ ቀለህ ፡ ይሆናል «—ወየ ጉድ ! የሱ ፡ መገኘት ! የርስዎ ፡ ደግሞ ፡ እየደጋገሙ ፡ እሱኑ ፡ መምዘዝ - - !» ሦስተኛ ፡ ጊዜ ፡ ሲመዝ ፡ ደንበኛ ፡ ጥይት ፡ ያወጣል—ይተኩሳል ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ይስታል ።— ጐርፉ ፡ በተራው ፡ መዞ ፡ ሲተኩስ ፡ ይመታል ።—

«እኩል ፡ በኩል ፡ ሆንን ፡ ማለት ፡ ነው ! » ይለዋል ፡ አደፍርስ ፡ «እንደገና ፡ ለመተኮስ ፡ ትፈልጋለህ - - - ?

«የለም ፡ ጌታዬ ፡ በዚህ ፡ ባጉል ፡ ነገር ፡ ጥይት ፡ አላባክንም - - -

«በኔ ፡ ጥይት ፡ እንወዳደር ፡ እንግዲያው - - -

«የርስዎ ፡ ብረትኮ ፡ እሺ ፡ ብላ ፡ አትገባም ፡ አልኩዎ - - እንጃ ፡ ብቻ ፡ ከወደ ፡ አናቷ ፡ ገደማ ፡ ጠመም ፡ ያለች ፡ መሰለኝ - - ተሳስቼ ፡ ሊሆን ፡ ይችላል - - -

«ደግ ፡ እንግዲያው ፡ ካልመሰለህ ፡ ይቅር - - ብቻ ፡ ቢሆንም ፡ የተማረ ፡ ሰው ፡ እስከዚህ ፡ እጅ ፡ እግሩ ፡ የታሠረ ፡ አይምሰልህ - - -

ይመለሳሉ ፡ ወደ ፡ እልፍኙ ።—

# ፴፫

# አደፍርስ

እልፍኙ ፡ ገብተው ፡ አረፍ ፡ አረፍ ፡ እንዳሉ « እኔኮ ፡ እምልዎ - - በኮፍ ፡ ጫማም ፡ ተሄደ ፡ በግምብ ፡ ቤትም ፡ በሮቅም ፡ ተኖረ - - ጸዳ ፡ ጸዳ ፡ ልብስም ፡ ተለበሰ - - የተማረ ፡ ሰው ፡ ምን ፡ የፈጠረው ፡ ነገር ፡ አለ ፡ እስከዚህ - - ? » ይጀምራል ፡ ጕርፉ ፡ ቀስ ፡ ይልና « - - እኛም ፡ መቼም ፡ ያዳል ፡ ጫማም ፡ ቢሆን ፡ እናደርጋለን - - ልብስም ፡ እንለብሳለን - - እንዳገራችን ፡ አንገታችንንም ፡ የምናስገባበት ፡ እንደ ፡ ነገሩም ፡ የተውተፈተፈ ፡ ጐጆ ፡ ቢሆን ፡ አለን ።— ጤንነት ፡ ኖሮን ፡ ሠርተን ፡ ከገባን ፡ ልጆች ፡ ወልደን ፡ አድገውልን ፡ በእርሻውም ፡ በእረኝነቱም ፡ ሲያግዙን ፡ ካየን - - ከዚህ ፡ የበለጠ ፡ ዓለም ፡ ከዚህ ፡ የበለጠ ፡ ምኞት ፡ ከዚህ ፡ የበለጠ ፡ ደስታ ፡ ምን ፡ ይኑረን - - - ?

«ያላዩት ፡ አገር ፡ አይናፍቅም ፡ ሆኖ ፡ ነው ፡ ነገሩ - - -

«እንዴ ! ያላዩት ፡ አገር ፡ ለምን ፡ ይናፍቅ - - - ?

«ስማ ፡ አጭር ፡ ምሳሌ - - አሁን ፡ አንተ ፡ የኔን ፡ ልብስ ፡ ለመልበስ ፡ አትፈልግም - - ?

«ውይ ፡ በስማብ ፡ ወልዴ ! እርስዎም ፡ ስለለበሱት ፡ ገርሞኛል ፤ ሙቀቱን ፡ መቻልዎ ! እውነቱን ፡ ልንገርዎ ፡ እኔ ፡ ከሆነልኝ ፡ ከቁምጣዬ በቀር ፡ ራቁቴን ፡ መሆን ፡ ነው ፡ የምፈልገው - - -

«ለምን ፡ ከቁምጣህ ፡ በቀር - - - ?

«አይ ፡ እሱማ ፡ መቼም ፡ አፍረቴን ፡ መከለል ፡ አለብኝ - - - !

«ለመሆኑ ፡ ልብስ ፡ ለጌጥ ፡ ይሆናል ፡ ሲሉ ፡ ሰምተህም ፡ አታውቅ ?

«እሰማለሁ ፤ ግን ፡ አይታየኝም ! ሴት ፡ ልጅ ፡ ይሁን ፡ ታጊጥ ፡ መቼስ ፡ ምን ፡ ይደረጋል - - የወንድን ፡ ጌጠኛ ፡ መሆን ፡ ግን ፡ አላውቅም ።— የወንድ ፡ ጌጡ ፡ ሠርቶ ፡ ማብላቱ ፡ ብቻ ፡ ነው - - -

«አሳረፍከኝ ፡ አሳረፍከኝ ! እንግዲህ ፡ እትራሴ ፡ እሰቅልና ፡ ቀና ፡ ባልኩ ፡ ቁጥር ፡ እሳለመዋለሁ - -» እያሉ ፡ ይገባሉ ፡ ወይዘሮ ፡ አሰጋሽ ።—

ከአቶ ፡ ወልዱና ፡ ከአቶ ፡ ክብረት ፡ ጋር ፡ ሆነው ፡ መመለሳቸው ፡ ነው ፤ የጉርጓዱን ፡ ማሽላ ፡ ደኅናውን ፡ ከደምበሾው ፡ ካስለዩ ፡ በኋላ ።—ክብረት ፡ ከሁኔታው ፡ አንድ ፡ ንጥረ ፡ ሐሳብ ፡ ስላገኘ 'ደንበሾው' በሚል ፡ ርእስ ፡ ሥዕል ፡ ለመሣል ፡ አንዳንድ ፡ ንድፍ ፡ አውጥቷል ።— እዚያው ፡ ሆኖ ፡ ግን ፡ ስለዚሁ ፡ ሐሳብ ፡ ሲያሰላስል ፡ የሚካኤልን ፡ ቤተ ፡ ክርስ ቲያን ፡ ወለል ፡ ብሎ ፡ ከሚታይበት ፡ አቅጣጫው ፡ ስላገኘው ፡ በእ ርሳስ ፡ ብቻ ፡ ጥሩ ፡ አድርጎ ፡ ነድፎ ፡ ለወይዘሮ ፡ አሰጋሽ ፡ ይሰጣቸ ዋል ።— ይኸን ፡ ስጦታ ፡ እየተመለካከቱ ፡ ነው ፡ እንግዲህ ፡ የገቡት — ልባቸውም ፡ ቢጠራጠር ፡ አንተ ፡ የሣልከውን ፡ ሥዕል ፡ አልሻም ፡ ሊሉት ፡ አልፈለጉም ።— ሲገቡ ፡ ጐርፉና ፡ አደፍርስ ፡ ብድግ ፡ ብድግ ፡ ይላሉ ፡ « - - መቼ ፡ መጣህ ፡ ጐርፉ » ይሉና « ና ፡ ሳመኝ ፡ እንጂ ፡ ታዲያ - - ! » እጃቸውን ፡ ዘርጋ ፡ ያደርጋሉ - - ጐርፉ ፡ ለጥ ፡ ብሎ ፡ መጫሚያቸውን ፡ ይስማል « - - ምነው ፡ ወደኛጋ ፡ ብትመጣ ፡ ኖሮ ! እኔ ፡ ደሞኮ ፡ እንዲ ያው ፡ ከልቤ ፡ አልለየሁህም - - ያቺ ፡ ደሞ ፡ የኔ ፡ ጺወኔ ፡ የት ፡ ሄዳለች - - መጣ ፡ እንኳን ፡ ብላ ፡ እስኪ ፡ ብትነግረኝ - - ለሌላ ፡ ነገር ፡ ቢሆን ፡ መቼም ፡ ይሄኔ ፡ ትሮጥ ፡ ነበር - - -

«ከሳቸው ፡ ካቶ ፡ አደፍርስ ፡ ጋር ፡ ጨዋታ ፡ ይዤ ፡ ነው - - - ከጀል ፡ አርጎኝ ፡ ነበር ፡ ለመምጣት ፡ እንኳን - - -

«ስለዚህ ፡ ስለ ፡ መሳም ፡ ነገር - - እንዴት ፡ አንድ ፡ ማሻሻያ ፡ ሳይገኝለት ፡ ቀረ - - ? » ይላል ፡ አደፍርስ ፡ እንደቆመ ።—ወይዘሮ ፡ አሰጋሽ ፡ የተለመደውን 'በአበው ፡ በጻድቃን ፡ ተቀመጥ'ን ፡ እንኳን ፡ አላሉ ትም ፤ እሱም ፡ ያጤነው ፡ አይመስልም ።

«ስለ ፡ የቱ ፡ ወዳጄ - - ? »ይሉታል ፡ ወይዘሮ ፡ አሰጋሽ ፤ ምን ፡ ነገር ፡ ሊያመጣ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ በፈራ ፡ እንደበት ።

«ይኸ ፡ እግር ፡ መሳም ፡ ጉንጭ ፡ መሳም ፡ ድንጋይ ፡ መሳም ፡ መስ ቀል ፡ መሳም - - ወረቀት ፡ መሳም - - እጅ ፡ መሳም - - -

«ምን ፡ ወጣው ፡ ታዲያ - - ? ባህላችን ፡ ነው ፡ መቼም ። ልማድን ፡ ልተውህ ፡ ቢሉት ፡ ይትተዋል - - እኔ ፡ አሁን ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ ልንገ ርህ ፡ እቤቴ ፡ ውስጥ ፡ ስላለው ፡ ሥራት - - ይቺ ፡ የኔ ፡ አገልጋይ ፡ አለች ፡ እግሬን ፡ የምታጥበኝ - - - ታዲያ - - ማታ ፡ ማታ ፡ እግሬን ፡ አጥባ ፡ ስታበቃ ፡ እንደኛውን ፡ ካልሳመች ፡ ጭራሽ - - ጭራሽ ፡ ነው ፡ የምልህኮ - - ! ጭራሽ ፡ የታጠብኩ ፡ አይመስለኝም - - እሷስ ፡ የታባቷ ፡

ልትገባ - - ሌላ ፡ ደሞ ፡ ልንገርህ—አሁን ፡ ይኸ ፡ የኔ ፡ ልጅ ፡ ጐርፉ ፡ አለ - - ለሁለት ፡ ወይም ፡ ሦስት ፡ ቀን ፡ እንኳን ፡ ሳላየው ፡ ቀርቼ ፡ የመጣ ፡ እንደሆን ፡ ካልሳመኝ ፡ ትልቅ ፡ ትልቅ ፡ ነገር ፡ የቀረብኝ ፡ ነው ፡ የሚመስለኝ - - - ድንጋይ ፡ ስላልከው ፡ ግን - - ድንጋይ - - ድንጋይ ፡ አልስምም - - ሌላም ፡ ሰው ፡ ሲስም ፡ አላየሁም - - ይኸን ፡ መሳለሚያውን ፡ ማለትህ ፡ ይሆን - - - ? አድባሩን - - -

«ምነው ፡ የቤተክሲያኑን ፡ ደፍ — የቤተክሲያኑን ፡ ግድግዳ — የቤተክሲያኑን ፡ ደረጃ - - -

«ተውተውተውተውተው ! ጥሩ ፡ አይደለም ፡ ወዳጄ ! ጥሩ ፡ አይደለም - - ስለ ፡ ቤተስኪያን ፡ መሳም ፡ አጉል ፡ አትናገር - - ምን ፡ እናርግ ፡ ትላለህ - - ? እዝጌርን ፡ ራሱን ፡ አግኝተን ፡ አንስመው ? ምን ፡ እናርግ ፡ ትላለህ - - ? ግን ፡ ግን ፡ ድንጋይ ፡ አይደለም ፡ የምንስመው - - እኔ ፡ እንዲያውም ፡ አሁን ፡ እስክትናገረው ፡ ድረስ ፡ የምስመው ፡ ድንጋይ ፡ መስሎ ፡ ታይቶኝም ፡ አያውቅ - - በጭራሽ - - ! ምን ፡ አጉል ፡ ነገር ፡ አሰማኸኝ ፡ ወንድሜ ! አጉል ፡ ነገር - - -

«ምን ፡ መስሎ ፡ ኖሯል ፡ የሚታይዎት - - ?

«የሚታየኝ ! የሚታየኝ - - ! የዝጊያብሔር ፡ ቤት ፡ ምኑ ፡ ይመረመራል ? ምን ፡ ሊታየኝ ፡ ይችላል - - ?

«ኢምልዎት ፡ ያም ፡ ያም ፡ ያም ፡ ሲስመው ፡ በሽታ ፡ ሊይዝዎት ፡ ይችላል - - ስንት ፡ ዓይነት ፡ ነገር ፡ ይመስልዎታል ፡ በዚህ ፡ መንገድ ፡ ሊተላለፍ ፡ የሚችለው - - -

«ተላልፎም ፡ አያውቅ ! የዝጊያብሔርን ፡ ቤት ፡ በሽታ ፡ አይደፍረውም - - - አጉል ፡ ነገር ፡ አሰማኸኝ ፡ ግን - - - እሱው ፡ ይሁነኚ - - እንጃልኝ ፡ እንግዲህ ፡ እንደ ፡ በፊቴ ፡ መሆኔን - - አጉል ፡ ነገር ፡ ያንተ ፡ ንግግር - - ቤተስኪያን ፡ በሄድሁ ፡ ቁጥር ፡ ነው ፡ ትዝ ፡ የሚለኝ - - ማስረሻ ፡ ዘዬ ፡ ቢገኝለት ፡ ለነፍስ ፡ አባቴ ፡ አጫውታቸዋለሁ - - - ሆድ ፡ ግን ፡ መቼ ፡ በጄ ፡ ይላል - - አንዴ ፡ አጉል ፡ ነገር ፡ ከያዘ ፡ በኋላ - - ባይቀበለውም ፡ ማስታወሱ ፡ አይቀርም - - -

«የሰው ፡ እግርማ ፡ የስንት ፡ ዓይነት ‘ ሚክሮብ ’ መጠራቀሚያ ፡ ነው - - - በውነቱ ፡ ከሆነ ፡ ሌላው ፡ ቢቀር ፡ እርስዎ ፡ በሚያዘውቡት ፡ ቦታ ፡ ሁሉ ፡ እንዲህ ፡ ያለውን ፡ ነገር ፡ ማስቀረት ፡ አለብዎ - - - ቢያንስ ፡ ቢያንስ ፡ በቅርብ ፡ የሚያስተዳድሯቸው ፡ ሰዎች ፡ እንዳያደርጉት - - -

«መቼ ፡ በጂ ፡ ይላል ፡ ሰዉ ፡ እግሬን ፡ እንዳይስም ፡ ብከለክለው - - ምን ፡ አድርጊያት ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ነው ፡ ያማላጇን ፡ መዐት ፡ የሚያኘ ጉደጉደው - - - ደግሞም ፡ ማንንም ፡ እግሬን ፡ እንዲስም ፡ የምፈልግ ፡ አይምሰልህ - - አዎ - - እመርጥበታለሁ ! በጣም ፡ የቅርቤ ፡ የምለውን ፡ ነው ፡ የምፈቅድለት - -

«እኮ ፡ ቢያስቀሩት - - -

«ነገርኩህኮ ! ይቅር ፡ ብሎ ፡ በመናገር ፡ ብቻ ፡ የሚቀር ፡ አይ ደለም ፡ ነው ፡ የምልህ - - እንደ ፡ እህል ፡ እንደ ፡ ውሃ ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ።— ያለ ፡ እሱ ፡ ለመኖር ፡ አይችልም ፡ ሕዝቡ - - እውን ፡ ጐርፉ ፡ አሁን ፡ አንተ ፡ ጫማዬን ፡ አትሳም ፡ ብልህ - - -

«አይ ፡ እርስዎም ፡ አይሉኝ - - -

«ይኸውልህ ፡ እንግዲህ ፡ እስከዚህ ፡ ድረስ ፡ ነው - - -

«አሁን ፡ አንተ ፡ ጫማ ፡ መሳም ፡ እፈልጋለሁ ፡ ማለትህ ፡ ነው - - ?

«ለምን ፡ አልፈልግም ? ማን ፡ አስገደደኝ ፡ ታዲያ - - - ?

«አትስመኝሞይ ፡ አሉህ ! ከዚህ ፡ የበለጠ - - -

«አይዶለም ፡ አይዶለም - - - ከትናንት ፡ ወዲያ ፡ እዚሁ ፡ ስለነበ ርሁ - - -

«አዎ ፡ ከትናንት ፡ ወዲያ ፡ መጥቶ ፡ ነበር - - - ምናልባት ፡ እንደኔ ፡ ጊዜው ፡ አልረዘመበት ፡ ይሆናል - - -

«ይልቅ ፡ አሁን ፡ ስለ ፡ ነገው ፡ ጉዞሽ ፡ ብንነጋገር - - ይኸ ፡ አጉል ፡ ትርኪ ፡ ምርኪ ፡ ለማንኛችሁም ፡ አይበጅ - - - እኔ ፡ እምለው ፡ አንቺ ፡ ከሄድሽ ፡ እኛስ ፡ ባለቤት ፡ እሌለበት ፡ ቤት ፡ ምን ፡ እንሠራለን - - እኔም ፡ እሁድ ፡ ስብሰባ ፡ አለብኝ - - - ስለዚህ ፡ ስለ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ማሠሪያ ፡ መዋጮ - - እና ፡ ብዙ ፡ ጉዳይ ፡ ብተኩስም ፡ ያለወትሮዬ ፡ ስን በትሁ - - - » ጣልቃ ፡ ይገባሉ ፡ አቶ ፡ ወልዱ ።—

«አይ ፡ እኔማ ፡ ከነጺወኔ ፡ ጋር ፡ ለመሄድ ፡ ተስፋ ፡ ሰጥቻ ለሁ - - -» ይላል ፡ አደፍርስ ፡ ይለጥቅና

«ተስፋ ! ተስፋ ! ተስፋ ፡ ሰጥቻለሁ ? ከነጺወኔ - - ! » ይገረማሉ ፡ ወይዘሮ ፡ አሰጋሽ « - - እነ ፡ ጺወኔ ፡ ደሞ ፡ እነማናቸው ? የኔን ፡ ልጅ፡ ማለትህ ፡ እንዳይሆን - - -

«ኋላ ፡ ስንት ፡ ጂ.ወኔ ፡ አለና - - -

«ታዲያ ፡ እሷ ፡ ከኛ ፡ ጋር ፡ የምትሄድ ፡ መስሎኝ ፡ ነበር - - እየፈጩ ፡ ጥሬ ፡ የሚሉት ፡ ነገር ፡ ሆነ ፡ እንዴ - - ? የተስፋው ፡ ጋጋታ - - ?!

« ምናለ ፡ እኔስ ፡ አብሬ ፡ ብሄድ - - -

«አይደለም ፤ ነገሩን ፡ የደረስክበት ፡ አይመስለኝም - - - እኛ ፡ ለዓለም ለደስታ ፡ አይደለም ፡ የምንሄደው ፡ ጠበል ፡ ለመጠመቅ ፡ ነው - - ዘመድ ፡ አዝማድ ፡ የምንለው ፡ ባቅራቢያው ፡ አይኖርም - - - ለአንድ ፡ ሁለት ፡ ቀን ፡ ብንቸገርም ፡ በማለት - - -

«አይ ፡ መቼምኮ ፡ እሳቸው ፡ አብረዋችሁ ፡ ሊሄዱ ፡ ከፈለጉ ፡ በር ከት ፡ ብለን ፡ ማረፊያ ፡ እንዳናጣ ፡ እኔ ፡ ልቀር ፡ እችላለሁ - - - » ይላል ፡ ጐርፉ ።

«ዕውር ፡ ያለበትሩ ፡ የት ፡ መንገድ ፡ ይወጣል - - - ያንተ ፡ መቅረት ፡ ዘበት ፡ ነው - - ደግሞስ ፡ እስከዚህ ፡ መቼ ፡ አደክምህ ፡ ነበር - - እን ዲህ ፡ በቀላሉ ፡ የምትተካ ፡ መሆንህን ፡ ባውቅ - - -

«- - እና ፡ ታዲያ ፡ እኛም ፡ ዕቃችንን ፡ በቅጥ ፡ በቅጥ ፡ አድርገን ፡ በጧት ፡ ብንነሣ - - » ጣልቃ ፡ ይገባሉ ፡ አሁንም ፡ አቶ ፡ ወልዱ ።—

«ለመሆኑ ፡ የኛን ፡ መሄድ ፡ ወሬ ፡ ከእንዴት ፡ ያለች ፡ ወፍ ፡ ሰማ ሽው - - ? ባለተስፋዋ ፡ ማለቴ ፡ ማነች - - ?

«ከየት ፡ እሰማዋለሁ ፡ እናንተው ፡ ስትነጋገሩ - - -

«እኔ ፡ ነኝ ፡ የነገርሁት - - - ማረፊያ ፡ የማይኖር ፡ አልመሰለኝም ፡ ነበር - - - » ትመልሳለች ፡ ጂ.ወኔ ፡ ቶሎ ፡ ብላ ።—

«ዮኔው ፡ ነሽ ፡ ለካ ? እኔስ ፡ ምን ፡ መንገድ ፡ አገኘ ፡ ብዬ - - -

« - - እንግዲያው ፡ እኔም ፡ መሄድ ፡ እልፈልግም ፡ ማረፊያው ፡ ችግር ፡ የሚፈጥር ፡ ከሆነ - - ጤነኛ ፡ ነኝ ፡ ደግሞ ፡ በዚያ ፡ ላይ - - ፍል ፡ ውሃ ፡ ምን ፡ ይሠራልኛል ? » ትቀጥላለች ፡ ጂ.ወኔ ።—

« - - ነገ ፡ ጧት ፡ ወደ ፡ ደብረ ፡ ሲና ! ሌላ ፡ ጭቅጭቅ ፡ የለም ፡ እንግዲህ ! » በቆረጠ ፡ ቃል ፡ ይናገራል ፡ አደፍርስ ።—

«ልጅ ፡ ነሽ ፡ አንቺ ! ስለ ፡ ጤንነትሽ ፡ የምታውቂው ፡ ነገር ፡ የለም - - - » ይገሥጿታል ፡ አሰጋሽ ፡ ጂ.ወኔን ።—

«እዚህ ፡ አገር ፡ ፍልውሃ ፡ ኖሯል ፡ ለካ ? ከሆነ ፡ ከሆነ ፡ በውነቱ ፡ ማየቱ ፡ አይከፋም ፡ ነበር - - ብቻ ፡ ከሰው ፡ ጋር ፡ ሆነን ፡ ከደብረ ፡ ሲና ፡ መጥተን ፡ ልናየው ፡ እንችላለን - - ከመሄዳችን ፡ በፊት - - -» ይናገራል፡ ክብረት ።—

«ቀስ ፡ ብለን ፡ ልንመጣ ፡ እንችላለን - - ከኔ ፡ ጋር - - - » አቶ ፡ ወልዱ ፡ ቃል ፡ ይገባሉ ።

«ጥሩ ፡ ነው ፡ እንደ ፡ ብጤታችሁ - - አሁን ፡ ስለ ፡ ጉዟችን - - » ይሉና፡ ወደ ፡ ጐርፉ ፡ ዘወር ፡ ይላሉ ፡ ወይዘሮ ፡ አሰጋሽ - - - አደፍርስ ፡ ከእልፍኝ ፡ ይወጣል - - አቶ ፡ ወልዱ ፡ ይለጥቃሉ - - ክብረት ፡ ይከተላል - - - ጺወኔም ፡ ብድግ ፡ ስትል «ምነው ፡ አርፎ ፡ አላስቀምጥ ፡ አለሽ ? የያዘሽ ፡ አባዜ - - ! ይኸው ፡ አኮረዶ ፡ ነው ፡ መሰለኝ ፡ እንዲህ ፡ ያናግር ፡ የነዛብሽ - - -» ቶሎ ፡ ብላ ፡ ተመልሳ ፡ ቁጭ ፡ ትላለች «እሺ ፡ ልጄ ፡ ምን ፡ ምን ፡ ብንይዝ ፡ የሚሻል ፡ ይመስልሃል ፡ ታዲያ - - - ? እንደ ፡ አገልግልም - - እንደ ፡ ድርቆሽም - - -

# ፴፬

# አደፍርስ

«እንዴት ፡ እንዴት ፡ በቀላል ፡ ነገር ፡ የምትተካ ፡ መስለሆይ ፡ ይሉታል ፡ ጉርፉን ? እኔ ፡ ነኝ ፡ ቀላሉ ? እኔ ፡ የጉርፉን ፡ ያህል ፡ ሳልሆን ፡ ቀርቼ ፡ ማለት - - ? የሳቸውን ፡ እግር ፡ ሳልስም ፡ ቀረሁና - - -

«የለም ፡ የለም ፡ አንተን ፡ ማለቷ ፡ አይደለም - - - ቦታውን ፡ እንደ እሱ ፡ የሚያውቀው ፡ የለም ፤ ሌላ ፡ ሰው ፡ የሚሆን ፡ ቢሆን ፡ እሱን ፡ አልፈልግም ፤ አላስቸግርም ፡ ነበር ፡ ማለቷ ፡ ነው - - - ካለ ፡ ነገሯ ፡ የጉድን ፡ አነጋገር ፡ አይሆንላትም ፤ የጉሪጥ ፡ ነው ፡ አቀራረቧ ፡ ሁሉ - - ያስከፋል ፡ አያስከፋም ፡ ሳትል - - ለጊዜው ፡ መስሎ ፡ የታያትን - - - » ያግባባሉ ፡ አደፍርስን ፡ አቶ ፡ ወልዱ ፤ ከእልፍኝ ፡ ወጥተው ፡ ወደ ፡ መኝታቸው ፤ ወደ ፡ ወርዶፉ ፡ ጉጆ ፡ እንደተመለሱ « የለም ፡ በእንዲህ ፡ ያለ ፡ ጉዳይ ፡ ልቡብ ፡ መሆን ፡ ይኖርብሃል - - -

«ቢሆንም ፤ ቢሆንም - - ያባባል ፡ ስሕተት ፡ ዓይነት ፡ ዓይነት ፡ አለው - - - እርግጥ ፡ ነው ፡ መቼም ፤ አልክድም - - ጉርፉ ፡ ደኅና ፡ ልጅ ፡ መሆኑን - -

«እንዲህ ፡ ያለ ፡ ጠዋይ ፡ አስተያየት - - -

«ጠዋይ ፤ ጠዋይ ! ምን ፡ ማለትዎ ፡ ይሆን ፡ ደግሞ ፡ እርስዎ - - ?

«የተወለጋገደ ፤ የተጣመመ ፡ አስተያየት ፡ ማለቴ ፡ ነው ፤ ጥሩ ፡ አይደለም - - - የኋላ ፡ ኋላ ፡ የሚጐዳህ ፡ ራስክን ፡ ነው ።— እንኳን ፡ አለመልኩ ፡ መልክ ፡ ሰጥተውት ፡ የዛሬን ፡ ነገር ፡ እንዲያውም ፡ አልተቻለ - - - አሁን ፡ በየፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የምሰማው ፡ ጠዋይ ፡ ክርክር - - ጠበቃው ፡ የሚያመጣው ፡ ጥውየት—ዳኛው ፡ የሚያሰማው ፡ ጥውየት ፡ የሕጉ ፡ መጽሐፍ ፡ የሚዘረዝረው ፡ ጥውየት - - ሰሚን ፡ ሰለቸው ፡ ነው - - እንዲያው ፡ ሄደት ፡ ብለህ ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ብታዳምጥ - - -

«ሰው ፡ መቼም ፤ ካነጋገሩ ፤ ከሁኔታው ፡ እንደ ፡ ገባው ፡ አይደለም ፤ የነገርን ፡ መሄጃ ፡ የሚያገኘው - - - ?

«እኮ ! እሱ ፡ ላይ ፡ ተሳስተሃል ፡ ነው ፡ የምለው - - -

«አዬ ፡ እንዲያውም ፡ እርስዎም ፡ ትንሽ ፡ ተጫኑኝ - - ምን ፡ ያረጋል ፡ መቀጠሉ - - -

«አንድ ፡ ነገር ፡ ተመልክተህልኛል ፡ ለመሆኑ - - - ?

«ምን - - - ?

«ስለዚህ - - ስለ ፡ እናንተ ፡ ስለ ፡ ዘመኑ ፡ ልጆች - - - አሁን ፡ እኛም ፡ በዘመናችን - - ችኮ ፡ መንቻኮች ፡ የመጨረሻ ፡ ምርዱዳን ፡ ተብለናል - - በተለይ ፡ አንድ ፡ ክርክር ፡ የያዝን ፡ እንደሁ - - እንዲያው ፡ ምን ፡ ቢሆን - - መረታታችንን ፡ እንኳን ፡ ልባችን ፡ ቢያውቀው ፡ እንዴት ፡ ብለን ፡ በገሃድ ፡ አጉራህ ፡ ጠናኝ ፡ ልንል - - ግትሮች ፡ ነበርን - - ታዲያ ፡ ቢሆ ንም ፡ አሁን ፡ ሳየው ፡ እናንተ ፡ የባሳችሁ ፡ መሰለኝ - - -

« 'ኦብስቲኔት' ማለትዎ ፡ ነው - - ?

«አዎ 'ኦፒስቲኔ' ናችሁ - - ከልክ በላይ - - !

« - - የትምህርታችን ፡ ይዞታ ፡ እንደሁ ፡ እንዲያ ፡ ያረገን ? አይታ ወቅምኮ - - -

« - - ሊሆን ፡ ይችላል - - የዛሬ ፡ ትምህርት ፡ ፍደሳና ፡ መድልው ፡ ይበዛበታል - - - 'ኢፓክሪት !' 'ኢፓክሪት' ብቻ ፡ ነው ፡ በየቦታው ፡ የሚታየው - - -

«ሆኖም ፡ ታዲያ ፡ የዘመናዊ ፡ ሰው ፡ ምልክት ፡ አይመስልዎትም - - ?

«አዎ ፡ አዎ ፡ የሚንነት ፡ ምልክት ፡ ነው ! የ 'ፌኔስ' ምልክት ፡ ፈረንሳዎች ፡ እንደሚሉት - - -

«አንድ ፡ ነገር ፡ ብጠይቅዎ - - ይቅርታ ፡ አድርገውልኝ - - -

«ጠይቀኝ ፡ ጠይቀኝ ፡ ምን ፡ አለ ? እምልህ ፡ የምመልሰው ፡ ከሆነ - -

«እንደዚህ ፡ እንደ ፡ እርስዎ ፡ ያለ ፡ ሰው ፡ ብዙ ፡ ዓለም ፡ ያዩ ! የተማረ ! ምን ፡ ይሠራል ፡ እዚህ ፡ እገጠር - - ?

«ብዙ ፡ ዓለም ! ብዙ ፡ ዓለም - - አዎ ፡ ብዙ ፡ ዓለም ፡ አይቻለሁ ፤ የፓሪው ፡ ወልዱ ፡ ነበር ፡ የቁልምጫ ፡ ስሜ - - - አለባበሴ ፡ አደናነሴ ፡ ልዩ ፡ ነበር - - ሁሉ ፡ ነገር ፡ ያምራል ፡ በጊዜው - - ስንቱን ፡ ስንቱን ፡ ሠራንበት - - አንዴ ፡ አስታውሳለሁ ፡ በ፲፱፻፲፯ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡

ገደማ ፥ ባልጋ ፡ ወራሽነታቸው ፡ ጊዜ ፥ ጃንሆይ ፡ መኳንንታቸውን ፡ አስከትለው ፡ ፈረንሳይ ፡ አገር ፡ መጥተው ፡ ነበር - - -

«ታዲያ ፡ እንዴት ፡ ዘመድ ፡ ሳያበጁ ፡ ቀሩ ? እምልዎ ? በዚያን ፡ ዘመን ፡ የኢትዮጵያዊ ፡ ፊት ፡ ፈረንሳይ ፡ አገር ፡ ማየት ፡ ብርቅ ፡ መሆን ፡ አለበት - - -

«ብርቅ ? በጣም ፡ እንጂ ! ብርቅ ፡ ነበር ።— እኛው ፡ ነበርን ፡ ሽር ፡ ጉድ ፡ ያልንበት - - - አስተርጓሚዎቹ ፥ ክራባት ፡ አሣሪዎቹ - - ምኑ ፡ ቅጡ - - -

«ታዲያ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሲመለሱ ፥ እንዴት ፡ ወገን ፡ አልሆኑዎትም ፥ እነዚያ ፡ ያስተናገዷቸው ፡ መኳንንት - - - ?

«ወገን ? ወገን ! ሀ ! ወገን ፡ ራስ ፡ ብቻ ።— ሰማሆይ - - እንዲህ ፡ ሆንሁልህ ፡ በዚያኑ ፡ ጊዜ - - አንዱን ፡ ትልቅ ፡ ሰው ፡ አምኜ - - አገሬ ፡ ወስጄ ፡ ላሹምህ ፡ ላሸልምህ ፡ አሉኝ - - እምቢ ፡ አልኳቸው ።— ብዙ ፡ ብዙ ፡ ስብከት ፡ አመጡ - - ስለ ፡ ሀገር ፥ ስለ ፡ ወገን ፥ ስለ ፡ ስንቱ - - ? ልቤን ፡ አሸፈቱት - - ጃንሆይን ፡ እጅ ፡ ልንነሣ ፡ ቀረብንና - - ያገሬ ፡ ልጆች ፡ የሆናችሁ ፡ ወደ ፡ እናት ፡ አገራችሁ ፡ ለመግባት ፡ የምትፈልጉ ፥ ልውሰዳችሁ - - እኔ ፡ ረዳታችሁ ፡ እሆናለሁ ፡ አሉን ።— ለጊዜው ፡ ማንም ፡ የፈለገ ፡ አልነበረም - - እኔም ፡ ሳመነታታ ፡ ብዙ ፡ ቆየሁ ።— በመከያው ፡ የኛሁ ፡ ጌቶቹን ፡ ተከትለው ፡ የመጡት ፡ ሰው - - ስማቸውን ፡ መጥራት ፡ አልሻም - - የሳቸው ፡ ስብከት ፡ አሸነፈኝ ።— ፓሪ ፡ መቼም ፡ ተደስቻለሁ ፤ ይክበር ፡ ይመስገን ፡ ለፈጣሪ ፥ ዓለምን ፡ አይቻለሁ - - በየዳንሱ ፡ ቤት ፡ አባክነው ፡ የነበረው ፡ ገንዘብ - - ! ተቀማጭ ፡ የሚሉትን ፡ ነገር ፡ ማን ፡ አስቦት - - እና ፡ ይኸውልህ ፡ ወዳገሬ ፡ ለመመለስ ፡ ስቆርጥ ፡ እከሌን ፡ የሚሉትም ፡ ገንዘብ ፡ አልነበረኝ - - እኝሁ ፡ እጃንሆይ ፡ አሸከር ፡ ላይ ፡ ነው ፡ ሽክም ፡ ሆኜ ፡ እዚህ ፡ የደረስሁት - - ምን ፡ አለ ፡ ከዚያማ - - እንደመጣሁ ፡ ነጋድራስ ፡ ብለው ፡ ሾሙኝ ።—አገር ፡ ቤት ፡ ሄደህ ፡ ዘመዶችህን ፡ ትጠይቃለህ ፡ ብለውኝ ፡ ነበርና ፥ ዘመዶቼን ፡ ልጠይቅ ፡ ይፍቀዱልኝ ፡ አልኳቸው - - ፈቀዱልኝ ። —በቅሎም ፡ እንዲታዘዝልኝ ፡ ጠየቅሁ - - አዘዙልኝ ፡ በቅሎውንም ።— ነገሩ ፡ እንግዲህ ፡ በቅሎ ፡ መረጣው ፡ ላይ ፡ ነው - - የገንዘብንም ፡ ጥቅም ፡ ያወቅሁት ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ ነው ።— በቅሎ ፡ ጋጥ ፡ ገባሁና ፡ በቅሎ ፡ ስመርጥ - - ያቺን ፡ ልውሰድ ፡ አልኩት ፡ ባልደራሱን - - ከት ፡ ብሎ ፡ ሳቀብኝ - - ድሃ ፡ በሕልሙ ፡ ቅቤ ፡

ባይጠጣ ፡ ደርቆ ፡ ይሞት ፡ ነበር ፡ አለኝ - - - ተናደድሁ ! ጦፍሁ ! የመረጥኋት ፡ በቅሎ ፡ የጌቶች ፡ ኖራለች - - አንድ ፡ መጋኘ ፡ ነገር ፡ ሰጠኝ - - የበቅሎ ፡ ዕቃውንም ፡ ስንቱን ፡ ብጥስጣሽ ፡ ከያለበት ፡ አጠራቅሞ - - - ምናለ ፡ መቼስ ፡ እምቢ ፡ አይሉት ፡ ነገር - - ብቻ ፡ ምን ፡ አለፋህ ፡ በዚያው ፡ ንዴት ፡ ባሙቱም ፡ እንደሁ ፡ ወደ ፡ ፈረንሳይ ፡ አገር ፡ ተመለስሁ - - የገንዘብንም ፡ ጥቅም ፡ ቀስ ፡ በቀስ ፡ ተረዳሁ ፤ እንደ ፡ በፊቱ ፡ አልታለልሁኝም - - ስድስት ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ በካናል ፡ ሱዌዝ ፡ ላይ ፡ የተመላለስኩት - - -

«ታዲያ ፡ ለምን ፡ የመንግሥት ፡ ሥራ ፡ ሳይዙ ፡ ቀሩ ? እምልዎት ፡ በመጨረሻ ፡ ጊዜ ፡ ላይመለሱ ፡ ቆርጠው ፡ አገርዎ ፡ ሲገቡ - - -

«አልፈለግሁም - - - ለሌላ ፡ ሰው ፡ ባሪያ ፡ ከመሆን ፡ ለራሴ ፡ ባሪያ ፡ መሆንን ፡ መረጥሁ - - - ለራሱ ፡ ባሪያ ፡ መሆን ፡ ያልቻለ ፡ ለሌላ ፡ ሰው ፡ ባሪያ ፡ ይሆናል ፡ ነው ፡ የኑሮዬ ፡ ፍልስፍና - - - ስለዚህ ፡ ለራሴ ፡ እንዳሽከርም ፡ እንደ ፡ ጌታም ፡ ሆኜ ፡ እኖራለሁ - - ይክበር ፡ ይመስገን ፡ ሀብት ፡ አለኝ ።— ግን ፡ ቢሆንም ፡ ከረዳቶቼ ፡ ጋር ፡ ቁፋሮም ፡ እንደሁ ፡ አብሬ ፡ ቆፍሬ - - ሸክምም ፡ እንደሁ ፡ አብሬ ፡ ተሸክሜ ፡ ነው ፡ የምኖረው - -

«እዚህ ፡ እገጠር ፡ ታዲያ ፡ ምን ፡ ይሠራሉ ? አዲስ ፡ አበባ ፡ መጥተው ፡ ንግድዎን ፡ አሻሽለው ፡ ለምን ፡ አይኖሩም - - ?

«አዲስ ፡ አበባ ፡ ለኔ ፡ ብርቄ ፡ አይደለም - - ያዲስ ፡ አበባን ፡ ዓይነቱ ፡ ከተማ ፡ ሰልችቶኛል - - - ከዚያም ፡ በላይ ፡ ሠራተኛ ፡ ሆኖ ፡ መገኘት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የትም ፡ ሆነ ፡ የት ፡ ልዩነት ፡ አያመጣም - - - እዚህም ፡ ንግዴን ፡ ላስፋፋ ፡ እችላለሁ ፡ ከፈለግሁ - - - የሰው ፡ ጠባይ ፡ ስለሆነ ፡ ነው ፡ እንዲያው ፡ አዲሳባ ፡ አዲሳባ ፡ የሚለው ፡ ሕዝቡ - - - ሱካር ፡ እንዳየ ፡ ጉንዳን ፡ አንድ ፡ ላይ ፡ ለመታጀብ - - እኔ ፡ እንዲህ ፡ ያለው ፡ ኑሮ ፡ ሰልችቶኛል - - - ! እህል ፡ በቀርባባ— ዕንቁላል ፡ በወታቦ ፡ የሚገዛበትን ፡ አገር - - ህ ! ገጠር - - - ? ! ሰፊ - - ሰፊ - - - ሰፊ - - ሜዳ ፡ ተራራና ፡ ሸንተረር ፡ የሚታይበት ፡ ንጹሕ ፡ አየር ፡ የሚተነፈስበት ፡ አገር ፡ ነው ፡ የማይሰለቸኝ ፡ እኔ ! እና - - - የማይሰለቸኝንም ፡ አግኝቻለሁ ፡ ነው ፡ የምልህ - - - » ለትንሽ ፡ ጊዜ ፡ ሁለቱም ፡ ዝም ፡ ይላሉ ።—

« - - ነገ ፡ እንግዲህ ፡ ማለድ ፡ ብለን ፡ መነሣት ፡ አለብን ? » ይጠይቃቸዋል ፡ አደፍርስ ።

«ምን ፡ አስቸኮለን ? ሞቅ ፡ ሲል ፡ እንወጣለን ፤ የሚያስቸኩልም ፡ ነገር ፡ የለ - - » ዝም ፡ ይላሉ ፡ እንደገና ፡ ሁለቱም ፡ ለትንሽ ፡ ጊዜ « - - አስ ለፈለፍከኝኮ ፡ አንተ ፡ ልጅ - - ውዴ ታዬን ፡ ዐወቅሀና - - - » ቆም ፡ እንደ ማለት ፡ ይሉና « እስኪ ፡ ልሰናበታት ፡ አሰጋሽን ፤ በሌሊት ፡ ሃያጅ ፡ ነች ፡ መሰለኝ - - » ወጣ ፡ ካሉ ፡ በኋላ « አንተም ፡ ብትሰናበታት ፡ አይከፋም - - » ወደ ፡ እኅታቸው ፡ እልፍኝ ፡ ያመራሉ ።—

# ፴፫

# አደፍርስ

እሁድ ፡ ለት ፡ ከቤተክርስቲያን ፡ መልስ ፡ ወደ ፡ ወርካው ፡ ጥላ ፡ ሲያመሩ « ስሚኝ ፡ ፍሬዋ ፡ ጋሼ ፡ ጥሶ ፡ የሚያመጣው ፡ የባህል ፡ ተጠየቅ ፡ ሁሉ ፡ ሳይገባኝ ፡ ቀርቶ ፡ እይምሰልሽ ፡ በየጊዜው ፡ ስንከራከር ፡ የምትሰሚው - - - » ይወተውታል ፡ አደፍርስ ።—

« እንዲሁ ፡ ስትከራከር ፡ ነው ፡ የሚመሽልህ ፡ በየጊዜው - - - እኔ እምለውኮ - - - ከገባህ ፡ ታዲያ ፡ ለምን ፡ አይገባህም ? ለምን ፡ መልስህ፡ መልስህ ፡ ያንኑ ፡ አንዱን ፡ ነገር ፡ ታመጣዋለህ - - - ?

« አንዱን ፡ ነገር ? ምን ፡ ማለትሽ ፡ ነው ፡ አንዱን ፡ ነገር ! እኔ ፡ የማመጣው ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ ብቻ ፡ አይደለም ፤ ብዙ ፡ ነገር ፡ ነው - - -

« እምልህ - - ስለ ፡ ባህላችን ፡ ስለ ፡ ሕጋችንም ፡ ሆነ ፡ ስለሌላው - - አሁን ፡ ለምሳሌ—ኢትዮጵያ ፡ ነበሩ ፡ አሉ ፡ ይመጣሉም ፡ ብላ ፡ ስለምታምንባቸው ፡ መሪዎችና ፡ ጀግኖች ፡ ጻድቃንና ፡ ሰማዕታት - - ከኔም ይሁን ፡ ካባዬ ፡ ጋር ፡ ስንት ፡ ስንት ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ የተከራከርከው - - -

« ነበሩ ፡ ስለሚባሉት ፡ መቼም ፡ አሁንም ፡ ቢሆን ፡ የማውቀው ፡ ነገር ፡ የለኝም - - - ይመጣሉ ፡ ስለሚባሉትም ፡ በሰማይ ፡ ላም ፡ አለኝ - - -

« እንዴት ፡ በሰማይ ፡ ላም ፡ አለኝ ፡ ይሆናል ? ደግሞስ ፡ ስለነበሩት፡ እንዴት ፡ አታውቅም ? ባይሆን ፡ እያወቅህ ፡ አላምንም ፡ ወይም ፡ አልቀበልም ፡ በል ፡ እንጂ ፡ ጨርሰህ ፡ አላውቅም ፡ የምትለውን ፡ ነገር ፡ አልሰማም - - - እንኳን ፡ አንተ ፡ ብዙ ፡ የተማርከው ፡ እኔም ፡ ዐውቃለሁ ፡ እላለሁ - - -

« እኮ ፡ ከመሪዎች ፡ ውስጥ ፡ እንደ ፡ ዘረ ፡ ያዕቆብ ፡ እንደ ፡ ዐምደ ጽዮን ፡ ያሉትን - - - ከጀግኖች ፡ እንደ ፡ ልዑል ፡ ራስ ፡ መኰንን ፡ ራስ ፡ ጐበና ፡ ደጃች ፡ ባልቻ ፡ ራስ ፡ አሉላ - - - ከጻድቃን ፡ እንደ ፡ አቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ እንደ ፡ ቅድስት ፡ ክርስቶስ ፡ ሠምራ - - - ከሰማዕታት ፡ እንደ ፡ ቴዎድሮስ ፡ እንደ ፡ ዮሐንስ ፡ ዓይነቶቹን ፡ ማለትሽ ፡ ይሆናል ፡ ምናልባት - - - ?

« ምን ፡ እኔ ፡ ብቻ ፡ አንተም ፡ ማለትህ ፡ ይሁን ፡ እንጂ ! በተዘረዘሩት ፡ በማንኛዎቹም ፡ መስኮችክ ፡ ቢሆን ፡ በሌላው ፡ ክፍለ ፡ ዓለም ፡ በጊዜያቸው ፡ ከነበሩት ፡ ባለታሪኮች ፡ የሚያንሱ ፡ አይደሉም - - -

አባ ፡ ዮሐንስ ፡ አቶ ፡ ጥሶ ፡ አቶ ፡ ወልዱ ፡ ወይዘሮ ፡ አከላትና ፡ በላይ ፡ ሆነው ፡ እየተጨዋወቱ ፡ ወደ ፡ ወርካው ፡ ሥር ፡ ይመጣሉ ።— ዛሬ ፡ ለትምህርት ፡ ቤት ፡ ማሠሪያ ፡ የሚያስፈልገውን ፡ ገንዘብ ፡ ለማዋጣት ፡ ባቀዱት ፡ መሠረት ፡ የሁለተኛው ፡ ትልቅ ፡ ስብሰባቸው ፡ ቀን ፡ መሆኑ ፡ ነው ። ፍሬዋና ፡ አደፍርስ ፡ ቀድም ፡ ብለው ፡ ሥፍራ ፡ በመያዝ ፡ ከርከራቸውን ፡ እንደ ፡ ቀጠሉ ፡ ይደርሳሉ ።—

« - - ለምሳሌ ፡ አቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትን ፡ ጻድቅ ፡ ሊያሰኛቸው ፡ የቻለው ፡ ምንድነው ? ደብረ ፡ ሊባኖስን ፡ አቅንተው ፡ ገዳም ፡ ስላደረጉ ? እምልሽ ፡ ምን ፡ ሠርተዋል ፡ እስከዚህ ? በእሳት ፡ ተቃጠሉ ? በአናብስት፡ ተቆራረጡ ? ታሠሩ ፡ ተገረፉ ፡ ተሰቀሉ ? ምን ፡ ሠርተዋል ፡ እስከዚህ ፡ ሊያሳውቃቸው ፡ የቻለ - - ? » እያለ ፡ በረጅሙ ፡ ይዘታል ፡ አደፍርስ ።-

« የወጣቶች ፡ ነገር - - ደግሞ ፡ አቡነ ፡ ተክለሃይማኖትን ፡ ምን ፡ አደረጉ ፡ ይሆን ፡ የምትለው - - - ? » እያሉ ፡ ይጠጋሉ ፡ አባ ፡ ዮሐንስ ።-

« ምን ፡ አደረጉ ፡ እንላለን - - - ? ምንም ፡ አላደረጉ ፡ ነው ፡ የምለው ፡ እኔ ፡ በበኩሌ - - -» ይመልሳል ፡ አደፍርስ ።

« እውነትህን ፡ ነው ፤ ሃይማኖትን ፡ የሚያበላሽ ፡ አገርን ፡ ወገንን ፡ የሚበድል ፡ ምንም ፡ ያደረጉት ፡ ነገር ፡ የለም - - -

« ጻድቅስ ፡ የሚያሰኝ - - ታቦት ፡ የሚያስቀርጽ ፡ ምን ፡ ነገር ፡ ሠርተዋል - - - ?

« እንዴት ፡ ነው ፤ ጻድቅነታቸውን ፡ ትጠራጠራለህ ፡ ልበል ፡ ይሆን - - - ?

« አዎን ፡ እጠራጠራለሁ - - -

« የጸላኤ ፡ ሠናያት ፡ መጠጋት - - ! ጸላኤ ፡ ሠናያት ፡ ቢቀርብህ ፡ ነው ፡ ወዳጄ ! ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ የጻድቅ ፡ ጻድቅ ፡ ናቸው ።— እንዴታ ! ጥርጥር ፡ ሊገባህ ፡ አይገባም ። ሙቶሎሚን ፡ የመሰለ ፡ የወላሞ ፡ አረመኔ ፡ ንጉሥ ፡ ወደ ፡ በጐ ፡ ምግባር ፡ መልሰው ፡ አስተምረውና ፡ አጥምቀው ፡ ክርስቲያን ፡ ያደረጉ -- ሰባት ፡ ዓመታት ፡ ሙሉ ፡ በአንድ ፡ እግራቸው ፡ ቆመው ፡ ስለ ፡ ሀገር ፡ ስለ ፡ ሕዝብ ፡ ሲጸልዩ ፡ የቆሙበት ፡ እግር ፡ እስከ ፡

መቆረጥ ፡ የደረሰ -- ስድስት ፡ ክንፎች ፡ እስከማብቀል ፡ ድረስ ፡ ክብር ፡ የተሰጣቸው - - - ጻድቅ ፡ ናቸው ፡ እንጂ ፡ የኔ ፡ ልጅ ! ከሳቸው ፡ የበለጠ ፡ ጻድቅ ፡ ከየት ፡ ሊመጣ - - - ?

« እኔኮ ፡ የምለው ፡ ስለ ፡ ክርስቶስ ፡ ሲሉ ፡ የተሠቃዩት ፡ ሥቃይ ፡ የለም ፡ ነው - - -

« ሥቃይ -- ? በቆዳ ፡ እየተጠቀለሉ ፡ እገደል ፡ ከመወርወር ፡ እባሕር ፡ ውስጥ ፡ ከመጣል ፡ የበለጠ ፡ መሠቃየት ፡ አለ ፡ እንዳትለኝ - - -

« ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ እገደል ፡ ተወርውረዋል - - እባሕር ፡ ተጥለዋል ፡ ነው ፡ የሚሉኝ - - -

« እንዴታ ! ከተጣሉበትም ፡ ሁሉ ፡ ምንም ፡ ሳይሆኑ ፡ ወጥተዋል -- ኋላ ፡ መቶሎሚን ፡ በየትኛው ፡ ጦር ፡ ሠራዊታቸው ፡ አሸነፉት - - - ?

« ስድስት ፡ ክንፎችም ፡ አውጥተው ፡ ነበር ፡ ነው ፡ የሚሉኝ ፡ ከቅድስናቸው ፡ የተነሣ - - - ?

« እንዴታ ! እተቆረጠው ፡ እግራቸው ፡ ላይ ፡ እቁርጭምጭሚታቸው ፡ ገደማ ፡ የበቀለላቸው ፡ ክንፍ ፡ ሳይቆጠር - - -

« እስከሱ ፡ ስምንት ፡ መሆኑ ፡ ነው ፡ እንግዲህ - - -

«አይ ፡ ገድላቸው ፡ ስምንት ፡ አይልም - - ስድስት ፡ ነው ! እየምስላቸው ፡ ላይ ፡ ግን ፡ በግልጽ ፡ ልታየው ፡ ትችላለህ - - - በርግጥ ፡ እግራቸው ፡ ክንፍ ፡ አጐጥጉጦ ፡ ይታያል - - -

« ጋሼ ፡ ጥሶስ ፡ ምነው ፡ ዝም ፡ አልህ -- ምንድነው ፡ ያንተ ፡ አስተያየት -- ?

«እንዲህ ፡ ዓይነቱን ፡ ነገርኮ ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ የተወያየንበት ፡ መስሎኛል ። ምናልባት ፡ እንኳ ፡ ከፍሬዋ ፡ ጋር ፡ ይሆን - - -

« በጠቅላላው ፡ ተነጋግረናል ፡ ከኔም ፡ ጋር - - -

« ስለ ፡ አቡነ ፡ ገብረ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ - - - አልተነጋገርንም ፡ ካንተ ፡ ጋር -- ?

« በተለይ ፡ ስለሳቸው ፡ አልተነጋገርንም ፤ ግብጻዊ ፡ መሆናቸውን ፡ ግን ፡ ዐውቃለሁ - -

« ግብጻዊስ ፡ ግብጻዊ ፡ ናቸው - - ብቻ ፡ ቢሆንም ፡ በመላ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የታወቁ ፡ ጻድቅ ፡ ናቸው - - -

« አቦ ፡ የሚሏቸው ፡ አይደሉም - - - ?

«አዎ ፡ አቦም ፡ አቡነ ፡ ገብረ ፡ ሕይወትም ፡ አቡየ ፡ ጻድቁም ፡ አቡነ ፡ ገብረ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ ይሏቸዋል - - -

« ያገራችን ፡ ጻድቃን ፡ መቼ ፡ እነሱንና ፡ ነው ፡ ታዲያ - - - ካሉ ፡ ማለቴ ፡ ነው - - - በሰው ፡ አገር - - ጻድቃን - - የምናምነው - - - ?

« ካሉ ፡ አትበል ፡ ወዳጄ ፤ ሞልተዋል - - ! እነ ፡ አቡነ ፡ ዜና ፡ ማርቆስ ፡ እነ ፡ አቡነ ፡ መልከ ፡ ጼዴቅ ፡ እነ ፡ ወለተ ፡ ጴጥሮስ ፡ እነ ፡ ዘርዓ ፡ ቡሩክ ፡ እነ ፡ ተክለ ፡ አልፋ ፡ እነ ፡ ሐራ ፡ ድንግል ፡ እነ ፡ መብዓ ፡ ጽዮን ፡ እነ ፡ አቡነ ፡ ፊልጶስ ፡ እነ ፡ አቡነ ፡ ተክለ ፡ ሐዋርያት - - እነ ፡ አቡነ ፡ ሳሙኤል ፡ ዘዋሊ ፡ እነ ፡ ቅድስት ፡ እማመዝ - - እነ ፡ አቡነ ፡ ዘርአ ፡ አብርሃም ፡ እነ ፡ አቡነ ፡ አቢየ ፡ እግዚእ - -

« እሽ ፡ እሺ ፡ ሰማሁ ፤ ብዙ ፡ ናቸው ፡ ማለት ፡ ነው - - -

«ብጣም ፡ እንጂ ፡ ብዙ ፡ ናቸው - - - ፈጣሪ ፡ ይክበር ፡ ይመስገን - - -

«ሸዋዎች ፡ መሆን ፡ አለባቸው ፡ መቼም ፡ እነዚህ ፡ ሁሉ ፡ ቅዱሳን - - -

« ሸዋዎች - - ? ሸዋ ፡ ግብጽ ፡ ቁስጥንጥንያ ፡ ሮም ፡ አይልም ፡ ቅድስና - - እንደ ፡ እንጉዳይ ፡ ነው ፡ የእግዚአብሔር ፡ ጸጋ ፡ በወረደበት ፡ ቦታ ፡ ሁሉ ፡ የሚበቅሉት - - -

« የምለው ፡ ኢትዮጵያውያኑ ፡ ጻድቃን - - -

« እነሱም ፡ ቢሆኑ ፡ ከጐጃም ፡ ከተጉለት ፡ ከበጌምድር ፡ ከደብረ ፡ ቢዘን ፡ ከትግሬ ፡ ከድፍን ፡ ኢትዮጵያ ፡ ናቸው - - -

« ለምሳሌ ፡ ከወሎ ፡ ከአሩሲ ፡ ከባሌ ፡ የሉባቸውም - - -

« አይ ፡ ከድፍን ፡ ኢትዮጵያ ፡ ናቸውኮ ፡ ብየሃለሁ - - ከድፍን ፡ ኢትዮጵያ ! ከአንድ ፡ ቦታ ፡ መርጋት ፡ የለባቸውም ፡ ጻድቃን ፡ ሲባሉ ።— ለምሳሌ ፡ አቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ድፍን ፡ ኢትዮጵያን ፡ በመዘዋወር ፡ ወንጌልን ፡ አስተምረዋል - - -

« እዚህ ፡ ላይ ፡ መቼም ፡ አባ ፡ ዮሐንስ ፡ ቅዱሳን ፡ ሲሉ ፡ የክርስትና ፡ ሃይማኖት ፡ ተከታዮችን ፡ ብቻ ፡ አይመስለኝም - - ማለቴ ፡ እስላሞችም ፡ ቢሆኑ ፡ በአንድ ፡ ፈጣሪ ፡ የሚያመልኩ ፡ ስለሆኑ — የእግዚአብሔርን ፡ ጥሪ ፡ የተከተሉ ፡ ቅዱሳን ፡ አሏቸው - - » ጣልቃ ፡ ይገባሉ ፡ አቶ ፡ ጥቦ ።

« አቦ ፡ የሚሏቸው ፡ አይደሉም - - - ?

« አዎ ፡ አቦም ፡ አቡነ ፡ ገብረ ፡ ሕይወትም ፡ አቡየ ፡ ጻድቁም ፡ አቡነ ፡ ገብረ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ ይሏቸዋል - - -

« ያገራችን ፡ ጻድቃን ፡ መቼ ፡ እነሱንና ፡ ነው ፡ ታዲያ - - - ካሉ ፡ ማለቴ ፡ ነው - - - በሰው ፡ አገር - - ጻድቃን - - የምናምነው - - - ?

« ካሉ ፡ አትበል ፡ ወዳጄ ፤ ሞልተዋል - - ! እነ ፡ አቡነ ፡ ዜና ፡ ማርቆስ ፡ እነ ፡ አቡነ ፡ መልከ ፡ ጼዴቅ ፡ እነ ፡ ወለተ ፡ ጴጥሮስ ፡ እነ ፡ ዘርዓ ፡ ቡሩክ ፡ እነ ፡ ተክለ ፡ አልፋ ፡ እነ ፡ ሐራ ፡ ድንግል ፡ እነ ፡ መብዓ ፡ ጽዮን ፡ እነ ፡ አቡነ ፡ ፊልጶስ ፡ እነ ፡ አቡነ ፡ ተክለ ፡ ሐዋርያት - - እነ ፡ አቡነ ፡ ሳሙኤል ፡ ዘዋሊ ፡ እነ ፡ ቅድስት ፡ እማሙዝ - - እነ ፡ አቡነ ፡ ዘርአ ፡ አብርሃም ፡ እነ ፡ አቡነ ፡ አቢየ ፡ እግዚእ - -

« እሽ ፡ እሺ ፡ ሰማሁ ፤ ብዙ ፡ ናቸው ፡ ማለት ፡ ነው - - -

« በጣም ፡ እንጂ ፡ ብዙ ፡ ናቸው - - - ፈጣሪ ፡ ይክበር ፡ ይመስገን - - -

« ሸዋዎች ፡ መሆን ፡ አለባቸው ፡ መቼም ፡ እነዚህ ፡ ሁሉ ፡ ቅዱሳን - - -

« ሸዋዎች - - ? ሸዋ ፡ ግብጽ ፡ ቁስጥንጥንያ ፡ ሮም ፡ አይልም ፡ ቅድስና - - እንደ ፡ እንጉዳይ ፡ ነው ፡ የእግዚአብሔር ፡ ጸጋ ፡ በወረደ በት ፡ ቦታ ፡ ሁሉ ፡ የሚበቅሉት - - -

« የምለው ፡ ኢትዮጵያውያኑ ፡ ጻድቃን - - -

« እነሱም ፡ ቢሆኑ ፡ ከጐጃም ፡ ከተጉለት ፡ ከበጌምድር ፡ ከደብረ ፡ ቢዘን ፡ ከትግሬ ፡ ከድፍን ፡ ኢትዮጵያ ፡ ናቸው - - -

« ለምሳሌ ፡ ከወሎ ፡ ከአሩሲ ፡ ከባሌ ፡ የሉባቸውም - - -

« አይ ፡ ከድፍን ፡ ኢትዮጵያ ፡ ናቸውኮ ፡ ብየሃለሁ - - ከድፍን ፡ ኢትዮጵያ ! ከአንድ ፡ ቦታ ፡ መርጋት ፡ የለባቸውም ፡ ጻድቃን ፡ ሲባሉ ። — ለምሳሌ ፡ አቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ድፍን ፡ ኢትዮጵያን ፡ በመዘዋወር ፡ ወንጌልን ፡ አስተምረዋል - - -

« እዚህ ፡ ላይ ፡ መቼም ፡ አባ ፡ ዮሐንስ ፡ ቅዱሳን ፡ ሲሉ ፡ የክርስትና ፡ ሃይማኖት ፡ ተከታዮችን ፡ ብቻ ፡ አይመስለኝም - - ማለቴ ፡ እስላሞችም ፡ ቢሆኑ ፡ በአንድ ፡ ፈጣሪ ፡ የሚያመልኩ ፡ ስለሆኑ — የእግዚአብሔርን ፡ ጥሪ ፡ የተከተሉ ፡ ቅዱሳን ፡ አሏቸው - - » ጣልቃ ፡ ይገባሉ ፡ አቶ ፡ ጥሶ ።

« እንዴታ ! ሞልተዋቸዋል - - እንደ ፡ ሼህ ፡ ከድር ፡ ዓይነቱ ፡ ለምሳሌ ፡ ከወሎ - - » ያብራራሉ ፡ አባ ፡ ዮሐንስ ።

« - - ቀይ ፡ ገደልስ ፡ ማነው ፡ ስማቸው—ጌታው ፡ ሼክ ፡ ሁሴን - - - ባሌ ፡ ደግሞ ፡ ሌላ ፡ ሼክ ፡ ሁሴን - - - አሩሲ ፡ ደግሞ ፡ እንዲሁ ፡ ሌላ ፡ ሼክ ፡ ኑረ ፡ ሁሴን - - ሞልተዋቸዋል - - - » ይቀጥላሉ ፡ አቶ ፡ ጥሶ ።—

« ስለዚህ ፡ ብቻ ፡ በጠቅላላው ፡ ሞልተውናል ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ጻድ ቃን ፡ በኢትዮጵያ - - » ያመቻቻል ፡ አደፍርስ

« እንዴታ ፡ እንዴታ ፡ ሞልተውናል - - » እያሉ ፡ ይስፋፋሉ ፡ አባ ፡ ዮሐንስ ።—

« - - ለምንድነው ፡ ታዲያ ፡ አቡነ ፡ አረጋዊ ፡ አባ ፡ ሊባኖስ ፡ አባ ፡ ገሪማ ፡ ቅዱስ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ቅዱስ ፡ እስጢፋኖስ ፡ የምንለው ? ግብጻው ያኑ ፡ ሶርያውያኑ ፡ ምን ፡ ያደርጉልናል ? ለምን ፡ የራሶቻችን ፡ ብቻ ፡ አይበቁንም - - - ?

« ቅዱሳኑንና ፡ ሰማዕታቱን ፡ አደባልቅሃቸው - - ብቻ ፡ ቢሆ ንም - - ጻድቃንና ፡ ሰማዕታት ፡ ለመሆን ፡ ጊዜና ፡ ቦታ ፡ አይወስነውም ፡ ያልኩህ ፡ ይመስለኛል - - » ይመልሳሉ ፡ አባ ።—

«ስለ ፡ አቡነ ፡ ገብረ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ጀምረን ፡ ነበር ፡ ቅድም - - » ረጋ ፡ ባለ ፡ አንደበት ፡ ያስረዳሉ ፡ አቶ ፡ ጥሶ « ግብጻዊ ፡ ናቸው ፡ ብለ ናል ።- በኢትዮጵያ ፡ የታወቁ ፡ ጻድቅ ፡ ናቸው ፡ ብለናል ።— ገድላቸው ፡ እንደሚያትተው ፡ ሲወለዱ ፡ እንሥተው ፡ የናታቸውን ፡ ጡት ፡ አልቀ መሱም ፡ ይባላል ።— ለመወለድም ፡ እንኳ ፡ የበቁት ፡ የአባታቸው ፡ ርስ ሐት ፡ ከቀጤማ ፡ ላይ ፡ ፈሶ ፡ ኖሮ ፡ እናቲቱ ፡ እንደ ፡ መተከዝ ፡ ብለው ፡ ቄጠማውን ፡ ቆርጠው ፡ ስለመጠጡት ፡ ፅንስ ፡ ሆኖ ፡ ነው ፡ ይባላል - - -

« ጋሼ ፡ ጥሶ ፡ አንዳንዴ ፡ ብረር ፡ ብረር ፡ ነው ፡ የሚያሰኘኝ ፡ ንግ ግርህ - - ደሞ ፡ ደሞ - - እንዴት - - በአፍ ፡ የገባ ፡ ነገር ፡ ወደ ፡ ማሕፀን ፡ ገብቶ ፡ ተፀንሶ - ሰው ፡ ሆኖ ፡ ተወለደ ፡ ብለህ ፡ ታወራልኛለህ - - - ?

«የሱስን ፡ ማርያም ፡ የወለደችው ፡ በድንግልና ፡ አይደለም - - ?

« ቢሆንም ፡ የሷ ፡ ይሻላል - - የመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ኃይል ፡ የእም ነት ፡ ጉዳይ ፡ ነው - -

«እንግዲያው ፡ የአቦም ፡ ፅንሰት ፡ የእምነት ፡ ጉዳይ ፡ ነው - - -

«ድግሞ ፡ ሲወለዱ ፡ ጀምሮ ፡ የእናታቸውን ፡ ጡት ፡ አልቀመሱም - - - » ይቀጥላል ፡ አደፍርስ ።—

«ምነው ፡ ለምን ፡ ያስገርምሃል ፡ ይኸ ? ስንቶቹ ፡ ናቸው ፡ የዛሬዎቹ ፡ እንኳ ፡ ልጆች ፡ በፍየል ፡ ወተት ፡ በላም ፡ ወተትና ፡ በዱቄት ፡ ወተት ፡ የሚያድጉት - - - ምናልባት ፡ በፍየል ፡ ወተት ፡ አድገው ፡ ይሆናል - - - » ትቋቋመዋለች ፡ ፍሬዋ ፡ ታዳምጥ ፡ ታዳምጥና ።

« - - - ዝቋላ ፡ የተባለውንም ፡ የሠይጣን ፡ ቦታ ፡ ለራሳቸው ፡ ለማድረግ ፡ በራሳቸው ፡ ተደፍተው ፡ ብዙ ፡ ዘመን ፡ ጸልየዋል ።—ክርኀራኄያቸው ፡ ብዛት ፡ የተነሣ ፡ አንድ ፡ የተጠማ ፡ አሞራ ፡ ቢመጣ ፡ ዓይናቸውን ፡ ሰጥተውታል ።—በጃቸው ፡ ይይዟት ፡ የነበረች ፡ ጭራ ፡ ግን ፡ አንድ ፡ ዝንብ ፡ መግደሏን ፡ በመመስከሯ ፡ ለሞታቸው ፡ ምክንያት ፡ ሆናባቸዋለች ።— አናብስትን ፡ አናብርትን ፡ መባርቅትን ፡ ለማዘዝ ፡ በቅተዋል - - -

‘አቡየ ፡ ጻድቁ ፡

አቡየ ፡ ጻድቁ ፡

ገደል ፡ እንዳክርማ ፡ የሚሰነጥቁ ፡

በዘንጋቸው ፡ ወግተው ፡ ጠበል ፡ የሚያፈልቁ’ ሲባልላቸው ፡ ይኖራል ፡ ይኸው ፡ እስከ ፡ ዛሬም - - -

«ድንቁርናና ፡ ዕውቀት ፡ ብሎ ፡ ነገር ! የሚገርመኝኮ ፡ የተቃራኒው ፡ ብዛት - - ጠበል ፡ ሊያፈልቁ ፡ ቢችሉ ፡ ዓይናቸውን ፡ ለአሞራው ፡ መስጠት -- በአንድ ፡ ዝምብ ፡ ሞት ፡ ምክንያት ፡ እሳቸው ፡ እንዲሞቱ ፡ መፈረድ - - ጭራው ፡ ደሞ ፡ ከፈረስ ፡ ላይ ፡ የተቆረጠ ፡ መሆን ፡ አለበት ፡ መቼም - - -

«ሳይቆረጥም ፡ አንዳንዱ ፡ ተንቅሎ ፡ የተበጀ ፡ ሊሆን ፡ ይችላል - -» ትናገራለች ፡ ፍሬዋ ። -

«ከብቃታቸው ፡ የተነሣ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ የተሰጣቸውም ፡ ሊሆን ፡ ይችላል - - » ይመክታሉ ፡ አባ ።

«ብቻ ፡ ያም ፡ ሆነ ፡ ይህ - - ባንተ ፡ አስተያየት ፡ አደፍርስ - - ከየትም ፡ ይምጡ - - ዕድለኛ ፡ ሆነህ ፡ ብቻ ፡ ይምጡልህ ፤ ኀያላን ፡ አውሬዎችን ፡ አዘው ፡ ከሥልጣናቸው ፡ ሥር ፡ የሚያውሉ - - መብረቅን ፡ ያህል ፡ ቁጣ ፡ ተቆጣጥረው ፡ ለጠላት ፡ መመከቻ ፡ የሚያደርጉ - - ለሕይወት ፡ ከመሳሳታቸው ፡ የተነሣ ፡ የዝንብን ፡ ሕይወት ፡ እንኳ ፡ ቢሆን ፡ ለማሳለፍ ፡

የማይሹ - - ከርኅራኄያቸው ፡ ከደግነታቸው ፡ የተነሣ ፡ ለተፈጥሮ ፡ ጓደኛ
ቸው ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ለእሞራ ፡ እንኳን ፡ ዓይናቸውን ፡ የሚሰጡ - - እን
ዲህ ፡ ያሉ ፡ ጻድቅ ፡ ቢኖሩህ ፡ አትወድም - - ?

«እንዲኖሩኝ ፡ መፈለግና ፡ የሌሉኝ ፡ መሆን ፡ የተለያዩ ፡ ነገሮች ፡
ናቸው - -

«አንድ ፡ ጊዜ ፡ ደግሞ ፡ ከሞቱ ፡ በኋላ ፡ ስእለት ፡ የቀረበላቸውን ፡
አውራ ፡ ዶሮ ፡ አንድ ፡ ዐቃቢ ፡ እርድ ፡ አድርጎ ፡ በልቶባቸው ፡ ኖሮ - -
ቄሶችና ፡ ዲያቆኖች ፡ ተሰብስበው ፡ ዶሮውን ፡ የሰረቀውን ፡ ሰው ፡ ለማ
ግኘት ፡ ተጨንቀው ፡ ሳለ - - በተአምር ፡ አርዶ ፡ እበላው ፡ ዐቃቢ ፡ ሆድ ፡
ውስጥ ፡ እንዳለ ፡ ኩኩሉ ፡ ብሏል ፡ ይባላል - - አውራ ፡ ዶሮው ፡ ታርዶ ፡
ተሰልቶ ፡ ሆድ ፡ ውስጥ ፡ የገባው ፡ አውራ ፡ ዶሮ - - እና ፡ ታዲያ ፡ ምድር ፡
ምንኛ ፡ በተሻሻለች ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ ምንኛ ፡ በተቀራረበ ፡ እንደ ፡ አቡየ ፡
ጻድቁ ፡ እውነትን ፡ ፈልፍለው ፡ የሚያወጡ ፡ ጻድቃን ፡ ቢፈጠሩ - - -

«አልተፈጠሩማ ፡ አልተፈጠሩም - - -

«ያልተፈጠሩ ፡ አይምሰልህ - - አደፍርስ ፡ ተፈጥረዋል - - ወደፊትም
ይፈጠራሉ ።—ዋናው ፡ ነገር ፡ ብቻ ፡ በእምነታችን ፡ ጸንቶ ፡ መገኘቱ ፡
ነው ።—ጻድቃን ፡ የትክክለኛ ፡ ኑሮ ፡ አርማዎቻችን ፡ ናቸው ፤ የእውነ
ተኝነት ፡ የርኅሩኅነት ፡ የመንፈሳዊ ፡ ኃይል ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ ትልቅነት ፡
- - የብዙው ፡ የብዙው ፡ ሰብእናችን - - -

« - - - የክርስቶስ ፡ ሠምራ ፡ አሁን ፡ ዋናው ፡ ልመናዋ ፡ ሰዎችን ፡
የሚያስተውን ፡ ሠይጣንን ፡ አስምራ ፡ ሁሉንም ፡ ሰው ፡ ለማጽደቅ ፡
ነበር ።—እና ፡ ታዲያ ፡ እግዜር - - ዲያብሎስ ፡ እሺ ፡ አይልሽም ፡ እንጂ ፡
እሺ ፡ ካለሽ ፡ ምንቸገረኝ ፡ ብሎ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ገብቶላት ፡ ከሲዖል ፡
አፋፍ ፡ ላይ ፡ ወጥታ ፡ ጠርታዋለች ፡ ዲያብዬ ፡ ዲያብዬ ፡ እያለች ፡ በማቆ
ላመጥ ።- እሱ ፡ ግን ፡ ያልለመደውን ፡ ፍቅራዊ ፡ አጠራሯን ፡ ሰምቶ ፡
በዓይኑ ፡ ለማየት ፡ ቀና ፡ ቢል ፡ መጥፎ ፡ ተግባሩ ፡ በሰውነቱ ፡ ሥራ ፡
ተገልጾ ፡ በቅንድቡ ፡ ስቦ ፡ ሲዖል ፡ ጨምሯታል ።— ይቅር ፡ ባዩ ፡ አም
ላክ ፡ ግን ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ ያይ ፡ ነበርና ፡ እባክህ ፡ ያቺ ፡ የዋህ ፡ ሴት ፡ ሲዖል ፡
ገብታለችና ፡ ሄደህ ፡ አውጣት ፡ ብሎ ፡ ሚካኤልን ፡ አዞላት ፡ ወዲያው ፡
ወጥታለች ።— ብዙም ፡ ነፍሳት ፡ እሷን ፡ ተከትለው ፡ ወጥተው ፡ ድነ
ዋል ።- አቡነ ፡ ዘርአ ፡ ቡሩክም ፡ ሱስንዮስን ፡ ለማውገዝ ፡ በሄዱ ፡ ጊዜ ፡
መጻሕፍታቸውንና ፡ ኩስኩስታቸውን ፡ በዐባይ ፡ ላይ ፡ አደራ ፡ ጥለው ፡

ቢሄዱ ፡ ምንም ፡ ሳይሆን ፡ ሲመለሱ ፡ አግኝተውታል ።— ከጽድቃቸ ውም ፡ ስፋት ፡ የተነሣ ፡ ሰማይና ፡ ምድርን ፡ ደግፈው ፡ የያዙትን ፡ የብ ሔሞትንና ፡ የሌዋታንን ፡ ጥርሶች ፡ ቆጥረው ፡ ወጥተዋል ። ቅድስት ፡ እማሙዝ ፡ የምትባለዋ ፡ ደግሞ - - ከቅድስናዋ ፡ ስፋት ፡ የተነሣ ፡ አምላ ክን ፡ ለምና ፡ ከሰንሰል ፡ የተሠራው ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያኗ ፡ እስከ ፡ ምጽ አት ፡ ድረስ ፡ እንዳይፈርስ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ገብቶላት ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ እንዳጋደለ ፡ ይኖራል - - -

« 'ሊኒንግ ፡ ታወር ፡ አፍ ፡ ፒዛ ! ' ም ፡ አለን ፡ በሉኝ ! » ጣልቃ ፡ ይገ ባል ፡ አደፍርስ ።

«ሊኒንቶርፒዛ ፡ አልወጣኝም - - ! » ይቀጥላሉ ፡ አባ

«እንግዲህ ፡ ሕዝቡ ፡ ተሰብስቧል - - የመጣንበትን ፡ ጉዳይ ፡ ብን ጀምር» ይናገራሉ ፡ አቶ ፡ ጥሶ ።—

« - - - የእማሙዝ ፡ ቤተክሲያን ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ እንዳጋደለ ፡ አለ ፡ ነው ፡ ያልኩህ - - እስከ - - ዛሬ - - » እያሉ ፡ ሕዝቡ ፡ መካከል ፡ ይገባሉ ፡ አባ ።—

# ፴፮

# አደፍርስ

ፍሬዋ ፡ እንደ ፡ ልማዷ ፡ አንድ ፡ እግሯን ፡ እውሃው ፡ ውስጥ ፡ ነክራ ፡ ሌላውን ፡ ከውሃው ፡ ውጪ ፡ አዛንታ ፡ በማሳረፍ ፡ እወንዙ ፡ ዳር ፡ ተቀምጣለች ።— የሚንሻሻ ፡ የሚቦልቅ ፡ የሚንዶቀዶቀው ፡ የውሃው ፡ ግርግርታ ፡ አፍዟታል ።- የፀሐይ ፡ ግለት ፡ ማቃጠሉንና ፡ ማዳከሙን ፡ ጀምሯል— አልፎ ፡ አልፎ ፡ በሚነፍሰው ፡ ቀዝቃዛ ፡ አየር ፡ ከመበረዙና ፡ ከመቀዝቀዙ ፡ በስተቀር ።— በቀዘቀዘ ፡ ቁጥር ፡ ከወራጁ ፡ ውሃ ፡ ጋር ፡ አብራ ፡ የፈሰሰች ፡ የመሰለችው ፡ ሕይወት ፡ ስትመለስ ፡ ይሰማል ።— በላይ ፡ እፍሬዋ ፡ አጠገብ ፡ ተቀምጧል ፡ ሁለን ተናው ፡ በአፍአዊ፡እንቅስቃሴ፡ ተውጦ ።—የሚወርደውን፡ውሃ፡ድምፅ ፡ አይሰማም ።— ያባን ፡ ዲስኩር ፡ አያዳምጥም ።— ሁለንተናው ፡ በጆቹ፡ ምሥጢር ፡ ተወስኖ ፤ ከዘልማድ ፡ ሥራቸው ፡ በላይ ፡ የተጠየቁ ፡ ተዝ ናንተው ፡ ያሉትን ፡ መሳይ ፡ አጣማጆቻቸውን ፡ የፍሬዋን ፡ እጆች ፡ ሠርዶ ፡ እንደ ፡ መንቀል ፡ እያሉ ፡ ነካ ፡ ለማድረግ ፡ የሚያደፊቡ ፡ የሚመ ስሉ ፡ ጣቶቹን ፡ እያንቀሳቀሰ ።— አባ ፡ ዲስኩራቸውን ፡ ያምበለብሉ ታል - - -

« - - - ዱር ፡ እየመነጠሩ ፡ አውሬ ፡ እያባረሩ ፡ የሚኖሩበት ፡ የድ ካም ፡ የፍርሃት ፡ ዘመን ፡ አለፈ ።— ከቆላ ፡ ወርዶ ፡ በረሽኛ ፡ ከደጋ ፡ ወጥቶ ፡ ደገኛ ፡ በመባል ፡ ብቻ ፡ የሰው ፡ ልክ ፡ የሚታወቅበት ፡ ዘመን ፡ አለፈ ።—ትምህርት ፡ በሚሉት ፡ መልክተኛ ፡ ተጭኖ ፡ አገራችን ፡ ገባ ፡ ሥልጣኔ ።— ‘መንፈስ ፡ ይትናገር ፡ በላዕሌከሙ’ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ በእናንተ ፡ ላይ ፡ አድሮ ፡ ይናገራል ፡ የተባለበት ፡ ዘመን ፡ መጣ - - - የረ ዘመውን ፡ የሚያሳጥር ፡ ያጠረውን ፡ የሚያስረዝም ፡ ምትሐት ፡ ትምህ ርት ፡ የሚሉት ፡ ነገር ፡ ተስፋፋ ፡ በሀገራችን - - ሻካራውን ፡ ለስላሳ ፡ ጉጣጉጡን ፡ መዘዞ ፡ ወልጋዳውን ፡ ሰተቶ ፡ ጠማማውን ፡ መለሎ ፡ የሚ ያደርገው ፡ ትምህርት ።— ልማትና ፡ ስፋት ፡ ውበትና ፡ ጽዳት ፡ ክብረ ትና ፡ ሀብት ፡ የያንዳንዱ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ዓላማና ፡ ግብ ፡ ሆኑ - - -

አህዮቹን ፡ አስቀድሞ ፡ ብቅ ፡ ይላል ፡ ደገኛው ፡ ነጋዴ ፡ ከወደ ፡ ቆላው ፡ እየዘፋፈነ

«ካራማራን ፡ ዞረሽ ፡ ጅግጅጋን ፡ ያየሽው ፡
እንደልብሽ ፡ ኩራት ፡ የታል ፡ ያገኘሽው - - » ከኋላው ፡ ከየህ ፡ መጣህ ፡ የማይባል ፡ የሚያጣድፍ ፡ አውሎ ፡ ነፋስ ፡ እየገገረ ፡ እየተጥ መለመለና ፡ በሰፊው ፡ ክብ ፡ እየሠራ ፡ ይመጣና ፡ የነጋዴውን ፡ ደበሎ ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ ከልብሶ ፡ የተሰበሰበውን ፡ ወንድና ፡ ሴቱን ፡ ሸማ ፡ አመ ሳቅሎ ፡ አጋልጦና ፡ አመናጭቆ ፡ ወንዙን ፡ እሻገራለሁ ፡ ሲል ፡ ፍሬ ዋን ፡ እበላይ ፡ ጭኖች ፡ ላይ ፡ ይደፋታል ።— በላይንም ፡ እፍሬዋ ፡ ራስ ፡ ላይ - - - እንደ ፡ ኀይለኛ ፡ የንብ ፡ ሠራዊት ፡ ሠፈሩን ፡ ሁሉ ፡ ያብረገር ግና ፡ ያልፋል ።— ሩምታው ፡ ጓጓታው ፡ ሸውሸውታው ፡ ሁሉ ፡ በቅጽ በት ፡ ይዋጣል ፡ ባካባቢው ።—

«አሥራሁለተኛን ፡ ክፍል ፡ እንዳለፍሁ - - - » ይላል ፡ በላይ ፡ ቀስ ፡ ይልና - - የተነከረውን ፡ እግሯን ፡ አምቦራጭቃ ፡ ራሷን ፡ ቀና ፡ ታደር ጋለች ፡ ፍሬዋ ፡ ከጭኑ ፡ ላይ - - ትክ ፡ ብላም ፡ ትመለከተዋለች « አሥራ ሁለተኛን ፡ ክፍል ፡ ስጨርስ - - - » ይላል ፡ በላይ ፡ ይደግምና ።—

ነፋስ ፡ ያስወረዛቸውን ፡ ዓይኖቿን ፡ እየጠራረገች « - - ኮሌጅ ፡ ትገባለህ - - ዲግሪ ፡ ታገኛለህ - - - » ትጨርስለታለች ፡ ፍሬዋ « ወይ ፡ ደግሞ ፡ እንደኔ ፡ የወደቅህ ፡ እንደሁ - - አሥራሁለተኛን - - » ትቀጥ ላለች ፡ ንግግሯን ።—

«አብረን ፡ ሥራ ፡ እንይዛለን - - -» ብሎ ፡ ይጨርሳል ፡ ያምጥ ፡ ያምጥና ፡ ጀምሮት ፡ የነበረውን ፡ ሐሳብ ።— ፀሐይዋ ፡ ትንተገተጋለች ፤ በብርማ ፡ ዓይነት ፡ ቀለም ፡ በአናቱ ፡ ላይ ፡ በሚያልፉት ፡ ዳመናዎች ፡ ላይ ፡ ብርማ ፡ ጨስ ፡ መልክን ፡ በመዘርጋት ።— ያየሩ ፡ ትኩስነት ፡ ዓይኖቹን ፡ በትንሹ ፡ ያረጥባቸዋል - - ሰውነቱን ፡ በዝግታ ፡ እየደሳሰሰ ፡ ወደ ፡ ሳምባው ፡ ሲፈስ ።—

« - - - አልፎ ፡ አልፎ ፡ ጉልበት ፡ እያወጣ ፡ ሥሩን ፡ እያዛመተና ፡ እያለመለመ ፡ መሬት ፡ ለመሬት ፡ ተስቦ ፡ሜዳውን ፡ እንደሚይዘው ፡ የሰኔ ፡ ሰርዶ ፡ በየጠቅላይ ፡ ግዛቱ ፡ በያውራጃው ፡ በየወረዳው ፡ በየቀበ ሌው ፡ ሥሩን ፡ ሰደደ ፡ ዘመናዊ ፡ ትምህርት ።— የመስፋፋቱ ፡ ዐዋጅ ፡ ከመሰማቱ ፡ ያፈራሩ ፡ ማማር ፡ ዜና ፡ እግር ፡ በእግር ፡ ተከተለ ።— ምን ፡ ልበ ፡ ሰፊነት ፡ ምን ፡ ተጋድሎ ፡ ምን ፡ መሥዋዕትነት ፡ ብናሳየው ፡ ምን ፡ ስጦታ ፡ ምን ፡ እጅ ፡ መንሻ ፡ ምን ፡ ገጸ ፡ በረከት ፡ ብናቀርብለት ፡ በዛ በት ፡ ሊባል ፡ ይቻላል - - - ? » ቀጥለዋል ፡ አባ ።—

የተሰበሰበው ፡ ሕዝብ ፡ በየተራ ፡ እየተነሣ ፡ የያቅሙን ፡ ገንዘብ ፡ ያዋጣል ።—

«ጣርማበር ፡ ላይ ፡ ሆኖ ፡ ይታያል ፡ ሞላሌ ፡
አንችው ፡ ነሽ ፡ ወዳጇ ፡ ቻይዋ ፡ እንዳመሌ» እያለ ፡ ነጋዴው ፡ የሚዘፍነውን ፡ ያስተጋባል ፡ ጋራው ፡ ጉራንጉሩ ።—

# ፴፯

# አደፍርስ

አቶ ፡ ወልዱ ፡ አደፍርስና ፡ አቶ ፡ ጥሶ ፡ ክርክራቸውን ፡ ቀጥለ ዋል ፡ ከስብሰባው ፡ መልስ —

«ንብና ፡ የወባ ፡ ትንኝ ፡ ሁለቱ ፡ የተለያዩ ፡ ነፍሳት ፡ አበባን ፡ ይቀሥማሉ ።— ንብ ፡ ከአበባ ፡ ባገኘችው ፡ ንጥር ፡ ማርን ፡ ትሠራለች ።— ለራሷ ፡ በቅታ ፡ ለሰው ፡ ትተርፋለች ።— የወባ ፡ ትንኝ ፡ ደግሞ ፡ ከዚያው ፡ ካበባ ፡ በተገኘው ፡ ንጥር ፡ መርዟን ፡ ትሠራለች ።— በመር ዟም ፡ የወባ ፡ በሽታን ፡ ታስተላልፋለች ።— እንግዲህ ፡ አንደኛው ፡ ለደግ ፡ ሌላው ፡ ለክፉ ፡ ስላዋሉት ፡ ያበባ ፡ ንጥር ፡ አያስፈልግም ፡ ለማለት ፡ አንችልም - -

«ባጭሩ ፡ ሥልጣኔ ፡ እንደ ፡ ተቀባዩ ፡ ነው ፡ ነው ፡ የሚሉት ፡ አቶ ፡ ወልዱ--» ያጠቃልላል ፡ አደፍርስ ፡ ያቶ ፡ ጥሶን ፡ ሐሳብ ፡ የሚቋቋምበት ፡ ነቁጥ ፡ ያገኘ ፡ ይመስለውና ።—

«ቢሆንም ፡ ቢሆንም - - -» ይለጥቃሉ ፡ አቶ ፡ ጥሶ « እኛ ፡ አገር ፡ የሚታየው ፡ ያሠለጣጠን ፡ ሁኔታ ፡ በይበልጥ ፡ የወባ ፡ ትንኞቹን ፡ መን ገድ ፡ የተከተለ ፡ ነው ፡ የሚመስለኝ - - - እንዴ ፡ የለም ፡ አይሆንም ! ያለንን ፡ ሳናውቅ ፡ የሌለንን ፡ ለማግኘት ፡ የምናደርገው ፡ ጥረት ፡ ሁሉ ፡ ከንቱ ፡ ነው - - - እየተማባባን ፡ እንጂ - - -አሁን ፡ ለምሳሌ ፡ ምዕራባዊ ፡ ሥልጣኔ ፡ ሀገራችን ፡ መግባት ፡ ከጀመረ ፡ ጊዜ ፡ አንሥቶ ፡ እስኪ ፡ ያፈ ራውን ፡ ፍሬ ፡ እንመልከት - - -

«በጣም ፡ ጥሩ ! በጣም ፡ ጥሩ ! እንመልከት - - -» ጣልቃ ፡ ይገባል ፡ አደፍርስ ።—

« እኛ ፡ አገር ፡ የገባው ፡ ምዕራባዊ ፡ ሥልጣኔ ፡ እንዴት ፡ ዓይነቱ ነው - - ? መጀመሪያ ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ማወቅ ፡ የሚኖርብን ፡ ይመስለኛል - - -

«ጥሩ ፡ ነው ፡ ዕንወቅ ፡ እንዴት ፡ ያለው ፡ ነው - - ?» አሁንም ፡ ጣልቃ ፡ ይገባል ፡ አደፍርስ ።—

«--እኛ ፡ አገር ፡ የገባው ፡ ምዕራባዊ ፡ ሥልጣኔ ፡ በቀጥታ ፡ ወይም ፡ በዝውርውር ፡ መንገድም ፡ ይሁን— ሀብት ፡ ወይም ፡ ማዕረግ ፡ የሚያስገኝ --- ድህነት ፡ አጨራምቶት ፡ የኖረን ፡ ሁሉ ፡ የመንግሥት ፡ ወይም ፡ የግል ፡ ድርጅት ፡ የቢሮ ፡ ሥራ ፡ የሚሉት ፡ ደረጃን ፡ የሚያሻሽል ፡ ነገር ፡ ስለተገኘ ፡ ፈተናን ፡ ሰጥቶና ፡ አሳልፎ ፡ እተባለው ፡ ቦታ ፡ የሚያደርስ --- ወደ ፡ ምዕራባውያን ፡ ማኅበራዊ ፡ ኑሮና ፡ ኅብረተ ፡ ሰብ ፡ የሚያስገቡ ፡ በሮችን ፡ የሚከፍት -- አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ በገቢር ፡ ላይ ፡ የማይውል ፡ የቀለም ፡ ትምህርትን ፡ እንዲያስተጋቡ ፡ እያደረገ ፡ በቅዠት ፡ ላይ ፡ የተመሠረተ ፡ ያኗኗርን ፡ ዘዴ ፡ የሚያሳይ -- ልዩ ፡ መቀመጫው ፡ እግዚአቤሔር ፡ ቢረዳንም ፡ እንደሁ ፡ ባይረዳን ፡ አላውቅ ፡ ልዩ ፡ መቀመጫው ፡ ከተማ ፡ የሆነ— ከመሃል ፡ ከተማው ፡ ውጪ ፡ አልፎ ፡ ወደ ፡ የገጠሩ ፡ ያልገባ -- ምዕራባዊ ፡ ሥልጣኔ ፡ በመባል ፡ ብቻ ፡ ተወዳጅ ፡ ወይም ፡ አስፈሪ ፡ የሆነ ፡ ነገር ፡ ነው ---

«ከማህል ፡ ከተማ ፡ አልፎ ፡ ወደ ፡ የገጠሩ ፡ አለመግባቱ ፡ እንኳ ፡ ያስደስታል ፡ እንጂ ፡ አያሳዝንም --- አገሬው ፡ ስንዴውን ፡ ከምርቁና ፡ ከገለባው ፡ ለይቶ ፡ ዳቦና ፡ ኅብስት ፡ እንደሚጋግር ፡ ሁሉ ፡ ከውጪ ፡ ከሚገባውም ፡ አዳዲስ ፡ ነገር ፡ ክፉና ፡ በጐ ፡ እንዳለው ፡ ተረድቶ ፡ የሚመርጥበት ፡ ትምህርት ፡ ገና ፡ ያስፈልገዋል -- ዘጠና ፡ በመቶ ፡ የሚሆነው ፡ በመድፈንፈን ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ገና ፡ ገና ፡ ዘመናዊ ፡ የሆነ ፡ የራስ ፡ ቁርና ፡ የደረት ፡ ጥሩር ፡ ያስፈልገዋል ---

«እውነትዎን ፡ ነው ፡ አቶ ፡ ወልዱ --- ጥንታዊቷን ፡ ኢትዮጵያን ፡ ከወራሪ ፡ ጠላት ፡ ያዳኗት ፡ ተራሮቿና ፡ ሸንተረሮቿ ፡ ሃይማኖቷና ፡ ቆራጥነቷ ፡ የነበሩትን ፡ ያህል ፡ ከዘመናዊዎቹ ፡ የሰብእና ፡ ወራሪዎች ፡ ሊያድኗት ፡ የሚታገሉት ፡ ደሞ ፡ በዱሮው ፡ መንፈስ ፡ የጠነከሩት ፡ አስተሳሰቧና ፡ ድንቁርናዋ ፡ ናቸው -- » ያምናሉ ፡ አቶ ፡ ጥሶ ፡፡—

«አሁንስ ፡ ረቀቃችሁብኝ—ጸጉር ፡ ስንጠቃ ፡ እንለዋለን ፡ በዘመናዊ ፡ አማርኛችን ፡ እንደዚህ ፡ ዓይነቱን -- » ይናገራል ፡ አደፍርስ ፡ « ለመሆኑ ፡ በእናንተ ፡ አስተያየት ፡ ኢትዮጵያን ፡ የሚጠብቃት ፡ ድንቁርናዋ ፡ ነው ፡ ማለት ፡ ነው --- ?

« የየዳንሱን ፡ ንቅናቄና ፡ ውዝዋዜ ፡ የየሙዚቃውን ፡ ንዝረትና ፡ ስግምግምታ ፡ የየሲኒማውን ፡ ቤት ፡ ብልጭልጭታና ፡ አይሠሩ ፡ ሥራ ፡ የየሥነ ፡ ጽሑፉን ፡ ውስጥ ፡ አጉል ፡ ሁኔታና ፡ ፕሮፓጋንዳ ፡ በእቅዱ ፡

መሠረት ፡ ገብቶን ፣ አንጥረን ፡ አንጠርጥረን ፡ ተረድተነው ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ ፣ ዛሬ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ሰውነታችን ፡ ጥንጣን ፡ እንደ ፡ በላው ፡ እንጨት ፡ ተበልቶ ፡ አልቆ ፡ ነበር - - ምዕራባውያን ፡ ሥልጣኔ ፡ የሚሸከምበት ፡ ጭንቅላት ፡ ትከሻና ፡ ደረት ፡ ባላገኘም ፡ ነበር - -» ይቀጥላሉ ፡ አቶ ፡ ወልዱ ።

« የኛ ፡ ሰውነት ፡ የሚተማመኑበትን ፡ ጥይት ፡ የሚያከሽፍ ፡ ነው ፡ የሆነው ፡ ለምዕራባውያን - - -» ያክላሉ ፡ አቶ ፡ ጥሶ ።

«ስለዚህ ፡ ብቻ ፡ ሁለታችሁም ፡ አጉሉ ፡ እንጂ ፡ ጥሩው ፡ መልኩ ፡ የታያችሁ ፡ አትመስሉም ፡ እንዳነጋገራችሁ - - -

« አጉል ፡ መልኩ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ የሚያንን ፡ የሚመስለውም ፡ በኩሉ ፡ ስለ ፡ ተገለጸልን ፡ ነው ፡ የምንነጋገረው - - እያዘንን ፡ እየተደ ሰትንም - - -

« - - እውነትዎንኮ ፡ ነው ፡ አሁን ፡ አቶ ፡ ጥሶ - - እንዴት ፡ ይመስ ልዎታል ፡ እኔ ፡ አሁን ፡ የማዝነው - - ምዕራባዊ ፡ ሥልጣኔ ፡ ሲባል ፡ ሊመኙትና ፡ ሊፈልጉት ፡ የሚገባ ፡ አድገት ፡ ነው - - ነገር ፡ ግን - - እን ዲህ ፡ እንደምናየው - - የፈረንጆችን ፡ እንቶ ፡ ፈንቶ ፡ ታሪክና ፡ ገናና ነት ፡ ለማስተባቃት ፡ እንጂ ፡ የራሳችን ፡ የምንላቸውን ፡ ጠቃሚ ፡ ነገ ሮች ፡ ለመረዳትና ፡ ለማወቅ ፡ ያላስቻለን ፡ ሆኖ ፡ ሳየው - - ዐወቅን ፡ ሠለጠንን ፡ የሚሉት ፡ ሰዎች ፡ በቅርቡ ፡ ከሚሠሩት ፡ ጥቅጥቅ ፡ ይልቅ ፡ በረጅሙ ፡ የሚወጥኑትን ፡ ሽክሽክ ፡ ስመለከተው - - መልካም ፡ ምግባ ርንና ፡ ጠባይን ፡ እያስረሳ ፡ መሄዱን ፡ ሳየው - - በተግባረ ፡ እድ ፡ በኪነ ፡ ጥበባት ፡ በጠቅላላው ፡ በሙያ ፡ ትምህርቶች ፡ ምንም ፡ ያህል ፡ ያላፈናፈነን ፡ መሆኑን ፡ ሳሰላስለው - - በጣም ፡ ነው ፡ የማዝነው ፡ አቶ ፡ ጥሶ ፡ በጣም - -

«የሚደስቱትስ—የሕዝቡ ፡ ጤና ፡ በመጠበቁ ፡ ትምህርት ፡ ቤቶች ፡ በመከፈታቸው ፡ ኢኰኖሚያችን ፡ ማደግ ፡ ስለጀመረ ፡ የሕዝቡም ፡ የኑሮ ፡ ደረጃ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ እያለ ፡ በመሄዱ ፡ ከፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ በላይ ፡ የሆነ ፡ ደንበኛ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ በመገኘቱ ፡ አስተዳደር ፡ በመሻ ሻሉ ፡ የምድር ፡ የአየር ፡ የባሕር ፡ ኀይሎቻችን ፡ በመደርጀታቸው - - ይሆን ፡ ይሆን ፡ ምናልባት - - - ?»ሐሳቡን ፡ ያቀርባል ፡ አደፍርስ ፡ የጐ ድን ፡ በሄደ ፡ ሁኔታ ።—

« አደፍርስ - - ! » ይላሉ ፡ አቶ ፡ ጥሶ ፡ « የሥልጣኔን ፡ አስፈላጊነ ትም ፡ ሆነ ፡ መሠልጠን ፡ ያስገኘውን ፡ ነገር ፡ ሳናውቅ ፡ የምንናገር ፡ አይምሰ

ልህ - - - መከላከያና ፡ መፈወሻ ፡ መድኀኒት ፡ ማግኘት ፡ የወሩን ፡ መን ገድ ፡ በአንድ ፡ ሁለት ፡ ሰዓት ፡ መድረስ ፡ ጠላትን ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ሳይ ተያዩ ፡ ድል ፡ መንሣት ፡ በሕግ ፡ ፊት ፡ እኩል ፡ የመሆንን ፡ ሥልጣን ፡ ማግኘት ፡ በበቅሎና ፡ በፈረስ ፡ ዘጥ ፡ ዘጥ ፡ ከማለት ፡ በመኪናና ፡ በአ ይሮፕላን ፡ መፍሰስ - - ሌሎችም - - ሌሎችም ፡ ብዙዎቹ ፡ ቀላል ፡ ነገሮች ፡ አይደሉም ።— ነገር ፡ ግን ፡ እኛ ፡ የምንለው ፡ ዘመናዊውን ፡ ሥልጣኔ ፡ ለመቀበል ፡ ኩብረት ፡ ምሰሶ ፡ የጠና ፡ ሰውነት ፡ እንዲኖረን ፡ ያሻል ፡ ነው ፤ እንዴ - - ! ምነው ፡ ለማኝ ፡ እንኳ ፡ አቅማዳውን ፡ ሳያዘጋጅ ፡ ልመና ፡ አይወጣም - - ስለዚህ ፡ ዘመናዊውን ፡ ሥልጣኔ ፡ ለመቀበል ፡ መጀመ ሪያ ፡ መቀበያ ፡ ሰብእናችንን ፡ እናጠንክር ፡ ነው ፡ የምንለው - - ባህላች ንን—ልማዳችንን ፡ ወጋችንን ፡ ቅርሳችንን ፡ እንመርምር - - መርምረን ፡ ያገኘነውን ፡ ይዘን ፡ ያላገኘነውን ፡ እንፈልግ—እለዚያ ፡ ነፍስ ፡ እንደ ፡ ተለየችው ፡ ሥጋ ፡ ሆነን ፡ ብንቀርብ ፡ በመዘውር ፡ የሚሄድ ፡ ሰብእና ፡ ነው ፡ የምናተርፈው ፡ ነው ፡ የምንለው - - -

« በመዘውር ፡ የሚሄድ ፡ ሰብእና ፡ አሉ - - ? ! ይገርምዎታል ፡ ስለ ዚህ ፡ ነገር— እፈረንሳይ ፡ አገር ፡ በነበርኩበትም ፡ ሆነ ፡ ባሁኑ ፡ ጊዜ ፡ ብዙ ፡ በመዘውር ፡ የሚሄዱ ፡ ሰዎች ፡ ዐውቃለሁ ።— አንዳንዶቹ ፡ ከሀገ ራቸው ፡ በልጅነታቸው ፡ ወጥተው ፡ በሰው ፡ አገር ፡ የኖሩ ፡ የሀገራቸው ንም ፡ ሆነ ፡ የሰውን ፡ ሀገር ፡ ሰብእና ፡ ያልሆኑ ፡ ግንጥል ፡ ነገሮች ፡ ናቸው ። አንዳንዶቹ ፡ ደግሞ ፡ በአንድ ፡ አሳዳጊ ፡ ሳይረጉ ፡ ይቆዩና ፡ የረጋ ፡ መንፈስ ፡ የሌላቸው ፡ የናት ፡ ያባት ፡ የዘመድን ፡ ፍቅር ፡ ያል ጠገቡ ፡ ቅዥቅዥ ፡ ያሉ ፡ ነገሮች ፡ ናቸው - - -

« ጨዋታዎን ፡ አላቋርጠዎና ፡ አንድ ፡ በጣም ፡ ሀብታም ፡ የሆኑ ፡ ወዳጄ ፡ ልጅ ፡ አለ ፡ አዲስ ፡ አበባ - - » ጣልቃ ፡ ይገባሉ ፡ አቶ ፡ ጥሶ « ታዲያ ፡ የመጀመሪያይቱ ፡ አሳዳጊው ፡ ብዙ ፡ ያገራችንን ፡ ቋንቋ ፡ የምትችል ፡ ሴት ፡ ነበረች ፡ አሉ—ከዚያ ፡ ደሞ ፡ ኢጣልያዊት ፡ አሳዳጊ ፡ ተለ ወጠችለት ፡ ይሉኛል—ከዚያ ፡ ደግሞ ፡ ፈረንሳዊት— ከዚያ ፡ ደግሞ ፡ እንግሊዛዊት - - በመጨረሻ ፡ ጀርመን ፡ አገር ፡ ላኩት ፡ ይሉኛል - - - አሁን ፡ ተምሮ ፡ ተምሮ ፡ ሲመለስ ፡ ጭንቅላቱ ፡ ትልቅ ፡ ማሰሮ ፡ አህሎ ፡ አንገቱ ፡ ሰልስሎ ፡ ከወደ ፡ ኋላው ፡ ደሞ ፡ ሾላካ ፡ ሆኖ - - ምን ፡ አለፋዎ ፡ ብቻ ፡ ሳይጠየቅ ፡ መናገር ፡ የጀመረ ፡ እንደሁ ፡ እጁን ፡ ማወዛወዝና ፡ አለ ፡ ምክንያት ፡ ምላሱን ፡ መጐልጐል ፡ ሆኖ ፡ ሥራው ፡ ተቀምጧል ፡

እልዎታለሁ - - - አሁን ፡ ቢቸግራቸው ፡ የጅ ፡ ሥራ ፡ ያስተምሩታል ፡ ይሉኛል ፡ ዘመዶቹ - - -

«ያንዳንድ ፡ ሰዎች ፡ ስሕተት ፡ መቼም ፡ ሁሉንም ፡ መርገሚያ ፡ ሊሆን ፡ አይገባውም - - ከሆነም ፡ ግን ፡ እንዴት ፡ ያሉ ፡ ይመስሉዎታል ፡ እርስዎ ፡ አቶ ፡ ወልዱ ፡ በእኛ ፡ ምዕራባውያን ፡ ሥልጣኔ ፡ ተቀበሉ ፡ በም ንባለው ፡ ወጣቶች ፡ ላይ ፡ የሚነገሩት ፡ አጉል ፡ ነገሮች - - -

« - - አንዳንዶቹን ፡ እጠቅስልሃለሁ - - ለማስታወስ ፡ ያህል - - - ለምሳሌ— ወላጆችን ፡ የመድፈር ፡ ሃይማኖትን ፡ የማፍረስ ፡ ሥልጣንን ፡ የመናቅ ፡ ሁናቴዎች ፡ ይታይባቸዋል ፡ ይሏችኋል - - ከቤተ ፡ ሰቦቻቸው ፡ ራቁ ፡ አጉል ፡ የገለልተኝነት ፡ መንፈስና ፡ ኑሮ ፡ ፈጠሩ ፡ ይሏችኋል - - ብዙ ፡ ጊዜ ፡ በማይቆዩ ፡ ከልዩ ፡ ልዩ ፡ ምዕራብና ፡ ምሥራቅ ፡ ሀገሮች ፡ በተ ጠራቀሙ ፡ መምህራን ፡ ስለሚመሩ ፡ ውጤታቸው ፡ የማያጓጓ ፡ ሆነ ፤ እንደ ፡ እስስት ፡ ይለዋወጣሉ ፤ ቋሚ ፡ ሐሳብ ፡ የላቸውም ፡ ጉደሎ ፡ ሰብእና ፡ ነው ፡ መደምደሚያቸው ፡ ይሏችኋል - - አንዳንድ ፡ መምህ ራን ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ የማገልገል ፡ ዕድልም ፡ ቢሰጣቸው ፡ የቀለም ፡ ትም ህርት ፡ እንጂ ፡ የሕይወት ፡ መርሕ ፡ የሚሆን ፡ አዲስ ፡ ትውልድ ፡ የሚ ፈጥር ፡ ትምህርት ፡ ስላልሰጧቸው ፡ የሚያስተማምኑ ፡ ዜጋዎች ፡ አልወ ጣቸውም ፡ ይሏችኋል - - የተማሩት ፡ ትምህርት ፡ በጠቅላላው ፡ የዱ ሮውን ፡ ትውልድ ፡ ጠቃሚ ፡ ነገሮች ፡ ከማይጠቅሙት ፡ የማይለይ ፡ በማይጠቅሙት ፡ የሚጠቅሙ ፡ ለመተካት ፡ ያልቻለ ፡ ነው ፡ ይሏች ኋል - - -

«እሺ ፡ እርስዎስ ፡ ምን ፡ ይሉናል - - ?

«አይ ፡ የኔ ፡ አይከፋም - - እኔ ፡ በመቻቻል ፡ ተፈጥሮ ፡ የማምን ፡ ሰው ፡ ነኝ - - -

«እኮ ፡ ምን ፡ ይሉናል - - ?

«እስከዚህ ፡ የእናንተ ፡ ሁኔታ ፡ አሳሳቢ ፡ አይመስለኝም ፡ እኔ ፡ ስመለከ ተው ።—ምዕራባዊ ፡ ሥልጣኔ ፡ ያላችሁ ፡ በሌላቸው ፡ ስትዋጡ ፡ እዱሮው ፡ ቦታችሁ ፡ ትመለሳላችሁ ።—ከትምህርት ፡ ቤት ፡ ያገኛችሁትም ፡ አንዳንድ ፡ እምነት ፡ ቢኖር ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ስትሠማሩ ፡ እንደማይጠቅማችሁ ፡ ስትረ ዱት ፡ ትተውታላችሁ ፡ ብዬ ፡ ነው ፡ የማስበው - - - የኛ ፡ የኛ ፡ እንኳን ፡ ጓደኞች ፡ ስንቶች ፡ ነበሩ ‘ነፃነት ፡ እኩልነት ፡ ወንድማማችነት’ እያሉ ፡

የሚፎክሩ ።— ሀብት ፡ ሹመት ፡ ትልቅነትን ፡ ሲያገኙ ፡ ደሞ ፡ መዝሙ ራቸውን ፡ ለውጠው ፡ ሰምተናቸዋል - - እና ፡ የእናንተ ፡ ሁኔታ ፡ እስ ከዚህ ፡ የሚያሰጋ ፡ አይመስለኝም - - እንዲያውም ፡ በትምህርት ፡ ቤታችሁ፡እንደ፡ፈለጋችሁ፡በመዝሙርም፡በጽሑፍም፡በሥዕልም ፡ በል ፍለፋም ፡ የፈለጋችሁትን ፡ እየተናገራችሁ ፡ ቢወጣላችሁ ፡ ነው ፡ የሚ ሻል ፡ የሚመስለኝ - - -

«ቅድም ፡ እንዳሉት ፡ ግን ፡ እናንተ ፡ በትምህርት ፡ ቤታችሁ ፡ ውስጥ ፡ የሚሰማችሁ ፡ ፍላት ፡ ለዘጠና ፡ በመቶው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ሙቀት ፡ ይሰጣል ፡ ተብሎ ፡ መውጣት ፡ የለበትም - - ቀስ ፡ በቀስ ፡ እስካጤነው ፡ ድረስ ፡ የሚበጀው ፡ ድንቁርናው ፡ ነው - - -

«'ወጣቱ ፡ ፈላስማ' እሚል ፡ ዩንቨርስቲ ፡ ቅጥር ፡ ግቢ ፡ እተነበበ ፡ ግጥም ፡ ውስጥ ፡ እንዳለው ፡ ዓይነት ፡ ነው ፡ ማለት ፡ ሐሳብዎ - - ? » ይጠ ይቃል ፡ አደፍርስ ።—

«'ወጣቱ ፡ ፈላስማ' የሚል ? ትዝም ፡ አይለኝ - - ብቻ ፡ ዩንቨርስቲ ፡ ውስጥ ፡ የሚነበቡት ፡ ግጥሞች ፡ ቅድም ፡ እንዳልኩህ ፡ ፍላት ፡ የሚሰማ ቸው ፡ ስለሆኑ ፡ እምብዛም ፡ ለኔ ፡ ለውጪው ፡ ጆሮ ፡ አይጥሙኝም - -

«ሳይሰሙት ! - - ይስሙት ፡ እንጂ - -

'ድሃን ፡ ድህነቱን ፡ ከምትነግረዉ ፡
ያንጀት ፡ በሽታውን ፡ ከምታሰማዉ ፡
ለምን ፡ በተማርከው ፡ አትደግፈውም ፡
ቅዝት ፡ ሆነህበት ፡ ከሚያጣ ፡ ሰላም - - -
ቂጣን ፡ መተናነቅ ፡ ዶዮ ፡ መዛቅን ፡
አሹቅን ፡ መከርተፍ ፡ ቆሎ ፡ መቃምን ፡
በሽታ ፡ ነው ፡ እያልክ ፡ በሽታ ፡ አትስጠው ፡
ስትነግረው ፡ ነውና ፡ ሆዱን ፡ የሚያመው - -»እያለ ፡ የተደረደረ፡ ነውኮ ! በፍላት ፡ የተጻፈ ፡ ይመስልዎታል ፡ ታዲያ - - ?

«ይኸ ፡ ምንም ፡ አይል ፤ ብቻ ፡ ቢሆንም ፡ ግጥማችሁ ፡ እግቢያ ችሁ ፡ ቢቀር ፡ የሚሻል ፡ ይመስለኛል - - -

«እሺ ! ከትምህርት ፡ ቤት ፡ ባገኙት ፡ አስተያየት ፡ የጠና ፡ እምነት ፡ የሚኖራቸው ፡ ኢትዮጵያውያንስ ፡ የተገኙ ፡ እንደሆነ ? አሻፈረኝ ፡ በዘ ጠና ፡ በሙቶው ፡ ውስጥ ፡ አልዋጥም ፡ የሚሉ ፡ የተነሡስ ፡ እንደሁ ? ምን ፡ ማገጃ ፡ የሚገኝለት ፡ ይመስልዎታል ፡ አቶ ፡ ወልዱ - - -

« - - ራሳቸውን ፡ እንዳይጎዱ ፡ ራሳቸውን ፡ ካላቀኑ ፡ ማቅኛ ፡ ዘዴዎች ፡ ይበጁላቸዋል ፡ አያስቸግርም - - -

« ጋሼ ፡ ጥሶ ፡ ባንተ ፡ አስተያየት ፡ አስተማሪዎች ፡ ለመንግሥቱም ፡ ሆነ ፡ ለሕዝቡ ፡ ያለባቸው ፡ ግዴታ ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ ይመስልሃል - - - ?

«አስተማሪዎች ፡ መንግሥት ፡ የቀጠራቸው ፡ ናቸው ። ራሳቸው ፡ በግል ፡ የሚያምኑበትን ፡ ሳይሆን ፡ መንግሥቱ ፡ የሚያምንበትን ፡ ማስ ተማር ፡ ነው ፡ ግዴታቸው ።— ሥልጣኔ ፡ መሻሻልም ፡ ቢሆን ፡ የነበረ ንም ፡ መጠበቂያ ፡ ስለሆነ ፡ አንዳች ፡ ለውጥ ፡ ሲያስፈልግ ፡ መምጣት ፡ ያለበት ፡ ከተማሩትም ፡ በኩል ፡ ቢሆን ፡ በርግጥ ፡ ተፈላጊነቱ ፡ ሲታወ ቅና ፡ መንግሥቱም ፡ ሲቀበለው ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በቀለም ፡ ትምህርት ፡ ወይም ፡ በፍልስፍና ፡ በመራቀቅ ፡ የማይኖር ፡ ዓለም ፡ ፈጥሮ ፡ ይጠ ቅመናል ፡ ከማለት ፡ አይደለም - - ኢትዮጵያም ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ የተከተ ለችው ፡ ይኸንኑ ፡ መንገድ ፡ ይመስለኛል - - -

« - - ማናቸውም ፡ ከንውንና ፡ ጥዩቅ ፡ ከታየ ፡ ከተገለጸ ፡ ከታወቀ ፡ በኋላ ፡ ነበር ፡ ከመባል ፡ አይቀርም ።— ስለዚህ ፡ ለሁሉም ፡ ነገር— ያለ ፈውን ፡ ከአልለው ፡ ከጊዜው ፡ ጥዩቅ ፡ ጋር ፡ አስተያይቶ ፡ ሙሉነቱንና ፡ ጎደሎነቱን ፡ ለማመዛዘን ፡ እንኳ ፡ ቢሆን—ነበርን ፡ ማወቁ ፡ የሚበጅ ፡ ይመስላል - - » እያሉ ፡ ብድግ ፡ ይላሉ ፡ አቶ ፡ ወልዱ ፡ ከመቀመጫቸው ።—

«- - ስማ ፡ አደፍርስ - - » ይለጥቃሉ ፡ አቶ ፡ ጥሶ ፡ እየተነሡ « በቴክ ኒክ ፡ በኢንዱስትሪ ፡ በጠቅላላው ፡ በሀገር ፡ ልማት ፡ በኩል ፡ ለመራ መድ ፡ ሥልጣኔ ፡ ያመጣውን ፡ ጥበብ—በማስተዋል ፡ በማመዛዘንና ፡ በማስላት ፡ ዓይነት ፡ መንገድ—ለመቀበል ፡ ዝግጁ ፡ ነን ።— ጐን ፡ ለጐን መተያየት ፡ ማከባበሩን ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ መቅረት ፡ ግን ፡ አነስተኛ ፡ ግምት ፡ ማስሰጠቱን ፡ አላጣነውም - - ነገር ፡ ግን ፡ ባነጋገራችን ፡ ባካሄዳችን ፡ ባለባበሳችን ፡ በአፍአዊው ፡ ድርጊታችን ፡ ሌላን ፡ በመምሰል ፡ ብቻ ፡ ተወስኖ ፡ እንዲቀር ፡ አንሻም ፡ እኩልነታችን ፤ የኒውክለር ፡ መሣ ሪያን ፡ በመሥራትና ፡ ወደ ፡ ጨረቃ ፡ የሚያስኬድ ፡ እርምጃን ፡ በማፋ ጠን ፡ እንኳ ፡ ቢሆን ።— እምብዛም ፡ ሊያጓጓን ፡ አይገባም ፡ እንዲህ ፡

ያለው ፡ ክንውን - - እንደ ፡ እጦትም ፡ ተቆጥሮ ፡ የበታችነት ፡ ስሜት ፡ ሊፈጥር ፡ አይገባውም ።— በኩልነት ፡ ደረጃ ፡ እኛ ፡ ያለንባቸውንም ፡ ወደ ፡ ማሳወቅ — ኢትዮጵያዊ ፡ ጥዩቆቻችን ፡ ከምዕራባውያን ፡ ጥዩቆች ፡ ይለዩ ፡ እንጂ ፡ ያነሱ ፡ ያለመሆናቸውን ፡ ወደማሳመን ፡ ደረጃ ፡ እንዲመ ራን ፡ መታገል ፡ ይኖርብናል — ሥልጣኔ ።— የኛ ፡ የኢትዮጵያውያን ፡ ጉጉት ፡ የላቀ ፡ የመጠቀ ፡ መሆን ፡ ይገባዋል— ውስጣዊውን ፡ ሰብእና ፡ ወልውሎ ፡ በሚያሳይ ፡ በመንፈሳዊ ፡ ጥበብ ፡ በልጽጎና ፡ በመንፈሳዊ ፡ ኀይል ፡ ጐልብቶ ፡ ለመገኘት ፡ መጣጣር ።—በውነት ፡ እልሃለሁ ፡ አደ ፍርስ ፡ አጣንም ፡ ቆረቆዝን ፡ የበታችም ፡ ሆንን ፡ ብለን ፡ ማዘን ፡ የሚገባን ፡ ይህ ፡ በውስጣችን ፡ ሲምቦለቦል ፡ የኖረው ፡ መንፈሳዊ ፡ የሰብአት ፡ ሕይወት ፡ ፈሳሽ ፡ ያለመኖር ፡ መሰናክል ፡ ይገጥመውና ፡ የደረቀ ፡ የተመጠጠለት ፡ ነው - -

## ፴፫

# አደፍርስ

ወይዘሮ ፡ አሰጋሽ ፡ ሮቢት ፡ ከወረዱበት ፡ ቀን ፡ ጀምረው ፡ ደጋግ መው ፡ ተጠምቀዋል ፡ በፍል ፡ ውሃው ።—የሚጨመዳድዷቸው ፡ ሥራ ፡ ሥሮች ፡ በመጠኑ ፡ ተፍታተዋል ።— ቁርጥማታቸውም ፡ ጨርሶ ፡ ባይ ተዋቸውም ፡ እንኳ ፡ ፋታ ፡ ሰጥቷቸዋል ። ሰንበት ፡ ብለው ፡ ደጋግመው ፡ ቢጠመቁ ፡ እየተሻላቸው ፡ እንደሚሄድ ፡ ተማምነውበታል ።— የፀሐዩ ፡ ግለት ፡ ያካባቢው ፡ ውበቃ ፡ ያየሩ ፡ ርበቃና ፡ ክብደት ፡ ቢሆን ፡ ግን ፡ የሚያስነብታቸው ፡ አይመስልም ።— በነጋ ፡ በጠባ ፡ ቁጥር — ዛሬስ ፡ ብረሪ ፡ ብረሪ ፡ ነው ፡ ያለኝ ፡ እንዳሉት ፡ አሉ ። ከጠበል ፡ መልስ ፡ ስለነበረ ፡ ጊዜው ፡ ትራስ ፡ መሳይ ፡ ተደግፈው ፡ እመደብ ፡ ላይ ፡ ጋደም ፡ ብለዋል - - ሁለት ፡ እግሮቻቸውን ፡ እቆሬ ፡ ውስጥ ፡ ነክረው ።—ሮማን ፡ ቀስ ፡ እያ ለች ፡ አሸት ፡ አሸት ፡ ታደርግላቸዋለች ፡ ቆጣቆጣ ፡ ብለው ፡ የሚታዩ ትን ፡ ሥራሥሮቻቸውን — ቀዝቀዝ ፡ ያለ ፡ በመሰላት ፡ ቁጥር ፡ ከጠበሉ ፡ ዕቃ ፡ ወደ ፡ ቆሬው ፡ እያፈለቀች ፡ ፍል ፡ ውሃውን ።—እምድጃው ፡ ላይ ፡ የባርማሽላ ፡ እሸት ፡ ይፍለቀለቃል ፡ በማሰሮ — ቲስ ፡ ቲስ ፡ በማድረግ ፡ እሳቱን ፡ እያነቆረ ።—

« ምንድነው ፡ ይኸ ፡ እሸታችሁ ፡ አሁንም ፡ አልበሰለም ? » ይጠ ይቃሉ ፡ ወይዘሮ ፡ አሰጋሽ ።

« ትንሽ ፡ ቀርቶታል » ትመልሳለች ፡ አገልጋያቸው—አንድ ፡ ራስ ፡ ታወጣና ፡ ሁለት ፡ ሦስት ፡ ፍሬዎች ፡ ፈንቀል ፡ ፈንቀል ፡ አድርጋ ፡ በመ ቅመስ ።—

« ባይሆን ፡ ያመኑ ፡ ያመነውን ፡ አውጪው ፡ እሥር ፡ እሥሩ ፡ ያለው ፡ ሳይገባው ፡ አይቀርም - - - -

# ፴፱

## አደፍርስ

ጐርፉና ፡ ጺወኔ ፡ ወደ ፡ ጅረት ፡ ወርደዋል ።— ባካባቢው ፡ የሚ ገኘውን ፡ የሸንኮር ፡ አገዳ ፡ የሙዝ ፡ የትርንጐ ፡ የብርቱካን ፡ የሎሚ ፡ የትምባሆ ፡ ተክል ፡ እየዟዟሩ ፡ ይመለከታሉ ።

የሮቢ ፡ ፀሐይ ፡ ያለወትሮው ፡ ያንገበግባል ፡ እራስን ፡ ፈጥርቆ ፡ እየ ገባ ። — በየመዓዘኑ ፡ ሲንተገተግ ፡ ርግብግብግብግብግብ ፡ ሲል ፡ ሲያ ውት ፡ አየሩ ፡ ላይ ፡ ረግቶ ፡ ሲያበቃ ፡ እየተቆረሰ ፡ በመውረድ ፡ ላይ ፡ ያለ ፡ ነው ፡ የሚመስለው —እየተግረገረገ ። ዙሪያ ፡ መሬቱም ፡ እንዲሁ ፡ በረሞጫ ፡ በሱፋጭና ፡ በባልጩት ፡ ይርገበገባል።—እግርን ፡ በመሞልቀቅ ፡ እየሰነጠረ ፡ ገብቶ ፡ ርግብግቢት ፡ ድረስ ፡ ሲያጠኸይ ፡ ነው ፡ የሚሰ ማው ።— በረገጡት ፡ ቁጥር ።

ጐርፉና ፡ ጺወኔን ፡ ቢሆን ፡ እምብዛም ፡ የተሰማቸው ፡ አይመስ ልም ።— ጐርፉ ፡ ትናንሽ ፡ ድንጋዮች ፡ በማንሣት ፡ እየወረወረ ፡ ይዝና ናል ። ጺወኔ ፡ አንዲት ፡ ሎሚ ፡ ከነቀምበጧ ፡ ለመቅጠፍ ፡ ትተናነቃ ለች ፤ እማትቆረጥበት ፡ ላይ ፡ ጠምዝዛ ፡ አልሰበር ፡ ብላት ።— ጐርፉ ፡ ውርወራውን ፡ አቁሞ ፡ ራመድ ፡ ራመድ ፡ ብሎ ፡ ይጠጋትና ፡ እሷ ፡ ለመ ቅጠፍ ፡ ከምትተናነቀው ፡ የተሻለውን ፡ ሎሚ ፡ ቀጥፎ ፡ ይሰጣታል ።— ምንም ፡ ያህል ፡ አይነጋገሩም ።— ቀስ ፡ እያሉ ፡ ወደ ፡ ፍል ፡ ውሃው ፡ ቦታ ፡ ያመራሉ ።

« ያስከፋሁሽ ፡ ነገር ፡ እንዳለኮ ፡ ብትነግሪኝ - - አጥፍቼ ፡ ይሆናል - - ከሰው ፡ መች ፡ ጥፋት ፡ ይጠፋል ፡ አልሽው ? » ሲፈራ ፡ ሲቸር ፡ መናገር ፡ ይጀምራል ፡ ጐርፉ —

ድንገት ፡ ፊቷ ፡ ቦግ ፡ ይልና « ማስከፋት ? ! ማንን ፡ ማነው ፡ የሚ ያስከፋው - - ? » ትጠይቀዋለች ፡ ጺወኔ ።—

« ኋላ ፡ ምን ፡ ይሏል ? ይኸው ፡ ሮቢ ፡ ከመጣን ፡ ጀምሮ ፡ እንደ ማንተዋወቅ ፡ ዓይነት ፡ ነው ፡ የሆነው - - ዝም ፡ ትይኛለሽ ! ለወትሮው፡ ዝምታ ፡ አትወጂ - - እኔ ፡ ነበርሁ ፡ ባይሆን ፡ ዱዳው - - -

« ያንተ ፡ ነገር ! » እጇን ፡ ያዘ ፡ ታደርገዋለች ፡ እንደ ፡ ዘበት ።

« ምናልባት ፡ ያደፍርስ ፡ አለመምጣት ፡ ቅር ፡ አሰኝቶሽ ፡ እንደሁ - - መቼስ ፡ ሚካኤል ፡ ምስክሬ ፡ ነው ፤ እኔ ፡ ቀርቼ ፡ እሱ ፡ ቢመጣ ፡ ፈቃዴ ፡ ነበር - - -

ቶሎ ፡ እጇን ፡ ለቀቅ ፡ ታደርግና « ጨዋታ ፡ ያውቃል ፡ አደፍ ርስ - - ምን ፡ ቢጫወት ፡ ጨዋታ ፡ አያልቅበትም ! » ትናገራለች ፡ አርቃ ፡ እየተመለከተች —

« አዎ ፡ ጥሩ ፡ ልጅ ፡ ነው » ይመልሳል ፡ ጐርፉ ። —

« ሁኔታው ፡ ሁሉ ፡ ደሞ ፡ እንደ ፡ ከተማ ፡ ሰው ፡ አይምሰልህ - - ይገርምሃል - - - » ትቀጥላለች ።

« የከተማ ፡ ሰው ፡ ሁናቴ ፡ ምናባቴ ፡ ዐውቄ ፡ እኔ ! »

« አዎ ፡ እንደናቴ ፡ ልጅ ፡ አምኜው ፡ የትም ፡ ልሄድ ፡ እችላለሁ፡ ከሱ ፡ ጋር - - -

« አይ ፡ ቁም ፡ ነገር ፡ የሚያጣ ፡ አይመስልም - - -

« ይገርምሃልኮ ፡ አሁን ፡ አንተ ፡ አለህ ፡ አይደለም - - አብሮ ፡ አደጌ ፡ በጣም ፡ ዐውቅህ ፡ ይመስለኛል ፡ መቼም - - -

« እንዴታ ፡ ምን ፡ ጥርጥር ፡ አለው ፤ ታውቂኛለሽ ፡ እንጂ ፡ በጣም - -

« አዎ ፡ የማውቅህን ፡ አንተን ፡ እንኳን ፡ የሱን ፡ ያህል ፡ አላምን ህም - - -

« ምን ፡ ታረጊው ! ጊዜው ፡ አላስተማመነም - - በዛሬው ፡ ጊዜ ፡ ከጐን ፡ ነው ፡ ጠላት ፡ የሚወጣው - - -

« እሱን ፡ ማለቴ ፡ ሳይሆን ፡ አሁን ፡ ለምሳሌ ፡ አንድ ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ብቻየን - - - ማለቴ - - ሌላ ፡ ሰው ፡ ሳይኖር - - ካንተ ፡ ጋር ፡ ብቻ - - አንድ ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ አላድርም - - -

« እኔም ፡ አላድር ፡ ካልሽስ - - - !

« አንተ ፡ ደሞ ፡ ለምን ፡ አታድርም - - ? እኔስ ፡ ሴት ፡ ስለሆ ንሁ ፡ አልደር ፡ አቅም ፡ ስለሌለኝ - - -

« እኔም ፡ ደሞ ፡ ወንድ ፡ ስለሆንሁ - - -

« ውሽታም ፡ ነህ - - አሁን ፡ እውነት - - -

« አላድርም ፡ አልኩሽ - - -

« እኔ ፡ ግን ፡ ካደፍርስ ፡ ጋር - - እምልህ - - -

« ብታድሪ ፡ ግዴለሽም - - -

« ባድር ፡ ግዴለኝም - - -

« አይ ፡ ለጥሩነቱ ፡ ጥሩ ፡ ልጅ ፡ ነው - - -

ለትንሽ ፡ ጊዜ ፡ ምንም ፡ ያህል ፡ አይነጋገሩም ። የየራሳቸውን ፡ ሐሳብ ፡ የሚያውጠነጥኑ ፡ ይመስላሉ ።— ከፊለፊታቸው ፡ ወደ ፡ ደሴ ፡ እሚወስደው ፡ ድልድይ ፡ ሥር - - ደስታ ፡ በተሞላበት ፡ ሁኔታ ፡ ይም በጫረቃሉ ፡ ያዳል ፡ ልጃገረዶች ፤ እውሃው ፡ ውስጥ ፡ ራቁታቸውን ፡ ቁጭ ፡ ቁጭ ፡ ብለው - - ካለፍ ፡ አገደም ፡ ውሃውን ፡ በጃቸው ፡ እየዘገኑ ፡ ራሳቸው ፡ ላይ ፡ ፈሰስ ፡ ፈሰስ ፡ በማድረግ ።—እንዲያ ፡ ርቀው ፡ ቅባት ፡ እንደ ፡ ጠገበ ፡ ቅቤ ፡ ቅል ፡ ሲያበራና ፡ ሲያብለጨልጭ ፡ ይታያል ፡ ሰው ነታቸው - - ከውሃው ፡ ጥብርብር ፡ ጋር ፡ ፉክክር ፡ የያዘ ፡ ይመስል ።—

ጐርፉ ፡ ጂወኔን ፡ ድንገት ፡ ቀረብ ፡ ይላትና « ጂወኔ ! » ይላ ታል ።— በጣም ፡ ያስጨነቀውን ፡ የስሜት ፡ እንፋሎት ፡ ለመተንፈስ ፡ የቸኮለ ፡ ይመስል ።— ጂወኔ ፡ መለስ ፡ ትል ፡ ታየውና ፡ ትቀጥላለች ርምጃዋን « አቅሜ ፡ በሚፈቅድልኝ ፡ ዓይነት ፡ እጠብቅሻለሁ - - - አቅሜ ፡ በሚፈቅድልኝ - - ! አቅሜ - - » ይቀጥላል ።—

« ምነው ፡ እስከዚህ ፡ የተጠራጠርኩህ ፡ መሰለህ ? ያደፍርስን ፡ ያህል ፡ አላምንህም ፡ ስላልኩህ ! » ትላለች ፡ ጂወኔ ፡ ቆም ፡ ብላ ፡ መለስ ፡ በማለት ።— በመቀጠልም ፡ እየሄደች « - - የለም ፡ ውሸቴን ፡ ነው ፤ አብሮ ፡ አደጌ ፡ የትምህርት ፡ ቤት ፡ ጓደኛዬ ፡ ካንተ ፡ የበለጠ ፡ የማም ነው ፡ ማን ፡ ሊኖር ፡ ብለህ - - -

« እንጋባ ፡ አንችና ፡ እኔ ! » በግና ፡ ቅዝቅዝ ፡ ባለ ፡ አንደበት ፡ ይና ገራል ፡ አደፍርስ—እንደ ፡ ድንገተኛ ፡ የመብረቅ ፡ ተግታ ።— ጂወኔ ፡ ዓይኗ ፡ ይጐርጥና ፡ ዘወር —መልከት—መለስ ፡ ብላ ፡ ከቀድሞው ፡ በፈ ጠነ ፡ ርምጃ ፡ ትመነጠቃለች ።—

« - - አዳል ፡ ሲባሉ ፡ ያው ፡ አዳል ፡ ናቸው ፤ ተመልሰው ፡ ቅቢያቸውን ፡ ሊነከሩ ፡ ይኸ ፡ ሁሉ ፡ ብቅ ፡ ጥልቅ ።— ደሞኮ ፡ አሽት ፡ አሽት ፡ አያ ደርጉትም—ምን ፡ አደከማቸው ፡ ግን - - እውነት ፡ ነው ፤ ጠረናቸው ፡ እንደሁ ፡ አይለወጥ - - - ደሞ ፡ ያ ፡ ጸጉራቸው ! እንኳን ፡ ውሃ ፡ ጥይት ፡

የማይበሳው --ዶቃቸውንስ፡መቼ፡ያወልቁታል ።—ወምበርቲያቸውንም፡ እንደ ፡ ታጠቁ ፡ ይሆናል ፡ ይኸነዜ - - የቅጭልጭላቸውስ ፡ ብዛት - - ምናባቱንስና - - አንድ ፡ ሦስት ፡ ወር ፡ እረግጣለሁ ፡ እዚህ ፡ መጥቼ - - ወታደርነትም ፡ ኑሮ ፡ ነው ፤ አምስት ፡ አለቃ ፡ አሥር ፡ አለቃ - - ሹመ ትም ፡ አላጣም - - - አናት ፡ በስቶ ፡ ነው ፡ የሚገባው ፡ ደሞ ፡ የዛሬ ፡ ፀሐይ - - - አረሞሜውስ ፡ እንዴት ፡ ያቃጥላል ።—ይኸኔ ፡ እዚያ ፡ ማዶ ፡ እንዲያ ፡ ጥቁር ፡ ድንጊያ ፡ የመሰለችው ፡ ራቁቷን ፡ የተኛች ፡ አዳል ፡ ነች - - » ብሶቱ ፡ ያናውዝ ፡ ያተራምስዋል ፡ ጕርፋን ፡ ያለ ፡ ወትሮው ።—

## ፱

# አደፍርስ

እፍል ፡ ውሃው ፡ ሲደርሱ ፡ አንድ ፡ ወንድና ፡ አንድ ፡ ሴት ፡ ሲጠ
መቁ ፡ ያገኛሉ ።— አንድ ፡ ደግሞ ፡ ሌላ ፡ ሽማግሌ ፡ ሰውዬ ፡ ራቅ ፡
ብለው ፡ ልብሳቸውን ፡ ጭፍ ፡ ጭፍ ፡ ያደርጋሉ ።

« የማዬን ፡ ልብስ ፡ አጥብልሻለሁ ፡ ስትል ፡ የሰማሁ ፡ መስሎኝ ፡
ነበር - - ! » ትላለች ፡ ጺወኔ ፡ እንደ ፡ ዘበት « እኔም ፡ ልብሴ ፡ ውሃ ፡
ውሃ ፡ ቢሸተኝ ፡ አልጠላ - - - » መለስ ፡ ትልና ፡ ወዳረፉበት ፡ ጐጆ ፡
እሚወስደው ፡ መንገድ ፡ ትገባለች ።— ጐርፉ ፡ ፍራት ፡ ፍራት ፡ ባለው ፡
እርምጃ ፡ ቀስ ፡ እያለ ፡ ኋላ ፡ ኋላዋ ፡ ይከተላታል ።

« - - - እግሬ ፡ ምን ፡ መስሏል ? ያዳል ፡ ጫማዬ ፡ ደሞ ፡ መንጋደዱ - -
እጇስ ፡ ቢሆን ፡ ምን ፡ እጅነት ፡ አለው ፡ ሞያሌ ፡ ያዶለዶመው ፡ ይመ
ስል - - - ስቃብኛለች ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ያንለት ፤ አፌን ፡ ከፍቼ ፡ ተረት ፡
ሳወራ ፡ ለዚያ ፡ ለከተማ ፡ ጮሌ - - እንደ ፡ ንክር ፡ ባላገር ፡ ገምታኛለች ፡
ማለት ፡ ነው - - ልብ ፡ እንደ ፡ ሌለው - - አሞቱ ፡ እንደ ፡ ፈሰሰ - - እንደ
ዝምባም ፡ ባላገር - - እንደ ፡ ሞያሊያም - - እንደ ፡ ፈለጋም - - እንደ ፡ ፎከ
ታም ፡ ባላገር - - ለሷ ፡ ጐርፉ ፡ የተጣመመ ፡ ያዳል ፡ ጫማ ፡ ያደረገ ፡
ነው - - ቁች ፡ ብሎ ፡ እንዳሮጊት ፡ ቤት ፡ ተረት ፡ የሚያወራ - - በጠመ
ንጃው - - በሞፈሩ - - ባዳል ፡ ዘመቻው ፡ አልዋለበትም ፡ በሷ ፡ ቤት -
- - ዋይ ፡ ነዶ - - ብቻ ፡ ቀረ ፡ ነገር - - አንግቻት ፡ ነበር ፡ ዛሬ ፡ አገሬ ፡
የምገባው — ደርሶ ፡ የማላቅበትን ፡ ልዝብ ፡ ንግግር - - የከተማ ፡ ሰው ፡
ይደልላት ፡ በልዝብ ፡ ንግግሩ - - እኔ ፡ ብሆን ፡ በጐልዳፋው ፡ ሥራዬ ፡
አሳያታለሁ - - - » ይታገላል ፡ ጐርፉ ፡ ከኀሊናው ፡ ጋር ።

ጺወኔ ፡ ዝም ፡ ብላ ፡ ትገሠግሣለች ። ድካሟ ፡ ገና ፡ አልታወቃትም -
የረሞጫውና ፡ የባልጩቱ ፡ እንትግትግ ፡ ባናቷ ፡ ከሚገባው ፡ የጠራራ ፡
ፀሐይ ፡ ግለት ፡ ጋር ፡ እየተፋጨ ፡ ዓይኖቿን ፡ ማስዋኘት ፡ ጀምሯቸዋል ፡
ግን ፤ ቀኟም ፡ ግራዋም ፡ ፊቷም ፡ ኋላዋም ፡ በውሃ ፡ የተጥለቀለቀ ፡
ሆኗል - - የምትራመድም - - የምትሮጥም - - የምትከንፍም - - የም
ትዋኝም —የተኛችም ፡ ይመስላታል ።— እቤት ፡ ትደርሳለች ።—ቁጭ ፡

ትላለች ። ትድረስ ፡ አትድረስ ፡ ቁጭ ፡ ትበል ፡ አትበል ፡ ግን ፡ አልታ ወቃትም ። ባናቷ ፡ ላይ ፡ ውሃ ፡ ያፈሱባትና ፡ ትንሽ ፡ ያርገፈግፏታል ።—

ጐርፋ ፡ ፈቅ ፡ ብሎ ፡ ተቀምጦ ፡ ሁኔታዋን ፡ ይመለከት ፡ ነበርና ፡ ጺወኔ ፡ ራሷን ፡ ስትገዛና ፡ ዓይኖቿ ፡ በደንብ ፡ ሲገለጡ ፡ መጀመሪያ ፡ የምታየው ፡ እሱኑ ፡ ነው ፡ ዓይን ፡ ለዓይን ፡ ግጥም ፡ ይላሉ ።— ፊቷ ፡ ቅጭም ፡ ይላል ።— ዓይኖቿንም ፡ ጨፈን ፡ ጨፈን ፡ እንደ ፡ ማድረግ ፡ ብላ ፡ ትከድናቸዋለች ።— በሽክና ፡ ውሃ ፡ ቀድቶ ፡ ይዩዝና ፡ ጠጋ ፡ ይላታል « አንዳንድ ፡ ጐደሎ ፡ ቀን - - ምን ፡ አሰኝንና ፡ ወጣን ፡ ይባል ፡ እንደ ፡ ዘበት - - የቀን ፡ ጐደሎ ፡ ማለት ፡ እንደ ፡ ዛሬው ፡ ያለው ፡ ነው - - » ይጀምራል ፡ ቀስ ፡ ይልና « እኔስ ፡ ብሆን ፡ ከየት ፡ አመጣ ሁት ፡ ይባል ፡ ምላሱን - - - ምናባቴ ፡ ያናግር ፡ እንደ ፡ ነዛብኝ ፡ አላው ቅም ፡ ደሞኮ - - ! ይገርማልኮ ፡ እባካችሁ ? ! ከወዴት ፡ አመጣሁት ፡ ልበል ፡ እንግዲህ - - -

« እባክህን ፡ ተወኝ ፡ ይበቃሃል - - - » ትላለች ፡ ጺወኔ ፡ ቀስ ፡ ብላ ።

« አልጠጣሁ - - አልሰከርሁ - - ከየቴ ፡ አመጣሁት ፡ ይባላል - - - ? »

« ምነው ፡ ብትተወው - - - !

« እጡብእጡብ ፡ የሚያሰኝ ፡ ነገር ፡ ነው - - ራስን ፡ የሚያጠራ ጥር - - » ይቀጥላል ፡ ጐርፋ ።— ጺወኔ ፡ እግሯ ፡ ሥር ፡ ወድቆ ፡ የነበ ረውን ፡ የሎሚ ፡ ቀምበጥ ፡ ታነሣና ፡ ብድግ ፡ ብላ ፡ ወደ ፡ ውጪ ፡ ትወ ጣለች ።— ጐርፋ ፡ ይከተላታል ።— ቀስ ፡ ብሎ ፡ ለራሱ ፡ የሚናገር ፡ ዓይ ነት « እውነት ፡ ይመስል ፡ እስቲ - - - » በሰሚ ፡ ፍለጋ ፡ ጉልህነት ፡ « እውነት ፡ በሆነ ፡ ደሞኮ ! » እያለ ።— አጐጀዋ ፡ ዙሪያ ፡ የምትገ ኘውን ፡ ያጋም ፡ ሽምጥ ፡ ወጥተው ፡ ይሄዳሉ ።—

# ፵፩

## እደፍርስ

« - - ደሞኮ ፡ እውነት ፡ በሆነ - - እውነት ፡ በሆነ ! » ይደጋግማል የተናገረውን ፡ ኋላ ፡ ኋላዋ ፡ እየተከለ ፡ ጐርፉ ።—

« ካፍ ፡ ከወጣ ፡ አፋፍ ፡ እውነት ፡ ሆነ ፡ አልሆነ - - -

« እርሺው ፡ አልኩሽ - - ለሚካኤል ፡ ብለሽ - - እርሽው - - - !

« እውነት ፡ በሆነ ፡ ብሎ ፡ አነጋገር ! ምነው ፡ አሁን ፡ ይልቅ ፡ ብት ተወኝ - - -

« እኔ ፡ ሳላውቅ ፡ ልቤ ፡ ተመኝቶ ፡ ይሆናል - - ሚካኤል ፡ ምስ ክሬ ፡ ነው - - ግን ፡ እውነት ፡ አይደለም - - -

በመገረም ፡ ዓይነት ፡ ራሷን ፡ ቀና ፡ ታደርግና « ውሸትነቱ ፡ እን ዴት ፡ ነው ? » ብላ ፡ ትጠይቀዋለች - - በዚያ ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ባንዘረዘ ረው ፡ የውስጡን ፡ በሚፈለፍል ፡ አስተያየቷ ፡ ታጠምድና ።—

« አዎ ፡ እውነቴን ፡ ነው ፡ እርሽው - - - ! አትቆጪ - - የማ ይሳሳት ፡ የለም - - - ራሴን ፡ ዘንጋ ፡ አድርጌ ፡ ነው - - በፀሐዩ ፡ ግለት ፡ ምክንያት ፡ ነፍሴን ፡ ረስቼ - - -

« በፀሐዩ ፡ ግለት ፡ ምክንያት ፡ ነፍስህን ፡ ረስተህ ! » ድንገት ፡ ቀለሟ ፡ ልውጥ ፡ ዓይኖቿ ፡ ድብዝዝ ፡ ይላሉ ።—

« አልተቆጣሽም ፡ ታዲያ ፡ እንግዲያው ? ! ረስተሽዋል ፡ ማለት ፡ ነው ? ረስተሽዋል ! አልረሳሽውም ? » ይደጋግማል ፡ ጥያቄዎቹን ፡ ጐርፉ ፡ ቀና ፡ ጐንበስ ፡ እያለ ፡ የጐድን ፡ እየተመለከታት ።—

« አሁንስ ፡ አበዛሽው ! ምንድነው የምትለው ? ምን ፡ ትፈልጋለህ ፡ ከኔ ? » ቁጣነቱ ፡ በሚታወቅ ፡ የዝግታ ፡ ድምፅ ፡ ትጠይቀዋለች ።— « - - የምትለው ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ጨርሶ ፡ አይገባኝም - - ምኑን ፡ ነው ፡ የም ረሳው ? ርሺው ፡ ብሎ ፡ ነገር - - ! » እንደ ፡ መንጠራራት ፡ ብላ ፡ ስትራ መድ ፡ ቀምበጡ ፡ ከእጅዋ ፡ ይወድቃል ።— አታነሣውም « ደግሞስ ፡

እኔ ፡ ምንቸገረኝ - - ደስ ፡ ይበልህ - - ልብም ፡ አልለው - - - እርሸው ፡ ብሎ ፡ ነገር ! ! » ጉንበስ ፡ ብላ ፡ ክትክታ ፡ ትቆርጥና ፡ ጥርሷን ፡ እንደም ትፍቅ ፡ ዓይነት ፡ በጥርሶቿ ፡ ነከስ ፡ ነከስ ፡ አድርጋ ፡ መልሳ ፡ ትጥለ ዋለች።— የሎሚውንም ፡ ቀምበጥ ፡ የክትክታውንም ፡ ግንጣይ ፡ ከመሬት ፡ ያነሣል ፡ ጉርፋ ።—እንደገና ፡ ድንገት ፡ የተቆጣችበት ፡ ምክንያቱም ፡ ባይገ ባው ፡ ያስቆጣበት ፡ ነገር ፡ በርግጥ ፡ ያለ ፡ ስለ ፡ መሰለው ፡ ተደናግጧል —

« - - ምን ፡ አባቴ ፡ ይብጀኝ - - ምን ፡ ብያት ፡ ይሆን ፡ ደሞ ? ምን ፡ ተናግሬያት ፡ ይሆን ፡ ሳላውቅ - - ? » ሲያሰላስል ፡ በጎሊናው ፡ ሎሚውንና ፡ ክትክታውን ፡ እጁ ፡ ላይ ፡ ያየዋል « በዚህ ፡ ይሆናል ፡ የተናደደችው ፤ እሥር ፡ እሥሯ ፡ እየተከተልሁ ፡ የጣለችውን ፡ ሁሉ ፡ በማንሣቴ - - -

« ቤቴ ፡ መመለሴ ፡ ነው ! » ትናገራለች ፡ ጺወኔ ፡ ድንገት ፡ ወደ ፡ ቤቷ ፡ ወደማይወስዳት ፡ መንገድ ፡ በመግባት ።— ካንጀቷ ፡ እየዳመነ ፡ የሚነሣ ፡ ነገር ፡ ጉሮሮዋን ፡ ያፍናታል ።— ለመቆጣጠርም ፡ የማትች ለው ፡ እንባ ፡ ፈንቅሎ ፡ የሚመጣባት ፡ ይመስላታል ።—

# ፵፪

## አደፍርስ

« - - መንገዱን ፡ ተሳስተሻል - - ይኸኛው ፡ መንገድ ፡ ይቀርብሻል - - እሱኛው ፡ ቅድም ፡ ወደነበርንበት ፡ ቦታ ፡ ነው ፡ የሚመልስሽ » ይላታል ፡ ጉርፉ ፡ እየተከታተለ ።— ጺወኔ ፡ ቢሆን ፡ በሩጫና ፡ ርምጃ ፡ ቅልቅል ፡ ትጣደፋለች - - ፊት ፡ ፊቷን ፡ እያየች ።— መለስ ፡ እንኳን ፡ አትልም።— ባጉልና ፡ በተጠመዛዘዘ ፡ መንገድ ፡ ሄደው ፡ አረፉበት ፡ ጉጆ ፡ አጠገብ ፡ ሲደርሱ ፡ ነው ፡ ዘወር ፡ እንደማለት ፡ ብላ - -

« ቀጣፊ - - ውሸታም - - አታላይ - - » በማለት ፡ ግማሹ ፡ ተውጦ ፡ ግማሹ ፡ በሚነገር ፡ ድምፅ ፡ መናገር ፡ የምትጀምረው ።—

« ያጠፋሁትንኮ ፡ ባውቀው - - - ?

« ከየት ፡ አነሣኸው ፡ ደሞ ፡ እሱን ፡ ቀምበጥ - - » ትለዋለች ፡ ትቀጥልና ፡ እጅ ፡ እጁን ፡ እየተመለከተች ።—

« ቀምበጥ ? ቀምበጥ - - ?

« እሱን ፡ እጅህ ፡ ላይ ፡ የያዝከውን - - - ውሸት ፡ ነው ፡ በል ፡ እሱንም - - -

« ከየት ፡ አነሣሁት - - አንቺ ፡ ስትጥይው ፡ ነው ፡ ያነሣሁት - - ከመንገድ ፡ ላይ - - -

« ማን ፡ አንሣ ፡ አለህ ? ውሸታም ፡ ከሆንህ - - ለምን ፡ አነሣኸው - - - ?

«ለምን ፡ አነሣሁት ? ለምን ፡ አነሣሁት ? ! አነሣሁታ ! ለምን ፡ አነሣዋለሁ - - ጣልሽው ፤ አነሣሁት - - ሳላስብ ፡ ነው ፡ ያነሣሁት - - -

« እረግዷያ - - ሳታስብ ፡ ነው ፡ ያነሣኸው - - -

« እንዴ ? ! ለምን ፡ ጣልሽው ፡ አንቺስ - - -

« ከጄ ፡ አመለጠኝ ፡ እኔማ - - -

« ሆን ፡ ብለሽ ፡ ነው ፡ የጣልሽው ፡ ተናደሽ - - - !

« ስለዚህ ፡ አንተ ፡ ተናድጄ ፡ ስለጣልሁት ፡ እንዣሽው - - -

« አዎ ፡ እንሣሁት - - - !

« በመናደዴ ፡ ደስ ፡ ብሎህ ፡ እንሣኸው - - !

« የምን ፡ ብቀታ ፡ ነው ፡ እንግዲህ - - - ! እሺ ፡ በመናደድሽ ፡ ደስ ፡ አለኝ ፡ እንሣሁት - - - ምንድነው ፡ ታዲያ - - - አጥፍቼ ፡ እን ደሁ - - -

« እኔ ፡ በመናደዴ ፡ ደስ ፡ አለህ - - - !

« በመናደድሽ ፡ ሳይሆን - - መቼስ ፡ ድኸው ፡ ሚካኤል ፡ ምስክሬ ፡ ነው - - ብቻ ፡ ቀምበጡን ፡ እንግሁት - - እና ፡ ደሞ ፡ ሮጥሽብኚ - - ልሰጥሽ ፡ ነበር ፡ መልሼ - - -

« እኮ ፡ እኔ ፡ በመናደዴ - - -

« በመናደድሽ ፡ አይደለም - - - ! እንዴት ፡ ብዬ ፡ ልንገርሽ - - እ - - እ - - አዎ ፡ ስላናደድሁሽ ፡ ነው ፡ ደስ ፡ ያለኝ - - !

« ስላናደድኸኝ - - - ? !

« በርግጥ ፡ ስትቆጪ ፡ ስላየሁ - - -

« በርግጥ ፡ ስቆጣ - - -

« ለወትሮው ፡ ሳናድድሽ ፡ ትስቂብኛለሽ - - - !

« ቀድሞ ፡ ምን ፡ አልከኝና ፡ እናደዳለሁ - - -

« ያልኩት ፡ እውነት ፡ አይደለም - እውነት ፡ አይደለም ፡ እያልኩ ፡ ስለደጋገምኩብሽ - - - !

« ታዲያ ፡ እኔ ፡ ምን ፡ ያናድደኛል - - አንተ ፡ ስለዋሸህ - - ደግሞስ ፡ እውነት ፡ ያይደለው ፡ ምንድነው ? እኔ ፡ እንደሁ ፡ ትዝም ፡ አይለኝ - - -

« ተናደድሽ - - !

« ስለዚህ ፡ ደስ ፡ አለህ - -

ፊቱ ፡ ላይ ፡ ብርሃን ፡ ያበራበታል « አዎን ፡ ደስ ፡ አለኝ - - - !

« ለምን ፡ ደስ ፡ ይልሃል - - - ?

« አልነግርም - - - !

« አትነግረኝም - - - ? !

« አልነግርም - - - !

አረፉበት ፡ ጐጆ ፡ ጥግ ፡ ገደማ ፡ ቁጭ ፡ ትላለች « እኔም ፡ አልፈል ግም - - እንድትነግረኝ ፡ አልፈልግም - - አልፈልግምአልፈልግም - - - !

« ውሸትሽን ፡ ነው - - - !

« ውሸትህን ፡ ነው - - - !

« ውሸቴን ፡ ነው - - -

« ውሸቴን ፡ ነው ? ውሸቴን ፡ ነው ? » ብድግ ፡ ትላለች ፡ ከተቀመ ጠችበት «ውሸቴን ፡ ነው - - - ? !

« የምን ፡ ውሸት ፡ ነው ፡ ደሞ ! እውነታችሁም ፡ እውነት ፡ እውነት፡ አይል ፡ እንኳን ፡ ውሸት ፡ ተናግራችሁ - - - » ይላሉ ፡ ወይዘሮ ፡ አሰጋሽ ፡ ጐጆዋ ፡ ውስጥ ፡ ጋደም ፡ እንዳሉ « ጺወኔ - - ጺወኔ ! አቅራቢያሽ ፡ እንዳለ ፡ ጐርፉን ፡ ጥሪልኝ ፡ እባክሽ - - ውሸት ፡ ብሎ ፡ ነገር - - ውሸ ቱን ፡ ሌላ ፡ ጊዜ ፡ ታረጊዋለሽ - - -

## ፴፫

# አደፍርስ

በማግስቱ ፡ ማታ ፡ ጐርፉ ፡ የደረሰበት ፡ ይጠፋል ። ጠመንጃና ፡ ገና ፉን ፡ ቢሆን ፡ አልወሰደም ። ምናልባት ፡ አዳል ፡ ጠልፋው ፡ እንደሆን ፡ በማለት ፡ በጣም ፡ ሰግተዋል ፡ ወይዘሮ ፡ አሰጋሽ ። የሮቢትን ፡ ከተማ ፡ ማቢያ ፡ አዛዥ ፡ የኅምሳ ፡ አለቃ ፡ ፖሊስ ፡ አረፋበት ፡ ቦታ ፡ ድረስ ፡ አስ ጠርተው ፡ ስጋታቸውን ፡ ይገልጻሉ

« ምን ፡ እንደነካው ፡ አላውቅም — ከጺወኔ ፡ ጋር ፡ እጅረት ፡ ወርዶ ሲመለስ ፡ አስጠራሁትና ፡ ቀሚስና ፡ ኩታዬን ፡ ጭፍ ፡ ጭፍ ፡ አድርግ ልኝ ፡ ብዬው ፡ ይዞ ፡ ወጣ - - - እኛ ፡ ደሞ ፡ ምን ፡ ይነካው ፡ ብለን - - እስከ ፡ ከብት ፡ መግቢያ ፡ ድረስ ፡ ጠበቅነው ፤ ሳይመጣ ፡ ቀረ ።— ቢቸግረኝ ፡ ይኸን ፡ ያረፍኩበትን ፡ ሰውዬ ፡ አስቸገርኩና ፡ እጅረት ፡ ቢወ ርድ ፡ ያው ፡ እንደሰሙት - - -

« ልብስዎ ፡ እንደ ፡ ተሰጣ ፡ ነው ፡ የተገኘው - - -

« አዎ ፡ መቼም ፡ ወጉ ፡ ደርሶታል - - -

« ምን ፡ ማለትዎ ፡ ነው ፡ ወጉ ፡ ደርሶታል - - ቅር ፡ ያለወት ፡ ነገር፡ እንዳለኮ ፡ ቢነግሩኝ - -

« ምን ፡ ቅር ፡ ይለኛል ? ምንም ፡ ቅር ፡ የሚለኝ ፡ ነገር ፡ የለ - - -

« ቅር ፡ ያለወትስ ፡ ነገር ፡ ያለ ፡ ይመስላል - - -

« አይ ፡ ባቦልዎ ፡ ምን ፡ ቅር ፡ የሚል ፡ ነገር ፡ አለኝ ፡ ብለው - - እንዲያው ፡ ብቻ ፡ አይፍረድ ፡ ነው ፤ ምን ፡ ሲያቀብጠኝ ፡ እሱን ፡ እንደላ ክሁ ፡ አላውቅም - - ወይኮ ፡ ደሞ ፡ ልብሴንም ፡ በደንብ ፡ ባጠበው ፤ እንዶዱ ፡ እንኳን ፡ ጨርሶ ፡ አለቀቀም - - -

« ቶሎ ፡ ቶሎ ፡ ጐረፍ ፡ ጐረፍ ፡ አድርጎ ፡ ይሆናል ፡ ያወጣው - -

« ነከር ፡ ነከር ፡ አድርጎ ፡ ማለትዎ ፡ ነው ፡ ደሞ ፡ እርስዎ - - - ? እንዲያው ፡ ምን ፡ ይሆናሊ ፡ አሳይዎት ፡ ነበር - - አሁን ፡ ሮማን ፡ ነች ፡ እንደገና ፡ መከራዋን ፡ አይታ ፡ የልብስ ፡ መልክ ፡ የሰጠችው - - ከብት ፡ ያኘከው ፡ ነበር ፡ አስመስሎ ፡ ያሰጣው - - -

« እንዲያው ፡ ምናልባት ፡ እስኪደርቅለት ፡ ቁች ፡ እንዳለ ፡ ሳትታስብ ፡ አደጋ ፡ ጥላበት ፡ ይሆን - - ? በዚህ ፡ ወራት ፡ ደሞ ፡ አስግታለች ፤ እንዲህ ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ አደጋ ፡ እየጣለች - - -

« ምናባቴ ፡ ዐውቄ ፡ እንግዲህ - - ቢሆንስ ፡ ታዲያ ፡ እንዴት ፡ አንድ ፡ ምልክት ፡ ይጠፋል - - እንደ ፡ ልብስም - - እንደ ፡ ደምም - - የሆነው ፡ ይሁን ፡ ብቻ - - አንድ ፡ ነገር - - -

« የልብሱን ፡ ይበሉኚ - - የደሙ ፡ እንኳ ፡ በምን ፡ ያስታውቃል ፤ ያውሬውም ፡ የምኑም - - ይታያል ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ በየመንገዱ - - -

« ቢሆንስ ፡ እንዴት ፡ ትኩስና ፡ የሰነበተ ፡ ደም ፡ አያስታውቅም - - እዝጊያብሔር ፡ ብቻ ፡ ከመዐቱ ፡ ያውጣኝ - - - ምን ፡ ይለኝ ፡ ቀኛዝማችስ ፤ አንድ ፡ ልጁን ፡ አምጥቼ ፡ እንደ ፡ ዋለ ፡ ሳስቀርበት - - - ምን ፡ ይለኝ - - ምን ፡ ይለኝ - - ምን ፡ ይለኝ - - - ! !

« እንዲህ ፡ በቀላሉ ፡ የሚጠቃ ፡ አይመስለኝም ፡ ልጁስ - - -

« ያውቁታል ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ጕርፋን - - ? » ትጠይቃለች ፡ ጺወኔ ፡ ንግግራቸውን ፡ ስታዳምጥ ፡ ትቆይና ።—

« እንዴታ ! በጣም ፡ ዐውቀዋለሁ ።— አንድ ፡ ሁለት ፡ ጊዜ ፡ አብረን ፡ ወርደናል ፡ ወደ ፡ ቆላው - - - አልፎ ፡ አልፎኮ ፡ መጐነታተሏ ፡ አልቀረም ፡ አዳል - -

« ነጭ ፡ ለባሽ ፡ ነኝ ፡ ብሎኛል ፤ አንድ ፡ ቀን ፡ እንዲሁ ፡ ስላዳል ፡ ጉስጐሳ ፡ ሲያጫውተኝ - - -

« አወን ፡ ነጭ ፡ ለባሽ ፡ ከሆን ፡ ቆይቷል ።— እና ፡ ታዲያ ፡ የዋዛ ፡ ልጅ ፡ አይደለም ፤ ጥንቁቅም ፡ ነው ፡ በጣም - - ራሱን ፡ አይጥልም - - -

« አይ - - እባክዎን ፡ ያምሳ ፡ አለቃ ! ዋናው ፡ ነገር ፡ ብቻ ፡ አለመቀደም ፡ ነው - - -

« እኮ ! ፡ አይቀደምም ፡ ነውኮ ፡ የምለው - - እጀውሃ ፡ ጅረት ፡ ወርዶ ፡ የሚያንቀላፋ ፡ አይመስለኝም - - -

« ሰውኮ ፡ ተጠንቅቆ ፡ ሲወጣ ፡ ነው - - እንዲህም ፡ እንዲያም ፡ ለማለት ፡ የሚቻለው ።— እሱ ፡ ለራሱ ፡ መሣሪያውን ፡ አልያዘ - - የኔን፡ ቀሚስ ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ ጠቅልሎ ፡ የወጣው - - -

« ቢሆንም ፥ ሌላው ፥ ቢቀር ፥ ወምበርቲውን ፥ ከወገቡ ፥ የሚለይ ፥ አይመስለኝም - - -

« አይ ፥ ወምበርቲውንስ ፥ ታጥቋል - - እሱን ፥ ከወገቡ ፥ ለይቶም ፥ አያውቅ - - - » ትናገራለች ፥ ጺወኔ ።—

« ለሁሉም ፥ እንግዲህ ፥ ዛሬ ፥ መቼም ፥ መሽቷል—ነገ ፥ ነጭ ፥ ለባሽም ፥ ከኛም ፥ ወታደሮች ፥ አደርግና ፥ ማለዳ ፥ ጀምሬ ፥ ፍለጋውን ፥ እቀጥላለሁ - - -

« አይርሱኝ ፥ ያምሳ ፥ አለቃ ! አይርሱኝ - - - ! ከዚህ ፥ ማጃ ፥ ያውጣት ፥ በሉኝ - - !

« ግዴለዎትም ፤ እስከዚህ ፥ የሚያሰጋ ፥ አይደለም ፥ ልጄ - - በዚያ ፥ ላይ ፥ ደሞ ፥ አገሬው ፥ ይወደዋል ።— ጉርፉ ፥ ጠፉ ፥ ብል ፥ ሽፍታ ፥ ጉስጓሹ ፥ ሁሉ ፥ ነው ፥ መሣሪያውን ፥ ጉትቶ ፥ ከየሥርቻው ፥ የሚነሣው - -

« እዝጊያብሔር ፥ ያውጣት ፥ በሉኝ ፥ ብቻ - - ዋናው ፥ ነገር ፥ እሱ ፥ ነው - - እሱ ፥ ሲለው ፥ ነው ፥ ሁሉም ፥ የሚሆነው - -

« እግዚአብሔር ፥ መቼም ፥ ሥራችንን ፥ ያቃናው ፥ እንጂ ፥ የተቻለንን ፥ እናደርጋለን - - -

## ፵፩

# አደፍርስ

« - - ገና ፡ ለገና ፡ ሳታጤነው ፡ ቀርተህ ፡ ስላልተሰማህ ፡ በዱሮ ውና ፡ በዛሬው ፡ ተጠየቅ ፡ ልጠይቅህ ፡ ሙግት ፡ መካከል ፡ ለውጥ ፡ የለም፡ አትበለኝ - - » ተቋቁመዋል ፡ አቶ ፡ ጥሶ ፡ አደፍርስን ፡ እንደ ፡ ወትሮው ፡ ከራት ፡ በኋላ ፡ ጠለላ ፡ ወጥተው ፡ ቁጭ ፡ ብለው ።—

« ካለ ፡ እንግዲያው ፡ ለኔ ፡ አልታየኝም ።— ነገ ፡ የሚሰቀለው ፡ ገዳይ ፡ ለምሳሌ ፡ በኔ ፡ አስተያየት - - በሽተኛ ፡ እንጂ ፡ ወንጀለኛ ፡ አይደለም - - እና - - ይኸ ፡ ለውጥ ፡ የምትለው ፡ ነገር - - -

« የትየለሌ ! ለውጥስ ፡ ለውጥ ፡ ነው - - - ? የዛሬውና ፡ የዱሮው ፡ ተጠየቅ ፡ ልጠይቅህ ! ደሞ ፡ ምንና ፡ ምን ፡ ወንድሜ - - - ! አንተ ፡ ልጅ ፡ ነህ ፡ አልደረስህበትም ፡ እንጂ - - ለውጥስ ፡ አልለ ፡ አደፍርስ - - አልለ ፡ ለውጥስ - - እንዲህ ፡ ነበር - - - እንዲህ ፡ ነበር ፡ የዱሮው ፡ ተጠየቅ ፡ ልጠይቅህ - - -

‘ ጊደሬ ፡ ጠፍታ ፡ ተደጋ ፡

እኔ ፡ መጥቼ ፡ በፍለጋ ፡

ከደጅህ ፡ አገኘሁ ፡ ሙዳ ፡ ሥጋ ፡

ያደርግሃል ፡ ባለ ፡ ዕዳ - - ’ በማለት ፡ ያቀርባል ፡ ከሳሽ ።—

‘ ጊደር ፡ ብትጠፋ ፡ ተደጋ ፡

አንተም ፡ ብትመጣ ፡ በፍለጋ ፡

እደጅም ፡ ቢገኝ ፡ ሙዳ ፡ ሥጋ ፡

ተቤቴ ፡ በታች ፡ ትልቅ ፡ መንገድ ፡

ቀን ፡ ሠራዊት ፡ ሌት ፡ አራዊት ፡ የሚያሳልፍ ፡

ተቤቴ ፡ በላይ ፡ ትልቅ ፡ ወርካ ፡

አሞራና ፡ አውሬ ፡ የሚያሽካካ —

አሞራና ፡ አራዊት ፡ ሲጣለፉ ፡

ሙዳ ፡ ሥጋ ፡ ቢተፉ ፡

ከደጃም ፡ ቢገኝ ፡ ሙዳው ፡ ሥጋ ፡

አያደርገኝም ፡ ባለ ፡ ዕዳ ’ ሲል ፡ ይመልስለታል ፡ ተከሳሽ - - -

« ይኸ ፡ ታዲያ ፡ ግሩም ፡ አይደለም ፡ እንዴ ! እንዴት ፡ ነው ፡ ደስ ፡ የሚለው - - -

« ደስ ፡ የሚል ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ እውነትን ፡ አያስገኝም ፡ አደፍርስ - - የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ የሚፈልገው ፡ እውነተኛ ፡ ፍትሕ ፡ ነው ።— አለ ዚያ ፡ እርስቱ ፡ ንብረቱ ፡ ሃይማኖቱ ፡ ዋጋ ፡ የላቸውም - - እርስቱን ፡ አራሙቻ ፡ ቢገማሸርበት ፡ ንብረቱን ፡ ወዳጅ ፡ ጠላት ፡ ቢሠርግበት ፡ በሃ ይማኖቱም ፡ ገሀነመ ፡ እሳት - - ሲያል ፡ ቢገባ—ግዴለውም።—እውነትን፡ አጣሁ ፡ ብሎ ፡ ካመነበት ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ ቀን ፡ እስኪሞላለት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የሚጠብቀው ፡ ኑሮው ፡ ኑሮ ፡ አይደለም ።—እውነትን ፡ ያገኘ ፡ ለት ፡ ግን ፡ እውነትን ፡ ያሳጣውን ፡ ሰው ፡ በመግደል ፡ እንኳ ፡ ቢሆን — ወዲያውኑ ፡ ሕይወቱን ፡ ቢያጣ ፡ ግዴለውም ።—ትክክለኛ ፡ ፍትሕን ፡ እንደ ፡ ዘለዓለማዊ ፡ ሕይወት ፡ አጉል ፡ ፍርድን—እንደ ፡ ዕድሜ ፡ ልክ ፡ ገሀነመ ፡ እሳት ፡ ነው ፡ የሚቆጥረው - - -

« ታዲያ ፡ እውነትን ፡ ያሳጣውን ፡ ሰው ፡ በመግደል ፡ እውነትን ፡ ያገኘ ፡ ይመስልሃል ፡ እንዴ ፡ ጋሼ ፡ ጥሶ - - ?

« አንተ ፡ ምን ፡ ይመስልሃል - - - ?

« እኔ ፡ ሰውዬውን ፡ በመግደል ፡ ውሸትን ፡ ዘለዓለማዊነት ፡ የሰ ጠው ፡ ነው ፡ የሚመስለኝ - - -

« ውሸትን ፡ ዘለዓለማዊነት ፡ የሰጠው ፡ ነው ፡ የሚመስልህ - -

« ሰውዬውን ፡ ገደለው ፡ እንጂ ፡ ውሸትን ፡ አልገደለውም - - -

« ምነው ፡ ሰውዬው ፡ ሲሞት ፡ አድራጎቱ ፡ ሁሉ ፡ አብሮ ፡ የሚ ሞት ፡ አይመስልህም - - ?

« አድራጎቱ ፡ አይሞትም ፤ እንዲያውም ፡ ዘለዓለማዊነት ፡ ነው ፡ የሚያገኘው - - -

« ዘለዓለማዊነት ፡ ስትል ፡ ምን ፡ ማለትህ ፡ ነው - - - ?

« የማይሞት ፡ ማለቴ ፡ ነው - - -

« ሰውዬው ፡ በሕይወት ፡ መኖር ፡ አለበት ፡ ማለትህ ፡ ነው ፡ እውነትን ፡ ከውሸት ፡ ለመለየት - - - ?

« እውነትን ፡ ለማኖር ፡ ውሸትን ፡ ለመግደል ፡ ሰውዬው ፡ በሕይወት ፡ መገኘት ፡ አለበት - - -

«እውነት ፡ የምትለው ፡ በሰውዬው ፡ በአእምሮው ፡ ውስጥ ፡ ያለውን ፡ ነው ፡ ወይስ ፡ ባንጓለለው ፡ በኀሊናው ፡ ውስጥ ፡ ያለውን - - - ?

« በሁለቱም ፡ ውስጥ ፡ ያለውን ፡ ነው - - - !

« እሺ ፡ በሁለቱም ፡ ውስጥ ፡ ያለው ፡ አንተ ፡ ውሸት ፡ ነው ፡ ብለህ፡ ያመንክበት ፡ የሆነስ ፡ እንደሁ - - - ?

« ድንቁርና ፡ ከዕውቀት ! እንዲያማ ፡ ከሆነ ፡ ሰውዬውን ፡ መግደልን ፡ አንድ ፡ ሕፃን ፡ ልጅን ፡ እንደ ፡ መግደል ፡ ያህል ፡ ነው ፡ የምቆጥረው - -

« ምን ፡ ማለትህ ፡ ይሆን - - - ?

« ምንም ፡ የማያውቅ ፡ ደንቆሮ ፡ ነው ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ሰውዬው - - ካለማወቁ ፡ የተነሣ ፡ ነው ፡ ማለት ፡ ነው ፡ እውነትን ፡ በውሸት ፡ የሚለውጠው - - በውነት ፡ በውነት ፡ ጋሼ ፡ ጥሶ ፡ እንዲህ ፡ ያለውን ፡ ሰው ፡ የሚገድል ፡ በኔ ፡ በኩል ፡ የመጨረሻ ፡ ትልቅ ፡ ወንጀለኛ ፡ የምለው ፡ ነው - - -

« እሺ ፡ እንዲህ ፡ ከሆነ ፡ እንግዲያው ፡ እውነትን ፡ ለማግኘት ፡ አይቻልም ፡ ማለት ፡ ነው - - - ?

« እንዴት ፡ አይቻልም ፡ ይቻላል ፡ እንጂ - - - !

« ሰውዬው ፡ እውነትና ፡ ውሸትን ፡ ያልለየው ፡ በድንቁርናው ፡ ምክንያት ፡ ከሆነ ፡ እንዴት ፡ አድርገህ ፡ እውነትን ፡ እንዲያውቅ ፡ ልታደርገው ፡ ትችላለህ - - - ?

« በማስተማር - - - !

« አንተ ፡ እውነት ፡ ነው ፡ ብለህ ፡ የምታምንበትን ፡ ማለት ፡ ነው - - ?

« አዎ ፡ ለጊዜው ፡ ሁኔታው ፡ ባህሉ ፡ አካባቢው ፡ እውነት ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ የሚገምተውን - - -

« ዘለዓለማዊ ፡ እውነት ፡ የለም ፡ ማለት ፡ ነው ፡ እንግዲህ ፡ እንደዚህ ፡ ከሆነ - - -

« ምናልባት ፡ በሳይንስ ፡ ጥበብ ፡ በኩል ፡ ሊኖር ፡ ይችላል - - -

« በኀብረተ ፡ ሰብአዊ ፡ ኑሮ ፡ ውስጥ ፡ ግን ፡ ሊኖር ፡ አይችልም - - ?

« ላይኖር ፡ ይችል ፡ ይሆናል - - -

« እንግዲህ ፡ እውነት ፡ እውነት ፡ ውሸት ፡ ውሸት ፡ የሚባሉት ፡ ነገሮች ፡ እንዳካባቢው ፡ ሁኔታ ፡ ይለዋወጣሉ ፡ ማለት ፡ ነው - - -

« አዎ ፡ ይለዋወጣሉ - - -

« እውነትም ፡ ሆነ ፡ ውሸት ፡ የሚኖሩት ፡ እሁኔታው ፡ እባህሉ ፡ አካባቢው ፡ ውስጥ ፡ ነው - - -

« ይመስለኛል - - -

« ስለዚህ ፡ ሰውዬውን ፡ በመግደል ፡ ውሸትን ፡ ዘለዓለማዊነት ፡ አልሰጠኸውም ፡ ማለት ፡ ነው - - ሰውዬውን ፡ በመግደል ፡ ጊዜያው ፡ እንፋሎትህን ፡ አስወጣህ ።-የምትፈልገውን ፡ ዓይነት ፡ እውነት ፡ ግን - ኅብረተ ፡ ሰቡን ፡ አስተምረህ ፡ ልታገኘው ፡ ትችላለህ ፡ ማለት ፡ ነው ፤ ማለት ፡ ከሰውዬው ፡ ጋር ፡ አይሞትም - - -

« ጋሼ ፡ ጥሶ ! ዛሬስ ፡ ክርክርህ ፡ የልክራክር ፡ ፍላጐት ፡ ይመስላል - - - በዚህ ፡ አስተሳሰብህ ፡ እውነትን ፡ አጣሁ ፡ የሚል ፡ ሰው ፡ እውነት ፡ ያሳጣውን ፡ ሰው ፡ በመግደሉ ፡ ትስማማለህ ፡ ማለት ፡ ነው - - - ?

« መስማማት ፡ አለመስማማቴ ፡ ሌላ ፡ ነገር ፡ ነው - - እውነትን ፡ ውሸት ፡ ያደረገብህን ፡ ሰው ፡ በመግደልህ ፡ ውሸትን ፡ ዘለዓለማዊነት ፡ ትሰጠዋለህ ፡ የሚለውን ፡ አስተሳሰብህን ፡ ግን ፡ አልተቀበልሁትም - - -

« ብዙ ፡ ትክክልና ፡ እውነት ፡ ነው ፡ ብዬ ፡ ያመንኩበትን ፡ ነገር ፡ አናወጥህብኝ - - -

«ዓለምን ፡ የያዛት ፡ አብዛኛው ፡ የምታምንበት ፡ ነገር ፡ ከሰው ፡ የመነጨ ፡ በመሆኑ ፡ ታምናለህ ? ማለቴ ፡ የምናምንበት ፡ አብዛኛው ፡ ነገር ፡ ራሳችን ፡ የፈጠርነው ፡ አይመስልህም - - - ?

«አብዛኛው ? አዎ ፡ ከሰው ፡ አእምሮ ፡ የመነጨ ፡ ነው - -

«እውነትና ፡ ውሸትም ፡ በኛው ፡ በሰዎች ፡ የተፈጠሩ ፡ ናቸው ፡ ማለት ፡ ነው - - -

« መሆን ፡ አለባቸው - - - ! ማለቴ ፡ በጠቅላላው ፡ መላ ፡ ምት ፡ ከተስማማን - - -

« እኛው ፡ የፈጠርናቸው ፡ በኛ ፡ ውስጥ ፡ ይኖራሉ - - -

« በሌላም ፡ ውስጥ ፡ እንዲኖሩ ፡ እንጥራለን - - -

« በኛው ፡ በሰዎች ፡ ውስጥ ፡ ማለት ፡ ነው - - -

« አዎ ፡ በሰዎች ፡ ውስጥ - - -

« እኛ ፡ ሰዎች ፡ ደግሞ ፡ ስንጠፋ ፡ ምናልባት ፡ የፈጠርነው ፡ ፈጠራ፡ ሁሉ ፡ ይጠፋ ፡ ይሆናል - - ከኛ ፡ የተሻለ ፡ ፍጥረት ፡ ተነሥቶ ፡ካል ቀጠለበት - - -

« ምናልባት - - -

« ውሸት ፡ ወይ ፡ እውነት ፡ ብለህ ፡ የምታምንበት ፡ ነገር ፡ በውስ ጥህ ፡ አለ - - -

« አዎን ፡ አለ - - -

« ቢያጤነውም ፡ ባያጤነውም — እውነትን ፡ በውሸት ፡ ለወጠ ፡ እምትለው ፡ ሰው ፡ ውስጥም ፡ አለ - - -

« መኖር ፡ አለበት - - -

« ያንዱ ፡ እምነትና ፡ እውነት ፡ በዚያው ፡ ባንዱ ፡ ላይ ፡ ተወስና ፡ ከቀረ ፡ ሰውዬው ፡ ሲሞት ፡ እምነትና ፡ እውነቱም ፡ አብሮ ፡ ይሞታል ፡ ማለት ፡ ነው - - -

« አዎን ፡ እምነትና ፡ እውነት ፡ ተከታይ ፡ ይፈልጋል—ዕድሜ ፡ የሚ ሰጠው - - -

« እውነት ፡ ብለህ ፡ ያሰብከውን ፡ በውሸት ፡ ቢለውጥብህም ፡ ለጊ ዜው ፡ ባመንክበት ፡ ነገር ፡ የገባ ፡ ሰው ፡ ነበር - - -

« አዎን ፡ ነበር - - -

« እውነት ፡ ወይም ፡ ውሸትህ ፡ ሌላ ፡ አንድ ፡ ተከታይ ፡ አፍርቶ ፡ ነበር - - -

« እርግጥ ፡ ነው ፡ ይኸ ፡ መቼም - - -

« አንተ ፡ ግን ፡ አንተ ፡ የመሰለህን ፡ እውነት ፡ ስላላወጣልህ ፡ ገደ ልከው - - -

« እኔኮ ፡ በመግደል ፡ አልተስማማሁም - - -

« ገብቶኛል ፡ ገብቶኛል ፡ ለነገሩ ፡ ያህል ፡ ማለቴ ፡ ነው - - -

« እሺ ፡ ገደልኩት - - -

« ታዲያ ፡ ምን ፡ ይመስልሃል ! ውሸትም ፡ ሆነ ፡ እውነት ፡ እንደገና ፡ ባንተው ፡ ብቻ ፡ ተወሰኖ ፡ ቀረ ፡ ማለት ፡ ነው - - - ዞረህ ፡ ዞረህ ፡ ደክመህ ፡ ደክመህ ፡ እጀመርክበት ፡ ተመለስህ ፡ ማለት ፡ ነው - - ቋቱ ፡ ጠብ ፡ አላለልህም - - -

« ስለዚህ ፡ ውሸትን ፡ ገደልከው - - -

« እውነትንም ፡ ጭምር ፡ ገደልከው - - - ማለት ፡ አንተ ፡ እውነት ፡ ብለህ ፡ ያመንክበትን — በጠባብ ፡ ደረት ፡ ባጭር ፡ ቁመት—ባንተ ፡ በራስህ ፡ ዕድሜ ፡ ብቻ ፡ ወሰንከው - - -

« ስለዚህ - - -

« ስለዚህ ፡ እውነትህ ፡ እምነት ፡ መሆኑ ፡ ቀረ - - ዘለዓለማዊነቱን ፡ አጣ - - -

« ሞትና ፡ ሕይወት ! ! ጋሼ ፡ ጥሶ ፡ የባሰ ፡ ሐሳቤን ፡ ሁሉ ፡ አዘበራረቅህብኝ - - - ፊት ፡ የተነጋገርንበትን ፡ ሳሰላስል ፡ ሌላ ፡ ነገር ፡ ደግሞ ፡ አምጥተህ ፡ ደነቀርህበት ፡ በሐሳቤ - - - በሌላ ፡ ጊዜ ፡ ብንነጋገርበት ? ይልቅ ፡ እስቲ ፡ አሁን ፡ ሌላ ፡ የዱሮ ፡ ሙግት ፡ ብትነግረኝ - - - እንደ ቅድሙ ፡ ዓይነት - - -

« የዱሮው ፡ የነገር ፡ አካሄድ - - መቼስ ፡ በጊዜው ፡ ሥርቷል - - እኛ ፡ የነሱ ፡ እንደሚያስቀን ፡ ምናልባት ፡ በአፀደ ፡ ነፍስ ፡ ቆመው ፡ ያዳምጡን ፡ እንደሁ ፡ የኛም ፡ ምንኛ ፡ ያስቃቸው - - -

« እኮ ፡ ታዲያ አንድ ፡ ተጠየቅ — ልጠይቅህ - - - ?

« ‘ - - እኔ ፡ ባርኮ - - -

መጣሁ ፡ እኮ ፡

እንደ ፡ ውሃ ፡ ስፈስ ፡

እንደ ፡ ጋጃ ፡ ስነፍስ ፡

ሚስቴ ፡ ገባር ፡

በቅሎዬ ፡ ሰጋር - - - » ይለዋል ፡ አንደኛው ፡ ።—

አንተ ፡ ባርኮ ፡

ብትመጣ ፡ እኮ ፡

እንደ ፡ ውሃ ፡ ብትፈስ ፡

አስቀድድሃለሁ ፡ ፈሰስ ፤

እንደ ፡ ጋሻ ፡ ብትነፍስ ፡

አሳጭድሃለሁ ፡ ለፈረስ ፤

ሚስትህ ፡ ብትገብር ፡

ቤቷን ፡ ታሳድር —

በቅሎህ ፡ ብትሰግር ፡

እመሸበት ፡ ታድር ! ’ ይመልስለታል ፡ ደሞ ፡ ሌላው ።— የዱሮው ፡ የዱሮ ፡ ስለሆነ ፡ አይናቅም - - የዛሬውም ፡ የዛሬ ፡ ስለሆነ ፡ አያስፈነድቅም ፡ አያከበስብስም - - ሁሉንም ፡ በየፈርጁ ፡ ተመልክቶ ፡ እንደሚበጅ ፡ ዓይነት ፡ አስተካክሎ ፡ መያዙ ፡ ይሻላል — አደፍርስ - - -

# ፵፫

## አደፍርስ

ሰኞና ፡ ሐሙስ ፡ የመንዝና ፡ ይፋቱ ፡ ገበያተኞች ፡ የሚገናኙባቸው ፡ ቀኖች ፡ ናቸው ። ካለፍ ፡ አገደም ፡ አንዳንድ ፡ ወንጀለኞችም ፡ ሲፈረድ ባቸው ፡ ግርፍም ፡ ሆነ ፡ ስቅላት ፡ የሚፈጸምባቸው ፡ በነዚሁ ፡ ቀኖች ፡ ነው ።

ዛሬ ፡ ሐሙስ ፡ ነው ። አንድ ፡ ቀን ፡ ቀደም ፡ ብሎ ፡ ቁመቱ ፡ ከሩቁ ፡ የሚታይ ፡ ረጅም ፡ መስቀያ ፡ እገበያው ፡ መካከል ፡ ገደማ ፡ ተዘጋጅቷል ፤ በረጃጅም ፡ የባሕር ፡ ዛፍ ፡ ግንዲላና ፡ አግዳሚ ። ማንቂያው ፡ ገመድ ፡ ከቡን ፡ አሳምሮ ፡ መካከል ፡ ላይ ፡ ተንጠልጥሏል ። እሥሩ ፡ አንድ ፡ መሰ ላል ፡ ከፍ ፡ ብሎ ፡ እተሠራ ፡ ቆጥ ፡ ዓይነት ፡ ርብራብ ፡ ላይ ፡ ተደግፎ ፡ ቆሟል ። ፖሊሶች ፡ አቶ ፡ ጥሶና ፡ ሌሎች ፡ ዳኞች ፡ እነ ፡ አቶ ፡ ወልዱና ፡ ሌሎች ፡ በከተማው ፡ የታወቁ ፡ ታላላቅ ፡ ሰዎች ፡ እነ ፡ አደፍርስና ፡ ፍሬዋ ፡ ተማሪዎች ፡ ሁሉ ፡ ሳይቀሩ -- የመስቀያውን ፡ ዙሪያ ፡ ከበው ፡ ይጠ ባበቃሉ ።— ከአንድ ፡ ቅጡ ፡ ከጠፋት ፡ በአንድ ፡ ቦታ ፡ አልረጋ ፡ ብላ ፡ እየለፈለፈችና ፡ እየሸለለች ፡ ካስቸገረች ፡ እብድ ፡ ሴትዮና ፡ እፊትና ፡ እኋላዋ ፡ እየመጣ ፡ ከሚጮህባት ፡ ባለቤቱን ፡ ያጣ ፡ ውሻ ፡ በስተቀር ፡ አብዛኞቹ ፡ ሰዎች ፡ በየሸቀጡ ፡ ተራ ፡ ሆነው ፡ የመጡበትን ፡ ገበያ ፡ ይገበያያሉ ።— ወሬውን ፡ ለማየት ፡ ቢሆን ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ ሰብሰብ ፡ ሰብሰብ ፡ ያሉት ፡ ገበያተኞች ፡ ብዛት ፡ እስከዚህም ፡ አልነበረም ።—

ሰባት ፡ ሰዓት ፡ ገደማ ፡ ገዳዩ ፡ በወሕኒ ፡ ቤት ፡ ዘበኞች ፡ ታጅቦ ፡ ይመጣል ። በተለይ ፡ አንዱ ፡ ዘበኛ ፡ የገዳዩ ፡ እርምጃ ፡ ቀረት ፡ ባለ ፡ ቁጥር ፡ እየገፈተረ ፡ ስለነበረ ፡ አመጣጡ « ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ይሙት ፡ ብለ ቀቅ ፡ ኖሮ ፡ አንተን ፡ ደሞ ፡ ነበር ፡ የጥይት ፡ ራት ፡ የማደርግህ --» እያለ ፡ ሲዝት ፡ ይሰማል ፡ ገዳዩ ።— እመስቀያውማ ፡ አጠገብ ፡ ሲደርስ ፡ ያዝ ፡ እንደ ፡ ማድረግ ፡ ብሎ ፡ ወደ ፡ ሕዝቡ ፡ መካከል ፡ ሊገፈትረው ፡ ሲል ፡ ሳይታሰብ ፡ ገዳዩ ፡ በኃይል ፡ ቢመነጭቀው ፡ ዘበኛው ፡ ተውተርትሮ ፡ ባፍ ፡ ጢሙ ፡ ተደፍቶ ፡ ነበር ።

ሰባት ፡ ሰዓት ፡ ተኩል ፡ ሲሆን ፡ ገዳዩ ፡ የሠራው ፡ ወንጀል ፡ የተ ዘረዘረበትና ፡ በስቅላት ፡ እንዲቀጣ ፡ የተፈረደበት ፡ የፍርድ ፡ ማስፈጸ ሚያ ፡ ግልባጭ ፡ ተነቦ ፡ ሲያልቅ ፡ እብዲቱ ፡ ሴትዮ ፡ ሽለላዋ ፡ ጨርሶ ፡ አላቋርጥ ፡ ይላል

«አውልቀው ፡ ወንድሜ

አውልቀው ፡ ሱሪህን ፡ ምን ፡ ያደርግልሃል ፡

ስንት ፡ አዕላፍ ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ አንቀው ፡ ይገድሉሃል » እያለች ፡ ታድረቀርቀዋለች ፤

«ያባቴ ፡ አገር—

ወንዜ ፡ ተራራዬ ፡ የሚሉት ፡ ምንድነው ?

ንዴቱ ፡ ብሶቱ ፡ ጥቃቱ ፡ ካልገባው ! » እያከታተለች ፡ በረጅሙ ፡ በማንቀርቀር ።—

ገዳዩን ፡ ባጉል ፡ ዓይነት ፡ አኳኋን ፡ ጥብቅ ፡ አድርጎ ፡ የፈጥኝ ፡ አሥሮ ፡ እርብራቡ ፡ ላይ ፡ ያወጣዋል ፤ ባፍ ፡ ጢሙ ፡ ሊደፋ ፡ የነበረው ፡ ዘበኛ ።— ዘበኛና ፡ ገዳይም ፡ ርብራቡን ፡ እንደ ፡ ረገጡ ፡ ገዳይ ፡ ዘራፍ ፡ ብሎ ፡ በመጀመር ፡ እያንጠረጠረው ፡ ይፎክራል

«ዐዋዲ ፡ ገዳይ

ቆሬ ፡ ላዩ ፡ ገዳይ

ራሳ ፡ ገዳይ - - ዘራፍ - - ዘራፍ - - ዘራፍ—ከምጫጫው—ከምጫ ጫው - - ዘራፍ - - ዘራፍ - - - ዘራፍ - - -

እብዲቱ ፡ ትሸልላለች

«ወንድሙን ፡ ሲገድሉት—

ወንድሙን ፡ ሲገድሉት ፡ ወንድሙን ፡ ካልከፋው ፡

አቅርቡለት ፡ ልብሱን ፡

የወንድሙን ፡ ሱሪ ፡ ደሙ ፡ እንዲከረፋው - - -

ገዳይ ፡ ፉከራውን ፡ ይቀጥላል ፤ በሞቀ ፡ በደመቀ ፡ በጋለና ፡ ልቡ ፡ ውጪ ፡ ወጥቶ ፡ ይምቦገቦግ ፡ በሚመስል ፡ ስግምግምታ - - -

«ዘራፍ - - - ዘራፍ - - ዘራፍ - - ዘራፍ - -

ራሳ ፡ ገዳይ —

ማፉድ ፡ ላይ ፡ ገዳይ —

ጀውሃ ፡ ገዳይ - - - ጀውሃ ፡ ገዳይ - - ዘራፍ - - ዘራፍ - - ዘራፍ - - - እዚህ ፡ ላይ ፡ ገዳይ - - ! ! » ዘበኛውን ፡ በርግጫ ፡ አሽቀንጥሮ ፡ እመሬት ፡ ይፈጠፍጠዋል « ደብረ ፡ ሲና ፡ ላይ - - - እጉባኤ ፡ ላይ - - - እጉባኤ ፡ ላይ - - ጠላቱን ፡ ገዳይ - - - » ድምፁ ፡ ጭርስ ፡ ወደማለቱ ፡ ይቃረብና ፡ ጸጥ ፡ ይላል ።—ድንገት ፡ እሳቱ ፡ ጠፍቶ ፡ አመዱ ፡ ብቻ ፡ ተከምሮ ፡ መክ ሰም ፡ የጀመሩ ፡ ሁለት ፡ ፍሞች ፡ እንደተዳፈኑበት ፡ ምድጃ ።— ጭንቅ



- - - የብዙ ፡ ሰው ፡ ጥፋት ፡ የአንድ ፡ ሰው ፡ ወንጀል ፡ ይሆናል - - ያልታደለ - - -

ላቱን ፡ እገመዱ ፡ ውስጥ ፡ ግራና ፡ ቀኝ ፡ አስታኮ ፡ ያገባና ፡ ርብራቡን ፡ ለቅቆ ፡ በገዛ ፡ እጁ ፡ ይንጠለጠላል ።—እመሬት ፡ የተዘረረው ፡ ዘበኛ ፡ ንቅንቅ ፡ ሳይል ፡ ይቀራል - - - እብዲቱ ፡ ትሸልላለች - - -

«አውልቀው ፡ ወንድሜ ፡

አውልቀው ፡ ሱሪህን ፡ ምን ፡ ያደርግልሃል

ስንት ፡ አዕላፍ ፡ ሴት ፡ ውስጥ ፡ አንቀው ፡ ይገድሉሃል - - -

# ፵፯

## አደፍርስ

አቶ ፡ ጥሶ « የብዙ ፡ ሰው ፡ ጥፋት ፡ የአንድ ፡ ሰው ፡ ወንጀል ፡ ይሆናል ፡ ያልታደለ ፡ ሰው ፡ የሚቀጣበት - - » እያሉ ፡ ከአቶ ፡ ወልዴና ፡ ከሥራ ፡ ጓደኞቻቸው ፡ ጋር ፡ እያወሩ ፡ ከገበያው ፡ ወጥተው ፡ ወደ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ አቅጣጫ ፡ ያመራሉ « - - ስለዚህ ፡ ስሕተት ፡ ሲደረግ ፡ ገና ፡ ለገና ፡ አያገባኝም ፡ ብሎ ፡ የሚያልፍ ፡ ሰው ፡ ራሱ ፡ ዋና ፡ ስሕተ ተኛ ፡ ነው ፤ ማለቴ ፡ በትንሽም ፡ ነገር ፡ እንኳን ፡ ቢሆን - - -

« እኔኮ ፡ ደሞ ፡ በጣም ፡ የገረመኝ ፡ የሰዉ ፡ ግዴለሽነት - - ባንድ ፡ እፍኝ ፡ ሽምብራ ፡ አንድ ፡ እንጓ ፡ አገዳ ፡ ባንድ ፡ ጭብጥ ፡ ጥጥ ፡ ላንድ ፡ ፍል ፡ የምትሆን ፡ ቡና - - - ዝም ፡ ብሎ ፡ ገበያ ፡ ገበያውን ፡ ብቻ - - - ትንሽም ፡ ዘበኛውን ፡ ገፍትሮ ፡ ሲጥልና ፡ ሲገድለው ፡ አዲስ ፡ ነገር ፡ ሆኖበት ፡ ሰብሰብ ፡ አለ ፡ እንጂኮ ፡ ከመጤፍም ፡ አልቆ ጠረን - - - » የሥራ ፡ ጓደኛቸው ፡ የተሰማቸውን ፡ ስሜት ፡ ይገልጻሉ - -

« - - እንደዚህ ፡ ያለው ፡ ሁናቴ ፡ ለነሱ ፡ እንደሚተነፍሱት ፡ አየር ፡ ሆኗል ፤ ጨርሶ ፡ አይሰማቸውም - - - ወደ ፡ ተስፋ ፡ ማድረግም ፡ ሆነ ፡ ወደ ፡ ተስፋ ፡ መቁረጥ ፡ ወደ ፡ ደስታም ፡ ሆነ ፡ ወደ ፡ ሐዘን ፡ ወደ ፡ ማመንም ፡ ሆነ ፡ ወደ ፡ መካድ ፡ አይገፋፋቸውም ።— ራሳቸውንም ፡ ሆነ ፡ ሀገራቸውን ፡ እዙሪያቸው ፡ በየዕለቱ ፡ ከሚያጋጥማቸው ፡ ድር ጊት ፡ ዝባዝንኬና ፡ ዝብዝብ ፡ ለይተው ፡ የመገንዘብ ፡ ችሎታ ፡ የላቸ ውም - - - እኛን ፡ ነው ፡ የሚሰማን ።— ሌላው ፡ ቀርቶ ፡ ለብዙ ፡ ጊዜ ፡ በመደጋገም ፡ ያየነው ፡ ድርጊት ፡ እንኳ ፡ ቢሆን ፡ እንደ ፡ አዲስ ፡ ነገር ፡ ሆኖ ፡ ሳያብሰለስለንና ፡ የስሜት ፡ ሰደድ ፡ ሳያስነሣብን ፡ የማያልፈው - - - እንደዚህ ፡ እንደ ፡ ዛሬው ፡ ዓይነት ፡ በየጊዜው ፡ የምናየው ፡ ግዳጃችንን ፡ የምንፈጽምበት ፡ ሁኔታ ፡ እንኳን ፡ ቢሆን - - የብዙ ፡ ጊዜ ፡ ቅሬታ ፡ እሳ ድሮብን ፡ ይቆያል - - » ያብራራሉ ፡ አቶ ፡ ጥሶ ።

«ታዲያ ፡ እንዲህ ፡ ከሆነማ ፡ መስቀሉስ ፡ መግረፉስ ፡ ምን ፡ ይበ ጃል ? የመንግሥቱ ፡ ጥረትኮ ፡ ባንዱ ፡ ቅጣት ፡ ሌላው ፡ እንዲማር ፡

ነው ፡ እንጂ ፡ እንግዲያማ ፡ እንደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ላለ ፡ ሠላሳ ፡ ሚሊዮን ፡ እንኳን ፡ ላልሞላ ፡ ሕዝብ ፡ ያንድ ፡ ሰው ፡ እንኳን ፡ ሞት ፡ ቢሆን ፡ ሳያ ጉዳ ፡ ቀርቶ ፡ አይደለም - - - » አቶ ፡ ወልዱ ፡ ሐሳባቸውን ፡ ያቀርባሉ ።

« ዛሬ ፡ ለምሳሌ ፡ ሕዝቡ ፡ ከቅጣቱ ፡ ምን ፡ የተማረ ፡ ይመስልዎ ታል - - ? » ይጠይቃሉ ፡ አቶ ፡ ጥሶ ።

«ምን ፡ ይታወቃል ?! ሱሪን ፡ ይታጠቃል ፡ እንዲያ ፡ ነው - - ! እናት ፡ ወለድሁ ፡ ትበል - - - ሠርግ ፡ እንጂ ፡ ሞት ፡ አይባልም - - - ወንድ ፡ ወንድን ፡ ያስንቃል - - - እውነትም ፡ ኮምጫጫ ፡ ጥርጥር ፡ የሌለው - - - ሲሉ ፡ ነበር ፡ የምሰማው - - -

« እኮ ፡ ታዲያ ፡ ይኽ ፡ አባባል ፡ ምን ፡ ፊር ፡ ይሰጥዎታል ? ስለ፡ ሕዝቡ ፡ አስተሳሰብ - - - » ይጠይቃሉ ፡ ደግመው ።

«መቼም ፡ የስሜት ፡ ጉዳይ ፡ ስለሆነ ፡ የጠየቁኝ - - - ወንዱም ፡ እንደ ፡ ገዳዩ ፡ ዓይነት ፡ ገዳይ ፡ ቢወጣው - - ሴቷም ፡ ወይ ፡ በጋብቻ ፡ ወይ ፡ በእናትነት ፡ እንዲህ ፡ ያለው ፡ ወንድ ፡ ወገን ፡ ለመሆን ፡ የፈለጉ ፡ ነው ፡ የመሰለኝ - - -

«- - እኔም ፡ እንግዲያው ፡ እንዲያ ፡ ነው ፡ የመሰለኝ - - ሌላው ፡ ቀርቶ ፡ ካንዳንድ ፡ ሰዎች ፡ ዓይን ፡ ሲረግፍ ፡ ያየሁት ፡ እንባ ፡ እንኳ ፡ የደስታና ፡ የፍንደቃ ፡ ዓይነት ፡ ነበር - - ሳቅ ፡ ጠርቶ ፡ ለመታየት ፡ ያለቀሰ ፡ እንጂ ፡ ሐዘን ፡ ብሶትን ፡ ለመወጣት ፡ ያነባ ፡ አይመስልም ፡ ነበር ።— ኩራት ፡ የወንድነትና ፡ የልበ ፡ ሙሉነት ፡ ስሜት ፡ ነበር ፡ በየሰዉ ፡ ፊት ፡ ሲግም ፡ የሚታየው - - - -

«እኮ ፡ ታዲያ ፡ ፊት ፡ ወደ ፡ ጠየቅሁት ፡ ጥያቄ ፡ ተመለስንኮ ! እንደዚህ ፡ ከሆነ ፡ የጥፋተኛው ፡ መስቀልና ፡ መገረፍ ፡ ምን ፡ ጠቀመ ?

«ምንም ፡ ጥቅም ፡ የለው ፡ ብሔራዊ ፡ በሆነ ፡ መንፈስ ፡ የተመለ ከቱት ፡ እንደሆነ - - -

«አፈረንጆቹ ፡ አገር ፡ እንደሚያደርጉት ፡ ታዲያ ፡ መስቀልና ፡ መግረፍ ፡ ቢቀር ፡ ጥሩ ፡ ይመስልዎታል - - ?

« የለም ፡ የፈረንጆችንም ፡ መንገድ ፡ መከተሉ ፡ ጥሩ ፡ አይመስለ ኝም - - - እንኳን ፡ ሞትንና ፡ ግርፋትን ፡ በእሥራት ፡ ለውጠንለት ፡ የወን ጀለኛው ፡ ብዛት ፡ አሁንም ፡ እሥር ፡ ቤቶቻችንን ፡ አጥለቅልቆታል - - -

«እኮ ፡ ታዲያ ፡ ሌላ ፡ ምን ፡ ፈትሕ ፡ ይገኛል - - - ?

« የብዙ ፡ ሰው ፡ ጥፋት ፡ የአንድ ፡ ሰው ፡ ወንጀል ፡ ከመሆኑ ፡ በፊት ፡ ነቅቶ ፡ ጥፋቱን ፡ ለማረም ፡ መሞከር - - - ዋናው ፡ ፈትሕ ፡ ይኸ ፡ ነው ፡ የሚመስለኝ - - - ለምሳሌ ፡ ባገራችን ፡ አንዱ ፡ አንዱን ፡ የሚገድልበት ፡ ዋና ፡ ዋና ፡ ምክንያት - - ወይ ፡ እርስቱን ፡ ወይ ፡ ሚስቱን ፡ ሲቀማ - - ከድንቁርና ፡ የተነሣ ፡ አዳሎች ፡ ለሰለባ ፡ ሲሉ ፡ የሚፈጽሙት - - ባልታሰበ ፡ ድንገተኛ ፡ አምባጓሮ ፡ ምክንያት ፡ የሚደርስ - - ችግርና ፡ መጉላላት ፡ ያጠቃውና ፡ ከችግሩ ፡ ለመውጣት ፡ ሲል ፡ በሚያደርገው ፡ ጥረት ፡ ወደ ፡ ሌብነት ፡ ወይም ፡ ወደ ፡ ቀማኛነት ፡ ስለሚያመራ ፡ እግረ ፡ መንገዱን ፡ ጥፋቱን ፡ እደብቃለሁ ፡ ሲል - - ወይም ፡ አንዳንዴ ፡ በዐባይ ፡ ጠንቋይ ፡ አነሣሽነት ፡ ስለሚሆን ፡ ወንጀሉ ፡ ከመሠራቱ ፡ በፊት፡ ለመቆጣጠር ፡ አያዳግትም ፡ ባይ ፡ ነኝ - - -

«እሌላውም ፡ ሀገር ፡ ቢሆንኮ ፡ ምክንያቶቹ ፡ እነዚሁ ፡ ይመስሉኛል - - -

«የሌላው ፡ ዓለም ፡ ግድያ ፡ እነዚህንም ፡ የያዘ ፡ ቢሆን ፡ ሌላ ፡ ሌላ ፡ በተንኮልና ፡ በምናለብኝነት ፡ የተመሠረተ ፡ አገዳደልም ፡ ይጨምራል - - እንደ ፡ መዝናኛና ፡ እንደመጫወቻ—በተፈጥሮው ፡ ሰውን ፡ እንደ ፡ እንስሳ ፡ እንጂ ፡ በአርአያ ፡ ሥላሴ ፡ የተፈጠረ ፡ መሆኑን ፡ በመካድ ፡ ላይ ፡ የተመሠረተ - - በአእምሮ ፡ ንክነትና ፡ በበሽተኝነት ፡ የሚፈጸም - - በግድያ ፡ ፍላጐት ፡ ብቻ ፡ በመነሣሣት ፡ ያለምክንያት ፡ የሚፈጸም ፡ ብዙ ፡ ብዙ ፡ ዓይነት ፡ ግድያ ፡ አለ - - -

«ታዲያ ፡ እንግዲህ ፡ የሚገድሉበት ፡ ምክንያት ፡ ስለተቀነሰኮ ፡ የሟቾች ፡ ብዛት ፡ ያንሳል ፡ ማለት ፡ አይደለም - - -

«እኔም ፡ አላልኩም ፤ ብቻ ፡ ግን ፡ ለመቆጣጠር ፡ ይቻላል ፡ ነው ፡ የምለው ።— በኔ ፡ አስተሳሰብ ፡ አንድ ፡ ሕዝብ ፡ ወደቀ ፡ የሚባለው ፡ ፈሪሀ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ሲያጣ ፡ ነው ። የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ እስላምም፡ ሆነ ፡ ክርስቲያን ፡ ወይም ፡ ሃይማኖት ፡ የሌለው ፡ በጠቅላላው ፡ እግዚአብሔርን ፡ ፈሪ ፡ ነው ።— ስለዚህ ፡ እኛ ፡ በዳኝነታችን ፡ ሌላው ፡ በፖሊስነቱ ፡ ሌላው ፡ ደግሞ ፡ ባስተዳደር ፡ በአመራሩ ፡ ኀሊናው ፡ ትክክል ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ለሚያስመለክተው ፡ ፍትሕ ፡ ከሠራ ፡ ገዳዩም ፡ ሆነ ፡ ሌባው ፡ ይቀነሳል ፡ እላለሁ ።— በድንቁርና ፡ ለሚመጣው ፡ መባላት ፡ ትምህርትን ፡ የመሰለ ፡ መቀራረቢያ ፡ ካለ - - ሚስቱንና ፡ ሀብቱን ፡ ለተቀማው ፡

እውነተኛ ፡ ፍትሕ ፡ ከተሰጠው — ለታረዘ ፡ ለተራበ ፡ ሠርቶ ፡ የሚያገኝ በት ፡ ዘዴ ፡ ከተገኘለት -- በድንገተኛ ፡ እምባጓሮ ፡ ለሚገድሉት ፡ ቅነሳ ፡ መጠጥ ፡ ቤቶችን ፡ የመቆጣጠሪያ ፡ ደንብ ፡ ከወጣ -- በየሠፈሩ ፡ እየዞሩ ፡ በየባላገሩ ፡ ንብረት ፡ ውስጥ ፡ እየገቡ ፡ የሚያታልሉትን ፡ ዐባይ ፡ ጠንቋ ዮች ፡ እየተከታተለ ፡ በሕግ ፡ የሚያስቀጣ ፡ የመንደር ፡ ሽማግሌዎች ፡ ሸንጎ ፡ ከተቋቋመ — አብዛኛው ፡ ችግራችን ፡ ይቀነሳል ፡ እላለሁ ---

«ጨርሶ ፡ ግን ፡ ገዳይንም ፡ ሆነ ፡ ሌባን ፡ ለማጥፋት ፡ አይቻልም --- ሌባ ፡ ላመሉ ፡ ዳቦ ፡ ይልሳል ፡ ነው ።— አጉል ፡ ልማድን ፡ የፍላጎት ፡ ሁሉ ፡ መሟላት ፡ ሊያስቀረው ፡ አይችልም --

«ጊዜ ፡ ይፈጃል ፡ እንጂ ፡ ጨርሶ ፡ ለማጥፋትም ፡ ቢሆን ፡ አይቻ ልም ፡ አልልም ።— ዋናው ፡ መንገድ ፡ ብቻ ፡ ቅድምም ፡ ደጋግሜ ፡ እንደ ፡ ጠቀስሁት ፡ የብዙዎቻችን ፡ ጥፋት ፡ ያንድ ፡ ሰው ፡ ወንጀል ፡ እስ ኪሆን ፡ ቸል ፡ አለ ፡ ማለትና ፡ በሕዝቡ ፡ ዘንድ ፡ አለ ፡ ብለን ፡ የምንኮራ በት ፡ ፈሪሀ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዳይጠፋ ፡ ቤተ ፡ እግዚአብሔር ፡ የም ትጠነክርበትን ፡ መንገድ ፡ መሻቱ ፡ ነው ።—

# ፵፯

# አደፍርስ

አደፍርስና ፡ ፍሬዋ ፡ እገበያው ፡ ውስጥ ፡ ሲዟዟሩ ፡ ይቆዩና ፡ አቶ ፡ ወልዱ ፡ ቤት ፡ ጐራ ፡ ብለው ፡ ጨዋታ ፡ ይዘዋል ፡ ስለተሰቀለው ፡ ገዳይ ።— ጨዋታውን ፡ እንደ ፡ ያዙ ፡ ነው ፡ እንግዲህ ፡ ዓይኑን ፡ ሌላ ፡ ነገር ፡ የሚጠልፍበት - - - ባለቤቲቱ ፡ ያጠለቁትን ፡ ጨሌ ፡ ያይና ፡ ያልጠረጠረው ፡ እጉል ፡ ነገር ፡ ያየባቸው ፡ በሚያስመስል ፡ አንደበት —

«ጨሌ ?! በጨሌ ፡ ያመልካሉ ?» ብሎ ፡ ድንገት ፡ የሚጠይቃቸው ፡ አደፍርስ ፡ ወይዘሮ ፡ ማለፊያን ።- እሳቸውም ፡ ያጠያየቁ ፡ አየር ፡ የገባቸው ፡ በሚመስል ፡ ሁኔታ ፡ ፊቱን ፡ እጁን ፡ ጠቅላላ ፡ ሰውነቱን ፡ ዝግ፡ ባለ ፡ የመንፈስ ፡ ብርሃን ፡ እየደሳሰሱ —

«አዎ ፡ ልጄ ፡ አመልኻለሁ -- ሰው ፡ እንደ ፡ ውቃቢው ፡ እንዳባዜው ፡ እንደ ፡ ብጤቱ ፡ አዶል ? » ብለው ፡ የሚመልሱለት ።-

«ቢሆንስ ፡ እንዴት ፡ እርስዎን ፡ ያህል ፡ አዛውንት ፡ በላይን ፡ ያህል ፡ የተማረ ፡ ልጅ ፡ ያደረሱ - - - ምን ፡ ይጐዳዎ ፡ ነበር ፡ እንዲህ ፡ ያለውን ፡ ልማድ ፡ ቢተውት ? » ይናገራል ፡ በድጋሚ ፡ አደፍርስ ።—

«ያስለመዱት ፡ ነገር ፡ ወዳጄ ፡ አልተው ፡ እያለ ፡ ነዪ ፡ ወደን ፡ ነው ፡ ይመስልሃል ?» ይቋቋማሉ ፡ ለውዴታቸው ፡ ወይዘሮ ፡ ማለፊያም ።

« ይኸነዬ ፡ አንድ ፡ ዐባይ ፡ ጠንቋይ ፡ ይሆናል ፡ አንግቱ ፡ ያለወት - - -

«ትግሪዋን ፡ ማለት ? አዶለም ፡ ወዳጄ ፡ ትግሪዋ ፡ ያባይ ፡ ጠንቋይ ፡ ሥራ ፡ አዶለችም ፤ ትግሪዋ ፡ የዘር ፡ ማንዘራችን ፡ አለኝታ ፡ ነች - - ትግሪዋ ፡ ስደተኛ ፡ ነች - - ትግሪዋ ፡ ማር ፡ የሚቆረስበትን ፡ ወተት ፡ የሚቀዳበትን ፡ አገር ፡ የምትመራ ፡ እመቤት ፡ ነች - - ባሌን ፡ ልጄን ፡ ከብቶቼን ፡ ትጠብቅልኛለች ፤ እንኳን ፡ ባመት ፡ አንዴ ፡ በየእኑም ፡ ባነግታት ፡ በወደድሁ - - -

« ከዘር ፡ የመጣች ፡ ጨሌ ፡ ነች ፡ ማለት ፡ ነው - - - ?

«ቅድም ፡ አያቴ ፡ ናቸው ፡ ከትግሬ ፡ ይዘዋት ፡ የመጡት - - - እና ፡ ከዚያ ፡ ቅድም ፡ አያቴ ፡ ለአያቴ ፡ እያቴ ፡ ለኔ ፡ እናት ፡ የኔ ፡ እናት ፡ ደሞ ፡

ለኔ ፡ አስተላለፈችልኝ - - ዋ ፡ የኔ ፡ ልጅ ፡ ባየሃት - - - አዛኝ ፡ ነች ፡ ሩሩ ፡ ነች ፡ ምን ፡ ከበደችኝና ፡ ልተዋት - - ?

« ይኸ ፡ ሁሉ ፡ መችም ፡ ከፍራት ፡ የተነሣ ፡ የሚመጣ ፡ ልማድ ፡ ነው - - -

«ፍራት ? ተሳስተሃል ፡ ልጄ ! የምን ፡ ፍራት ! ሰው ፡ እናቱን ፡ ይፈራል ? ፍራት ፡ ታይሆን ፡ ውዴታ ፡ ነው ፡ እኔ ፡ ያለኝ ፡ ለሷ ። እወዳታለሁ - - - ሁሉ ፡ ዘመዶቼ ፡ ቢያልቁ ፡ የቀረችኝ ፡ እሷ ፡ ብቻ ፡ ናት - - -

« እምልዎ ፡ አሁን ፡ በርግጥ ፡ ያምኑባታል ፡ ማለት ፡ ነው - - - ?

«እምነት ? አንተ ፡ የደላህ ፡ እቴ - - - እንደኔ ፡ ያለ ፡ ደካማ ፡ እምነትን ፡ ከየት ፡ ያገኘዋል ? መነኾሳቱና ፡ ቐሳውስቱም ፡ አላገኙት - - - እንደኔ ፡ ያለ ፡ ደካማ ! እምነትማ ፡ በኖረኝ ፡ ከዚህ ፡ ከሚያሰቃየኝ ፡ ኡርጥማትና ፡ የሰውነት ፡ ማቃጠል ፡ ድኜ ፡ ባልነበር ? ተየት ፡ ተገኝቶ ፡ ውላጄ ? እንደዜ ፡ ወላዋይ ፡ ልብ ፡ ተፈጥሮብን - - -

« ታዲያ ፡ ታላመኑባት - - -

«እምነትና ፡ ጥናቱን ፡ እንዲሰጠኝ ፡ ያልተሳልኩት ፡ ታቦት ፡ የለም - - -

«አንተስ ፡ እምነት ፡ አለህ - - ? »ድንገት ፡ ትጠይቀኛለች ፡ አደፍርስን ፡ ፍሬዋ ፡ ታዳምጥ ፡ ታዳምጥና ።

«የምን ፡ እምነት ? መቼም ፡ በጨሌ ፡ እንደማላምን ፡ ታውቂያለሽ - - - ቢፈልጉ ፡ አሁን ፡ አውጥቼ ፡ ገደል ፡ እጨምርላቸዋለሁ - - ምንም ፡ እንደማታደርገኝ ፡ ሊያዉ ፡ ይችላሉ - -

«ምን ፡ አፍ ፡ ምን ፡ አቅም ፡ አላትና ፡ ምን ፡ ብላ ፡ ትጎዳሃለች - - ?

« በጨሌስ ፡ አትመን ፡ እሺ ! ብቻ ፡ በምንም ፡ ይሁን ፡ እምነት ፡ አለኝ ፡ ባይ ፡ ነህ ፡ መቼም - - -

«እንዴታ ! መጠርጠሩስ — አለኝ ፡ እንጂ ፡ በደንብ ፡ እምነት ፡ አለኝ - - - ! መቅቀለዱ ፡ ይሆን ፡ ባንቺ ፡ ቤት - - - ?

« እሷን ፡ ብትጥላት ፡ እኔን ፡ ገደልሽኝ ፡ ማለት ፡ ነው - - ያለጥርጥር ፡ እሞታለሁ - -

«እባክዎን ፡ የበላይ ፡ እናት ፡ ዶቃ ፡ ስለ ፡ ተጣለ ፡ እንዴት ፡ እርስዎ ፡ ይሞታሉ - - ?

«ዶአ ! ዶአ ! የለም ፡ ውላጇ ፡ አልተግባባንም ፤ እሷ ፡ ለኔ ፡ ዶአ ፡ አዶለችም ፤ የዘር ፡ ማንዘሬ ፡ ቅሪት ፡ ነች - - - ቅርሴ ፡ ነች - - - አለኝ ታዬ ፡ ነች - - - አዘኔን ፡ ብሶቴን ፡ ተካፋዬ ፡ ነች - - -

«ትገርማለህ - - - » ትጀምራለች ፡ ፍሬዋ ፡ ራሷን ፡ በማወዛወዝ ፡ « ብትቀበለው ፡ ባትቀበለውም ፡ ልንገርህ ፤ እምነት ፡ የሚሉት ፡ ነገር ፡ ጨርሶ ፡ የለህም ፡ አንተ ።- ከዚያም ፡ በላይ ፡ ደግሞ ፡ የሚያሳዝነው ፡ እምነት ፡ የሌለህ ፡ መሆንህን ፡ እንኳን ፡ አለማወቅህ - - እምነተቢስነት ህን ፡ እምነት ፡ አለኝ ፡ ብሎ ፡ ብቻ ፡ በሙሉ ፡ አፍ ፡ በመናገር ፡ ለመሸ ፈን ፡ ማሞከርህ - - - !

«ለመሆኑ ፡ አንቺን ፡ ራስሽን ፡ ልጠይቅሽ - - - ስንት ፡ አገር ፡ ያዩ ትን ፡ ያቶ ፡ ወልዱን ፡ ባለቤት ፡ በጨሌ ፡ ሲያመልኩ ፡ ማየትሽ ፡ አልገረ መሽም - - - ?

«መግረም ! ህ ! የማይጠረጠር ፡ እምነት ፡ አለኝ ፡ ባይነትህ ፡ ነው ፡ እኔንስ ፡ የገረመኝ - - -

«እኮ ፡ በጨሌ ፡ ሲያመልኩ - - -

«በጨሌ ፡ ማምለክ ፡ በጨሌ ፡ ማምለክ ፡ እያልህ ፡ ደጋግመኸ ዋል - - - በጨሌው ፡ በርግጥ ፡ ያመልኩ ፡ አያመልኩበት ፡ እንደሁ ፡ እንዳንተም ፡ ርግጠኛ ፡ ባልሆን ፡ ምናልባትም ፡ እንዳልከው ፡ አምልኮት ፡ ካለበት ፡ አታምልኩበት ፡ እያልህ ፡ ስለጨቀጨቅሃቸው ፡ አይደለም ፡ የሚተውት - -

«ታዲያ ፡ እንዴት ፡ ባደርግ ፡ ነው ፡ የሚተውት ? እስኪ ፡ እንስ ማው ? እሳቸውን ፡ ከጨሌ ፡ አምልኮት ፡ እናውጣቸው ፡ እንጂ ፡ ሐሳቡ ፡ ከኔም ፡ መጣ ፡ ካንቺ ፡ ልዩነት ፡ የለውም - - -

«ነገርኩህኮ ፡ በጨሌ ፡ ያመልካሉ ፡ የምትለውን ፡ አነጋገር ፡ ስላል ተቀበልሁት ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲመለሱ ፡ የማድረጉ ፡ ነገር ፡ አላሳሰበኝም - - -

«አሁን ፡ በቅርቡ ፡ አንቺው ፡ ራስሽ ፡ የቦረንትቻ ፡ ሥጋ ፡ ካልበ ላሁ ፡ ብለሽ ፡ የእንዴት ፡ ያሉ ፡ አዛውንት ፡ ግብዣ ፡ ረግጠሽ ፡ አልተመ ለስሽም - - - ?

«ያ ፡ ሌላ ፡ ይኸ ፡ ሌላ - - - ! በነገራችን ፡ ላይ ፡ የሰው ፡ ግብዣ ፡ ረግጬ ፡ አልተመለስሁም ፤ አስፈቅጄ ፡ ነው ።— ካመጣኸው ፡ አይቀር ፡ ግን ፡ ልንገርህ ፡ ልዩነቱን - - -

«ያኛው ፣ መንገድ ፡ አምልኮት ፣ ይኸኛው ፡ ጨሌ ፡ አምልኮት ፡ ነው - - -

«ቀልድና ፡ ለገቻ ፡ ከሆነኮ ፡ ፍላጐታችን ፡ ክርክራችንን ፡ ብንተወው ይሻላል - - -

«እሺ ፡ እሺ ፡ ቀጥይ ! የምን ፡ ቀልድና ፡ ለገቻ ? ክርክራችንስ ፡ ደርዝ ፡ ያለው ፡ ነገር ፡ ላይ ፡ ለመድረስ ፡ ነው - - -

«ጥሩ ፡ አንተ ፡ እንዳየኸውና ፡ እንደ ፡ ሰማኸው - - በዚያን ፡ ጊዜ ፡ እኔ ፡ ባለቦረንትቾቼን ፡ አስከፍቻለሁ - - ?

«አላዩሽም ፡ እንጂ ፡ ክፉት ፡ ሳይሆን ፡ ደስታ ፡ ነበር ፡ የሚሰማ ቸው - - ሠይጣኑ ፡ ባንቺ ፡ አድሮ ፡ መሥዋዕታቸውን ፡ የተቀበላቸው ፡ መስሏቸው - - -

«እመየቴን ፡ ወይዘሮ ፡ አሰጋሽንም ፡ ሆነ ፡ ቤተ ፡ ሰቦቻቸውንስ ፡ አስከፍቻለሁ ? ስሜታቸውን ፡ እምነታቸውን ፡ ነክቼባቸዋለሁ - - ?

«የበጉ ፡ ሥጋ ፡ ከገባ ፡ በሽታው ፡ ይጨርሰናል ፡ ብለው ፡ የሚያም ኑትን ፡ ሰዎች ፡ አይጨርሳችሁም ፡ ብለሽ ፡ አጐዝለሽባቸዋል ፤ ባታስ ከፊያቸውም ፡ የነካሽባቸው ፡ ነው ፡ የሚመስለኝ ፡ እምነታቸውን - - -

«ራሴን ፡ ለመሥዋዕትነት ፡ አሳልፌ ፡ ልስጥ ፡ አልኩ ፡ እንጂ ፡ እምነታቸውን ፡ አልነካሁም - - -

«እኔም ፡ ጨሌውን ፡ ልጣልላቸው - - ጨሌይቱ ፡ የምትችል ፡ ከሆነ ፡ እኔን ፡ ትመመኝ ፡ ትግደለኝም ፡ ብዬ ፡ ራሴን ፡ ለሳቸው ፡ ሰጠሁ ፡ እንጂ ፡ እምነታቸውን ፡ አልነካሁም - -

«ያንተና ፡ የኔ ፡ አቀራረብ ፡ ግን ፡ ትልቅ ፡ ልዩነት ፡ አለው - - የኔ ፡ ፍቅርና ፡ ችግራቸው ፡ በገባው ፡ ልብና ፡ አንጀት ፡ ሲሆን - - -

« የኔ ፡ በድፍረትና ፡ በግዴለሽነት ፡ መንገድ ፡ ነው - - -

«አዎ ፡ ባይሆንም ፡ ነው ፡ የሚመስለው - - -

«ይልቅ ፡ እኔን ፡ አሁን ፡ የቸገረኝ ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ታውቃለህ ፡ የኔ ፡ ልጅ - - -» ይጀምራሉ ፡ ወይዘሮ ፡ ማለፊያ ፡ ያዳምጡ ፡ ያዳምጡና ፡ « ሴት ፡ ልጅ ፡ ያለመውለዴ ! ! አንጀቴ ፡ ነው ፡ የሚርመሰመሰው ፡ ባሰብሁት ፡ ቁጥር - - - -

«ምን ፡ የመሰለ ፡ ወንድ ፡ ልጅ ፡ ወልደዋል ፤ ሴት ፡ ልጅ ፡ ምን ፡ ያደርግልዋል - - - ? ማለቴ ፡ ወንድና ፡ ሴት ፡ መውለድ ፡ የሚመኙት ፡ ነገር ፡ ነው - - ግን ፡ እስከዚህ ፡ ካልሆነ ፡ ዘንዳ ፡ ምን ፡ የሚያስጨንቅ ፡ ነገር ፡ አለ - - - ?

«አላገኘሽኝም ፡ ውላጄ - - - ! ትግሪት ፡ የወንድ ፡ ልጅ ፡ አደራ ፡ አዶለችም - - ሴት ፡ ልጅ ፡ ብትኖረኝ ፡ ሴት ፡ ልጄ ፡ ካልሆነም ፡ እዝጊ ያብሔር ፡ ልበ ፡ ሰፊዋን ፡ ሚስት ፡ ለልጄ ፡ ቢሰጥልኝ ፡ የልጄ ፡ ሚስት ፡ ነች ፡ የምትወርሳት - - -

«እሷን ፡ ማንስ ፡ ወረሳት ፡ ማ ፡ እርስዎ ፡ ከሞቱ ፡ ወዲያ ፡ ምን ፡ አስጨነቀዎት - - - ?

«ያያት ፡ የቅድም ፡ አያቶቼ ፡ ቅሪት ፡ የትም ፡ እንድትወድቅ ፡ አልሻም ፡ የኔ ፡ ልጅ ።— እዝጊያብሔር ፡ ፈቃዱ ፡ ከሆነ ፡ አንጀቴ ፡ የሚረጋባት ፡ ልጅ ፡ ይስጠኝ - - -

«ከእንግዲህ ፡ እንዲወልዱ ፡ ማለት - - - ?

«ምነው ፡ የልጄስ ፡ ሚስት ፡ ልጄ ፡ አዶለችም ? ምን ፡ ፋይዳ ፡ አለው ፡ ብለህ ፡ ዘጠኝ ፡ ወር ፡ አርግዞ ፡ መውለድ - - ፋይዳ ፡ የለውም - - -

« ለመሆኑ ፡ አንተ ፡ በጨሌ ፡ ያመልካሉ ፡ ብለህ ፡ እንዴት ፡ ደፍ ረህ ፡ ትናገራለህ - - - ? » ትጠይቀዋለች ፡ ፍሬዋ ፡ አደፍርስን ፡ የወይዘሮ ፡ ማለፊያን ፡ ፍላጐት ፡ ካዳመጠች ፡ በኋላ ።—

«ለምን ፡ አልናገርም - - - ? » ይጠይቃታል ፡ መልሶ ፡ በመገረም— አደፍርስ ።—

«እንዴት ፡ ዐወቅህ - - ?

«ንግግርሽ ፡ አንዳንዴ ፡ ቆማጣ ፡ ያስሮጣል ።-እዚሁ ፡ ቁጭ ፡ ብለሽ ፡ እያወራሽና ፡ እየሰማሽ ፡ እንዴት ፡ ዐወቅህ ፡ ትይኛለሽ - - ?

«አይ ፡ የኔን ፡ ምስክርነት ፡ ከጠየቅህ ፡ እኔ ፡ የሰማሁት ፡ በእግዚአ ብሔር ፡ ማመናቸውን ፡ ታቦቶችን ፡ መማለዳቸውን ፡ ጨሌዋንም ፡ ካያት ፡ ከቅድም ፡ አያታቸው ፡ የመጣች ፡ ስለ ፡ ሆነች ፡ የሚወዷትና ፡ የሚያከብሯት ፡ መሆኗን ፡ ነው - - -

«ይኸ ፡ ያንቺ ፡ ነገር ፡ ማሳመር ፡ የሳቸውን ፡ እምነት ፡ አይለውጠ ውም ።- ደግሞም ፡ ከፈለግሽ ፡ በጨሌዋ ፡ ማምለክ ፡ አለማምለካቸውን ፡ ለመረዳት ፡ መልሰሽ ፡ ልትጠይቂያቸው ፡ ትችያለሽ - - -

«እሳቸው ፡ ያሉት ፡ የገባኝ ፡ ስለመሰለኝ ፡ እኔ ፡ አልጠይቃቸውም - - -

«እኔ ፡ ያልገባኝ ፡ እንግዲያው ፡ ደግሜ ፡ ልጠይቃቸው - - - በጨሌ ፡ ያምናሉ ፡ አያምኑም ፡ የበላይ ፡ እናት - - ?

«ባፌ ፡ ሙሉ ፡ አምናለሁ ፡ አልልም ፤ ድፍረት ፡ ይሆንብኛል - - ሰው ፡ ስንባል ፡ መጣም ፡ ደካሞች ፡ ነን - መጣምመጣም - - እድም ፡ እን ዳልሁት - - የሱ ፡ የፈጣሪ ፡ ምርጦች ፡ እንኳ ፡ ካገኙት ፡ ዓለም ፡ ነው - - -

«ምነው ፡ ትንሽስ ፡ ቢሆን ፡ እምነትዎን ፡ በዶቃ ፡ ላይ ፡ መጣልዎ--?

« ከመስጠም ፡ ለመዳን ፡ የሚፍጨረጨር ፡ ሰው ፡ የሚጨብጠውን ፡ ነገር ፡ ውበትና ፡ አስጠሊነት ፡ አይመለከትም ፤ መዳኑን ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ የሚያስበው - - - አስረዜ ፡ ዶቃ ፡ ዶቃ ፡ አትበል - - - » ትመል ስለታለች ፡ ፍሬዋ ።—

« እና ፡ በዚህ ፡ አነጋገርሽ ፡ በርግጥ ፡ በጨሌዋ ፡ ያምኑባታል ፡ ማለት ፡ ነው - - ሲታመሙ ፡ የምታድናቸው ፡ መከራ ፡ ሲመጣባቸው ፡ ከመከራ ፡ የምታወጣቸው ፡ በመሆኗ ፡ ያምናሉ ፡ ማለትሽ ፡ ነው - - -

« ጥሩ ፡ እንዲያም ፡ ከሆነ ፡ የገባህ - - አንዳንድ ፡ ጥያቄዎች ፡ ልጠ ይቅህ - - ?

«የፈለግሽውን - - - የፈለግሽውን - - -

«የሥነ ፡ ጥበብ ፡ መጽሐፍ ፡ ስታነብ ፡ በኀልያህ ፡ ከተጻፈው ፡ በላይ ፡ አታስብም - - ?

«ተመራማሪ ፡ ከሆንሁ ፡ አስባለሁ - - -

«ጥሩ ፡ የሥነ ፡ ጽሑፍ ፡ መጽሐፍ ፡ ስታነብ ፡ ከተጻፈው ፡ በላይ ፡ አትመለከትም - - በሐሳብህ ፡ እየጨማመርህ ፡ እየጨማመርህ ፡ ያልታየ ፡ ዓለም ፡ የምታይ ፡ አይመስልህም - - ?

«መጽሐፉ ፡ የሚያስደስት ፡ ከሆነ ፡ ከተጻፈው ፡ የበለጠ ፡ ሊመጣ ፡ ይችላል ፡ በአእምሮ - - -

«የታሪክ ፡ የሳይንስ ፡ መጻሕፍት ፡ ስታነብ ፡ ከተተረከለት ፡ ጀግና ፡ በላይ ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ ከተፈጠረው ፡ የሳይንስ ፡ ውጤት ፡ የበለጠ ፡ ክንውን ፡ ሊኖር ፡ እንደሚችል ፡ በኀልያህ ፡ መጥቶብህ ፡ አያውቅም - - ?

«ይኸ ፡ ይኸ ፡ ሁሉ ፡ የምትይው ፡ እርግጥ ፡ ነው ፤ ብቻ ፡ የዚህ ፡ ሁሉ ፡ ተጠየቅ ፡ አመጣጥ ፡ ለምን ፡ እንደሆን ፡ አልገባኝም - - -

«የሚካኤልን ፡ የገብሬልን ፡ የጊዮርጊስን ፡ ምስል ፡ ስታይ ፡ ከም ስሉ ፡ የበለጡ ፡ በሰማያዊ ፡ ኀይል ፡ የጐለበቱ ፡ መላእክት - - - እም ልህ - - በራቀ ፡ በጠለቀ ፡ ዓይነት ፡ መንገድ ፡ አይታዩህም - - ?

«ድንቁርናና ፡ ዕውቀት - - ! አይ ፡ እዚህ ፡ ላይ ፡ አይታዩኝም - - -

« እሺ ፡ ግዴለም ፡ አይታዩህ ።— ማንኛውንም ፡ ሥዕል ፡ ስታይ ፡ ከፎርሙና ፡ ከቀለሙ ፡ ውበት ፡ ውጪ ፡ የሆነ ፡ ልዩ ፡ ዓይነት ፡ ውበት ፡ ያየህ ፡ አይመስልህም - - - ?

«ያየሁ ፡ ይመስለኛል ፤ ግን ፡ ላላይ ፡ እችላለሁ - - -

«ታቦት ፡ ስትሳለም ፡ ለታቦቱ ፡ ነው ፡ ስግደትህ ፡ ወይስ ፡ ለእግ ዚአብሔር - - ?

«ለእግዚአብሔር ፡ ነው - - -

«ለምን ፡ ታዲያ ፡ ለታቦት ፡ እየሰገድህ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ነው ፡ ትላለህ ? በኀልያህ ፡ ለሚታሰብህ ፡ እንጂ ፡ በሚታይ ፡ በሚጨበጥ ፡ በሚ ዳሰስ ፡ ነገር ፡ በሚገለጠው ፡ አለማመንህ ፡ ከታወቀህ ፡ ታዲያ ፡ ለምን ፡ ሰውን ፡ እምነተ ፡ ቢስ ፡ ታስመስላለህ - - - ?

«ብለሽ ፡ ብለሽ ፡ ታቦትና ፡ ጨሌን ፡ አንድ ፡ ናቸው ፡ በይኝ - - !

«አንድ ፡ ናቸው ፡ አልወጣኝም— ብቻ ፡ እኔ ፡ የምለው ፡ አንተ ፡ በኀልያህ ፡ ከታቦቱ ፡ በላይ ፡ መጥቀህ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ያደርህ ፡ ከሆንህ ፡ እሳቸውም ፡ ከጨሌው ፡ በላይ ፡ መጥቀው ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ያደሩ ፡ ሊሆኑ ፡ ይችላሉ ፡ ነው - - - ሥነ ፡ ጽሑፍን ፡ ሥነ ፡ ጥበብን ፡ ታሪክን ፡ ሥዕልን ፡ ቅርጻቅርጽን ፡ ሳይንስን ፡ አምጥቆ ፡ ሰማያዊ ፡ ጥል ቀት ፡ የሚሰጠው ፡ ኀልያ - - ጨሌን ፡ አድባርን ፡ ታቦትን ፡ ማምለክን ፡ አምጥቆ ፡ ሰማያዊ ፡ ጥልቀት ፡ የማይሰጥበት ፡ ምክንያት ፡ የለም ፡ ነው ፡ የምልህ ።— ባንድ ፡ ልብ ፡ ባንድ ፡ ኀሊና ፡ የተቀበሉት ፡ እምነት ፡ እግ ዚአብሔር ፡ መንግሥት ፡ ያደርሳል ፡ ነው ፡ የምልህ - - - ከዚህ ፡ በተረፈ ፡ ማታ ፡ እንደ ፡ ልማድህ ፡ እንግዲህ ፡ ካባዬ ፡ ጋር ፡ ልትከራከር ፡ ትችላለህ ፡ እኔ ፡ ክርክር ፡ ቶሎ ፡ ይሰለቸኛል - - -

«ባላውቅሽ ፡ ኖሮ ፡ በዛሬው ፡ አነጋገርሽ ፡ ከሆነ ፡ ጭራሽ ፡ የመሻ ሻል ፡ ፍላጐት ፡ ያለሽ ፡ አትመስይኝም ፡ ነበር - - -

«መሻሻል ?! መሻሻሉን ፡ እርሳው ፡ እባክህ ! መሻሻል ፡ ትላለህ ፡ ደግሞ ፡ ያንተን ፡ አስተያየት - - - ስማኝ ፡ ልንገርህ - - - አሁን ፡ አንተ ፡ እንዳረከው ፡ ዓይነት ፡ ለሰው ፡ ስሜት ፡ ለሰው ፡ እምነት ፡ ዋጋ ፡ ሳይ ሰጡ ፡ የሚደረገው ፡ መሻሻል ፡ ባፍንጫዬ ፡ ይውጣ - - መሻሻል - - ?! ልን ገርህ ፡ አንድ ፡ ነገር ! ለማንም ፡ ሰው ፡ ቢሆን ፡ መጀመሪያ ፡ የሚያስፈ ልገው ፡ ፍቅር ፡ መግባባትና ፡ መከባበር ፡ ነው ።— ስንፋቀር ፡ አንድነ ታችን ፡ ሲጸና ፡ ነው ፡ መሻሻል ፡ ሊገኝ ፡ የሚችለው - - ያኔ ፡ መሻሻል ፡ ያላንዳች ፡ ድካም ፡ ከውስጣችን ፡ ይመነጫል ።—መሻሻል ፡ ትለኛለህ፡ ደርሶ ! መጀመሪያ ፡ አንተ ፡ ራስህ ፡ ሰው ፡ ሰው ፡ መስሎ ፡ ይታይህ - - ሰው ፡ ሰው ፡ መስሎ ፡ ሲታይህና ፡ እነሱም ፡ የታየህ ፡ መሆኑን ፡ ሲረዱ ልህ ፡ ነው ፡ የምትለውን ፡ የሚቀበሉህ - - አለበለዚያ ፡ ግን ፡ ጥሩው ፡ ነገርህ ፡ እንኳን ፡ ይጐዳ ፡ ስለሚመስላቸው ፡ ትርፍህ ፡ ድካም ፡ ነው - - የሚሰማህ ፡ አይገኝም - - - መሻሻል ፡ ትለኛለህ ፡ ደሞ - - - ?!

«መሻሻል ፡ እስከዚህ ፡ ደካማ ፡ ናት - - ? እንደዚህ ፡ በመደባበስ ፡ ካልተጠበቀች ፡ በስተቀር ፡ የማትገኝ - - ?

«ብትገኝም ፡ አንተ ፡ የቀየስከውን ፡ መንገድ ፡ ተከትላ ፡ አይደ ለም ።— ፈረንጆች ፡ ገሥጋሾች ፡ ናቸው - - ፈረንጆች ፡ ይሮጣሉ - - ፈረ ንጆች ፡ ይበራሉ - - ፈረንጆች ፡ በጭንቅላታቸው ፡ ወድቀው ፡ አንገታ ቸው ፡ አልተሰበረም - - -

« ያውም ፡ እጨረቃ ፡ ላይ - - - ! » ያደናቅፋታል ፡ አደፍርስ ።

« ፈረንጆች ፡ ኀይለኞች ፡ ጠንካሮች ፡ ናቸው ፡ እያልን ፡ የነ ሱን ፡ መንገድ ፡ ለመከተል ፡ ብንፈልግ ፡ የግሥጋሤውም ፡ የሩጫውም ፡ የበረራውም ፡ ትርፉ ፡ ተደናቅፎ ፡ መደፋት ፡ ነው ።— ባንገት ፡ የማረ ፉን ፡ መልስ ፡ እርግጠኛ ፡ ነኝ ፡ ታውቀዋለህ ።—

«እኔኮ ፡ እንደ ፡ ፈረንጆች ፡ ካልሆንን ፡ መሻሻልን ፡ አናገኝም ፡ አላ ልኩም - - -

«እንግዲያው ፡ እነሱን ፡ እንዳናስተጋባ ፡ ከተስማማን ፡ ራሳችንም ፡ እነሱን ፡ ሆነን ፡ ከመቅረት ፡ ድነናል ፡ ማለት ፡ ነው - - ሌላው ፡ ነገር ፡ አይቸግርም - - -

«ሌላው ፡ ነገር ፡ አይቸግርም ? ምን ፡ ተናገርሽና ፡ ነው ፡ ሌላው ፡ ነገር ፡ አይቸግርሙ - - ?

«አገርህን ፡ ያገርህን ፡ ሰው ፡ እንደ ፡ ባይተዋር ፡ ሳይሆን - -እወጉ ፡ እልማዱ ፡ እቅርሱ ፡ ውስጥ ፡ ገብተህ ፡ ዕወቀው ።-የፈረንጆች ፡ ሐሳብ ፡ ሳይሆን ፡ የራስህ ፡ ሐሳብ ፡ ይኑርህ - - ማንኛውንም ፡ ያገርህን ፡ ችግር ፡ በራስህ ፡ ዓይን ፡ እየው - -አስብበት ፡ አውጠንጥነው ። ጥሩውን ፡ ገና ፡ ለገና ፡ ሰው ፡ በወደደው ፡ አትውደደው - - መጥፎውንም ፡ ሰው ፡ ባጥላላው ፡ አታንጓለው ።- መታረም ፡ እሚገባው ፡ ነገርም ፡ ቢኖር ፡ እውስጡ ፡ ሆነህ ፡ ቀስ ፡ እያልህ ፡ ንቀለው ፡ እንጂ ፡ በንዴት ፡ አትጐድፍረው - - አባዬ ፡ ሁለዜ ፡ ቀስ ፡ ብለሽ ፡ አርሚ— የሚሉ ፡ አነጋገር ፡ አለው - -

«ጋሼ ፡ ጥሶ ፡ ደንበኛ ፡ የገደል ፡ ማሚቶ ፡ ወልዷል ።-ሆኖም ፡ ሲበዛ ፡ ጥሩ ፡ አይደለም— እምልሽ ፡ አንዳንዴ ፡ የራስሽም ፡ አስተያየት ፡ ቢኖርሽ ፡ አይከፋ - - -

«ያመንሁበትና ፡ ከሰውነቴ ፡ የተዋሐደው ፡ አስተያየት ፡ ሁሉ ፡ ምን ፡ ጊዜም ፡ እንደ ፡ ራሴ ፡ ነው - - እለዚያ ፡ የራስ ፡ የሚባለው ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ዋጋ ፡ የለውም— ትርጉም ፡ የለውም - -

ወይዘሮ ፡ ማለፊያ ፡ ጆሯቸውን ፡ ጭምር ፡ በጆቦነው ፡ ራስ ፡ ማሠሪያ ፡ የታሠረውን ፡ ራሳቸውን— ምንም ፡ እንኳ ፡ ከእርጅና ፡ የተነሣ ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ ቢንቀጠቀጥም— ደስ ፡ የሚላቸው ፡ የሚስማሙበት ፡ ነገር ፡ በሰሙ ፡ ቁጥር - በማወዛወዝ - - አክብሮት ፡ ርኅራኄና ፡ ያለጭቅጭቅ ፡ የመታዘዝ ፡ ልማድ ፡ በሚታይባቸው ፡ ደብዛዛ ፡ ዓይኖቻቸው ፡ ትክ ፡ ብለው ፡ እየተመለከቱ ፡ ሲያዳምጧቸው ፡ ከቆዩ ፡ በኋላ ፡ ብድግ ፡ ብለው ፡ መሬት ፡ ድርሶ ፡ የሚክበሰበሰውን ፡ ቀሚሳቸውን ፡ ሰብሰብ ፡ሰብሰብ ፡ በማድረግ ፡ መቀነታቸውን ፡ እያጠባበቁ ፡ ወደ ፡ ጓዳ ፡ ይገቡና ፡ ሁለት ፡ ኩባያ ፡ እርጐ ፡ ይዘው ፡ ይመጣሉ ።— ከንፈሩን ፡ ጠረግ ፡ ጠረግ ፡ በማድረግ ፡ አንዱን ፡ ኩባያ ፡ ለፍሬዋ ፡ ይሰጧታል

«አጥቤ ፡ አጥፌ ፡ ነው ፡ ያስቀመጥሁት ፤ ራሴ ፡ የምጠጣበት ፡ ኩባያ ፡ ነው » ይሏታል ፡ ፍሬዋን—ኩባያውን ፡ እየት ፡ እየት ፡ ስታደርግ ፡ ሲያዩ ።—ሌላውን ፡ ኩባያ ፡ ላደፍርስ ፡ ሲሰጡት —

«የለም ፡ እኔ ፡ አሁን ፡ እርጐ ፡ አልጠጣም ፤ ምሳዬን ፡ አያስበላኝም - - - » ይላቸዋል ።

«ታዲያ ፡ ምሳ ፡ እየበላህ ፡ ጠጣዋ ፡ ምሳ ፡ ላምጣ - - - ! »

«የለም ፡ እቤት ፡ ይጠብቁኛል - - -

«እባክህ ፡ የኔ ፡ ልጅ - - ምንም ፡ አይልህ ፤ ባይሆን ፡ ቀመስ ፡ አር ገህ ፡ ተወው - - ቆራስማ ፡ አትወድ ፡ ይሆን - - ?

«የለም ፥ ለሱ ፡ ብዬ ፡ ሳይሆን - - በሌላ ፡ ጊዜ ፡ ይሻላል - - -

«የምን ፡ በሌላ ፡ ጊዜ - - በሌላ ፡ ጊዜ ፡ ደግሞ ፥ ሌላ ፡ ይገኛል - - ምንም ፡ አይልህ ፡ ግዴለህም - - -

«ይቅርብኝ ፤ ቢቀርብኝ ፡ ይሻላል - - እና ፡ እንዲያውም ፥ ልሂድ ፡ መሰለኝ - - ደኅና ፡ ዋሉልኝ - - -

«ደኅና ፡ ዋልልኛ ! ከደኅና ፡ ምሳህ ፡ ለምን ፡ ላሰናክልህ - - እውነትህን፡ ነው - - » ወደ ፡ ፍሬዋ ፡ ጠጋ ፡ ብለው ፡ እጅዋን ፡ ያዝ ፡ በማድረግ « የኔስ ፡ ልጅ ፡ አልጣፈጠሽ ፡ ይሆን - - ? በርበሬ ፡ መሳይ ፡ ባረግልሽ - - ?

«ምንም ፡ አያስፈልገው ፡ እማዬ ! እንዲሁ ፡ ብቻውን ፡ ሆኖ ፡ በጣም ፡ ነው ፡ የሚጣፍጠው - -

«ወደድሽልኝ ? እንኳን ፡ የወደድሽልኝ - - - ! » እንደገና ፡ ወደ ፡ ጓዳ ፡ ይገቡና ፡ የእርጐውን ፡ ማሰሮ ፡ ይዘው ፡ ይመለሳሉ « ላንድዬ ፡ ምን ፡ ይሳነዋል ! አንድዬ ፡ ያውቃል ! እንዲህ ፡ እንዳንቺ ፡ ልበ ፡ ሰፊዋን ፡ ቢሰ ጠኝ ፡ ምን ፡ ይሳነዋል - - - ? አንድዬ ፡ ያውቃል - - -

# አደፍርስ

ወይዘሮ ፡ አሰጋሽ ፡ በበኩላቸው ፡ ጺወኔን ፡ ሮማንን ፡ አገልጋያቸውን ፡ ጭምር ፡ አስከትለው ፡ ወደ ፡ ጅረት ፡ በመውረድ ፡ ወፍ ፡ ሳይቀምሰው ፡ በፊት ፡ እንደ ፡ ልማዳቸው ፡ በፍል ፡ ውሃው ፡ ከተነከሩ ፡ በኋላ ፡ የሰው ፡ እግር ፡ ዱካ ፡ ያመን ፡ ያመነበትን ፡ ስላች ፡ እየመረጡ ፡ ፍለጋቸውን ፡ ይይዛሉ ። እስከ ፡ ረፋዱ ፡ አጋማሽ ፡ ድረስ ፡ ሲፈልጉ ፡ ይቆያሉ ። ምንም ፡ ዓይነት ፡ ምልክትም ፡ ሆነ ፡ ሌላ ፡ ተስፋ ፡ የሚሰጥ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ አያገኙም ።—ድካም ፡ እየተጫጫናቸው ፡ ሲሄድ ፡ ስጋታቸውም ፡ እየበረታ ፡ ይሄዳል ።—

« በጣም ፡ የደከመሽ ፡ መስለሻል ፤ ሰውነትሽ ፡ ሁሉ ፡ ጥውልግልግ ፡ ነው ፡ ያለው ፡ እማዬ -- » ትናገራለች ፡ ጺወኔ ፡ እየት ፡ ታደርጋቸውና « አንችና ፡ እንኮዬ ፡ ወደ ፡ ቤት ፡ ብትመለሱ ፡ ይሻላል ---

« የራሽን ፡ ሰውነት ፡ ባየሽው --- ትናንት ፡ ጭርስ ፡ እንዳልሽው፡ ዓይነት ፡ የሆንሽ ፡ ነው ፡ የምትመስይው -- ባይታወቅሽም ---

« ግዴለም ፡ እማዬ ፡ ለኔ ፡ አታስቢ ።— ትናንት ፡ ጠራራው ፡ ፀሐይ፡ ነው ፡ ራሴን ፡ ያዞረኝ ።— አሁን ፡ ግን ፡ እንደምታይው ፡ ፀሐይዋ ፡ ገና ፡ እናት ፡ አልደረሰችም -- ለኔ ፡ አታስቢ ፡ ግዴለሽም ---

« ባቦልሽ ! መቆየት ፡ ከፈለገሽ ፡ ምን ፡ እላለሁ ? እኔ ፡ ብሆን ፡ እንዳልሽው ፡ ብመለስ ፡ ይሻላል -- ሻል ፡ ያለኝ ፡ ቁርጥማቴ ፡ ነው ፡ ደሞ ፡ የሚነሣው -- ቢሆንም ፡ ታዲያ ፡ እየጥላው ፡ ዐረፍ ፡ እያላችሁ -- እዎ፡ እሪያውንም ፡ እንድስቅጤውንም ፡ እየተጠነቀቃችሁ ፡ ታዲያ --ኋላ ፡ አይሆንም ---

ትንሽ ፡ ወዲያ ፡ ወዲህ ፡ እያሉ ፡ ፍለጋውን ፡ እንደቀጠሉ ፡ የፀሐዩ ፡ ግለት ፡ እየተሰማቸው ፡ ስለሄደ ፡ እጥላ ፡ ዐረፍ ፡ ይላሉ ፡ ጺወኔና ፡ ሮማን ።— ምንም ፡ ያህል ፡ ጊዜ ፡ ሳይቆዩ ፡ ግን ፡ አከላፋ ፡ ነገር ፡ ቁቂታ ፡ ይሰማሉ ፡ ከወዳረፉበት ፡ መንደር ።—ደንግጠው ፡ በመነሣት ፡ በሩጫና ፡ ርምጃ ፡ ቅልቅል ፡ ወደ ፡ ቤት ፡ እሚወስደው ፡ ስላች ፡ መንገድ ፡ ይጣደፋሉ ።— በዚህን ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ እንግዲህ ፡ ከወደጢሻ ፡ ውስጥ ፡ ሁለት ፡ ጐረ

ምሶች ፡ ብቅ ፡ ብቅ ፡ ይሉና ፡ ጂ.ወኔን ፡ አፈፍ ፡ ጅቡን ፡ የሚያደር
ጓት ።— ሮማን ፡ ቀድማ ፡ ነበርና ፡ አካሄዷ ፡ መለስ ፡ ስትል ፡ ጓደኛ
ዋን — ዱሮ ፡ በቡልኮ ፡ ተጠቅላ ፡ እሰው ፡ ጀርባ ፡ ላይ ፡ ስትፈራገጥ ፡ ትመ
ለከታለች ።— ትጮሃለች - - እንደ ፡ ቁቁታም ፡ ይከጅላታል ።—ጉረም
ሶቹ ፡ ሁለት ፡ ጥይት ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ይተኩሱና ፡ እግሬ ፡ አውጭኝ ፡ ይላ
ሉ ።— ሮማን ፡ የምትሆነውን ፡ የምታረገውን ፡ እንዳጣችው ፡ እገላጣና ፡
አዳጋ ፡ ምፍራ ፡ ላይ ፡ ትደርሳለች ።— ውጭ ፡ ነፍስ ፡ ግቢ ፡ ነፍስ ፡ ድን
ገት ፡ ኀይል ፡ ትገዛለች ።—ቁቁታውን ፡ በረጅሙ ፡ ትለቀዋለች ።—እን
ድም ፡ ሰው ፡ ግን ፡ አልደረሰላትም ።— ቀድሞ ፡ የጀመረው ፡ የመንደሩ ፡
ቁቁታ ፡ ነበር ፡ የሚያስተጋባ ፡ የመሰለው — ላገሬው ።— እንዳበደ ፡ እየ
ከነፈች ፡ ቤት ፡ ስትደርስ ፡ ነው ፡ ኋላ ፡ ሁኔታው ፡ የሚታወቀው ።—

አስቀድሞ ፡ ወደ ፡ መንደሩ ፡ ገደማ ፡ ቁቁታውን ፡ የጀመሩት ፡ ግን ፡
ወይዘሮ ፡ አሰጋሽ ፡ ነበሩ ። ከነጂ.ወኔ ፡ ተለይተው ፡ እቤት ፡ እንደ ፡ ደረሱ ፡
የጕርፉን ፡ ጠመንጃና ፡ ዝናር ፡ እተሰቀለበት ፡ ቢመለከቱ ፡ ስላጡት ።—
እንዲጋጣሚ ፡ ፖሊሶችና ፡ ነጭ ፡ ለባሾች ፡ ፈጥነው ፡ ይደርሱላቸውና ፡
ቁቁታቸው ፡ እየደከመ ፡ እየደከመ ፡ ይሄዳል - - ቀስ ፡ በቀስ ፡ ያዘው ፡ ያዘው
ለሚል ፡ አገር ፡ ምድሩን ፡ ለሚሞላው ፡ ጩኸት ፡ እየለቀቀ ።— የተኩስ ፡
መለዋወጥ ፡ ይጀምራል ። ትንሽ ፡ ቆይቶ ፡ ይፋፋማል ።—ቀዬው ፡ በሙሉ
ይሸበራል ፡ ላንዳፍታ ።— ወዲያው ፡ ግን ፡ የሚተኮሰው ፡ ጥይት ፡ ብዛት፡
እየተቀነሰ ፡ ድምፁም ፡ እየራቀ ፡ እየራቀ ፡ ይሄዳል ።—ወደ ፡ ተሲያቱ ፡ ገደማ ፡
ጭራ ፡ ሜዳ ፡ በታች ፡ እሚገኘው ፡ ሸለቆ ፡ ውስጥ ፡ ይደርሱባቸዋል ፡ ወን
ጀለኞቹን ።—እምጥ ፡ ይግቡ ፡ ስምጥ ፡ ግን ፡ ሊያገኟቸውም ፡ ሆነ ፡ ሊይ
ዟቸው ፡ አልቻሉም ። ጕርፉና ፡ ጓደኞቹ ፡ ያመልጣሉ ፡ ለጊዜው ።—ጂ.ወ
ኔን ፡ ቢሆን ፡ ያፍዝ ፡ ያደንግዝ ፡ የደገሙባት ፡ ይመስል ፡ ተጠቅላበት ፡
እነበረው ፡ ቡልኮ ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ተቀመጠች ፡ ያገኟታል ።— የባሻገሯን ፡
ስትመለከት ። — እመኪና ፡ መንገድ ፡ ዳር ፡ ይባባላሉ ፡ ሁለት ፡ ቄሶች ፤
በርግጫና ፡ በጡጫ—የተሰረቀችውን ፡ የማርያምን ፡ ታቦት ፡ አጠገባቸው፡
ቁጭ ፡ አርገው ።—እንኳን ፡ አርማኒያ ፡ አዲሳባም ፡ ወስደህ ፡ አትተክላት፡
የኛን ፡ ማርያም ፡ እያለ ፡ ትንፍስ ፡ ትንፍስ ፡ ይላል ፡ አንደኛው ፡ ቄስ ።—
ከገበያ ፡ የምትመለስ ፡ ሴት ፡ ቆም ፡ ብላ ፡ ነገራቸውን ፡ ታዳምጥና ፡
የተሸከመችውን ፡ የሸመታ ፡ እህል ፡ አውርዳ ፡ ጥላ ፡ በቦታው ፡ ታቦቷን ፡
እዝል ፡ አድርጋ ፡ ቁልቁል ፡ ትመነጠቃለች - - ወደ ፡ ተሰረቀችበት ፡
ቀበሌ « እንዴታ ! የማንን ፡ ማርያም ፡ ማን ፡ ይሰርቃታል ! » እያ
ለች።—ቄሶቹ ፡ በባዶ ፡ ሜዳ ፡ ይፍረመረማሉ ።—

# ፵፱

## አደፍርስ

« አይ ፡ እ - - ! » ይላል ፡ ያምሳ ፡ አለቃው ፡ ለወይዘሮ ፡ አሰጋሽ ፡ ሲያወራ « ይኸው ፡ ሚካኤል ፡ ምስክሬ ፡ ነው - - የርስዎን ፡ ልጅ ፡ ለመ ጥለፍ ፡ ማሰቡን ፡ አጫውቶኝ ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ - - -

« እረዳው ፡ ነበር ፡ እንዳትለኝ - - - ! !

« ወንድ ፡ ነውኮ ፡ ጐርፉ ! ባለ ፡ ሱሪ ፡ ነው ! ዋይ ፡ ነዶ ! ምን ፡ ይሆናል ፡ ብቻ - - ሰኔና ፡ ሰኞ - -

« አንድ ፡ ገዳይ ፡ ተሰቀለ ፡ አሉ ፡ ዛሬ — ደብረሲና - - የምናው ቀው ፡ ሰው ፡ ይሆን - - ሰምተህ ፡ እንደሁ ? አዎን ፡ አዎን - - ምንድ ነው ፡ የሚከነክነኝኮ ፡ ብያለሁ - - ዋናውን ፡ ነገር ፡ ረስቼው ፤ ጠላ ፡ መጠ ጫችሁን - - » ሁለት ፡ ብር ፡ የያዘ ፡ እጃቸውን ፡ ዘርጋ ፡ አድር ገው « እንካልኝ ፡ ወንድሜ - - -

« አፈር ፡ ልጠጣ - - ደሞ ፡ የምን ፡ ጠላ - - ደሞ ፡ የምን ፡ ጠላ - - ! » ሰውነቱ ፡ ልውጥውጥ ፡ ይላል ፡ ያምሳ ፡ አለቃው « አፈር ፡ ልጠ ጣ - - አፈር ፡ ልጠጣ ! !

« ምነው ፡ ያምሳ ፡ አለቃ ! ግዴታ ፡ የለብህምኮ - - እኔ ፡ በሰ ጠሁ ፡ ያንተ ፡ መንገሽገሽ - - -

« አፈር ፡ ልጠጣ ፡ አልኩዎት - - - !

« የሚጥምህን ፡ የምታውቀው ፡ ራስህ ፡ ነህ - - እንዴ ! አሰጋሽ ፡ ነኝኮ ! ማን ፡ መሰልኩህ - - ? ግዴለህም ፡ ፋከራ ፡ ፈርቶ ፡ ሀብቱን ፡ የሚበትን ፡ የለም - - ለወደፊቱ ፡ እንጠነቀቅበታለን - - ደግሞም ፡ አሰ ጋሽ ፡ ወንድ ፡ ብርቋ ፡ አይምሰልህ— ስንቱን ፡ ጀግና ፡ ነው ፡ የምታስረግ ደው ።— ስንቱን ፡ ስንቱን ፡ ጀግና - - -

« እረ ፡ እባክዎ ፡ የትና ፡ የት ! ወንድ ፡ ቢባል ፡ ወንድ ፡ አይደለም - - ጥይት ፡ እንደ ፡ ዝናብ ፡ ሲወርድ ፡ ግምባሩን ፡ የማይመልስ ፡ ነው ፡ ጐር ፉ - - - በራሳ ፡ ነቀልቃል - - -

« እባክህ ፡ ምነው ፡ ያምባ ፡ ገነን ፡ ጨዋታህን ፡ አታምጣ ፡ የመንግሥት ፡ ወታደር ፡ ሆነህ - - የወንድ ፡ ልጅ ፡ ሙያው ፡ በልቡ ፡ ነው - - የምን ፡ ራሳ ፡ ነው ፡ ደሞ ፡ ሥራ ፡ ቤት ፡ ይመስል - - ጌታውን ፡ ተከትሎ ፡ የወረደ ፡ ሁሉ ፡ ወግ ፡ ነው ፡ ይኸ - - -

« አከላፋ ፡ ሆንበቲኮ ! ጀምበር ፡ ሳትጠልቅ ፡ ያገኙት ፡ ነበር ፡ የወንድን ፡ ልክ - - -

« ለወደፊቱ ፡ እንጠነቀቅበታለን - - ፍልውሃ ፡ ብሎ ፡ ነገር - - ባፍንጫዬ ፡ ይውጣ - - በቀዬውም ፡ አታያት ፡ ሁለተኛ ፡ አሰጋሽን - -

« ምን ፡ ይሆናል ፡ ብቻ - - ቀረ - - !

«አትድከምኮ ፡ አልኩህ - - ትርፍ ፡ ነገር ፡ አትናገር - - ቀማኛ ፡ አጥፋ ፡ እንጂ ፡ ቀማኛ ፡ አበረታታኮ ፡ አላሉህም ፡ ንጉሡ - - ላቶ ፡ ጥሶ ፡ ነው ፡ ወጥቼ ፡ የምነግርልህ ፡ ቆይ - - -

« ቀረ ፡ ነገር - - ብቻ - - ምን ፡ ያረጋል - - -

« የሮቢን ፡ ዘብጥያ ፡ አብራችሁ ፡ ነው ፡ የምትገቡባት ፡ አርፈህ ፡ ካልተቀመጥህ - -

« እሳት ፡ ውስጥም ፡ በገባሁ - - እሳት ፡ ውስጥ ፡ እልዎታለሁ - - የልቡን ፡ አድርሶ ፡ በሆነና - - -

« በሚካኤል ፡ ይገርሃለሁ - - በኃይለ ፡ ሥላሴ - - በቃህ - - ይበቃሃል - - አትናገርኝ - - አትናገረኝ - - -

ጺወኔ ፡ ቡልኮውን ፡ አጣጥፋ ፡ እድብኝት ፡ ውስጥ ፡ ታስቀምጠዋለች ።— የተጠለፈችበትን ።—

# ፺

## አደፍርስ

የቀኑን ፡ ሁኔታ ፡ የሚያስላስሉ ፡ ይመስል ፡ ሦስቱም ፡ በአርምሞ ፡ ይቆዩና —

«እናት ፡ ለልጅዋ ፡ መድኀኒት ፡ ስታጠጣ ፡ መጀመሪያ ፡ ራሷ ፡ መድኀኒቱን ፡ ቀምሳ ፡ ነው ። አልታመመችም ።— የመድኀኒትም ፡ ቀመሰ ፡ ቅንጦት ፡ የለውም ። ለምን ፡ ይመስልሃል ፡ እንዲያ ፡ የምታደርገው - - ? » በማለት ፡ ይጀምራሉ ፡ አቶ ፡ ጥቦ ።-

«ራሷን ፡ በማታለል ፡ ልጁም ፡ የተታለለ ፡ ስለሚመስላት - - - » ይመልሳል ፡ አደፍርስም ፡ ቶሎ ፡ ይነቃና ።—

«የለም ፡ ራሷን ፡ አላታለለችም ፤ ዐውቃ ፡ የምታደርገው ፡ ድርጊት ፡ ትሊያ ፡ ሊሆን ፡ አይችልም - - ሳታውቀው ፡ ብታደርገው ፡ ነበር ፡ ራሷን ፡ አታለለች ፡ ልንል ፡ የምንችለው ።—ልጁም ፡ ቢሆን ፡ የተታለለ ፡ መስሏት ፡ አይደለም ፤ ልቧ ፡ ያውቀዋል ፡ እንዳልታለለ ።— መድኀኒቱ ፡ በሽታውን ፡ እንደሚያድነው ፡ ታውቃለች ።—ስለዚህ ፡ ዐውቆ ፡ ያልተቀበለውን ፡ በሽታ ፡ ሳያውቅ ፡ አስወገደው ፡ እንጂ ፡ አልታለለም - - -

«እናቲቱ ፡ ባትቀምሰው ፡ ኖሮ ፡ ልጁ ፡ መድኀኒቱን ፡ አይጠጣም ፡ ነበር ፡ ለማለት ፡ ነው ፤ ወይስ ፡ እናቲቱ ፡ በመቅመሷ ፡ ልጁ ፡ የማይጥመውን ፡ መድኀኒት ፡ ይጠጣል ፡ ለማለት ፡ ነው ፡ ያሁኑ ፡ ሐሳብህ - - ?

«ሁለቱም ፡ ጥያቄዎችህ ፡ ለማለት ፡ የምፈልጋቸውን ፡ ጥቃቅን ፡ ነቁጦች ፡ ይዘዋል - - ለማለት ፡ ወደምፈልገው ፡ ግን ፡ በሙሉ ፡ አይመሩም ።— እናቲቱ ፡ ባትቀምሰውም ፡ ልጁ ፡ መጠጣቱ ፡ አይቀርም ፤ ግን ፡ እየፈራ ፡ እያንገፈገፈው ፡ እየተጨነቀ ፡ አንዳንዴም ፡ እያለቀሰ ፡ ነው ፡ የሚጠጣው ።—እናቲቱ ፡ አስቀድማ ፡ በመቅመሷ ፡ ግን ፡ ፍራት ፡ አይኖርበትም ፤ አይጨነቅም ፤ አያለቅስም - - ቢያንገፈግፈውም ፡ እንኳ ፡ እናቱን ፡ ስትንገፈገፍ ፡ ስላላያት ፡ ይችለዋል ።—ሳትታመም ፡ ታምማ ፡ መድኀኒቱን ፡ የቀመሰችለት ፡ የናቱ ፡ ፍቅር ፡ ጥንካሬን ፡ ይሰጠዋል - - -

«ሳትታመም ፡ መታመሟን ፡ ያውቀዋል ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ልጄ - - ?

«ልጄ ፡ ምናልባት ፡ የሚያውቀው ፡ ነገር ፡ ቢኖር ፡ እንደሱ - - የታመመች ፡ መሆኗን ፡ ነው - - -

«ስለዚህ ፡ ታዲያ ፡ በስሕተት ፡ መንገድ ፡ መራችው ፡ ማለት ፡ ነዋ - - !

«አልመራችውም - - የታመመች ፡ በመምሰል ፡ ከልጅዋ ፡ ጋር ፡ ያላትን ፡ የመንፈስና ፡ የድርጊት ፡ አንድነት ፡ ገለጸች ፡ እንጂ ፡ ወደ ፡ ስሕተት ፡ መንገድ ፡ መራችው ፡ ለማለት ፡ አንችልም - - ለልጅዋ ፡ እሱ ፡ ባለበት ፡ ሁኔታ ፡ ላይ ፡ ያለች ፡ ሆና ፡ በመታየት ፡ እናታዊ ፡ ፍቅሯን ፡ ገለጸች ፡ እንጂ ፡ ወደ ፡ ስሕተት ፡ መንገድ ፡ አልመራችውም - - -

«እንደምሰማውኮ ፡ አሁን ፡ በአንተ ፡ አስተያየት ፡ የማልፈልገውን ፡ የማይጥመኝን ፡ ነገር ፡ ለፍቅርና ፡ መስሎ ፡ ለመታየት ፡ ስል ፡ ማድረግ ፡ አለብኝ ፡ ማለት ፡ ነው - - -

«ለፍቅርና ፡ እምነትን ፡ ለማትረፍ ፡ አንድነትህን ፡ ለማሳየት ፡ ማድረግ ፡ ይኖርብሃል - - -

«ዛሬ ፡ በምሳ ፡ ሰዓት ፡ ያደረገውን ፡ ብትሰማ ፡ አባዬ - - -» ትናገራለች ፡ ፍሬዋ ፡ ክርክራቸውን ፡ ስታዳምጥ ፡ ትቆይና - - -

«ምን ፡ አደረግሁ ፤ ምሳዬን ፡ አያስበላኝም ፡ አሁን ፡ እርጎ ፡ አልጠጣም ፡ ማለት ፡ ነውር ፡ ነው - - - ?

«የበላይ ፡ እናትኮ ፡ ናቸው - - እንዴት ፡ ይመስልሃል ፡ አባዬ ፡ አንጀታቸው ፡ ቁርጥ ፡ ያለው ።—ልጄ ፡ ልጄ ፡ እያሉ ፡ እንዲያ ፡ ሲለምኑት ፡ ምሳዬን ፡ አያስበላኝም ፡ ብሎ ፡ እምቢ ፡ ብሏቸው ፡ ሄደ - - - ደግሞ ፡ ስለጨሊያቸውስ ፡ ያመጣኸው ፡ ክርክር - - -

«ጨሌ ፡ በማጥለቃቸው ፡ ተቆጥተህ ፡ ይሆናል - - -» አቶ ፡ ጥሶ ፡ ቀስ ፡ ብለው ፡ ይጠይቃሉ ።—

«መቆጣት ፡ አንድ ፡ ቃል ፡ እንዲያውም ፡ እርጎ ፡ አልጠጣ ፡ ያለው ፡ በጨሌው ፡ ምክንያት ፡ ተቆጥቶ ፡ መስሏቸው ፡ እሳቸው - - -

«ብጠጣ ፡ ኖሮ ፡ መቆጣቴ ፡ አይታወቃቸውም ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ባንቺ ፡ ቤት - - -

«አይታወቃቸውም ፤ ወዲያውኑ ፡ ነበር ፡ የሚረሱት - - -

« - - ዛሬ ፡ የየከተማውስ ፡ ልጆች ፡ ያነግቱት ፡ የለም ፡ ጨሌውን - - ?» ብለው ፡ በመጠየቅ ፡ ይጀምራሉ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ አቶ ፡ ጥሶ ።

«ታዲያ ፡ እነሱ ፡ ቢያነግቱት ፡ ለጌጥ ፡ እንጂ ፡ ለአምልኮት ፡ አይ ደለም---» ይመልሳል ፡ አደፍርስም ፡ በጀመረው ፡ መንገድ ፡፡—

« ምን ፡ ማለትህ ፡ ነው ፡ ለአምልኮት ፡ አይደለም ፡ ስትል---እግ ዚአብሔር ፡ በጌጥ ፡ በውበት ፡ አይገለጥም---?

«ማለቴ ፡ ማር ፡ ጐዝጉዘው ፡ ገንፎ ፡ አገንፍተው ፡ ድፍን ፡ ቡና ፡ ቆርጥመው ፡ አይማጠኑትም---

« ምኑን ፡ ነው ፡ የማይማጠኑት---?

«ጨሌውን !

«--ጽዱ ፡ ለብሰው ፡ ሽቶ ፡ ተቀብተው ፡ ጨሌውን ፡ በአንገታቸው ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ በጃቸውም ፡ ዙሪያ ፡ አድርገው ፡ ቤተክሲያን ፡ የሚ ስሙ ፡ አላየህም---?

«ጨሌውን ፡ እንደ ፡ ጌጥ ፡ በማሠራት ፡ አድርገው ፡ ቤተክሲያን ፡ የሚስሙ ፡ አይቻለሁ---

« ጌጣቸው ፡ ይመስልሃል ፡ እምነታቸው ፡ ብዙ ፡ ሕዝብ ፡ ወደሚ ሰበሰብበት ፡ ቤተክሲያን ፡ የሚስባቸው---?

«የሚስባቸው ፡ ስትል ፡ ምን ፡ ማለትህ ፡ ነው---?

« የሚመራቸው ፡ ማለቴ ፡ ነው---

«እንግዲያው ፡ ጌጣቸውም ፡ እምነታቸውም ፡ ነው ፡ እላለሁ ፡ ወደ ፡ ቤተክሲያን ፡ የሚመራቸው---

« በተለይ ፡ ሴቶች ፡ ጌጣቸውን ፡ ውበታቸውን ፡ ለማሳየት ፡ የሚ ጥሩ ፡ አይመስልህም---?

«ያው ፡ ነው ፤ ወንዶችም ፡ ቢሆኑ ፡ ይጥራሉ---

« ጥሩ ፡ ነው ፤ ወንዶችም ፡ የማሳየት ፡ ፍላጐት ፡ ይኑራቸው ፡ እን በል--አያጣላንም--ብቻ ፡ እንግዲህ ፡ ወንዶችም ፡ ይሁኑ ፡ ሴቶች ፡ የማሳየት ፡ ፍላጐት ፡ አላቸው ፡ ማለት ፡ ነው---

«አዎ ፡ አላቸው---

«--ጌጣቸውን ፡ ወይም ፡ ውበታቸውን ፡ ወይንም ፡ ሁለቱንም ፡ የማ ሳየት ፡ ፍላጐት ፡ ካላቸው ፡ ዘንድ ፡ ይህን ፡ ፍላጐታቸውን ፡ ለማርካት ፡ ሲሉ ፡ ቤተክሲያን ፡ መሄዳቸውን ፡ ስታይ ፡ ጌጡ ፡ እነሱ ፡ ካሰቡት ፡ በላይ ፡ ዋጋ ፡ ያለው ፡ አይመስልህም---?

«ሰው ፡ እተሰበሰበበት ፡ ቦታ ፡ እንዲሄዱ ፡ በማድረግ ፡ ቤተክሲያን ፡ ስላሳማቸው --- አዎ ፡ ይኸን ፡ እንደ ፡ ዋጋ ፡ ከቆጠርከው --- ካሰቡት ፡ በላይ ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ---

«ታዲያ ፡ እነዚህ ፡ ሰዎች ፡ ጌጡን ፡ አይማጠኑትም ---

«አይማጠኑትምኮ ፡ ብያለሁ ---

«ባላሰቡትም ፡ መንገድ ፡ ቢሆን ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ደጅ ፡ አድርሷቸዋል ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ግን ---

«አድርሷቸዋል ፤ ግን ፡ የልብን ፡ የሚያውቅ ፡ አምላክ ፡ በርግጥ ፡ የሄዱበትን ፡ ስለሚያውቀው ፡ በዚህ ፡ አይደለልም ---

«ቤተክሲያን ፡ እየሄዱ ፡ በሙሉ ፡ ልባቸው ፡ ገብረኤል ፡ ሚካኤል ፡ አንተ ፡ ታውቃለህ ፡ የሚሉትንም ፡ ጭምር ፡ እግዚአብሔር ፡ ይከፋባቸዋል ፡ ማለትህ ፡ ነው -- ?

«ለምን ፡ ይከፋባቸዋል ፤ ገብርኤል ፡ ሚካኤል ፡ ማለት ፡ አምልኮ ፡ ባዕድ ፡ አይደል --- ?

«ለምን ፡ አይደለም ? ቤተክሲያን ፡ ሄደው ፡ እግዚአብሔርን ፡ በማመስገን ፡ ፈንታ ፡ ገብርኤልንና ፡ ሚካኤልን ፡ ሲያመሰግኑ -- ? እኔ ፡ አምላካችሁ ፡ ቀናተኛ ፡ ነኝ ፡ ብሎ ፡ የለም ፡ እንዴ --- ?

«እግዚአብሔር ፡ የልባቸውን ፡ ያውቀዋል ።—ከአክብሮታቸው ፡ የተነሣ ፡ ራሳቸውን ፡ ዝቅ ፡ አድርገው ፡ በመላእክቱ ፡ በኩል ፡ እንጂ ፡ ቀጥታ ፡ እንዳይማጠኑ ፡ ያደረጉት ፡ መሆኑን ፡ ያውቀዋል ---

«ስለዚህ ፡ እግዚአብሔር ፡ በሰው ፡ ዘንድ ፡ ሙሉ ፡ ልብ ፡ መስሎ ፡ ከሚገመተው ፡ ባላይ ፡ ነው -- የልብ ፡ ልብ ፡ ሕልማችንን ፡ ጥረታችንን ፡ ዓላማችንን ፡ ያውቀዋል ፡ ማለት ፡ ነው ---

«አዎ ፡ ያውቀዋል ---

«እግዚአብሔር ፡ ባጭር ፡ ቁመት ፡ በጠባብ ፡ ደረት ፡ ተወስኖ ፡ በልጁ ፡ በየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ታውቋል ፡ ብለን ፡ እናምናለን ---

«አዎ ፡ እናምናለን ----

« በራሱ ፡ ፈቃድ ፡ ሊገባን ፡ በሚችል ፡ በተወሰነ ፡ ነገር ፡ ባይገለጽ ፡ ኖሮ -- ዘመን ፡ ሳይቆጠር ፡ ዓለም ፡ ሳይፈጠር ፡ የነበረን ፡ ወደፊትም ፡ የሚኖር ፡ እግዚአብሔርን ፡ እንዲህ ፡ ነው ፡ ብለን ፡ ለመገመት ፡ ባልተቻለንም ፡ ነበር ----

«አንችልም ፡ ነበር - - -

«ወሰን ፡ የሌለው ፡ ሐሳብ ፡ በመጠኑ ፡ በቃላት ፡ እንደሚገለጽ ፡ ሁሉ ፡ መጀመሪያና ፡ መጨረሻ ፡ የሌለው ፡ እግዚአብሔርም ፡ መጀመሪያና ፡ መጨረሻ ፡ ባለው ፡ በየሱስ ፡ ተገልጾ - - ፎርም ፡ የሌለው ፡ በፎርም ፡ ታወቀ - - - -

«ይኸ ፡ ሁሉ ፡ እርግጥ ፡ ነው - - - ማለቴ ፡ ይገባኛል - - -

«ጥሩ ፡ እንግዲያው - - እስካሁን ፡ ጨሌ ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ እግዚአብሔር ፡ የሚመራ ፡ ጌጥ ፡ ቤተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ የሚመራ ፡ ቦታ ፡ በመሆኑ ፡ ተስማምተናል - -

«አዎ ፡ ተስማምተናል - - -

«የበላይ ፡ እናት ፡ በጨሌ ፡ በቤተ ፡ እግዚአብሔር ፡ በእግዚአብሔር ፡ እንደሚያመልኩ ፡ ነግረውታል ፡ ብላኛለች ፡ ፍሬዋ - - -

«አዎ ፡ ነግረውኛል - - -

«ታዲያ ፡ ጨሌው ፡ በቅርብ ፡ ቤተ ፡ እግዚአብሔሩ ፡ በሩቅ ፡ ወሰን ፡ የለሹን ፡ እግዚአብሔርን ፡ ወስኖ ፡ ለማወቅ ፡ የሚያደርጉት ፡ ጥረት ፡ ላለመሆኑ ፡ ምን ፡ ማስረጃ ፡ አለህ ? ደግሞስ ፡ ወሰን ፡ የሌለው ፡ እግዚአብሔር ፡ በብዙ ፡ ጥቃቅን ፡ ወሰን ፡ አለሽ ፡ ነገሮች ፡ መገለጹ ፡ ለምን ፡ እንግዳ ፡ ነገር ፡ ይሆንብሃል ? እግዚአብሔር ፡ የልብ ፡ ልብን ፡ ያውቃል ፡ ብለናል - - - ካወቅነው ፡ ዘንድ ፡ በጨሌው ፡ እንጂ ፡ በኔ ፡ አላመለኩም ፡ ብሎ ፡ የሚከፋው ፡ ይመስልሃል ? እርግጥ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከዘመንና ፡ ከወሰን ፡ ውጪ ፡ ነው ።- ነገር ፡ ግን ፡ ለሙሴ ፡ በእሳት ፡ ምላስ ፡ ተገልጿል ።- ለአብርሃም— በተራራ ፡ በግ ፡ ተመስሎ ፡ መከራና ፡ ጭንቁን ፡ አሳልፎለታል ።— ለሐዋርያት ፡ ከድንግል ፡ ማርያም ፡ በመወለድ ፡ ሰው ፡ ሆኖ ፡ የሰውን ፡ ልጅ ፡ ኀጢአት ፡ ዋጅቷል— ዛሬም ፡ በዘመናችን ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ በሚሠራው ፡ አስደናቂ ፡ ፈጠራ ፡ እየተገለጸ ፡ እናያለን - - ስለዚህ ፡ ወሰን ፡ የሌለው ፡ እግዚአብሔር ፡ ቁጥር ፡ በሌላቸው ፡ ውሱኖች ፡ ሲገለጥ - - ወሰን ፡ ያለውና ፡ ወሰን ፡ የሌለው ፡ ፎርም ፡ ያለውና ፡ ፎርም ፡ የሌለው ፡ ሆኖ ፡ ዘለዓለማዊነቱን ፡ አጽንቶ ፡ ይኖራል - - - -

«ስለዚህ ፡ በጨሌ ፡ ማመንን ፡ ትደግፋለህ ፡ ማለት ፡ ነው - - ?

«ቆይ ፡ አስጨርሰኝ - - ! ስለዚህ ፡ ማንኛውም ፡ ሰው ፡ እንደ ፡ ተፈጥሮ ፡ ችሎታው - - ወሰን ፡ የሌለውን ፡ ወሰን ፡ ባለው— ወይም ፡

ጣጣ ፡ ፈንጣጣ ፡ ሳያበዛ ፡ እግዚአብሔርን ፡ በወሰን ፡ የለሽነቱ ፡ የማም ለክ ፡ መብት ፡ ያለው ፡ ይመስለኛል ---

«እኮ ፡ በጨሌ ፡ ማምለክም ፡ በተወሰነ ፡ ነገር ፡ እንደ ፡ ማምለክ ፡ ስለሆነ ፡ ይደገፋል ፡ ማለት ፡ ነው ---

«ባልደግፈውም ፡ አልቃወመውም ።— የኔ ፡ በወሰን ፡ የለሽነቱ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ማመን ፡ ከነሱ ፡ በውሱኑ ፡ ነገር ፡ እግዚአብሔርን ፡ ለማግኘት ፡ መሞከር ፡ ይበልጣል ፡ ወይም ፡ ይሻላል ፡ ብዬ ፡ አልናገርም ---

«ካልተቃወምከው ፡ እንዴት ፡ አድርገህ ፡ ወደ ተሻለው ፡ መንገድ ፡ ልትመራቸው ፡ ትችላለህ ---?

«አንደኛ ፡ ነገር ፡ እኔ ፡ የኔው ፡ መንገድ ፡ ይሻላል ፡ አላልኩም ፡ ሁለተኛ ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ ቢሆን ፡ ራሱ ፡ ለራሱ ፡ እንዲመራመር ፡ እንጂ ፡ የኔን ፡ መንገድ ፡ እንዲከተል ፡ አልፈልግም ---

«ታዲያ ፡ እንግዲህ ፡ በዚህ ፡ ዓይነት ፡ የጥንታውያኑን ፡ አድራጐት ፡ ብቻ ፡ እያደነቅን ፡ ከተቀመጥን— እንዴት ፡ ልንሻሻል ፡ እንችላለን --- ባሁኑ ፡ ጊዜ ፡ የኛ ፡ ትግል ፡ ከዘመኑ ፡ ጋር ፡ የሚስማማውን ፡ መምረጥ ፡ ሲሆን ፡ በየጊዜው ፡ በሆነ ፡ ባልሆነው ፡ ተጠየቅ ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ ብንመለስ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ የሚጨበጥ ፡ ነገር ፡ እናገኛለን ---?

«ስማሆይ ፡ አደፍርስ ! ከዘመኑ ፡ ጋር ፡ የሚስማማውንማ ፡ ሁሉ ፡ እንምረጥ ፡ ካልን ፡ ሰብእናችንን ፡ ድራሹን ፡ አጠፋነው ፡ ማለት ፡ ነው ። ደግሞስ ፡ ያለፈውን ፡ አልፏል ፡ በማለት ፡ ብቻ ፡ እንዴት ፡ ልንረሳው ፡ እንችላለን ? ባለፈው ፡ ጊዜ ፡ እውነት ፡ የነበረ ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ዛሬም ፡ እውነት ፡ መሆኑ ፡ እንዴት ፡ ይካዳል ? እውነት ፡ አያረጅም ፡ አይጠፋም ፡ አደፍርስ ፤ እውነት ፡ ዘለዓለማዊ ፡ ነው ።— እንኳን ፡ እውነት ፡ እውነት ፡ ያለው ፡ ሰውም ፡ አያረጅም ፡ አይሞትም -- እምነቱ ፡ እውነቱ ፡ በልጅ ፡ ልጆቹ ፡ ነቅቶ ፡ ሕያው ፡ ሆኖ ፡ ይኖራል ---

«ታዲያ ፡ ቢሆንስ ፡ እንዲያው ፡ አልባሌው ፡ ነገር ፡ ውስጥ ፡ ሁሉ ፡ ሁሌ ፡ እውነትና ፡ ትምነት ፡ አሉዋይ ፡ እያልን ፡ የኋሊት ፡ በመመልከት ፡ መከራችንን ፡ ከምናይ ፡ ለምን ፡ እኛ ፡ የእምነትና ፡ እውነት ፡ ትውልዶች ፡ በምናደርገው ፡ ድርጊት ፡ ሲገለጽ ፡ አይታይም --?

«--ትናንሹን ፡ እውነት ፡ ከናቃችሁ ፡ ትላልቁን ፡ ለማክበራችሁ ፡ ምን ፡ ዋስትና ፡ ይኖረናል ---? በተወሰነው ፡ ተግባራችሁ ፡ ጥሩ ፡ ነገር ፡ ካልታየ ፡ በወሰን ፡ የለሽ ፡ ሐሳባችሁ ፡ ፋይዳ ፡ ትሠራላችሁ ፡ እምነትና ፡ እውነትን ፡ ታበሥራላችሁ ፡ ብለን ፡ እንዴት ፡ ዝም ፡ ብለን ፡ እንያችሁ ? ስማኝ ፡ አደፍርስ -- የእምነትና ፡ የእውነት ፡ ውጤቶች ፡ ነን ፡ ከማለት ፡ ይልቅ ፡ ከጥቃቅኑ ፡ ድርጊታችሁ ፡ ጀምሮ ፡ የሆናችሁ ፡ መሆናችሁን ፡ የሚያሳይ ፡ ምስክር ፡ እንዲኖር ፡ ያስፈልጋል --» እያሉ ፡ ብድግ ፡ ብለው ፡ ወደ ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ይገባሉ ።— አደፍርስም ፡ ይከተላቸዋል—ተዋሥኦቱ ፡ እንዲቋረጥበት ፡ ያልፈለገ ፡ በሚመስል ፡ ሁኔታ ።—

## ፵፩

# አደፍርስ

«ለመሆኑ ፡ ጋሼ ፡ ጥሶ ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ ልጠይቅህ - - - መቼም ፡ ባህላችንን ፡ ከመረመርን ፡ ጥሩ ፡ ጥሩ ፡ እውነትና ፡ እምነት ፡ ይገኝባቸ ዋል ፡ የሚል ፡ አስተሳሰብ ፡ ስላለህ— ምናልባት ፡ መልስ ፡ ይኖርህ ፡ ይሆናል - - » እያለ ።—

«አይ ፡ መልስም ፡ ባይኖረኝ ፡ እውነት ፡ ያጣሉ ፡ ብዬ ፡ አላምንም - - -

«እሺ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ነገሥታት ፡ የሰሎሞን ፡ ዘሮች ፡ ናቸው ፡ በሚ ለው ፡ ታሪክ ፡ ትስማማለህ ? ታምንበታለህ - - ?

«እንዴታ - - መስማማቱን ፡ ተወውና ፡ በርግጥ ፡ አምንበታለሁ ።— የሰሎሞን ፡ ዘር ? ! ከሰማይ ፡ በታች ፡ ከምድር ፡ በላይ ፡ ለሰሎሞን ፡ ያል ተገለጸ ፡ ጥበብ ፡ እንዳልነበረ ፡ አታውቅም ፡ እንዴ - - - ?

«እኮ ፡ ስለ ፡ ንግሥተ ፡ ሳባ - - ስለ ፡ ቀዳማዊ ፡ ምኒልክ - - ስለ - - -

«ምን ፡ አስዘረዘረህ ? አትድከም ፤ አምንበታለሁ ፡ ብየሃለሁ - - -

«ምክንያት ፡ እንዳለህ ፡ ልትነግረኝ ፡ ትችላለህ - - ?

«ምክንያት ? አዎ ፡ ምክንያት ፡ አላጣም - - ? ለእምነት ፡ ምክንያት ፡ ያስፈልጋልም ፡ ብዬ ፡ ባላምን - - ብቻ ፡ በመላ ፡ ምቴ ፡ ከተስማማህ - - -

«መላ ፡ ምትህ ፡ ምንድነው - - ?

« ከዚህ ፡ በፊት ፡ አብዛኛው ፡ የምናምንበት ፡ ነገር ፡ በራሳችን ፡ በኛ ፡ በሰዎች ፡ የተፈጠረ ፡ ነገር ፡ ነው ፡ በሚለው ፡ ሐሳብ ፡ ተስማምተን፡ ነበር ፡ ይመስለኛል - - -

« አዎ ፡ ተስማምተናል - - -

«ዛሬ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የምንላት ፡ ባንድ ፡ ዘመን ፡ የትልቋ ፡ ኢትዮጵያ ፡ አካል ፡ ነበረች - -

«ዐውቃለሁ - - -

«ዛሬ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የምንላት ፡ በተለይ ፡ የሳባ ፡ ሳብዓይ ፡ የናምሩድ ፡ ተከታይ ፡ በነበረው ፡ በኩሽ ፡ ልጅ ፡ በአቢስ ፡ ስም ፡ አቢሲኒያ ፡ በመ

ባል ፡ የታወቀች ፡ ነበረች - - እስከ ፡ ቅርብ ፡ ጊዜም ፡ የምትታወቀው ፡ በዚሁ ፡ ስም ፡ ነበር - - -

«ዐውቃለሁ - - -

«ከቅርብ ፡ ጊዜ ፡ ወዲህ ፡ ደግሞ ፡ የስፊዋን ፡ ጥንታዊት ፡ ኢትዮጵያ ፡ ስም ፡ ክፍሏ ፡ የሆነችው ፡ አቢሲኒያ ፡ ወረሰች - - -

«እርግጥ ፡ ነው - - -

«ዛሬ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ከሷ ፡ በፊት ፡ ታላቅና ፡ ሰፊ ፡ ኢትዮጵያ ፡ እን ደነበረች ፡ ብትዘነጋና ፡ ባትቀበል ፡ አይገርምም - - - -

«አይገርምም - - -

«ግሪኮችም ፡ ሐዋርያትም ፡ የጻፉት ፡ ሁሉ ፡ ስለ ፡ ዛሬዋ ፡ ስለ ፡ አዲ ሲቱ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ቢመስላት ፡ አያስገርምም - - አያስነውርምም - - -

«ባለማስገረሙ ፡ እስማማለሁ ፤ ግን ፡ የመላዋን ፡ ኢትዮጵያን ፡ ዝናና ፡ ታሪክ ፡ ክፍሏ ፡ የነበረችው ፡ የዛሬዋ ፡ ኢትዮጵያ ፡ መውሰዷ ፡ የሚያስነውር ፡ ይመስለኛል - - -

«እንዴት ፡ ያስነውራል ? እግር ፡ ሄዶ ፡ እጅ ፡ ሠርቶ ፡ ያተረፈውን ፡ ዝናና ፡ ታሪክ ፡ እጅና ፡ እግር ፡ አብረን ፡ አገኘነው ፡ ብለው ፡ ቢያወሩ ፡ ወይም ፡ እያንዳንዳቸው ፡ አስገኘሁ— አስገኘሁ ፡ ቢሉ ፡ ባይሆን ፡ አብሮ ነታቸውን ፡ በመዘንጋታቸው ፡ ይወቀሳሉ ፡ እንጂ ፡ እያንዳንዳቸው ፡ ለግቡ ፡ መድረሻ ፡ ድርሻ ፡ ድርሻቸውን ፡ ማከናወናቸውና ፡ ታሪክ ፡ ማስ ቀረታቸው ፡ ይካዳል - - - ?

« እና ፡ ትልቋ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ስትጠፋ ፡ አካሏ ፡ የሆነችው ፡ ትንሿ ፡ አቢሲኒያ ፡ ስሟን ፡ ወረሰች - - ተገቢ ፡ መብቷ ፡ ነው ፡ ነው ፡ የምትለኝ - - -

« ትልቋ ፡ ኢትዮጵያ ፡ አካሏ ፡ በነበረችው ፡ አቢሲኒያ ፡ እንደገና ፡ ታደሰች ፡ እንጂ ፡ ጠፋች ፡ አልወጣኝም - - የዛሬይቱ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ከጥንታዊቷ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የወረሰችው ፡ ስሟን ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ታሪ ኳን ፡ ዝናዋንም ፡ ጭምር ፡ ነው ።—ከኑቢያ ፡ አንሥቶ ፡ እስከ ፡ ሕንደኬ ፡ መንግሥት ፡ ከሚሴፖታሚያ ፡ እስከ ፡ ሱዳን ፡ ግርጌ ፡ ድረስ ፡ የተዘረ ጋው ፡ ታሪክ ፡ የዛሬይቱም ፡ ኢትዮጵያ ፡ ጭምር ፡ ነው - - መዳኒት ፡ ስላነሰ ፡ አያሽርም ፡ አይባልም - - -

«ስለዚህ ፡ የሰሎሞንና ፡ የሳባም ፡ ታሪክ ፡ የአዲሲቱም ፡ ኢትዮጵያ ፡ ታሪክ ፡ ነው ፡ ነው ፡ የምትለኝ - - -

እዎን ፡ ያዲሲቱም ፡ ኢትዮጵያ ፡ ታሪክ ፡ ነው - - -

«የሶርያም— የኑቢያም— የሱዳንም - - -

«አትዘርዝረው ፡ ግዴለህም - - ለማለት ፡ የፈለግኸው ፡ ገብቶኛል - - - ለታሪኩ ፡ ብቁ ፡ ሆነው ፡ ከተገኙ ፡ ታሪኩ ፡ የዘረዘርካቸው ፡ ሀገሮችና ፡ የሌሎችም ፡ ያልዘረዘርካቸው ፡ በጥንታዊት ፡ ኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ የተ መለከቱ ፡ ሀገሮች ፡ ሁሉ ፡ ታሪክ ፡ ነው - - - -

«ለታሪኩ ፡ ብቁ ፡ ሆኖ ፡ መገኘት ፡ ስትል ፡ ምን ፡ ማለትህ ፡ ነው - - ?

«የዚያን ፡ ዓይነት ፡ ባለ ፡ ታሪኮች ፡ ነን ፡ የሚሉት ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ አሳፋሪ ፡ ነገር ፡ የሚሠሩ ፡ ናቸው ፡ ከመባል ፡ ያልደረሱ ፡ ሆኖ ፡ መገኘት - -

«ታዲያ ፡ እንግዲህ ፡ ለታሪኩ ፡ ብቁ ፡ ሆና ፡ የተገኘችው ፡ አዲሲቱ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ብቻ ፡ ነች ፡ ማለት ፡ ነው - - ?

«በታሪኳ ፡ የማታፍርበት ፡ ኢትዮጵያ ፡ ነች ፡ አልኩ ፡ እንጂ ፡ የጥንታዊቷን ፡ ኢትዮጵያን ፡ ስም ፡ ለመውረስ ፡ ብቁ ፡ እሷ ፡ ብቻ ፡ ነች ፡ አልወጣኝም - - -

«ታዲያ ፡ በጥንታዊቱ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ታሪክ ፡ አለማፈር ፡ የጥንታ ዊቷን ፡ ኢትዮጵያን ፡ ታሪክ ፡ ለመውረስ ፡ በቂ ፡ ሆኖ ፡ ይገኛል - - ?

«እሱንማኮ ፡ የመለስኩልህ ፡ መሰሎኛል - - ስለ ፡ እጆችና ፡ እግ ሮች ፡ ሥራ ፡ በመጥቀስ - - ካልተደማመጥንኮ ፡ ክርክራችን ፡ ዞሮ ፡ ዞሮ ፡ መዝጊያው ፡ ጭራሮ ፡ ዓይነት ፡ ይሆናል - - -

« አዎ ፡ አዎ ፤ መልሰህልኛል - - እሺ ፡ ሌላ ፡ ጥያቄ ፡ አለኝ ።— ታሪክ ፡ ስትል ፡ ምን ፡ ማለትህ ፡ ነው - - ?

«የጥንታዊቷን ፡ ኢትዮጵያን ፡ ባህል — ወግ ፡ ልማድና ፡ ቅርስ ፡ ፍልስፍናና ፡ ሃይማኖት ፡ አነጋሥና ፡ ውድቀት ፡ የሚያሳይ ፡ የቃልም ፡ ሆነ ፡ የጽሑፍ ፡ ቅሪት ፡ ነው - - -

«እና ፡ ይኸንን ፡ ቅሪት ፡ አጥብቀን ፡ የያዝነው ፡ እኛ ፡ ብቻ ፡ ነን ፡ ነው ፡ የምትለው - - -

«ሳንሆን ፡ አንቀርም ፡ ነው ፡ ያልኩት - - -

«ሰሎሞንና ፡ ሳባም ፡ ከቅሪቱ ፡ ውስጥ ፡ ናቸው ፡ ነው ፡ የምትለው - - -

«አዎን ፡ ናቸው ---

«ቀዳማዊ ፡ ምኒልክ ፡ ከሰሎሞን ፡ መወለዱ ፡ ይነገራል ---

«በርግጥ -- !

«በቅሪቱ ፡ ውስጥ ፡ ነው ---

«ጥርጥር ፡ የለውም ---

«ስለዚህ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ነገሥታት ፡ የሰሎሞን ፡ ዘሮች ፡ ናቸው ---

«ብለን ፡ እናምናለን ---

«እኔ ፡ አልቀበለውም -- !

«ለምን ፡ አትቀበለውም ? የምናምንበት ፡ አብዛኛው ፡ ነገር ፡ ራሳችን ፡ የፈጠርነው ፡ በመሆኑ ፡ ደጋግመን ፡ ተስማምተናል --- ስለዚህ ፡ እንኳን ፡ ታሪክ ፡ ያቀየውንና ፡ ድንገትስ ፡ ተፈጥሮ ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ ፡ እንደ ፡ ሰደድ ፡ እሳት ፡ የሕዝብን ፡ መንፈስ ፡ ያዳረሰ ፡ መሆኑን ፡ ከተመለከትህ ፡ አንተ ፡ ብቻ ፡ የማትቀበልበት ፡ ምን ፡ ምክንያት ፡ አለህ -- ?

«የሌላው ፡ ሰው ፡ እምነት ፡ እኔን ፡ እንዳምንበት ፡ የሚገፋፋኝ ፡ ምክንያት ፡ ሊሆን ፡ አይችልም ---

«አንደኛ ፡ የጥንታዊት ፡ ኢትዮጵያ ፡ ታሪክ ፡ የኛም ፡ ታሪክ ፡ ቢሆን ፡ እኔ ፡ አልቀበለውም --- ሁለተኛም ፡ አብዛኛው ፡ የምናምንበት ፡ ነገር ፡ የራሳችንም ፡ ፈጠራ ፡ ቢሆን ፡ በዚህኛው ፡ ፈጠራ ፡ አላምንም --- ኅሊናዬ ፡ አልተቀበለውም ፡ ነው ፡ የምትለው -- ?

«አዎን ፡ ኅሊናዬ ፡ አልተቀበለውም --- ኅሊናዬም ፡ ስላልተቀበለው ፡ እምነት ፡ ሊኖረኝ ፡ አልቻለም ---

«ኅሊናህ ፡ ያልተቀበለው ፡ ለምን ፡ ይመስልሃል -- ?

«ለምን ፡ እንደሆነ ፡ አላውቅም ፤ ብቻ ፡ አልተቀበለውም ---

«ለመቀበል ፡ ስላልፈለግህ ፡ ነው ---

«ለምን ፡ አልፈልግም ---

«የባዕድ ፡ ተጽእኖ ፡ የሚገዛህ ፡ ስለሚመስልህ --- በራስህ ፡ ስለማትተማመን ፡ ስለምትፈራ --- ስለዚህ ፡ ነው ፡ ለመቀበል ፡ የማትፈልገው --- ስማኝ ! እስኪ ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ ልጠይቅህ --- ?

« ጠይቀኝ ፤ የምችለው ፡ ከሆነ ፡ እመልሳለሁ ---

«ዘመናዊ ፡ ሥልጣኔ—እንደ ፡ ጋንዲ ፡ እንደ ፡ ኬነዲ ፡ እንደ ፡ ኪንግ ፡ ያሉ ፡ የፖለቲካ ፡ መሪዎች - - እንደ ፡ የሱስ ፡ እንደ ፡ ሞሐመድ ፡ እንደ ፡ ቡድኀ ፡ ያሉ ፡ የሃይማኖት ፡ መሪዎች - - እንደ ፡ ናፖሊዎን ፡ እንደ ፡ ደጐል ፡ ያሉ ፡ ጀኔራሎች ፡ ለማፍራት ፡ እንደጣረች ፡ ነች ፡ ሁል ፡ ጊዜ - - -

«አዎ ፡ እንደ ፡ ጋሊሊዎ ፡ እንደ ፡ ኒውተን ፡ እንደ ፡ ኤንስታይን ፡ ያሉ ፡ የሳይንስ ፡ ሊቆች - - እንደ ፡ ቤቶቨን ፡ እንደ ፡ ሞዛርት ፡ እንደ ፡ ዮሐንስ ፡ ስትራውዝ ፡ ያሉ ፡ ሙዚቀኞች - - እንደ ፡ ሊዎናርዶ ፡ ዳቪንቺ ፡ እንደ ፡ ራፋኤል ፡ እንደ ፡ ሚካኤል ፡ አንጀሎ ፡ ያሉ ፡ ኬንያት - - እንደ ፡ ዶስቶቪስኪ ፡ እንደ ፡ ፎክነር ፡ እንደ ፡ ሼክስፒር ፡ ያሉ ፡ ደራስ ያን - - እንደ ፡ ሮክፌለር - - -

«ጥሩ ፡ ነው ፡ ጥሩ ፡ ነው - - በዘመናዊ ፡ ሥልጣኔ ፡ ዓላማ ፡ ተስማም ተናል ፡ ማለት ፡ ነው ። በዚህ ፡ ዓላማ ፡ ከተስማማን ፡ ዘንድ ፡ እንግዲህ ፡ ኢትዮጵያ ፡ በበኩሏ ፡ ከሆነላት ፡ እንደ ፡ ሰሎሞን ፡ ዓይነት ፡ ጠቢብ ፡ መሪ ፡ ማግኘትን ፡ እርማ ፡ ማድረጓ ፡ እንዴት ፡ አዲስ ፡ ነገር ፡ ሊሆንብህ ፡ ቻለ ? ደግሞስ ፡ በሙሉ ፡ ልባችንና ፡ አእምሯችን ፡ ካመንንበትና ፡ ከፈ ለግነው ፡ ሰሎሞንን ፡ መሰል ፡ መሪ ፡ በኢትዮጵያ ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ የማ ይበቅልበት ፡ ምን ፡ ምክንያት ፡ አለ - - ?

«ምክንያቱን ፡ አላውቅም ፤ በቅሎባት ፡ ግን ፡ አላየሁም ፡ ከዚህ ፡ በፊት - - -

«ተሳስተሃል ፡ እንግዲያው ፡ የኔ ፡ ልጅ - - ብዙ ፡ ብዙ ፡ ጠቢባን ፡ ብፁዓን ፡ ቆራጥና ፡ ኮምጫጫ ፡ የሆኑ ፡ ሰዎች ፡ በቅለውባታል ፡ ኢት ዮጵያ - - - እንደ ፡ ኤዛና ፡ እንደ ፡ ላሊበላ ፡ እንደ ፡ ምኒልክ ፡ ያሉ ፡ ጠቢ ብ ፡ መሪዎች - - - እንደ ፡ ዐምደ ፡ ጺዎን ፡ እንደ ፡ ቴዎድሮስ ፡ እንደ ፡ መኰንን ፡ ያሉ ፡ የወታደር ፡ መሪዎች - - -

«በቅለውባት ፡ ይሆናል - - -

«እሺ - - - ! የበቀሉባት ፡ ከመሰለህ ፡ ዘንድ ፡ ታዲያ ፡ በርግጥ ፡ ባርማችን ፡ ካመንን ፡ ታላላቅና ፡ ብፁዓን ፡ ሰዎች ፡ የማንፈጥርበት ፡ ምን ፡ ምክንያት ፡ ሊኖረን ፡ የሚችል ፡ ይመስልሃል ? እርግጥ ፡ ነው ፡ እምነታችን ፡ የድንገተኛ ፡ ስሜት ፡ ጉዳይና ፡ ጉንጭ ፡ አልፋ ፡ ሆኖ ፡ ከቀረ ፡ በስም ፡ ብቻ ፡ መኖር ፡ ለሮማውያንም ፡ ሆነ ፡ ለግሪኮች ፡ ወደ ፊትም ፡ ላሜሪካኖችና ፡ ለመስኮቦች ፡ የሚበጅ ፡ አይሆንም ።— ምድር ፡ በሰው ፡ መሰል ፡ ዲያብሎሶች ፡ እንደተመራች ፡ ትቆያለች - - - ሥጋን ፡

ወደ ፡ መርዝ ፡ በረከትን ፡ ወደ ፡ መርገም ፡ በሚለውጡ - - መሪነታቸውን ፡ በመጥሮ ፡ ተግባራቸው ፡ ብቻ ፡ የምናውቅላቸው - - ውለታቸውን ፡ ወህኒ ፡ ቤት ፡ በመጥጣል ፡ የምንከፍላቸው ፡ መሪዎች ። እምነታችንም ፡ መሽቶ ፡ እንደሚጠፋ ፡ ጥላ ፡ ቆይቶ ፡ እንደሚበተን ፡ አቧራ ፡ ይሆናል - - -

«እና ፡ አርማው ፡ ምንም ፡ ይሁን ፡ እምነታችን ፡ ነው ፡ ዋናው ፡ መሣሪያ ፡ ነው ፡ የምትለው - - -

«አዎን ፡ እምነታችን ፡ ነው ፡ ዋናው ፡ መሣሪያ— ዛፍ ፡ እፍሬው ፡ ውስጥ ፡ እንደሚደበቅ ፡ የምንፈልጋቸው ፡ ሰሎሞኖች ፡ ጻድቃንና ፡ ሰማዕታት— ኢትዮጵያ ፡ ፍላጐታችንና ፡ ዓላማችን ፡ ውስጥ ፡ ይደበቁ ፡ እንጂ ፡ መውጣታቸው ፡ አይቀርም - - -

«መቼ ፡ ነው ፡ ታዲያ ፡ የሚወጡት ? እነዚህ ፡ ሰሎሞኖች ፡ ጻድቃንና ፡ ሰማዕታት - - ?

«አትቸኩል ፡ ይወጣሉ— ነበሩን ፡ አሉን ፡ ይኖሩናል ።—ባርማችን ፡ በእምነታችን ፡ ውስጥ ፡ ስለተደበቁ ፡ የሌሉ ፡ አይምሰልህ - - - ! ፍራት ፡ የለሽ ፡ ስስት ፡ የለሽ ፡ ፍርድ ፡ አያዛቤ ፡ የጥበብ ፡ ምንጮች ፡ የሚሆኑን - - ሐዘንን ፡ ደምሳሽ ፡ ብስጭትን ፡ አጥፊ—ሕይወታቸው ፡ የየሱስን ፡ መንገድ ፡ የተከተለ - - በማጣት ፡ የማይጨነቁ ፡ በማግኘት ፡ የማይፎክሩ ፡ በጠቅላላው ፡ ለዓለማዊ ፡ ድሎት ፡ የማያፈችሉ - - ጽኑ ፡ ብሩህ ፡ ታጋሽ ፡ ርጉ ፡ ሰሎሞኖቻችን ፡ ጻድቃናችንና ፡ ሰማዕታታችን ፡ ይወጣሉ ፡ ከየፍሬዎቻችን - - ከእኛ ፡ የሚፈለገው ፡ በእምነታችን ፡ ብቻ ፡ ጸንቶ ፡ መገኘቱ ፡ ነው - - -

«መቼም ፡ ተስፋ ፡ ስለሰጠሽኝ ፡ ያሸነፍከኝ ፡ መሰለኝ - - -

«እኔ ፡ ምን ፡ ተስፋ ፡ እስጥሃለሁ - - ምናልባት ፡ ራስህ ፡ ለራስህ ፡ ተስፋ ፡ መስጠት ፡ ጀምረህም ፡ እንደሁ ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ ነው - - - ደግሞስ ፡ ምን ፡ ዋጋ ፡ አለው ፡ ብለህ ፡ አንተ ፡ ወይ ፡ እኔ ፡ በክርክር ፡ ብናሸንፍ - - - ያንተ ፡ ወይም ፡ የኔ ፡ በኩል ፡ ክርክር ፡ ለጊዜው ፡ እውነት ፡ ወይም ፡ ውሸት ፡ መስሎ ፡ ቢታይ ? ዋናው ፡ ነገር ፡ ይልቅ ፡ በኅሊናህ ፡ ያለው ፡ የምታምንበት ፡ ነገር - - - ዋናው ፡ ነገር ፡ ራስህ ፡ ችሎት ፡ ያለው ፡ ደኅና ፡ አድርጎ ፡ የጸደቀው ፡ እምነትህ - - -

## ፺፪

# አደፍርስ

ወይዘሮ ፡ አሰጋሽ ፡ ከሮቢት ፡ ወደ ፡ አርማኒያ ፡ እንደ ፡ ተመለሱ ፡ ወዲያው ፡ ወደ ፡ ደብረ ፡ ሲና ፡ አልወጡም ።—የሮማን ፡ ሠርግ ፡ መዳረሱ ፡ ስለነበረ ፡ ሥራው ፡ ፋታ ፡ አልሰጣቸውም—ጌሾ ፡ ማስቀርጠፉ ፡ ከየጉድጓዱ ፡ እህል ፡ ማስወጣቱ ፡ ብቅል ፡ ማስበቀሉ ፡ ወደየውሃ ፡ ወፍጮው ፡ እየላኩ ፡ ማስፈጨቱ ፡ ያሯሩጣቸው ፡ ነበር ።—

ሮማን ፡ በበኩሏ ፡ ከጺወኔ ፡ መጠለፍ ፡ ወዲህ ፡ ዕረፍት ፡ አልነበራትም ።—ወዴትም ፡ ይሁን ፡ ብቻ ፡ ካርማኒያ ፡ የምትወጣበትን ፡ መንገድ ፡ ነበር ፡ የምትፈልገው ።— ጴጥሮስ ፡ ይገኜሽ ፡ እጠፋለሁ ፡ ብሎ ፡ ተስፋ ፡ በሰጣት ፡ መሠረት ፡ ከዛሬ ፡ ነገ ፡ ይቆርጣል ፡ እያለች ፡ ብትጠብቀው ፡ ማመንታት ፡ ብቻ ፡ ሆነ ።— ከማትፈልገው ፡ ሰው ፡ ጋር ፡ መጠመጃዋ ፡ ቀን ፡ እየተቃረበ ፡ ሄደ ።— ሳምንት ፡ ያህል ፡ ቀረ ፡ ለሠርጉ ።— አንድ ፡ ቀን ፡ ማታ ፡ ትጠፋና ፡ ደብረ ፡ ሲና ፡ ገብታ ፡ ታድራለች ።—

‘ሽጋው ፡ ካቲካላ ፡ ያገር ፡ ተወላጅ ፡

በእምብርክ ፡ ያስኬዳል ፡ እንደ ፡ ሕፃን ፡ ልጅ’ እያሉ ፡ እበራቸው ፡ ደፍ ፡ ላይ ፡ ቁጭ ፡ ብለው ፡ ሲዘፋፍኑ ፡ የምታገኛቸው ፡ እንዷት ፡ የካቲካላ ፡ ነጋዴ ፡ ሴትዮ ፡ ትለምናቸውና ፡ ያሳድሯታል ።— በማግስቱ ፡ ጧት ፡ ሞቅታቸው ፡ ሲበርድላቸውና ፡ ሮማንንም ፡ በደንብ ፡ ለማየት ፡ ሲችሉ ፡ ጠፍታ ፡ የመጣችበትን ፡ ምክንያት ፡ ይሰሙና ፡ በማዘን ፡ ለጊዜው ፡ እቤታቸው ፡ እንድትሰነብት ፡ ይፈቅዱላታል ።—ትውላለች ፡ ታድራለች ።— ነጋዴዋም ፡ ጠባያቸው ፡ አይለወጥም ፤ መሸት ፡ ባለ ፡ ቁጥር ፡ ብቻ ፡ ሞቅ ፡ ሲላቸው ‘ ሽጋው ፡ ካቲካላ ፡ ያገር ፡ ተወላጅ . . ’ ነው ፡ እደፋቸው ፡ ለይ ፡ ቁጭ ፡ ብላው ‘በእምብርክ ፡ ያስኬዳል ፡ እንደ ፡ ሕፃን ፡ ልጅ . . . . .

## ፺፫

# አደፍርስ

አቶ ፡ ጥሶ ፡ ከነልጃቸው ፡ የሥራ ፡ ጊዜያቸውን ፡ ፈጽመው ፡ ወይ ዘሮ ፡ አካላት ፡ ከነአሽከራቸው ፡ ቤታቸውን ፡ በቅጥ ፡ በቅጥ ፡ አድርገው ከልጃቸው ፡ ጋር ፡ ለመክረም ፡ ሊመለሱ ፡ ወደ ፡ አዲስ ፡ አበባቸው ፡ ያመ ራሉ ።—አደፍርስ ፡ አነስ ፡ ያለ ፡ ቤት ፡ አግኝቶ ፡ እስኪከራይ ፡ ወደ ፡ ደሴ ፡ እሚወስደው ፡ አውራ ፡ መንገድ ፡ ዳር ፡ እሚገኘው ፡ ሆቴል ፡ ይዛወርና ፡ ሥራውን ፡ ይጀምራል ።—ክብረትም ፡ አብሮት ፡ ቆይቷል ፡ ለጊዜው ።—

«ሞትና ፡ ሕይወት ፡ ድንቁርናና ፡ ዕውቀት - - ! ባንተ ፡ አስተያየት ፡ እንግዲህ ፡ የሚያደርጉትን ፡ አያውቁትም ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ተማሪዎቼ - - ክፍል ፡ አንገባም ፡ ማለታቸው ፡ ሰላማዊ ፡ ሠልፍ ፡ ማድረጋቸው ፡ ድን ጋይ ፡ መወራወራቸው ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ መሰለኝ ፡ የሚታይህ - - ጥሩው ፡ ሥራቸው ፡ ተሰውሮብሃል - - » ይናገራል ፡ አደፍርስ ፡ ከክብረት ፡ ጋር ፡ እሆቴሉ ፡ ቤት ፡ መዝናኛ ፡ ክፍል ፡ ውስጥ ፡ ቁጭ ፡ ብሎ ፡ ሲያወጋ ።—

« ማንኛውም ፡ ነገር ፡ ከመጠን ፡ ሲያልፍ ፡ እጉል ፡ ነው— ትምህ ርታቸውን ፡ እንዲቀጥሉ ፡ ተደጋግሞ ፡ ተነገራቸው— በምክርም ፡ በግሣጻም - - እምቢ ፡ አሉ —ቤተ ፡ ሰቦቻቸውን ፡ አቃቱ - - ሕግ ፡ አስከ ባሪዎቹን ፡ የከተማ ፡ ፖሊሶች ፡ አቃቱ - - እና ፡ በመንግሥቱስ ፡ ለምን ፡ ትፈርዳለህ ?— ወታደሮች ፡ ከደብረ ፡ ብርሃን ፡ መምጣታቸውን ፡ አልጠ ላሁትም - -

«ምን ፡ ጠቀማቸው ፡ ታዲያ ፡ የባሰውን ፡ አመሳቀላቸው ፡ እንጂ ፡ ተማሪዎቹን - - - ?

« ይጥቀምም ፡ አይጥቀም ፡ ለጊዜው ፡ ጸጥታን ፡ አግኝተናል - - - እና ፡ ደሞ ፡ እናንተም ፡ መምህራኑ ፡ ብትረዱ ፡ አይከፋም - - -

«ትቀልዳለህ ፡ ጋሼ ፡ ክብረት - - በውነት ፡ ነው ፡ የምልህ ፡ ትቀል ዳለህ - - አንድ ፡ ነገር ፡ ልንገርህ ፡ በቀደም ፡ ቢል ፡ ያረገኝን ፡ በንዴት - - እንግዲህ ፡ እንግሊዝኛ ፡ አይደለም ፡ ማስተማር ፡ የጀመርኩት - - - ?

«ነግረሽኛል ፤ ከሰላም ፡ ጓዱ ፡ ጋር ፡ የተጋጩሽውን ፡ አይደለም ?

« መጋጨታችንንስ ፡ ነግሬሃለሁ - - - ይኸው ፡ መክረሚያውን ፡ እንደምታየው ፡ እነዚያ ፡ ፍርፋሪ ፡ የሚያበላቸው ፡ ተማሪዎች ፡ እየተከታተሉ ፡ ይገላምጡኛል ፤ ያሰቡትን ፡ እንግዲህ ፡ ማን ፡ ያውቃል - - - ?

« እስከዚህ ፡ ምን ፡ አደረግሽውና - - -

« እንግዲህ ፡ ምን ፡ ዐውቃለሁ - - ? ብቻ ፡ ያልነገርኩህ ፡ ነገር ፡ አለ - - በእንዴት ፡ ያለ ፡ መንገድ ፡ ቅኝ ፡ አገዛዛቸውን ፡ ሊቀጥሉ ፡ እንደሚፈልጉ ፡ ነጮች - - -

«አልነገርሽኝ ፡ ይሆናል - -

«- - እና ፡ ታዲያ ፡ አንድ ፡ የስምንተኛ ፡ ክፍል ፡ ተማሪ ፡ ደብዳቤ ፡ ጽፎልሃል ፡ በእንግሊዝኛ ፡ ለ 'Ethiopian Herald ' ጋዜጣ - - እንዳርምለት ፡ አመጣው ፡ እኔ ፡ ጋ ።—እኔም ፡ ቀስ ፡ ብዬ ፡ እንደ ፡ ተቻለኝ ፡ አረምኩለት ፡ እንግሊዝኛውን - - እንግዲህ ፡ አስበው ፡ እንግሊዝኛውን ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ እኔ ፡ ያረምኩት— ሐሳቡን ፡ አልነካሁም ።— ከዚያ ፡ በኋላ ፡ ለሰላም ፡ ጓዱ ፡ ደሞ ፡ ወስዶ ፡ አሳይቶት ፡ ኖሯል - - ቋንቋው ፡ ስለሆነ ፡ በተሻለ ፡ መንገድ ፡ እንዲያርምለት - -

«ብሔራዊ ፡ ቋንቋው ፡ እንግሊዝኛ ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ የተሻለ ፡ የሚያስተምረው ፡ አይመስልህም - - ?

«ይሻልም ፡ አይሻል ፡ ገና ፡ ተጠንቶ ፡ አልታወቀም ፡ እንዲህ ፡ ያለው ፡ ነገር— ብቻ ፡ እኔ ፡ ልነግርህ ፡ የፈለግሁት ፡ ይኸ ፡ ሰላም ፡ ጓድ ፡ ያደረገውን ፡ ነው - - የልጁን ፡ ደብዳቤ— ሰርዞ ፡ ሰርዞ ፡ ዐረፍተ ፡ ነገር ፡ በዐረፍተ ፡ ነገር— ድልዝና ፡ እመጫት ፡ አሽክሞ ፡ ይሰጠዋል ። ሞኙ ፡ ተላሌው ፡ ተማሪ ፡ ሆዬ ፡ እቤቱ ፡ ወስዶ ፡ አሳምሮ ፡ ይገለብጥና— እንደ ፡ ገና ፡ ሊያሳየኝ ፡ መምጣት - - -

«አንተ ፡ ደሞ ፡ ለምን ፡ ሌላ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሰው ፡ አረመው ፡ ብለህ ፡ መናደድ - - - !

« እሱ ፡ አደለም ፡ እባክህ - - ! ባነበው ፡ ጊዜ ፡ አብዛኛው ፡ የልጁ ፡ የነበረው ፡ ሐሳብ ፡ ጠፍቶ ፡ የሰላም ፡ ጓዱ ፡ ሐሳብ ፡ ሆኗል - - - ሐሳብህኮ ፡ ተለውጧል ፡ ብዬ ፡ ነገርኩት ፡ ለተማሪው - - ያንተ ፡ ሐሳብ ፡ ለእንግሊዝኛ ፡ ቋንቋ ፡ ተናጋሪዎች ፡ እንዲገባ ፡ እንዲህ ፡ መሆን ፡ አለበት ፡ ብሎ ፡ ነው ፡ የለወጠልኝ ፡ ብሎ ፡ መለሰልኝ - - -

«እኮ ፡ ሐሳቡን ፡ አስተካከለለት ፡ ማለት ፡ ነው - - -

«የለም ፡ የተማሪውን ፡ ሐሳብ ፡ ደምስሶ ፡ የራሱን ፡ ሐሳብ ፡ ጻፈ ለት - - -

« እና ፡ በቋንቋ ፡ ጥናት ፡ ውስጥ ፡ እንኳን ፡ ቢሆን ፡ የራሳቸውን ፡ ፕሮፓጋንዳ ፡ ነው ፡ የሚነዙት ፡ ነው ፡ የምትለኝ - - - ?

«እንዲያ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን—የራሳችንን ፡ ሐሳብ ፡ እያጐዘሉ ፡ የነሱን ፡ ሐሳብ ፡ ብቻ ፡ እንድናደንቅ ፡ ነው ፡ የሚፈልጉት ፡ ነው ፡ የምልህ - - -

«ታዲያ ፡ ምናለበት ፡ የራስህ ፡ ሐሳብ ፡ ያው ፡ የራስህ ፡ ነው- - የነሱ ንም ፡ ከነሱ ፡ የምትፈልገውን ፡ ወድደህ ፡ የምትቀበለውን ፡ እስከታገኝ ፡ ድረስ ፡ የተቀበልከላቸው ፡ ምሰል - - -

«መምሰል ፡ ሳይሆን ፡ እየተለወጡ ፡ ሄዱ ፡ እንጂ ፡ ተማሪዎቻችን— ከነሱ ፡ የሚፈልጉትን ፡ እስኪያገኙ ፡ ዱሮ ፡ ተለውጠው ፡ ቁጭ ፡ ሆነዉ ! ! የራሳቸው ፡ የሆነ ፡ ነገር ፡ ያስጠላቸው ፡ ጀመረ — በእንግሊዝኛ ፡ ቃል ፡ ያልተገኘለት ፡ ያማርኛ ፡ ቃል — በእንግሊዝኛ ፡ ለመግለጽ ፡ የሚያስቸ ግር ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ሐሳብ—በእንግሊዝኛ ፡ ቋንቋ ፡ የማይገለጽና ፡ የሌለ ፡ ማንኛውም ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ባህል ፡ ሁሉ ፡ ዋጋ ፡ እንደሌለው ፡ ተቆጠረ ፡ እንጂ — እንጀራውን 'ብሬድ' ወጡን 'ሱፕ' ጠይሙን 'ብላክ' ጥቁሩን 'ኔግሮ' እንዲሉ ፡ ተገደዱ — ምን ፡ አለፋህ ፡ ብቻ - - የኢትዮጵያውያ ንን ፡ ሰብእና ፡ አጥፍተው ፡ የፈረንጁን ፡ ሰብእና ፡ ተኩበት ፡ ነው ፡ የም ልህ - - -

« የራስህ ፡ በሆነ ፡ ነገር ፡ ማፈር ፡ ስትጀምር ፡ የባዕድ ፡ ተገዥ ፡ መሆንህ ፡ የማይጠረጠር ፡ ነው— ብቻ - -

« እምልህኮ ፡ አንድ ፡ ዐረፍተ ፡ ነገር ፡ በእንግሊዝኛ ፡ ትጽፋለህ - - ያንን ፡ ዐረፍተ ፡ ነገር ፡ የሰላም ፡ ጓዱ ፡ ይሰርዝና ፡ የተሻለው ፡ ይኸ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ የራሱን ፡ ይጽፋል ።— አስተማሪህ ፡ ነውና ፡ ትቀበለዋለህ ፡ አንተም— ይቀጥላል ፡ እንዲሁ ፡ በየጊዜው— ትጽፋለህ ፡ ይሰረዛል— ትጽፋለህ ፡ ይሰረዛል— ከጊዜ ፡ በኋላ ፡ ትክክለኛ ፡ ዐረፍተ ፡ ነገር ፡ መጻፍ ፡ ጀምረሃል ፡ ብሎ ፡ ይመሰክርልሃል— የሱ ፡ ግልባጭ ፡ መሆን ህን ፡ በትክክል ፡ ሲያረጋግጥ— 'ቢቢ' — 'ሀይ !' እያልክ ፡ መዘባነን ፡ ነው ፡ አንተም ፡ ከዚያ ፡ ወዲያ ።—እግሩን ፡ ሰብስቦ ፡ ተቀምጦ ፡ የሚለ ውን ፡ ዐረፍተ ፡ ነገር — ይኸማ ፡ ለሁኔታው ፡ አይበጅም — መዝናናቱ ፡

መታየት ፡ አለበት— ስለዚህ ፡ እግሩን ፡ እጠረጴዛው ፡ ላይ ፡ ዘርግቶ ፡ መባል ፡ አለበት - - ጥፍሯን ፡ አስተካክላና ፡ አሳምራ ፡ ቆርጣ ፡ የሚለ ውን — ይኸማ ፡ ያው ፡ ገልቱነትን ፡ ነው ፡ የሚያሳየው—ጥፍሯን ፡ አሳ ምራ ፡ አሳድጋና ፡ ቀለም ፡ ቀብታ ፡ መባል ፡ አለበት - - ወይም ፡ ከንፈሯ ፡ ሰው ፡ ሠራሽ ፡ ጌጥ ፡ ያልደባለቀ ፡ በተፈጥሮ ፡ ውበቱ ፡ የሚያጓጓ ፡ የሚ ለውን — ከንፈሯን ፡ ዓይኖችህን ፡ እንዲያብለጨልጭ ፡ የሚያደርግ ፡ ሮዝ ፡ የከንፈር ፡ ቀለም ፡ ቀብታ - - ምናለፋህ ፡ ብቻ ፡ ቀስ ፡ በቀስ ፡ እግርን ፡ እጠረጴዛ ፡ ላይ ፡ በመዘርጋት ፡ ጥፍርን ፡ በማሳደግ ፡ ከንፈርን ፡ ቀለም ፡ በመቀባት ፡ ዓይነት ፡ መንገድ ፡ የተሻሻለ ፡ በመሰለህ ፡ ሐሳብህ ፡ ውስጥ ፡ ዘቅጠህ ፡ ትቀራለህ ፡ ነው ፡ የምልህ - - እነ ፡ አቶ ፡ ጥሶ ፡ ልማድ ፡ ወግ ፡ ቅርስ ፡ የሚሏቸው ፡ ሁሉ ፡ ድራሻቸው ፡ ይጠፋል ፡ ነው ፡ የምልህ - - - አንተም ፡ ዱሮ ፡ መሬትህ ፡ ነበር ፡ በቅኝ ፡ አገዛዝ ፡ የሚያዘው ፡ ዛሬ ፡ ሰውነትህን ፡ ሰብእናህን ፡ ለቅኝ ፡ ገዥዎች ፡ ሰጥተህ ፡ ትቀራለህ ፡ ነው ፡ የምልህ - - ለምሳሌ ፡ አሁን ፡ የጥንቱን ፡ የተመለከትህ ፡ እንደሆነ — ሰብእናቸው ፡ በቅኝ ፡ ገዥዎች ፡ ያልተያዘ ፡ ስለነበረ ፡ መሬታቸውም ፡ ቢያዝ ፡ ለማስመለስ ፡ ችለው ፡ ነበር ።— ዛሬ ፡ ግን ፡ እንዳያያዛችን ፡ መሬታችን ፡ ቢያዝ ፡ እንኳ ፡ በየትኛው ፡ ሰብእናችን ፡ እናስመልሰዋለን - - ? ደግሞስ ፡ ሰብእናችንን ፡ እያጣን ፡ ከሄድን ፡ መሬታችንንስ ፡ ጭምር ፡ እያጣን ፡ ላለመሄዳችን ፡ ምን ፡ መተማመኛ ፡ አለን ? ሰብእናችን ፡ ሲገዛ ፡ መሬታችንም ፡ መገዛቱ ፡ አይታወቀንም ፡ ይሆን ? ተመልሶ ፡ የኛ ፡ የመ ሆን ፡ ተስፋ ፡ በሌለው ፡ አኳኋን - - ! በየትኛው ፡ ሰብእናችን ፡ ልናስመ ልሰው - - ? እኛንም ፡ መሬታችንንም ፡ እንዴት ፡ አድርገን ፡ የምንችል ፡ ይመስልሃል ፡ ከቅኝ ፡ አገዛዝ ፡ ሥር ፡ ለማውጣት - - ? ሌላው ፡ ቢቀር ፡ እንደ ፡ አበው ፡ እንደ ፡ ጥንታውያኑ ፡ ያህል ፡ እንኳ ፡ ሰብእናቸው ፡ ያል ተነካ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ካልተነሡ - - -

« ያንን ፡ እዚያ ፡ እግርግዳው ፡ ላይ ፡ የተሣለ ፡ ሥዕል ፡ ትመለከታ ለህ - - - ? » ይጠይቀዋል ፡ ድንገት ፡ አደፍርስን ፡ ከብረት—አዲስ ፡ ነገር ፡ እንደ ፡ ተከሠተለት ፡ ዓይነት « መጀመሪያ ፡ ዛፉን ፡ ተመልከት ፤ አምስት ፡ ቅርንጫፎች ፡ አሉት ።— ወደ ፡ ቀይ ፡ የሚያደላ ፡ ሮዝ ፡ ዓይነት ፡ ቀለም ፡ ነው ፡ የተቀባው ፡ ግንዱ ፡ ደሞ ።—የቅጠሎቹን ፡ ደሞ ፡ ትንንሽነት ፡ ትመ ለከትልኛለህ - - - ? እሺ - - ! በነጭ ፡ ወረቀት ፡ ላይ ፡ በጥቁር ፡ ቀለም ፡ የተሣለ ፡ ሰው ፡ ሥዕል ፡ ነው ፡ ያ ፡ ደሞ - - - እቅርንጫፎቹ ፡ መካከል ፡ የተለጠፈው — ከሌላ ፡ ዘንድ ፡ ቆርጠው ፡ አምጥተው ፡ ነው ፡ የለጠ

ፉት - - እሺ - - ! እሥሩ ፡ ደሞ - - እንዲሁ ፡ ከሌላ ፡ ዘንድ ፡ ቆርጠው ፡ አምጥተው ፡ የለጠፉትን ፡ የኮካኮላ ፡ ማስታወቂያ ፡ ታየዋለህ - - - ? ወንድና ፡ ሴት ፡ ኮካኮላ ፡ ከካኮላቸውን ፡ ጨብጠው ፡ እኮላቸው ፡ ውስጥ ፡ ብራቸውን ፡ ሰክተው— አንጋጠው— በኀይል ፡ ስቀው ፡ ወደ ፡ ዛፉ ፡ ላይ ፡ ሰው ፡ ሲመለከቱ ።— ከተሰቀለበት ፡ ዛፍ ፡ ወርዶ ፡ የማያመል ጣቸው ፡ በመሆኑ ፡ ተማምነው ፡ የተደሰቱ ፡ ይመስል ።— እዞሪያቸው ፡ እግርግዳው ፡ ላይ ፡ ደሞ ፡ የተምቦጫረቀውን ፡ ቀለም ፡ ትመለከተዋለህ - - ? ይኸ ፡ ምንድነው ፡ ስሙ - - ለምጨቅ ፡ ነው ፡ ሮንቄ - - ? ይኸ ፡ ረግረግ ፡ የሆነ ፡ የሚዋልል ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ የተቀመጡ ፡ እንደሚመስል ።— እዳሩ ፡ ላይ ፡ ደሞ ፡ ከወደ ፡ ግራ ፡ በኩል ፡ አባት ፡ ነፍጠኛን ፡ ትመለከታ ለህ - - ? ጥቁር ፡ ጸጉራቸው ፡ ቀይ ፡ ማሠሪያ ፡ ካለው ፡ ነጭ ፡ ባርኔጣቸው ፡ ሥር ፡ ብቅ ፡ ብሎ— ፊታቸውና ፡ እግራቸው ፡ ሮዝ ፡ ተቀብቶ— ቀይ ፡ ጥለት ፡ ያለው ፡ ሸማ ፡ ለብሰው— አረንጓዴ ፡ ሱሪ ፡ ታጥቀው— ጨበጥ ፡ አርገው ፡ የያዙትን ፡ ቀይ ፡ ጐራዴ ፡ አገንድረው - - - በነጩ ፡ ግርግዳ ፡ መሣላቸው ፡ ደሞ ፡ በጅቷቸዋል - - - -

አቅራቢያቸው ፡ ቆማ ፡ ታዳምጣቸው ፡ የነበረች ፡ አሳላፊ ፡ የቢራ ቸውን ፡ ተጠጥቶ ፡ ማለቅ ፡ ታይና « የብሩታዊትና ፡ የባለ ፡ ክንፉ ፡ ዘንዶ ፡ ምሳሌ ፡ ነው ፡ ሥዕሉ - - » እያለች ፡ ሁለት ፡ የጊዮርጊስ ፡ ቢራ ፡ ታመጣና ፡ መክፈት ፡ ትጀምራለች ።—

« ባለ ፡ ክንፉ ፡ ዘንዶ ፡ ታዲያ ፡ የታል - - - ? » ይጠይቃታል ፡ ክብረት ።—

« አይታይም ፡ እሱ - - ተሰውሯል - - ጋኔል ፡ አይደለም ፡ እንግ ዲህ ? ! ሊሰወር ፡ ይችላል - - - » ትመልሳለች ፡ አሳላፊዋ ፡ ሳቅ ፡ ሳቅ ፡ እያለች —

## ፶፬

# አደፍርስ

ወይዘሮ ፡ አሰጋሽ ፡ ሮማንን ፡ በየገጠሩም ፡ በየከተማውም ፡ ቢያስ ፈልጉ ፡ ሳትገኝ ፡ በመቅረቷ ፡ በመግመን ፡ በመጨስ ፡ ላይ ፡ እንዳሉ ፡ አማላጅነት ፡ የተላኩ ፡ ሦስት ፡ ሽማግሌዎች ፡ ይመጣሉ ፡ እቤታቸው - - - ሲፈሩ ፡ ሲቸሩ - - -

« - - ባልና ፡ ሚስት ፡ ካንድ ፡ ባሕር ፡ ይቀዳል ፡ ነው ፡ የሚባለው - - እኛም ፡ መቼም ፡ ደፍረን ፡ የመጣነው ፡ አባቱ ፡ ያባቷ ፡ እናቱ ፡ የናቷ ፡ አብሮ ፡ አደግና ፡ በችግርም ፡ ሆነ ፡ በደስታ ፡ ያልተለያያችሁ ፡ በመሆና ችሁ ፡ ልጆቻችሁም ፡ የእናንተን ፡ ፈር ፡ ተከትለው ፡ እንዲተኩ ፡ በማ ሰብ ፡ ነው - - -» እያሉ ፡ የመጡበትን ፡ ጉዳይ ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ዓይነት፡ መንገድ ፡ በመደጋገም ፡ ይናገራሉ ፡ እንጋፋው ፡ ሽማግሌ ።—ወይዘሮ ፡ አሰጋሽ ፡ በዝምታ ፡ ያዳምጣሉ ።—

«ልጁ ፡ መቼም ፡ አላጠፋም ፡ አንልም - - - » ይለጥቃሉ ፡ ሌላው።—

«አዎ ፡ እውነት ፡ ነው ።— እኔም ፡ አባትሽ ፡ ብሆን ፡ ይኸው ፡ አሁን ፡ ሊቀ፡ መልአኩ ፡ ምስክሬ ፡ ነው ፤ ለሌላ ፡ ሰው ፡ ቢሆን፡ እደ ጅሽ ፡ ድርሽ ፡ አልልም ፡ ነበር— በዛሬው ፡ ጊዜ ፡ ማን ፡ ይታመናል ? ይኸው ፡ ሮማን ፡ እንኳን ፡ እንዲህ ፡አሳፍራን ፡ ጠፍታለች ።—እና ፡ ታዲያ - - ለሮማንስ ፡ የተደገሰው ፡ ድግስ ፡ ለምን ፡ መና ፡ ይቅር - - ? እዎ ፡ ይኸንን ፡ ሁሉ ፡ አስቤ ፡ ነው - - - » ይናገራሉ ፡ ያዳምጡ ፡ ያዳምጡና ፡ አባ ፡ አዲሴ ።

«እንደሱ ፡ እንኳ ፡ አይናገሩ ፡ አባቴ ! የኔ ፡ ልጅ ፡ በሮማን ፡ ድግስ ፡ አታገባም - - የምታገባም ፡ ቢሆን - - ሁለት ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ ጋን ፡ ጠላ - - አምስት ፡ ስድስት ፡ ፍሪዳ ፡ ሦስት ፡ አራት ፡ ሰቀላ - - -» ድንገት ፡ ቱግ፡ ይላሉ ፡ ወይዘሮ ፡ አሰጋሽ ።—

«ወዴት ፡ ወዴት ፡ ወሰድሽብኝ ? ምን ፡ ቢያገደኝ ፡ የኔ ፡ ልጅ ! ያንችን ፡ የልጄን ፡ ምግባር ፡ አጣሁትና - - -

« - - - አዎ ፡ ድፍን ፡ ይፋትን ፡ ጠርቼ ፡ አምቦዝቡኸቦታለሁ ፡ የሮማንን ፡ ሠርግ ፡ ድግስ ፡ ቢሆን - - - ጐርፉ ፡ ግን ፡ ወደ ፡ መጣችሁ

በት ፡ ቁም ፡ ነገር ፡ ልመለስና ፡ አከባሪዬ ፡ ልጅ ፡ ነበር - - ምን ፡ ይሆ ናል ! በሰው ፡ አገር ፡ ደፍሮኛል ።— አቅሜን ፡ ሴትነቴን ፡ አይቶ - - -

« ጥፋቱኮ ፡ ጥፋት ፡ አያህልም ፤ አላጣነውም - - - ኋላ ፡ አፋች ንን ፡ ያስተሣሠረው ፡ ምኑ ፡ ነው - - - ? አይ ፡ ጥፋቱ ፡ ጥፋት ፡ ነው ። እንደመቤታችን ፡ ተማምነንብሽ ፡ የመጣነው ፡ ይቅርታሽ ፡ አይለየንም ፡ ብለን ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ጥፋታችንማ ፡ መቼ ፡ ታጥቶን ።— የኔ ፡ ልጅ ፡ ለስንቱ ፡ ለስንቱ ፡ በዳይሽ ፡ ነው ፡ ይቅር ፡ የምትይው ፤ ልበ ፡ ሰፊ ፡ ነሽ - - አሁን ፡ በቀደም ፡ አንድ ፡ አኮሪዶ ፡ የሚጫወት ፡ ልጅ ፡ ሮማንን ፡ ቢደፍርባት - - ሰው ፡ እንዴት ፡ ጋብዞ ፡ ያመጣውን ፡ አስቀይሞ ፡ ያባር ራል ? ብላ ፡ የተሠራውን ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ ልቧ ፡ እያወቀው — አምን ሃለሁ ! ጥፋቱ ፡ ያንተ ፡ አይደለም ፡ ብላ— ጉዱን ፡ ሁሉ ፡ ሸፋፍና— ከዚያ ኋላ ፡ ደሞ ፡ አውላ ፡ አሳድራ ፡ በደስታ ፡ አልሸኘችውም - - ? ይቅር ፡ ማለት ፡ ብቻኮ ፡ አይደለም - - ጉዱ ፡ ከግቢዋ ፡ አልወጣም ።— ምግ ባሯ ፡ ነው ፡ ያኖራት - - ምግባሯ ፡ የኔን ፡ ልጅ - - -

«አሁን ፡ ታዲያ ፡ ቀን ፡ ቢወስኑልን - - ! » ይጠይቃሉ ፡ አንጋፋው ፡ ሽማግሌ ።—

«እስከ ፡ አሥራምስት ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ እስቲ ፡ ከልቤ ፡ ጋር ፡ እመክ ርና ፡ ለማንኛውም— ቁርጡን ፡ እነግራችኋለሁ - - - አዎ ፡ አንድ ፡ ልጅን ፡ ያህል ፡ መስጠት ፡ ቀላል ፡ ነገር ፡ አይደለም - - -

«ጐርፉስ ፡ ቢሆን ፡ ያው ፡ የርስዎ ፡ አይደለሞይ - - - ምን ፡ ለየው - - ?

«ጐርፉም ፡ የኔ ፡ ነው ፡ ቢሆንም - - ቢሆንም - -

ሽማግሌዎቹ ፡ እጅ ፡ ነሥተው ፡ ይወጣሉ ።— ጺ.ወኔ ፡ አማላጅነት ፡ የመጡበትን ፡ ካሽከሮች ፡ ትሰማለች ።—

## ፶፩

## አደፍርስ

ነጋዴዋ ፡ ሴትዮ ፡ የሮማን ፡ ጉልበት ፡ እየጣማቸው ፡ ስለሄደ ፡ እን ድትቆይላቸው ፡ ይለማመጣሉ ፡ በየቀኑ ።— ሮማንን ፡ ቢሆን ፡ አይደላ ትም—ትከሳለች ፤ ትጠቁራለች ፤ በጥቂት ፡ ቀኖች ፡ ውስጥ ፡ ያ ፡ የሚያም ረው ፡ ወዛም ፡ ሰውነቷ ፡ ይመጠጣል ።— ከጧት ፡ እስከ ፡ ማታ ፡ የካ ቲካላ ፡ ድፍድፍ ፡ ሲቀቅሉ ፡ መዋልና ፡ ማምሸት ፡ ቀላል ፡ ሥራ ፡ አል ነበረም ።—

ለሠርጉ ፡ የተዘጋጀውን ፡ ድግስ ፡ ቢሆን 'ድፍን ፡ ይፋትን' ሳይጋ ብዙበት ፡ ይቀራሉ ፡ ወይዘሮ ፡ አሰጋሽ ።— ጺወኔም ፡ ትገነግናለች ፡ በዚህን ፡ ጊዜ ።— ጉርፋ ፡ የላካቸው ፡ ሽማግሌዎች ፡ የተቀጠሩት ፡ እንደነገ ፡ ሊሆን ፡ ማታውኑ ፡ ጠፍታ ፡ ደብረ ፡ ሲና ፡ ትገባለች ።— አጎቷ፡ ቤት ፡ ድረስም ፡ ሄዳ ፡ ተደብቃ ፡ ትጠብቅና ፡ በላይን ፡ ታገኘዋለች ።— በላይ ፡ የፈለገችውን ፡ እርዳታ ፡ ያደርግላታል።—ይወስድና ፡ ለብቻቸው ፡ ቤት ፡ ተከራይተው ፡ እየኖሩ ፡ ከሚማሩ ፡ ሁለት ፡ የትምህርት ፡ ቤት ፡ ልጃገረድ ፡ ጓደኞቹ ፡ ጋር ፡ ያስቀምጣታል ፡ ስድስት ፡ ቀን ፡ ያህል ።— በሰባተኛው ፡ ቀን ፡ ግን ፡ በምንም ፡ ዓይነት ፡ መንገድ ፡ ቢሆን ፡ አደፍ ርስን ፡ ካላገኘሁና ፡ ካላነጋገርሁት ፡ ሞቼ ፡ እገኛለሁ ፡ ብላ ፡ ስላስቸገረ ችው ፡ አደፍርስን ፡ ይጠራላታል ።—

# ፺፮

# አደፍርስ

አደፍርስ ፡ የጺወኔን ፡ ሁኔታ ፡ በሰማበት ፡ ወቅት ፡ አሁን ፡ ጊዜም ፡ የለኝ ፡ የሚልበት ፡ ዩንቨርስቲ ፡ የሚያዘውን ፡ የአንድ ፡ ዓመት ፡ አገልግሎቱን ፡ የጀመረበት ፡ አፍላ ፡ የሥራ ፡ ወራቱ ፡ ነበር ፤ ከወዲያ ፡ ወዲህ ፡ ያሯሩጠዋል ።—ሆኖም ፡ የበላይ ፡ ጉትጐታ ፡ ስለ ፡ በዛበትና ፡ ለጺወኔም ፡ አንዳንድ ፡ ጠቃሚ ፡ ምክር ፡ ቢሰጣት ፡ የምትመለስ ፡ ስለመሰለው ፡ ይሄድና ፡ ያነጋግራታል

«--ጺወኔ ፡ መኰብለል ፡ አልነበረብሽም ፤ በጣም ፡ አጥፍተሻል --በጣም ፡ ነው ፡ የምልሽ ---! እናትሽ ፡ ምን ፡ ይሉ ---? በሐዘን ፡ የሞቱ ፡ እንደሁ ፡ ጉዳቱ ፡ የማን ፡ ይመስልሻል ---? አዙረሽ ፡ አትመለከችም ? » እያለ ፡ ይጀምራል ፡ ግሠጻውንና ፡ ምክሩን ፡ እበላይ ፡ ፊት « ሮማን ፡ ይኸው ፡ እንደጠፋች ፡ አልተገኘችም -- በሷ ፡ ምክንያት ፡ የደረሰባቸውን ፡ ኪሳራና ፡ ንዴት ፡ ሳይወጡት ፡ ደሞ ፡ ያንቺ ፡ መጨመር ! እውነቴን ፡ ነው ፡ የምልሽ ፡ በጣም ፡ ነው ፡ የሚያናድደኝ ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ነገር -- እኔኮ ፡ የማይገባኝ -- እንዴት ፡ አዙረሽ ፡ አትመለከችም --? እሺ ፡ ይሁን ፡ ደሞ ፡ ከኔም ፡ ጋር ፡ ተነጋግረሽ ፡ በሆነ ---

«ሆዴ ፡ አልችል ፡ አለኝ -- የምትጨክንብኝ ፡ አልመሰለኝም -- የማስቸግርህ ፡ አልመሰለኝም ፡ ነበር ፡ ደሞ --- እግርህን ፡ አጥቤ ፡ እንኳን ፡ ብቀመጥ ---

«ሞትና ፡ ሕይወት ! እግር ፡ ማጠብ -- እግር ፡ ማጠብ --! እኔ ፡ እግር ፡ አጣቢ ፡ አልፈልግም ! እፈልጋለሁ ፡ ወጣኝ ?! የት ፡ ቦታ -- የት ፡ ቦታ ፡ ወጣኝ ፡ እግር ፡ አጣቢ ፡ እፈልጋለሁ --- ራሴ ፡ የራሴን ፡ እግር ፡ አጥበዋለሁ -- የራሴን ፡ እድፍ --- እግር ፡ አጥቤ ?!

« ሮማን ፡ የምትሠራው ፡ አያቅተኝ -- ያ .. ልከው -- ማንኛውም ፡ ሥራ ፡ ቢሆን ---

«ስሚኝ ፡ ልንገርሽ ፡ ጺወኔ ! እኔ ፡ ለራሴ ፡ ይኸን ፡ ዓመት ፡ ስጨርስ ፡ ወደ ፡ ዩንቨርስቲ ፡ ተመላሽ ፡ ነኝ ።— እዚያ ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ እቆ

ያለሁ ።— ከዚያ ፡ በኋላ ፡ ደሞ ፡ ምኑ ፡ ይታወቃል ? ወይ ፡ ለከፍተኛ ፡ ትምህርት ፡ ወደ ፡ ወዳጅ ፡ ሀገር ፡ እሄዳለሁ - - ወይ ፡ ሥራ ፡ እይዛለሁ -- እምልሽ ፡ ብቻ ፡ ነፃ -- ነፃ ፡ ለመሆን ፡ ነው ፡ የምፈልገው -- በምንም፡ ዓይነት ፡ ነገር ፡ እንድታሠር ፡ አልሻም ---

« እኔ ፡ ታዲያ ፡ ምን ፡ ይብጀኝ -- ?

« የሚበጅሽ ፡ ወደናትሽጋ ፡ መመለሱ ፡ ነው -- አዎ ፡ ሳትውዪ ፡ ሳታድሪ --- ምናልባት ፡ ቢያስፈልግ ፡ አቶ ፡ ወልዱን ፡ አማላጅ ፡ ጨምረሽ ---

« ጉርፉን ፡ እንዳገባ ፡ ተመልሼ --- ?!

« ምናለበት ?! ጥሩ ፡ ልጅ ፡ ነው ።— እወደዋለሁ ፡ ብለሽኛል ፡ ደግሞ -- የባላገሩንም ፡ ኑሮ ፡ ለምደሽዋል ---

«ምነው ፡ ልቡስ ፡ ጥላሽ ፡ ካልገጠመ ፡ አጉል ፡ ነው ፡ ብለሽኝ --- ? ምነው ---

«ነገርኩሽ -- ! ስለ ፡ ልቡስ ፡ ጥላ ፡ ብዙ ፡ ብዙ ፡ የማይገባሽ ፡ ነገር ፡ አለ ።— ከፍ ፡ ያለ ፡ ትምህርት ፡ ያስፈልግሻል -- እሱ ፡ እንዲ ገባሽ --- !

« አታስተምረኝም ፡ ታዲያ --- ?

« እምልሽ ፡ የሁለተኛ ፡ ደረጃ ፡ የዩንቨርስቲ ፡ ትምህርት ---

« ጉርፉን ፡ በጭራሽ ፡ አላገባም -- እዚሁ ፡ ደብረ ፡ ሲና — አንተ ፡ ፊት ፡ ደሜ ፡ ይፈሳታሊ --- !

«አብደሻል ፡ መሰለኝ ፡ ጺወኔ ! የምለው ፡ ነገር ፡ የገባሽ ፡ አይመስ ለኝም --

« የሮማንን ፡ ያህል ፡ እንዴት ፡ መሥራት ፡ ያቅተኛል -- ? ለሷ ፡ ሥራ ፡ እፈልግልሻለሁ ፡ ብለሃታል -- ለምን ፡ ለኔስ ፡ አትፈልግል ኝም --- ?

«ነገርኩሽ ፡ እንግዲህ ! አቶ ፡ ወልዱን ፡ ይዘሽ ፡ ታረቂ ፡ ተመለ ሽና ፡ ከናትሽ ፡ ጋር --

«አብዬ ፡ ወልዱንማ ፡ መቼ ፡ አጣሁት -- የፈለግሁት ፡ አንተን ፡ ሆንዩ -- አንተን ፡ ባመንሁ— ስንቀዠቀዥ ፡ መጣሁ ፡ እንጂ --- ?

«አሁንም ፡ ልትመለሽ ፡ ትችያለሽ - - -

«ልብ ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ ከቀረ ፡ በጄ ፡ ይላል - - ?

«በጄ ፡ እንዲልሽ ፡ ማድረግ - - -

« - - ከማዬም—ከባዬም—ከጕርፉም - - ከማንም ፡ ከማንም ፡ አብ ልጨ ፡ የምወደው ፡ አንተን ፡ ብቻ ፡ ነው - - እባላገር ፡ ብመለስ ፡ ርግ ጠኛ ፡ ነኝ ፡ እምታለሁ - - እንዴት ፡ እንዴት ፡ ትጨክናለህ ፡ በኔ - - ስሞት ፡ ዝም ፡ ትላለህ - - - ? » በላይ ፡ ሹልክ ፡ ይልና ፡ ይወጣል « የትም ፡ አትተወኝ - - አትተወኝ - - አትተወኝ - - ይዘሽኝ ፡ ሂድ - - የትም ፡ ጅብ ፡ ይብላኝ ፡ ካንተ ፡ ጋር ፡ ሄጄ - - - » እያለች ፡ እሜማው ፡ ላይ ፡ ዘፍ ፡ ትላለች ።— ሰውነቷን ፡ ሁሉ ፡ እንደ ፡ ሰደቻ ፡ ይመታታል ።— ከሙ ጥኗም ፡ መንጭቆ ፡ የሚወረውራት ፡ ኀይል ፡ የተነሣ ፡ ይመስል ፡ አንድ ፡ እግሩን ፡ ጥርቅም ፡ አድርጋ ፡ ትይዛለች ። — መጀመሪያ ፡ እያንዘረዘረ ፡ ቀጥሎ ፡ እያንሰቀሰቀ ፡ ከዚያም ፡ በየትዝታው ፡ እየቆነጣጠረ ፡ እያለሳ ለሰ ፡ መምቦልቦል ፡ ይጀምራል ፡ እንባዋ ።— ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ታፍኖ ፡ የቆ የና ፡ በልብ ፡ ውስጥ ፡ የሚግፈጠፈጥ ፡ ዳፈን ፡ አውጥቶ ፡ የሚያበርድና ፡ ሐዘንና ፡ ሥቃያትን ፡ የሚያስጥም ፡ ይመስል ።— እያለሳለሰ - - እያለ ሳለሰ - - ይወርዳል - - ይወርዳል - - ቀስ ፡ በቀስ — ህቅታው - - ስር ቅታው ፡ ሁሉ ፡ እየቀረ - - ድምፅ ፡ የሌለው ፡ ውርደት - - ይወርዳል - - ጽናትና ፡ ፈውስን ፡ ያገኘችበት ፡ ይመስል ፡ በፊቷ ፡ ላይ ፡ ባበጀው ፡ መንገድ ፡ ፍልቅ ፡ ፍልቅ ፡ እያለ - - ብድግ ፡ ስትል ፡ እንዳቋረ ፡ አሸንዳ ፡ ይጀጅራል ።— አደፍርስን ፡ አልተመለከተችውም ። በሩን ፡ ከፍታ ፡ ልትወጣ ፡ ስትል ፡ ቁቁታው ፡ ይቀልጣል — እውጪ ።— ወይዘሮ ፡ አሰጋሽ ፡ ወንድማቸውን ፡ አቶ ፡ ወልዱንና ፡ ሁለት ፡ ፖሊሶች ፡ አስከ ትለው ፡ ይደርሳሉ ።— በላይ ፡ ራቅ ፡ ብሎ ፡ ተከትሏቸዋል ።—

## ፵፯

# አደፍርስ

ጺወኔና ፡ አደፍርስ ፡ ተይዘው ፡ ፖሊስ ፡ ጣቢያ ፡ ይሄዳሉ ። ቃል ፡ ያሠረችውን ፡ ልጃገረድ ፡ ከትውልድ ፡ አገሯ ፡ አስኰብሎ ፡ በማጉደፍ ፡ ወንጀል ፡ ይከሰሳል ፡ አደፍርስ ።— ጺወኔ ፡ ቃሏን ፡ ትሰጣለች ።—

«ለመሆኑ ፡ ምን ፡ አደርግልሻለሁ ፡ ቢልሽ ፡ የሞቀ ፡ ቤትሽን ፡ ጥለሽ ፡ ኮበለልሽ ? » ይጠይቃታል ፡ ፖሊሱ ።

« ምንም ፡ አደርግልሻለሁ ፡ አላለኝ ! » ትመልሳለች ፡ ጺወኔ ።—

« እሱ ፡ ነው ፡ ግን ፡ ያስኮበለለሽ - - ?

« አላስኮበለለኝም - - -

« እውነቱን ፡ ተናገሪ ፡ ኋላ ፡ አንቺ ፡ መድረሻ ፡ ቢስ ! » እያሉ ፡ ይን ጕራደዳሉ ፡ ወይዘሮ ፡ አሰጋሽ ።—ፖሊሱ ፡ ከቢሮው ፡ ያስወጣቸዋል ።—

« ቃል ፡ ያሠርሽ ፡ ልጃገረድ ፡ ነሽ ? » ይጠይቃታል ፡ ፖሊሱ ።— አሰጋሽ ፡ እንደገና ፡ ወደ ፡ ቢሮው ፡ በራፍ ፡ ይመጣሉ ።—

« ቃል ፡ አላሠርኩም ! » ትመልሳለች ፡ ጺወኔ ።—

« እንዴት ፡ አባሽ፡ብለሽ - - ! » ይጮሃሉ ፡ ወይዘሮ ፡ አሰጋሽ ፡ ውጪ፡ እንደቆሙ « እንዴት ፡ ብትፏንኚ ፡ ትዋሻለሽ - - ! ጕርፉ ፡ ምንሽ ፡ ነው ፡ በይ - - ? ምንሽ ፡ ነው ? ከጕርፉ ፡ ጋር ፡ አልተፈጣጠምሽም ? አልተፈጣጠምሽሞይ - - ? » ዘለው ፡ ሊጨቡጿት ፡ ዓይነት ፡ ይሻቸ ዋል ፤ በኀይል ፡ ይይዝና ፡ ያቆማቸዋል ፡ በር ፡ ላይ ፡ የቆመው ፡ ፖሊስ ።—

« ፊርማም ፡ ምንም ፡ የለ ? » ይጠይቃል ፡ ፖሊሱ ፡ እንደገና ።—

« ምነው ፡ የሽማግሌ ፡ ቃልስ ፡ ቢሆን ? የምን ፡ የወረቀት ፡ ቅርንጥ ፡ ነው ፡ ደሞ - - ? እኔ ፡ አሰጋሽ ፡ ከወረቀት ፡ እበልጣለሁ - - - ! » ቀጥለዋል፡ ወይዘሮ ፡ አሰጋሽ ።—

« ፊርማ ፡ የለሽሞይ ፡ ነው ፡ የምልሽ ? » ይጠይቃል ፡ ፖሊሱ ።—

«የለኝም ! » ትመልሳለች ፡ ጺወኔ ።

«ድግስም ፡ ፍጥምጥምም ፡ አልነበራችሁ - - ?

«አልነበረንም - - - ?

«እንዴት ፡ አባሽ ፡ ብለሽ - - ! የተደገሰው ፡ ድግስ ፡ እንኳ ፡ ተበልቶ ፡ ሳያልቅ - - » ጣልቃ ፡ ይገባሉ ፡ እያከታተሉ ፡ ወይዘሮ ፡ አሰጋሽ ፡፡—

«አሁን ፡ የምጠይቅሽን ፡ ጥያቄ ፡ ተጠንቅቀሽ ፡ መመለስ ፡ አለ ብሽ - - - » ያስገነዝባል ፡ ፖሊሱ « አደፍርስ ፡ የሚባለው ፡ ሰው ፡ ክብረ ፡ ድንግልናሽን ፡ ደፍሯል ? አልደፈረም - - !

«አልደፈረም !

«እምልሽኮ ! ምናልባት ፡ አርማኒያ ፡ በሰነበተበት ፡ ጊዜ - - -

«በጭራሽ - - - !

«እዚሁ ፡ ቤት ፡ ነው ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ከመጣሽ - - - !

«አዎ ፡ እዚሁ ፡ ቤት ፡ ነው - - -

«ተማሪዎቹ ፡ ወደ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ሲሄዱለት - - -

«እንደ ፡ መጣሁ ፡ እዚሁ ፡ ነው ፡ ያረፍኩት - - -

«አገባሻለሁ ፡ በሚል ፡ ተስፋ ፡ ደልሎሽ ፡ እንደሁ - - -

«ከመጣሁ ፡ ጀምሮ ፡ ዛሬ ፡ ገና ፡ ነው - - -

«ፍቅር ፡ መቼም ፡ የማያሠራው ፡ ሥራ ፡ የለ - - እና - - ምናል ባት ፡ ከውዴታሽ ፡ የተነሣ - - - » አንገቷን ፡ ቀርቀር ፡ አድርጋ ፡ መሬት ፡ መሬቱን ፡ ትመለከታለች— አትመልስለትም ፡ ጺወኔ ፡፡—

«ትወጂዋለሽ ፡ አትወጂውም ፡ አደፍርስን - - - » ይጠይቃታል ፡ ፖሊሱ ፡ የጀመረውን ፡ በሌላ ፡ ዓይነት ፡ መንገድ ፡፡— አትመልስለትም ፡ እሷ ፡ ግን « መቼም ፡ እዚህ ፡ የመጣሽበት ፡ አንድ ፡ ምክንያት ፡ አለ - - ይ ልቅ ፡ ነግረሽን - - - » ይቀጥላል ፡ ፖሊሱ ፡፡—

«ቁርዝ ፡ መሳይኮ ፡ ቢኖር ፡ እኔው ፡ ራሴ ፡ ባናገርኳት - - ዋይ ፡ ነዶ ! » ይናገራሉ ፡ ወይዘሮ ፡ አሰጋሽ ፡ ከበር ፡ ውጪ ፡ እንደቆሙ ፡፡—

« እንግዲያው ፡ ለምን ፡ ኮበለልሽ ? ! » ይጠይቃታል ፡ ፖሊሱ ፡ የቁጣ ፡ ጅመራ ፡ በሚመስል ፡ አንደበት ፡፡—

«ጐርፉን ፡ ማግባት ፡ ስላልፈለግሁ - - - » ትመልሳለች ፡ ጺወኔ ፡ ቀስ ፡ ብላ ፡፡—

«እንዲያ ፡ ነው ፡ እንጂ - - ! ተፈጣጥመሽ ፡ ነበር ፡ ማለት ፡ ነዋ - - ገብ ቶኛልኮ ፡ ከቅድሙም ፡ እውነት ፡ እንዳልተናገርሽ - - እንዲያ ፡ ነው - - እን ዲያ ፡ ነው - - - !

« ማለቴ - - በሮማን ፡ ሠርግ ፡ ሊድሩኝ - - -

« እኮ ፡ ሠርግሽ ፡ መድረሱን ፡ ሲያይ ፡ በጐን ፡ መጣና ፡ አቶ ፡ አደፍርስ - - -

«እሱ ፡ በጐን ፡ የመጣበትም ፡ ነገር ፡ የለ - - -



«ባንቺ ፡ ስውነት ፡ ውስጥ - - እንዲህ—እንዲህ—እንዲህ - - እንዲህ ፡ ያለ ፡ ነገር - -

«ጥሩ ፡ ጥሩ ፡ በቀጥታ ፡ አባብሎ ፡ አስኮበለለሽ ፡ እንበል - - -

«እንዴት ፡ ብዬ ፡ ልንገራችሁ - - -

«ግዴለም ፡ ግዴለም ፡ ገብቶናል - - ካስኮበለለሽ ፡ በኋላ ፡ ደሞ ፡ እዚህ ፡ ቤት ፡ አስቀመጠሽ - - ከተማሪዎቹ ፡ ጋር - - -

«እኔው ፡ ራሴ ፡ ነኝ ፡ እዚህ - - - ከበላይ ፡ ጋር - - -

« የተያዘ ፡ እንደሁ ፡ ከልጃገረዶች ፡ ጋር ፡ ነው ፡ ያኖርኳት ፡ ለማለት - - -

« በላይ ፡ ነው ፡ እዚህ ፡ ያስቀመጠኝ ፡ ነውኮ ፡ የምለው - - -

«በላይ ? በላይ - - - ? » ወደ ፡ አቶ ፡ ወልዱ ፡ መልከት ፡ ይልና « ግዴለም ፡ ግዴለም ፡ አያጣላንም ፡ ይኸ - - ብቻ ፡ አሁን ፡ ዋናው ፡ ነገር ፡ ክብርሽን ፡ የደፈረው - - -

«አልደፈረም ፡ ብያለሁኮ ፡ ቅድም - - -

«አሃ ! ክብርናሽ ፡ አልተደፈረም ፡ እንበላ ፡ ታዲያ - - - ? » መልስ ፡ ከመስጠቷ ፡ በፊት ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ትቆያለች ።—

«ሌጊዎን ፡ እንኳን ፡ አልደፈራትም ፡ የኔን ፡ ልጅ - - - ! » ይላሉ ፡ ወይዘሮ ፡ አሰጋሽ ፡ ወደ ፡ በሩ ፡ እንደ ፡ መምጣት ፡ ይሉና ።—

ፖሊሱ ፡ እንደገና ፡ መጠየቅ ፡ ይጀምራል ፡ እየተስፋፋ « ሕግሽ ፡ አልተደፈረም ፡ ማለት ፡ ነው - - -

« ይመለጥ ፡ መስሏታል ፡ በዚህ ፡ ብቻ - - ምናሳባለን ፡ ነው ፡ የማመጣት - - ጉዱን ፡ የምታወጣውን - - » ጮክ ፡ እንደማለት ፡ ብለው ፡ ደሞ « ይመለጥ ፡ መስሎሻል ፡ በዚህ ! ምናሳባለን ፡ ነው ፡ የምናመጣት - - ! ጉድሽን ፡ የምታወጣውን - - -

« አልመለሰችልንምኮ ፡ ገና - - ! » ወደ ፡ እሷ ፡ መለስ ፡ ይልና ፡ « ምነዋ - - ! ቀላል ፡ ነውኮ ፡ ጥያቄው - - ክብርናሽ ፡ ተገሷል ፡ አልተገሰሰም - - ? አጭር ፡ መልስ ፡ ነው ፡ የምፈልገው - - ተገሷል ፡ አንድ ፡ ቃል - - አል . . .

«ተገሷል - - ! » ትመልሳለች ፡ ድክም ፡ ባለ ፡ አንደበት ።—

«የዶቃቂት ፡ ሚካኤል ፡ ያለህ ! ! » ይጮሀሉ ፡ ወይዘሮ ፡ አሰጋሽ ።—

አደፍርስ ፡ ሰውነቱ ፡ ይለዋወጣል ።— ጺወኔ ፡ ቀና ፡ ብላ ፡ ታየውና ፡ የተናገረችውን ፡ ትደግማለች ።—

«ክብርናዬ ፡ ተገሿል - - - ! »

« እና ፡ ታዲያ ፡ ለምን ፡ ትዋሻለሽ ? አቶ ፡ አደፍርስ ፡ ነው ፡ ማለት ፡ ነው ፡ የገሰሰው - - » ይናገራል ፡ ፖሊሱ ፡ ሳቅ ፡ ሳቅ ፡ ለማለት ፡ እየቃ ጣው ።— አደፍርስ ፡ ጣቶቹን ፡ ይጨብጥ ፡ ይዘረጋል ።— ጥርሶቹን ፡ እንደ ፡ ማፋጨትም ፡ ይሞካከረዋል « አቶ ፡ አደፍርስ ፡ ነው ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ቃል ፡ ያሠርሽውን ፡ ልጃገረድ ፡ አስኮብሎ ፡ አምጥቶ ፡ ሕግሽን ፡ የደፈረው ? » ይጠይቃል ፡ ፖሊሱ ፡ ያስተካክልና ።—

«አቶ ፡ አደፍርስ ፡ አላስኮበለለኝም - - ሕጌንም ፡ አልደፈረ ! » ትመልሳለች ፡ ጺወኔ ።—

« ግዴላችሁም ፡ ምናልባት ፡ በኃይል ፡ አንቆ ፡ ፈጽሞት ፡ እንደ ሁኮ ፡ ድርጊቱን ፡ ጭንቅላቷም ፡ ተነክቶ ፡ ሊሆን ፡ ይችላል - - » አስ ተያየት ፡ ያቀርባል ፡ ፖሊሱ ፡ ወደ ፡ አቶ ፡ ወልዱ ፡ መለስ ፡ ይልና ።—አቶ ፡ ወልዱ ፡ ምንም ፡ አይናገሩም ።—

«እኔ ፡ ጭንቅላቴ ፡ ደኅና ፡ ነው - - - ስለ ፡ ክብሬ ፡ ነው ፡ ማወቅ ፡ የፈለጋችሁት - - አርማኒያ ፡ ነው ፡ ያስወሰድሁት ።— እውሃ ፡ መቅጃ ።— እናቴ ፡ ትቆጣኛለች ፡ ብዬ ፡ ፈርቼ ፡ ነው ፡ ከቤትም ፡ የኮበለልሁት - - አቶ ፡ አደፍርስ ፡ ምንም ፡ ያደረገው ፡ ነገር ፡ የለ - - -

«አይደረግም - - ! አይደረግም - - ! የኔን ፡ ልጅ ፡ የሚደፍራት ፡ የለም ፡ አርማኒያ ! ሌጊዎን ፡ እንኳን ፡ ቢሆን - - - ! ባኮሪዶ ፡ ተጭኖ ፡ የመጣ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ! ! አይደረግም ! የኔን ፡ ልጅ ፡ የሚነካት ፡ የለም ፡ አርማኒያ - - ሌጊዎን ፡ እንኳን ፡ ቢሆን - - ሌጊዎን ፡ እንኳን ፡ ቢሆን - - - » ራሳቸውን ፡ እንደ ፡ መሳት ፡ ያደርጋቸዋል ፡ ወይዘሮ ፡ አሰጋሽን « - - ቀበ ርኋ ! ቀበርኋ ! ቀበርሁ ፡ ልጄን - - - ለሌጊዎን ፡ ሰጠሁ ፡ ልጄን - - - ከእን ግዲህ ፡ ወዲያ ፡ ምን ፡ ልጅ ፡ አለኝ ! ምን ፡ ልጅ ፡ አለኝ ? ቀብሪያለሁ ፡ ማለት ፡ ነው ።— ቀብሪያለሁ ፡ ማለት ፡ ነው ።— ምን ፡ ልጅ ፡ አለኝ ! መካን ! መካን ! የሌጊዎን ፡ ሲሳይ - - - ዓይንሽን ፡ አያሳየኝ ፡ ሊቀ ፡ መል አኩ - - ሬሳዬ ፡ ዳር ፡ እንኳ ፡ እንዳትደርሽ - - እሾህ ፡ ሆኖ ፡ ይወጋ ሻል - - አጥንታቸው ፡ የናት ፡ ያባቴ ! እሾህ ፡ ሆኖ ፡ ይወጋሻል - - እሾህ ፡ ሆኖ - - እሾህ ፡ ሆኖ - - » አቶ ፡ ወልዱ ፡ ብድግ ፡ ይሉና ፡ እየደጋገፉ ፡ ይዘ

ዋቸው ፡ ይሄዳሉ ፡ እኅታቸውን ።—ፖሊስ ፡ ጣቢያው ፡ አደፍርስን ፡ ያሰና ብተዋል ።— ውኃ ፡ የጠጣ ፡ የወይራ ፡ ጉርማጅ ፡ በመምሰል ፡ ላይ ፡ ያለ ውን ፡ ፊቱን ፡ በይበልጥ ፡ አቀጭሞ ፡ አፉን ፡ አሆምጥጦ ፡ ዓይኖቹን ፡ በማለቅ ፡ ላይ ፡ ያሉ ፡ ሁለት ፡ በመቅረዝ ፡ ሊዋጡ ፡ የደረሱ ፡ የሻማ ፡ ጉጦች ፡ አስመስሎ —

«ባንቺ ፡ ሰውነት ፡ ውስጥ - - እንዲህ — እንዲህ — እንዲህ - - እን ዲህ ፡ ያለ ፡ ነገር - - አለ ፡ ብዬ ፡ አላስብም ፡ ነበር ! » ይላትና ፡ ተመና ጭቆ ፡ ወጥቶ ፡ ይሄዳል ።— ጥርኘ ፡ ብርኘ ፡ እንደሚል ፡ ናፍታው ፡ ሊያልቅ ፡ እንደ ፡ ደረሰ ፡ ኩራዝ ፡ ዓይኖቿን ፡ ለመግለጥ ፡ እየሞከረች ፡ ከፖሊስ ፡ ጣቢያው ፡ ስትወጣ - - በላይ ፡ ቶሎ ፡ ይልና ፡ ደገፍ ፡ ያደርጋ ታል ።—

# ፶፰

# አደፍርስ

አደፍርስ ፡ ቤት ፡ ያገኘና ፡ ይከራያል ።— እናቱ ፡ ወይዘሮ ፡ አካላትና ፡ ገረዳቸው ፡ አጣሁ ፡ ወሮታም ፡ ካዲስ ፡ አበባ ፡ ተመልሰውለታል ።—እተ መደበበት ፡ አብዬ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ አማርኛና ፡ እንግሊዝኛ ፡ ቋንቋዎ ችን ፡ ማስተማሩን ፡ ቀጥሏል ።—ከሥራው ፡ እቤቱ ፡ ሆኗል ፡ ፕሮግራሙ ።— ካለፍ ፡ አገደም - - - ያውም ፡ ከክብረት ፡ ጋር ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ - - ካርታ ፡ ለመጫወትም ፡ ሆነ ፡ ቢራ ፡ ለመጠጣት ፡ መኪና ፡ መንገድ ፡ ዳር ፡ አለው ፡ ሆቴል ፡ ዘንድ ፡ ካልወጣ ፡ በስተቀር ።— ሮማን ፡ አደፍርስን ፡ ፈልጋ ፡ በማግኘት ፡ ደጋግመው ፡ ከተወያዩ ፡ በኋላ ፡ ለጊዜው ፡ ራቅ ፡ ብላ ፡ ሄዳ ፡ በተመቻቸ ፡ ጊዜ ፡ እንድትመለስ ፡ ይመክራትና ፡ የካቲካላ ፡ ነጋዴዋን ፡ ቤት ፡ ለቃ ፡ ደብረ ፡ ብርሃን ፡ ሄዳ ፡ ቡና ፡ ቤት ፡ ትቀጠራ ለች ።— በላይ ፡ የሁለተኛ ፡ ደረጃ ፡ መልቀቂያ ፡ ፈተናውን ፡ ያልፍና ፡ ዩንቨርስቲ ፡ ይገባል ። ጉርፉ ፡ ጂወኔ ፡ እንዳጫወተችው ፡ ሁሉ ፡ አደፍ ርስን ፡ አምናው ፡ አብራው ፡ ተኝታ ፡ ያጉደፋት ፡ ይመስለውና ፡ ቂምና ፡ በቀል ፡ ልቡን ፡ እንዳነደደው ፡ ተነሥቶ ፡ ጠባሴ ፡ ይወጣና ፡ ወታደርነት ፡ ይመለመላል ። ወይዘሮ ፡ አሰጋሽ ፡ እዚያው ፡ አርማኒያቸው ፡ ተመል ሰዋል ።— ብቸኝነትና ፡ እርጅና ፡ እየተጫናቸው ፡ ቢሄድም ፡ ልባቸው ፡ ገና ፡ አላረጀም ።— አሁንም ፡ ቢሆን ፡ ፈቃዳቸው ፡ አይጣስም ።— አሁ ንም ፡ ቢሆን ፡ የፈለጉትን ፡ ከማድረግ ፡ ወደ ፡ ኋላዬ ፡ አይሉም ።—አቶ ፡ ወልዱን ፡ መጽሐፈ ፡ ቄደር ፡ አስነክረው ፡ ታርቀዋቸው ፡ ስለነበረ ፡ ጂወ ኔንም ፡ ይቅር ፡ እንዲሏት ፡ የምትነከረውን ፡ መጽሐፍ ፡ ዓይነት ፡ ስላላገ ኙት ፡ ሁለዜ ፡ ያጠያይቃሉ - - ያወጣሉ ፡ ያወርዳሉ ።—

## ፺፱

# አደፍርስ

ጺወኔ ፡ ከአጐቷ ፡ ጋር ፡ ተቀምጣለች ።— ከፖሊስ ፡ ጣቢያው ፡ ሁነት ፡ ወዲህ ፡ ምድራዊ ፡ የሰው ፡ ኑሮ ፡ ያስጠላት ፡ ይመስላል ።— ከመንፈሳውያን ፡ ሰዎች ፡ ጋር ፡ መነጋገር ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መሳም ፡ ማዘውተር ፡ ሆኗል ፡ ሥራዋ ።— አደፍርስን ፡ ከእናቷ ፡ ጥላቻና ፡ መራራ ፡ ንግግር ፡ ያወጣችው ፡ መስሏት ፡ ሕን ፡ ሳይደፈር ፡ ተደፍሯል ፡ ብላ ፡ የሰ ጠችው ፡ ቃሏ ፡ ኀሊናዋን ፡ እንደ ፡ ወቀሰው ፡ አለ ።—የብዙ ፡ ጊዜ ፡ ሱባ ዔና ፡ ጸሎት ፡ እንኳን ፡ የሚዋጀው ፡ መስሎ ፡ አይታያትም ።— እንዲ ያውም ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜማ ፡ የመኝታ ፡ ክፍሏን ፡ እየዘጋች ፡ ማልቀስ ፡ ነው ፡ ሥራዋ -- በተለይ ፡ አደፍርስ ፡ በርግጥ ፡ ክብርናዋን ፡ አስወስዳለች ፡ ብሎ ፡ አምኖ ፡ ያመናጨቃትና ፡ የጠላት ፡ መሆኑን ፡ ባሰበችው ፡ ጊዜ -- ማል ቀስ ፡ ማልቀስ ፡ ነው ፡ ሥራዋ ።— ቤቱንስ ፡ ፈልጌ ፡ ብደርስበት -- ከክብሬስ ፡ ነኝ ፡ ብለው --እንዴት ፡ አድርጎ ፡ ያምነኛል ---? ያሁኑስ ፡ ነገሬ ፡ ውሸት ፡ ያለመሆኑን ፡ በምን ፡ ያውቀዋል --? አምላኬ ! አምላኬ ! የሚበጀውን ፡ መንገድ ፡ አሳየኝ -- በበትረ ፡ መንግሥትህ ፡ አትርሳኝ -- እያለች ።— አንዳንዴ ፡ ደግሞ ፡ የራሷን ፡ ክብር ፡ ለሱ ፡ ክብር ፡ ስትል ፡ ተገፋ ፡ ያሳየችው ፡ ተጋድሎ ፡ ያልገባው ፡ መሆኑን ፡ ስታስበው ፡ ለወደፊቱም ፡ ቢሆን ፡ ያደረገችለትን ፡ መሥዋዕትነት ፡ ያውቀው ፡ ይሆ ናል ፡ የሚል ፡ ተስፋዋ ፡ እየመነመነ ፡ መሄዱን ፡ ስታየውና ፡ ሞታ ፡ እንኳን ፡ ቢሆን ፡ በትዝታው ፡ የመኖር ፡ መጽናናት ፡ እንዳልነበራት ፡ ስትገነዘበው ፡ የሠራ ፡ አካላቷን ፡ ያቃጥላትና ፡ እንደ ፡ እብደት ፡ ዓይ ነት ፡ ስሜት ፡ ብረሪ ፡ ብረሪ ፡ የሚል ፡ አጣድፊኝ ፡ ነው ፡ የሚነዛባት ።— አልፎ ፡ አልፎም ፡ ቢሆን ፡ ብቅ ፡ ያሉ ፡ እንደሆን ፡ ነው ፡ አባ ፡ ዮሐንስ ፡ ትንሽ ፡ ወደሷነቷ ፡ የምትመለሰው ።— የሚናወጸው ፡ መንፈሷ ፡ የሚረ ጋጋላት -- ሰውነቷን ፡ የሚያስጨንቀው ፡ ንዚት ፡ የሚነሣላት —

« --- አንዳንዱ ፡ ለምድራዊ ፡ ኑሮ ፡ እንደሚስማማ ፡ ሆኖ ፡ ይፈ ጠራል -- ከባላባት ፡ መካከል ፡ ተወልዶ ፡ ባላባት ፡ ይሆናል ።— በሰው ፡ ልጅነት ፡ አጥንቱ ፡ በባላባትነት ፡ ንብረቱ ፡ ይንደላቀቃል ።—ችግርና ፡

መከራ ፡ የሚያገኙት ፡ አይመስለውም ።— አፋሽ ፡ አከንፋሹ ፡ ጠብ ፡ ርግፍ ፡ ባዩ ፡ ዙሪያውን ፡ ይከበዋል ።— ሲናገር ፡ እውነት ፡ እውነት ፡ ሲጣራ ፡ አቤት ፡ አቤት ፡ ባዩ ፡ ግቢውን ፡ ይሞላዋል ።— ያዩት ፡ ሁሉ ፡ ይጨንቁለታል ።—ይርበተበቱለታል ።—ገና ፡ ከሩቁ ፡ ብቅ ፡ ሲል ፡ ይነሡለታል ።—ቆይቶ ፡ ሲሄድ ፡ ተሽቆጥቁጠው ፡ ይሸኙታል ።—ያለም ፡ ጠርዟ ፡ እሱ ፡ ቤት ፡ የተወሰነች ፡ ይመስለዋል ። — ከርሱም ፡ ኑሮ ፡ የተሻለ ፡ ኑሮ ፡ ይንኖራል ፡ ብሎ ፡ ለመፈለግ ፡ አይነሣም '--ገመል ፡ እንተ ፡ ስቁረተ ፡ መርፍእ ፡ እምባዕል ፡ በዊአ ፡ መንግሥተ ፡ እግዚአብሔር ---' ባለጸጋ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያትን ፡ ከመውረስ ፡ ይልቅ ፡ ግመል ፡ በመርፌ ፡ ቀዳዳ ፡ ብትወጣ ፡ ይቀላታል —ተብሎ ፡ የተነገረለት ፡ ዓይነት ፡ ሰው ፡ ይሆናል ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ባጭሩ..........................................

..................................................

...............................................

.........................................

...................................

.............................

.........................

....................

.............

......

እያሉ ፡ በመደሳሰስ ፡ ሲያጫውቷት ፡ በሌላው ፡ ዓለም ፡ ተስፋ ።—ወይም ፡ ደግሞ —

## ፳

# አደፍርስ

- - - 'ቀደስኩከ ፡ እምከርሠ ፡ እምከ'— ገና ፡ ከናትህ ፡ ማሕፀን ፡ መርጬሃለሁ ፡ እንደተባለው ፡ ገና ፡ ሲፈጠር ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የሚ መረጥ ፡ አለ - - እንደ ፡ ጳድቃኑና ፡ እንደ ፡ ሰማዕታቱ - - - ምንም ፡ እንኳ፡ ከባላባት ፡ ወገን ፡ ቢሆንም ፡ የተወለደው ፡ ባካባቢው ፡ የሚያያቸው ፡ ድሪያ ፡ ዝሙት ፡ ስካር ፡ መጋደል ፡ በጌጣጌጥ ፡ መብለጭለጭ ፡ መከዳ ዳት ፡ ምቀኝነት ፡ ተንኰልና ፡ ኩራትን ፡ የመሳሰሉት ፡ የኑሮ ፡ ተውሳ ኮች ፡ ሁሉ ፡ ያስጠሉትና ፡ በምግበ ፡ ሥጋ ፡ ምግበ ፡ ነፍስን ፡ ተክቶ ፡ በሚያልፈው ፡ ዓለም ፡ ምትክ ፡ የማያልፈውን ፡ ዘለዓለማዊ ፡ ዓለም ፡ ለማግኘት ፡ ይነሣል ።— ዘመድ ፡ አዝማዱን ፡ ጐጆ ፡ ንብረቱን ፡ ትቶ ፡ ዳባ ፡ አስኬማ ፡ መቋሚያ ፡ የመቁነን ፡ መቀበያ ፡ ቅልና ፡ ቆሬውን ፡ ብቻ ፡ ይዞ ፡ ይወጣል ።—ቁር ፡ እሚጋገርበት ፡ ወይም ፡ ሐሩር ፡ እሚያቃጥል በት ፡ ቦታ ፡ ሄዶ - - ቅጠላቅጠል ፡ ፍራፍሬና ፡ የዱር ፡ እንሰሳት ፡ ወተት ፡ ብቻ ፡ እየተመገበ ፡ በጾም ፡ በጸሎት ፡ ተወስኖ - - የጌታ ፡ አገልጋይ ፡ ሆኖ ፡ ለመኖር ፡ ቆርጦ ፡ ይመንናል - - - አንቺ ፡ የኔ ፡ ልጅ ፡ እንግዲህ ፡ ገና ፡ ስትፈጠሪ ፡ ለጌታ ፡ አገልጋይነት ፡ የተመረጥሽ ፡ ሰማያዊ ፡ መንግሥቱን ፡ ሊገልጽብሽ ፡ ያቀደሽ ፡ ነው ፡ የምትመስይኝ ።— የደረሰብሽም ፡ ፈተና ፡ እንኳን ፡ ቢሆን ፡ ያልሆንሽውን ፡ ሆኛለሁ ፡ ብለሽ ፡ የወያድሽውን ፡ ሰው ፡ ክብር ፡ ለመጠበቅ ፡ ስትይ ፡ ያሳየሽው ፡ ሰማዕትነት ፡ የጌታን ፡ መስቀል ፡ መሸከምሽን ፡ ነው ፡ የሚያሳየው ።— ወደፊትም ፡ ቢሆን ፡ ይኸን ፡ የመሳሰለ ፡ ብዙ ፡ ፈተና ፡ ይገጥምሻል ።— እና ፡ ዋናው ፡ ነገር ፡ ብቻ ፡ ወዲያ ፡ ወዲህ ፡ ሳትይ ፡ ዓይንሽን ፡ አቅንተሽ ፡ እጆችሽን ፡ አን ሥተሽ ፡ ልብሽን ፡ ለሱው ፡ ላንድ ፡ አምላክ ፡ ማደሪያ ፡ አድርገሽ ፡ 'አቤቱ ፡ አቤቱ ፡ የሚበጀውን ፡ መንገድ ፡ አሳየኝ ፤ በበትረ ፡ መንግሥ ትህ ፡ አትርሳኝ'ን ፡ ጸሎትሽ ፡ ማድረጉ ፡ ነው - - አዎ ፡ በበትረ ፡ መንግሥ ትህ ፡ አትርሳኝ ፡ ዋና ፡ ጸሎት ፡ ነው ።— የኔ ፡ ልጅ ፡ የምድራዊ ፡ ፍቅር ፡ የምድራዊ ፡ ጋብቻና ፡ የመውለድ ፡ የመክበድ ፡ ሰው ፡ አይደለሽም ።— የለም ፡ አይደለሽም ።— እና ፡ ታዲያ ፡ ካልሆንሽ ፡ ዘንዳ ፡ ከሴቶች ፡ ሁሉ ፡ ተመርጠሽ ፡ ክርስቶስ ፡ ሠምራን ፡ ቅድስት ፡ ወለተ ፡ ጴጥሮስን ፡

ቅድስት ፡ እማሙዝን ፡ ብትሆኚ - - እንግዳ ፡ ጌጥ ፡ ሊሆንብሽ ፡ እንዴት ፡ ይችላል - - - ? እንግዳ ፡ ጌጥ ፡ ሊሆንብሽ ፡ አይችልም - - ‘ቀደስኩኪ ፡ እምከርሰ ፡ እምኪ’ ብሎሻል ፡ እላለሁ ፡ እኔ ፡ አባትሽ ፡ ፈጣሪሽ ።— ምነው ፡ ዛሬምኮ ፡ ቢሆን ፡ እግዚአብሔር ፡ በሰው ፡ አድሮ ፡ ይናገ ራል - - በሰው ፡ አድሮ ፡ ይናገራል ..................................................

..................................................

..................................................

..................................................

..................................................

..................................................

..................................................

..................................................

.......

ወይም ፡ ደግሞ - - -

# ፳፬

# አደፍርስ

……

…………

……………

………………

…………………

……………………

………………………

…………………………

……………………………

--- ጎዲገ ፡ አብያትንና ፡ መንኖ ፡ ጥሪትን ፡ ዮሐንስ ፡ አፈወርቅ ፡ የሰጠው ፡ አንድ ፡ ጻድቅ ፡ ሰው ፡ ከዚህ ፡ ዓለም ፡ ሐሳብ ፡ ድኖ ፡ በዕረፍት ፡ ይኖር ፡ ነበር ።— ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ እከብር ፡ ባይ ፡ ልቡና ፡ እቤቱ ፡ እንግድነት ፡ ያድርና ፡ እንደምን ፡ ትኖራለህ ፡ ይለዋል ? ጻድቁም ፡ ጎዲገ ፡ አብያትንና ፡ መንኖ ፡ ጥሪትን ፡ ካገኘሁ ፡ ወዲህ ፡ ከዚህ ፡ ዓለም ፡ ጣጣ ፡ አርፌ ፡ እኖራለሁ ፡ ይለዋል ።— እንግዳው ፡ ሰውዬ ፡ በዚህን ፡ ጊዜ ፡ ሞኙ ፡ ተላላው ፡ 'ዐባይን ፡ ያላየ ፡ ምንጭ ፡ ያመሰግናል' -- እንዳንተ ፡ ያለ ፡ ሰው ፡ ከተማ ፡ ገብቶ ፡ ተሾሞ ፡ ተሸልሞ ፡ ቤት ፡ ሠርቶ ፡ ንብረት ፡ ገዝቶ ፡ ለተራብ ፡ አብልቶ ፡ ለተጠማ ፡ አጠጥቶ ፡ እያስተማረ ፡ ይኖራል ፡ እንጂ ፡ እንዴት ፡ እዚህ ፡ ይቆራመዳል -- ? እነዚህን ፡ ያልካቸውን ፡ የኋላ ፡ ኋላ ፡ አታጣቸውም -- ደግሞስ ፡ ከመነነና ፡ ከመነኮሰ ፡ የሰጠ ፡ የመጸወተ ፡ እንዴት ፡ እንደሚሻል ፡ ሳታውቅ ፡ ቀረህ ፡ እያለ ፡ በሆነ ፡ ባልሆነው ፡ ነገር ፡ ግራ ፡ ያጋባውና --ለንጉሥ ፡ ላሳድርህ ፡ ብሎ ፡ ይጠይቀዋል ።—ጻድቁም ፡ ዲያብሎስ ፡ መቼም ፡ አንዴ ፡ ከደጁ ፡ ደርሷልና -- ነገሩስ ፡ ደግ ፡ ነበር ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ጎዲገ ፡ አብያትንና ፡ መንኖ ፡ ጥሪትን ፡ ተከተሉኝ ፡ ብላቸው ፡ እሺ ፡ ብለው ፡ ወደ ፡ ከተማ ፡ አይሄዱልኝ -- ማንን ፡ አስከትዬ ፡ እሄዳለሁ ፡ ይለዋል ።— እደጅ ፡ የደረሰ ፡ ዲያብሎስ ፡ መቼም ፡ ተዘጋጅቷልና ፡ ፊቱው

የሚባለውን ፡ አሽከሩን ፡ አንተ ፡ ተከትለህ ፡ እያዘገምህ ፡ እኔ ፡ ዘንድ ፡ ይዘኸው ፡ ና - - እኔ ፡ ቀድሜ ፡ ቦታ ፡ አዘጋጅቼ ፡ እጠብቃችኋለሁ ፡ ይለውና ፡ ይሄዳል - - አቶ ፡ ዲያብሎስ ፡ ተንዘራፍጦ ፡ ቦታውን ፡ ይይዛል - - - አቶ ፡ ጸድቅም ፡ መጠጣት ፡ መስከር ፡ መዳራት ፡ መጋደል - - ምን ፡ ቅጡ ፡ በያይነቱ ፡ ኀጢአት ፡ አለበት ፡ ከተማ ፡ ይገባዋላ - - የዚህ ፡ ዓለም ፡ ነገር - - እንደ ፡ ጐርፍ ፡ ውሃ ፡ እያሳቀ ፡ እንደ ፡ ቆንጆ ፡ ሴት ፡ ወይዘሮ ፡ እየደለለ ..........................................................

..........................................................

....................................................

..............................................

........................................

..................................

..........................

....................

............

......

# ፳፪

## አደፍርስ

አጕቷ ፡ እቶ ፡ ወልዱ ፡ ደሞ ፡ በበኩላቸው ፡ የራሳቸው ፡ ዓይነት ፡ ድግግሞሽ ፡ ነበራቸው - - ማታ ፡ ማታ ፡ ገብታ ፡ ከፍ ፡ ካለ ፡ በኋላ ፡ አብ ረዋት ፡ ቁጭ ፡ ሲሉ —

- - - ሁሉ ፡ ነገር ፡ እንዳስቀመጡት ፡ አይገኝም ።— እንዳሰቡት ፡ አይሳካም - - የሁሉ ፡ ነገር ፡ ውዶታ ፡ አይዘልቅም - - ይለዋወጣል - - ይቋ ረጣል ።— ምን ፡ እለ ፡ ብለሽዋል ፡ የዚህ ፡ ዓለም ፡ ኑሮ ? እንዳደረጉት ፡ ነው ።— ሳትደሰች ፡ ተደስተሽ - - ምንም ፡ ነገር ፡ ሳትሆኚ ፡ ተከፍተሽ ፡ የምትኖሪበት ፡ ዓለም ..........................................................

..........................................................

....................................................

...............................................

.........................................

....................................

...............................

.........................

..................

......

ወይም ፡ ደግሞ - - -

# ፳፫

......

............

..................

........................

..............................

....................................

..........................................

................................................

....................................................

....................................................

- - - እናትሽ ፡ የምትቆጨው ፡ የምትናደደው ፡ ለማ ፡ ክብር ፡ ለማ ፡ መታወቅ ፡ ይመስልሻል ? ለአንቺው ፡ ነው ።— ቆላና ፡ ደጋ ፡ የምትረግጠው ፡ የምትጥረው ፡ የምትግረው ፡ ለማ ፡ ይመስልሻል ? ለአንቺው ፡ ነው ።— የለም ፡ የለም ፡ ጺወኔ ! መንገድ ፡ ፈልገን ፡ መታረቅ ፡ አለብሽ ፡ አሁንስ ፡ ከናትሽ ።— ያባትሽን ፡ ሀብት ፡ እንኳን ፡ መሰብሰቡስ ፡ ቀላል ፡ ነገር ፡ ይመስልሻል ? በጽሑፉም ፡ በምኑም ፡ ብትረጃትኮ ፡ ከድካም ፡ አዳንሻት ፡ ማለት ፡ ነው ።—እስኪ ፡ ተመልከች ፡ የጊዜውን ፡ አካሄድ - - - ከአራት ፡ ወር ፡ በላይ ፡ መሆኑ ፡ ነው ፡ እንግዲህ ፡ ከኛ ፡ ጋር ፡ ከተቀመጥሽ ።— እርግጥ ፡ ማለፊያ ፡ እንድትለያት ፡ አትሻም ።— እኔም ፡ ብሆን ፡ አጉል ፡ ልማድ ፡ አስለምደሽኛል ፡ ማታ ፡ ማታ ፡ ቁጭ ፡ እያልን ፡ ማውራት - - ከማን ፡ ጋር ፡ አወጋ ፡ ነበር ፡ አንቺ ፡ ባትኖሪ ? የማለፊያን ፡ ነገር ፡ ታውቂዋለሽ ፤ ከማድ ፡ ቤት ፡ አትወጣ—እንደ ፡ ተርመጠመጠችው ፡ ይመሽላታል........................................................................

....................................................

............................................

....................................

..............................

........................

..................

............

......

# ፳፩

# አደፍርስ

*ወይም ፡ ደግሞ ፡ አንዳንድ ፡ ታሪክ ፡ በማውራት - - -*

......

............

................

....................

........................

............................

................................

....................................

........................................

............................................

- - በቁስጥንጥንያ ፡ ከተማ ፡ አንድ ፡ ወሮበላና ፡ ፈታል ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ ይኖር ፡ ነበር ።— ጥሩ ፡ ጩልፋትና ፡ የፈታልነት ፡ ሥራውን ፡ አጣርቶ ፡ የሚያውቅ ፡ ስለነበረ ፡ አገሬው ፡ ወሮበሌ ፡ ወይም ፡ ፈታሌ ፡ ይሉት ፡ ነበር ።—እሱ ፡ ግን ፡ ሥራው ፡ ስለነበር ፡ እምብዛም ፡ ሰዎቹ ፡ ከስሙ ፡ ጋር ፡ አዛምደው ፡ የሚያስቡት ፡ አጉል ፡ መልኩ ፡ አይታየውም ፡ ነበር ።— ነውርነቱንም ፡ የተገነዘበው ፡ ሰው ፡ አይመስልም ፡ ነበር ፡ ባኳኋኑ ።— ሲጠሩት ፡ አቤት ፡ ሲልኩት ፡ ወዴት ፡ ጩልፋትነቱን ፡ በርግጥ ፡ ያስመሰክር ፡ ነበር ፡ በድርጊቱ ።— እያደር ፡ ግን ፡ በተለይ ፡ በፈታልነት ፡ ሥራው ፡ መበለቶችንና ፡ ባል ፡ የለሾችን ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ባለ ፡ ትዳሮችንም ፡ ጭምር ፡ እያቃጠረ ፡ ከተማውን ፡ አጉል ፡ ስም ፡ ስላሰጠው ፡ አገሬው ፡ በተለይ ፡ ረጋ ፡ ያለና ፡ የተደላደለ ፡ ኑሮ ፡ ለመኖር ፡ የሚፈልገው ፡ ጠላው ።— እንዲያውም ፡ ካንድ ፡ ሁለት ፡ ጊዜ ፡ በጥይት ፡ ሊገድሉት ፡ ፈልገው ፡ ሳቱት ።— በቁስጥንጥንያ ፡ ከተማ ፡ ለመኖር ፡ አልቻለም ።— ወደ ፡ አሜሪካን ፡ አገር ፡ ተሰደደ ።— አሜሪካ— በዚያው ፡ በለመደው ፡ ሥራው ፡ ቀጠለ ።— እና ፡ በጥቂት ፡ ዓመታት ፡ ውስጥ ፡ የሱን ፡ ዓይነት ፡ ሥራ ፡ ይሠሩ ፡ ከነበሩት ፡ ካገሬው ፡

ሰዎች ፡ ይበልጥ ፡ ታወቀ ።— ሀብት ፡ አገኘ ። በለጸገ ።— ነገር ፡ ግን ፡ ባለጸጋ ፡ ብርቅ ፡ ባልሆነበት ፡ ባሜሪካ ፡ የሱ ፡ ብልጽግና ፡ ከሌሎች ፡ በልጦ ፡ ሊያሳውቀው ፡ አልቻለም ።— የሰበሰበውን ፡ ሰብስቦ ፡ ወደ ፡ ትውልድ ፡ ሀገሩ ፡ መመለስ ፡ ግድ ፡ ሆነበት ።— ምን ፡ አለ ፡ አልሽው ? የሰው ፡ ተፈጥሮ ! ገንዘብ ፡ ሲገኝ ፡ ሹመት ፡ ሹመት ፡ ሲገኝ ፡ መታወ ቅና ፡ መግነን— ምናለ ፡ ብቻ— ክብረት ፡ በሰው ፡ አገር ፡ አይደምቅምና ፡ ሀብቱንና ፡ ብልጽግናውን ፡ ይዞ ፡ ወደ ፡ ቁስጥንጥንያ ፡ ተመለሰ ።—

ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ አምሮና ፡ ተሸትሮ ፡ ፒፓውን ፡ አፉ ፡ ላይ ፡ አጉጦ ፡ እግሩን ፡ እብን ፡ በረድ ፡ ጠረጴዛው ፡ ላይ ፡ አሳርፎ ፡ ጋዜጣ ፡ ሲያነብ ፡ የተመልካቾችን ፡ ዓይኖች ፡ ስቦ ፡ ስለነበር ፡ በየቦታው ፡ ስለ ፡ እሱ ፡ መወራት ፡ ጀመረ ።— አንዳንዱ ፡ በርግጥ ፡ ፈታሌ ፡ ወሮበሌ ፡ መሆ ኑን ፡ ዐወቀ ። ሌላው ፡ ከሀብቱ ፡ ትልቅነት ፡ የተነሣ ፡ ስለተጠራጠረ ፡ በም ንም ፡ ዓይነት ፡ ሁኔታ ፡ እሱ ፡ እስከዚህ ፡ አድጐ ፡ ሊመጣ ፡ አይችልም ፡ በማለት ፡ እሱነቱን ፡ ካደ ።— ደፍሮና ፡ ቀርቦ ፡ ሊጠይቀው ፡ የመጣ ፡ ሰው ፡ ግን ፡ አልነበረም ።— የሱን ፡ የሀብታም ፡ ልብስ ፡ እነሱ ፡ ከለበ ሱት ፡ ጋር ፡ በማወዳደር ፡ ለመጠጋት ፡ አሳፍሯቸው ።- ጊዜው ፡ ይሄ ዳል -- እና ፡ ከመቆየት ፡ መቼም ፡ አስፈሪና ፡ አስደንጋጭ ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ገራም ፡ መስሎ ፡ ይታያል ።—አንድ ፡ ቀን ፡ አንድ ፡ አብሮ ፡ አደጉ ፡ የነ በረ ፡ ሰው ፡ ተጠግቶ ፡ ያነጋግረዋል -- እንዴት ፡ ዋሉ ፡ ጌታዬ ---! እረ ፡ ዐውቅዎ ፡ ይመስለኛል -- ይለዋል ።— ሀብታሙም ፡ እንዴታ ! ከማወቅም ፡ ማወቅ ፡ አብሮ ፡ አደጌ ፡ ነበርህ ፡ እንዲያውም ፡ ይመል ስለታል ።— በመቀጠልም ፡ ምነዋ ፡ ስሜን ፡ ረሳኸው ፡ እንዴ ? ይለዋል ።— አብሮ ፡ አደግም ፡ ፍራት ፡ ፍራት ፡ እያለው ፡ አዎን ፡ ጌታዬ ፡ ይቅር ፡ ቢሉኝ ፡ ስምዎን ፡ ዘንግቼዋለሁ ፡ ይመልስለታል ።— ስሜንስ ፡ አልዘነጋኸውም ፤ ታውቀዋለህ--እዚያ ፡ ከሰዎቹ ፡ ጋር ፡ ቆመህ ፡ ስትተማሙብኝ ፡ ሰምቻለሁ -- እና ፡ መፍራት ፡ አያስፈልግህም -- በዚያው ፡ በምታውቀው ፡ ስሜ ፡ ጥራኝ -- ግዴለም ! ግዴለም ፡ አትፍራ ! ይለዋል ።— ትዝም ፡ አይለኝ ፤ በፍጹም ፡ ዘንግቼዋለሁ ፡ እያለ ፡ እንደማ ሰብ ፡ ይከጅለዋል ።— ከዚያም ፡ የጥንቱ ፡ ስምህ ፡ የሚጀምርበት ፡ ፊደል ፡ አቶ ፡ ወ . . ወይም ፡ አቶ ፡ ፈ . . እንዲህ ፡ ይመስለኛል ፡ ባልሳሳት ፡ ብሎ ፡ ተናግሮ ፡ ሳይጨርስ -- አዎን ፡ አዎን ! ልክ ፡ ነው ።- አይዞህ ፡ አትፍራ ! አቶ ፡ ወሮበሌ ፡ አቶ ፡ ፈታሌ ፡ በለኝ ።- እኔ ፡ ተጠሪው ፡ ሳላ ፍር ፡ አንተን ፡ ጠሪውን ፡ ምን ፡ አሳፈረህ ? እኔ ፡ ያ ፡ ወሮበላ ፡ ያ ፡ ፈታል ፡

የምባለው ፡ ሰው ፡ ነኝ ። አንተ ፡ ቆሸሸህና ፡ ደህይተህ ፡ ስትጠብቀኝ ፡ እኔ ፡ አምሬና ፡ ከብሬ ፡ ተመለስሁ ፡ ይለዋል ።— በዚህን ፡ ጊዜ ፡ ይናደዳል ፡ ጓደኛው -- ካንተ ፡ ማማርና ፡ መክበር ፡ የኔ ፡ መልካም ፡ ስምን ፡ ይዞ ፡ በድህነት ፡ መኖር ፡ ሳይሻል ፡ ቀርቶ ? ድህነት ፡ ነውር ፡ ሆነና ፡ ትሰድበኛለህ ? ሞሽላቃ ፡ ሌባ ፡ ወሮበላ ፡ ፈታል ፡ ምናምንቴ ፡ ነውረኛ ፡ እያለ ፡ እያከታተለ ፡ ይሰድበዋል -- ሀብታሙ ፡ ግን ፡ ከምንም ፡ ሳይቆጥረውና ፡ ሳይናደድ -- ደስ ፡ እንዳለኝና ፡ የሰደብኸኝን ፡ ስድብ ፡ እንዳልዘነጋው ፡ አላፊ ፡ አግዳሚውም ፡ እንዲያነበውና ፡ እንዲያውቀው ፡ በዚህ ፡ በቀለም ፡ እዚህ ፡ እነጩ ፡ እብነ ፡ በረድ ፡ ላይ ፡ በጉልህ ፡ ጻፈው ፡ ይለዋል ።— ጓደኛውም ፡ እንደታዘዘው ፡ ይጽፈዋል ።— በዚህን ፡ ጊዜ ፡ ሀብታሙ ፡ ተኪሱ ፡ የባንክ ፡ ኖቱን ፡ መዘዝ ፡ መዘዝ ፡ አድርጐ ፡ ስድቡ ፡ በተጻፈበት ፡ እብነ ፡ በረድ ፡ ጠረጴዛ ፡ ላይ ፡ በሙሉ ፡ ይዘረጋበትና ፡ እስቲ ፡ ተሳዳቢው ፡ ጓደኛዬ ፡ አሁን ፡ አንብበው ፡ ይለዋል ።—ተሳዳቢውም ፡ አሁንማ ፡ በባንክ ፡ ኖት ፡ ሸፈንከው ፡ እንዴት ፡ ላንብበው ፡ ብሎ ፡ ይመልስለታል ።— አያ ፡ ቂሎ ፡ ይኸውልህ ፡ ገንዘብ ፡ እንደዚህ ፡ ነውርን ፡ ይሸፍናል ። ያንተን ፡ ድምፃዊ ፡ ስድብ ፡ የኔ ፡ ድምፅ ፡ የለሽ ፡ ባንክ ፡ ኖት ፡ ሸፈነው ፡ ብሎ ፡ አሰናበተው -- እየተባለ ፡ ሲወራ ፡ እሰማ ፡ ነበር ፡ ፓሪ ፡ በነበርኩበት ፡ ጊዜ ፡ እልሻለሁ ።—እና -- ስለገንዘብና ፡ በጠቅላላው ፡ ስለ ፡ ሀብት ፡ ያለሽ ፡ አስተያየት ፡ ጤነኛ ፡ አይመስለኝም ፡ ነው ፡ የምልሽ ፡ አንቺንም ።— በኋላ ፡ ይቆጭሻል ----

« ሀብታሙ ፡ በኖት ፡ ቢሸፍነው ፡ ድሃው ፡ የጻፈው ፡ ካልለ ፡ ከቃሉ ፡ አያነብለትም -- ? » በማለት ፡ መንገድ ፡ ትጀምራለች ፡ ጺወኔ ።

« ምን ፡ ለማለትኮ ፡ ይመስልሻል --- ?

« እኔም ፡ ብሆን ፡ ድህነትን ፡ እመርጣለሁ ፡ እንዲያ ፡ ሆኖ ፡ ሀብት ፡ ከማግኘት ---

« ያንቺ ፡ ሀብት ፡ በእንዲያ ፡ የተገኘ ፡ አይደለማ ? !

« ቢሆንም --! ሀብት -- ? ሀብት -- ? የእንዲህ ፡ የእንዲህ ፡ ዓይነቱ -- ሀብት --! » ይቀጥላል ፡ በእንዲሁ ፡ ዓይነት -- ልዩ ፡ ልዩ ፡ ዓይነት ፡ ቀለም ፡ እየተቀባ -- ልዩ ፡ ልዩ ፡ መልክ ፡ እያወጣ ።— ስልቾታ ፡ አይታይባትም ።—

## ፳፫

# አደፍርስ

ሮማን ፡ ከደብረ ፡ ብርሃን ፡ ተመልሳለች ።— የማርያምን ፡ ቤተክሲያን ፡ ልትስም ፡ ሄዳ ፡ ኖሮ ፡ ጺወኔንም ፡ እዚያው ፡ ታገኛትና ፡ አብረው ፡ የመኪና ፡ መንገዱን ፡ ዳር ፡ ዳር ፡ ይዘው ፡ ወደየቤታቸው ፡ ሲመለሱ ፡ አደፍርስና ፡ ክብረት ፡ አርፈውበት ፡ እነበረው ፡ ሆቴል ፡ ውስጥ ፡ ቁጭ ፡ እንዳሉ ፡ ያይዋቸዋል ።— አደፍርስ ፡ ነው ፡ ባንዴ ፡ ያወቃቸው—

« - - - ይቺ ፡ ምናምንቴ ! በሷ ፡ ቤት ፡ አልታየችም - - ደጋግሜ ፡ ባልነግራት ፡ ደሞ ፡ በሆነ - - » ብሎም ፡ ባንዳፍታ ፡ እሳት ፡ የሚሆነው ።—

« አንተ ፡ እስከዚህ ፡ ምንቸገረህ ? ለምን ፡ እንዳትገጥም ፡ ትክለክ ላታለህ - - ? ጺወኔ ፡ አብሮ ፡ አደጓ ፡ እኅቷ ፡ ነች - - » ይጠይቀዋል ፡ ክብረት ።

« በምንም ፡ ዓይነት ፡ መንገድ ፡ ቢሆን ፡ ከሷ ፡ ጋር ፡ እንዳላይሽ ፡ ብያታለሁ - - በምንም ፡ ዓይነት ፡ መንገድ - - - !

«መቼስ ፡ ከደብረ ፡ ብርሃን ፡ ከመጣች ፡ ይኸው ፡ እንግዲህ ፡ አሥራ ምስት ፡ ቀን ፡ ሊሆናት ፡ ነው ።— እና ፡ ፈልጋት ፡ አልሄደች - - እንዳጋጣሚ ፡ ቤተክሲያን ፡ ስታያት ፡ መጥታ ፡ አነጋግራት ፡ ይሆናል - - -

«ደሞ ፡ እሷ ፡ ብሎ ፡ ቤተክሲያን ፡ ሳሚ ! ማን ፡ እንድትሄድ ፡ ፈቀደላት ፡ ቤተክሲያን - - - ? ! ቤተክሲያን ፡ ሳሚ - - ! የትም ፡ ስትናዝር ፡ ቆይታ - - - !

«እውነቴን ፡ ነው ፡ የምልህ ፡ አደፍርስ ፤ የምትናደድበት ፡ ምክንያት ፡ አይታየኝም - -

«ቃሌ ፡ አለመጠበቁ - - ! ቃሌ ፡ አለመጠበቁ - - ! ከዚህ ፡ የበለጠ ፡ ምን ፡ ያናደኝ - - ? !

«እኮ ፡ ለምን - - ?

«ከቤት ፡ እንድትወጣ ፡ አልፈልግም - - በተለይ ፡ ከጂ.ወኔ ፡ ጋር ፡ ተገናኝታ ፡ እንዳያት - - -

«ምናልባት ፡ ስላንተና ፡ ስለራሷ ፡ ግንኙነት ፡ የምታወራት ፡ መስ ሎህ ፡ እንደሁ - - ?

«አሂሂ ! እማባቷ ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ ቆማ - - ? አታደርገውም - - - ደግ ሞስ ፡ ምኔ ፡ ነች - - እሷ - - ገረድ ፡ ነች - - ! በቃ - - ገረድ - - - !

«ወይዘሮ ፡ አካላት ፡ አብረውህ ፡ ናቸው ።— በዚያ ፡ ላይ ፡ አጣሁ ፡ ወሮታ ፡ አለኝ— ምስተኛ ፡ ደሞ— ሮማን - - - ? እኔ ፡ እምልህ ፡ ወር ዶፋ ፡ የልጁን ፡ አንተ ፡ ዘንድ ፡ መቀመጥ ፡ ቢሰማ - - -

« ይስማ ! በግድ ፡ አስቀምጫታለሁ ፡ እንዴ ፡ እኔ - - -

« ከበፊቱም ፡ ያስኮበለልካት ፡ አንተስ ፡ የመሰልከው ፡ እንደሁ - - -

« ይምሰለዋ !

« እጁን ፡ አጣምሮ ፡ ይቀመጥ ፡ ይመስልሃል ፡ ታዲያ ? የጉድባ ውን ፡ ታሪክ ፡ ረሳኸው ? !

« ካልሀስ ፡ ያየሁት ፡ መሰለኝ ፡ ያለችም ፡ መስሎኛል—ጴጥሮስን ፡ ሮማን - - - ብቻ ፡ ለሁሉም—እስቲ ፡ እንርሳው—እንነጋገርበት ፡ አሁን ፡ ጋሼ ፡ ክብረት - - ዝም ፡ ብለን ፡ እንጠጣ ፡ ቢራችንን - - ሌላ ፡ ሌላ ፡ ነገር ፡ እየተጫወትን - - -

በስተግራ ፡ በኩል ፡ ተማሪዎች ፡ ተሰልፈው ፡ ይመጣሉ ፡ እየዘመሩ ። በወፋፍራም ፡ ወረቀት ፡ ላይ ፡ የተጻፈ ፡ አቤቱታ ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ ተሸ ክመው - - ወታደሮች ፡ በየቦታው ፡ በተን ፡ በተን ፡ ብለው ፡ ይጠብቋቸ ዋል ።—

# ፳፪

## አደፍርስ

ጺወኔ ፡ ወደ ፡ አጐቷ ፡ ቤት ፡ ትመለሳለች « - - ዓመት ፡ ሙሉ ፡ ስጠብቀው ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ እንኳን ፡ እንዴት ፡ ዋልሽ ፡ ያላለኝ ፡ አደፍርስ - - ለካስ ፡ ፍቅሩ ፡ ለሮማን ፡ ቢሆን ፡ ኖሯል - - ? ከመጀመሪያውም ፡ ቢሆን ፡ ጨርሶ ፡ አይወደኝም ፡ ማለት ፡ ነው - - ሮማንን ፡ ነው ፡ ማለት ፡ ነው ፡ የወደደው - - ካያት ፡ ቀን ፡ ጀምሮ - - ሮማንን ፡ ነው ፡ የወደደው - - » እያለች ፡ ስትብሰለሰል ፡ እቤተክሲያን ፡ በሩቅ ፡ ያየቻት ፡ ጊዜ — በፊለፊቷ ፡ ባርኔጣዋን ፡ ወደታች ፡ ቀልበስ ፡ አርጋ —የጥላው ፡ መሥመር ፡ ልክ ፡ እከንፈሮቿ ፡ ገደማ ፡ እንደሚቆም ፡ ሆኖ ፡ ፊቷን ፡ ከፀሐዩ ፡ አጥልቶላት — ያደረገችው ፡ ታኮ ፡ ጫማ ፡ ቁመቷን ፡ ጨምሮላት— የለበሰቻቸው ፡ አጫጭር ፡ ዘመናውያን ፡ ልብሶች ፡ አምረውና ፡ አሳምረዋት—የማነች ፡ ቆንጆ ፡ በማለት ፡ ደጋግማ ፡ የተመለከተቻት ፡ በተጨማሪ ፡ ይታሰባትና ፡ የባሰውን ፡ ብስጭትጭት ፡ ትላለች ።—እቤቷ ፡ እንደ ፡ ደረሰች ፡ ሮጣ ፡ ትገባለች ፡ ወደ ፡ መኝታ ፡ ክፍሏ «- - እሷን ፡ ነው ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ከመጀመሪያውም ፡ የወደዳት - - እሷን ፡ ነው ፡ ማለት ፡ ነው ፡ የሚወዳት - -» መኝታዋ ፡ ላይ ፡ ቁጭ ፡ እያለች « እሷን ፡ የሚወዳት - - ! እሷን - እሷን ! እሷን ! እሷን - - »ትራሷን ፡ ትመታታዋለች ፡ በጡጫዋ ።—እንባዋ ፡ አይመጣላትም ።- የባሰ ፡ ትበሳጫለች ።—በስንት ፡ ትግል ፡ ትንሽ ፡ ታለቅሳለች ።— አይበቃትም ።— እንደገና ፡ ደግሞ ፡ ትንሽ ፡ ታለቅሳለች ።— አይበቃትም ፡ አሁንም ።— እንደሚንቀሳቀስ ፡ ከባድ ፡ ሸክም ፡ የሚሰማትን ፡ ልቧን ፡ የመነዘለውን ፡ ሥቃይና ፡ ሐዘኗን ፡ ጭር ፡ ጭር ፡ በሚል ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ እየወረጨ ፡ በሚወርድ ፡ እንባዋ ፡ ልታሰጥመው ፡ አልተቻላትም ።— የመጽናናት ፡ ኀይል ፡ አላገኘችበትም።—የመተንፈስ ፡ የመገላገል ፡ እፎይታ ፡ ሊሰጣት ፡ አልቻለም ።—ከክፍሏ ፡ ሳትወጣ ፡ ካንድ ጐኗ ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ ጐኗ ፡ እንደ ፡ ተገላበጠች ፡ ይመሽላታል ።—

## ፳፯

# አደፍርስ

መኪና ፡ መንገድ ፡ የተማሪዎች ፡ ሰልፍ ፡ ሕጋዊ ፡ ያልሆነ ፡ መን ገድን ፡ ይከተላል ።— ከወታደሮች ፡ ጋር ፡ ድንጋይ ፡ መወራወር ፡ ይጀ ምራሉ ።— ሰላማዊ ፡ ሰው ፡ ይመትታል ።— ይቆስላል።— ጩኸትና ፡ ቁቁታ ፡ ይነግሣል ።— አደፍርስና ፡ ክብረት ፡ ከነበሩበት ፡ ሆቴል ፡ ይወ ጡና ፡ እተማሪዎቹ ፡ ማህል ፡ ይገባሉ ።— እንዲያቆሙ ፡ ለማድረግ ፡ ይሞክራሉ ፡ ውርወራውን ።— ከወዲያ ፡ ወዲህ ፡ እየተሯሯጡ ።— የድ ንጋይ ፡ ውርጅብኝ ፡ እየበዛ ፡ እየበረከተ ፡ ይሄዳል ።— ውርወራውን ፡ አላፊ ፡ አግዳሚው ፡ ሁሉ ፡ ሳይቀር ፡ ይገባበታል ። አደፍርስ ፡ እጭንቅላቱ ፡ ገደማና ፡ እደረቱ ፡ ላይ ፡ በኀይል ፡ ይመታና ፡ ይወድቃል --ክብረትም ፡ አንዴ ፡ ሁለቴ ፡ ያርፍበታል ፤ አይጐድዳም ፡ ግን ፡ እሱ ፤ አይወድቅም ።— ሦስት ፡ ጥይት ፡ ያህል ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ይትተኮሳል ።—ተማሪዎች ፡ ይበታተናሉ ።— አደፍርስን « --የኛ ፡ ድንቁርና ፡ ይሻላል ፡ ጌታዬ ፡ የኛ ፡ ድንቁርና --ዕው ቀት ፡ ብሎ ፡ ነገር ፡ ደሞ ---የምን ፡ ዕውቀት ? ባፍንጫችን ፡ ይውጣ --- ዕውቀት ---? » እያለ ፡ ከሚያነበንብ ፡ አንድ ፡ ምክትል ፡ አሥር ፡ አለቃ ፡ ወታደር ፡ ላይ ፡ ተቀብሎ ፡ ደገፍ ፡ ያደርገዋል ፡ ክብረት « ሞትና ፡ ሕይወትን ፡ ላያራርቁ -- ዕውቀት ፡ ብሎ ፡ ነገር---» ይቀጥላል ፡ ወታ ደሩ ።—ክብረት ፡ ገንገን ፡ ይልና ፡ ቀና ፡ ብሎ ፡ ያየዋል ።— ወዲያውኑ ፡ በጥድፊያ ፡ ያነሡታል ፡ አደፍርስን ፤ የሣንሳ ፡ ይሸከሙታል—ወደ ፡ ክሊ ኒክ ፡ ያመራሉ « -- ሞትና ፡ ሕይወት -- ድንቁርናና ፡ ዕውቀት -- ላያራ ርቁ --» የሚሉት ፡ ቃላት ፡ እያቃጨሉበት ፡ ኋላ ፡ ኋላ ፡ እያለ ፡ ክብረት ። ማታ ፡ ሦስት ፡ ሰዓት ፡ ገደማ ፡ ይሞታል ፡ አደፍርስ ።—

በማግስቱ ፡ ጧት ፡ ያኗትን ፡ ሁለት ፡ ሦስት ፡ ቀሚሶች ፡ ለማጣ ጠብ ፡ ትዘገጃጃለች ፡ እውጪ—ጺወኔ ። — የወይዘሮ ፡ ማለፊያን ፡ በመ ቀነት ፡ የታጠፈው ፡ ብቻ ፡ ለሷ ፡ ቀሚስ ፡ ሊወጣው ፡ የሚችል ፡ ረጅም ፡ ቀሚስ ፡ ለብሳ --- አራት ፡ ሰዓት ፡ ገደማ ፡ ያደፍርስን ፡ መሞት ፡ ትሰ ማለች ።—

# ፳፲

## አደፍርስ

ሸንተረሩን ፣ ገመገሙን ፣ ተራራውን ፣ ጋራውን ፣ ኮረብታውን ፣ ተረተሩን ፣ ጉባውን ፣ ሸጡን ፣ ሸለቆውን ፣ ድሬ ፣ በሉውን ፣ ፋልማውን - - ብጫ ፣ አፈርቻ ፣ አረንጓዴ ፣ ቀይ ፣ ቀለሞች ፣ ተምቦራጭቀውበታል— የደረቀው ፣ የተቆረጠው ፣ የታጨደው ፣ የተሰበሰበው ፣ የተወቃው ፣ የተከመረው - - ድንጋዩ ፣ ሸኮቴው ፣ መረሬው - - ማሽላው ፣ ባርማሽ ላው ፣ ዘንጋዳው - - የተመነጠረው ፣ የታረሰው ፣ የተጨፈለቀው—እብቁ ፣ ቆረቆንዳው ፣ ግቻው ፣ አገዳው ፣ ቃርሚያው ፣ ቆረኑ ፣ ቆረኑ ፣ ቃርሚ ያው ፣ አገዳው - አገዳው - አገዳው - ቃርሚያው - - ሾላው ፣ ዋንዛው ፣ እንዶዱ ፣ ወይባው ፣ ጀንፎቁ ፣ አለንቋጣው ፣ ወደል ፣ አስፈሱ ፣ አገሩን ፣ አልብሰውታል ።— እየዳሁ ፣ እየተጥመለመሉ ፣ ጉርጓዳቸውን ፣ እየለቀቁ ፣ ትሎች—እየጋጡ ፣ እየቀነጠቡ ፣ ጋጣቸውን ፣ በረታቸውን ፣ እየዘነጉ ፣ እንስሶች—እየተንሳፈፉ ፣ እየመጠቁ ፣ ጐጆዋቸውን ፣ እየተው ፣ ወፎች— እየቦጨቁ ፣ እየወጉ ፣ ጐሬያቸውን ፣ እየለቀቁ ፣ አውሬዎች—እያሸተቱ፣ እየቀመሱ ፣ ቀፏቸውን ፣ እየከፈቱ ፣ ንቦች—እየጮሁ ፣ እየገዘፉ ፣ ከተማ ቸውን ፣ መንደራቸውን ፣ ቤታቸውን ፣ እየዘጉ ፣ ሰዎች— ሁሉ ፣ አዲስ ፣ ሆኖባቸዋል —

'የት ፣ ትሄዳለህ ፣ የት ፣ ትሄዳለህ ፣
ዋይ ፣ ዋይ ፣ የት ፣ ትሄዳለህ ፣
እናት ፣ አባትህን ፣ ታሳዝናለህ ፣
ዋይ ፣ ዋይ ፣ የት ፣ ትሄዳለህ ፣
የት ፣ ትሄዳለህ ፣ የት ፣ ትሄዳለህ ፣
ዋይ ፣ ዋይ ፣ የት ፣ ትሄዳለህ ፣
ወዳጅ ፣ ዘመድህን ፣ ታስለቅሳለህ ፣
ዋይ ፣ ዋይ ፣ የት ፣ ትሄዳለህ ፣
የት ፣ ትሄዳለህ ፣ የት ፣ ትሄዳለህ ፣
ዋይ ፣ ዋይ ፣ የት ፣ ትሄዳለህ ፣

ውዷን ፡ አገርህን ፡ ታጕላታለህ ፡
ዋይ ፡ ዋይ ፡ የት ፡ ትሂዳለህ ?
ዋይ ፡ ዋይ ፡ የት ፡ ትሂዳለህ ?
ዋይ ፡ ዋይ ፡ የት ፡ ትሂዳለህ - - ?’ እያሰኘ ፡ ያስደልቅ ፡ ያስና

ድል ፡ ያስገዝፋቸዋል ።—በቆሙበት፡ ቦታ ፡ ሁሉ ።—ከሞትም ፡ ከሕይ ወትም ፡ ይምቦለቦላል ፡ ውዶቱ—ከጣኑም ፡ ካዝርእቱ ።— የዳዊት ፡ መዝ ሙሮች ፡ ይንዶቀዶቃሉ—መቶ ፡ ኀምሳ ፡ እንዱም ፡ እስኪፈሱ—በሰባት ፡ ጊዜ ፡ ቊመት ። የወይዘሮ ፡ አካላት ፡ ዘመድ ፡ የሆን « ጉዞ ፡ ፍታት ፡ የከፈል ነውኮ ፡ ለቀልድ ፡ አይደለም ! » እያለ ፡ በጥንቃቄ ፡ ይከታተላል - - አን ዷቷ ፡ እንኳ ፡ መዝሙር ፡ እንዳትሰግር ።—



« ጉዞ ፡ ፍታት ፡ የከፈልነውኮ ፡ ለቀልድ ፡ አይደለም - - -

« - - - ሹመቴ ፡ አልገረመሽም - - - ?

ራሳቸው ፡ ወይዘሮ ፡ አካላት ፡ ደረታቸውን ፡ ጥለዋል ።— ከንፈ ራቸው ፡ ያለረፍት ፡ ይንቀሳቀሳል ፤ አንዳንዴ ፡ በመሐረባቸው ፡ አበስ ፡ እየተደረገ ። —እንባ ፡ ቢሆን ፡ አይወርዳቸውም ።— አቶ ፡ ጥሶ ፡ ያለቅ

ሳሉ ፣ በለኖሳስ ።— ሮማን ፣ ታለቅሳለች ፣ ላርጋጅ ፣ ለቀባሪው ፣ አስቸ ግራ ።— ጺወኔ ፣ ታለቅሳለች ፣ የሥዕል ፣ አልቃሽ ፣ ሆና— ሳያቋርጥ ፣ እንባዋ ፤ የሕይወት ፣ ምልክት ፣ እንጂ—ሕይወት ፣ ያለባት ፣ ያለመም ሰል ።— እጐን ፣ እጐና ፣ እያለ ፣ ጐርፉ —


« - - - ምን ፣ ላርግ ፣ ትይኛለሽ ? ላድነው ፣ ነበርኮ ፣ የሮጥሁት— ምን ፣ አስቤ ፣ ደሞ - - ! እሱስ ፣ ደሞ ፣ እጁን ፣ ያዝ ፣ ሳደርገው ፣ የዘነጋ ኝም ፣ መሰለኝ — ሊመነጭቀኝም ፣ ፈለገ — መንፈቅ ፣ እንኳን ፣ አልሆ ነን— ይኸ ፣ የወታደር ፣ ልብስ ፣ ሌላ ፣ አስመስሎኛል ፣ መሰለኝ - - ? የነሱው ፣ ተማሪ ፣ የሆነ ፣ ነውኮ ፣ ድንጋዩን ፣ የወረወረው— ለኔ ፣ ይመስለኛል ፣ ድንጋዩ— ርግጠኛ ፣ ነኝ ፣ አስተማሪውን ፣ ሊመታ ፣ አል ወረወረም— እያድርስ ፣ ነው ፣ መቼም ፣ ስኔና ፣ ሰኞ ፣ የሚሉት ፣ ነገር - - - ጺወኔ ፣ አትናገርም ።— ያለማቋረጥ ፣ የሚፈሰው ፣ እንባዋ ፣ ግን ፣ እያ ደር ፣ ተግታ ፣ ያገኛል - - አገሬን ፣ ለቀቅሁ ፣ ይኸውልሽ ፣ እኔም— ምን ፣ ላድርግ ፣ ትይኛለሽ - - ? መቼም ፣ እውነቱን ፣ ልንገርሽ ፣ እንዲህ ፣ አጠ ገብሽ ፣ ታስቆሚኛለሽ ፣ ብዩ ፣ በውኔ ፣ ቀርቶ ፣ በልሜ ፣ አላስብኩትም— ያው ፣ ያነዩ ፣ አገሬው ፣ ሁሉ ፣ ሳቀብኝ— አንቺንም ፣ አጉላልቼ— ሳይሳካልኝ ! ምን ፣ ይደረግ ፣ ቀረ - - ይኸን ፣ መሳይ ፣ ልጅ—ጥሩ ፣ ልጅ፣ ነበር ፣ አደፍርስ— እጂ ፣ ላይ ፣ ነውኮ ፣ የወደቀው ፣ ሲመቱት— እኔ ፣ ደሞ ፣ ምን ፣ ይሞት ፣ ብዩ—ሐኪሙ ፣ እንኳ ፣ ከተናገረ ፣ በኋላ ፣ አላመ ንኩም — ይገርምሻል —ትኩር ፣ ብሎ ፣ ያየኝ ፣ ነበር ፣ እጂ ፣ ላይ ፣ ሲወ ድቅ —ከንፈሩ ፣ ሁሉ ፣ ይላወስ ፣ ነበር - - የሰው ፣ ነገር ፣ እንደዋሉ ፣ መቅ ረት — ደሙ ፣ ከፊቱ ፣ ላይ ፣ ሲጠፉ ፣ ሳየው ፣ እንኳ ፣ አለመጠርጠሬ - - ! እንደዚሁ ፣ ዓይነት ፣ ሁኔታ ፣ ወደዚህ ፣ ወደ ፣ ተጉለት ፣ ውስጥ ፣ ሽፍቶች ፣ አስቸግረው ፣ የሄድኩ ፣ ጊዜ ፣ ሰው ፣ ሲሞት ፣ አይቼ ፣ ነበር— ትዝ ፣ ይለኛል —እንዲሁ ፣ ደሙ ፣ ሲሠርግ ፣ ይታይ ፣ ነበር ፣ ሲሞት ፣ ሲል— ሹመቴ ፣ አልገረመሽም - - ? ምክትል ፣ አሥር ፣ አለቃኮ ፣ ሆኛለሁ — ያነዩ ፣ ነው ፣ ይኸውልሽ ፣ የሆንኩት — ሁለቱንም ፣ ሽፍቶች ፣ ገደልና ቸው— ማ ፣ መሰለሽ ፣ ደሞ ፣ የገደላቸው - - ? እንባዋ ፣ እየደረቀ—እንደ ኮሸሽላ ፣ ዓይነት ፣ መልክ ፣ እያወጣች ፣ ትሄዳለች ፣ ጺወኔ - - አንድ ፣ ጩልፋት ፣ አንደኛውን ፣ እኔ ፣ ነኝ ፣ የገደልሁት ፣ ብሎ ፣ ተጫውቶ ብኝ ፣ ነበር—ጉድ ፣ ሠራሁት ፣ ግን ፣ እኔ ፤ አስመሰከርሁበት — ስንት ፣ ያገሮቻችን ፣ ልጆች ፣ ያሉ ፣ መሰለሽ ? — አብረውኝ — ይገርምሻል ! ጥቃት ፣ የሚወጡ ፤ እሳት ፣ ውስጥ ፣ የሚገቡልኝ ፣ እኔ ፣ ከፈለግሁ - - አንቺ ፣ ግን ፣ አልተለወጥሽም — እናትሽስ ? እንዴት ፣ ናቸው ? መቼስ ፣ እር

ጅና ፡ ሳይጫጫናቸው ፡ አይቀርም — ካዲሳባ ፡ በወሯ ፡ ተመልሳ— ሰምተሻል ፡ ይኸን ፡ ጨዋታ - - ? ወርካው ፡ ምነዬ ፡ አደገ ፡ እንዳለችው ፡ እንዳታደርጊኚ— አንችም ፡ በጣም ፡ ያማርሽና ፡ የተለዋወጥሽ ፡ ነው ፡ የመሰለኝ — አላወቅሁሽም ፡ ነበርኮ ፡ መጀመሪያ— የማን ፡ ጕታታ ፡ ቀሚስ ፡ ነው ፡ የለበሽው ? ያሮጊት ፡ ልብስ ፡ የመሰለ — አያስጠላብ ሽም ፡ ግን— ያምርብሻል— ያንቺ ፡ ቀሚስ ፡ አደለም ፡ ርግጠኛ ፡ ነኝ— መቀነቱስ ፡ ምንኛ ፡ አርጅቷል— ያምርብሻል ፡ ግን— እውነቴን ፡ ነው— ሰውነትሽን ፡ ሁሉ ፡ ደብቆታል - - - በሞተር ፡ እንደሚሄድ ፡ ነገር ፡ ምን ጥቅ ፡ ብላ ፡ ትወጣና ፡ ከለቃስተኛው ፡ ማህል ፡ ወደ ፡ ማርያም ፡ ቤተክሲያን ፡ ወደሚወስደው ፡ መንገድ ፡ ትገባለች - - - ምነው ፡ ወዴት ፡ ትሄጂ ? ቀብሩኮ ፡ አረጋይ ፡ ነው — ልከተልሽ ? እምልሽ ፤ ወዴት ፡ ነው ፡ የም ትሄጂው - - ? አመመሽ ፡ ልበል - - ? » እያለ ፡ ይከተላታል ፡ ጕርፉም ።— አባ ፡ ዮሐንስ ፡ ከጕርፉ ፡ ኋላ ፡ ኋላው ፡ ለጥቀዋል . . .

« - - - እየሀልኝ ፡ ይኸን ፡ ታምር - -» እያሉ « ይኸን ፡ ታምር—የሚ ገርምኮ ፡ ነገር ፡ ነው ፤ እንደ ፡ ጥይት ፡ ነውኮ ፡ ተስፈንጥራ ፡ የወጣችው— ስታጽናናት ፡ ነበር ፡ ይመስለኛል—ለሷ ፡ ምኗ ፡ ነው ? እውነቷን ፡ ነው— ሙቶች ፡ ሙታቸውን ፡ ይቅበሩ—ጌታ ፡ ያለው ፡ የፈቀደው ፡ ሲፈጸምኮ ፡ ነው ? ለራሱ ፡ ያለውን ፡ ማን ፡ ይወስድበታል ፡ ዱሮስ ? ለራሱ ፡ አገልጋይ የመረጣት ፡ ልጅ— ለራሱ ፡ የፈጠራት—ለሥርዐተ ፡ ምንኩስናዋ ፡ እግ ዚአብሔር ፡ በደኅና ፡ ያድርሰና - - ! የሚገርም ፡ ነገር — እሬቷ ፡ ላይ ፡ የታየኝ ፡ መለስ ፡ ስትል — በአምሳለ ፡ ርግብ ፡ መልክ ፡ እንደ ፡ ጥላ ፡ ጃበብ ፡ ብሎ ፡ ሲርገበገብ—ባናቷ ፡ ላይ ፡ ሲያበራ — ምን ፡ ይሳነዋል ፡ ለሱ - - ? የዘለዓለም ፡ ቤቷን ፡ አስመለከታታ - - ! ምን ፡ ይሳነዋል - - ? ፍጥነቱን ፡ እየጨመረ ፡ ይሄዳል ፡ ርምጃዋ ፡ የጂወኔ— ባይነቱ ፡ ይከተ ላታል ፡ ጕርፉ ።—አባ ፡ አዲሴም ፡ ከጕርፉ ፡ ኋላ ፡ ኋላ ።—እየጨመረ— እየጨመረ—እየጨመረ—ይሄዳል— እርምጃዋ ።—እንደሷ ፡ ለመፍጠን ፡ ከጀል—ከጀል—ከጀል—ያደርገዋል ፡ ጕርፉም ።—አንዶ ፡ ሁለቴ ፡ ጀመር ፡ ጀመር ፡ አድርጐ— ያባ ፡ ዮሐንስ ፡ መከታተል ፡ ገንፈል ፡ ያደርገውና ፡ ይቆማል ፤ ያመነታታል — ወደ ፡ ለቃስተኛው ፡ ይመለሳል ።— ለሥር ዐተ ፡ ምንኩስናዋ . . . ቢያቆየኝ . . . የኔ ፡ ልጅ . . . ሥርዓተ . . . ምንኩስ ናዋ . . . ቢያቆየኝ . . . ዱሮም . . . ብያ . . ለሁ - - - » ቅትት ፡ ቅትት ፡ እያሉ ፡ በመጣደፍ ፡ እሷ ፡ ዘንድ ፡ ለመድረስ ፡ ይታገላሉ ፡ አባ ፡ ዮሐ ንስ - - - ግርማዊ ፡ ሞገሳዊ ፡ መንፈሳዊ ፡ የሆነ ፡ የደወል ፡ ድምፅ ፡ ማስ

ተጋባት ፡ ይጀምራል ፡ በቀዬው — ከሩቅም ፡ ከቅርብም ፡ እየመሰለ — የጺወኔን ፡ እርምጃ— እያስቀረ— እያስቀረ— እያስቀረ — ከአረጋዊ ፡ ደብር ፡ ላይ ፡ ነጫጭ ፡ ጉሴዎች ፡ ያስነሣና — አንዴ ፡ ደረታቸውን ፡ አንዴ ፡ ጀርባቸውን ፡ ለአቆልቋይዋ ፡ ፀሐይ ፡ አስሰጥቶ—ነጭ—ደብዛዛ— ብጫ— ብጫ—ብጫ—ወርቅማ—ወርቅማ— ወርቅ ፡ እያስደረገ—ለዛዛ ፡ ዓይነት ፡ የማዕበል ፡ ፍራቻ ፡ ድንጋጤ ፡ በሰውነት ፡ እየነዛ—እያቋረጠ— እየቀጠለ— እያቋረጠ—እየቀጠለ ..........................................

.........................................



ንግድ ፡ ማተሚያ ፡ ቤት ።